# ምርኮኛ

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ቆንጅት ብርሃን

2002

# ኦሳገ

©ቆንጂት ብርሃን

መብቱ በህግ የተጠበቀ

የሽፋን ዲዛይን፡ ዮሐንስ ሰረቀ

አድራሻ፡ ቆንጂት ብርሃን

0911405427

Email: Merkognakon@Gmail.Com

መታሰቢያነቱ

በቀይ ሽብር ዘመን የህይወትና የአካል መስዋትነት

ለከፈሉ ወጣቶች ይሁንልኝ

- ምስጋና

ላመሰግናቸው የሚገባኝ ሰዎች እጅግ ብዙ ናቸው:: ሁሉንም ስምና ውለታ መዘርዘር ግን አስቸጋሪ በመሆኑ እንዲያው በጠቅላላ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

የምስጋናዬን አድማስ ጠበብ ሳደርግ በመጀመሪያ ልጆቼንና ቤተሰቦቼን ማንሳት ግድ ይሆንብኛል:: ሁላችሁም በሕይወት ለመኖሬ ዋና ምክንያቶቼ በሕይወቴ እንድጠነክርና ችግሮቼን ሁሉ እንዳሸንፍ ድጋፎቼ ናችሁና ላመሰግናችሁ ይገባኛል:: ዛሬ በሕይወት አብረኸኝ ባትኖርም ለሕይወት ፍልስፍናችንና ለእምነታችን መሰረት የሆንከው አባቴ መምሬ ብርሀን፣ደግነትሽና ርህራሄሽ ውርሳችን ለሆነው በሕይወት ዘመናችን ባለፍንበት ውጣ ውረድ አብረሽን ለተንገላታሽው ዛሬም ለኑራችን ድምቀት ለምትሸጭልን እናቴ ለወይዘሮ ይመኙሻል ምስጋናዬ የላቀ ነው::

ለእህቶቼ አክሊለ ፣ወይንሸት፣ ትግስት፣ አልማዝ ፣ፍቅርተ፣ በላይነሽና መሰሉ ለወንድሞቼ ቀሲስ ፣ታዬ፣ ሰይፌ ፣ከበደ፣ ዮሴፍ፣ ጌቱ፣ ወጋየሁ፣ በሻህ ፣ታዬ ፣ተዘከር ዘለቀ፣ ለልጆቼ መታሰቢያ፣ትዕግስት (ትንሿ)፣ዮፍታሄ፣ ዮሐንስ ፣ህሊና፣ ታጠቅ ፣ጌታቸው፣ እፀገነት፣ኤፍሬም፣ ዘላለም ፣አዜብ፣ ራሄል፣ ኤደን ፣ ቃልኪዳን ፣አብዮት፣ ሽመልስ፣ አስቴር፣ ፍፁም፣ መርሀዊ፣ እስክንድር፣ ናርዶስ ፣ዘካሪያስ ፣ሀረግ፣ ህይወት፣ ራሄል ፣አይናለም፣ሰርካለም፣ ሂሩት፣ መሰረት፣ አስራት፣ ድርቤ ፣ቤተሰባዊ አንድነታችን ፅንቶ እንዲኖር የሁላችሁ መልካምነት ታላቅ አስተዋፆኦ አለው ስለሰጣችሁኝ ማበረታታት በጣም አመሰግናለሁ:: መደበኛ ስራዬን ትቼ ይህን መፅሐፍ እንድጨርስ በመፍቀድ ለከፈላችሁት መስዋትነት እና የሰጣችሁኝ የሞራል ድጋፍ ረቂቁን አንብባችሁ ለሰጣችሁኝ አስተያየቶች የሚያስፈልጉኝን ነገሮች በማሟላት ስላደረጋችሁልኝ እገዛ ሁላችሁንም እጅግ አድርጌ አመሰግናችኋለሁ:: ለታዳጊዎቹ ሜላት፣

ሄርሜላ፣ በህይወት፣ ናትናዬል ኑሀሚን ፣ትንቢት፣ ሄኖክ እና ሚኪያስ በጣም እወዳችኋለሁ::

ከብዙ ዘመናት በኃላ ለመፃሐፍ እንድሞክር በውስጤ ፍላጎትን የጫርሽልኝና ፅሁፍን በማንበብ ገንቢ አስተያየትሽን ለሰጠሽን እፀገነት አሰፋ ፣ለፅሑፉ የሚያስፈልጉኝ ግብሃቶችን ሁሉ በማይታመን ፍጥነት ፈልገህ ላቀረብክልኝና ረቂቁን በተደጋጋሚ በማንበብና ሌሎች እንዲያነቡልኝም በማድረግ ላገዝከኝ ተስፋዬ ወ/ዮሐንስ፣ ረቂቁን በማንበብ አስተያየትህን በመስጠትና ተከታትለህ በመጠየቅ እንዳልሰንፍ ላበረታህኝ ብሩክ አሰፋ እናንተ የሰጣችሁኝ አስተያየቶች የወጣቱን ስሜትና ፍላጎት እንዳጤን ረድቶኛል እናም ፅሑፉ በወጣቱም ተነባቢ እንዲሆን ለማድረግ እንድሞክር መንገድ ከፍቶልኛልና አመሰግናችኋለሁ::

የፅሑፌን ረቂቅ እንድታነቡልኝ ስጠይቃችሁ በደስታ የተቀበላችሁኝ ጓደኞቼ መታሰቢያ ማሞ፣ እንዳንቺ የለም መኮንን፣ አባይነሽ ብሩ እንዲሁም ገነት መንግስቱ ያደረጋችሁት ማበረታታት ጉልበት ፈጥሮልኛል ከተለያየ አቅጣጫ ተመልክታችሁ የሰጣችሁኝ አስተያየት የትውልዳችንን ስሜት እንዳልዘነጋው ጠቅሞኛልና በጣም አመሰግናችኋለሁ:: ሙሉጌታ፣ ሄኖክ፣ ድጋፌ፣ መድሀኒት፣ ንግስት ፣ፍቅረዓለም፣ መሪም፣ኤፍሬም አሳልፍና ስምረት ፍቅራችሁን እና የሞራል ድጋፋችሁ ትልቅ ኃይል ሰጥቶኛልና በርትቻለሁ አመሰግናለሁ:: ሌሎች የኤፍ ኤች አይ (ፋሚሊ ኸልዝ ኢንተርናሽናል ) የሥራ ባልደረቦቼ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመዋጋቱ ጥረት ውስጥ ከኤፍ ኤች አይ ጋር በጋራ የሠራችሁ አጋር ድርጅቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች የማህበረሰብ ተቋማት መሪዎች እንዲሁም በጎ ፍቃደኞች ቀና አመለካከት እና መግባባትና መተባበር ካለ የማይናድ ተራራ ያለመኖሩን እንድማር ስላደረጋችሁኝ ኤፍ ኤች አይ ውስጥ ስሠራ በነበርኩበት ጊዜና ከለቀቅኩም በኋላ ላሳያችሁኝ ፍቅርና ክብር የልቤን ጥያቄ እንድመልስ ላደረጋችሁልኝ ማበረታታት ከልቤ የመነጨ ምስጋናዬን ይድረሳችሁ::

የፅሑፌን ረቂቅ በማንበብ ለሰጣችሁኝ ሙያዊ አስተያየት ለአቶ ደረጀ እና ለኤፍሬም በጣም አመሰግናለሁ::

ድርሰት ቀላል እንዳልሆነ ያስተማርከኝ በይሉኝታ ሳታልፈኝ ትህግስቴን እስካሟጥጥ ድረስ ረቂቁን እንድከልስ ያላሰለሰ አስተያየትህን ለሰጠኸኝ ነስሩ ኡመር እንዴት አድርጌ እንደማመሰግንህ ግራ ይገባኛል:: በመሰላቸት ነካክቼ የምመልስልህን ፁሑፍ ደጋግመህ የማንበብ ትግስትህ አሁንም ይገርመኛል አስተምረኸኛልና ፅሑፉም አሁን ላለበት ይዘት እንዲደርስ ያስቻለው ያንተ ጥረት ነውና በጣም አመሰግንሃለሁ::

የሁሉ በላይ የሆነ እግዚያብሔር ምስጋና ይድረሰው ሁሉም ነገር የሆነው በእርሱ ነውና!

# ፍሬሕይወት ማን ናት?

የቤት ለቤት እንክብካቤና ድጋፍ ሥራ ተጀምሮ ብዙም ሳይቆይ አንድ እሁድ ማታ ስልኬ ሲያንቃጭል ከየት እንደሆነ ሳልጠራጠር ነበር ከተቀመጠበት ያነሳሁት፡፡ አዎን ትክክል ነበርኩ ፍቅርተ ነበረች፡፡ ፍቅርተ ከእኔ ጋር እንዲሠሩ ከተመደቡት በጎፈቃደኞች ውስጥ አንዷ ስትሆን በሳልና ሩህሩህ ወጣት ነች፡፡ እንደ ፍቅርተ ባሉት በጎፈቃደኞች እንዴት እንደምኮራባቸው፣ ሳያቸውና ድምጻቸውን ስሰማ የቱን ያህል ነፍሴ በሀሴት እንደምትሞላ መግለጽ በጣም ይቸግረኛል፡፡ ስልኩን ዘጋሁና መልሼ ደወልኩ፡፡

"እንዴት አመሸሽ ፍቅር፣ ችግር አለ?" አልኳት ለምን እንደደወለች አሳምሬ ስለማውቀው

"ችግር የት ይጠፋል ሲስ፣ ለነገ ጠዋት ቢሮ ከመግባትሽ በፊት ልትመጪ ትችይ እንደሆን ልጠይቅሽ ነበር" አለችኝ በሚጥመኝ አንደበቷ፡፡ በጎፍቃደኞች "ሲስተር" የሚለውን የነርሶቹን የሙያ መጠሪያ ሲያቆላምጡት ነው "ሲስ" ብለው ነው የሚጠሩን ፡፡

"አሳምሬ ፍቅር! ምን ጥያቄ አለው፣ የት ልምጣ?" አልኩኝ ያለ ምንም ተጨማሪ ጥያቄ።

"ቀበሌ ጽሕፈት ቤት" አለች ፍቅር።

ስልኩን ከዘጋሁ በኋላ ባልፈልገውም ሃሳቤ ወደ ካዛንችስ ግቢ ገብርኤል ገሰገሰ፡፡ እንደምንም ብዬ ግን ሀሳቤን እመንገድ አስቀረሁት፡. ሃሳቤ ገብርኤል ሰፈር ከገባ መውጫ እንደሌለው አውቀዋለሁ፡፡ ምን ያስቸኩለኛል ሲነጋ እደርስበት የለ፡፡ ከሀሳብ መገላገያ የሚሆን ፊልም ከፈትኩና መመልከት ጀመርኩ፡፡ ዓይኖቼን እንዲያደክምልኝ ያህል እንጂ ለፊልም ያለኝ ፍላጎት ከጠፋብኝ ሰንብቷል፡፡

በጠዋት ጉዞ ወደ ገብርኤል ሰፈር ሆነ፡፡ ከፍቅር ጋር የተለመደ ሰላምታችንን ተለዋውጠን ጊዜ አላባከንም፣ ፍቅር መንገዱን

ጀመረችው፤ ተከተልኳት፡፡ ጥቂት ሄደት ብላ ቆም አለችና ተመለከተችኝ፡፡

""ምነው ፍቅር?" አልኳት ገጽታዋ የሀዘን ጥላ አጥልቶበት ተመልክቼ

"ስትገቢ እንዳትደናገጭ ብዬ ነው፡፡ ምናልባትም እስከዛሬ ድረስ እንዲህ ዓይነት ህመምተኛ አጋጥሞን አያውቅም"

"ፍቅር ደግሞ፤ ስንቱን ካየን በኋላ ዛሬም መደንገጥ አለ እንዴ?" አልኳት ሳጽናናት፡፡ ምንም አልመለሰችልኝም እርምጃዋን ቀነስ አድርጋ እየተራመደች ስለምንጎበኛቸው ሴት ሁኔታ አስረዳችኝ፡፡

ብዙም ሳንርቅ ከአፍሪካ ዳቦ ቤት በስተጀርባ በሚያስገባው ቅያስ ዘለቅን፡፡ ፍቅር ቆም አለችና "እዚህ ነው" አለችኝ ጥቂት እንደሄድን፡፡ አካባቢው ጸጥ ብሏል፤ ሁለተኛው ግቢ በር ላይ ቆም አለችና ገመድ ነገር ጎተት ስታደርግ የግቢው በር ተከፈተ። ጸጥታው የበለጠ ከበደኝ፤ ቤቱም ሰው የሚኖርበት አይመስልም። ፍቅር ገርበብ ያለውን መዝጊያ ገፋ አድርጋ ስትገባ ተከተልኳት። ቤቱ ጨለምለም ብሏል፤ ፍቅር ግድግዳውን ዳበስ ዳበስ አደረገችና መብራቱን አበራችው።

የቤቱን ውስጥ በዓይኖቼ ማተርኩ፤ ንጹሕ ቤት ነው። አነስተኛ የሶፋ መቀመጫ ከበስተቀኝ በኩል፤ ከበስተግራ ደግሞ የምግብ ጠረጴዛና ወንበሮች እንዲሁም ብፌ አለ። በግድግዳዎቹ ላይ አልፍ አለፍ ብለው የተሰቀሉት የፎቶግራፍ `ፍሬሞች ዓይን ይስባሉ፤ ለቤቱም ድምቀት ሰጥተውታል።

"እዚህ ናቸው" አለችኝ ፍቅር በሳሎኑ መሀል አልፋ በወደውስጠኛው ክፍል እየሄደች። ወደክፍሉ ውስጥ ስንገባ ከፊት ለፊት ግድግዳው ላይ የተሰቀለው ትልቅ ፎቶግራፍ ተቀበለን። ዓይኖቼን ከፎቶው ላይ ማንሳት አቃተኝ፤ በአስራዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኙ የሚመስሉት ወንድና ሴት ልጆች ቀልብን ይገዛሉ።



"እማማ እማማ" ብላ ተጣራች ፍቅር ወደአልጋው እየቀረበች። በአልጋው ላይ ሰው የተኛበት አይመስልም። የሰለለ ድምጽ ከተጠቀለለው ጨርቅ ውስጥ ተሰማኝ፡፡ ከግምቴ በላይ ሆነብኝ፡፡ ፍቅር ጨርቁን ገለጥ ስታደርገው የሰው ጭንቅላት መሆኑን በፍጹም ማመን የሚያዳግት ነገር ብቅ አለ፡፡ ሴትዮዋ አንገታቸውን ለማንቀሳቀስ ትግል አደረጉ፡፡

"እንዴት አረፈዱ እማማ" አልኩ ከሀሳቤ ወጥቼ።

"እግዚአብሔር ይመስገን" አሉኝ በዚያ በሰለለ ድምጻቸው፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የምስጋና ቃል መውጣቱን አስቤ ተደነቅሁ፡፡

ሴትዮዋን ለመገላለጥና ምልከታዬን ለማድረግ ጓንቶቼን አጠለቅሁና ጠጋ ብዬ እላያቸው ላይ የተጠቀለለውን ጨርቅ ገለጥለጥ አድርጌ ለመደባበስ ሞከርኩ፡፡ አብሯቸው የከረመው ቆሻሻ ጨርቅ ገለጥ ሲል ይሰነፍጣል፡፡

"አምላኬ ሆይ በዚህ ሁኔታ ለስንት ጊዜ ይሆን የቆዩት" አልኩ ለራሴ፡፡ ፍቅር አጠገቤ አልነበረችም፡፡ ወዲያውኑ ግን በትንሽ ባልዲ ለሰስ ያለ ውሀ ከጎረቤት ይዛ መጣች፡፡ ማታ ስትደውልልኝ ገና አይታቸው እየተመለሰች እንደነበር ስለነገረችኝ ለምን የመጀመሪያውን እንክብካቤ እንዳላደረገች መጠየቅ አላስፈለገኝም፡፡

አንገታቸው ላይ ሌላ ጨርቅ ተደግልሏል፡፡ ካናቴራ መበል ነገር ነው፡፡ ካናቴራውን ገለጥ አድርጌ ዳበስኳቸው፤ ሰውነታቸው በውስጡ ሥጋ ያለው አይመስልም፤ ቆዳና አጥንት ብቻ ቀርቷቸዋል፡፡ ከውስጣቸው ያልተሟጠጠው እስትንፋሳቸው ብቻ ነው፡፡ ከፍቅር ጋር ተጋግዘን እንደሚሆን እንደሚሆን አድርገን አጸዳዳናቸው፡፡

"እማማ ሀኪም ቤት መሄድ ያስፈልግዎታል፡፡ በቅርብ ጊዜ ሄደው ያውቃሉ? ምንድነው የመመዎት?" አልኳቸው

"ከሄድኩ እንኳ ሰንብቻለሁ፡፡ ህመሜ ግን ኤች.አይ.ቪ. ነው፡፡ ሀኪም የሚያስፈልገኝም አይደለሁም..." አሉኝ ሴትዮዋ

ግልጽነታቸው በጣም ገረመኝ፡፡ ተስፋ የሚባል ነገር በውስጣቸው እንዳልቀራቸው ገባኝ፡፡ "በጣም ያስፈልግዎታል እንጂ! ለአንድ ቀንም ቢሆን እንኳ ከስቃይ መተንፈስ ቀላል አይደለም፤ ደግሞም እኮ ቫይረሱ ተገኘ ማለት ወዲያውኑ መሞት ማለት አይደለም። እኛን እንደርስዎ ዓይነት ጠንካራ ሰው ደግሞ መሞት የለበትም። እኛን ልክ እንደልጆችዎ ይቁጠሩን፡፡ በሁሉም ነገር ልናገለግልዎት ነው እዚህ የተገኘነው። ስለዚህ አሁኑኑ ሀኪም ቤት እንወስድዎታለን" አልኳቸው።

መልስ አልሰጡኝም። "ልብስ ያለው የት ይሆን?" አልኩ አፀዳድተናቸው ስንጨርስ ጋቢ ብቻ እንደለበሱ በመሆናቸው፡፡ ሴትዮዋ ስንጥር የመሰለ እጃቸውን እንደምንም ለማንሳት ሞክረው ከበስተጀርባዬ የሆነ ነገር አመላከቱ፡፡ እጃቸውን ተከትዬ ዞር ስል ቁም ሳጥን መኖሩን አስተዋልኩ፡፡ ፍቅርም ቀልጠፍ ብላ ሄዳ ከፈተችው፡፡ ከቁም ሳጥኑ ያወጣችውን ልብስ ይዛ ቀረበች ፍቅር፡፡ ረዘም ያለ ዘመናዊ ቀሚስና ከቀሚሱ እንዲስማማ ታስቦ የተሠራ ነጠላ! ልብሳቸውን አለበስናቸው።

ወዲያውኑ ወደ ቢሮ ስልክ ደወልኩና ያለንበትን ቦታ በምልክት አስረድቼና መኪና እንዲላክልን ጠይቄ መጠበቅ ያዝን፡፡ ፍቅር የሆነ ዱካ ነገር ከአንደኛው ጥግ አምጥታ እንድቀመጥበት ሰጠችኝ፡፡

ዓይኖቼን ከሁለቱ ልጆች ፎቶ ላይ ማንሳት አልሆነልኝም። "እነማን ይሆኑ?" የሚለውን ጥያቄ ከአእምሮዬ ማውጣት አልቻልኩም። ከፊት ለፊቴ ባለው ግድግዳ ላይ አነስ ባሉ ፍሬሞች የተሰቀሉ ሁለት ሙሉ ሰውነት የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ደግሞ አየሁ፤ የወንዱ ልጅ ከላይ የሴቷ ደግሞ ከታች ተሰቅለዋል፤ ሴቷ ልጅ አጭር ቀሚስና ጥብቅ ያለች ሸሚዝ ለብሳለች። ዓይኖቼን ወደሌላው ግድግዳ አዞርኳቸው፤ እዚያም እንዲሁ ሁለት ፎቶግራፎች አሉ፤ ሙሉ የወጣትነት ዕድሜ ላይ ያለች ሴትና ትንሽ ወንድ ልጅ ናቸው። ሴቷ ረጅም የሚያምር



ጸጉሯ ትከሻዋ ላይ ተንዠርግጎአል፤ አቋቋሟ ደግሞ ጸጉሯ የበለጠ እንዲታይ አድርጎታል። ወንዱ ልጅ እርሷን አተኩሮ የሚያይ ይመስላል።

"እነዚህ ሁሉ ልጆቻቸው ይሆኑ? የት ሄደው ይሆን እኝህ ሴት እንዲህ ብቻቸውን የቀሩት?" አልኩኝ ለራሴ።

የመኪናው ድምጽ ከገባሁበት የሃሳብ ባህር በድንገት አወጣኝ፡፡ ፍቅር ከምኔው ተነስታ በሩ ጋ እንደደረሰች አላየኋትም፡፡ "መጥተዋል" አለችኝ መለስ ብላ፡፡
"እማማ" ብዬ ተጣራሁ፡፡ ያ የሰለለ ድምጽ በፍጥነት መለሰልኝ፡፡ ለማንሳት ጎንበስ ስል መልካሙ፤ የመኪናችን አሽከርካሪ ገብቶ ከበስተጀርባችን ደርሶ ኖሮ "ዞር በይ" አለኝ፡፡ የማንንም ድጋፍ ሳይፈልግ እንደ ህፃን ልጅ እቅፍ አድርጎ አነሳቸው፡፡ የቁመታቸው ርዝማኔ ካልሆነ በቀር ምንም የሚከብድ ሰውነት አልነበራቸውም፡፡ ፍቅርተ ከቤት ወጥተን በሩን ለመዝጋት ሳብ ካደረገች በኋላ መለስ አለችና ነጠላ ጫማ ቢጤ አግኝታ ወዲያውኑ ተመልሳ መጣች፡፡ ሮጥ ብዬ ለመልካሙ የመኪናውን በር ከፈትኩለት ኋለኛው ወንበር ላይ ሴትዮዋን አስቀምጦ በፍጥነት ወረደና መኪናውን ለማስነሳት ገባ፡፡

ስምን መላክ ያወጣዋል እንዲሉ መልካሙ የእውነትም እንደስሙ መልካም ነው፡፡ ብዙ ባይናገርም የልቡን ሀዘን ገጽታው እያሳበቀበት ሁልጊዜ እርዳታ ለመስጠት እንደተጋ ነው፡፡ እንደ መልካሙ ያሉ አጋሮች ባይኖሩን ኖሮ የመጀመሪያዎቹን የቤት ለቤት እንክብካቤና ድጋፍ ጊዜያት ፈተናዎች እንዴት መወጣት ይቻል ነበር?

ሴትዮዋ ለአስራ አምስት ቀናት ሆስፒታል ከተኙ በኋላ ሴትዮዋ የተአምር ያህል ለውጥ አመጡ፡፡ ጤናቸው በጣም ተሻሻለ፡፡ ከሆስፒታል መውጣት ነበረባቸው፡፡ ያን እለት ሴትዮዋን ከሆስፒታል አውጥተን ወደቤታቸው ስንመልሳቸው የተሰማኝን ደስታና በጉንጮቼ ላይ የፈሰሱት የእንባ ዘለላዎች፣ ከሴትዮዋ ገፅታ ላይ የተመለከትኩትን ደስታና እርካታ በሕይወቴ ሙሉ አልረሳቸውም፡፡ የሴትዮዋን ለመግለጽ የሚያዳግት ደስታ

ተመልክቶ ዓይኖቹ በእንባ ያልረጠበ ማን ይኖራል? ከዛ በላይ መንፈሳዊ እርካታስ ከየት ሊገኝ ይችላል?

አብረውን የሚሠሩት በጎ ፍቃደኞች፣ የቤት ለቤት ድጋፍና እንክብካቤ ኮሚቴ አባላት እቤት ተሰባስበው ጠበቁን፡፡ ቄጤማ ተጎዝጉዞ፣ ቡናው ተቆልቶ፣ ፈንዲሻው በትሪ ሞልቶ፣ እጣኑ ተጫጭሶ ያ የሞት ጥላ አንዣቦበት የነበረ ጥቁር ቤት በብርሃን ተሞልቶ ነበር የጠበቀን፡፡

የተባረኩ የአብራክ ክፋዮች ወላጆቻቸውን እንደሚንከባከቡ ሁሉ በጎ ፍቃደኞቹ በቡድን እንክብካቤያቸውን ቀጠሉ፡፡ የህሙማን ጉብኝት በማደርግባቸው ቀናት በጎ ፈቃደኞቹ ላስቲካቸውን አሸርጠው፣ ትልቁን ጥቁር ጓንት እጆቻቸው ላይ አጥልቀው የሕሙማኑን ልብስ ሲያጥቡ፣ መጥረጊያዎቻቸውን ይዘው አካባቢውን ሲያፀዱ ቆም ብዬ እመለከታቸዋለሁ፡፡ አንዳንዶቹ በጎፈቃደኞችማ ህሙማኑን አልጋቸው ላይ እንዳሉ የማጽዳት ክህሎታቸው በእነዚያ አጭር ቀናት ተለማምደው የሚሠሩ አያስመስላቸውም፣ የልብ ያደርሳሉ፡፡

ከሁሉም የሚደንቀኝ በጎ ፍቃደኞቹ ለሚያገለግሏቸው ህሙማን የሚያደርጉት ሙግት ነው፡፡ "ለእከሌ ይሄ ያስፈልገዋል፣ ለእከሊት ይሄ ሊደረግላት ይገባል..." የሚለው ክርክር በተለይ የቁሳቁስ እደላ በሚደረግባቸው ቀናት ጦፍ ይላል ፡፡ የፍቅርን ሁኔታ መግለጽ አዳጋች ነው፡፡ ፍቅር ማንም ባዕድ ናት ሊል በማይችለው ሁኔታ ራሷን ሰጥታ አንዳንዴም እንባዋን አፍስሳ፣ አለቃቅሳ፣ ከምስኪን እናቷ ምስኪን ቤት ሳህን ቋጥራ፣ ሌላ ጊዜም ለምና ነው ህሙማኑን የምትንከባከባቸው፡፡

ሴትዮዋን አስተኝተን ቡናውን ለመጠጣት ተቀመጥን። ፍቅር ቡናውን ለታዳሚዎቹ በማስተናገድ ጉድ ጉድ አለች፣ የእርሷን እንቅስቃሴ በዓይኖቹ እየተከተልኩ በሀሳቤ ጭልጥ ስል አልታወቀኝም። ሁለት ዓመታት ወደኋላ ሄጄ ወደዚህ ሥራ የገባሁበትን ጊዜ አስታወስኩ።



በነርስነት ከተመረቅሁ ሰባት ዓመታት ሊቆጠሩ እነሆ ሁለት ወራት ብቻ ቀርተዋል፡፡ ያለፉት ሁለት ዓመታት ግን በተቀላቀለ ስሜት አዕምሮዬ ሲታወክ የቆየባቸው ዓመታት ናቸው፡፡ ሙያዬን በጣም የጠላሁባቸውና በጣምም የወደድኩባቸው የሕይወቴን ብዙውን ጊዜ የኖርኩባቸው የሚመስሉኝ ሁለት ረጅም ዓመታት፡፡

ወደዚህ ሥራ ስገባ ይህ ይገጥመኛል ብዬ በጭራሽ አላሰብኩም፡፡ በጤና ተቋም ውስጥ የተወሰነው ሥራዬ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ችግር ዘርፈ ብዙነት በሚገባ እንዳጤን አላስቻለኝም ነበር፡፡ እናም የቤት ለቤት እንክብካቤና ድጋፍ ተቆጣጣሪ ነርስ ለመሆን ሳመለክት፣ ፈተናውን ስወስድ፣ አልፌ ስቀጠርና ለስልጠና ስታደም በደስታ ነበር፡፡

የመጀመሪያው ሥራ እንደ እድር ያሉ የማህበረሰብ ተቋማትን መቀስቀስና ማስተባበር ነበር፡፡ እጅግ በሚያስገርም መልኩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የማህበረሰብ ተቋማት እና የመንግሥት የተባበረ እንቅስቃሴ የታየበት ጅማሮ ጉድ ተባለ፡፡ የበጎ ፍቃደኞች ምልመላ በየአቅጣጫው ተጀምሮ በአስር ክፍለ ከተማዎች ስልጠናው ሲካሄድ የነበረው የሥራ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት በሕይወቴ ሙሉ ያላየሁትን የተባበረ ክንድን ጥንካሬ አሳየኝ፡፡

ከፍተኛው የሥራ ፍቅርና የጋራ እንቅስቃሴ በአጭር ጊዜ ተአምር ሊባል የሚችል የሥራ ውጤት አሳየ፡፡ በሶስት ሳምንታት ውስጥ ከሁለት መቶ በላይ በጎ ፍቃደኞች ሰልጥነውና የተግባር ልምምድ አድርገው ለሥራ ዝግጁ ሆኑ፡፡ የበጎ ፍቃደኞቹ የመጀመሪያ ሥራ በዕድሮቹ መሪነት፣ በአገር በቀል ግብረ ሠናይ ድርጅቶች ተቀጥረው በአንድ ዓለምአቀፋዊ ግብረ ሠናይ ድርጅት የሠለጠኑት ሳተናዎቹ ነርሶች ቴክኒካዊ ድጋፍ፣ በመንግሥት እና በሀገር በቀል ድርጅቶቹ አዝማችነት የቤት ለቤት እንክብካቤና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ሕሙማን መፈለግ ሆነ፡፡

ምንም እንኳ አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያስችለው መስፈርት ሕመም ሳይለይ ማንኛውንም ለአንድ ወርና ከዚያ በላይ አልጋ ላይ የቆየ ሕመምተኛ ሁሉ የሚያካትት ቢሆንም የአገልግሎቱ

ተጠቃሚ ለመሆን ፍቃደኛ የሆኑት ጥቂት ነበሩ፡፡ ምንም አማራጭ የሌላቸው ድሆች፡፡ በርካታ ወገኖች የሚደርስላቸው አጥተው እየተሰቃዩ መሆናቸውን ልቦናችን ቢያውቀውም ቤተሰቦቻቸው ክፍል ዘግተውባቸው የሰው ያለህ የሚሉ ህሙማን፣ የተንከባካቢ እጅ እንደናፈቃቸው በርካቶች ለህልፈተ ሕይወት እየተዳረጉ ማስተዛዘኛው የዕድሮቹን ካዝና እያራቆተ ቢሆንም አድልዎና መገለሉን ሰብሮ መግባት ፈተና ሆነ፡፡

ህሙማንን ለመፈለግ በየመንደሩ የሚንከራተቱት በጎፍቃደኞች ለጥቅማቸው እንደሚዞሩ ተቆጥረው ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የሚመጣውን ገንዘብ ለመቀራመት እንደሚስገበገቡ ሆዳሞች ተወስደው ውሻ ሲለቀቅባቸው አመራር የሚሰጡት የዕድር መሪዎችም ስማቸው ተቀይሮ "አባባ/እማማ ኤድስ" የሚል ቅጽል ስም ወጥቶላቸው ሙያቸውንና ወኔ ሰንቀው ወደማህበረሰቡ የገቡት የጤና ባለሙያተኞች እንደ አልባሌ ሰው በንቀት ዓይን እየታዩ ፊት ሲነሱ… ኧረ ስንቱ! ጥንካሬ ያላቸውና ዓላማው ውስጣቸው የዘለቀ ተጋፈጡት፡፡ እኔም የቴክኒክ አመራር ከሚሰጡን ባለሙያዎች፣ ፕሮግራሙን ከሚመሩት አንጋፋ የእድር አመራር አባላት፣ ችግሩን ፊት ለፊት ከተጋፈጡት በጎፍቃደኞች ወኔ እየተጋራሁና ከራሴ ጋር እየታገልኩ ያን ፈታኝ ጊዜ አልፌ ከዘለቁት ውስጥ ሆንኩ፡፡

እንደ ዕውነቱ ከሆነ ከኤች.አይ.ቪ. እና ከማግለልና መድልዎ ጋር የተደረገው ትግል ከጦር ሜዳ ውሎ የሚተናነስ አልነበረም፡፡ ማግለልና መድሎው ተሰብሮ ያለመሸማቀቅ ህሙማን ቤት መግባትና መውጣት ስንጀምር የተሰማንም ኩራትና ደስታ እንዲሁ ነበር፡፡

እንግዲህ በዚህ የታሪክ አጋጣሚ ነበር የዚህ መጽሐፍ ባለታሪክ የሆነችውን ፍሬሕይወትን ያገኘኋት። ቡናውን የጠጣሁበትን ስኒ በእጇ እንደያዝኩት መሆኑን ያስተዋልኩት የቡና ታዳሚዎቹ በምርቃት እየተሰናበቱ ሲወጡ ነው። ብዙም ሳልቆይ ፍቅር አስፈላጊ ከሆነ እንድትደውልልኝ ነግሬያት እኔም ወጣሁ።

* * *



ሁሉንም ህሙማን መጎብኘት የሙያና የሥራ ግዴታ ከመሆኑም ባሻገር የኀሊናም ጥያቄ ነው፡፡ ፕሮግራሙ በተጀመረበት ወቅት የነበረው ሁኔታ የስንቶቻችንን ሕይወት ረብሾ የህሊና ሰላም ነስቶ እንደነበር እኛና ቤተሰቦቻችን ዛሬም እናስታውሰዋለን፡፡ ስንት ጊዜ ሥራውን መልቀቅ እንደሚገባኝ ወስኜ መልቀቂያ ለመጻፍ ወረቀትና ስኪሪፕቶ አንስቼ እንደገና ወርውሬ ሥራዬን እንደቀጠልኩ ሳስበው ራሴን አሞካሸዋለሁ፡፡

ታዲያ አንዳንዶቹ ህሙማን የተለየ ስሜት ይፈጥሩብኛል። የትም ቦታ ሆኜ ትዝ ይሉኛል። ልክ እንደዘመዴ ሆነው ይታዩኛል፡፡ አንዳንዴ ከሥራ ሰዓትም ውጭ እንድጠይቃቸው መንፈሴ ያስገድደኛል፡፡ ከእነዚህ ህሙማን መሀል አኚህ ሴት አንዷ ናቸው፡፡ ከህመምተኛዋ ጋር እጅግ በጣም ተግባባን፤ ሳላያቸው መዋል ቅር እስኪለኝ ድረስ ሴትዮዋ ለልቤ ቅርብ ሆኑ ፡፡ ከሆስፒታል በወጡ ሰሞን በጣም ተሽሎአቸው ቀና ማለት ጀመሩ፤ ልንጎበኛቸው ስንሄድ ተኝተው እንድናገኛቸው በፍጹም አይፈልጉም፡፡ ትራሳቸው ላይ ደገፍ ብለው መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነቡ ነው የምናገኛቸው፡፡

ከሴትዮዋ ጋር በጣም ተላመድንና ለብዙ ጊዜ የማውቃቸው እስኪመስለኝ ድረስ ቀረብኳቸው። ከዚያ በኋላ ብዙ ነገሮች አውርተናል፣ አብረን ስቀናል፣ ራሴን መቆጣጠር አቅቶኝም አልቅሼ አስለቅሻቸዋለሁ፡፡ አንድ ቀን ስናወራ ቆየንና የተመለከትኩትን ክፍተት ለመሙላት አሰብኩ፡፡

"በቃ ከዛሬ ጀምሬ አንቺ ብልሽስ?" አልኩ ዓይን ዓይናቸውን እያየሁ፡፡

"አንቺ ማለት ብቻ ሳይሆን እባክሽ ፍርዬ በይኝ" አሉና እጃቸውን ዘረጉልኝ፤ ሊያቅፉኝ እንደፈለጉ ገባኝና ተጠጋሁ፤ ለደቂቃዎች ያህል ራሴን ደረታቸው ላይ ጥግት አድርገው ጥብቅ አድርገው አቀፉኝ፤ ከእቅፋቸው ለመውጣት አልሞከርኩም፡፡ በኋላ ግን "ተባረኪ እግዚአብሔር ይባርክሽ" አሉና እቅፋቸውን ላላ አደረጉት፡፡ ብድግ ብዬ አየኋቸው፡፡ ደስ ብሏቸዋል እኔንም ደስ

አለኝ፡፡ ከቆይታ በኋላ ወደ ቤቴ ለመሄድ ስወጣ "ደህና እደሪ ፍርዬ" ብዬ ወጣሁ፡፡

ከዚያ በኋላ ባለችኝ ትርፍ ሰዓት ሁሉ ተፈልጌ የምገኘው ፍርዬ ቤት ሆነ። ፍርዬ የማታሳየኝና የማታጫውተኝ ነገር የላትም። የወጣትነት ትዝታዋን አለፍ አለፍ ብላ ስትነግረኝ ከገጽታዋ ላይ የሚነበበው ስሜት ከድምጿ ውስጥ የሚሰማኝ ጥንካሬ ወደኔም የተላለፈ እስኪመስለኝ ድረስ በሀሳብና በመንፈስ አብሬአት እየወደቅሁና እየተነሳሁ አዳምጣታለሁ፤ ደስም ይለኛል።

ፎቶዎቿን ዓይቼ አልጠግባቸውም፤ አንዳንዴ ፎቶው ላይ ያለችውን ፍርዬንና አሁን በአካል የማያትን ፍርዬን ማመሳሰል እስከሚያቅተኝ ድረስ ይሆንብኝና ትኩር ብዬ እመለከታታለሁ።

"ይሄ ፎቶሽ የመቼ ነው?" አልኳት አንድ ቀን እርሷ መሆኗንም እየተጠራጠርኩ።

"የትኛው?" አለችኝ ፎቶውን ለመውሰድ እጇን ዘርግታ። ፎቶውን አቀበልኳት። እፎቶው ላይ ያለችውን ለግለግ ያለች ወጣት እየተመለከተች ፍዝዝ አለች። እኔ ደግሞ የምመለከተው እርሷን ነበር። ከነበራት ውበት ሁሉ የቀሯት ዓይኖቿ ብቻ መሰሉኝ። ፎቶው ላይ የተመለከትኩት የሚያምረው ሰልካካ አፍንጫ ዛሬ ለፊቷ በጣም የተለቀ መሰለኝ፤ የሚገመጡ የሚመስሉት ድንቡሽቡሽ ጉንጮቿ ዛሬ ስርጉድ ብለው የጉንጮቿ አጥንቶች ግጥጥ ብለዋል፣ ትከሻዋ ላይ የተንዘንዘው ጸጉሯ ዛሬ የለም...

ፍርዬ ድንገት ቀና ብላ ተመለከተችኝ። ድንግጥ አልኩ። የእውነትም ዓይኖቿ በጉድጓዶቻቸው ውስጥ ራቅ ያሉ ቢመስሉም ውበታቸው ዛሬም አለ። ያዘነች መሰለኝና በመጠየቄ ተቆጨሁ።

"የመቼ ነው አልሽኝ?" አለችኝ ፎቶግራፉን እንደገና እየተመለከተችው። "ዕድገት በህብረት ሲባል ሰምተሽ ታውቂያለሽ?" አለችኝ ዓይኖቿን ከፎቶው ላይ ሳትነቅል።

"ይመስለኛል" አልኳት



"ዓየሽው ልብሱን? የተሰጠን የዘመቻ ልብስ ነው፤ ፎቶውን የተነሳሁት ዘመቻ ልንሄድ አንድ ሳምንት ሲቀረን ነበር።" አለችኝ ፍርዬ በሀሳቧ ርቃ የሄደች በሚመስል መልኩ።

ፎቶውን ተቀብያት እንደገና ተመለከትኩት፤ የለበሰችው ካኪ ሸሚዝ ወደሱሪው ውስጥ ገብቶ የታጠቀችው ቀበቶ የወገቧን ቅጥነት አጋልጦታል። ሸንቅጥ ያለ ወገብ የሚባል ዓይነት ነው። ፎቶዋን ሳም ማድረግ አማረኝና ፈገግ ብዬ አስቀመጥኩት።

ደግሞ ሌላ ፎቶ አነሳሁ፤ በረጂም ፀጉር ላይ ሰፊ ባርኔጣ ያደረገች፣ ጥብቅ ያለች እጀ ጉርድ ሹራብና እስከቁርጭምጭሚቷ የደረሰ ረጂም ቀሚስ የለበሰች ቀጭን ወጣት፤ በጣም ታምራለች። ቀደም ባሉ የአውሮፓ ፊልሞች ላይ የማያቸውን ሴቶች ትመስላለች።

"እኔ ነኝ እንዳትይኝ" አልኳት ሳላስበው። ፍርዬ ፈገግ አለች፤ የትኛው ፎቶ እንደሆነ የገባት መሰለችኝ።

"በረጂም ቀሚስ ነው አይደል?" አለችኝ ፈገግታዋ ከገጽታዋ ላይ ሳይጠፋ። መልሴን ሳትጠብቅ ቀጠለችና "ኢትዮጵያ ትቅደም የሚባለው ቀሚስ ነበር። ያው ዘመቻ መልበስ የሚቻለው ረጂም ቀሚስ ብቻ ስለነበረ ረጂሙን ቀሚስ ለማሳመር ለወጣት ቀላል ነበር፤ ሁላችንም ማለት ይቻላል እንዲህ ዓይነት ቀሚሶች አሰፋንና የወቅቱ ፋሽን አደረግነው።" አለችኝ ፈገግታዋ አሁንም ገጽታዋን እንደሸፈነው።

"ፍርዬ በጣም ታምሪ ነበር" አልኳት አሁንም ሳላስበው።

"ነበር!" አለችኝ ፍርዬ ከመቅጽበት ፈገግታዋ ከገጿ ላይ ጠፍቶ። ሳላስበው በማነሳቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች ትካዜ ውስጥ በመግባቷ በራሴ እየተናደድኩ ደግሞ ሌላ ፎቶ አነሳሁ።

በርካታ ሴቶችና ወንዶች ወጣቶች ያሉበት ፎቶ ነው። በጉብታ ሥፍራ ላይ ልክ እንደቦታው አቀማመጥ ሁሉም እንደሚታዩ ሆነው ተደርድረዋል።

"አቤት ከለር ቢሆን እንዴት ያምር ነበር?" አልኩ ለራሴ። ፍርዬን ፈለግኋት፤ በቀላሉ ማግኘት አልሆነልኝም። ያገኘኋት ከብዙ ሙከራ በኋላ ነው፤ መሀል አካባቢ ላይ ሸሚዟን እወገቧላይ ሸብ አድርጋ ቆማለች፤ ከበስተግራ በኩል ትከሻዋን አቀፍ ያደረገ ወጣት አለ፤ ከበስተቀኝ ደግሞ ትከሻዋ ላይ ደገፍ ያለች ወጣት ትታያለች። የፍርዬ ፍልቅልቅ ያለ ፈገግታ የሳባቸው ይመስል የብዙዎቹ ዓይኖች ወደእርሷ የሚመለከቱ ይመስላሉ።

"ምን ቢያስደስትሽ ነው እንደዚህ የሳቅሽው?" አልኳት አሁንም ሳላስበው።

"የቱ ነው ልጄ? በወጣትነት ለመደሰት ምን ጭንቅ አለ፤ በሳሩም በቅጠሉም መሳቅ አልነበረ ሥራችን" አለችና ፎቶውን ተቀበለችኝ። "ወይ ጉድ!" አለች ገና ፎቶውን እንዳየችው።

"ምነው ፍርዬ?" አልኳት

"አሁን ከነዚህ ውስጥ ስንቶቹ ያሉ ይመስልሻል?" አለችና ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰችልኝ።

"ማለት? እዚህ አገር የሉም ማለትነው?" አልኳት ተደናግሬ።

"ወይ እዚህ አገር? በዚህ ምድር የሉም እንጂ!" አለችና ትክዝ ብላ ቆየች።

"አይገርምሽም? ከነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ ሞተዋል ጥቂቶቹ ደግሞ የት እንዳሉ አላውቅም፤ ምናልባትም ሞተዋል ወይ ተሰደዋል..."

"ይሄኛው ልጅስ?" አልኳት ደግሞ ትከሻዋን ያቀፋትን ልጅ እያሳየኋት። ከገጽታዋ ላይ አንዳች ነገር ተመለከትኩ።



"በጣም ይቅርታ ፍርዬ፤ ዝም ብዬ መጠየቅ እወዳለሁ" አልኳትና ፎቶውን ላስቀምጠው ስል እንደገና ወሰደችው።

"ታውቂያለሽ? አንድ ክፉ ቀን ድንገት ነጣጥለን እንጂ ከአንተነህ ጋር የምንለያይ አልነበርንም። የደረሰብትን ከማላውቀው ሰዎች አንዱ ነው" አለችኝ።

አንተነህን እንደገና በደንብ ተመለከትኩት፤ በዕድሜ ከፍርዬ በጣም የሚበልጥ ይመስላል፤ ቁመት ግን ብዙም አይበልጣትም፤ ጥቂት ብቻ ነው ቀና ብላ የምትመለከተው። ዓይኖቿና ጥርሶቿ አብረው የሚስቁ ይመስላሉ፤ አንተነህን የእርሷ ደስታ ያስደሰተው ይመስል በደስታ ፍንድቅ ያሉ በሚመስሉ ዐይኖቹ ይመለከታታል። ፍርዬና አንተነህ የሌሎቹን ሁሉ ትኩረት የሳቡ ይመስላሉ።

"ይህቺኛዋ ደግሞ ኤልሳ ነች" አለችኝ። ትኩረቴን ለመሳብ የተናገረች መሰለኝ። ኤልሳ ትከሻዋን የተደገፈቻት ወጣት ነች፤ በቁመት ከፍርዬ ትበልጣለች፤ ትከሻዋ ላይ ለመደገፍ ጥቂት ሸብረክ ማለት ነበረባት፤ ፎቶ ግራፉ ባለቀለም ባለመሆኑ ከለርን መለየት ቀላል ባይሆንም ኤልሳ ቀይ ትመስላለች፤ ጎረድረድ ያለችና የደም ግንቦ የምትባል ዓይነት።

"ከኤልሳ ጋር ከዘመቻ በኋላ ብዙም አልተገናኘንም፤ መንገዶቻችን ተለያይተው በየፊናችን ተጓዝንና በዚያው ቀረን። ግን ውጭ አገር መሆኗን ሰምቻለሁ" አለችኝ ፍርዬ።

"ከቤተሰብ ጋር የተነሳሽው የለሽም እንዴ?" አልኳት ድንገት ቤተሰቦቿን የማየት ፍላጎት አድሮብኝ። እግድግዳው ላይ የተሰቀሉትን ፎቶግራፎች የማን እንደሆኑ ማወቅም ፈልጌ ነው።

"አሉ እንጂ!" አለችኝና እነዛን ብዛት ያላቸው ፎቶዎች ገልበጥበጥ አድርጋ አንድ ፎቶ አወጣች። ፎቶውን ቅዝዝ ባሉ ዐይኖቿ ተመለከተችና አቀበለችኝ።

ስድስት ሰዎች ያሉበት ፎቶግራፍ ነው። ሳሎኑ ውስጥ በትልቁ ፍሬም ፊትለፊት ከተሰቀለው ፎቶ ጋር ይመሳሰላል። ሁለቱን ሰዎች መቼም ማስተዋወቅ አይጠበቅባትም፤ አባትና እናቷ ናቸው። ሁለቱም ተቀምጠዋል። አባቷ ግንባር ላይ ያሉት መስመሮች ጎልተው ይታያሉ፤ ከግንባራቸው ስር ያሉትን ዓይኖች ያየ ሰው ፍሬሕይወትን ማሰቡ የማይቀር ነው፤ ዓይኖቻቸው በጣም ይመሳሰላሉ። ከገጽታቸው ላይ ጥንካሬ ይነበባል። ቶሎ ብዬ ደግሞ እናቷን ተመለከትኩ፤ የፍርዬ አፍንጫ፣ ጉንጮችና ከንፈሮቿ ቁርጥ የእናቷ ናቸው። ልጆቹ ገና ልጆች ሳሉ የተነሱት ፎቶ ነው። ፍርዬ ከአባቷ አጠገብ፣ ታናሽ ወንድሟ ቃለአብ ከእናቱ በኩል፣ ሚሚና ሮቤል ደግሞ ከአባታቸውና ከእናታቸው እግር ስር ተቀምጠዋል። ፍርዬን መጠየቅ ፈራሁና ፎቶውን ዝም ብዬ መመልከት ቀጠልኩ።

"አየሻቸው?" አለችኝ ፍርዬ።

"አዎን" በጣም የሚያምር የቤተሰብ ፎቶ ነው አልኳት።

"ግን..." አልኩና መቀጠል አቃተኝ፤ እኔ ያቃተኝን ግን እርሷ ጨረሰችው።

"ግንማ ዛሬ ማንም አጠገቤ የለም። አባቴና እናቴ እንዲሁም ከእናቴ አጠገብ የቆመው ታናሽ ወንድሜ ቃለአብ ሞተዋል፤ ሚሚ የት እንደደረሱ ከማላውቃቸው ሰዎች መሀል ሊላዋ ነች። እኔ ከብዙ መከራ በኋላ ወደቤቴ ስመለስ እርሷ ግን የደረሰችበት ሳይታወቅ ወጥታ ቀረች። ሮቤል፤ ትንሹ ሮቤል አሜሪካን አገር ሄዷል" አለችኝ።

ያ ከፀጉረ ረጅሟ ወጣት አጠገብ የተሰቀለው ፎቶ የሮቤል መሆኑ ያስታውቃል፤ "ልጅቱስ ማን ትሆን?" ፎቶዎቹን ቀና ብዬ ስመለከት አየችኝና "ሮቤልን አየሽው? ልጅቱንስ?" አለችኝ ፍርዬ።

"ሮቤልን አወቅሁት፤ ልጅቱን ግን..." አልኩና ዝም አልኩ።



"እስኪ በደንብ እይኝ" አለችኝ ፍርዬ፤ አየኋት ግን ፎቶው ላይ ያለችውን ልጅ ከፍርዬ ጋር ማመሳሰል ተቸገርኩ። "እኔ ነኝ" አለችኝ ፍርዬ። ጮክ ብዬ ባለቅስ ደስ ይለኝ ነበር።

አንገቷን ዞር አድርጋ ወዲህኛው ግድግዳ ላይ የተሰቀሉትን ፎቶግራፎች ተመለከተችና "እነዚህ ደግሞ ቃለአብና ሚሚ ናቸው" አለችኝ። መንፈሴ በጣም ተጎዳብኝ፤ ልቤ ተጨነቀች። ልጆቿ መስለውኝ ነበር እንጂ ወንድምና እህቷ ናቸው ብዬ አልገመትኩም ነበር።

ያንን ዓይን የሚስብ የሁለት ልጆች ፎቶግራፍ ደግሞ ተመለከተችው፤ ዓይኖቿን ማንሳት አልሆነላትም። ዐይኖቿ እንባ ሲያቀሩ ተመለከትኩ፤ "ፍርዬ" አልኳት ሳላስበው። ዞር ብላ ተመለከተችኝ።

"ይቅርታ ፍርዬ ላሳዝንሽ ፈልጌ አልነበረም" አልኳት

"አይ ስናፍቅ! ሐዘን መቼ ተለይቶኝ ያውቃል? ብቻዬንስ እያየኋቸው ሳለቅስ አይደል የምኖረው? ሁላችንም ያልታደልን ነን፣ በተለይ ደግሞ ልጆቼ፤ እኛ እንኳን ብዙ አሳልፈናል" አለችና ተመለከተችኝ። እነዚያ ዓይን የሚስቡ ሁለት ልጆች ልጆቿ መሆናቸው ገባኝ።

የተፈጠረባትን ስሜት ለመለወጥ በጣም ፈለግሁ። ሃሳቤ ይህን ሲያሰላስል እጆቼ በደመነፍስ እፊቴ ያሉትን ፎቶዎች እያነሱ ማስቀመጣቸውን አላቋረጡም። በዝምታ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ።

"እየመሸብሽ ነው ስናፍቅ" አለችኝ ፍርዬ። ሰዓቴን ተመለከትኩ የእውነትም እየመሸ ነው፤ አስራ ሁለት ሰዓት ሊሆን የቀሩት ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ናቸው። ፍርዬን ግን በዚያ ስሜት ውስጥ ትቻት መሄድ በጣም ከበደኝ።

የፍርዬ ግንባር ላብ ችፍፍ አድርጓል፤ ዳበስኩት ትኩሳቷ ኃይለኛ አይደለም። የሆነ ነገር እንድላት ውስጤ በጣም ይፈልጋል፤ ምን እንደምላት ግን ግራ ግብት አለኝ።

"ፍርዬ!" አልኳት ድንገት

"ወዬ!" አለችኝ በገጽታዋ ላይ ከሚስተዋለው የድካም ስሜት ጋር በማይሄድ ጥንካሬ።

"በጣም እወድሻለሁ፤ ስላወቅሁሽ በጣም ደስ ብሎኛል፤ ከአሁኑ በበለጠ በቅርብ ብንከባከብሽ ደግሞ የበለጠ ደስ ይለኝ ነበር" አልኳት።

"ስናፍቅ! እናንተን የሰጠኝ እግዚአብሔር ይመስገን። በሕይወቴ ሁሉ ብዙ መልካም ሰዎችን እንዳገኝ እግዚአብሔር በመፍቀዱ ደስተኛ ነኝ። መመላለስሽን ሳስበው ከሚጨንቀኝ በቀር አሁን እያደረግሽልኝ ያለሽው ለእኔ ከበቂ በላይ ነው" አለችኝ።

"ፍሬ! እንዴት አመሸሽ" የሚል የትልቅ ሰው ድምጽ ተሰማን።

"እግዚአብሔር ይመስገን፤ ግቡ የበላይሁን እናት" አለች ፍሬ የቻለችውን ያህል ጮክ ብላ።

መቋሚያቸውን ደገፍ እያሉ የሚያዘግሙ አሮጊት ገቡ። "ጎሽ ዛሬስ ሰው አለሽ" አሉ ሴትዮዋ እጃቸውን ግንባራቸው ላይ ከለል አድርገው ለማዬት እየሞከሩ።

"እግዚአብሔር ዘመዶች ሰጠኝ የበላይ እናት፤ ስናፍቅሽ ትባላለች፤ የነገርኩዎት ስለእነርሱ ነው" አለቻቸው ፍርዬ። "ዘመዶቻቸው ወስደዋቸው ነበር፤ ሰሞኑን ነው የተመለሱት፤ እዚህ ግቢ ያለነው እኔና እርሳቸው ብቻ ነን" አለች ደግሞ ወደኔ ዞራ።

"ተባረኩ ልጆቼ" ከማለት ሌላ ምንም አላሉም።

"ይመሽብሻል ስናፍቅ" አለችኝ ፍርዬ።



ፍርዬን ተሰናብቼ ስወጣ ልቤ አብሮኝ የወጣ እስከማይመስለኝ ድረስ ከሀሳቤ ሳላወጣት አምሽቼ በአእምሮዬ እንዳመላለስኳት ወደአልጋዬ ሄድኩ።

* * * *

ሰሞኑን ሥራ በጣም በዝቶብኝ ሰነበትኩ። በርካታ ህሙማን ወደ ፕሮግራሙ የገቡበት ጊዜ በመሆኑ ሁሉንም ማየት ነበረብኝ። ፍርዬንም ሳላያት ሰንብቻለሁ። ማታ ቤት ገብቼ አረፍ ስል ፍርዬን ከሀሳቤ ላወጣት አልቻልኩም "ነገ ሄጄ አያታለሁ" አልኩ ለራሴ።

ጠዋት ፍርዬን ለማየት በመሄድ ላይ እያለሁ ፍቅር ደወለችልኝና "እማማን አሟቸዋል በጣም ይፈልጉሻል" አለችኝ፡፡ ወደእርሷ እየሄድኩ መሆኔን ነገርኳት። በውስጤ ብዙ ተመኘሁ "ሀብታም ብሆን ኖሮ እንደሰማይ የራቀንን የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት ለስንቶቹ ህሙማን ባዳረስኩ ነበር" አልኩ ለራሴ። መድሃኒቱን ቢያገኙ ጤናማ ሊሆኑ የሚችሉትን ሁሉ ቆጠርኳቸውና "አይ ድህነት!" አልኩ፤ አሁንም ለራሴ ነው።

የሆነ ነገር በጭንቅላቴ አቃጨለብኝና ሀሳቤን ቀይሬ "ፍቅር! ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ታገሽኝ መጣሁ" አልኳትና ስልኩን ዘጋሁት። ወደ አለርት ሆስፒታል የሚያደርሰኝን ታክሲ ያዝኩ፤ ደቂቃዎች ቢረዝሙብኝም ደረስኩና ከታክሲ ወርጄ እርምጃዬን ፈጠን በማድረግ አቀበቱ ምንም ሳይሰማኝ አለርት ሆስፒታል ገባሁ፡፡ የሁላችንን ጥረት ጎደሎ ያደረገው፣ ከዛሬ ነገ ይመጣል እያልን ስንጠብቅ የነበረው የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት ስርጭት ይጀመራል የሚለውን ጭምጭምታ ለማረጋገጥ ነበር ወደአለርት ያቀናሁት፡፡

በውስጤ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ የመነጋገር ያህል እየለመንኩትና እየተማፀንኩት ሁልጊዜ እየተመላለስኩ የምጨቀጭቃቸውን ሀኪም በር አንኳኳሁ። ሐኪሙ ቀና ብለው ሲመለከቱኝ ከወንበራቸው ብድግ አሉ። ፊታቸው ፈክቷል፤

ፈገግታቸው ወደ እኔም የተጋባ ይመስል እኔም ፈገግ ብዬ ለሰላምታ ተጠጋሁ።

“እንኳን መጣሽ፤ እንዴት እንደምነግርሽ እያሰላሰልኩ ሳለሁ ነው የመጣሽው” አሉኝ እየጨበጡኝ።

“መድሃኒቱ መጣ?” አልኳቸው ደስታ ከውስጤ እየፈነቀለኝ።

“አዎን ደርሷል፤ መድሀኒት ሊጀምሩ የሚገባቸውን ሰላሳ ሀሙማን ነገ እንድታመጡ ያስፈልጋል” አሉኝ ወንበራቸው ላይ እየተቀመጡ።

እንዴት አድርጌ እንዳመሰገንኳቸው በውል አላስታውስም፤ ብቻ ለእርሳቸው ይሁን ለእግዚአብሔር ባላውቀውም ምስጋና በምስጋና ላይ አነባብሬ ተሰናብቼ ወጣሁ።

ፍርዬ ቤት ለመድረስ የወሰደብኝ ጊዜ ሰላሳ ደቂቃ ብቻ ነው፡፡ እንደተለመደው ገርበብ ያለውን በር ከፍቼ ስገባ ፍቅርን እዛች ዱካ ላይ ኩርምት ብላ አየኋት፡፡

“ፍቅር የምስራች ነገ መድሃኒት ልንጀምር ነው” አልኳት። ከተቀመጠችበት ተፈናጥራ አንገቴ ላይ ተጠመጠመች። የሁለታችንም እንባ ዐይኖቻችንን ዘልቆ ሲወርድ ተያየን። የደስታ እንባ ነበረ።

"መጣሽ ልጄ?" አለችኝ ፍርዬ የግዴን።

"አዎን ፍርዬ መጥቻለሁ ምነው ሰሞኑን ደህና አልነበርሽም እንዴ?" አልኩኝ ግንባሯን እየደባበስኩ፡፡ ላብ ችፍፍ ብሎበታል።

"ይበቃኛል! ኧረ አሁንስ ይበቃኛል። እግዚአብሔር እናንተን ከሰጠኝ ይበቃኛል..."



“አሁንማ መብቃት የለም ፍርዬ! መድሀኒቱን ከሚጀምሩት ሰዎች በአንደኛ ደረጃ ላይ ያለሽው አንቺ ነሽ” አልኳት ወደአጠገቧ ቀርቤ።

“መስሎሽ ነው ስናፍቅ፤ እኔ እኮ አብቅቻለሁ” አለችኝ የግንባሯን ትኩሳት ለመለካት የዘረጋሁትን እጄን ለመያዝ ጥረት እያደረገች።

"ሲስ ደርሼ ልምጣ?" አለችኝ ፍቅር የፍርዬ ሁኔታ እያስጨነቃት፡፡ በአንገቴ ምልክት አሳየኋትና ቀስ ብላ ወጣች።

ጸጥታ ሆነ፤ ፈራሁ በጣም ፈራሁ፡፡ እግዚአብሔር የአንድ ቀን ዕድሜ እንዲጨምርላት ደጋግሜ ጠየቅሁ፤ መድሀኒቱን ካገኘች እንደሚሻላት እርግጠኛ በመሆን፡፡ በሕይወትና በሞት መሀል ያለውን ቅርበት ሳስበው ተጨነቅሁ። “አቤት እንዴት ይገርማል? ያችን ከሕይወት ወደ ሞት የምንሸጋገርባትን ቅጽበት በእርግጠኛነት መናገር የሚችል ማንም የለም...” ፍርዬ ከሃሳቤ መንጥቃ አወጣችኝ።

"አደራዬን ልሰጥሽ ነበር ያስጠራሁሽ..." በማለት።

"የምን አደራ ፍርዬ?" አልኩ ልቤ በድንጋጤ እየተንደፋደፈች።

"ለልጆቼ የሚደርስ አደራ"

"ልጆችሽን እኔ እንዴት ላገኛቸው እችላለሁ ፍርዬ?"

"ግዴለሽም ልጆቼን ማግኘት አያስፈልግሽም። የአንቺ አደራ እነዚህን የተበታተኑ ወረቀቶች አሰባስበሽ ሕይወት ዘርተሽባቸው ማሳተም ብቻ ነው..."

"አልገባኝም ፍርዬ የምትይኝ በጭራሽ አልገባኝም..."

"ይኸውልሽ" አለችኝ ከትራሷ ስር በላስቲክ የተጠቀለለ ነገር እየጎተተች፡፡ መጎተቱን አገዝኳትና አወጣሁት ወረቀት መሆኑን አየሁ፡፡

"ቀነጫጭቤ የነገርኩሽን ታሪኮች ሁሉ በእነዚህ የተበታተኑ ወረቀቶች ላይ ታገኛቸዋለሽ። እስከአሁኗ ደቂቃ ድረስ ተስፋዬን አላሟጠጥኩም ነበር። እነዚህን የተበታተኑ ጽሑፎች ወደ አንድ ለማምጣት እንድችል እግዚአብሔር ዕድሜ እንዲሰጠኝ እየጸለይኩም ነበር... አሁን ግን አበቃሁ... በዚህ ሰዓት ደግሞ አንቺን አጠገቤ እንድትሆኝ ፈቀደ... እናም አደራዬን ተቀበይኝ..." አለችኝና በረጅሙ ተነፈሰች። ያጠራቀመችውን ኃይል ሁሉ ያሟጠጠች ይመስል፡፡

"እንግዲህ የዘላለም እንቅልፌን የማንቀላፋው በደስታ መሆኑን ልታምኚ ይገባሻል..." በድጋሚ በረጅሙ ተነፈሰች፡፡ እጄን ጠበቅ አድርጋ ያዘችኝ ፍርዬ። "እዛ ሳጥን ውስጥ ደግሞ እንዲሁ በርካታ ወረቀቶች አሉ ሌላ ቀን ታያቸዋለሽ" አለችኝ እንደገና።

"እንዴት በጣም የሚያምር የእጅ ጽሑፍ ነው?" አልኩና መልስ ሳልጠብቅ ማንበቤን ቀጠልኩ፡፡ ጽሑፉ በጣም መሰጠኝ፤ ለምን ያህል ደቂቃዎች እንዳነበብኩ አላስታውስም፡፡ ብቻ የሆነ ስሜት ከተመስጦዬ ውስጥ አወጣኝ። ጠበቅ አድርጎኝ የነበረው የፍርዬ እጅ ለቀቅ ብሏል ቀና ብዬ ፍርዬን አየኋት፡፡ ሳላስበው ደጋግሜ ስሟን መጥራቴ ትዝ ይለኛል...

በጭራሽ የምሠራውን አላወቅሁትም፤ ብቻ መላው ጥፍት ብሎብኝ ተደነጋገርኩ። ድንገት ፍርዬ ቀስቀስ አለች። ልቤም ወደቦታዋ የተመለሰች መሰለኝ። ራሴን በጣም ወቀስኩት፤ የህክምና ባለሙያነቴን ሁሉ ዘንግቼ እንዲያ መሆኔ ለራሴም ገረመኝና "እንኳንም ሌላ ሰው ያላየኝ" አልኩ ።

"ፍርዬ! እንዴት ነሽ?" አልኳት ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ።

"በጣም ደከመኝ" አለችኝ በዝቅተኛ ድምጽ።

"ፍርዬ ለአንድ ቀን ብቻ በርቺና ጠንክሪ" አልኳት በልመና ዓይነት።



"እስኪ እግዚአብሔር ያውቃል!" አለችኝ።

"እስኪ እንቅልፍ ይውሰድሽ" ብዬ ልብሷን አመቻቸሁላት። ብዙም ሳትቆይ ኃይለኛ እንቅልፍ ወሰዳት። ፍቅር እስክትመጣ መጠበቅ ነበረብኝና እርሷን እየጠበቅሁ ፍርዬ የሰጠችኝን ጽሑፍ ማንበቤን ቀጠልኩ።

በሚቀጥለው ቀን የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መድሃኒቱን የሚወስዱትን የመጀመሪያዎቹን ሰዎች ሆስፒታል ለማድረስ ቅድመ ዝግጅት መደረግ ነበረበት። ይህንኑ መረጃ ለመለዋወጥ እንድችል ወደ ቢሮ መሄድ ነበረብኝና ፍርዬንና ፍቅርን ትቻቸው ወጣሁ። ውስጤ የፍርዬን ጽሑፍ ለማንበብ በጣም ጓጉቷል፤ ግን ወደ ቢሮዬ አቀናሁ። በዐይነሕሊናዬ የሥራ ባልደረቦቼ ይህንን መረጃ ሲሰሙ የቱን ያህል ሊደሰቱ እንደሚችሉ እያየሁ ወደቢሮ ገባሁ።

* * * *

መንፈሴ እንደተጨናነቀ፤ የረባም እንቅልፍ ሳይወስደኝ እንደምንም ብሎ ሌሊቱ ነጋና በጠዋት ወደሥራዬ ሔድኩ። ፍርዬንና ሌሎቹንም ሕሙማን ወደ ሆስፒታል ለማድረስ ባደረግነው የሥራ ክፍፍል መሠረት ሁሉም በሰዓቱ አለርት ጊቢ ተገኙ። ሊደረጉ የሚገባቸው ቅድመ ዝግጅቶች ሁሉ ተደርገው ከመጡት ህሙማን ውስጥ ብዙዎቹ መድሃኒቱን እንዲጀምሩ ተወሰነ።

ፍርዬ አልጋ እንድትይዝና መድሃኒቱን እንድትጀምር በመወሰኑ እዚያው ሆስፒታል ተኛች። ትቻት መሄድ አልፈለግሁም፤ እንዲህ ነው ብዬ መግለጽ ባልችልም ከገጽታዋ ላይ የማነበው አንዳች ነገር አለ። ፍቅርን ወደቤት እንድትሄድ ነገርኳትና እኔ ፍርዬ ዘንድ ለመቆየት ወንበር ስቤ ተቀመጥኩ።

"አደራዬን ተቀብለሽኛል ሰናፍቅ?" አለችኝ ፍርዬ ብቻችንን ስንሆን።

“መቀበሉንማ ምን ጥያቄ አለው ፍርዬ! ግን ተስፋ እንድታደርጊ እፈልጋለሁ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከአልጋሽ ተነስተሽ ሁሉን ነገር የምናደርገው አብረን ይሆናል። የሚሆነውን ነገር ሳስበው ልቤ በሀሴት ትሞላለች” አልኳት በዐይነህሊናዬ ፍርዬ ተሽሏትና ተነስታ አብረን ብዙ ነገሮች ስናደርግ እያየሁ።

የፍርዬ ዐይኖች እንባ አቁተው በመመልከቴ ደግሞ ተስፋዬ ጭልም አለብኝ። ቢሆንም ብዙ ልነተርካት አልፈለግሁም። እንድትተኛና እንቅልፍ እንዲወስዳት አመቻቸሁላትና እዚያው አጠገቧ ቆየሁ። የተረጋጋና የሰላም እንቅልፍ ወሰዳት።

መድሃኒቱን ለጀመሩት ሕሙማን ልዩ ትኩረት በመስጠት ክትትሉ ቀጠለ። መቼም ሁሌም አዲስ ነገርን መልመድ ቀላል አይደለም፤ መድሃኒቱም በሁሉም ሕሙማን ላይ ተመሳሳይ ውጤት አያሳይም አንዳንዶች በቀላሉ ሲላመዱት ሌሎች ደግሞ የበለጠ ምክር፣ መድሀኒቱ በሚያስከትላቸው የጎንዮሽ ውጤቶች የበለጠ ምክር፣ እንክብካቤና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ሆኑ። በእንክብካቤና እንክብካቤና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ሆኑ። በእንክብካቤና ድጋፉ ሥራ ላይ የተሠማራን የጤና ባለሙያዎችና በጎ ፈቃደኞች ከምንጊዜውም የበለጠ ጥንቃቄ ያለው ሥራ መሥራት ነበረብንና የማያቋርጥ ቴክኒካዊ ድጋፍ እየተሰጠን ሥራችንን ቀጠልን።

ፍርዬ ከአሥር ቀናት በኋላ ከሆስፒታል እንድትወጣ ሆነ። የመድሃኒቱ የጎንዮሽ ችግሮች ጠንከር ብለው ከተከሰቱባቸው ሕሙማን አንዷ ፍርዬ ሆነች። በአንጻሩ ደግሞ ችግሩ ጊዜያዊ መሆኑንና ጤንነቷ እንደሚመለስ የተሰጣትን ምክር በመቀበል ከሆስፒታል ስትወጣ የነበራት የመንፈስ ጥንካሬና ተስፋ ከፍተኛ ሆኖ ተመለከትኩ።

መድሃኒቱ በብዙዎች ጤንነት ላይ “ተዓምራዊ” የሚባል ለውጥ አመጣ። በርካቶች ከአልጋ ተነስተው ወዲያ ወዲህ ለማለት ቻሉ፤ የመኖር ፍላጎት አንሰራራ፣ ተስፋቸው በገጽታቸው ላይ ተነበበ፤ ልጆቻቸው በወላጆቻቸው ሁኔታ ፍንድቅ አሉ። ከህሙማኑ ባልተናነሰ ሁኔታ ደስታችን ከፍተኛ ሆነ።



ፍርዬ ግን ዕጣ ክፍሏ ከእነኚህ ወገን አልሆነም። እኛም ተመላልሰን ከመጠየቅ ወደኋላ አላልንም። በተለይ እኔ የፍርዬን ጽሑፍ እያነበብኩ ስለነበረ ብዙ የምጠይቃት ነገሮች ነበሩኝና በፍርዬ ጤንነት ያለመሻሻል በጣም አዘንኩ። አንድ ቀን ወደ ፍርዬ ቤት ስሄድ ሁኔታው ሁሉ ተባብሶ ደረስኩ። ፍቅር አዝናና ተክዛ አገኘኋት። ብዙዎች ተንከባካቢዎች የፍቅርን ስሜት ተጋርተው እንደተከዙ ከፍርዬ ቤት ሲወጡ ነበር የደረስኩት።

ፍርዬን ተጠግቼ ስመለከታት፤ በውስጧ የነበረችው የተስፋ ሻማ ተሟጠጠች። በመጨረሻዋ ሰዓት ላይ እንደደረስኩ ተረዳሁ። በፍርዬ ግንባር ላይ ችፍፍ ያለው ላብ ጥቃቅን የውሀ ጠብታዎች ፈጥሯል። ከእግሮቿ ጀምሬ ሁለመናዋን ዳሰስኩት። ፍርዬ የመጨረሻዋ ህቅታ ላይ ደርሳለች። “ግን ሳልሰናበታት፤ መልስ ለማግኘት የምጓጓላቸውን ጥያቄዎቼን ሳልጠይቃት፣ ያን የሚጥመኝን እንደበቷን ሳልሰማው...” መንፈሴ መረጋጋት አቃተው...

የልብ ምቷን ለማዳመጥ እጇዋን ለመያዝ መሞከሬን አስታውሳለሁ... ከዛ ደግሞ ግንባሯን የሳምኳትም ይመስለኛል ዓይነ ህሊናዬ ግን የሚያየው እናቴን ነበር... ከሶስት ዓመታት በፊት በሞት የተለየችኝ እናቴን... ከዛ ደግሞ የፍቅር ድምጽ... መጀመሪያ ኃይለኛ የድንጋጤ ጩኸት ተሰምቶኝ ወዲያው ደግሞ ልስልስ ያለ ድምጽ... በቃ ከዛ ሁሉም ጨለመ፡፡

ከስንት ደቂቃ ወይንም ሰዓት በኋላ ከገባሁበት ስመመን እንደነቃሁ አላወቅሁም ፤ ግን ነቃሁ፤ ስነቃ ያለሁበትን ለማስታወስ ጥቂት ደቂቃዎች ቢወስዱብኝም ፍርዬን አስታወስኳት። ፍርዬ ጋ ተመልሼ ገባሁ ያው በመጀመሪያ ሳያት የነበረችበት ሁኔታ ውስጥ ነች። ትንፋሿ ብቻ አልተሟጠጠችም። አልጋዋ ላይ ተቀመጥኩ፤ እስከመጨረሻ ትንፋሽ ድረስ ካጠገቧ ላለመለየት ስሜቴን መቆጣጠር ነበረብኝ።

አንድ ሰው ወደነበርንበት ክፍል ገባ፤ ፍርዬን ተመለከታት የተሳሳተ መሰለውና የዕውነት ፍሬሕይወት መሆኗን ጠየቀ። በፍጹም ሊያምን አልቻለም፤ ከንፈሮቹ ሲደርቁና ጉንጮቹ

ሲንቀጠቀጡ አስተዋልኩት። ያንን እኔ ለመጀመሪያ ቀን ሳየው የፍሬሕይወት ልጅ ፎቶ የመሰለኝን ፎቶግራፍ አሳየሁት። ብዙዎች በሀዘን ሲጎዱ አይቻለሁ፤ እኔም በእናቴ ሞትና አሁንም በፍርዬ ተጎድቻለሁ ሰውየው የሆነውን መሆን ግን በሕይወቴ አላየሁም። ተንበረከከ፤ የፍሬሕይወትን ግንባርና ጉንጮች ሳመ ዳበሳት። ዓይኖቹ የፈነዳ የውሀ ቧንቧ ይመስል እንባቸውን አንዶለዶሉት... ሁላችንንም አስለቀሰን። ያን ሰው በቀብሯ ላይም ሆነ ከዛ በኋላ አላየሁትም። ሁልጊዜ ፍርዬን ሳስብ ግን ሳስበው እኖራለሁ። የፍርዬን ጽሑፍ ግን ጨርሼ ሳነብ የሰውየውን ማንነት መገመት ችያለሁ። ግምቴንም በመጨረሻው የፍሬሕይወት ስንብት ላይ ትክክል መሆኑን አረጋግጫለሁ። ግን አእምሮዬ ፈጥኖ አላሰበም፤ ፍሬሕይወት መቃብር ላይ አበባ ያስቀመጠችውን ሴትዮ አላናገርኳትም ከዚያም በኋላ ላገኛት አልቻልኩም።

የፍርዬን ሞት መቀበል ግድ መሆኑን ባምንም፣ ሌሎች በርካቶች መሞታቸውን ባውቅም ተፈተንኩበት። በፍርዬ ለቅሶ ላይ ያልጠበቅሁትን ያህል ሰው ነበር፤ ብዙዎችም ሲያለቅሱላት ተመልክቼ "እነዚህ ሁሉ በታመመችበት ጊዜ የት ነበሩ?" ብዬ ራሴን ጠይቄአለሁ። ከሁሉም የተለየ ግን ሁለት ሰዎች ምርር ያለ ለቅሶ ሲያለቅሱ አስተዋልኩ። ለቅሶአቸው እኔንም የበለጠ አስለቀሰኝ። "እነዚህ ሰዎች እነማን ይሆኑ?" የሚለው ጥያቄ አእምሮዬ ውስጥ ሲጉላላ ቆየ።

ፍርዬ ሞታ ከመቃብር በታች ውላለች እኔ ግን አደራዬን አልበላሁም፡፡ እንባ በጉንጮቼ እየወረደ የፍርዬን የተቆራረጡ ጽሑፎች ደጋግሜ አነብቤአቸዋለሁ፡፡ ተገጣጥመው ትልቅ ታሪክ ሊወጣቸው እንደሚችልም ጥርጥር የለኝም። ግን ፍርዬን ልጠይቃት የምፈልጋቸው በርካታ ጥያቄዎች ነበሩኝ፤ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጠኝ ኃይል ከየት አባቴ አገኛለሁ?

የፍርዬን ጽሑፎች ደጋግሜ ከማንበብ የተነሳ አንዳንዶቹን በቃሌም አስታውሳቸዋለሁ። ሆኖም ዛሬም ብድግ አድርጌ ማንበቤን አልተውኩም። ከሥራ ገብቼ ጥቂት እንደቆየሁ ሳላስበው የፍርዬን ጽሑፎች ወዳስቀመጥኩበት ሄድኩ፤ ወረቀቶቹን ገለጥለጥ



አድርጌ አንዱን አወጣሁና ወደወንበሩ አመራሁ። ማንበብ ስጀምር እስከዛሬ ሳላየው ቀርቼ ይሁን ወይንም ልብ ሳልለው ያላስተዋልኩትን ነገር ተመለከትኩ። ሥምና የስልክ ቁጥር ነው፡፡ በፍጹም አላቅማማሁም ስልኩን ደወልኩ።

ስልኩ እየጠራ ልቤን ፍርሀት ተሰማው፤ ልዘጋውም አሰብኩ በኋላ ግን ጨከንኩ "ከሆነ ይሆናል ካልሆነም ይቅርታ መጠየቅና መዝጋት ነው..." ድንገት ስልኩ ተነሳና ድንብርብሬን አወጣው።

"ጤና ይስጥልኝ" አልኩ ድምጼ እየተንቀጠቀጠ።

"አብሮ ይስጥልኝ ማን ልበል?" የማያስፈራና ቀለል ያለ ድምጽ ነበር።

"አያውቁኝም፤ ግን አንዳንድ ነገር ስለፍሬሕይወት..." አቋረጡኝ።

"ስለፍሬሕይወት ምን?" ቆጣ ያሉ መሰለኝ።

"ሌላ ነገር አይደለም፤ አንድ አደራ ሰጥታኝ ነበር ያን አደራዬን ለመወጣት በቅርብ የሚያውቋትን ሰዎች እገዛ ፈልጌ ነው" አልኩ በትህትና።

"ምን ዓይነት እገዛ?" ቁጣቸው ቀዝቀዝ ብሏል።

"ተገናኝተን ብንነጋገር ደስ ይለኝ ነበር" አልኩኝ አሁንም በልመና ዓይነት።

ሰውየው እንዳገኛቸው ፈቃደኛ ሆኑልኝ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ሰውየውን ለማግኘት ወደቀጠሮዬ ስሄድ የፍርዬን ድርጅታዊ የፖለቲካ ሕይወት የመጀመሪያ ቀጠሮ አስታወስኩ።

"መፋቂያሽ ከየት መጣልሽ?"

"ከጃማይካ" አልኩኝ ለራሴ።

ሁለታችንም ልክ በሰዓቱ ቀጠሮው ቦታ ደረስን። ያገኘሁት አምርረው ያለቀሱ ከነበሩ ሰዎች አንዱን ነው። ታረቀኝ ይባላል። ልክ ፍርዬን በማይበት ዓይኔ ስላየሁት ታረቀኝን ወዲያውኑ አንተ ማለት ጀመርኩ ። ከመጀመሪያው ንግግራችን አደራዬን ለመወጣት የሚያስፈልገኝን እገዛ ሁሉ እንደማገኝ እርግጠኛ ሆንኩ። ሁለታችንም ስሜታችንን የምንገልጽበት ቃላት እስከሚያጥረን ድረስ ተደሰትን። ታረቀኝ የፍርዬን መጽሐፍ እውን ለማድረግ የበኩሉን ከማድረግ ወደኋላ እንደማይል አረጋገጠልኝ፤ ደስም አለኝ። ታረቀኝና ሌሎች የፍርዬ ወዳጆች የፍርዬን ሕልም እውን ለማድረግ ያደረጉት አስተዋጽኦ ከምንም በላይ ነው።

ፍርዬን የሁለት ጦርነቶች ምርኮኛ ሆና አገኘኋት እናም ለጽሑፉ ርዕስ እንዲሆን ወሰንኩ፡፡ ፍርዬ ጀግና ነች፤ በአንደኛው ጦርነት ቁስለኛ ሆና ቆየች፤ ሁለተኛው ጦርነት ግን ሕይወቷን ነጠቃት። ፍርዬ ዛሬም ጀግና ነች፤ ወደመጨረሻ የጻፈቻቸው አንዳንዶቹን ገፆች መቼ እንደጻፈቻቸው ሳስብ ጥንካሬዋን አደንቃለሁ፡፡ በጣም ሙንጭርጭር ያለ በመሆኑ ምናልባትም ከሞት ጋር እየታገለች በስቃይዋ መሀል እንደጻፈችው እገምታለሁ።

የፍርዬን ጽሑፎች ሳነብ ላጫሩብኝ ጥያቄዎች መልስ የሚሆኑኝ አንዳንድ ነገሮችን ለማግኘት በአቅሜ ብዙ እርምጃዎች ተራምጃለሁ። ሙሉ ፈቃደኝነቱን ከሰጠኝ ከታረቀኝ ብዙ ማወቅ ችያለሁ። በእርሱም በኩል ብዙ ሰዎችን አግኝቻለሁ፤ ፍርዬ ያደገችበትን ሰፈር እኔ ያደግሁበት ያህል አውቄዋለሁ።

በዕድሜ ብቻ ሳይሆን በሀዘን ምክንያት እርጅና የተጫጫናቸውን የበላይሁንን እናት ተመላልሼ ጠይቄአቸዋለሁ። የተሰማኝን ስሜት መግለጽ በጣም ይከብደኛል፤ የፍርዬን ቤተሰቦች በጣም የማውቃቸው ያህል እንዲሰማኝ አደረጉኝ።

"እግዚአብሔር ያሰበው በልጠ እንጂ ፍርዬን በላይ እንዲያገባትና አበባዎቻቸውን እንዳይ እመኝ ነበር" አሉኝ አንድ ቀን የበላይሁን እናት እንባቸው እየፈሰሰ። "የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን የበላይሁንን ልጆች የማየት ዕድል ባላገኝም፤ የፍሬን ልጆች



በማየቴ ደስ አለኝ..." የበላይሁን እናት ስለፍርዬ አንስተው ተናግረው መጨረስ አይሆንላቸውም፤ እንባቸው ይቀድማቸዋል።

በታረቀኝ በኩል ፍርዬ እንደልጇ ታየው ከነበረው ከወንድሟ ከሮቤል ጋር የደብዳቤ ልውውጥ ማድረግ ችያለሁ፤ ፍርዬ ከእያንዳንዱ ዕሑፏ ውስጥ ሳትጠቅሰው የማታልፈውን ዘውዱን የማግኘት ዕድል ገጥሞኝ በጣም ተደስቻለሁ። በዘውዱም በኩል ፍርዬ የትዳር ሕይወቷን አብዛኛውን ዓመታት የኖረችበትን ቦታና የሠራችበትን መሥሪያ ቤት መጎብኘትና የሥራ ባልደረቦቿን ማግኘት ችያለሁ።

ከነዚህ ሰዎች ሁሉ መረጃዎች ባገኝም በርካታ ያልተመለሱ ጥያቄዎች ነበሩኝ እናም ታረቀኝን እንደገና ማስቸገር ነበረብኝ። ስለፍርዬ የዘመቻና የእስር ቤት ጓደኞች የሚያውቀው ነገር ካለው ብዬ ጠየቅሁትና የሚያውቃቸውን ጥቂት ሰዎች እንዳገኝ ጥረት አደረገልኝ፤ ተሳካለትም። ከዚህም በኋላ ቢሆን ሁሉን ነገር አውቄአለሁ ለማለት አልደፈርኩም፤ ቢሆንም "ከሞላ ጎደል" ማለት እችላለሁ።

የነፍርዬን ወቅትና አመለካከት ለመረዳት እነርሱ በትግሉ ወቅት ይከተሉት የነበረውን ፍልስፍና ለማወቅ ማንበብም ጀምሬአለሁ። ይህ ደግሞ ከነፍርዬ ልወስድ የሚገባኝ አንዱና ትልቁ ተሞክሮ መሆኑን እንድቀበል አደረገኝ። እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ በማወቅና በመነጋገር ላይ ማነጻቸውን አደንቃለሁ፤ የተቀበሉትን ስቃይ ሁሉ እንዲቀበሉ ያጸናቸው አውቀውና አምነው መግባታቸው ይመስለኛል። እናም የእነርሱን አስተሳሰብ በደንብ ለመረዳት እንድችል ጥርሴን ነክሼ፤ እየከበደኝ መዝገበ ቃላት አጠገቤ አስቀምጬ በቁርጠኝነት አነበብኩ። ተጨማሪ ገፆችን ባነበብኩ ቁጥር ደግሞ እየሳበኝ እየመሰጠኝ ሄደ። ካሰብኩት በላይ አነበብኩ፤ ለሕይወቴ ሁሉ የሚሆነኝን የማንበብ ልማዴንም አዳበርኩ።

## ክፍል 1
## ልጅነትና ዘመቻ

ሕይወት በፍሬሕይወት ሀሳብ ሳይሆን በራሷ መንገድ ይዛት መንጎድ የጀመረችው ገና በልጅነቷ ነበር፡፡ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ነበረች፡፡ "ነገን" ማሰብ የጀመረችበት ወሳኝ ዕድሜ!

ወሩ ጥቅምት ነበር፡፡ የጠዋቱ ውርጭ ይሸነቁጣል፡፡ የፀሐይዋ ጨረር ለማለዳው ወርቃማ ድምቀት ቢሰጠውም በብርዱ ላይ ያለውን የበላይነት ገና አላረጋገጠም፡፡ ጠዋቱ እንደቀዘቀዘ ቢሆንም በአራት ኪሎ ጎዳና ላይ ግን ለየት ያለ ትእይንት ይታያል፡፡ ዋናውን መንገድ ከዳር እስከ ዳር ግጥም አድርጎ የሞላው ካኪ ለባሽ ሰልፈኛ ከሩቅ ለሚመለከቱ ዓይኖች በዝግታ የሚፈስ ድፍርስ የወንዝ ውሃ ይመስላል፡፡

በእግረኛው መንገድ ላይ የሚተላለፈው ሰው ሁሉ የታዘዘ ይመስል ቆሞ ሰልፈኛውን ይመለከታል፡፡ ፍሬሕይወት የጃኬቷ ኮሌታ ብርዱን እንዲከላከልላት ወደ ላይ አቁማና እጆቿን ሱሪዋ ኪሶች ውስጥ ሸጉጣ ሰልፈኞቹን በትዝብት ብቻ ሳይሆን በንዴት ጭምር ተመለከተቻቸው ፡፡

ጊዜው 1967 ዓ.ም ሰልፈኞቹም "የዕድገት በሕብረት ዕውቀትና የሥራ ዘመቻ" ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ በለበሱት ካኪ ሸሚዝና ባደረጉት ኮፊያ ላይም ይሄው ተጽፏል፡፡ በጎዳናው ዳርና ዳር ከቆመው ሰው መሀል ከፊሉ በሀዘኔታ ከንፈሩን ሲመጥ ሌላው ደግሞ በአድናቆት የተዋጠ ይመስላል፡፡

"ጉረኞች" አለች ሳታስበው፡፡ ዘመቻው ቁርጠኛ መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ አምና ተቀበለች፡፡ እየተቃጠለችም እየበገነችም ቢሆን ከማመን በስተቀር አማራጭ አልነበራትም፡፡ ንዴቷን ለመዋጥ በረጅሙ ያስወጣችው ትንፋሿ ሙቀት ለራሷ ተሰማት፡፡

በዝግታ የሚተመው ሰልፈኛ ገና አላበቃም፡፡ ፍዝዝ ብላ እየተመለከተች ዘመቻው ቀዝቃዛ ውሃ የቸለሰበትን ዕቅዷንና ምኞቷን አሰበችው፡፡



"ምነው ያኔውኑ አቋርጬ በሆነ ኖሮ" አለች ለራሷ።

ቤተሰቦቿ በዝቅተኛ የኑሮ እርከን ላይ የሚገኙ ድሆች ናቸው፡፡ አባቷ አናፂ ነበሩ፤ በቋሚነት ባይቀጠሩም ሥራ ፈተው አያውቁም፡፡ አንድም ቀን ደከመኝ ብለውም አያውቁም፤ የሚያባክኑት ጊዜም የለም፤ ያገኙትን ሥራ ሁሉ በመሥራት ነው የሚታወቁት። በአባቷ ጥረት ይውተረተር የነበረው የቤተሰባቸው የኢኮኖሚ አቋም ከሁለት ዓመታት በፊት አባቷ በድንገት ሲሞቱ ተሽመድምዶ ወደቀ፡፡ በቤታቸው የሚላስና የሚቀመስ ጠፍቶ በባዶ አንጀት መጠቅለል ሲመጣ ነበር "ትምህርቴን ጨርሼ...ሥራ ይዤ... ለእናቴ..." የሚለውን ምኞቷን ፈተና የገጠመው። ትምህርቷን ለማቋረጥና ቤተሰቡን ለመደጎም አሰበች፡፡ እርሷ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኗ አባታቸውን ተክቶ ቤተሰባቸውን ለመደገፍ የሚችል ከእርሷ የተሻለ ትክክል አልነበረም፡፡

የ1967 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ገና እንደተጀመረ የሚነፍሰው ወሬ ደግሞ ለዓላማዋ እንቅፋት ሆኖ ነገን ሁሉ ያጨለመባት መሰላት፡፡ በጣም ተበሳጨች ወሬው እውነት እንዳይሆንም ፀለየች፡፡ ዘመቻውን አባቷን ከነጠቃት ሞት ጋር አመሳሰለችው፤ በጣምም ጠላችው፡፡

ዘመቻው የሚመለከተው ወጣት ሁሉ በዘመቻው ካልተሳተፈ ወደፊት የመማር ዕድል እንደማያገኝ በሰፊው ይነገራል። እናም ትምህርት አቋርጣ ሥራ መፈለግ የትምህርት ዕድሏን ሙሉ በሙሉ ያጨልምባታል፤ ዘመቻ መሄዱም ለቤተሰቡ ያለባትን ኃላፊነት እንዳትወጣ ያደርጋታል። እናም ግራ ግብት አላት ፍሬሕይወት።

ተማሪው በዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ላይ ሁለት አቋም ያዘ፡፡ ከፊሉ ዘመቻውን በመቃወም ቅስቀሳ ሲጀምር ግማሹ ደግሞ በመደገፍ ይፈነጥዝና ይጨፍር ጀመር፡፡ የዘመቻው ደጋፊዎች ዘመቻውን እንደትልቅ ጀብዱ ቆጥረውት ጉሮ ወሸባዬውን ተያያዙት፡፡ ከደጋፊዎቹ ጥቂቶቹ የፖለቲካ አቅጣጫ

ያላቸው ቢሆኑም ብዙዎቹ ግን የወጣትነት ትኩስ ስሜት የቀጣቸውና ምንም ይሁን አዲስ ነገር በአዲስነቱ ብቻ የሚያስደስታቸው ነበሩ። ተቃዋሚዎቹም እንዲሁ የተለያየ ምክንያት አላቸው። ብዙዎቹ ምክንያታቸው የፖለቲካ ጥያቄ ቢሆንም የፖለቲካ ብስለታቸው ተመሳሳይ ነው ማለት አዳጋች ነው። እንደፍሬሕይወት ከወዲሁ ለሕይወታቸው ዕቅድ የነደፉና ዘመቻው ለዕቅዳቸው እንቅፋት የሆነባቸው ከተቃዋሚው ጎራ ተሰለፉ።

በየትምህርት ቤቱ በርካታ የተቃውሞ ስብሰባዎች ተካሄዱ። እሷም በስብሰባዎቹ ተገኘች። ውይይቶቹ ብዙም የሚጥሟት ባይሆኑም፣ ለፖለቲካ ጆሮዎቿን መስጠት ባትፈልግም መደምደሚያው "አንዘምትም!" የሚለው መፈክር ልቧን እያንጠለጠለው ከስብሰባ መቅረት በጭራሽ አይሆንላትም።

በመጨረሻ የኃይል ሚዛኑ አጋደለና ዘመቻው እውን ሆነ። "አንዘምትም!" ብለው ከነበሩት ውስጥ ጥቂቶቹ ቆራጥ አቋም ይዘው ቢዘልቁም አብዛኛው ተማሪ ለዘመቻው ተመዘገበ። ፍሬሕይወትም የወደፊቱን አስባ በሁለት ዓመታት ሊጓተት መሆኑ የቆጫት የሕይወት ዕቅድ እስከወዲያኛው እንዳይጨናገፍባት ሰግታ የግዷን ተመዘገበች።

በዚያ ሰልፍ ላይ የመሳተፍ ፍላጎት ግን አልነበራትም። ተሰልፈው በማየቷም ተበሳጭታለች። ከመንገዱ ዳር ቆማ ተሰላፊዎቹን እየተመለከተች አንጀቷ ሲኮማተር ተሰማት። በሃሳብ ጭልጥ ብላ ጠፋች ለአፍታ ያህል።

ትከሻዋን ነካ አድርጎ "ሀይ ፍሬ" ሲላት ነው ከሄደችበት በድንጋጤ የተመለሰችው። በላይሁን ነበር "በናትሽ እነዚህን "ጎቦዎች" (በወጣቱ አነጋገር ለትግል አደናቃፊዎች የተሰጠ መጠሪያ ስም) ምናቸውን ታያቸዋለሽ? የደርግን ዕድሜ ለማራዘም በሚራወጡ ባንዳዎች እኮ ነው የሚነዱት።" አላት ሰልፈኞቹን በንቀትና በጥላቻ እያስተዋለ።



"ሌላውን እንኳን አላውቅም ለማንኛውም ግን በጣም አስጠልተውኛል" አለችው። በላይሁን ለፖለቲካ ያላትን ዝንባሌ አሳምሮ ስለሚያውቀው አባባሏ ብዙም አላስቆጣውም። ቢሆንም እንደሌላው ጊዜ ዝም ብሎ አላለፋትም፤

"እኔ እኮ ፍርዬ ይህን የመሰለ ጭንቅላት ለፖለቲካ ሲሆን ምን እንደሚያደነዝዘው ይገርመኛል። ሰሞኑን የተሳተፍሽባቸው ስብሰባዎች እንኳን ትንሽም አልለወጡሽም..." ዓይኖቿን ስታፈጥበትና ግንባሯን ስትቋጥርበት እንደሁልጊዜውም ደንገጥ አለ። በላይሁን ቁጣዋን ከማይወዱላት ጓደኞቿ አንዱ ነው ።

"በቃ በቃ ትቼዋለሁ ይቅር። ለሁሉም ጊዜ አለው ብሏል ጠቢቡ ሰሎሞን" አለና እንደወትሮአቸው ሁሉ አንገቷን አቀፍ አድርጎ ከቆመችበት አነቃነቃት። ለስንት ደቂቃዎች እንደቆመች ባታስታውስም ለረጅም ጊዜ መቆሟ ግን ታውቋታል።

"እኔ እንኳን መቼም ቢሆን ፖለቲካ ውስጥ ቢዘፈዝፉኝም አያርሰኝም" አለችው ቁጣዋን ትታ እየሳቀች።

"እናይ ኋላ አለች አሉ ዝንጀሮ" ብሎ ተረተባት በላይሁን።

በላይሁን ረጅም ነው፤ ከእርሱ አጠገብ ስትሆን ፍሬሕይወት አጭር የሆነች ይመስላታል። ሰውነቱ ደልዳላ ባይሆን ኖሮ እንዲያውም የበለጠ ረጅም ይመስል ነበር። ጭንቅላቱና ፊቱ ከረጅም ቁመቱ ጋር የሚመጣጠኑ አይመስሉም፤ ጭንቅላቱ አነስ ያለ ፊቱም መልከመልካም ነው። በተለይ ሲስቅ ልዩ ውበት አለው፤ ሲስቅ አነስ አነስ ያሉ ዓይኖቹ ወደ ውስጥ ይገቡና የጉንጮቹ ስርጉዳቶች ይጎላሉ። ሁሌም በሳቀ የሚባል ዓይነት ነው በላይሁን።

ፍሬሕይወትና በላይሁን አብሮ አደጎች ናቸው ማለት በቂ አይደለም። ከወንድሞቿ ለይታ አይታው አታውቅም። በዕድሜ ብዙ አይራራቁም የሚበልጣት በሁለት ዓመታት ብቻ ነው። በአንድ ክፍል ቢበልጣትም የሚማሩት አንድ ት/ቤት ነው። ዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት። ይሄ ጣጠኛ ዘመቻ

ባይመጣ ኖሮ በላይሁን ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ይወስድ ነበር፡፡ ይህንኑ እያብሰለሰለች በላይሁንን በሀሳቧ ትታው ሄደች፡፡

"ደግሞ ምን እያሰብሽ ነው? አበዛሽው መቼ ነው ይሄ የሃሳብ ጉዞ የሚያበቃው?" አላት አገጪን በእጁ ያዝ አድርጎ ፊቷን ወደ እርሱ እያዞረ፡፡

"የሚታሰብ ነገር ሲጠፋ ነዋ! በቃ ትምህርት መቋረጡ ነው አይደል?" አለችው ፊቷን እንደከሰከሰች፡፡

"አይ ፍርዬ በጣም የዋህ ነሽ ትምህርት ከመቋረጡም በላይ ከተማውን ለቀንለት ደርግ ስሩን እንዲሰድ ልናደርገው ነው፡፡ የደርግ ስሮች ደግሞ ምን እንደሚመጡ ታውቂያለሽ? ላብ! የሕዝብን ላብ መጠው ነው ደርግን የሚያፋፉት፡፡ ሺት!" አለ የደም ስሩ እየተገታተረ፡፡

"ስትናደድ ግን እንዴት ደስ እንደምትል ታውቃለህ? እኔ ግን ደርግ ስሩን ሰደደ አልሰደደ ጉዳዬ አይደለም፡፡ ደግሞም አያገባኝም፡፡ እኔን የሚቆጨኝ ትምህርቴ መቋረጡ ሃሳቤን በወቅቱ መፈፀም ያለመቻሌ ብቻ ነው፡፡ ፖለቲካውን ለእናንተ ትቼዋለሁ" አለችው፤ ከልቧ ነበር፡፡

"በጣም የዋህ ነሽ ፍርዬ ራስሽን ከሌላው ማህበረሰብ ለይተሽ ብቻሽን ሊያልፍልሽ፣ የብቻሽ የሕይወት ዕቅድ እንዲሰምርልሽ ትጥሪያለሽ፡፡ ግን አይሆንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለፈለት ብቻ እንደሚያልፍልሽ እወቂ፡፡ የአንቺ ሕይወት የሁለንተናዊ ሕይወት አካል መሆኑን አትዘንጊ... ለመሆኑ ስለዘመቻው ምን አሰብሽ?" አላት ማብራሪያውን ተወት አድርጎ፡፡

"መሄድ እንጂ ሌላ ምን ምርጫ ይኖረኛል? አንተስ?"

"እስካሁን አልወሰንኩም።"

"እንደፔንዱለም በሀሳብ ስትወዛወዝ ጊዜ እንዳይቀድምህ"



"በመጨረሻው ደቂቃም ቢሆን ወስኜ ከጊዜው እኩል እንደምራመድ አትጠራጠሪ።"

"ግን አንድ ላይ ብንመደብስ?" አለችው ደግሞ ድንገት።

"ደስታውን የምችለው ይመስልሻል? እነእማማስ እንዴት እንደጨነቃቸው አታይም አብረን ብንመደብላቸው ጭንቀታቸው ቀለለ ማለት ነው፡፡" አለ በላይሁን ከአንጀቱ በመነጨ ሁኔታ፡፡ "አንችስ ግን?" አላት መጠየቋ ራሱ ያስገረመው በሚመስል ዓይነት፡፡

"የሞትክ፤ እኔማ በጣም ያስጠላኛል" አለችው፤ ልታበሽቀው መሆኑን በሚገባ ያውቀዋል፡፡

* * * *

ወይዘሮ ስርጉት ሌሊቱን እንቅልፍ አልወሰዳቸውም፤ ማታ ለልጆቻቸው የሚረባ እራት ሳይሰጧቸው ነው የተኙት። ቤታቸው ባዶ ነው፤ ለነገ ሊሆን የሚችል ሙጣጭ እንኳ የሌለው የተራቆተ ቤት! እናም እንቅልፍ በአይናቸው ሳይዞር በሀሳብ ሲብከነከኑ ነው ሌሊቱን የገፉት። ወደንጋቱ ላይ እንቅልፍ ቢወስዳቸውም ተኝተው አላረፉዱም። እንዴት አድርገው ሊተኙ ይችላሉ? ማታ ሳይጠግቡ ያደሩ ልጆች ያለቁርስ ሲያረፍዱ የመመልከት አቅም የላቸውም?

ከአልጋቸው ወረዱና መብራቱን አብርተው ሳጥን ከፈቱ፤ ከሳጥኑ ውስጥ አንዲት ሙዳይ አለች። ሙዳይዋ ውስጥ በማዕረግ ጠቅለለው ያስቀመጧቸው የተዳሩባቸው ጌጦች፤ ትልቅ የወርቅ መስቀልና የጣት ቀለበት፤ የብር ሀብልና የጆሮ ጉትቻ ናቸው። ካጌጡባቸው ዓመታት ተቆጥረዋል፤ አንዳንዴ ሳጥኑን ሲከፍቱ ትዝ ቢሏቸውም ሊያጌጡባቸው ሳይሆን ልጃቸው ፍሬሕይወት ስታገባ እንደሚሰጧት ሲያስቡ ደስ ይላቸዋል።

"አይ አንተ መድህኔዓለም! ምነው እንዲህ ፊትህን አዞርክብኝ?" አሉ ወይዘሮ ስርጉት ሙዳይዋን ከሳጥኑ ውስጥ ሲያወጡ። ሙዳይዋን አገላብጠው ተመለከቷትና ከፈቷት ጌጦቹ

የተጠቀለሉበትን እራፊ ጨርቅ ነጣጥለው ትልቁን የወርቅ መስቀል አንስተው በእጃቸው እንደመመዘን አደረጉት። በጣም ትልቅ ነው መስቀሉ። በሌላው እጃቸው ደግሞ የጣት ቀለበታቸውን አወጡ፤ ሁለቱንም ተራ በተራ ተመለከቷቸው። ሊያደርጉ ያሰቡት ነገር መንፈሳቸውን ረበሸው፤ ግን ግድ ነው። እናም የወርቅ ቀለበቱንና የብር ጌጦቹን በጨርቁ ጠቅልለው ሙዳይዋ ውስጥ ከተቱና ወደ ሳጥኑ መለሷት።

"ምናባቱ ልጆቼን ሲርባቸው ከምመለከት..." ሀሳባቸውን ሳይቋጩት ከተቀመጡበት ተነሱ። መሀረባቸውን ከጉያቸው አውጥተው የወርቅ ሀብላቸውን ከነመስቀሉ ጠቀለሉበትና መልሰው ከተቱት። እጉያቸው የከተቱት ወርቅ ቁልቁል እንዳይወርድ መታጠቂያ ጨርቅ ቢጤ ፈለጉና ወገባቸውን ታጠቁ።

ጊዜው ገና ማለዳ ነው። እሰው ቤት ደግሞ እንደመርዶ ነጋሪ በጠዋት መሄድ ከበዳቸው። ቤተክርስቲያን መሳለም ፈለጉና ነጠላቸውን ለብሰው ሊወጡ ሲሉ

"ፍሬ! ጎሽ ነይ በሩን ዝጊው" አሏት።

"እንዴ ወዴት ልትሄጂ ነው?" አለቻቸው ፍሬሕይወት።

"ቤተክርስቲያን ተሳልሜ እመጣለሁ" አሏትና ወጡ።

ለምን ይሆን ሰዓቱ ሁልጊዜ እንዲያጥር ሲፈልጉት የሚረዝመውና እንዲረዝም ሲፈልጉት የሚያጥረው? በቀስታ ርምጃ ወደገብርኤል ቤተክርስቲያን ሄዱ። ገና ከሩቅ ነው ማማተብ የጀመሩት፤ እበሩ ጋ ሲደርሱ ቆም አሉ፤ እንደገና አማተቡ፤ በርከክ ብለው ምድሩን ስመው ተነሱና ወደውስጥ ዘለቁ። እቤተክርስቲያኑ በር ላይ ሲደርሱ እንደገና ተንበረከኩ፤ እንደተንበረከኩ ሳያስቡት እጉያቸው ውስጥ የከተቱት ወርቅ መኖሩን ለማረጋገጥ ዳበሱት።

አእምሮአቸው ጭንቅንቅ አለባቸው፤ "አምላኬ! ኧረ ብርታትን ስጠኝ!" አሉ ግንባራቸውን እመሬቱ ላይ እንዳስደገፉ።



ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ቀላል መስሏቸው የነበረው ነገር አሁን በጣም ከበዳቸው።

"እንዴት አድርጌ ይሆን የምጠይቃት?" አሉ ለራሳቸው። "እባክሽን ይህንን ወርቅ ያዥና ገንዘብ አበድሪኝ ነው የምላት ወይስ ግዥው ብዬ ነው የምነግራት? እባክህን አምላኬ ድፍረት ስጠኝ! ከእርሷ የተሻለ እማን ቤት ልሄድ እችላለሁ? ማንን መጠየቅስ ይቀለኛል? ..." ድንገት ሮቤል ከፊታቸው ድቅን አለባቸው፤ ጥውልግልግ ያለ ገጽታው ታያቸው... "እማ ራበኝ!" የሚል ድምጹ ተሰማቸው። ከተንበረከኩበት ተነሱና "ኧረ መላ ስጠኝ!" አሉ ወደሰማይ አንጋጠው ከገብርኤል ጋር የሚነጋገሩ ይመስል። እበረንዳው ላይ የተደረደሩት አግዳሚዎች ባዶአቸውን ናቸው፤ አንዱ ጥግ ላይ ተቀመጡ፤ በሀሳብ ጥፍት ብለው ለምን ያህል ጊዜ እንደተቀመጡ እንኳ አላወቁትም... ድንገት ብድግ ደግሞ ብለው ከቤተክርስቲያን ወጡ።

የሚፈልጉበት ቤት የደረሱት ሳያስቡት ነው። ከሴትዮዋ ጋር የጠበቀ መግባባት ባይኖራቸውም ዘመድ ናቸው ። ገንዘብ እንደሚኖራት ደግሞ እርግጠኛ ናቸው። በሩ ላይ ሲደርሱ ቆም አሉ፤ ድፍረታቸው ሁሉ ከውስጣቸው ወዴት እንደደረሰ አልገባቸውም። እጆቻቸውን በጠዋቱ አላባቸው፤ የልባቸው ምት ጨመረ፤ እግሮቻቸውም የተንቀጠቀጡ መሰላቸው... ድንገት ከግቢው ውስጥ የሚነጋገሩ ሰዎች ድምጽ ተሰማቸው። እንዴት እንደተራመዱ ሳይታወቃቸው ከበሩ ላይ ተፈናጥረው ሄዱ፤ ወደኋላቸው ዞር ብለው ሳይመለከቱ፤ እንደዚያ ሲያስቡበት ያደሩትን ጉዳይ ለመፈጸም ብርታት አጥተው ወደቤታቸው ተመለሱ።

የሮቤልን ገጽታና ድምጽ ግን ሊሸሹት አልቻሉም፤ መኖራቸውን ጠሉት፤ ወደቤታቸው መግባት ከበዳቸው። ጊዜው ግን እየሄደ ነው፤ የቁርስ ሰዓትም አለፈ፤ ለሮቤል ሊሰጡት የሚችሉት ነገር ግን የላቸውም...

የባለቤታቸውን ጓደኛ ድንገት አሰቧቸው፤ ከጓደኝነትም በላይ ሚዜያቸው ነበሩ። እቤታቸው ሊደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው ሳያስቡት ፊታቸውን አዙረው ወደዚያው አመሩ።

"ገጽታሽ ትክክል አይደለም፤ ደህና አይደለሽም እንዴ?" አሏቸው ሰውየው ገና ሲያዩዋቸው።

"ኧረ ችግር ብሎኛል" አሉ ወይዘሮ ስርጉት በተሰበረ አንደበታቸው።

"እህቴን! እንዴት አይቸግርሽ? እኛም ተሳክቶልን አልጠየቅንሽም" አሉ ሰውየው ሀዘን እየተሰማቸው።

እቤት እንዲገቡና ቡና እንዲጠጡ ቢጋብዟቸውም ወደቤት አልገቡም። የሰውየውን ባለቤት ከርቀት እማድቤታቸው ውስጥ ሲንጎዳጎዱ አይተዋቸው ሰላምታ አቀረቡ።

"ወደቤት አትገቢም እንዴ ምነው እውጭ ቆማችሁ?" አሉ ሴትዮዋ እዚያው እማድቤት እንዳሉ።

"ኧረ እቸኩላለሁ" አሉ ወይዘሮ ስርጉት ባጭሩ።

ሰውየው የሴቶቹን ሰላምታ ልውውጥ እየሰሙ ሁለት ባለአሥር ብር ኖቶች ከኪሳቸው አውጥተው ሰጧቸው። ወይዘሮ ስርጉት እንዴት ብለው እንደሚያመሰግኗቸው እስኪጠፋቸው ድረስ ነው የተደሰቱት።

በአምስት ብር ለልጆቻቸው ቁርስ የሚሆን ዳቦ ስኳርና ሻይቅጠል ገዝተው ወደቤታቸው ተጣደፉ፤ በልባቸው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ።

"እንዴ እማ ምን ሆነሽ ነው?" አለቻቸው ፍሬሕይወት የውጭውን በር ስትከፍትላቸው።



"አረፈድኩ አይደል?" አሏት ለቁርስ የገዙትን እየሰጧት። ባይነግሯትም የቆዩበት ምክንያት ገባትና ዓይኖቿ ያቀረሩት እንባ አቃጠላት። እናቷ ግን ለልጆቻቸው ቁርስ የሚሆን፤ ለምሳቸውም የሚተርፍ ነገር በማግኘታቸው ተደስተዋል።

እቤት ሲገቡ ያዩት ደግሞ አስደነገጣቸው፤ ቡናው ቀርቦ እጣኑም ተጫጭሷል ሮቤልና ሚሚም ቁርሳቸውን እየበሉ ናቸው።

"ከየት አምጥተሽ ነው ፍሬ?" አሏት ከመቀመጣቸው በፊት። ለመልሱ የበላይሁን እናት ያመጡትን ሁሉ አሳየቻቸው።

የበላይሁን እናት ባይነገራቸውም ችግር የሚገባቸው፤ ያላቸውን አካፍለው የማይታክታቸው ለጋስ ጎረቤት ናቸው። የፍሬሕይወት እናት ደግሞ ይህ በጣም ያስጨንቃቸዋል፤ "እስከመቼ ደጉመውኝ እዘልቃለሁ?" ይላሉ እንባቸው እየተናነቃቸው።

የበላይሁን እናት ቡና ለመጠጣት ሲመጡ "ስርጉቴ! እንግዲህ ተዘጋጂና፤ አንዳንድ ነገር መጀመር ይሻላል" አሉዋቸው።

"በምን እንደምጀምረው ግራ ገብቶኝ እንጂ ጠላም ባደርግ እኮ ይሸጣል?" አሉ ወይዘሮ ስርጉት ግራ በተጋባ አነጋገር።

"ይሄውልሽ በዚች መገዛዛትና መጀመር ትችያለሽ" አሉ የበላይሁን እናት በእጃቸው የያዙትን ገንዘብ እየሰጧቸው።

* * * *

ዕለቱ ሰኞ ጥር 12 ቀን 1967 ዓ.ም ነው፤ ሁለተኛው የዘማች ቡድን የሚንቀሳቀስበት ቀን። ፍሬሕይወት በጠዋት ተነስታ ለጉዞ ተዘጋጀች፡፡ እናቷ፣ እህቷና ወንድሞቿ እንደእርሷው በጠዋት ተነስተዋል፡፡ የበላይሁን እናትና ሌሎቹም ጎረቤቶች ተከታትለው መጡ፡፡ እንደሁሉም ምኞት ፍሬሕይወትና በላይሁን አንድ ላይ ሳይመደቡ ቀርተው እርሱ ከመጀመሪያዎቹ ዘማቾች ጋር ከአንድ ሳምንት በፊት ሲሄድ የነበረው መላቀስ ድቅን አለባትና ሆዷ

ተረበሸባት፡፡ የበላይሁን እናት ገና ሲያዩአት ዕንባቸው በዓይናቸው ግጥም ሲል ተመለከተችና ዓይኖቿን አሸሸቻቸው፡፡

ሰዓቱ የራሱን ቀመር ጠብቆ ደረሰ። እናቷ ተርበተበቱ፣ ድንግርግር አላቸውና የሚይይዙትና የሚጨብጡት ሲጠፋባቸው ተመለከተች፡፡

"እማ እንዲህ የምትሆኝ ከሆነ እንደምቀር እወቂ" አለቻቸው የውስጥ ስሜቷን ለመደበቅ እየጣረች ቢሆንም ድምጿ ተርገበገበባት፡፡

"እሺ አሁን ምን ስሆን አየሽኝ? ይልቅ እንውጣ" አሉ እናቷ በሚገርም ጥንካሬ።

አምስት ኪሎ የዘመቻ መምሪያው ግቢ በዘማቾችና በሸኝዎች ተጨናንቋል፡፡ እዚህም እዚያም ሸኝና ተሸኝ እየተቃቀፉ ይላቀሳሉ፡፡ ምድር ቀውጢ ሆናለች። አውቶቡሶቹ በራቸውን ከፍተው ይጠባበቃሉ፡፡ አንዱ ስለሌላው ምንም ደንታ የለውም፤ ሁሉም በየራሱ ጉዳይ ተጠምዶ ወዲያ ወዲህ ይላል፡፡ ብዙዎች ቡድናቸውን ፍለጋ ነው ከወዲያ ወዲህ የሚሉት፤ ቡድናቸውን ያገኙት መለስ ብለው ከወላጆቻቸውና ጓደኞቻቸው ጋር ያወራሉ፡፡

ፍሬሕይወት ቡድኗን አግኝታ ከቤተሰቧ ጋር ጥቂት እንዳወራች አንዳንዶች አውቶቡስ ውስጥ መግባት በመጀመራቸው ተሰነባብታ ወደ ቡድኗ ተመለሰች፡፡ የቡድኗ ዘማቾች አብዛኞዎቹ ተሰናብተው ተመልሰው ገና እንባቸውን እየጠራረጉ ናቸው፡፡ ከፊት ለፊቴ የተመለከተቻቸው ወጣቶች ግን ከሌሎቹ ለየት ያሉ ሆኑባትና ቀልቧን ሳቡት፡፡ በቡድኑ ውስጥ የሚያለቅስ የሚነፈርቅ የለበትም ከሁሉም ገጽታ ላይ ሀዘን ሳይሆን ጥንካሬ ይነበባል፡፡ ንግግራቸው ባይሰማትም በእርሷ ውስጥ ያለ ስሜት እነርሱ ውስጥ ያለመኖሩ ተሰማት፡፡

ጥቂት ፈንጠር ብሎ ያለው ቡድን ደግሞ በመጠኑ ለየት ያለ ስሜት ይንፀባረቅበታል፡፡ ትኩረታቸውን በዚያኛው ቡድን ላይ ያደረጉ ይመስላሉ፡፡ እንደዚያኞቹ ሙሉ ትኩረታቸው



በሚነጋገሩበት ላይ ያረፈ አይመስልም፡፡ ፍሬሕይወትን ግራ ገባትና ጥቂት ተመለከተቻቸው፡፡ ድንገት ዞር ብላ ቤተሰቦቿን ለማየት ሞከረች፤ እንደቆሙ ናቸው። እናቷ በሀሳብ ርቀው የሄዱ ይመስላሉ። ወደ እርሷ የሚያዩ ቢመስሉም እጆቿን ስታወዛውዝላቸው አጸፋውን አልመለሱላትም፡፡ ተመልሳ ለመሄድ ፈልጋ ራመድ ስትልና ድምፅ ማጉያው ሲሰማ እኩል ሆነ ቆመች፡፡ ወደየመኪናዎቻቸው እንዲገቡ ትዕዛዝ ተሰጠ፡፡ እናቷንም ድምፁ ከሄዱበት ድንገት መለሳቸውና ዙሪያቸውን መማተር ጀመሩ።

"ዘማቾች ወደ መኪናዎቻችሁ እንድትገቡ ትጠየቃላችሁ" የሚለው ድምፅ ተደጋገመ፡፡ ቤተሰቧን ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰናበት ፈለገችና በግርግሩ ውስጥ እየተሹለከለከች ሮጠች፡፡ ቤተሰቦቿን ስታያቸው ሳታስበው ዕንባዋ አሸነፋት፡፡ ለስንት ሰዓታት ታግላ የገደበችው የዕንባ ጎርፍ በጉንጮቿ ላይ ፈሰሰ፡፡ ከሁሉም ድምፅ በላይ ከፍ ብሎ የእናቷ ድምፅ ተሰማት።

"ፍሬ! ጠንካራ ልጅ ነሽ ብዬ ነበር የማስበው" አሏት፡፡ እነኝህን ቃላት ለማውጣት የቱን ያህል ትግል ማድረግ እንደነበረባቸው የተገነዘችው ቆይታ ቢሆንም ለዛች ቅፅበት ግን ትልቅ ጉልበት ሆናት፡፡ ዓይኖቿን ጠራርጋ ቀና አለች፤ እጆቿን ከፍ አድርጋ አውለበለቻቸው፡፡ እናቷ "እሰይ የኔ ልጅ" ያሏት መሰላት፡፡

ወደ አውቶቡሱ ስትሄድ አብረዋት የሚዘምቱትን ተማሪዎች አየቻቸው፡፡ የሁሉም ዓይኖች ድብልቅልቅ ብለው ቀልተዋል፤ ገና እንባቸውን መግታት ያልሆነላቸውም አሉ፡፡ መኪናው ውስጥ ገባች፡፡ ቤተሰቦቿን ለማየት ጥረት አደረገች ግን አልተሳካላትም፡፡ መኪናው ተንቀሳቀሰ፤ ገና ያልገቡት ዘማቾች መኪናው ውስጥ ለመግባት ተተራመሱ፡፡

መኪናው ሞተሩን አሙቆ ተነሳ። በአውቶቡሱ መስኮቶች አንገታቸውን አውጥተው የመጨረሻ ስንብት ለማድረግ ተረባረቡ ዘማቾቹ፡፡ ድንገት ቤተሰቦቿን ዓየቻቸውና ጮኸች ፍሬሕይወት፤ ቢሰማም ባይሰማም። ጩኸቷ ግን ከፍተኛ ነበር፡፡

"አይዞሽ እማ!" አለች የምትችለውን ያህል በመጮህ፤ ከዚያ ሁሉ ሰው ጩኸት መሀል የራሷ ድምፅ በጆሮዋ አንቃጨለ... መኪናውም ግቢውን ለቆ ወጣ፡፡ እንባዋ ገንፍሎ ጉንጮቿን አጠባቸው፤ ዓይኖቿም በእንባዋ ጭጋግ ተሸፈኑ፡፡ ከፊቷ ባለው መቀመጫ መደገፊያ ላይ ግንባሯን አሳርፋ እንባዋን ያለገደብ ለቀቀችው፡፡ አውቶቡሱ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ፡፡ አልፎ አልፎ ግን ዝቅተኛ ስቅስቅታ ይሰማል፡፡

ኤልሳ ትከሻዋን መታ መታ አደረገችኝ ቀና ፍሬሕይወትን ቀና እንድትል አደረገቻት፡፡ የደፈረሱ ዓይኖቻቸው ለመጀመሪያ ጊዜ እንድትል አደረገቻት፡፡ የደፈረሱ ዓይኖቻቸው ለመጀመሪያ ጊዜ

"የሚበቃን አይመስልሽም?" አለች ኤልሳ ጭፍግግ ባለ ገፅታዋ ላይ ፈገግታ ልትዘራበት እየሞከረች፡፡

"እውነትሽን ነው ኤልሳ ይበቃናል" አለች ፍሬሕይወት የዘረጋችላትን ዳቦ ቆሎ እየዘገነች፡፡

ወጣት መሆን እንዴት ጥሩ ነው፡፡ ሁኔታውን ለመለወጥ ብዙ ደቂቃዎች አላስፈለጉም፡፡ መኪናው የግብዣ አዳራሽ መሰለ፤ ቆሎ፤ ዳቦቆሎ፤ዳቦ ፤ኩኪስ... ከፊት ወደኋላ፤ ከኋላ ወደፊት እየተመላለሱ መበላት ጀመሩ፡፡ ሳቅና ጨዋታው ተሟሟቀ... ጭፈራውም ቀጠለ፡፡

የመጀመሪያው አውቶቡስ ሲቆም ሁሉም ተከታትለው ይቆማሉ፡፡ ሁሉም ይወርዳሉ ጥቂት እረፍት ይደረጋል ሌላ አውቶቡስ ላይ ያሉትን ጓደኞቻቸውን ለማግኘት ወዲያ ወዲህ ይተረማመሳሉ፡፡ እንዲህ እየተባለ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ሲሆን ዝዋይ ለመድረስ ጥቂት ሲቀር የምሳ እረፍት ሆነ፡፡ በአካባቢው ያለው ግራር ብቻ ነው፡፡ ያገኙትን ነገር ነጠፍ እያደረጉ በግራሮቹ ስር አረፍ አሉ፡፡

ምሳው ዳቦና የታሸገ የቆርቆሮ ምግብ ነው፡፡ የቆርቆሮውን ምግብ ዘማቾቹ አልወደዱትም፤ ማጉረምረም በረከተ፤ አዝማቾቹ መደናገጥ ታየባቸው፡፡ ዘማቾቹ ግን ከቤታቸው ያመጧቸውን



ደረቅ ምግቦች እያወጡ በሉና የኮዳዎቻቸውን ውሀ እየተጎነጩ ወደመኪናዎቻቸው ገብተው ተቀመጡ፤ እንደገና ጉዞ ሆነ፡፡ የከሰዓት በኋላው ሙቀት ጠንከር ያለ ቢሆንም ብዙም አልተቸገሩም፤ በየመንገዱ ባሉ ጣቢያዎች የሚቀሩት ዘማቾች እየቀሩ ሌሎቹ ጉዞ ይቀጥላሉ፡፡

ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን እነፍሬሕይወት ጣቢያቸው ደረሱና ሌሎቹን ተሰናብተው ሄዱ፡፡ ጣቢያቸው ምዕራብ ዓባያ ትባላለች፤ ለአርባ ምንጭ አርባ አምስት ኪሎ ሜትር ሲቀር የምትገኝ በሙቀቷ የምትታወቅ ከተማ ነች፡፡ የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ ተቀበላቸው፡፡ ፍራሾቻቸው ከአውቶቡሶቹ ላይ እየወረዱ ለጊዜው እንዲያርፉበት በተሰጣቸው ትምህርት ቤት ክፍሎች ውስጥ ተደረደሩ፤ ሻንጣዎቻቸው በየፍራሹ አጠገብ ተቀመጡ፡፡ ክፍሎቹ አቧራ ብቻ ናቸው፤ ግራ መጋባት ሆነ፡፡ ከዚያ ረጅም ጉዞ በኋላ ሰውነታቸውን ለቅለቅ ቢሉ በጣም ያስፈልግ ነበር ግን ውሀ የለም፡፡ የምዕራብ ዓባያ ትልቁ ችግር ውሀ መሆኑን እያስተዛዘኑ ነገሯቸው፡፡

ለሴቶቹ አንድ ክፍል ተለቀቀ፡፡ አቧራውን እያረጋገፉ ፍራሾቻቸው ላይ ቁጭ አሉ የክፍሉ አየር በጣም አስጨናቂ ስለሆነ በሩን መዝጋትና መተኛት የማይታሰብ ሆነ፡፡ በሩ ለአፍታ ያህል መለስ ቢደረግ የሚሞቱ መሰላቸው፡፡

"ወይኔ እማምዬ እንዴት ነው የሚነጋው" አለችና አንደኛዋ ስቅስቅ አለች፡፡ ብዙዎቹ ተከተሏት፡፡ ጥቂት ቆየት ብሎ አንድ ሌላ ክፍል ተፈልጎ ከፊሎቹ ወደዛ እንዲሄዱ ተደረገና በመጠኑ ቀለል ያለ ሁኔታ ተፈጥሮ ማደር ተቻለ፡፡

በማግስቱ ከህዝቡ ጋር ትውውቅ ተደረገ፡፡ ከተማዋንም ተዘዋውረው ተመለከቷት። ትንሽ መንደር ታህላለች፡፡ ሙቀቱ "አይጣል!" የሚያሰኝ ነው፡፡ "ምዕራብ ዓባያ'ኮ ወታደሮች ለቅጣት የሚላኩበት ቦታ ነው" የሚል ወሬ በሰፊት ተዛመተ፡፡ የአካባቢውን ሕዝብ ከሚያጠቁት በሽታዎች የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው ወባ መሆኑን በመስማታቸው የወባ ኪኒን ለመውሰድ ያቅማማ ዘማች ሁሉ ኪኒኑን ከጤና መኮንኑ እየጠየቀ መውሰድ ቀጠለ፡፡

የዘመቻ ጣቢያው ከዋናው መንገድ በሀምሳ ሜትር ብቻ ነው የሚርቀው፡፡ በዚያ መንገድ አውቶቡሶቹ ሲያልፉ ተሳፋሪው እጁን ሳያውለበልብ በጭራሽ አያልፍም፡፡

* * * *

እነሆ ዘማቾቹ ምዕራብ አባያ ከገቡ አንድ ሳምንት ሆነ፤ ብዙዎቹ ገና ምን እንደሚሠሩም አልገባቸውም። እዚያ የሚያቃጥል ክፍል ውስጥ መቀመጥ የሰለቸው ድንጋይ ቢጤ እየፈለገ በየ ግራሩ ስር ተቀምጧል፣ ከፊሉ ወደከተማ ወጥቷል፣ ሌላው ደግሞ እዚያው ክፍል ውስጥ ፍራሹ ላይ ጋደም ብሏል።

ከአዲስ አበባ ወደ አርባምንጭ የሚያልፍ አውቶቡስ ጡሩምባውን በረጅሙ አሰማና ቆመ። በግራሮቹ ጥላ ስር ከተቀመጡት ዘማቾች አንዱ ተነስቶ ወደ አውቶቡሱ ሲሄድ የአውቶቡሱ ረዳት ለመያዝ ያቃተውን የልብስ ማጠቢያ ሳፋ የሚያህል አገልግል ተጋግዘው አወረዱ፤ ሾፌሩ ደግሞ አንድ ፖስታ አቀበሉት ለዘማቹ።

አገልግሉን በመተጋገዝ አምጥተው ማደሪያ ቤቶች መሀል አስቀመጡት፡፡ ዘማች ሁሉ ከያለበት እየመጣ እርስ በእርስ መተያየት ሆነ፡፡ በሁሉም አእምሮ ውስጥ "የዘመቻው ሕግ መጣስ ተጀመረ" የሚል ሃሳብ የሚመላለስ ይመስላል፡፡ መፋጠጥ ሆነ፡፡

የአገልግሉ ባለቤት ሁኔታው አስፈርቷት በፀጥታ ስትመለከት ከቆየች በኋላ ያለ የሌለ ኃይሏን አሰባስባ "ልታግዙኝ አትችሉም?" አለች ጥቂት ወደ አገልግሉ ተራምዳ፡፡

"ወዴት?" አለ አንዱ ዘማች ከወደጥግ በኩል፡፡

"ወደቤታችን ነዋ?" አለች አሁንም አንድ ርምጃ ተራምዳ።

"አይቻልም" የሚል ድምጽ ከወደ መሀል በኩል ተሰማ ሌሎችም በርካታ ድምፆች ተከተሉ፡፡ ልጅቱ በድንጋጤ ወደቦታዋ ተመለሰች፡፡ እንደገና መፋጠጥ ሆነ፡፡ ሰዓታት አለፉ። በሥፍራው



ከነበሩት ዘማቾች መሀል ማንም አልተንቀሳቀሰም፡፡ ምግቡ የተላከላት ዘማችና ጓደኞቿ ግን ወደ ማደሪያ ክፍላቸው ገቡ፡፡ ወደአስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ወደ ከተማ ሄደው የነበሩ ዘማቾች ሁሉ ተመለሱ፡፡

"የምን ስብሰባ ነው?" አለ ወፈር ያለ አስደሳች ድምፅ ያለው አንተነህ። አንተነህ በአጭር ጊዜ ከሁሉም ዘማቾች ጋር መግባባት የቻለ ዘማች ነው።

"ዛሬ አዋጅ ይወጣል" አለ "አይቻልም" ካሉት አንደኛው፡፡ ጉዳዩ እንደአጀማመሩ በቀልድ ማለቅ ግን አልቻለም፡፡ ልጆቹ አመረሩ፤ ፍትፍቱ የተላከላት ልጅና ጓደኞቿም ከክፍላቸው እንዲወጡ ሆነ፡፡

"ስሚ ምንም እንኳ የመደብ ትግል በመሀላችን ልናካሂድ ባንመጣም የመደብ ልዩነቱን የሚያንጸባርቅ ማንኛውንም ነገር እንቃወማለን" አለ አንድ ከአዲስ አበባ ልዑል መኮንን ት/ቤት የመጣ ዘማች፡፡

"ትክክል ነው፡፡ የመጣነው ለገበሬው ቅንጦታችንን ልናስተምረው ሳይሆን ኑሮውን ኖረን ልንደግፈው ይመስለኛል" ሌላው ቀጠለ።

ቃላት ከወዲያና ከወዲህ በተሰነዘረ መጠን ውዝግቡ እየተካረረ ሄደ፡፡ በመጨረሻ በሰለጠነ ሁኔታ በአግባቡና ስርዓት ባለው መልክ ተወያይቶ ጉዳዩን ማቃለል እንደሚያስፈልግ ተወሰነ፡፡ ስብሰባውን የሚመራ ሊቀመንበርና ቃለጉባኤ የሚይዝ ፀሐፊ ተመረጡ፡፡

ስብሰባው ተጀመረ ሀሳቦች ተዥጎደጎዱ፡፡ አንዱ እጁን አውጥቶ "ሀሳብ" ይላል፣ ሌላው ቀጠል ያደርግና "ስፒሲመንት" በማለት ይጨምራል፣ "ጥያቄ" የሚለው ደግሞ ይነሳል፡፡ ይሄኛው ሲጨርስ ሌላ ይነሳና "አብጀክሽን" ይቀጥላል..."ሞሽን ሙቭ ይደረግ"..."ሞሽኑን ሰከንድ የምታደርጉ"...ወዘተ እየተባለ ጊዜው ከነፈ፡፡ ለነፍሬሕይወት እየተደረገ ያለው ነገር ብዙም አልገባቸውም። የእራት ሰዓትም አለፈና ምሽቱ መግፋት ጀመረ፡፡

ግራ የተጋባ ሁኔታ ተፈጠረ፤ ማንም ገብቶ መተኛት እንደማይችል ተነገረ፡፡

ለወረዳ ጣቢያው በአዛዥነት የተመደቡት አንድ ሀምሳ አለቃና አንድ መምህር ሁኔታውን ከመከታተል በስተቀር ሊያደርጉ የሚችሉት አልነበራቸውም፡፡ ውይይቱ ለረጅም ሰዓታት ቀጠለና በመጨረሻ ቅንጠትንና ዘማቹን የሚከፋፍል ማንኛውንም ድርጊት የሚያወግዙ ውሳኔዎች ተላልፈው ስብሰባው ተደመደመ፡፡ አገልግሉም ለባለንብረቷ ተፈቀደላት፡፡ አብዛኛው ዘማች ክፍትፍቱ ለመብላት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረና ወደ እራት ሄደ፡፡ ጥቂት ከአዲስ አበባ የዘመቱ ተማሪዎች ብቻ ነበሩ የመጣውን ፍትፍት ለመብላት ወደኋላ የቀሩት በዚህም የተነሳ ተቃውሞውን ካስነሱት ዘማቾች ጋር መቃቃር ተፈጠረ፡፡ ፍሬሕይወት ፍትፍቱን ለመብላት ካልፈቀዱት ጋር ሆነች፡፡

ምንም እንኳ አጋጣሚው በስብሰባ ቢፈታም ያ ዕለት በዘማቹ መሀል የሆነ የሀሳብ መስመር ሳያሰምር አላለፈም፡፡

የዘማቾቹ መኖሪያ በአግባቡ ተሰርቶ ባያልቅም ሰሞኑን በችኮላ ተጠናቆ ት/ቤቱን ለተማሪዎች መልቀቅ ነበረበት፡፡ የተጀመረው ግንባታ ወለሉ በኮንክሪት ተሠርቶ አለፍ አለፍ ብለው በቆሙት አጠናዎች ላይ ሳጠራ ተሸፈነባቸውና ቤት ሆነ፡፡ በርና መስኮቶች ከቆርቆሮ ተሠርተው ተገጠሙ፡፡

ወደአዲሱ ቤት ለመዘዋወር ዝግጅት ተደረገና ዕቃዎቻቸውን አስረው ማጓጓዝ ጀመሩ፡፡ በግልጽና በቃላት አይነገር እንጂ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በአገልግሉ ጉዳይ በተደረገው ስብሰባ ወቅት የተፈጠረውን የሀሳብ መስመር የተከተለ ነው፡፡ በአዲሱ ቤት ቦታ ሲያዝ እንደመጀመሪያው ዕለት እንደተገኘ ሳይሆን እየተመራረጡ ሆነ፡፡ የቡድን ስሜት ነገሰ፤ በጥቃቅኑ ጉዳይ ላይ ሁሉ ግጭቶች ተስተዋሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንደቀልድ የተጀመሩ ነገሮች ይካረሩና ፈር ይስታሉ፡፡ ግጭቶቹ አንዳንዴ መደባዊ ይዘት ያላቸው ይመስላሉ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ አካባቢያዊ ይሆኑና በአዲስ አበባ ልጆችና በአካባቢው ልጆች መሀል የተከሰቱ ልዩነቶች ይሆናሉ፡፡



አንዳንድ ዘማቾች ሁኔታውን ለማርገብ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋሉና፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ እነርሱ ራሳቸው የግጭቱ ዋና ተዋናይ ሆነው ይገኛሉ፡፡

ያም ሆነ ይህ የዘመቻው ሥራ መጀመር ነበረበት፡፡ ታዲያ ሥራውን በአግባቡ ለመሥራት በዘማቾቹ መሀል ያለው ግጭት መወገድ እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡ የተወሰኑ ዘማቾች ሁኔታውን ለማስተካከል በፈቃደኝነት መንቀሳቀስ ጀመሩ።

አንድ ማታ ስብሰባ ተጠራና ሁሉም ዘማች ከእራት በኋላ በምግብ ቤት ውስጥ እንዲታደም ሆነ፡፡ የስብሰባው አጀንዳ "በመሀላችን የተፈጠረውን ችግር እንዴት መፍታት እንችላለን?" የሚል ነበር፡፡

እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ስብሰባው ቀጠለ፡፡ አንዳንዴ ወደባሰ መካረር ሲሄድ፤ እንደገና ሲለዝብ...ደግሞ እንደገና አንዱ በሚሰነዝረው አስተያየት ነገሩ ጥሬ ሆኖ ወደ ፀብ ሲመለስ...በመጨረሻ ከስምምነት ላይ ተደረሰና ሂስና ግለሂስ የዘማቹ ባህል እንዲሆን ተወስኖ ስብሰባው በደስታ ተጠናቀቀ፡፡

የዘመቻው ሥራ ተጀመረ፡፡ በቡድን ተከፋፈሉ በተለያየ አቅጣጫ ተሰማርተው መዋል የየዕለት ተግባራቸው ሆነ፡፡ ገበሬ ማህበራት ማደራጀት፣ መሠረተ ትምህርት ማስተማር፣ የገበያ ቦታና መንገዶችን መሥራት... የዘማቹ ኃይል ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ዋለ፡፡ በየዕለቱ ማታ ከእራት በኋላ ለአጠቃላይ ጉባኤ የየቡድኑን ሥራ ሪፖርት ማቅረብ፣ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ መወያየትና ለተጣዩ ቀን ሥራ መዘጋጀት የየዕለቱ ተግባራት ሆኑ፡፡ ዘመቻ ጣቢያው ሕይወት ዘራ። እንደሥራ ምን መልካም ነገር አለ?

በአጋጣሚ ፍሬሕይወት እና አንተነህ የአንድ ቡድን አባላት ሆኑ፡፡ አንተነህ ለንግግር የተፈጠረ ይመስላል፡፡ ሲናገር ልዩ የሆነ የስበት ኃይል አለው፡፡ ድምጹ ወፍራምና ልዝብ፣ ንግግሩ ረጋ ያለ ቢሆንም እንደንግግሩ ይዘት ድምጹን ከፍና ዝቅ ሲያደርገው

የአድማጩን ስሜት ይገዛል፡፡ ስሜትን ይኮረኩርና በውስጥ ያለውን ሁሉ ለመናገር ያነሳሳል፡፡

ፍሬሕይወት ከሥራ በኋላ ለሚደረጉት ስብሰባዎች ልዩ ፍቅር እያደረባት መጣ፡፡ ከእነዚያ ስብሰባዎች ብዙ የማታውቃቸውን ነገሮች ተምራለች፡፡ ስለ መሬት ላራሹ፣ ስለተማሪዎች ንቅናቄ፣ ስለሕዝባዊ መንግሥት፣ ስለ ሩሲያና ቻይና አብዮቶች፣... በነዚያ ስብሰባዎች ምን የማይነሳ ነገር አለ፡፡ፍሬሕይወትን ግርም ይላታል ።

በጣም ይገርማት የነበረው ደግሞ አንተነህ ለገበሬዎቹ ስለ እነዚህ ሁሉ በሚገባቸው ቋንቋ መግለጽ መቻሉና አንዳንድ ገበሬዎች የሚሰጧቸው አስተያየቶች ብስለት ነው፡፡

አንተነህ ስለጭቆና ሲናገር ተመስጠው በጣም ይደንቃል፡፡ ስለመደብ አፈጣጠር፣ ማህበረሰብ በመደብ ከተከፋፈለ በኋላ ስላለው የገዥና ተገዥ፣ የጨቋኝና ተጨቋኝ ግንኙነት ሲያስረዳ እርሱ ራሱ በዚያ ሕይወት ውስጥ ያለፈ ነው የሚመስለው፡፡ ስለ ባላባታዊው ስርዓት፣ የፖለቲካ ፣የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ ሲተነትን ብዙዎቹ ገበሬዎች በተመስጦ እስከማልቀስም ይደርሳሉ፡፡ "መሬት ላራሹ!" በማለት የኢትዮጲያ ተማሪዎች ለስንት ዓመታት እንደታገሉ ሲገልጽ የደም ስሮቹ ሁሉ በስሜት ይወጠራሉ፡፡

በንግግሮቹ ሁሉ መሀል ደርግ የሕዝቡን ትግል እንዳኮላሸ ሳይገልጽና ለሕዝባዊ መንግሥት መታገል እንደሚያስፈልግ ጣል ሳያደርግ አያልፍም፡፡ ገበሬዎቹ አንተነህን በጣም ይወዱታል፤ ፍሬሕይወትም ብትሆን እያደር ለእርሱ ያላት አድናቆት እየጨመረ ሄዷል፡፡ እንዲያውም ዘመቻውን እንድትወደው ያደረጋት ከእርሱ ጋር አንድ ቡድን መመደቧ ይመስላታል፡፡

አንተነህ ከቁምነገረኛነቱና ከፖለቲካ ውይይቶች ውጭ በጣም ተጫዋችና ቀልድ አዋቂ፤ ሩህሩህና ተንከባካቢም ነው፡፡ አብረውት ለሥራ ለተመደቡት ሁሉ የሚያደርገው እንክብካቤ በቡድን



መሪነቱ ያለበትን ኃላፊነት ከመወጣት አኳያ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮአዊም ነው፡፡

ለሴቶች ልዩ አክብሮት አለው፡፡ "አረፍ በሉ ይደክማችኋል፣ ውሀ ጠጡ ይጠማችኋል..." ከማለት ባሻገር ዘማች ሴቶች ከሴት አርሶ አደሮች ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ግንኙነትና ሊሰጡ የሚገባቸውን ትምህርት ከመግለፅ ወደኋላ ብሎ አያውቅም፡፡ እንዲያነቡ ማበረታታት፣ የሚነበቡ መጻሕፍትን መስጠት፣ በስብሰባ ላይ ያላቸው ተሳትፎ እንዲጎለብት ዕድሉን ማመቻቸት የዘወትር ተግባሩ ነው፡፡

ፍሬሕይወት ሳታስበው በፖለቲካ መሳብ ጀመረች፡፡ አንተነህ የሚያመጣቸውን መጻሕፍት በማንበብ ሌሊቱን ማገባደድ ለመደባት፡፡ ትናንሽቹን የማኦ ሴቱንግ መጻሕፍት በጣም ወደደቻቸው፡፡ አንተነህ ለእያንዳንዱ የሥራ እንቅስቃሴ ማጣቀሻ መጽሐፍ አለው፡፡ የአንተነህን ፈለግ ተከተልችና ፖለቲካ መጻሕፍት አንባቢነቷ በጣም ጨመረ፤ ፖለቲካም እያደር ስሜት እየሰጣት ሄደ፡፡ የምታነባቸውን መጻሕፍት የመያዝ ፍጥነቷና የተረዳችውን የመግለፅ ችሎታዋ ደግሞ አንተነህን ሲያስደስተው ተመለከተች፡፡ ከአንተነህ ጋር በጣም ተቀራረቡ:: አንዳንዴ እንደ ታላቅ ወንድም ታየዋለች:: ሲንከባከባት፣ ሲያስብላት፤ በልጅነቷ ሲያዝንላት ተፈጥሮው ይደንቃታል፡፡

አንድ ቀን አንተነህ የሚመራው ቡድን ራቅ ወዳለ ሥፍራ ለሥራ ወጣ፤ ውሎአቸው አድካሚ ነበር፡፡ ሲመለሱ የቡድኑ አባላት ሦስትም ሁለትም እየሆኑ ሄዱ፡፡ ፍሬሕይወት በጣም ስለደከማት ከሌሎቹ እኩል መራመድ አልሆንልሽ አላት፡፡ ብዙዎቹ የቡድን አባላት በጨዋታ ተመስጠው ድካሟን አላስተዋሉላትም፡፡ ቀስ በቀስ ወደኋላ ቀረች፤ አንተነህ ብቻ ነበር መድከሟን ያስተዋለው፤ እናም እንድታርፍ ጠየቃት፡፡ ጥላው ስር ካለው መስክ ላይ ተቀመጠች ውሀ እንድትጠጣ ኮዳውን ሰጣት፡፡ የኮዳው ውሀ ግን ለብ ያለ ነው፡፡ በውሀው አፏን ተጉመጥምጣ መለሰችለት፡፡

"እንሂድ አይደል?" አለችው ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ።

"ለምን ትንሽ አታርፊም?" አላት ሳሩ ላይ ጋደም እያለ፤ አልመለሰችለትም።

"ይበቃኛል እንሂድ" አለችው ተነስታ መንገድ እየጀመረች። እንተነህም ተከተላት፤ ከፊት ሆና ጥቂት እንደተራመዱ የረገጠችው ድንጋይ ተፈንቅሎ ጣላት። አንተነህ በሚገርም ፍጥነት አነሳት። ወዲያውኑ ደግሞ በሳቅ ፍርስ አለ።

"አሁን መውደቅ ይህን ያህል ያስቃል?" አለችው በሳቁ እየተናደደች።

"ይቅርታ አናደድኩሽ? ለምን እንደሆነ ሳላውቀው ሰው ሲወድቅ በጣም ያስቀኛል" አላት እየሳቀ አንገቷን አቀፍ አድርጎ። አንገቷን ሲያቅፋት የሆነ ነገር ውርር አደረጋት፤ ደነገጠች። በአቧራ የተበላሸውን ሱሪዋን አራገፈላት፤ የተጋጋጠ እጇን አሻሸላት።

"ተጎዳሽ?" አላት ደግሞ ትከሻዋን ያዝ አድርጎ።

"እ...አይ አልጎዳኝም" አለች። ምላሷ ተያያዘ። ምን እንደነካት ግራ ገባት። እጁ ትከሻዋ ላይ ሲያርፍ የተሰማት ስሜት አስደነገጣት። እንዳያውቅባት ጥረት አደረገች።

በደካማነቷ እያሾፈባት፣ በአወዳደቋ ሲቀልድባት ትከሻዋን እንዳቀፋት ነበር ዘመቻ ጣቢያ የደረሱት። ብቻቸውን ወደኋላ የመቅረታቸው አጋጣሚ በሌሎች አመለካከት ጥርጣሬ መፍጠሩን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደባትም ነበርና በራሷ ተናደደች። ማታ እንደወትሮው እንቅልፍ አልወሰዳትም፤ ብቻ አንተነህን በየደቂቃው ታስበዋለች። ባሰበችው ቁጥር ደግሞ ትደነግጣለች፤ ትከሻዋ ላይ የነበረው ክንዱ እየተሰማት ተቸገረች።

ሁኔታዋ አላማራትም። ድንገት ለምለም ድቅን አለችባት። ለምለም በዕድሜ ጥቂት ብትበልጣትም አብሮ አደጎች ነበሩ። ሚኒስትሪ አልፌው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንደጀመሩ ነበር ለምለም ጭንቀቷን የነገረቻት።



"ፍርዬ እኔ ይህንን ሰውዬ ሳልወደው አልቀረሁም" አለቻት ለምለም በጭንቀት።

"የቱን ሰውዬ ለምለም?" አለች ፍሬሕይወት ጥርጣሬዋን እያሰበች።

"የአማርኛ አስተማሪያችንን"

"ሊሆን አይችልም! በፍፁም መሆንም የለበትም" አለቻት በቁጣ። ለምለም ላይ በተመለከተቻቸው ሁኔታዎች ጥርጣሬ ቢያድርባትም ነገሩን ለማንሳት ድፍረት አጥታ ነበር ዝም ብላ የቆየችው፤ እናም ዕውነቱን ስታውቅ ዝም ብላ ማለፍ አልቻለችምና ፍሬሕይወት ተቆጣች።

"ሆኗል ፍርዬ ምንም ማድረግ አልቻልኩም" አለችና ማልቀስ ጀመረች ለምለም። ፍሬሕይወት ግራ ተጋባች።

ለምለምና ፍሬሕይወት የሚደባበቁት ነገር አልነበራቸውም። ጓደኝነታቸው በአካባቢያቸው እንደምሳሌ የሚጠቀስ ነበር። በትምህርታቸውም ብርቱዎች ስለነበሩ "ምነው ሁሉም ልጅ እንደነርሱ በሆነ" የሚባልላቸው ነበሩ።

"መተው ትችያለሽ ለምለም! ዕድሜያችን ገና ነው ዛሬ ለፍቅር ቦታ ልንሰጥ የሚገባን አይመስለኝም። ለእርሱ የሚሆን ጊዜ ወደፊት ይኖረናል፤ ለትምህርታችን ግን ያለን ጊዜ አሁን ነው አንዴ ካለፈና ከተጨናገፈ ተመልሶ ላይገኝም ይችላል። ደግሞስ እማማን አታስቢም! አንቺን እኮ ነው በጉጉት የሚጠብቁት" ነበር ያለቻት።

"ያልሽኝን ሁሉ አላጣሁትም ፍርዬ! የወደድኩትም ፈልጌ አይደለም። ምን ብዬ ልንገርሽ? እንዴትስ ስሜቴ ሊሰማሽ ይችላል?..." አለች ለምለም ጭንቀትዋን ስታካፍላት ፍሬሕይወት አልረዳ ስላለቻት።

የአማርኛ ክፍለጊዜ ሲደርስ ለምለም ለየት ያለ ሁኔታ ይታይባታል፡፡ ትቁነጠነጣለች ፈገግ፣ ኮስተር ያደርጋታል፡፡ የአማርኛ አስተማሪያቸው ደልደል ያለ ወንዳወንድ ቁመና ቢኖረውም እዚህ ጋር ተብሎ የሚጠቀስ መልክ የለውም፡፡ ለለምለም ግን እንደእርሱ መልከመልካም ተፈጥሮ የሚያውቅ አይመስላትም፡፡ ሁኔታዋ በጣም ይገርማታል ፍሬሕይወት፡፡

የክፍል ተማሪዎች በሙሉ የለምለምን ሁኔታ አውቀው ሹክሹክታና መጠቃቀስ ሲበዛ ፍሬሕይወት በጣም ነበር የተናደችው፡፡ እናም "ለምለም ይህን ነገር መተው አለብሽ፡፡ እስኪ ተመልከች፤ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ልጆቹ ሁሉ ትምህርቱን ሳይሆን የሚከታተሉት አንቺን ነው፡፡..." ለምለም አላስጨረሰቻትም፤

"የራሳቸው ጉዳይ! አስፈላጊ ከሆነ ፊታቸው ቆሜ እንደምወደው ልነግራቸው እችላለሁ፡፡ እኔን የጨነቀኝ እንዴት አድርጌ መውደዴን ልነግረው እንደምችል ነው፡፡" አለችና እቅጩን አሳወቀቻት፡፡ አጋጣሚው ለለምለም አልሰመረላትም። የአማርኛ መምህራቸው ቀልብ ያረፈው ሌላ ተማሪ ላይ ሆነ፡፡

ቀስ በቀስ ለምለምና ትምህርት ተራራቁ፡፡ የማይጨበጥ ፍቅር እሹሩሩ ስትል ትምህርት አመለጠ፡፡ ዘጠነኛ ክፍል ወደቀች፤ ዳግመኛም ትምህርት የደረሰበት ላትደርስ የማለች ይመስል ትምህርቱን እርግፍ አድርጋ ተወችውና ቤት መዋል ጀመረች፡፡

ፍሬሕይወት ሳታስበው ልቧን ጨነቃት። ከተኛችበት ተነስታ ተቀመጠች፡፡ በፍራሾቻቸው ላይ ተኝተው በእንቅልፍ ዓለም ውስጥ ያሉትን ጓደኞቿን ስታያቸው ቀናች፡፡ "በፍጹም! በለምለም ላይ ያየሁት አጋጣሚ በእኔ ላይ እንዲደገም አልፈቅድም" አለች ለራሷ፡፡ እንቅልፍ እንዲወስዳት ለመሞከር ተመልሳ ተኛች፤ ግን እንቅልፍ ሊመጣ አልቻለም፡፡ ይልቁንም ሂዋንን በዓይነህሊናዋ አየቻት፡፡

ሂዋን በጣም ዘናጭ ልጅ ነች፤ የጠይም ቆንጆ! ዘለግ ያለና ለስራ የሚመች ቁመና አላት፡፡ ተጫዋች ነች፤ የማይወዳትና "ሂዊ"



የማይላት ዘማች የለም፡፡ መዝፈን መጨፈርና መዝናናት ትወዳለች፡፡ አትጨነቅ፣ አታዝን፣ ልክ እንደ ታላቅ እህት ሌላው ሲከፋው የምታፅናና እርሷ ነች፡፡ ፍሬሕይወትም ብትሆን በጣም ትወዳታለች፤ ከገፅታዋ ላይ ጠፍቶ የማያውቀው ፈገግታዋ በጣም ያስደስታታል፡፡ ሂዋን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዓመት ተማሪ ነች፡፡ አብዛኛውን የእረፍት ቀናት ሂዋንና አንተነህ ከምግብ ቤቱ በስተጀርባ ብቻቸውን ተቀምጠው አንገቷን ትከሻው ላይ ደገፍ አድርጋ፤ አንዳንዴም ጭኑ ላይ ጋደም ብላ ሲጫወቱ አገጥሚታል፡፡ "ታድላ" ትላለች ደግሞ ሳታስበው፡፡

ያን ማታ የቱን ያህል ከራሷ ጋር እንደታገለች ስታስበው ይገርማታል፡፡ በመጨረሻ ሀሳቧን ወደሌላ ለመውሰድ ቻለች፡፡ እናቷን አሰበች፤ እነርሱን ለማሳደግ ውሎዋቸውን ከጠላ አተላ ጋር ያደረጉት እናቷ ድቅን አሉባት። ታናናሽ ወንድሞቿና እህቷ፣ ትምህርቷ...ወደፊት የሚጠብቃትን ኃላፊነት አሰበችውና ራሷን ታዘበች። ስንት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ እያለ ለፍቅር በመጨነቋ ተበሳጨች፡፡

ሁሉን ያስከተለባት ይሄ ዘመቻ አልቆላት ተገላግላ፤ ወደ ቤቷ ተመልሳ፤ ከምትወደው ትምህርት ጋር ተገናኝታ... በቃ ከዛ በኋላ ያሰበችው ሁሉ ተሳክቶ፤ እናቷን እፎይ ካሰኘቻቸው በኋላ... ያን ጊዜ ስለፍቅር ለማሰብ ትችላለች። አሁን ግን አያስፈልጋትም!

"ከአንተነህ ጋር አንድ ቡድን ውስጥ ባንመደብ ምን ነበረበት?" አለች ደግሞ ወዲያውኑ በሀሳቧ።

* * * *

ዘመቻው ገና ስድስት ወራት ሳያስቆጥር የገበሬ ማህበራት ተጠናክረው መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴው እየተጠናከረ፣ የመደብ ትግሉም እየተካረረ ሄደ። አርሶ አደሩ "የመሬት ላራሹን" አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግና መብቱን ለማስከበር አልፎ አልፎ ባለመሬት ከነበሩ ባላባቶች ጋር የሚያደርገው ግጭት ግን እያሳሰበ መጣ፡፡

አንዳንዶቹ የገበሬ ማህበራት በጣም ጠንካሮች ሆኑ። መሪዎቻቸው ፖለቲካውንና ኢኮኖሚውን እኩል ማስኬድ በሚገባ ተሳክቶላቸዋል። በመሆኑም "በየአደባባዩ ወሬውን ሲያቀልጥ መሬቱ ጾሙን ያድር የለ፣ ከዛ አዳሜ ያገኛታል!" እያሉ ስለ ገበሬው አወዳደቅ የሚያወሩትን ባላባቶች አሳፍሯል። አንዳንዶቹ ባላባቶች በዚህ በጣም ይናደዳሉ፣ ገበሬዎቹ የተሻለ ኑሮ ከኖሩ የቀድሞውን ሥርዓት የበለጠ እንደሚጠሉ፣ እግዚአብሔርም የማስተዳደርን ሥራ ለንጉሳዊው አገዛዝ አንጡራ ሀብትነት እንዳልሰጠ ማረጋገጫ እንደሚሆን በማሰብ ለማደናቀፍ የተቻላቸውን ያህል ይጥራሉ።

ገበሬዎቹ በበኩላቸው "ለመብታችን መታገል ይኖርብናል፡፡ መንግስት ባያግዘንም የባላባቶቹን ትጥቅ ራሳችን እናስፈታለን! በሰላም ለመኖር ሌላ ምርጫ የለም" አሉ ዘማቾቹ:: የገበሬው ትግል መገታት እንደሌለበት ያስባሉ፣ እምነታቸው ከሆነ ያለምንም ማወላወል እስከመጨረሻው መዝለቅ እንደሚገባቸው ያምናሉ፡፡ መስዋዕትነት የሚያስከፍል ቢሆን እንኳ ማፈግፈግ እንደማይገባ ተነጋግረዋል፡፡

"በጭራሽ አናፈገፍግም! በወንድሞቻችሁ እና በእህቶቻችሁ ደም ያገኘነው መሬታችንን ለማንም አሳልፈን ለመስጠት አንሻም፡፡" አሉ ገበሬዎቹ፡፡ ገበሬዎቹ የባላባቶቹን አቅም ለማዳከምና ራሳቸውን ከጥቃት ለመከላከል እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ ተማመኑ። በአካባቢው የሚኖሩና ትጥቅ ያላቸው ባላባቶች ትጥቅ እንዲፈቱ ለመጠየቅ ሁሉም ማህበራት በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት ስብሰባ እንዲጠሩ ተወሰነ፡፡

አንተነህ እና ሂዋን በአጠቃላይ ሁኔታው ላይ ለመነጋገር መገናኘት ነበረባቸው። ከምግብ ቤቱ ጀርባ በግራሩ ጥላ ስር ተቀመጡ፣ እንደተለመደው አንተነህ እግሮቹን ዘርግቶና ሂዋን ጋደም ብላበት ነበር የሚነጋገሩት።

ስብሰባውን ባብልሀት መምራት እንደሚያስፈልግና በዚህ አጋጣሚ ደግሞ ዘማቹን መቀስቀስ እንደሚያስፈልግ፣ በተቻለ መጠን አባል ሊሆኑ የሚችሉ ዘማቾችን ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ተነጋገሩ።



ሂዋን ድንገት ቀና ስትል ፍሬሕይወትን አየቻት፣ ፍሬሕይወት ወደእነርሱ ላለመመልከት እየጣረች መሆኗን ተረድታለች። "ምስኪን! ይህን ግዜ እኮ እርሷ የምታስበው ሌላ ይሆናል" አለች ለራሷ። ሂዋን በበኩሏ አንተነህ ለፍሬሕይወት ያለውን ስሜት ብዙ ጊዜ ታዝባለች። እናም ያደረገችውን ነገር እያስታወሰች "ይህን ጊዜ እኮ!" በማለት ትቆጫለች ሂዋን።

አንተነህና ሂዋን የሚተዋወቁት ዩኒቨርሲቲ ነው። አንተነህ ከብዙዎቹ ሴቶች ጋር የሚግባባው በቀላሉ ስለሆነ ብዙዎች ወንዶች ጓደኞቹ ይቀኑበታል። እናም ከሂዋን ጋር ለመግባባት ጊዜ አልወሰደባቸውም፣ ብዙም ሳይቆዩ ነበር የፍቅር ጥያቄ ያቀረበላት። ሂዋን ደነገጠች፣ እናም ሳታመነታ እንኳን ወዲያውኑ መልስ ሰጠችው።

"አልችልም" አለችው ልክ እንደእርሱ ጥያቄ ቀለል አድርጋ።

"ለምን?" አላት። ለመልሱ ንግግር አላስፈለጋትም፣ ቦርሳዋን ከፈት አደረገችና ፎቶግራፍ አውጥታ ሰጠችው። ፎቶው ላይ አንድ ወጣት ለሂዋን ቀለበት ሲያደርግላት ይታያል፣ ወጣቱ በቁመቱ ከሂዋን አነስ ያለ፣ ፀጉሩ ከግንባሩ ገባ ብሎ ወደኋላ ያፈገፈገ ነው። ሁለቱም ከልባቸው የሚስቁ ይመስላሉ።

"እጮኛ አለኝ ለማለት ነው?" አላት ፎቶውን እየመለሰላት።

"ምነው አንመስልም?" አለችው ጥያቄውን በጥያቄ እየመለሰች።

"መልክም ጋብቻ!" አላትና ትቷት ሄደ።

የፍቅር ጥያቄው ያለመሳካት ከመግባባት አላገደውም። አንተነህ በዚህ ፀባዩ በጣም ይታወቃል፣ መልሶ አልጠየቃትም፣ አልተለወጠባትም። እንደወትሮአቸው ጓደኝነታቸውን ቀጠሉ።

ብዙም ሳይቆይ አንተነህ አዘውትሮ ከጊቢ መውጣት ሲያከታትል ጓራ መጋባት ጀመረች። ልትጠይቀው ብትፈልግም መድፈር አልቻለችም፣ በውስጧ እየተብሰለሰለች ጊዜው ነጎደ። አንድ ቀን ግን ለጥያቄዋ

መልስ ሰጣት። አንተነህን ከአንዲት ልጅ ጋር እዚያው ጊቢ ውስጥ አገኘችው።

“ጓደኛዬ ናት፤ የስድስት ኪሎ ተማሪ ነች” አላት ሄዋንን በቀላሉ። ሄዋን ገጽታ ላይ ድንጋጤ ተመለከተ። አንተነህና ጓደኛው ሄዋንን እዚያው ጊቢ ውስጥ ትተዋት ሄዱ።

በሚቀጥለው ቀን ሄዋንን ክፍል ሲያገኛት “ትናንት ምን ነበር ያስደነገጠሽ?” ብሎ ጠየቃት። በጣም ከሚገርማት ባህሪው ምንም የሚያስጨንቀው ነገር ያለመኖሩ ነው፤ ያልገባው ነገር ካለ መጠየቅ፣ ቅሬታ ከተሰማው ስሜቱን መግለጽ፤ መልካም ነገር ሲመለከት ማድነቅ… ብቻ በሆዱ የሚያሳድረው ነገር የለውም አንተነህ።

“አንተ እርሷ እያለች ነው እኔን የጠየቅከኝ?” አለችው በትዝብት ዓይነት።

“አንቺ እምቢ ስትይኝ ምን ማድረግ ነበረብኝ? በዚያው ሰሞን በአጋጣሚ ኬኔዲ ላይብረሪ ስሄድ ተገናኘን። ጓደኛ እንድትኖረኝ እፈልግ ነበርና ተከታተልኳት፤ ብዙ መመዘኛዎቼን አሟላች፤ ጠየቅኋት እሺ አለችኝ፤ በቃ ጓደኝነታችን ቀጠለ” አላት በቀላሉ።

ሄዋን ለደቂቃዎች ዝም አለች፤ ሰዓቷን ተመለከተችና “በል እንግባ አስተማሪ መምጫው ደርሷል” አለችው። ሁኔታዋ የሆነ መልእክት እንዳስተላለፈ ቢገባትም አንተነህ ምንም እንዲጠይቃት አልፈለገችም፤ ቀደም አለችና ወደክፍል ገባች።

ክፍለጊዜው እንዳለቀ አስተማሪው ዕቃዎቹን ሰብስቦ እስኪወጣ አላስቻለውም።

“ግልጽ አድርገሽ እንድትነግሪኝ እፈልጋለሁ፤ የሆነ ነገር በውስጥሽ እንዳለ ተሰምቶኛል” አላት ደብተሩን እየጠፈ።

“በቃ በኋላ እነግርሀለሁ” አለችው።



“ቀጠሮ አያስፈልግም፤ ታውቂኛለሽ፤ ሀሳብ ይዤ መማር አልችልም” አላት ኮስተር ብሎ።

“ውጋት እኮ ነህ አንተነህ፤ አሁን ምንም የማይጠቅም ነገር ብትሰማው ባትሰማው ምን ያደርግልሀል?” አለችው።

“የፈለገውም ቢሆን መስማት አለብኝ” አላት።

“ሌላ ምን መስለሀ ነው እኔ በአንተ እንዲህ እየታማሁ ጓደኛህን ስታስተዋውቀኝ ገርሞኝ ነው” አለችው

“ታዲያ ምን አስጨነቀሽ፤ አለመሆኑን መንገር ለማያምኑሽ ደግሞ ያንን ፎቶ ማሳየት፤ በቃ ከዚያ በኋላ ይተውታል” አላት ነገሩን አቅልሎት።

ለሄዋን ግን ቀላል አልነበረም። ሄዋን የተደላደለ ኑሮ ያለው በወቅቱም ጥቂቶች ብቻ የሚታደሉት የተማረ ቤተሰብ አላት፤ አስተዳደጓ የቅንጦት የሚባል ዓይነት ሲሆን ሲያዩአት የምታሳሳ የጠይም ቆንጆ ነች። ገና ከልጅነቷ ጀምሮ የወንዶች የፍቅር ጥያቄ ቢያስቸግራት ትምህርቷን እንዳያደናቅፍባት ሰግታ መላ መታች፤ አስራሁለተኛ ክፍል ስትገባ ነው ያሰበችው፤ ይህንኑ ለአክስቷ ልጅ አማከረችው፤ እርሱም ተስማማላትና ፎቶ ቤት ሄደው ያንን ገና ወንዶች ጥያቄ ሲያነሱ የምታስፈራራበትን ፎቶ ተነሱ።

የብዙ ወንዶችን የፍቅር ጥያቄ ለመመለስ እንዲጠቅማት የቀየሰችው ዘዴ አሁን ግን አልጠቀማትም። በዚሁ መንድ ተጠቅማ እንዲርቋት ያደረገቻቸውን ወንዶች አስታወሰች፤ ማንም የሚቆጫት አልነበረም፤ ዘዴውን ፍቱን ሆኖ ስላገኘችው ነበር ለአንተነህም የተጠቀመችበት። አንተነህ ግን በመልሷ በርግጎ አልራቃትም፤ ለፍቅር ጥያቄው የሰጠችውን መልስ ተቀብሎ በጓደኝነቱ ቀጠለ። ተግባቡ፤ ባህሪውንና መላ ስብእናውን ወደደችለት።

“ግን በቶሎ መሆኑ እንዴት ጥሩ ነው” አለች ለራሷ፤ ብዙ ከመዝለቋ በፊት ሁኔታውን ማወቋን ወደደችው። ሃሳቧንና ስሜቷን ሰብስብ ለማድረግ ይመቻታል።

"ግን አንተ ምን ዓይነት ልጅ ነህ?" አለችው አንተነህን ከሀሳቧ መለስ ስትል።

"ምን አደረግሁ?" አላት

"አንድ ጊዜ ጠይቀህ እርግፍ አድርገህ መተው አለብህ እንዴ?" ሳቋ ቀደማት።

"የሰው እርሾኛ ለመቀማት ማስቸገር ነበረብኝ ማለት ነው?"

ሁሉንም ነገረችው፤ ስትነግረው ነገሩን ለማቅለል የተቻላትን ሁሉ ሞከረች። ሁለቱም ሆዳቸውን ይዘው በሳቅ ፍርስ አሉ፤ ጓደኞቻቸው ከርቀት እያዩዋቸው እስኪታዘቧቸው ድረስ።

"በፍጹም ያልጠበቅሁት ነገር ነው፤ ከአንቺ ይህንን አልጠበቅሁም፤ ተናግረሽ ልታሳምኚኝ የምትችይ ሰው እንዲህ ዓይነት ዘዴ ትጠቀሚያለሽ ብዬ አልገመትኩም"

"ጭቅጭቅ ስልችት ቢለኝ እኮ ነው"

"ቢያንስ ከዚህ በኋላ መተው አለብሽ" አላት።

ለሂዋን የወንድ ጓደኛ ማግኘት ቀላል ቢሆንም፤ ፍቅረኛዋን ለአንተነህ ብታስተዋውቀውም፤ ከአንተነህ ጋር አብረው ለመሆን ያለመታደላቸው ሁሌም ይቆጫታል።

"ወዴት ጠፋሽ?" አላት አንተነህ በሀሳብ አብራው እንዳልነበረች ተመልክቶ።

"የትም!" አለችው ከተንተራሰችው እግሩ ላይ እየተነሳች።

* * * *



ትጥቅ የማስፈታቱ ጥያቄ በተባለው ቀን ስብሰባ ተካሂደና ተከናወነ፤ ባላባቶቹ ያለምንም ተቃውሞ "እኛ በሰላም አብረን መኖር እንፈልጋለን" በማለት መሣሪያዎቻቸውን እምጥተው ለየገበሬ ማህበራቱ አስረከቡ፡፡ በሰላም አብሮ መኖር እንደሚቻል፤ ባላባቶቹ ፈቃዳቸው ከሆነ በመከባበር ከሕዝቡ ጋር ቢኖሩ የሁሉም ደስታ እንደሆነ ተነግሮ ስብሰባዎቹ ተጠናቀቁ፡፡

ከዚህ ስብሰባ ወደዘመቻ ጣቢያ በመመለስ ላይ እያሉ "ምናልባትም ችግር ሊፈጠር ይችል ይሆናል" አለ አንተነህ።

"ለምን?" አሉት ብዙዎቹ።

"መንግሥት ጥርት ያለ አቋም የለውም። በውስጡ ካሉትም ሰዎች ውስጥ የፊውዳሉን ሥርዓት የሚደግፉ ይገኙባቸዋል። ዕድሉ ካጋጠማቸው የገበሬውን ርምጃ ከማደናቀፍ ወደኋላ አይሉም። ለዚህ ነው የገበሬዎቹ መሪዎች ጠንቃቃና ጠንካራ መሆን የሚጠበቅባቸው" አላቸው። ሁሉም በዝምታ አደመጡት።

ጥቂት እንደሄዱ አንተነህ ፍሬሕይወትን ወደኋላ አስቀራትና "ጣቢያ ስንደርስ አንድ ዕቃ እንድታስቀምጭልኝ እሰጥሻለሁ" አላት።

"ምንድነው?" ብላ ጠየቀችው።

"ምን እንደሆነ ሌላ ጊዜ እነግርሻለሁ፤ ለአሁን ግን ሰው በቀላሉ የማያየው ቦታ ታስቀምጭዋለሽ" አላት።

ምን እንደሆነ ባታውቅም "እሺ" አለችው ሳታቅማማ።

ማታ ከእራት በኋላ ወደስብሰባ ከመግባታቸው በፊት አንተነህ ጠራት፡፡ የተጠቀለለ ነገር በእጁ ይዟል፡፡ "ከልብሶችሽ ስር ሻንጣሽ ውስጥ አስቀምጪው" አላት ወደጆሮዋ ተጠግቶ፤ ጥቅሉ ከበድ ያለ ነው፡፡

"ምን ይሆን?" የሚለው ጥያቄ በአእምሮዋ እየተመላለሰ ቢሆንም በፍሬሕይወትና አንተነህ በነገራት ዓይነት አስቀምጣ ተመለሰች፡፡ በፍሬሕይወትና በአንተነህ መሀል እየተፈጠረ ያለውን ግንኙነት በጥርጣሬ ዓይን የሚመለከቱት ዘማቾች እየተበራከቱ መሄዳቸውን ሁለቱም በሚገባ ተገንዝበዋል፡፡ አንተነህ የበለጠ ይቀርባታል□ ያቅፋታል፤ ብዙውን ጊዜ አብረው እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ እርሷ ደግሞ ግራ ይገባታል፡፡

ከአንድ ሳምንት በኋላ ያስቀመጠችለትን ዕቃ እንድትሰጠው ጠየቃትና አመጣችለት፡፡ ዕቃውን ወደመኝታ ክፍሉ ይዞ ገብቶ ሲመለስ "አንድ ነገር እሰጥሻለሁ" አላት ደግሞ ለእግር ጉዞ ከግቢ ሲወጡ፡፡ ከሥራ በኋላ፤ ወደአመሻሹ ላይ ዋናውን መንገድ ተከትለው ራቅ ብለው ሄደው መመለሳቸው የተለመደ ሆኗል፡፡

"ምንድነው የምትሰጠኝ" አለችው መጓጓቷን በሚያሳይ መልኩ፡፡ ሊሰጣት የሚችለውን ነገር አሰበችና ግምቷ ለራሷው አሳፈራት፡፡

"ታዲያ እንድትጠነቀቂ እፈልጋለሁ" አላት ጥቂት ቆይቶ።

"በናትህ አንተነህ ልቤን አታንጠልጥላት" አለችው ከግምቷ ጋር ያደረገችውን ሙግት አቋርጣ፡፡

"ይኸውልሽ" አላት የተጣጠፈ ወረቀት ከጃኬቱ ውስጥ አውጥቶ፡፡ እዛው ገልጣ ብታነበው ተመኘች፤ ግን ፈራች፡፡ ግራ መጋባቷ እንደታወቀው ርግጠኛ ነበረች፡፡ "ጥንቃቄ ማድረግሽን ግን መዘንጋት የለብሽም" አላት ጠጋ አድርጎ እያቀፋት፡፡

ማታ ከተለመደው ስብሰባ በኋላ ያን ወረቀት እስከምታነበው ቸኮለች፡፡ ሁልጊዜም ከመኝታ በፊት ጸሎት የምታደርስበት ጊዜ ስላላት ለማንበብ እንደማትቸገር አስባ ደስ አላት፡፡ ወረቀቱን በጉያዋ የጸሎት መጽሐፏን በእጇ ይዛ ወደተለመደችው የጸሎት ቦታዋ አመራች፡፡ ገልመጥ ገልመጥ አለችና ወረቀቱን ከጉያዋ አወጣችው፡፡ ያየችውን ማመን አቃታት ግራ ገባት፤ ቢሆንም ማንበብ ጀመረች፡፡ ከወረቀቱ አናት ላይ በትላልቅ ፊደላት በቀይ ቀለም የተጻፈው "ዴሞክራሲያ" ይላል፡፡ አንብባው ባታውቅም



ስለዚህ ወረቀት ሲወራ ሰምታለች። ልቧ መዝለል ጀመረች፡፡ አንተነህ ወዴት እየመራት እንደሆነ በሚገባ ተረዳች፡፡ ወረቀቱን አጣጥፋ ወደጉያዋ መለሰችና የጸሎት መጽሐፏን አነሳች፡፡ ለምታነበው ጸሎት ግን ትኩረት ሊኖራት አልቻለም፤ መልሳ አስቀመጠችው፡፡ አእምሮዋ ውስጥ በርካታ ሀሳቦች ተመላለሱ፤ ያንን ወረቀት ለማንበብ የተፈጠረባት ፍላጎት ግን ሁሉንም አሸነፈና ከከተተችበት መልሳ አወጣችው፤ አነበበችው፡፡

ጽሑፉ በጣም መሰጣት፣ ጣማት፣ ደስ አላት ስሜቷን ኮረኮረው፡፡ አንብባ ስትጨርሰው ግን "ቢሆንም" አለች ለራሷ "ቢሆንም ግን በፍጹም ፖለቲካ ውስጥ መግባት አልፈልግም" አለችና ወደመኝታ ክፍሏ ገባች፡፡ ከሀሳቧ ጋር እያወራች ወረቀቱን በጥንቃቄ አስቀምጣ በፍራሻቸው ላይ ክብ ሰርተው ከሚጫወቱት ጓደኞቿ ጋር ተቀላቀለች፡፡

ሌሊቱን ግን በተደጋጋሚ ከእንቅልፏ ስትነቃ የሚታያት ያ በትላልቅ ፊደላት የተጻፈ "ዴሞክራሲያ" የሚል ጽሑፍና አንተነህ ነበሩ፡፡ ጠዋት ወደሥራ ልትሔድ ስትነሳ መንፈሷ እርብሽ እንዳለ ነበር፡፡ ከአንተነህ ጋር ላለመሆን ወሰናለች፡፡ ስለ ፖለቲካም ሆነ ስለአንተነህ እየተሰማት ያለውን ስሜት አላውቅም ልትለው ሞከረች፤ እናም ከሌሎቹ የቡድን አባላት ጋር ሆና ለሥራ ወጣች፡፡ ጥቂት እንደሄዱ አንተነህ ሲጠራት ተሰማት፤ እንዳልሰማች ማስመሰል አልሆነላትም፤ ድምጹን ትወደዋለች፤ ዞር አለች፡፡

"ምን ሆነሽ ነው ትተሽኝ የምትሄጂው" አለ አንተነህ አጠገባቸው ለመድረስ ሮጥ ሮጥ እያለ፡፡ አብረዋት የነበሩት ልጆች ሲተያዩና ሲጠቃቀሱ አየችና ተናደደች፡፡ እርሱ ግን ለማንም ደንታ አልነበረውም። ትከሻዋን አቀፈና ጉዞውን ቀጠለ፡፡

"አነበብሽው?" አላት ወደጆሮዋ ተጠግቶ።

"አዎ" አለች ቀዝቀዝ ባለ አነጋገር።

"እንዴት አገኘሽው?"

"እኔኮ ፖለቲካ ውስጥ መግባት አልፈልግም።"

"አሁንስ ምን እየሠራሽ ይመስልሻል?" አለ እየሳቀ፡፡

"ምን ሠራሁ?" አለችው ለማለት የፈለገው ግን ገብቷታል።

"ይልቅስ እንዴት ነው?"

"ጥሩ ነው ግን ባላነበው ይሻላል።"

"አለማንበቡ ለውጥ ያመጣል ብለሽ ካሰብሽ።"

ከኋላቸው እየቀረበ የሚመጣ ኮቴ ሲሰማው ጠበቅ አድርጎ አቀፋትና ጉንጯን ሳማት፡፡ በጣም ደነገጠች፡፡ በተለይ ሄዋንን ከሩቅ አይታት ስለነበረ በጣም ተናደደች፡፡ የሄዋንና የአንተነህ ነገር ግራ እንዳጋባት ነው፡፡

ቀስ በቀስ ዴሞክራሲያን ማንበብ ይናፍቃት ጀመረ፡፡ "የለም እንዴ?" ትለዋለች አንተነህን ጥቂት ሲዘገይባት፤ እርሱም ምን እንደሆነ ይገባዋል፡፡ ከአንተነህ ግን ለመራቅ መሞከሯን አልተወችም። ወደሥራም ሲሄዱ ሆነ ሲመለሱ ለብቻቸው እንዳይሆኑ ትጥራለች፡፡ ቢሆንም ለተወሰኑ ሰዓታት እንኳን ሳታየው መቆየት አይሆንላትም፡፡ እሱም ቢሆን በፍፁም እንድትለየው አይፈልግም፡፡ የሚሰጣትን መጻሕፍት እንድታነብ የሚፈልገው ማታ ብቻ ነው፤ ቀን አብረው ሲሆኑ ወሬያቸው በአብዛኛው ፖለቲካ ሆነ፡፡ ስታነብ ያልገባትን ትጠይቀዋለች በመልሱ ይመስጣታል፤ ዕውቀቱ ይደንቃታል፡፡

በርካታ የዴሞክራሲያን እትሞች አነበበች፤ ከማይነጥፍ የፖለቲካ ዕውቀት ምንጭ ለሚጨለፉትና በየእትሙ ለሚወጡት ጽሑፎች የምትሰጠው ግምት ከምንም በላይ ሆነባት። ዴሞክራሲያን የሚጽፉት ሰዎች ይደንቋታል፤ በየጊዜው የሰው ስሜት የሚሰርቁ የተለያዩ ጽሑፎችን የመጻፋቸው ነገር እጅጉን ይገርማታል፡፡ በዐይነ ሕሊናዋ ልታያቸው ስትሞክር የሚታዩአት



ማርክስ፣ኤንግልስና ሌኒን ናቸው፡፡ ልክ እንደነሱ ፂማምና ግዙፍ ይመስሏታል፡፡

"ግን በናትህ አንተነህ ይህንን የሚጽፉት ሰዎች የት ነው ያሉት?" አለችው አንድ ቀን ጋዜጣውን ሲሰጣት፡፡

"ሁሉም ቦታ" አላት ከልቡ እየሳቀ።

"እግዚአብሔር ናቸው ማለት ነዋ" አለች እርሷም እየሳቀች።

"የእውነቴን እኮ ነው ሁሉም ቦታ ነው ያሉት" ፍርጥም አለ።

"እዚህም?" አለች ግራ ገብቷት።

"አዎን እዚህም"

"እስኪ በእውነት በለኝ"

"አይ ፍርዬ ምስኪን" አለና እቅፍ አደረጋት፤ ያ ስውነቷን የሚነዝራት ስሜት ደግሞ ወረራት፤ ቀና ብላ አየችው፡፡

"እንደሱ አትይኝ" አለና ዐይኖቿን በእጁ ጨፈናቸው፡፡ የሆነ ስሜት ከዐይኖቹ ውስጥ ያነበበች መሰላት፡፡ ለደቂቃዎች በሃሳብ ትታው ሄደች፡፡

"ምን እያሰብሽ ነው?" አላት ድንገት፤ ራሱም ሃሳብ ውስጥ ነበረ።

"ምንም።"

"ትወጅኛለሽ?" አላት ሳታስበው፡፡ ደነገጠች "ምነው መውደድ ያስደነግጣል እንዴ? እኔ ግን እወድሻለሁ" አለና በጣም ጥብቅ አድርጎ አቀፋት።

ሄዋን ከፊት ለፊታቸው ወደእነርሱ ስትመጣ አየቻት፤ ከው ብላ አንተነህ ላይ አፈጠጠችበት፡፡ ንዴትም ተሰማት፡፡

"በቃ ልቀቁኝ አንተ ክፉ ነህ፤ እስኪ አሁን ሂዋን ምን ትላለች?" አለችው ከእጁ ለማምለጥ እየታገለች፡፡ ከልቧ ነበር፡፡

"ሂዊ ምንም አትልም"

"አትወድህም ማለት ነው?" ከጠየቀችው በኋላ ግን አሳፈራት

"ትወደኛለች" አለ በቀላሉ።

"አንተስ አትወዳትም?"

"እወዳታለሁ" አለ፡፡ ግራ መጋባቷን ከገፅታዋ ላይ አነበበና "ፍርዬ የመውደድ ዓይነቱኮ ይለያያል፡፡ ይልቅ ለጥያቄዬ መልስ ስጭኝ አንቺ ትወጅኛለሽ?" አላት፡፡ ልትመልስለት ግን አልቻለችም፡፡

* * * *

በሚያማምሩ ትናንሽ ፊደላት፤ ቀልድና ቁምነገር በያዙ አረፍተነገሮች የተከሸነውን የፍርዬን ደብዳቤ አንድ ጊዜ እንኳ አስቀምጦት አያውቅም። ወዲያውኑ ሲያገኘው አንድ ጊዜ በፍጥነት ይወጣውና ከዚያ በኋላ ደግሞ ደጋግሞ ያነበዋል። በላይሁንና ፍሬሕይወት ላለፉት ወራት ባለማሰለስ ደብዳቤ ሲለዋወጡ ቆይተዋል። ዛሬም የፍሬ ደብዳቤ ደርሶታል።

በላይሁን ሁል ጊዜ ከስራ መልስ እንደሚያደርገው ከዘመቻ ጣቢያው ወጥቶ በቀስታ እርምጃ መንገዱን ተያያዘው። ይህ የዘወትር ልምዱ በሁሉም ዘንድ ታውቆለት ልከተልህ የሚለው ወይንም ወዴት ነህ ብሎ የሚጠይቀው ሰው የለም። እንደወትሮው ሁሉ የተለመደው ቦታ ሲደርስ ክብድ ብሎ የነበረ መንፈሱ ቀለል እንደሚለው እርግጠኛ ነበር።

በምዕራቡ አድማስ ስር ልትጠልቅ እያሽቆለቆለች፤ ድብዝዝ እያለች በተራራው አናት ላይ ጉብ ያለች የምትመስለው ፀሐይ የምትፈነጥቀው ወርቃማ ቀለም ለአካባቢው የሚሰጠው ውበት



በበላይሁን ልብ ውስጥ ልዩ ቦታ አለው። መንፈሱ ልዩ የሆነ ደስታን ይጎናፀፋል።

ከሜዳው አለፍ ብሎ ያሉት ጉብታዎች ላይ ወጥቶ እስከሚቀመጥና ቆላውን ማየት እስከሚችል ይቸኩላል። እዚያ ሲደርስ ደስታው ይጨምራል፤ ተመቻችቶ ይቀመጥና ዐይኖቹን በርቀት ወዳለው የትላልቅ ተራሮች ሰንሰለት ይልካቸዋል። ከተራራዎቹ በስተግርጌ ያለው ረጅም ገደል ኀበዝ መሀንዲስ የነደፈው ሕንፃ ይመስላል። ከገደሉ አናት ላይ እየተወረወረ የሚንቧቸው ውሀ ድምጹ ባይሰማውም ዕይታው ብቻ መንፈሱን ያማልለዋል። ፏፏቴው ተወርውሮ ከሚያርፍበት ባሕር ረጋ ብሎ ስርዓት ባለው መልኩ እየፈሰሰ ከትልቁ ወንዝ ጋር ይቀላቀላል። ትልቁ የጀማ ወንዝ ከየሥፍራው ገባሮቹን እየተቀበለ በሰፊ መልካው ያካትትና በእርጋታ ሲጓዝ በርቀት ለሚመለከቱት የበላይሁን ዐይኖች ረጅም መቀነት ይመስላል።

ከተራራው በስተጀርባ ለመደበቅ የምታሽቆለቁለው ፀሐይ ቀይ ጨረር ኩል ከመሰለው የጠራ የበጋ ወንዝ ውሃ ላይ ሲያርፍ የሚፈጥረው ሕብረቀለም ልብን ይሰርቃል።

በላይሁንን ከተመስጦው የሚመልሰው ግታቸው የያዛቸው ላሞች ለጥጆቻቸው የሚያሰሙት የጥሪ ድምጽና ወደየጎጆአቸው ለመግባት የሚጠራሩት የወፎች ዝማሬ ነው። ደንገዝገዝ ማለቱን ተመልክቶ ከተቀመጠበት ተነስቶ እየተንጠራራ "ወይ ተፈጥሮ?" ይላል ለራሱ።

በመልስ ጉዞው ላይ ከአእምሮው ጠፍተው የነበሩ ሀሳቦች ሁሉ ሳይጠሩቸው ይመጣሉ። ሰሞኑን ሁለት ነገሮች አእምሮውን ያስጨንቁታል፤ ከፍርዬ የደረሰው ደብዳቤና የዘመቻው ሁኔታ እየተከተለ ያለው አቅጣጫ። የዘመቻው ሁኔታ ወዴት እያመራ እንደሆነ በሚገባ ተረድቶታል። ከጓደኞቹ ጋር ተነጋግረው ከዚህ በኋላ ብዙም የሚያስቆይ እንዳልሆነና ወደ አዲስ አበባ መመለስ እንዳለባቸው ተማምነዋል። አእምሮው ወዲያውኑ ወደፍርዬ ደብዳቤ ሄደ።

"በፍጹም የማጣት አይመስለኝም ነበር" አለ ለራሱ ድንገት።

ከልጅነታቸው ጀምሮ የነበራቸውን ቀረቤታ አሰበው፤ ይህ ዘመቻ ከመምጣቱ በፊት ተለያይተው አያውቁም። ገና ሕፃናት ሳሉ ዕቃ ዕቃ ተጫውተዋል፤ አብረው ትምህርት ቤት ሄደዋል፤ ትያትር ቤት ገብተዋል… ሕይወታቸውን በሙሉ አብረው ነው ያሳለፉት። በጣም ይወዳታል እንደምትወደውም ያውቃል፤ ደግሞ እህቱንና ቃለአብን አሰባቸው፤ እርሱ እህቱን የሚወዳትን ያህል ፍሬን ይወዳታል ቃለአብንም ልክ እንደወንድሙ ነው የሚያየው። ፍሬሕይወትም ቢያንስ የወንድሟን ያህል እንደምትወደው ያውቃል፤ ከእህትነት ያለፈ ስሜት ግን አይቶባት አያውቅም። እርሱስ ቢሆን ከወንድምነት ያለፈ ስሜት መቼ አሳይቷት ያውቃል፤ ብቻ አብራው ስትሆን ይደሰታል ሲያጣትም ይከፋዋል። በቃ ይሄው ነው።

ዘመቻ ከመጣ ወዲህ ግን ከሁሉም ሰው ይበልጥ ናፍቃዋለች፣ በሀሳቡ ትመጣለች፣ በሕልሙም ትታየዋለች። እንዲህ ሲሆን ደብዳቤ ይጽፍላታል፤ በተመሳሳይ ትመልስለታለች፤ ናፍቀሽኛል ይላታል እርሷም ናፍቀኸኛል ትለዋለች። የደብዳቤዎቻቸው ብዙ ክፍል የሚይዘው ግን ሌሎች ጉዳዮችን ነው፤ ስለሚያነቧቸው መጻሕፍት፣ ስለአካባቢያቸውና ስለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች።

የዛሬው ደብዳቤዋ ግን የተለየ ሆነበት፤ ብዙውን የደብዳቤ ክፍል የያዘው የአንተነህ ጉደይ ነው። ስለአንተነህ ምን ያላችው አላት? አንተነህን በአካል ባያውቀውም በፍርዬ ደብዳቤዎች በሚገባ ያውቀዋል፤ ሌሎቹንም ጓደኞቿን እንዲሁ ያውቃል። እርሱም ስለዘመቻ ጣቢያ ጓደኞቹ ይጽፍላታል። ታዲያ አንተነህን እንደማንኛውም የዘመቻ ጣቢያ ጓደኛ ነበር የቆጠረው። በአሁኑ ደብዳቤዋ ግን አንተነህ በጣም ጎላበት። "ፍርዬ ወዳዋለች ማለት ነው?" አለ ለራሱ።

ጓደኞቹን አሰባቸው፤ በጣም ይግባባሉ። እንደመጡ አካባቢ የነበረውን ሁኔታ አስታወሰ፤ የነበሩትን ጥቂት ሴቶች ጓደኛ ለማድረግ የተፈጠረው ርብርብ ትዝ አለውና ፈገግ አለ። እርሱ ፍቅረኛ ለማግኘት በተደረገው ሽኩቻና ፍጥጫ ውስጥ አልተሳተፈም። ያ የሆነው ግን እርሱ ለፍቅር ቦታ ስላልነበረው ሳይሆን ሳያውቀው በልቡ ውስጥ ፍርዬ በመኖሯ ነው።



የአሁኑ ደብዳቤዋ ግን በፍርዬ ልብ ውስጥ ያለው በላይሁን ሳይሆን አንተነህ መሆኑን እየነገረው ነው።

"ሺት!" አለ ሳያስበው። ቀና ሲል ጓደኞቹ ከፊት ለፊቱ እየመጡ አጠገቡ ደርሰዋል።

"ሉብቻህ የሚያነጋግር ምን ተገኘ?" አለው አንደኛው።

"ፍርዬ ናፍቃው ይሆናላ!" አለ ሌላው።

አንዳንዴ ብሽሽቅ ከተጀመረ ስለማይለቁት ስለፍርዬ ያወራበትን እለት ይረግማል። ሁሉም ግን የየራሱ መብሽቂያ ስላለው ብዙም አይጨካከኑም። ወዲያውኑ ርዕሱ ተቀየረና ከዘመቻ ስለሚመለሱበት ሁኔታ መነጋገር ጀምረው በቀስታ ወደ ጣቢያቸው አዘገሙ። ጣቢያው አካባቢ ሲደርሱ ቆሙና ምክክራቸውን ቀጠሉ፤ የራት ሰዓታቸውን እስከሚረሱና ጠሪ እስከሚላክባቸው ድረስ።

* * * *

ዕለቱ እሁድ ነው፤ የእረፍት ቀን፡፡ ሁሉም በሳጠራ በተሸፈነው ምግብ ቤታቸውና በመኝታ ቤቶቻቸው ውህ ልክ ላይ ተቀምጠው ይጨዋወታሉ፡፡ አንተነህ ለፍሬሕይወት መጽሐፍ ሊያመጣላት ወደመኝታ ክፍሉ ገባ እንዳለ አንድ ገበሬ በሩጫ እያለከለከ ወደእነርሱ ሲመጣ አየችው፡፡ ብዙዎቹ በጨዋታ ላይ ስለነበሩ ልብ አላሉትም፤ እርሷ ግን ቀረብ እያለ ሲመጣ ደነገጠች፡፡ አጠገቧ ደርሶ ገና ሳያናግራት "ምነው?" አለችው፡፡

"አንተነህ የለም?" አለ ገበሬው ቁና ቁና እየተነፈሰ።

"አለ! ምን ሆናችሁ?" አለችና መልሱን ሳትጠብቅ አንተነህን ለመፈለግ ሄደች፡፡ አንተነህን ስትጠራው በገጿ ላይ ድንጋጤ አየችበት፡፡ ራሱን አረጋግቶ ገበሬው ለምን እንደመጣ ጠየቀው፡፡

"ባላባቶቹ ከመንግሥት ወታደሮች ጋር መጥተው የማህበር መሪዎችን ወሰዷቸው መሳሪያውንም ከተቀመጠበት አውጥተው

ወሰዱት፡፡ መሪዎቻችን ወደ እስር ቤት እንደሚገቡም ነገሩን፡፡"
አለ ገበሬው በሚቆራረጥ ትንፋሽ፡፡

አንተነህ ያለው ነገር ትዝ አላት። "ምናልባትም ችግር ሊፈጠር ይችል ይሆናል" ነበር ያለው። ባላባቶቹ የተስማምተው የሉትን መግሪያቸውን ቢያስረክቡም በሰላማን ላይ ደጋፊዎቻቸውን አሳምነው ሁኔታውን ለመቀልበስ እንደተንቀሳቀሱና የገበሬ ማህበራቱን መሪዎች ለእስር እንደዳረጓቸው ገባት።

"ታዲያ ምን አደረጋችሁ?" የአንተነህ ጥያቄ ነበር።

"ሁኔታውን ለሁሉም ማህበራት እንዲያሳውቁ መልዕክተኞች በየአቅጣጫው ልከናል። በነቂስ ወጥተንም አስተዳደሩን ለመጠየቅ ቀጠሮ ይዘናል፡፡"

"ለመቼ?"

"ዛሬ በአስር ሰዓት፤ ይህንኑ እንድታውቁት ለመንገር ነው የመጣሁት፡፡"

ገበሬው ተመልሶ ሄደ፡፡ ወሬው ከመቅጽበት ለሁሉም ዘማች ደረሰና አስቸኳይ ስብሰባ ተደረገ፡፡ እያንዳንዱ ዘማች ከገበሬዎቹ "መንግሥት ነን እንደሚቆም ሲናገር ቆራጥነት ይነበብበት ነበር፡፡ "መንግሥት ጉን እንደሚቆም ሲናገር ቆራጥነት ይነበብበት ነበር፡፡" እርምጃ ቢወስድና ገበሬዎች ቢጎዱብንስ?" አለና አንድ ዘማች ጥያቄ አነሳ፡፡

"ቡተቻለ መጠን የገበሬዎቹ ጥያቄ ሰላማዊ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄያቸው የማይፈታ ከሆነ ግን እስከመጨረሻው ድረስ አብረናቸው ልንዘልቅ ይገባናል፡፡" አለ ሌላው ዘማች፡፡ በዚሁ ስምምነት ስብሰባው አበቃ።

ለሰላማዊ ሰልፉ የሚያስፈልጉ መፈክሮች ተዘጋጁ፡፡ በመጨረሻም ሰዓቱ ሲቃረብ ወደ ቀጠሮ ቦታ ለመሄድ ዘማቹ ሁሉ እየተለከ አንድ በአንድ ከጣቢያው ወጣ፡፡ የቀጠሮው ቦታ በሰው ግጥም



ብሎ ሞልቷል፡፡ ሰፊ አዝማች የሚጠብቅ ወታደር ይመስላል፡፡ ወንዱ ቆንጨራ ወይንም ጦር ይዟል፤ ሴቶቹ ነጠላቸውን ወገባቸው ላይ ጠምጥመውታል፡፡ አካባቢው የአመፅ መንፈስ ሰፍኖበታል፡፡

የሚታየውን የእልህ ስሜት ለማርገብና ሰላማዊ ሁኔታ ለመፍጠር ጥቂት ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ነበር፡፡ ስብሰባውን የመራው አንተነህ ነው። ጉብታ ቦታ ላይ ቆም ብሎ ግና ሰላምታ ሲያቀርብ እልልታው ቅልጥ አለ፡፡ አንተነህ ስብሰባውን ከመክፈቱ በፊት አንድ ገበሬ እጃቸውን አወጡና የሚከተለውን ተናገሩ።

"ምንም ስጋት ሊያድርባችሁ አይገባም፡፡ ምንም ሊመጣብን አይችልም ከሁለቱም በኩል ያለውን የስልክ ግንኙነት ቆርጠናል።" አሉ፡፡ ጭብጨባው አስተጋባ ዘማቾች ያልጠበቁትነው ነገር ነበርና ተደናግጥን እርስ በእርሳችን ተያየን፡፡ ስብሰባው ቲጀመረ ሀሳብ ከየአቅጣጫው ተወረወረ፡፡ እያንዳንዱ በውስጡ ያለውን ስሜት ለመግለጽ መቀስቀስ አላስፈለገውም፡፡ አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ ሰው ተነስተው እንዲህ አሉ፤

"እኛ ቂም በቀል በውስጣችን የለም፡፡ ሲያሰቃዩን የኖሩትን የማሰቃየት ሃሳብ የለንም፤ ነገር ግን ከእንግዲህ የገዥነትና የተገዢነት ግንኙነትን የምናስተናግድበት ሁኔታ አይፈጠርም፡፡ ከእኛው እኩል ሥርታችሁ ተስማምታችሁ ኑሩ አታስፈራሩን ነው ያልናቸው፡፡ ከእናንተ እኩል አንኖርም፤ እንደለመድነው አናታችሁ ላይ ካልተፈናጠጥን አይሆንም የሚሉን ሲሆን ግን የሕዝብ ኃይል ማዕበል ነው እንጠራርጋቸዋለን፡፡ ልጆቻችን በደማቸው ያስገኙልንን መሬት ለመልቀቅ ከቶ አንሞክረውም..."
ሲሉ ተሰብሳቢው ጭብጨባውን ማቋረጥ አቃተው፡፡

የተቻከለ መስዋዕትነት መክፈል እንደማይገባና ሰላማዊው መንገድ ቁያስኬድ እስከሚችልበት ደረጃ ድረስ በትዕግስት መራመድ ሰላማዊው ዕድል ሲጠጥ ብቻ ወደአመጽ መሄድ እንደሚገባ ቀጓልፆ ሰልፈኛው ተነቃነቀ፡፡

"የሦስት ሺህ ዓመታት የባላባት ሥርዓት

አለቀ ደቀቀ ገባ ወደ መሬት ..." የሚለው መዝሙር በአካባቢው ቋንቋ እየተዘመረ ጉዞ ወደ አስተዳደር ሆነ፡፡

የአስተዳደሩ አካላት የገበሬዎች አመፅ መቀስቀሱን አስቀድመው ሰምተዋል፤ እናም ተጨማሪ ኃይል እንዲላክ ለክፍለ ሀገሩ ኃላፊዎች በስልክ ለመንገር ሲሞክሩ መስመሩ መቋረጡን ተረድተዋል፡፡ ሰልፈኛው አስተዳደር ሲደርስ የወረዳው አስተዳዳሪ እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው ይንቆራጠጣሉ፡፡ ትልቁን ማይክራፎን አንስተው አንባረቁ፡፡

ጥያቄዎቻቸውን ራሳቸው ገበሬዎቹ እንደሚያቀርቡና በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ዘማቾች መናገር እንደሌለባቸው በተደረሰው ስምምነት መሠረት አንድ ገበሬ ተመርጠው የሰልፈኛውን ጥያቄ እንዲያቀርቡ ተወክለዋል፡፡

"እኛ መንግሥት የጭቁኑ ሕዝብ አጋር እንደሆነ ነው የምናምነው፡፡" አሉ ተወካዩ ንግግራቸውን ሲጀምሩ፡፡ "ስልጣን የወጣውም የሕዝቡን አመፅ በመከተል መሆኑን እናውቃለን፡፡ ከባላባቶቹ ጋር በመወገን እኛን ገበሬዎችን ሰፊውን ሕዝብ ያጠቃል ብለን በፍፁም አናምንም፡፡... የዛሬው ዕለት ጠዋት ሲሆን ያየነው ግን ከእምነታችን ውጭ ነው፡፡ በመሆኑም የተፈጠረው ስህተት የሚስተካከልበትን እርምጃ መንግስት እንዲወስድ እንጠይቃለን፡፡" አሉ ሰልፈኛው የጋራ አቋም መሆኑን ለማሳየት ጭብጨባውን አስከተለ፡፡

አስተዳዳሪው ወዲያና ወዲህ መንቆራጠጣቸውን ቀጠሉ፡፡ "እንዲህ ዓይነቱን ቅስቀሳ የሚያደርጉት እነማን እንደሆኑ..." ተናግረው ሳይጨርሱ የሰልፈኛው ጉርምርምታ አስቆማቸው፡፡ አንድ ሰው ከመሃል ተነስተው መናገር ሲጀምሩ ጉርምርምታው ፀጥ አለ፡፡

" ለብዙ ዘመናት በዝምታ የኖርነው አፋችን በጭቆና ተለጉሞ እንጂ መናገር የማንችል ሆነን አይደለም፡፡ ከእንግዲህ ጭቆናን መቀበል አንችልም፡፡ ለመብታችን መታገል የማንንም ቅስቀሳ አንፈልግም...፡፡" ጭብጨባው በየመሃሉ እያስተጋባ የልባቸውን ተናገሩ፡፡



አስተዳዳሪው ለማስፈራራት ሲሞክሩ ...የሕዝቡ ማጉረምረም ሲገታቸው ገበሬው ዙሪያ ገባውን እያማተረ የልቡን እያወጣ ሲናገር ጊዜው ሄደ፡፡ ከአስተዳዳሪው ጋር ያሉት ሹማምንት ዓይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ ከመቆም ሌላ ትንፍሽ አላሉም፡፡

ቀስ በቀስ ግን የወታደሮቹ ቁጥር እየተበራከተ መሄዱ መስተዋል በመጀመሩ አካባቢውን የሚቃኙ ሰዎች ተላኩ፡፡ የወታደር ካሚዎኖች ከከተማዋ ውጭ እያቆሙ ፈጥኖ ደራሾች በእግር ወደከተማ እየገቡ የመሆናቸው መረጃ ተሰራጨ፡፡ መረጃው ገበሬዎቹን የበለጠ አስቆጣቸው፤ ዘማቾቹ አላስፈላጊ ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማረጋጋት ውስጥ ለውስጥ ቢሞክሩም የሚሆን አልነበረም፡፡

ገበሬዎቹ ጦርና ቆንጨራቸውን እየሰበቁ መፎከር ጀመሩ፡፡ በነቂስ የወጣው የሃያ ገበሬ ማህበራት ህዝብ ቁጣ በቀላሉ እንደማይመለስ አስተዳዳሪዎቹም ተረድተውታል፡፡

"...ከእንግዲህ በኋላ በባላባት ጥይት ከመሞት ዛሬውኑ እዚሁ ቦታ ላይ እንዲለይልን እንፈልጋለን፡፡ ሞት ለማንም የሚቀር ስላልሆነ በእኛ ሞት የቀሪዎቹን መብት ለማስከበር ቆርጠናል፡፡" አሉ ገበሬዎቹ

የህዝብ ቁጣ እንደማዕበል ያስፈራቸው አስተዳዳሪዎች ቀስ በቀስ መለሳለስ ጀመሩ፡፡ ሕዝቡ "የታሰሩት መሪዎች ይፈቱ! የተወሰደው መሣሪያ ይመለስ!" እያለ ይጮሃል፡፡ ዘማቾቹ በሕዝቡ ውስጥ ተበታትነው ተስፋ በመቁረጥ መበታተን እንዳይኖር፣ የተቻኮለ ግጭትም እንዳይፈጠር መቀስቀሳቸውን ቀጥለዋል፡፡ ከዚያ ሕዝብ መሀል ካኪ ለባሽ ዘማቾቹን መለየት መቼም ቀላል አይደለም፡፡

በመጨረሻ አስተዳዳሪው መሪዎቹ እንደሚፈቱና መሣሪያውም መንግሥት ግምጃ ቤት እንደሚገባ ተናገሩ፡፡ "አሁኑኑ!" አለ ሕዝቡ፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መሣሪያ የተጫነበት መኪና ቀረበ መሳሪያውም እየወረደ በሕዝቡ ፊት ወደግምጃ ቤት ገባ፡፡ የማህበራቱ መሪዎች ግን የታሰሩት ክፍለ ሀገሩ አስተዳደር

መሆኑንና በነጋታው ተፈተው ወደቤታቸው እንደሚመለሱ ተናገሩና ሰልፉ እንዲበተን ሆነ፡፡

የገበሬዎቹና የአስተዳደሩ ሰብሰባ ከተካሄደ ከአንድ ሳምንት በኋላ አንድ ገበሬ መጥቶ እስረኞቹ እንዳልተፈቱና ወደፊትም ላይፈቱ እንደሚችሉ ወሬዎች እየተናፈሱ መሆናቸውን ለዘማቾቹ ተናገረ፡፡

ዘማቾቹ የታሰሩት መሪዎች ካልተፈቱ ዘመቻውን ለቀው ወደቤታቸው እንደሚመለሱ ለአስተዳደሩ ቢያስታውቁም የሚሰማቸው ጆሮ አላገኙም፡፡ ከሰሞኑ አንድ ሌሊት ሙሉ የወሰደ ውይይት ሲያደርጉ አደሩ፡፡ በመጨረሻም ለመንግሥት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተረቀው በተከታዩ ቀን ዘመቻ ጣቢያቸውን ለቀው ወደ ምድብ ጣቢያ ለመሄድ ተስማሙ፡፡

በስብሰባው ማግስት መኪና አስገድደው የሚያስቆሙ ዘማቾች ተመረጡና በጠዋት ተነስተው ወደ አዲስ አበባ መስመር የሚያልፍ መኪና አስቁመው ወደ አርባምንጭ እንዲመለስ አስገደዱት፡፡ በጭነት መኪናው ተሳፍረው ጉዞ ወደ አርባምንጭ ሆነ፡፡

ዘማቾቹ በቀጥታ የሄዱት ወደምድብ ጣቢያ ነው፤ ለምድብ ጣቢያው አዛዥ አቤቱታቸውን እንዲያቀርብ የተመረጠው አንተነህ በጽሑፍ የቀረቡትን ጥያቄዎቻቸውን አነበበ። ከጥያቄዎቹ መሀልም "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ባስቸኳይ ይቋቋም" የሚልም ይገኝበታል፡፡ የምድብ ጣቢያው ኃላፊ ፊገግ ብለው አዳመጡና ዘማቾቹ እንዲረጋጉ ነግረው ወደተዘጋጀላቸው ማደሪያ እንዲሄዱ መከሯቸው።

የታሰሩትን የማህበር መሪዎች የማስፈታቱ ሙከራ አልተሳካም፡፡ ከተስፋ ቃላት ባሻገር ተግባራዊ ምላሽ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ወደወረዳ ጣቢያቸው እንዲመለሱ የሚያደረገው ግፊት ግን ከፍተኛ ነበር፡፡ ከዚያም ሌላ አንዳንድ ዘማቾች ላይ ከፍተኛ ክትትል እየተደረገ መሆኑን መረጃ ደረሳቸው፡፡ ከመመለስ የተሻለ አማራጭ አልተገኘም፡፡



ምድብ ጣቢያ ከሄዱ ከአራት ቀናት በኋላ ዘማቾቹ ስብሰባ አድርገው ወደወረዳ ጣቢያቸው ለመመለስ ስምምነት ላይ ደረሱ፤ ሲመለሱ ግን ለገበሬ ማህበራቱ ስለሁኔታው ማሳወቅ የመጀመሪያ ሥራቸው መሆን እንደሚገባው ወሰኑ፡፡

ወደጣቢያቸው ሲመለሱ በየቡድናቸው በመሆን ወደየማህበራቱ እየሄዱ መንግሥት በአንዳንድ ዘማቾች ላይ ትኩረት እያደረገ መሆኑንና በነፃነት መንቀሳቀስ እንዳልቻሉ ለገበሬዎቹ አስረዱ፡፡ ሁኔታው ሁሉ በጣም ተቀያየረ፡፡ እንዲያ በልበሙሉነት ገጠሩን ለመለወጥ ደፋ ቀና ይል የነበረ ዘማች ሞራል ወደቀና የዘመቻ ጣቢያው ቀዘቀዘ፡፡

አንድ ቀን ወደ አስር ሰዓት አካባቢ ከመስክ ሲመለሱ አዝማቹ ፍሬሕይወትን ጠራት። "አቤት! ፈለግኸኝ?" አለች ቀጠግታ።

"ነገ አዲስ አበባ ትሄጃለሽ" አላት ወረቀት ከሚያነብበት ቀና ሳይል።

"ለምን? እናቴ ምን ሆነች?" አለች

"ምንም! በቅደም ተከተል ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ እንድትመለሱ ስለተፈቀደና ለአንች ቅድሚያ ስለሰጠሁሽ ብቻ! መሄድ ካልፈለግሽ ሌላ ዘማች ልልክ እችላለሁ" አለ ፍርጥም ብሎ።

"እስኪ ሙች ዘለኝ" አለች እጇን እንዲመታላት ዘርግታ።

"ይህንን የልጅ ነገርሽን ጀመርሽ ደግሞ" አለ ሁኔታዋ እያሳቀው።

"አሁን ይችን ማድረግ ይከብዳል?" አለች እጇን እንደዘረጋች።

"ሙች!" አለና እጇን መታው።

በደስታ እየፈነጠዘች ወደ ማደሪያ ክፍል ገባችና ለጓደኞቿ ነገረቻቸው። ጓደኞቿ ተንጫጩ፤ ቤተሰብ ለመጠየቅ እንድትሄድ

ፈቃድ የተሰጣት የመጀመሪያ ዘማች ነበረች። አንተነህን ማደሪያ ክፍሉ ድረስ ሄዳ ጠራችውና አዲስ አበባ ልትሄድ መሆኑን ነገረችው።

"ማባበያ መሆኑ ነው?" አለ አንተነህ።

"ለምንድነው የሚያባብለኝ?" አለች ግራ በመጋባት።

"አንቺን ብቻ ሳይሆን ሁላችንንም። በየዘመቻ ጣቢያው እየተፈጠሩ ያሉትን ሁከቶች ለማብረድ መንግሥት የተጠቀመበት ዘዴ መሆኑ ነው" አላት። ብዙም ግን አልገባትም።

ያም ሆነ ይህ ወደቤት ለመመለስ በመቻሏ በጣም ተደሰተች። አዲስ አበባ አሥራ አምስት ቀናት ቆይታ ተመለሰች። አዝማቹ እንዳለውም ዘማቹ በየተራ ቤተሰቡን እንዲጠይቅ ፈቃድ መስጠቱን ቀጠለ።

* * * *

ከአዲስ አበባ ተመልሳ ብዙም ሳትቆይ አንድ እሁድ ጠዋት ፍራሿ ላይ ጋደም እንዳለች አንተነህ የሰጣትን መጽሐፍ በተመስጦ እያነበበች በሃሳብ ርቃ ሄዳለች፡፡ ድንገት የመኝታ ክፍላቸው ቆርቆሮ መዝጊያ ተንኳኳና ፍሬሕይወትን ከሄደችበት መለሳት፡፡

"ሂዋን! ትፈለጊያለሽ" አለ በሩን ያንኳኳው ሰው።

"ማነው የፈለገኝ?" አለች ሂዋን

"ኧረ አላውቀውም"

"እሺ መጣሁ" አለች ሂዋን በጣም ጮክ ብላ፡፡ ወዲያውኑ ትጽፍበት የነበረውን ወረቀት ሰበሰበችና ቦርሳዋ ውስጥ ከትታ ወጣች፡፡ የያዘችውን ፓስታ እየከፈተች ወዲያውኑ ተመልሳ መጣች፤ ፍራሿ ላይ አረፍ አለችና ማንበብ ጀመረች። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ሂዋን



እሪታዋን ለቀቀችው፤ በጣም ተደናግጠው ወደእርሷ ሄዱ፤ ለቅሶዋን ማቋረጥ አልተቻለም። በለቅሶዋ መሃል "ወይኔ እናቴ" ትላለች።

አዝማቻቸው ለቅሶውን ሰምቶ ወዲያውኑ መጣ። ለሚጠይቃት ጥያቄ መልስ ልትሰጠው አልቻለችም፤ ፍርሿ ላይ ተደፍታ መንሰቅሰቅ ብቻ ሆነ። ደብዳቤውን እንዲያነብ ከእጇ ላይ ወስደው ሰጡት፤ አነበበው።

"በቃ በቃ! አሁን እንዲህ መሆን ምንም ጥቅም የለውም፤ ተነሽ በተገኘው መኪና ትሄጃለሽ" አላትና ወጣ።

ዘማቾቹ ደግሞ ተጋግዘው ልብሶቿን በትንሿ የመንገድ ቦርሳ ውስጥ ከተቱላት። አዝማቹ የፈቃድ ወረቀቷን አዘጋጅቶ ወዲያውኑ ተመለሰ፤ በርካታ ዘማቾች አጅበዋት እያጽናኗት አውቶቡስ የሚቆምበት ቦታ አደረሷት። ወዲያውኑ መኪና ተገኘላትና ሄደች።

ያ እሁድ ለአንተነህ የጭንቅ ዕለት ነበር። በየጣቢያው የሚገኙ የፖለቲካ ብስለት ያላቸውና ዘማቹን በቀላሉ ሊያሳምጹ የሚችሉ ዘማቾች ሩቅ ወደሆኑ ቦታዎች እንዲመደቡ መወሰኑን የሰሙት ሰሞኑን ነበር።

በመጀመሪያ እንዲቀየሩ ከተወሰነባቸው ውስጥ ሂዋን አለችበት። በምድብ ጣቢያው ስር ከሚገኙ ከሌሎች ወረዳ ጣቢያዎችም እንዲሁ የሌሎች ዘማቾች ዝርዝር አለ፤ በጠቅላላው አስር ዘማቾች ናቸው ዝርዝሩ ውስጥ ያሉት። ከእነዚህ ዘማቾች ውስጥ ሶስት ሴቶችን ጨምሮ ስምንቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ናቸው። በአጋጣሚ ሁሉንም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አንተነህ ያውቃቸዋል፤ በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ንቁ ተሳታፊዎች የነበሩ ናቸው።

"ግን ለምን ሂዋንን?" አለ አንተነህ ለራሱ። ራሱን ጨምሮ ከፍተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ ያላቸውን ዘማቾች በሀሳቡ አሰባቸው። ሂዋን ለምን የመጀመሪያዋ ተቀያሪ እንደሆነች ግን አልገባውም። ባይገባውም ማንንም ጠይቆ መረዳት አይችልም።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እያሉ ሂዋን በተወሰነ መልኩ በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ተሳታፊ ነበረች፤ ከፖለቲካ ተሳትፎዋ ይልቅ የሰዎችን

ቀልብ በሚስብ ባህሪዋ ትታወቃለች። በጣም ትሁት ነች፣ በማንኛውም የሰው ችግር ውስጥ የምትገባና ለጊዜቀም ሆነ ለገንዘብዋ የማትሳሳ፤ ብዙ የማትናገር፤ ከተናገረች ግን አካባቢዋን የምታገናዝብና የተናገረችው ሁሉ መሬት የማይወድቅ ነው።

አንተነህ ሳያስበው ፈገግ አለ። ፈገግ ያሰኘው የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያሉ ከሂዋን ጋር ሲተዋወቁ የተፈጠረውን ሁኔታ አስታውሶ ነው። "አይ ሂዋን!" አለ ሳያስበው። ያን ዓመት ሲያስታውስ ድንገት የሚመጣበት ትዝታው ጭልጥ አድርጎ በሀሳብ የኋሊት ይዞት ከነፈ።

በግቢው ውስጥ አንተነህን እና ፍቅረኛውን ማህሌትን የማያውቅ አልነበረም፡፡ እንዲያውም "ሮሚዮና ዡሊዬት" የሚል መጠሪያ ተሰጥቷቸው ነበር። የእውነትም ልዩ ፍቅር ነበራቸው። ማህሌት በትናንሽ

ዐይኖቿና በረጅም ሉጫ ፀጉሯ፣ ከዚያም በላይ ደግሞ በጎበዝ ተማሪነቷ ትታወቃለች። የክፍሏ ተማሪዎች ስለባህሪዋ ሲናገሩ "በሚገባ ክፍል ትከታተላለች፣ ትጠይቃለች፣ ታጠናለች፣ "ትሰቅላለች" ይላሉ። አስተማሪዎቿም በጣም የሚያደንቋት ተማሪ ነበረች ማህሌት። ለማንም ወንድ ፊት የማታሳይ፣ ለፍቅር ጥያቄም ቦታ ያልነበራት፣ ወንዶች በውርርድ ሊጠይቋት መድፈር ያቃታቸው ተማሪ ነበረች ።

አንተነህ በመጀመሪያው ቀን ኬኔዲ ቤተመጻሕፍት ሲያገኛትና ሲተዋወቃት ግን በቀላሉ ነው የተግባቡት። በተደጋጋሚ ተገናኙ፤ ቀስ በቀስ ጓደኝነት መሰረቱ፤ ተማሪም ጉድ አለ።

የአንደኛ ዓመት ትምህርት ሲጠናቀቅ አንድ የውጭ አገር ዜጋ አስተማሪዋ ለማህሌት የጎበዝ ተማሪነት ሽልማት ሰጣት፤ የትምህርት ዕድል። ስለሁኔታው ለአንተነህ ነገረችው፤ በዕድሉ እንድትጠቀምበት መከራት። በመጀመሪያ አልተስማማችም ነበር በኋላ ግን ከአንተነህ ጋር ባደረጉት ተደጋጋሚ ውይይት ተስማምታ ዕድሉን ተቀበለች። አንተነህና ማህሌት ተለያዩ፤ የተለያዩት ግን ለጊዜያዊ መለያየት እንጂ ለመጨረሻው አልነበረም።



በሁለተኛ ዓመት ትምህርት መጀመሪያ ላይ አንተነህና ማህሌት ለተወሰኑ ጊዜያት በደብዳቤ ተገናኝተዋል፤ ናፍቆታቸውን ተገላልጸዋል። ማህሌት ሳያስበው የደብዳቤ ግንኙነቷን አቋረጠች፤ አንተነህን ግራ ገባው። ምናልባትም በሕይወቱ ሙሉ ከጻፋቸው ደብዳቤዎች የበለጠ ቁጥር ያላቸው ደብዳቤዎችን ጽፎላታል፤ ለአንዱም ግን መልስ አላገኘም። ምክንያቱን ለማወቅ ያልሞከረው ሙከራ አልነበረም፤ አልተሳካለትም። ወንድ ልጅ በፍቅር ይጎዳል ተብሎ በማይገመት ሁኔታ ተጎዳ አንተነህ። የዚያ ሴሚስተር ውጤቱ እንዳልነበረ ሆኖ አለፈ።

ብዙዎች ጓደኞቹ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ እየተጠናከረ የመጣው የፖለቲካ እንቅስቃሴ አንተነህን ከጉዳቱ እንዲያገግም አስተዋጽኦ እንዳበረከተለት ይናገራሉ። እርሱም ቢሆን ይቀበለዋል። ፖለቲካዊ ተሳትፎው ማህሌትን ለመርሳት እንዳገዘው ይናገራል። እናም ላያስባትና ላያስታውሳት ይጥራል። አንዳንዴ ቢያስታውሳትም እንደበፊቱ አይብሰለሰልም። አሁን ደግሞ ያንን የልቡን ቁስል አስረስታ ፍቅርን እንደገና እንዲያስበው ያደረገችው ፍርዬ ገጥማዋለች። አስባበትና ተዘጋጅታበት ሳይሆን እንዲያው ከተፈጥሮአዊ እሷነቷ የሚመነጨው ፍቅሯ ፍርዬን በልዩ ዐይን እንዲያያት አድርጎታል። በጣም ይሳሳላታል ይንከባከባታል። እናም በፍቅር ግንኙነት እርሱ የተጎዳውን ጉዳት እንዳትጎዳ ይሰጋል። ግን ይወዳታል ሳይፈልግም አፍቅሯታል።

* * * *

ከሂዋን መሄድ በኋላ አንተነህ እንደወትሮው መሆን አልቻለም፡፡ ለመጫወትና ለመሳቅ የሚያደርጋቸው ጥረቶች ሁሉ አልሳካ ሲሉት አንዳች ነገር መንፈሱን ሲሰርቅበትም ይታያል፡፡ ፍሬሕይወት ሁኔታውን ከሂዋን መሄድ ጋር ብታዛምደውም እውነታውን ግን በትክክል የተረዳችው አልመሰልሽ አላት፡፡

"አዲስ አበባ መሄዴ ነው" አላት አንተነህ አንድ ቀን ።

"ፈቃድ ደረሰህ እንዴ?" አለችው።

"እኔስ ቤተሰቦቼ አይናፍቁኝም እንዴ?" አለ እየሳቀ።

"ሂዋን ናፈቀችኝ ብትል አይሻልህም" አለችው፤ ከተናገረች በኋላ ግን አሳፈራት "እሺ በቶሎ ትመለሳለህ?" አለች ምንተ እፍረቷን።

"እርግጠኛ አይደለሁም ፍርዬ! እርግጠኛ ሆኜ መናገር የምችለው አንድ ነገር ብቻ ነው። በጣም እንደምወድሽ!"

"ይህንን ለመቀበል ይቸግረኛል" አለች ፍሬሕይወት ዐይኖቿ እንባ እያቀረሩ።

"ፍርዬ እባክሽን እመኚኝ፤ ሂዋን ፍቅረኛዬ አልነበረችም ወደፊትም አትሆንም፡፡ እንደኔ ቢሆን ማንንም ማፍቀር አልፈልግም ነበር፤ ግን ከቁጥጥሬ ውጭ በሆነ ሁኔታ አፈቀርኩሽ፤ መለየቱም ፤ግዴታዬ ሆነ። እንደምንገናኝ ግን ተስፋ አደርጋለሁ...በጣም እንደምጎዳሽ ይሰማኛል..." ድምፁ ተርገበገበ ቀና ብሎ ተመለከታት፤ ዐይኖቹ እንደመቅላት ብለዋል። እንባውን እየታገለ እንደሆነ ገባት፡፡ የእርሷ ዐይኖች ግን በእንባ ረጥበዋል፡፡ ወደ ደረቱ አስጠግቶ አቀፋትና በሚንቀጠቀጡ ከንፈሮቹ ሳማት፡፡ ለዘለዓለም ከእቅፉ እንዳትወጣ የሚያደርግ ይመስል የበለጠ ወደደረቱ አስጠግቶ አቀፋት፡፡ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እስኪል፤...ጉንጮቿ እስኪቀሉና ቲማቲም እስኪመስሉ ድረስ፡፡

ከዚያ በኋላ ቀና ብላ ልታየው አልደፈረችም፣ አፈረችው፡፡ ማንም ስሜት አያውቅም፤ ቀድሞውንም ከወንድ ጋር እንዲህ ዓይነት ቅርርብ ኖሯት አያውቅም፡፡ በጣም የምትቀርበው ወንድ ቢኖር በላይሁንን ነው፡፡ ከእርሱ ጋር ደግሞ አብረው ውለው አብረው ቢያድሩም እንዲህ ዓይነት ስሜት ውስጥ በፍፁም ገብተው አያውቁም። ልክ ከወንድሞቿ ጋር እንደምትሆነው ነው ከበላይሁን ጋር የሚሆኑት፡፡

በቀስታ ከንፈሮቿን በእጇ የዳበሰቻቸው ያበጡ መሰሏት ነበር፡፡ ግን ምንም የማበጥ ምልክት አላገኘችም። ድርጊቷ ለራሷ ገርሟት ቀና ብላ አንተነህን አየችው። ዐይን ለዐይን ተጋጩ፤ የበለጠ ደነገጠች፡፡



"ጓደኛ ኖሮሽ ያውቃል?" አላት፡፡ አልመለሰችለትም፡፡ በድጋሚ ጠየቃት፤ ኖሯት እንደማያውቅ በአንገት ንቅናቄ ነገረችው፡፡

"በፍፁም አልረሳሽም ፍርዬ" አላት በጆሮዋ፡፡ ወፍራምና ልዝብ ድምጹ ከቃላቱ ጋር በእርሷነቷ ውስጥ ሲሰርጽ ተሰማት፡፡ ከአንተነህ መለየት ሞት መሰላት፡፡

"እኔም አልረሳህም እንዴትስ ልረሳህ እችላለሁ... " ሌላ መጨመር አልቻለችም፡፡ አንተነህ ለምን እንደሚሄድ መገመት አልቸገራትም፤ ከአነጋገሩ ብዙ ተረድታለች። ባትለየውና አብራው ብትሄድ የቱን ያህል ደስ ባላት? ግን የሚሆን አልነበረም፡፡

አንተነህ በማግስቱ ተሸኘ፡፡ አሸኛኘቱ ግን በአደባባይ አልነበረም ማንም ሳያውቅ መኪና የሚያገኝበት ቦታ ድረስ የሚሸኙት ልጆች ተመረጡ፡፡ እርሱና ፍሬሕይወት እንደተለመደው ተያይዘው በፊትለፊት ሲወጡ ልጆቹ ሻንጣውን ይዘው በጓሮ በኩል ሄዱ፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ፍሬሕይወት ብቻዋን ተመለሰች፡፡ ወደመኝታ ክፍል ስትገባ በሀሳቧ መሸሸጊያ ሊሆናት የሚችል ነገር እየፈለገች ነበር፤ መልስ ያልሰጠችው የበላይሁን ደብዳቤ ትዝ አላት፤ ቢያንስ ለጥቂት ጊዜ ሀሳቧን ይከፍልላታል።

ወደመኝታ ክፍል ስትገባ እንባ እየተናነቃት ነበር፡፡ ወረቀትና እስኪሪፕቶ አንስታ ለበላይሁን ደብዳቤ ለመጻፍ ጀመረች፤ ሀሳብ ግን ከየት ይምጣ? ወረቀትና እስኪሪፕቶውን ወርውራ ፍራሿ ላይ ተጋደመችና እንቅልፍ እንዲወስዳት ተመኘች፤ እንቅልፍ ግን የሚታሰብ አልሆነም፡፡ ብቸኝነት ተሰማት፣ ጨነቃት ራሷን ከማዳመጥ በስተቀር ለምንም ነገር ደንታ አልነበራትም፡፡ አንተነህን በተመለከተ ያለመኖሩ ነገር ሲታወቅ በማንኛውም ሰዓት ጥያቄዎች ሁሉ ወደእርሷ እንደሚያነጣጥሩ ብታስብም ከምንም አልቆጠረችውም፡፡ ግን በውስጧ የታመቀውን ስሜቷን መግለጽ አለባት። እንደገና ወረቀትና እስኪሪፕቶውን አንስታ ለበላይሁን ደብዳቤውን መጻፍ ጀመረች። እንደጠበቀችው ሳይሆን ወሬው ውስጥ ለውስጥ አለቀና ከቅርብ ጓደኞቿ በስተቀር ብዙ ጥያቄዎች ወደእርሷ የሰነዘረ አልነበረም፤ ደስ አላት፡፡ የሰሞኑ ወሬ ሁሉ ዘመቻ ትቶ ወደቤት የመመለስ ጉዳይ ሆነ፡፡

አንተነህ "...በየትኛውም ቦታ ለማንኛውም ጭንቀት መድሃኒቱ መጽሐፍ ነው" ያላትን አስታውሳ ራሷን መጽሐፍ ውስጥ ለመደበቅ አሰበች፡፡ በቅርብ ቀን አንተነህ እንድታነበው የሰጣት መጽሐፍ ትዝ አላትና ሻንጣዋን ከፍታ አወጣችው፡፡ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ነው "What is to be done" ("ምን መደረግ አለበት") ይላል፡፡ የመጽሐፉን ማውጫ ማንበብ ስትጀምር ብቻዋን በሳቅ ፍርስ አለች፡፡ ከሌኒን መጽሐፍ ውስጥ ስለፍቅርና ስለብቸኝነት የሚያወራ ነገር ለማግኘት ማሰቧ ነበር ያሳቃት፡፡

"ይሄ ፍቅር ማለት ሞኝ ያደርግ ይሆን እንዴ?" አለች ለራሷ ከሳቋ መለስ ስትል፡፡

ንባቧን አላቋረጠችም፤ ግን ጠጠረባት፡፡ እንዲያ በተወጣጠረ አእምሮ ቀርቶ በተስተካከለ አእምሮዋም ቢሆን ሊገባት የሚችል አልመሰላት አላትና መልሳ ከተተችው፡፡ ጊዜው ለማንም ለምንም ብሎ ሳይሆን በራሱ መንገድ መሸ፡፡ በተለመደው ሰዓት ከጓደኞቿ ጋር ለእራት መቀመጥ ነበረባትና ለተረብ ራሷን አዘጋጅታ፡፡ ብሽሽቁን አልጠላችውም፤ የአንተነህ ስም በየሰከንዱ ሲጠራ መስማቱም ቀላል አልነበረምና ተረባቸውን ከምንም ሳትቆጥረው ራት ተበልቶ አበቃ፡፡

ሁሉም ወደእንቅልፍ ዓለም ገብቶ ምሽቱ ፀጥ ረጭ አለ፡፡ የፍሬሕይወት ዐይኖች ግን ከእንቅልፍ የተጣሉ ይመስል ቁልጭ ብለዋል፡፡ አካላዊ ድካም ባይኖርባትም መንፈሷ ግን ደቋል፤ አዕምሮዋን ማሳረፍ አልቻለችም፡፡ ኮርኒስ በሌለውና አልፎ አልፎ በሚስማር በተበሳሳው የጣሪያ ቆርቆሮ ዘልቆ የገባው የጨረቃ ብርሃን በክፍሉ ውስጥ ቀጫጭን ቢጫ መስመሮች ዘርግቶአል፡፡ ዐይኖቿ ከአንዱ መስመር ወደሌላው ተንከራተቱባት፤ ሃሳቧም ልክ እንደመስመሮቹ ብትንትን ብሎ መጨበጫው የጠፋ መሰላት፡፡ ግን አንድ ነገር ብቻ ጥርት ብሎ ይሰማታል፤ ወፍራምና ልዝብ የሆነው የአንተነህ ድምጽ "በጣም እወድሻለሁ ፍርዬ" ሲላት፡፡

ቀስ በቀስ ትርምስምስ ያሉ ሃሳቦቿን ሁሉ ደምስሶ የአንተነህ ድምፅ መላ አካሏን ተቆጣጠረው፡፡ በእቅፉ ውስጥ ያለች እስኪመስላት በተጠጋችው ደረቱ ውስጥ የምትዘለውን የልቡን ድምፅ ሳይቀር



በጆሮዋ እያዳመጠች የሚፋጁና ርብትብት ከንፈሮቹ... ጭልጥ ብላ በሀሳቧ ዓለም ተዋጠች፤ ደስም አላት፡፡ ሁለትነት በአንድነት ወደሚዋጥበትና አንዱ በሌላው ውስጥ ወደሚጠፋበት ወደዚያ ልቀቂኝ ወደማይለው እውነተኛ የደስታ ስሜት ወደሚፈልቅበት የፍቅር ዓለም እልም ጭልጥ ብላ ገባች፡፡

"ፍርዬ በናትሽ ተነሽ" አለች ኤልሳቤጥ ዐይኖቿን እየጠራረገች።

ገና መንፈሷ ዘና ማለት ሲጀምር ኤልሳ ስለጠራቻት ብስጭት ብላ ተነስታ አተኩራ ተመለከተቻት፡፡

"ምን ሆንሽ?" አለች ንዴቷን ለመሸፈን እየሞከረች።

"ራበኛ!" አለች ኤልሳ ሙልቅቅ ባለ ሁኔታ።

"አበዛሽው እሺ ስንት ሰዓት እንደሆነ ታውቂያለሽ?" ቆጣ ለማለት ሞከረች ፍሬሕይወት።

"ፍርዬ ደግሞ አዲስ ትሆኛለሽ እንዴ እንደሚያመኝ ታውቂ የለ?" ኩርፍ አለች ኤልሳ።

"እሺ በቃ ተነሽ" አለቻት ፍሬሕይወት የኮዳውን ውሀ እጇን እንድትታጠብበት እየሰጠቻት።

የኤልሳን ፀባይ ሁሉም አውቀውላታል፡፡ ማታ እራቷን በአግባቡ አትበላም፤ እንደህፃን ልጅ ሌሊት ስትነቃ ራበኝ ማለቷም ቢሆን የተለመደ ነው፡፡ ኤልሳ የተሰማትን ሳትቆጥብ በመናገር ሰው ብታስቀይምም ልቧ ግን ሩህሩህ ነው፡፡ ቆየት ስትል የተናገረችውን አታስታውሰውም፡፡

"እናንተ ይሄንን ሌሊት መብላት የምትተውት መቼ ነው?" አለች አንደኛዋ ዘማች ከተኛችበት ቀና ብላ።

“ይልቅስ ነይ ብይ የሌሊት ምግብ እንዴት እንደሚጣፍጥ ስለማታውቂ ነው” አለች ፍሬሕይወት።

“እንችማ በፍጹም አልተኛሽም አይደል?” አለች ልጅቱ ተደላድላ ፍራሿ ላይ እየተቀመጠች።

“እባክሽን እርሷ ፍቅር ይዟታል” ቀበል አለች ኤልሳ ፍሬን ዓይን ዓይኗን እየተመለከተች።

“እሱማ ትክክል ነው፤ እንዲህ እንቅልፍ የሚያሳጣት ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ወይኔ እህቴን በዚህ በበረሀ እንዲህ ያንገላታብኝ” ልጅቱ ቀጠለች።

ቀስ በቀስ ሁሉም ከእንቅልፋቸው ነቅተው ተቀመጡና ወሬውን መቀባበል ጀመሩ፡፡ ተረቡ ከግራና ከቀኝ ሲወረወር ሳቁ ከጣሪያ በላይ ሆነና ተያይዞ ባለው ክፍል የተኛውን አዝማቻቸውን ቀሰቀሰው፡፡

“እባካችሁን አትረብሹ እናንተ ልጆች ገና ስምንት ሰዓት እኮ ነው” አለ አዝማቹ ከእንቅልፉ ሲባንን።

“ምኑን ተኛነው ሀምሳ አለቃ ፍቅር ጉድ የሠራቸው መሀላችን እያሉ እንቅልፍ ከየት ይመጣል ብለህ ነው” አለች ዘነበች።

“ሀምሳ አለቃ እኔ አዲስ አበባ መሄድ እፈልጋለሁ” አለች ፍሬ ሳታስበው።

“እውነት ነው አንቺማ መሄድ አለብሽ” አለና ሳቁን ለቀቀው፤ ሁሉም በሳቅ አወኩ።

* * * *



ክፍል 2

## ትግልና ፍቅር

በላይሁን ቀድሞ ከዘመቻ መጥቶአል፡፡ ፍሬሕይወት ለጻፈችለት ደብዳቤ መልስ ሳይመልስ በመቅረቱ ስጋት አድሮባት ነበርና ስታገኘው በጣም ተደሰተች፡፡ ሲገናኙ የተቀበላት በተረብ ነው "ፖለቲካው አልዘልቅ ብሎሽ ነዋ ዘመቻ ጥለሽ የመጣሽው?" አላት እየሳቀ፡፡

ከዘመቻ መልስ ሕይወት በምንም መልኩ የዱሮውን የወጣትነት ስሜት ይዞ ሊዘልቅ አልቻለም፡፡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ የተለወጠ ይመስላል፡፡ አንድ ዓመት ያልደፈነው የዘመቻ ቆይታ ወጣቱ እንደገና የተፈጠረ እስኪመስል ድረስ ቀይሮታል፡፡ ለወንዶች ወጣቶች በየኪዮስኩ ደጃፍና በየጎዳናው ተሰብስቦ ልጃገረዶችን መልከፍና ማበሳጨት፣ በለቅሶአቸው መሳቅና መቀለድ ጊዜው ያለፈበት ጉዳይ ሆነ፡፡

1968 ዓ.ም ቀደም ሲል የተጀመረው የትግል ጥንስስ ተብላልቶ የተደፈደፈበት ወቅት ሆነ፡፡ ፖለቲካ ቀስ በቀስ ከበቀለበት የዩኒቨርሲቲ ግቢ ወጥቶ በየትምህርት ቤቱና በየመሥሪያ ቤቱ ጭምር እግሩን ሰደደ፡፡ ፖለቲካ የእያንዳንዱ ሰው እስትንፋስ የሆነ መሰለ፡፡

ከዘመቻ መልስ አዲስ አበባ የበርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች መናኸሪያ ሆና ጠበቀቻቸው። ማሌሊት፣ ኢጭአት፣ መኢሶን፣ ወዘተ ሁሉም የየራሳቸውን ፕሮግራም ይዘው አባላትን ለመመልመል ወዲያ ወዲህ የሚሉበት ጊዜ ነበር። እናም በርካታ የስብሰባ ጥሪዎች ይተላለፋሉ፡፡ በርካታ ወረቀቶች ይሰራጫሉ…

ከየዘመቻ ጣቢያው ከብልለው የተመለሱ ዘማቾች በመገናኘት ጠንከር ያለ የፖለቲካ አቋም መያዝ ጀመሩ፡፡ እንደሚያመቻቸውና እንደሁኔታው እየተሰበሰቡ መወያየቱ ቀጠለ።

በላይሁን ፋታ የለውም ቀን በየስብሰባው መዋል፤ ለሕቡዕ ድርጅት አባል የሚሆኑ ወጣቶችን መመልመልና ሌሊት ማንበብ ሆኗል ሥራው። ጊዜውንም ሆነ አእምሮውን ፖለቲካ ተቆጣጠረበት።

ከፍሬሕይወት ጋር የሚገናኙት በጣም አልፎ አልፎ ነው። ሲገናኙም ወሬአቸው ሁሉ ያው ፖለቲካ ነው። ከዱሮው ወሬያቸው የሚለየው ዛሬ የሚነጋገሩበት ነገር ሁሉ የጋራ ጉዳያቸው መሆኑ ነው። ፍሬሕይወት እንዲህ ለፖለቲካ ያላት አመለካከት መቀየሩን ሲያስበው ይገርመዋል።

አንደ ቀን ረፋዱ ላይ እንደተለመደው የጠዋት ቡና እነፍሬሕይወት ቤት ሲፈላ ሽታው ጊቢውን አውዶታል። በላይሁን ለጠዋቷ ጸሀይ ጀርባውን ሰጥቶ መጽሐፍ ያነባል። ፍሬሕይወት እናቱን ለቡና ልትጠራ ሳትወጣ አየችውና ጀርባውን ነካ አድርጋው አለፈች።

"ዛሬ ሰርግ አለብሽ እንዴ?" አላት ቀና ብሎ ተመልክቷት።

"ታድዬ ሰርግ የምሄድ እመስላለሁ?" አለችው አለባበሷን እየተመለከተች፡፡ ትከሻዋ ላይ ወርዶ የተንዘንዘው ጥቁር ጸጉሯ ከለበሰችው ነጭ ሹራብ ጋር ልዩ ሕብር ፈጥሯል። ወገቧ ላይ ጥብቅ ብሎ ከታች ብትን ያለው ቀሚስ ደግሞ ቅርጿን አጋልጦታል።

እናቱን ቡና ጠርታ ስትወጣ "ከመቼ ወዲህ ነው አባክህ እንዲህ ሞልቶልህ መቀመጥ የቻልከው? እኛ እኮ አንተን ማግኘት ብርቅ እየሆነብን ነው" አለችው።

"አንቺ ራስሽ መች ተገኝተሽ፤ መጨበጥስ ያቃተን አንቺን ነው፡፡" አላት ከሚያነበው መጽሐፍ ላይ ቀና ብሎና ሰዓቱን ተመልክቶ፤ መቼም በላይሁንን በእጁ መጽሐፍ ሳይዝ አገኘሁት ማለት ዘበት ነው፡፡



"ፀሐይ እየደረሰብህ ነው ተነሳ" አለችው አሁንም እያቅማማች። እንተነህንና በላይሁንን ልታስተዋውቃቸው ሁሌም ታስባለች፡፡

"አይ የኔ አሳቢ" አላት እየሳቀ።

"መቀለዱ ነው፡፡ ይልቅስ ተነስ ዐይኖችህ ገና ብዙ ይጠብቃቸዋል..." የበላይሁን እናት ሲጠሯት "እመት" አለችና ወደቤት ተመለሰች።

"ጎሽ ቁርሳችሁን ከወንድምሽ ጋር ብሉ እስኪ" አሏት እያቀራረቡ፡፡ የበላይሁን እናት ሁልጊዜም "ከወንድምሽ ጋር ከእህትህ ጋር" ሲሉ ልዩ ስሜት ይሰማታል። የእውነትም ወንድምና እህት እንጂ ባዕድ የሆኑ አይመስላትም፡፡

"እኔ እኮ በልቻለሁ እማማ" አለቻቸው።

"ግዴለሽም ልጄ ከአንቺ ጋር ሲሆን ትንሽ ቢበላ ብዬ እኮ ነው፡፡ ቀለቡ መጽሐፍ ብቻ ሆኗል፡፡ አታይውም ሰውነቱን አጥንት ብቻ ቀርቶት፡፡ በይ ጥሪውና ብሉ እኔ ለቡናው እሄዳለሁ" አሏት።

በላይሁንን በግድ ጎትታ አስገባችው "አንተ አሳበዛኸውም ደግሞ ለምግብ መለመን አለብህ፡፡ ለዚያውም ይሄን የመሰለ ቁርስ ቀርቦልህ፡፡ አትጨማለቅ እሺ" አለችው ለጉርሻ እጇን እየዘረጋች፡፡ እየተጎራረሱ የቀረበውን ቁርስ ግጥም አድርገው በልተው ሲጨርሱ

"በናትሽ ፍርዬ ሻይ አፍይ" አላት በላይሁን።

"ቤት እንሂድ የተፈላ ሻይ አለ" አለችውና ተያይዘው ወደ እነፍሬሕይወት ቤት ሄዱ።

"በላችሁ?" አሉ የበላይሁን እናት ገና ሲገቡ።

"ዱሮም ሲቀብጥብዎት ነው፡፡ ሳህኑንም ሲበላ ምንም አልቀረውም" አለቻቸውና ሻይ ልታቀርብለት ወደጓዳ ገባች፡፡

በላይሁን ፍሬሕይወትን ከበስተጀርባዋ እየተመለከታት ለአፍታ ያህል በሀሳቡ ወደዘመቻ ሄደ። ዘመቻ እያለ ሲያስበው የነበረውንና አዲስ አበባ እንደተመለሰ ለፍሬሕይወት ሊነግራት የወሰነውን ሀሳብ እርግፍ አድርጎ የመተው ነገር አንዳንዴ በጣም ይገርመዋል። ፍሬሕይወትን ድሮም ይወዳት ነበር፤ በእርሱነቱ ውስጥም ልዩ ሥፍራ ያላት አብሮ አደጉ ናት። ነገር ግን በጣም ከመቀራረባቸው የተነሳ ለልቡ የሚሰማው ባዕድነቷ ሳይሆን እህትነቷ ነበር። የዘመቻ ጓደኞቹ ግን መንፈሱን ለውጠውበታል፤ ስሜቱ ትክክል ያለመሆኑንና ፍሬሕይወት እህቱ ልትሆን እንደማትችል እንዲያስብበት አድርገውታል። ግን በፍጹም መድፈር አቃተው፤ ለፍሬሕይወት የፍቅር ጥያቄ ማቅረብ ከበደው፤ ባሰበው ቁጥር ግን የበለጠ እያፈቀራት መሆኑ ይታወቀዋል።

ሻዩን አምጥታ ጠረጴዛው ላይ ስታስቀምጥለት ቢያየትም ከሀሳቡ አልተመለሰም። ዝም ብሎ ከሀሳቡ ጋር ቆየ።

"እንዴ ምን ሆነሃል? ልጆቹ እንደሆነ በዕድላቸው ያድጋሉ" አለችው ፍሬሕይወት በሀሳብ መኰብለሉን ተመልክታ።

አልመለሰላትም። ስሜቱን ፈራው፤ ስሜቱ ደግሞ ከአላማው እንዲያዘናጋው በፍጹም አይፈልግም። እናም ሀሳቡን ወደ ወትሮ አንገብጋቢ ጉዳይ ለመመለስ ፈለገ።

"ዛሬ ወጣት ማህበር ስብሰባ አለ፤ አትሄጂም?" አላት ከነበረበት ሀሳብ ለመውጣት ባደረገው ሙከራ።

"አይ ዛሬ አልሄድም፤ ከእነአንተነህ ጋር ቀጠሮ አለን" አለችው በአጭሩ።

አንተነህን በአካል ባያገኘውም በስም ያውቀዋል፤ እንዲያውም ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ፍሬሕይወት ስለአንተነህ ባነሳች ቁጥር



የሚሰማውን ስሜት መቆጣጠር እያቃተው ተቸግሯል። ሳያስበው ስሜቱ ልውጥ አለበትና

"አንቺ ግን አብዝተሽዋል እሺ፤ ከሁሉም በላይ አንተነህ ያልሽ ያስመስልብሻል" አላት ቆጣ ብሎ። ፍሬሕይወት ገጽታ ላይ የተመለከተው ስሜት አስደነገጠውና ፈገግ ለማለት ሞከረ። ፍሬሕይወትን ግራ እንዳጋባት ተሰምቶታል። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳያወሩ ሻዩን ጠጥቶ ሲጨርስ ከቤት ወጣ።

* * * *

ፍሬሕይወት ወደቀጠሮዋ ስትሄድ የበላይሁን አባባል እንደገረማት ነበረች። እየቀለደ እንዳልነበረ በሚገባ አውቃለች፤ ከድምጹ ቅላጼ የታዘበችውና ከገጽታው የተመለከተችው ቀልድ አልነበረውም። ግራ እንደገባት ነው ቀጠሮ ቦታ የደረሰችው።

ያን ዕለት አብዛኛዎቹ የዘመቻ ጣቢያ ልጆች ተገኝተዋል፤ በዚያን ዓይነት ሁኔታ ግን እየተገናኙ መወያየት ስለማይቻል ሁሉም ዘማቾች በየአካባቢያቸው በተቋቋሙ ወጣት ማህበራት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ሊያደርጉ ተስማምተው ነበር የተለያዩት። የወጣት ማህበር ተሳትፎ ለጠቅላላዎቹ ዘማቾች የተነገረ ሲሆን ለአብዛኞቹ በየአካባቢያቸው በሕቡዕ የሚታገለው ፓርቲ ባደራጃቸው ህዋሶች ውስጥ እንዲገቡ እነአንተነህ አመቻችተዋል።

ስብሰባው ሲበተን "እሺ ፍርዬ" አላት አንተነህ እንደተለመደው ፍሬሕይወትን ትከሻዋን አቀፍ አድርጎ።

"አለን" አለችው ደንገጥ ብላ፡፡ ጓደኞቿን ተሰናብታቸው ከአንተነህ ጋር ስትሄድ በላይሁንን እያሰበችው ነበር።

"ዛሬ ስብሰባ ብጋብዝሽስ? ትልቅ ስብሰባ አለን" አለ ሰዓቱን እየተመለከተ።

"ደስ ይለኛል" አለችው በላይሁን የጋበዛትን ስብሰባ እያስታወሰች።

ትክሻዋን እንዳቀፋት ቀኖቻቸውን ይዘው የቢስ መብራትን አቀበት ወጥተው ሲኒማ ኢትዮጵያ ሲደርሱ ምንም አልታወቃቸውም፡፡ እንዴ ፖለቲካውን መለስ ብሎ ደግሞ ፍቅሩን ሲገልጽላት የምታዳምጠው በተመስጦና በደስታ ነው፡፡ ስትሰማው ብትውልና ብታድር እንኳ በፍጹም አይሰለቻትም፡፡ ሲኒማ ኢትዮጵያ ሲደርሱ ቆም አለና ተመለከታት፤ ገጽታው በፈገግታ እንደፈካ ነው፡፡

"ዛሬ መልካም ፈቃድዎ ሆኖ የመጀመሪያውን የኬክ ግብዣ እንዳደርግ ይፈቀድልኝ ይሆን?" አለ ድራማ እየሠራ በሚያስመስለው መልኩ፡፡

"አድርገውት ነው" አለችው ሳቋን መቆጣጠር እያቃታት፡፡ መቼም ወጣትነትና ሳቅ አብረው ናቸው፤ በወጣትነት የማያስቀው ሁሉ ያስቃል፡፡

ክሪየዚስ ኬክ ቤት ገቡና ፊት ለፊት ተቀመጡ፡፡ "አቦ እንዲህ ለብቻሽ እስካገኝሽ እንዴት ቸኩዬ ነበር" አለ እጇን ይዞ እያሻሸ፡፡ ድንገት የተፈጠረ ዝምታ በመሃላቸው ገብቶ ለአፍታ ያህል አለያያቸው፡፡ አንተነህ በዝምታ ዓይን ዓይኗን ተመለከታት ጎንበስ አለች፡፡

"በጣም አዝናለሁ ፍርዬ" አለ ከጥቂት ዝምታ በኋላ፡፡ ውስጧን ድንጋጤ ተሰማት "ለምኑ?" ብላ ለመጠየቅ ቀና ስትል "ለሆነው ነገር ሁሉ በጣም አዝናለሁ" አላት በድጋሚ፡፡ ስለምን እየተናገረ እንደሆነ ገባት፡፡ ሁሉም ነገር በዐይነ ህሊናዋ መጣባት፤ እርሱ ወደ አዲስ አበባ በተመለሰ ሰሞን እዛ ዘመቻ ጣቢያ የገጠሟትን ሁኔታዎች ማስታወስ ባትፈልግም በሀሳቧ ወደዚያው ኮበለለች።

አንተነህ ወደአዲስ አበባ በተመለሰ በማግስቱ ዘማቾቹ ራቅ ወደአለ የገበሬ ማህበር መሄድ ነበረባቸው፡፡ ከሴቶች ሩት፣ ፍሬሕይወትና ኤልሳ ነበሩ ለሥራው የተመደቡት፡፡ የገበሬ ማህበሩ አመራር አባላት ተሰብስበው ስለጠበቋቸው ሥራቸውን የጀመሩት እንደደረሱ ነበር። አጠር ያለው ስብሳባ ሲያበቃ አዝማች መምህሩና አንደኛው ዘማች ወደ ሊቀመንበሩ ቤት ሄዱና



እነፍሬሕይወት እነርሱን ለመጠበቅ ጥላ ቢጤ ፈልገው ተቀመጡ፡፡

"አንቺ እንዴት ሳትሄጂ ቀረሽ" አላት አንደኛው ልጅ።

"የት ነው የምሄደው?" አለችው።

"አዲስ አበባ ነዋ።"

"ሌሎችስ መቼ ሄዱ?"

"የአንቺንና የሌሎቹን ምን አንድ አደረገው?" አለ ሌሎቹን በመመልከት እየተሳሳቁ፡፡ ፍሬሕይወት ዝም አለች ከኤልሳ ጋር ዐይን ለዐይን ተገናኙ፡፡

"ጨዋራሽን ግን ተሻለሽ?"

"ዛሬ አንተ ልጅ ምን ሆነሃል የመቼውን ነው የምትጠይቀኝ?" አለችው በመገረም።

"የአንቺ ጨዋራ ግን አሪፍ ነው ባክሽ በአንድ ጊዜ ዳነልሽ" ንግግሩ ምጸት አዘል ነው።

ስለምን እንደሚያወራ ገብቷታል። በአንድ ወቅት ጨዋራዋን ታማ የበላችው ሁሉ አልረጋ እያለ ወደላይ ይላት ነበር። አርባምንጭ ሆስፒታል ገብታ ለተወሰኑ ቀናት ከተኛች በኋላ አዲስ አበባ ሄዳ እንድትታከም ተደረገ። በዚያ ጊዜ ብዙ ነገር ተወርቶባት እንደነበረ ጓደኞቿ ነግረዋታል።

"ምን ለማለት ፈልገህ ነው ግን? ለምን ቁጥቋጦውን ትዞረዋለህ የምትፈልገውን በግልጽ አትናገርም?" አለች በስጨት በማለት፡፡ ሊሎቹ ሳቁ፤ ሳቃቸው ደግሞ የበለጠ አናደዳት፡፡ ምን ለማለት እንደፈለገ እነርሱም በሚገባ ገብቷቸዋል፡፡

"ለማያውቅሽ ታጠኝ ባለፈው አዲስ አበባ ሄደሽ ምን አድርገሽ እንደመጣሽ የማናውቅ ይመስልሻል? "ጨጓራሽን" በሚገባ ታክመሽ አስወጥተሽው መምጣትሽን አናውቅማ!" አለና በሳቅ ተንተከተከ ሌሎቹም አጀቡት፡፡

እንባዋ በዓይኖቿ ሲሞላ ላለማልቀስ ታገለችው፡፡ ውስጧ በንዴት ድብን አለ፡፡ የምትለው ግን አልነበራትም፤ ደግሞስ ምን ማለት ያስፈልጋል?" ተብሎ ያበቃውን ነገር እርሱ ፊት ለፊት እንዳፈረጠው በሚገባ አውቃለች። የውስጥ ሃዘኗን ገጽታዋ በሚገባ እንዳንፀባረቀ የተሰማት ልጆቹ ቀስ በቀስ እየተነሱ ሲሄዱ ነው፡፡ ልጁ ሲነሳ ወደጆሮዋ ጠጋ ብሎ፤

"ዛሬ ግን አልምርሽም ማን እንደሚደርስልሽ ይታያል" አላትና ሄደ፡፡ ፍሬሕይወትና ኤልሳ ብቻቸውን ቀሩ፡፡

"መሄዴ ነው" አለች ፍሬሕይወት እየተነሳች።

"ወዴት" አለች ኤልሳ ደንግጣ።

"ወደጣቢያችን ነዋ።"

"እንዴ! ብቻችንን?"

"ይሻላል፤ አልምርሽም ብሎኛል።"

"ታዲያ መንገዱን እናውቀዋለን?"

"አይጠፉንም" አለች ዕንባዋን እየጠራረገች።

ፍሬሕይወትና ኤልሳ መንገድ ጀመሩ፡፡ ቀጭኑን የጫካ መንገድ ተከትለው ፈጠን ባለ ርምጃ ተራመዱ፡፡ ጫካው በጣም ያስፈራል ወደመሀል ሲዘልቁ ደግሞ ቀጫጭኖቹ መንገዶች በጣም ተበራከቱ፡፡ ትክክለኛው መንገድ የትኛው እንደሆነ ማወቅ አቃታቸው በግምት አንደኛውን ተከተሉ፤ እንደገና ደግሞ ሌሎች ቀጫጭን መንገዶች... አቅጣጫቸውን መሳታቸውን ገብቷቸዋል



ግን ወደመጡበት እንኳ መመለስ የሚታሰብ አይደለም፡፡ ጊዜው እየመሸ ነው፡፡ ጫካው የበለጠ አስፈሪ እየሆነ ይሄዳል ልቦቻቸው መምታት ጀምረዋል፡፡ ድንገት የሰዎች ንግግር ሰሙ፤ የወንዶች ድምጽ ነው፡፡ ሁለቱም በድንጋጤ ተያዩ፤ አጠገባቸው በነበረው ጎርፍ የሸረሸረው ቦይ ውስጥ ዘለው ገቡ፡፡ የሰዎቹ ድምፅ በጣም እየቀረበ ሲመጣ በፍርሀት ተፋጠጡ ትንፋሻችን አጥፍተው ተሸጎጡ፡፡ ሰዎቹ ሲያልፏቸው "ተመስገን" አሉ፡፡ ጥቂት ቆየት አሉና ከቦዩ ውስጥ ወጥተው ሰዎቹ የሄዱበትን አቅጣጫ ተከትለው መሄድ ጀመሩ፡፡ ወዴት እየሄዱ እንደሆነ ግን በፍጹም ማወቅ አልቻሉም፡፡

በጫካው ውስጥ በመባዘን ጊዜው ነጎደ ፀሐይዋ አየጠለቀችና የጫካው ውስጥ ድንግዝግዝ እያለ ሲሄድ የልቦቻቸው ምት ጨመረ፡፡ ግራ ግብት ሲላቸው ቆመው መተያየት ሆነ፤ ሁለቱም እንዳለቀላቸውና የአውሬ እራት መሆናቸውን አመኑ፡፡ ፍሬሕይውት ኤልሳን ትኩር ብላ እያየቻት የጥፋተኝነት ስሜት ተሰማት ይህ ደግሞ የበለጠ እንድታዝን አደረጋት፤ እንባዋ ከየት መጣ ሳትለው ተከለበሰ፡፡ ኤልሳ ያ ሁሉ ቀልድና ጨዋታዋ ጠፍቶባት አመድ መሰለች፡፡ ሳያስቡት ተቃቅፈው፣ ተላቀሱ፣ ተስፋ መቁረጥ መንፈሳቸውን አደነደነው፡፡ ፍሬሕይወት በውስጧ የነበረው ፍርሃት ጠፍቶ ቆራጥነት የተተካበት መሰላት፤ እንደተቃቀፉ ጫካው መሀል ከቆሙ ደቂቃዎች አለፉ፡፡

ድንገት ራቅ ያለ የመኪና ድምጽ ተሰማቸው፡፡ ሁለቱም የድምጹን አቅጣጫ ተከትለው ሮጡ፡፡ ጨለማው ለዓይን እየያዘ ቢሆንም ሮጡ፡፡ የነበሩበት ቦታ ከዋናው መንገድ መቶ ሜትር እንኳ የሚሞላ አልነበረም በፍጹም ሳያስቡት መንገዱ ላይ ደርሰው የሞት ሞታቸውን እጆቻቸውን አውለበለቡ፡፡ የጭነት መኪናው ጎማዎቹን አንሳጦ ቆመ፡፡ ሾፌሩ መኪናው ውስጥ እንዲገቡ የጋቢናውን በር ከፈቱላቸው፡፡ ገብተው ሲቀመጡ ሁለቱም ሆድ ባሳቸው፤ እንደገና ተቃቅፈው መላቀስ ጀመሩ፡፡

"አፈር በሆንኩት ልጆቼ፤ አሁን ይሄ መንግስት እግዚያብሔር ያወድለታል" አሉ ሾፌሩ ከልባቸው፡፡ የልጆቹን ማንነት መጠየቅ አላስፈለጋቸውም። የልብሶቻቸው ቀለም፣ ኬፖቻቸውና

ከፊትለፊት ያለው ጽሑፍ ማንነታቸውን ያስረዳሉ፡፡ ዘመቻ ጣቢያ ደርሰው ከመኪና ሲወርዱ ሁሉም ሰው እነርሱን ፍለጋ ወጥቶ ጥቂት ሰዎች ብቻ መንገዱ ላይ አገኙ፡፡ ለፍለጋ የወጡትን ለመመለስ ተሯሯጡ...

አንተነህ እጇን ጠበቅ አድርጎ ሲይዘው፤ ከእንቅልፏ የነቃች ይመስል ከገባችበት ትውስታ ወጣችና "ግን'ኮ አንተ ምንም አላደረግህም" አለችው።

"አድርጌያለሁ እንጂ ፍርዬ ቅርበታችን እጅግ የጠበቀ ባይሆን ኖሮ ያን ሁሉ ሊያስቡ አይችሉም ነበር፡፡ ለማንኛውም እርሸው" አለና እጇን ጎተት አድርጎ ሳመው፡፡ ከምኔው ወሬውን እንደሰማው ደነቃት፡፡ ከዓይኖቹ ውስጥ ፍቅርና ስስት ይነበባል፤ በእርሷም ልብ ውስጥ ያለው ይሄው ነው፡፡ እጇን እንደገና ሳመው፡፡

"ፍርዬ! በጣም እወድሻለሁ!" አላት፡፡ መቼም ፍቅሩን ለመግለጽ ስስት የለበትም።

"እኔም በጣም እወድሃለሁ" አለችው ለመጀመሪያ ጊዜ፤ ከገጽታው ላይ እርካታን ያነበበች መሰላትና መንፈሷ በደስታ ተሞላ፡፡

ልቦቻቸው የተጣመሩ መሰላት፡፡ ልክ እንደዘመቻ ጣቢያው ሁልጊዜም አብረው እንዲሆኑ ተመኘች፤ ሳታስበው በረጅሙ ተነፈሰች። እንዲህ ጠረጴዛ በመሀላቸው ሆኖ ሳይሆን እንደዘመቻ ጣቢያው በነጻነት ጥላው ስር ጥግትግት ብለው እንዲቀመጡ ተመኘች፡፡ አንተነህ ሰዓቱን ተመለከተ፤ ከቀኑ አስር ሰዓት ሆኗል፡፡ "ፍርዬ ትቸኪያለሽ?" አላት ድንገት።

"እስከ አስራ ሁለት ሰዓት መቆየት እችላለሁ፤ ስብሰባው በስንት ሰዓት ነው" አለችው በሀሳቧ ሲመላለስ የነበረውን ያወቀባት መስሏት ደንገጥ አለች፡፡

"ለዛሬ ስብሰባው የኔና ያንቺ ብቻ እንዲሆን ብናደርገውስ?" አላት እየሳቀ።



ከክሪያዚስ ወጡና ታክሲ ያዙ፡፡ ታክሲው ውስጥ ከገቡ በኋላ ምንም አልተነጋገሩም ሁለቱም በየሃሳባቸው ተመሰጡ፡፡ አራት ኪሎ አማኑኤል ባፕቲስት አጠገብ ሲደርሱ ከታክሲ ወርደው ከጥቂት እርምጃዎች በኋላ ከመንገዱ ባሻገር ካለው አፓርትመንት ውስጥ ሲገቡ አንገቷን አቅፎ ጉንጯን ሳማት፡፡ በአፓርትመንቱ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ሲደርሱ ኪሱን ዳበሰና ቁልፍ አወጣ፡፡ በኮሪዶሩ ላይ ካሉት በሮች አንደኛውን ከፈተና "ቤት ለእንግዳ" አላት፤ እንድትገባ በእጁ እያመለከታት፡፡

ምንም አላቅማማችም፤ ወደውስጥ ገባች፡፡ ክፍሉ በጣም ንጹህ ነው፡፡ ቀላል ግን የሚያማምሩ ዕቃዎች አሉበት፡፡ አልጋው ላይ የተነጠፈው የአልጋ ልብስ ውብ ነው፡፡ ከአልጋው አጠገብ በስተግራ በኩል ያለው ኮመዲኖ ላይ የተቀመጠው የራስጌ መብራት በልዩ ጌጥ ተሠርቷል፡፡ በስተቀኝ በኩል ባለው ኮመዲኖ ላይ ደግሞ ትልቅ ቴፕ ሪከርደር ጉብ ብሏል፡፡ ከአልጋው ትይዩ ባለው ግድግዳ ጥግ አንድ መለስተኛ ጠረጴዛና ሁለት ወንበሮች ተቀምጠዋል፡፡ የሌላኛው ግድግዳ ሙሉ ስፋት የተያዘው በቁምሳጥንና በረጅም መጻሕፍት መደርደሪያ ነው፡፡ መደርደሪያው ኮርኒሱን ሊነካው ምንም አልቀረውም ጥቅጥቅ ብሎ በመጻሕፍት ተሞልቷል፡፡ በአንደኛው የቤቱ ማዕዘን በኩል ደግሞ በነጭ ጨርቅ የተሸፈነ ጠረጴዛ አለ፡፡

"የጓደኛዬ ቤት ነው፡፡ እንደራስሽ ቤት ልትቆጥሪው ትችያለሽ" አላት እጇን ያዝ አድርጎ አልጋው ላይ እያስቀመጣት፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርሃት ቢጤ ልቧን ጨረፍ አደረገው፡፡ ራሷን ታዘበችው ያለምንም ማንገራገር አንተነህን ተከትላ መምጣቷ ገረማት፡፡ በእርግጥ አንተነህን እንድታምነው፤ ያለወቀቱና ያለፍላጎቷ ምንም እንደማያደርግ እርግጠኛ እንድትሆን ያደረጓት ብዙ ምክንያቶች አሏት፤ ቢሆንም ግን ስህተት መሆኑን ለራሷ ነገረችው፡፡

አንተነህ ጃኬቱን አውልቆ ወንበሩ ላይ አስቀመጠ፤ የሸሚዙን እጅጌ ጠቅለል አደረገና በጠረጴዛው ላይ የተሸፈነውን ጨርቅ ገለጠ፡፡

"ምን ልታደርግ ነው?" አለችው

"ለእንግዳዬ ሻይ ላፈላ" አለ እየሳቀ

"አሁን አይደል የጠጣነው፤ እንግዳህ ሻይ አያስፈልጋትም፤ ይልቅስ እንጫወት ሌላ ቀን ታፈላልኛለህ።"

"እና በባዶ ቤት ነው የምንጫወተው?"

"ምን አስጨነቀህ?" አለችው። ድንገት አቀፈና አልጋው ላይ አስቀመጣት። የልቧ ምት ከመቅሰፊት ሲጨምር ተሰማት። የአንተነህ ሰውነት እንደተጣደ ብረትድስት መፋጀት ጀምሯል። ጥብቅ አድርጎ አቀፋት ሁለመናዋን ሳማት፤ አጸፋውን ልትመልስለት የሚያስችል አቅም ግን አልነበራትም። አንዳች ኃይል በቁጥጥር ስር ያዋላት እስኪመስላት ድረስ ሰውነቷ ሁሉ ዛለባት። አንተነህም ልክ እንደእርሷው በዚያ ኃይል ቁጥጥር ስር ውሏል፤ ልዩነታቸው እርሱ ስሜቱን ለመግለጽ ብርታት ያለማጣቱ ነው።

"ፍርዬ ምን ላድርግሽ? የምትወደጂ እኮ ነሽ" አለ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ።

"እንዴት ደስ ይላል" አለችው በደከመ ድምጿ።
"በጣም! ፍርዬ እንዴት እድለኛ ነኝ? ለኔ የተፈጠርሽ እስኪመስለኝ ድረስ እንድንከባከብሽ እንድጠብቅሽ ኃላፊነት ያለብኝ ሆኖ ይሰማኛል። እናም ከድል በኋላ በአንድ ጣሪያ ስር መኖር እስከምንጀምርባት ዕለት ድረስ ላልነካሽ ቃል እገባለሁ" አለና እንደገና ጥብቅ አድርጎ አቀፋት።

"እስኪጋብቻ ዕለት!" ትርጉሙን በውስጧ ደገመችው። መንፈሷን ዘና አደረገላት።

"እምንሃለሁ!" አለችው ዕድለኛነት እየተሰማት።



ጊዜው እንዴት ይሮጣል። ድንገት ቀና ስትል የግድግዳውን ሰዓት ተመለከተችው፤ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ይላል።

"አሁን መሄድ አለብኝ" አለች ምንም ሳታመነታ።

"አስመሽሁብሽ አይደል?" አለ እንደገና አቅፎ እየሳማት

"ቤቴ ስሄድ እንደምትናፍቀኝ ግን ታውቃለህ?" አለችው ጫማዋን እያጠለቀች። ያልጠበቀችው ፍጹም ነፃነት ተሰምቷታል፤ ለአንተነህ ስሜቷን ሁሉ በነፃነት መግለጽ እንዳለባት የሚገፋፋት አንድ ኃይል ያለ መሰላት።

"ለዚህ እኮ ነው ፍርዬ ታድያለሁ የምልሽ እኔም በጣም ትናፍቂኛለሽ። በልቤ ውስጥ ያለውን ፍቅር እንዴት አድርጌ ላሳይሽ? ልቤ የደነገጠው በመጀመሪያው ዕለት ቢሆንም በልቤ ውስጥ ልዩ ቦታ እንዲኖርሽ ያደረገሽን ስብእናሽን ለመረዳት ምንም ያህል ጊዜ አልወሰደብኝም፤ ምንም ነገር ያላጎደፈሽ ንጹህ እኮ ነሽ ፍርዬ። ታዲያ ብወድሽ ማን ይፈረድብኛል?" አላት እንደገና እቅፉ ውስጥ አስገብቶ ጥብቅ አድርጎ እያቀፋት።

* * * *

ወይዘሮ ስርጉት ፍሬሕይወት ከዘመቻ ስትመለስ የጠላ ንግዱን አቋርጠው በበላይሁን እናት አማካኝነት ለአንድ ትልቅ ሆቴል እንጀራ ማቅረብ ጀምረው ነበር። እናም የሚያቋርጥ ገቢ በመኖሩ በቤታቸው ውስጥ የሚያስጨንቅ ሁኔታ አልነበረም። ሰሞኑን ግን ሀሳብ እየተጫናቸው ተቸግረዋል። ዘመቻ ያቋረጡ ዘማቾች ተመልሰው ትምህርት ቤት የመግባት ዕድል እንደማይኖራቸው መንግሥት የሰጠውን መግለጫ እየሰሙ ጭንቅ ብሏቸዋል።

እንዲህ በሀሳብ የሚያብሰለስላቸውን ጉዳይ ለፍሬሕይወት ማዋየት ግን ከብዷቸዋል።

"ወይጉድ! በሰላም የመጣችልኝልን ልጅ ሂጂ ብዬ አንድ ነገር ብትሆንብኝስ?" ይላሉ ገና ሀሳቡ ወደአእምሮአቸው ሲመጣ።

"አንተ ቅዱስ ገብርኤል ይህን አልሽ አትበለኝ! ልጇ ትምህርቷ እንዳይጨናገፍባት እንጂ ለእኔማ እዚህ መሆኗ ይጠቅመኛል እንጂ..." ይላሉ እቤት ውስጥ የምትሸፍንላቸውን ጉዳዮች ሲያስቡ።

ወይዘሮ ስርጉት ልጆቻቸውን ማዘዝ አይጠበቅባቸውም አንዳንዴ ልጆቹ ኃላፊነታቸውን አውቀው ያለምንም ትእዛዝ መሥራታቸው እስከሚገርማቸው ድረስ ይሆንባቸዋል። ትንሹ ሮቤል እንኳን ሳይቀር የሥራ ድርሻውን አውቆ ያለምንም ጭቅጭቅ ያከናውናል። ይህንን ሲመለከቱ፡ "ምን ነበረበት ይህንን መመልከት ቢችል ኖሮ!" ይላሉ ባለቤታቸውን እያስታወሱ።

"ደግ ሰው አይሰነብትም የሚባለው እውነት እኮ ነው" ይላሉ የፍሬሕይወት እናት የባለቤታቸውን ያልታሰበ ሞት ባስታወሱ ቁጥር።

"እንዲያው ጊዜው ከመቼው ነው የሚደርሰው?" አሉ ደግሞ የባለቤታቸው ሙት ዓመት መቃረቡን አስበው። ጣቶቻቸውን ቆጣጠሩና ቀናቱን አስልተው "ወይጉድ! አስራአምስት ቀን ብቻ ነው የቀረው" አሉ ለሰው የሚያወሩ ይመስል።

አጠገባቸው የተኛውን ሮቤልን እንዳይረግጡት ተጠንቅቀው ከአልጋቸው ወረዱና ልብሳቸውን ለባብሰው ወጡ። ገና ከጠዋቱ አሥራሁለት ሰዓት ባይሆንም ሚሚ ተነስታ ቁርስ እየሠራች አገኟት። ጠረጴዛው ላይ የተደረበውን እንጀራ ሲመለከቱ፡ ደግሞ ፍሬሕይወት ሳትተኛ ማደሯን አስበው "ወይኔ ልጄን ተገትራ ነው ያደረችው ማለት ነው" አሉ። ፍሬሕይወትን ሊያዩአት ፈለጉ፤ ፍሬሕይወት ብርድልብስ እንኳ አልለበሰችም፤ ከላይ ጋደም እንዳለች አገኟት።

"ምነው ሚሚዬ እንዲህ ስትተኛ ዝም አልሻት" አሉ የለበሱትን ጋቢ ለፍሬሕይወት እያለበሷት።

"ሞቀኝ አለችኝ እኮ እማ!" አለች ሚሚ።



ፍሬሕይወት ተኝታ አረፈደች፤ እናቷ ለአባቷ ቁርባን የሚሆነውን ጠላ ለማዘጋጀት ጌሾውን ገብሱንና በቆሎውን አወጣጥተው መለቃቀም ጀመሩ።

የበላይሁን እናት ከቤት ሲወጡ የፍሬሕይወትን እናት እደጅ በማግኘታቸው "ምነው ስርጉት በጠዋት? ምን እያደረግሽ ነው ደግሞ መቼም የምትሠሪው አታጭ" አሏቸው።

"ምን እሠራለሁ ብለው ነው? ትዝ ቢለኝ ለቁርባኑ ጥንስስ ልጠንስስ ብዬ ነው" አሉ የፍሬሕይወት እናት።

"ውይ በሞትኩት የኔ ነገር፤ ለካ ቀኑ እየደረሰ ነው። ጊዜው እንዴት ይሮጣል?" አሉ የበላይሁን እናት ከወይዘሮ ስርጉት አጠገብ እየተቀመጡ።

"የጊዜውማ ነገር ምኑ ቅጡ፤ ዓመቱ የተጀመረ ሳይመስል ያልቃል" አሉ ወይዘሮ ስርጉት በሀሳባቸው እነፍሬ ከዘመቻ የተመለሱበትን ጊዜ እያሰቡ። "ይሄው ልጆቹስ ከዘመቻ ከተመለሱ ሶስት ወር አለፉቸው አይደል?" አሉ ሌሊቱን ሲያሳስባቸው ያደረው ጉዳይ ከአእምሮአቸው አልጠፋ ብሎ።

"ለመሆኑ በላይሁን ምን እያለ ነው?" አሉ ደግሞ ቀጠል አድርገው።

"ያው አልሄድም እንዳለ ነው። ትናንት ሬዲዮው ይህንኑ ሲያወራ ነው የዋለው፤ ከዘመቻ ለኮበለሉ ዘማቾች መንግሥት ይቅርታ ማድረጉንና ወደዘመቻቸው እንዲመለሱ ዕድል የተሰጣቸው መሆኑን ሲያወራ ነበር። ልጆቹ ግን ልባቸው ድንግጥ አላለም፤ ለበላይሁን ይህንኑ ብነግረው "አላደርገውም ተመልሼም ዘመቻ አልሄድም" አለኝ።" አሉ የበላይሁን እናት።

"ልጆቹ እንደሆነ ግንባራቸውን ማጠፍ አይሆንላቸውም፤ እስኪ እስከውዲያኛው ትምህርት ቤት መግባት እንደማይችሉ እየተነገረ እንዲህ ድርቅ ማለት ምን ይሉታል?" አሉ የፍሬሕይወት እናት ግራ ገብቷቸው።

የጀመሩትን ሥራ አጠናቀው ወደቤት ሲገቡም ፍሬሕይወት አልተነሳችም፡፡ እንጀራ ስትጋግር ለብሳው የነበረውን ልብስ እንኳ ሳትቀይረው፣ ሰውነቷንም ሳትታጠብ መተኛቷን በማየታቸው ውሃ አሙቀው አስነሷት፡፡

ሰውነቷን ተጣጥባ ልብሷን ስትቀይይር ቀለል ብሏት ስትነቃቃ "ልጆቹስ?" አለች ቤቱ ጭር ብሎባት።

"ልጆቹ እኮ ተማሪዎች ናቸው፣ ፍርዬ የጨነቀኝ የአንቺ ነገር ነው፡፡ እስከመቼ ለእኔ እንጀራ ጋጋሪ ሆነሽ እንደምትዘልቂ ሳስበው..." ሲያስጨንቃቸው የነበረውን ጉዳይ ድንገት አንስተው ሀሳባቸውን ነገሯት።

"ምነው እማ! ስንት ጊዜ ተነጋግረንበት የለም እንዴ?፡፡ትናንት መንግሥት በሬዲዮ በመናገሩ ምን አዲስ ነገር አለው፣ ደግሞስ ይሄ በእኔ ብቻ የሆነ አይደል ሌሎቹ እንደሚሆኑት እሆናለሁ።"

"ምናለ ተመልሳችሁ ብትሄዱ መንግሥት እንደሆነ ጨክኗል፣ ዘመቻውን ያላጠናቀቁ ትምህርት ቤት እንደማይገቡ እኮ ነው የተናገረው። አንዳንዶቹም እኮ እየተመለሱ ሄደዋል፡፡ መቼስ ዕድሜ ልክ የትምህርት ዕድል ከማጣት..."

"እማ እኔ በፍጹም አላደርገውም፣ ላንመለስ ቃል ገብተን ነው የመጣነው እኔ ደግሞ ያን ቃል አፍርሰው ከሚመለሱት ጋር መወገን አልፈልግም፡፡ ዕድሜ ልክ የትምህርት ዕድል የማጣበት ምክንያትም አይኖርም ደርግ እንደሆነ በሕዝባዊ አመፅ መውደቁ አይቀርም..."

"በይ ተይው ያንን ስብከትሽን ደግሞ ልትጀምሪ ነው፡፡ ቡና ጠጡ በይልኝ፣ እግዚአብሔር ልባችሁን እስኪመልሰው ምን ማድረግ ይቻላል" አሉ የፍሬሕይወት እናት ሁሌም የፖለቲካ ቃላት መጠቀም ስትጀምር እንደሚያደርጉት፡፡



የፍሬሕይወት እናት የዘወትር ቡና አጣጭዎች ሁለት ናቸው፡፡ የበላይሁን እናትና እትዬ ደብሬ ብቻ! ሌሎቹ ጎረቤቶች የሚጨመሩት ለየት ያለ አጋጣሚ ሲኖርና ለበአል ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ ሁለት ሴቶች ጋር አንድም ቀን ለየብቻቸው ቡና ጠጥተው አያውቁም፡፡ እትዬ ደብሬ ልጅ ስለሌላቸው በጣም ያዝናሉ፣ ጎረቤቶቻቸው ያልተሳሉበት ታቦት የላቸውም፣ ስሜታቸውን ለመጠበቅ የሚያደርጉትም ጥረት ከፍ ያለ ነው፣ ስለልጅ ሲነሳ እንኳ በጥንቃቄ ነው። የፍሬሕይወት እናት በውስጣቸው ሊያወጡት ባይችሉም ስለዘመቻውና ስለትምህርት ማውጠንጠናቸውን ባያቋርጡም ለእትዬ ደብሬ የሚጥም ጨዋታ መጫወት ነበረባቸው።

* * * *

በላይሁን እንድትቀሰቅሰው የሞላት ሰዓት ስትጮህ ከአልጋው ላይ እንዴት ተፈናጥሮ እንደወረደ ሳይታወቀው ክፍሉ መሃል ቆሞ ራሱን አገኘው። የተኛው ለጥቂት ሰዓታት ብቻ ነው፣ ዐይኖቹን ጠራረገና ተመልሶ አልጋው ላይ ተቀመጠ። ለምንድን ነበር ሰዓቷን የሞላት? ለማስታወስ ሞከረ፣ ምንም ትዝ ሊለው አልቻለም። በጀርባው ተንጋለለና ኮርኒሱ ላይ አፈጠጠ፣ ደቂቃዎች አለፉ።

ለምን ሰዓት እንደሞላና ሌሊት ሊነሳ እንደፈለገ ትዝ አለው። በርካታ ሥራዎች ከፊቱ ተደቅነዋል፣ የኢሕአፓን የወጣት ክንፍ የማጠናከር ሥራው በከፍተኛ ፍጥነት እንዲቀጥል የሥራ ክፍፍል ተደርጓል። በየቀበሌው የተቋቋሙ ወጣት ማህበራት የያዙትን መድረክ ብዙሀኑን ወጣት ለመቀስቀና ወደመኢሶንና ወደሌሎቹ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳይገቡ ለማድረግ እንዲጠቀሙበት፣ እስከአሁን ባሳዩት እንቅስቃሴ መስመራቸውን የለዩ ወጣቶችን ደግሞ በህቡዕ የተደራጀው የኢሕአፓ ወጣት ሊግ አባል እንዲሆኑ የመመልመል፣ የተመለመሉትን ወጣቶች ደግሞ በየአቅራቢያዎቻቸው ከሚገኙ ሕዋሶች (ህቡዕ የጥናት ቡድኖች) ጋር የማገናኘት ሥራ እንዲጠናከር መመሪያ ወደታች የማስተላለፍና ለየጥናት ቡድኖቹ የሚሰራጩትን ጽሑፎች የማዘጋጀትና የማሰራጨት ሥራ ሁሉ እፊቱ ተደቅኗል።

ለወጣት ሊግ ኮሚቴ ስብሰባ በተሰጠው የመወያያ ርዕስ ላይ መዘጋጀት፣ ነገ በአንድ ቀበሌ ወጣት ማህበር በተጠራ ስብሰባ ላይ በተጋባዥነት የሚያቀርበውን ጽሑፍ ማንበብና ማጠናቀቅ፣ የተመለመሉ ወጣቶችን ከየአካባቢያቸው ሕዋሶች ጋር እንዲገናኙ ለማስቻል የሚስጥር መገናኛዎችን መጻፍ... አስቦ ለመጨረስ ጊዜ የለውም፤ ከተጋደመበት ተነሳና ከግድግዳው ጥግ ወዳለችው ትንሽ ጠረጴዛ ሄደ። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆኗል፤ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የተመለከተው የሻዩን ፒርሞስ ፍላስክ ነው፤ እህቱ በምንም ዓይነት እንድታደርግለት የጠየቃትን ረስታ አታውቅም፤ የሚፈልገውን ነገር እንደሚወደው አድርጋ ስታቀርብለት ይገርመዋል። "እህቶች ሁሉ እንደ ሜሮን ይሆኑ?" ይላል አንዳንዴ እየገረመው። የሚወደውን ሻይ እየጠጣ ሥራውን ጀመረ።

አንገቱን ካቀረቀረበት ሳያቀና ለወጣት ማህበር የሚያቀርበውን ጽሑፍ አጠናቀቀና ተንጠራራ። ከወንበሩ ላይ ተነስቶ በመኝታ ክፍሉ ውስጥ ጥቂት ተንጎራደደና ከትንሿ የመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ ሁለት መጻሕፍት አንስቶ ተመልሶ ተቀመጠ። ከሚፈልገው ርእስ ላይ ጥቂት አነበበና እንደገና ተነስቶ ወደ መጽሐፍ መደርደሪያው ሄደ፤ መዝገበ ቃላት አውጥቶ ተመለሰ። የሚያነበው መጽሐፍ ዲያሌክቲካል ማቴሪሊዘም ነው፤ ሁሌም ባነበበው ቁጥር ይጠጥርበታል፤ ግን አይተወውም ያነበዋል። የወቅቱ መሰረታዊ ፍልስፍና ስለሆነ በሚገባ አብጠርጥሮ ለመረዳት የወጣት ሁሉ የንባብ አቅጣጫ ወደዚያው ሆኗል። የወሰደውን ማስታወሻ አስተካክሎ ጻፈና ሰዓቱን ተመለከተ። ለአስራ ሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ይላል።

እየተጣደፈ የሚስጥር መገናኛዎቹን መጻፍ ጀመረ። በላይሁን ሀሳብ ተቸግሮ አያውቅም፤ በአንድ ጊዜ በርካታ የመገናኛ ኮዶችን የመጻፍ አቅም አለው፤ ስለሆነም ነው ብዙውን ጊዜ የኮሚቴው አባላት እርሱ እንዲሠራ የሚለቁለት። የመጨረሻውን ጽፎ ሲጨርስ ከጠዋቱ አሥራሁለተ ሰዓት ከሩብ ሆነ፤ አነበበውና ፈገግ አለ፤ ሁልጊዜም የሚጽፋቸው ነገሮች ያስደስቱታል።



"መፋቂያሽ ከየት መጣልሽ?"

"ከጃማይካ!" ይላል በመጨረሻ የጻፈው የመገናኛ ኮድ።

ሁሉንም በየሥፍራቸው አስቀመጠና የሌሊት ልብሱን አውልቆ ቱታውን አጠለቀ። እየተቻኮለ በቧንቧው ውሀ ፊቱን ተጣጠበና በሩጫ ከጊቢ ወጣ፤ ወደተለመደው የጠዋት ስፖርት።

* * * *

ቀጭኑ የስልክ ድምጽ ከነበረበት ሀሳብ መንጥቆ ሲያወጣው ምን ማድረግ እንደነበረበት የተረዳው ወዲያውኑ አልነበረም። ስልኩ በድጋሚ እስከሚጠራ ድረስ ከሀሳቡ ሙሉ በሙሉ አልተመለሰም። ስልኩ ደጋግሞ ሲጮህ አነሳና "ሄሎ!" አለ።

"ተኝተሃል እንዴ?" የሚል ድምጽ ተሰማው። ድምጹን አልተጠራጠረም። ሄዋን ነች።

"ኧረ በፍጹም!" አላት ሰዓቱን ተመለከቶ። ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ሆኖአል።

"ጊዜ ካለህ ልንገናኝ እንችላለን?" አለችው።

"በስንት ሰዓት?" አለ አንተነህ ከፍሬሕይወት ጋር በሰባት ሰዓት ያለውን ቀጠሮ እያሰበ።

"አሁንም ቢሆን ይሆናል"

"ያቆየናል?" ሌላ ጥያቄ አስከተለባት።

"ምነው አንተ እንዲህ ጥያቄ አበዛህ?" አለችው ሄዋን በስጨት ብላ።

"ስድስት ሰዓት እቤት መመለስ ስላለብኝ ነው" አላት በደፈናው።

"እስከዛም ላያቆይህ ይችላል" አለችው።

ስልኩን ዘግቶ ሲያስበው የነበረውን ጉዳይ ለማስታስ ሞከረ፤ በፍጹም ሊመጣለት አልቻለም። ልብሱን ለባበሰና ሄዋን ለምን እንደፈለገችው ለመገመት እየሞከረ ወደፒያሳ ሄደ።

ፒያሳ ቲ ሩም ሲገናኙ ብቻዋን አልነበረችም፤ ከፍቅረኛዋ ጋር ነች። ገብተው ተደላድለው እንደተቀመጡ ሄዋን መሳቅ ጀመረች፤ አንተነህ ግራ ገባው።

"አንተ እንደማታስታውሰው አውቃለሁ፤ መልካም ልደት" አለችና የተጠቀለለ ነገር ሰጠችው። አንተነህ በድንጋጤ ዐይን ዓዐኗን ተመለከታት።

"እስኪ ክፈተው" አለችው።

በደመነፍስ ከፈተው፤ ራንግለር ሱሪና እጀ ጉርድ ሸሚዝ እንዲሁም ፖስታ አለበት። አንተነህ የሚናገረው ጠፍቶት ሁሉቱንም በየተራ ተመለከታቸው። "በጣም አመሰግናለሁ ሄዊ! ግን ይህንን ሁሉ መልፋት አልነበረብሽም፤ ስሜቴን የምገልጽበት ቃላት የለኝም" አላት ከቆይታ በኋላ።

"ይሄ ለአንተ ለውድ ጓደኛዬ የሚበዛ አይደለም፤ የጓደኝነት ምሳሌዬ ነህ" አለችው።

"በነገራችን ላይ አብረን ፊልም ብንመለከት ደስ ይለኝ ነበር፤ ቀጠሮ እንዳለህ ስለነገርከኝ ላስጨንቅህ አልፈልግም" አለችው ደግሞ።

"ቀጠሮው ሊተላለፍ የሚችል ከሆነ ግን አብረን ብንቆይ እኔም ደስ ይለኛል። ሄዊ ለአንተ ያላትን ቦታ ከጓደኝነት አንጻር ብቻ ለማየት ይቸግረኝ ነበር። ዛሬ ግን ንጹህ የጓደኝነት ፍቅራችሁን እንድቀበል አንዳች ኃይል አስገደደኝ" አለ ልጁ ትኩር ብሎ አንተነህን እየተመለከተው።



"በጣም አመሰግንሃለሁ፤ ዛሬ አብሬያችሁ መቆየት አልችልም፤ እንዲያውም አሁን መሄድ አለብኝ" አለ አንተነህ ሰዓቱን እየተመለከተ።

"ከመሄድህ በፊት ግን ካርዱ ላይ ያለውን ብታነበው ደስ ይለኛል" አለች ሄዋን።

ካርዱን ከፖስታው ውስጥ አወጣና ተመለከተው "የእውነተኛ ጓደኝነት ምሳሌዬ በመልካም ሰውነትህ ደግሞ አርአያ ነህ። መልካም የልደት ቀን እንዲሆንልህ እመኛለሁ" ይላል ካርዱ። ድምጹን ዘለግ አድርጎ አነበበውና ሄዋንን ተመለከታት።

"በጣም ይበዛብኛል ሄዊ! የአንቺ መልካምነትና ጓደኝነት የላቀ ነው" አላት።

ልትሰናበተው ስትነሳ ወንበሩን ገፋ አደረገና ወደእርሷ ተጠጋ፤ አቀፋት "ጓደኝነታችን ለዘላለም ይኑር" አላት ድምጹን ከፍ አድርጎ። ደግሞ ወደፍቅረኛዋ መለስ ብሎ ተመለከተው "በነጻነት የጓደኝነት ስሜታችንን እንድንገላለጽ ስለፈቀድህ በጣም አመሰግንሀለሁ፤ ለሄዊ መልካም የሕይወት ጓደኛ እንደምትሆናት አምናለሁ" አለውና እርሱንም አቅፎ ተሰናበተው።

"ውይ ረስቼው! ነገ በስምንት ሰዓት ውይይት አለ፤ እንደምትመጣ ልጠብቅ?" አለችው ሄዋን።

"ምን ጥያቄ አለው? በደስታ!" አላት። ለበርካታ ጊዜያት እየጋበዘችው ውይይታቸውን ተሳትፏል።

ተለይቶአቸው ሲሄድ ለየት ያለ መንፈስ ነበረው፤ ሄዋን እርሱን ደስ ለማሰኘት ያደረገችውን ሁሉ አደነቀ። ሰዓቱን እንደገና ተመለከተ፤ ገና አምስት ሰዓት ነው። ከፍሬሕይወት ጋር ላለው ቀጠሮ ድፍን ሁለት ሰዓት ይቀረዋል፤ መንገዱ ላይ ወዳለ ሱፐር ማርኬት ጎራ አለ ለፍሬ መስተንግዶ አንዳንድ ነገሮችን ሊገዛ።

* * * *

“ምነው ፀሐዩ በረድ ቢልልሽ ልጄ፤ ሊሊት እሳቱ ቀን ደግሞ ፀሐዩ ይከብዳል እኮ” አሏት እናቷ ፍሬሕይወት በጠራራው ፀሐይ ከቤት ስትወጣ በስስት እየተመለከቷት፡፡

“ሩቅ አልሄድም ቅርብ ነው” አለቻቸውና ወጣች፡፡ ቀስ በቀስ ከቤት መውጣት እየተለመደ ስለሄደ ብዙም የሚያስጨንቅ መሆኑ ቀርቷል፡፡

አስፋልቱን አቋርጣ አፓርትመንቱ ዋና መግቢያ ላይ ስትድርስ ሰዓቷን ተመለከተች፤ አልዘገየችም አልፈጠነችም ልክ በሰዓቱ ነው የደረሰችው፡፡ ቀጠሮ እንደማክበር የሚያስደስታት ነገር የለምና እርካት አለች። ደረጃውን ፈጠን ብላ ወጥታ ገና በሩ ላይ ስትደርስና በሩ ሲከፈት እኩል ሆነ፡፡ “የት ልትሄድ ነበር?” አለችው።

“ልከፍትልሽ ነዋ” አለና እቅፉ ውስጥ አስገባት፡፡ “እንዴት እንደናፈቅሽኝ” አለ ስፍስፍ ብሎ እየሳማት፡፡ “ምን ይሻለኛል ፍርዬ?” አላት እንደገና።

“ምኑ?” አለችው፤ ምን እንደሆነ ግን ገብቷታል።

“አልቻልኩም ፍርዬ! ፍቅርሽና ናፍቆትሽን መቋቋም አልሆነልኝም” አለና እንደገና አቀፋት።

ቤቷ ከመጀመሪያው ቀን የበለጠ አምራለች፤ የቤቱ ሽታም ተቀይሯል፤ የሚሸተው ፈሊት ሳይሆን ምግብ ነው፡፡ ከበሩ ጥቂት እልፍ ብላ ያለችው ጠረጴዛ በነጭ ጨርቅ ተሸፍናለች፡፡

“ምሳሽን መቼም እንዳልበላሽ እርግጠኛ ነኝ” አላት።

“እንደቁርስ አበላሌ ከሆነ ምሳ መብላት አያስፈልገኝም” አለችው።

“አታደርጊውም፡፡ ልፋቴን መና ማስቀረት ይሆንብሻል” አለና ተነስቶ ነጭ ጨርቅ የተሸፈነችውን ትንሽ ጠረጴዛ አቀረባት፡፡



“እኔ ሠራሁት ለማለት ነው አይደል?” አለችው፡፡ ሽታው ያስጎመጃል፤ የዳቦዎቹ አቆራረጥና አቀማመጥ የተለየ ነው፡፡

“ስሠራው ከአንቺ ጋር እንደምንመገበው እያሰብኩ ስለነበረ ሙያዬን ሁሉ ነው የተጠቀምኩት፡፡ እስኪ ቅመሺው?” አላት እጁን ለጉርሻ ዘርግቶ።

ለደስታቸው ወሰን አልነበረውም እየተጎራረሱና እየተጫወቱ በልተው ጨረሱ፡፡ ለስላሳና አምቦ ውሃ እየበረዙ ጠጡ፡፡ በልተው ሲጨርሱ ዕቃዎቹን አብረው አጣጠቡ፤ ቤቱንም አጸዱና አልጋቸው ላይ ወጥተው ሰፈሩ፡፡

ከሰዓት በኋላውን በጨዋታ ብቻ ሊያሳልፉት ወስነው አንድም ፖለቲካ ላያነሱ ተስማሙ፡፡ ድክም እስኪላቸው ድረስ ሲኮራኮሩና ሲደባደቡ፣ ሲታገሉ… ዋሉ፡፡ የግድግዳው ሰዓት አስራ ሁለት ማለቱን ስትመለከት በጣም ገረማት አንድ ሰዓት እንኳን የቆየች አልመሰላትም፡፡

“በናትህ ከምኔው መሸ” አለችው።

“ሁሌም የሚወዱትን ሲያገኙ ይኼው ነው” እያለ ከአልጋው ላይ ወረደ። “ዛሬ አንድ የምታነቢው ጽሑፍ እሰጥሻለሁ፡፡ ከአሁን በኋላ ደግሞ የምታነቢውና የምትወያይው ከኔ ጋር አይሆንም።” አላት ኮስተር ባለ አነጋገር፡፡ ሁልጊዜም ወደ ቁምነገሩ ሲገባ ተጫውቶና ቀልዶ የሚያውቅ አይመስልም፡፡ አንዳንዴ ትኩር ብላ ትመለከተውና ሁለት ሰዎች በአንድ ሰው ሰብዕና ውስጥ ያሉ ይመስላታል፡፡

“በዚህ ወረቀት ትጠቀልይዋለሽ ደግሞ የበለጠ መጠንቀቅም ይኖርብሻል” አላት የተጣጠፈውን ወረቀት እየሰጣት፡፡ ወረቀቱን ገልጣ ለማየት አልተጣደፈችም፤ ምን እንደሚሆን ገምታለች፡፡ ወረቀቱን ማግኘት በመታደሏ ግን ከልቧ ደስ ብሏታል፡፡ ከዘመቻ ከተመለሱ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ማግኘቷ ነው፡፡

"ይህንንም አንብቢው" አላት፤ አጠርና ዳጎስ ያለ መጽሐፍ እየሰጣት፡፡ በመጨረሻ አንዲት ብጣሽ ወረቀት አውጥቶ "እንኳን ደስ ያለሽ ተመልምለሻል" አላት፡፡ አልገባትም መደናገሯ ገብቶታል "የኢሕአፓ የወጣት ሊግ አባል ለመሆን ብቁ ሆነሽ በመገኘትሽ ተመልምለሻል" አላት፡፡ እንዴት አድርጋ አንገቱ ላይ እንደተጠመጠመችበት ስታስበው ሁልጊዜም ይደንቃታል፡፡

"እንደዕንቁ ተጠንቀቀሽ ያገኘት አንብበሽ በቃልሽ መያዝሽን እርግጠኛ ስትሆኚ ቀዳደሽ ጣያት፡፡ ቀጠሮ አክባሪ መሆንሽን አውቃለሁ፤ በሰዓቱ ድረሽ" አላት፡፡ የአንተነህ ኮስተር ማለትና የነገሩም ጠበቅ ማለት ልቧን ረበሸባት፤ ትንሿን ወረቀት በጥንቃቄ ጃኬቷ ኪስ ውስጥ ከተተች፡፡

"አሁን መውጣት እንችላለን" አላት ደግሞ ለስንብት እየሳማት፡፡ አንገት ላንገት ተቃቅፈው ከአፓርትመንቱ ወረዱና አስፋልቱን አቋርጠው በትምህርት ሚኒስትር በር ላይ አልፈው የተለመደው ቦታ ድረስ ሸኛት። ታክሲው እስከሚንቀሳቀስ ጠብቆ እጁን አውለበለበላት፤ አጸፋውን መለሰችለት። ታክሲው ከዕይታው እስከሚሰወር ድረስ በዐይኖቹ ተከተለው።

* * * *

ግቢው የተወረረ ይመስላል፤ የበላይሁን እናትና የፍሬሕይወት እናት ነጠላቸውን ዘቅዘቅ አድርገው ከወጡ በቶሎ እንደማይመለሱ የታወቀ ነው። አዘውትረው አይወጡም እንጂ አንድ ቀን ተሳክቶላቸው ሲወጡ እንደሚቆዩ ሁሉም ይገባቸዋል።

"ሚሚ! ግቢውን እያዳመጥሽ" ብለዋት ሲወጡ ከምታነበው ወረቀት ላይ አንገቷን ሳታቀና ነው "እሺ" ያለቻቸው።

ለነሚሚ "ጎሕ" ማለት ተወዳጁ የጊዜው መጽሔት ነው። ጎሕን አግኝቶ ሳያነብ የሚያስቀምጥ ማን አለ? ጥቂት ከቆየ እንደሚወሰድና ላይመለስም እንደሚችል ስለሚገመት እጅ ከገባ ማንበብ ነው። በጎሕ መጽሔት ላይ ምን የማይወጣ ነገር አለ? ምን የማይተነተን የፖለቲካ ጉዳይ አለ? ትረካዎቹና ልቦለዶቹ



ልብን ይነካሉ፤ ግጥሞቹ ስሜት ይቀሰቅሳሉ፤ ትንታኔዎቹ ዕውቀት ያስጨብጣሉ። ብቻ እነሚሚ ጎሕ የወቅቱ የሕዝብ የልብ ትርታ የሚደመጥበት መጽሔት መሆኑን የማያምን አለ ብለው መገመት በጭራሽ የማያስቡት ነገር ነው።

ሚሚ ደግሞ ለስነጽሑፍ ያላት ስሜት ልዩ ነው፤ ማንበብ ብቻ ሳይሆን መጻፍም ትሞክራለች። እንዲያውም ለጎሕ ከላከቻቸው ጽሑፎቿ ውስጥ ሁለት ግጥሞች ወጥተውላት አንድ ሰሞን ፍንድቅድቅ ብላ ነበር። እነዛን መጽሔቶች እንዳይጠፉባት በጥንቃቄ አስቀምጣቻቸዋለች።

ሚሚ አንዴ ማንበብ ከጀመረች መቆም አትወድም፤ ለብዙ ሰዓታት ተቀምጣ የማንበብ ችሎታዋ ከፍተኛ ነው።አሁንም ማንበብ ከጀመረች ሰዓታት አልፈዋል። ትከሻዋንና ወገቧን ሲያማት ተነሳችና መንጎራደድ ጀመረች፤ ስትንጎራደድ የዕንቁላል ቅርጽ ባለው የብፌ መስታወት ውስጥ ራሷን ተመለከተች። ቤት ውስጥ የምትታወቅበት የሚሚ ሌላው ባህሪ በመስታወት ራሷን መመልከት ነው። መስታወት ካያዘች በፍጹም አታስቀምጥም፤ በዚህ ሁልጊዜ ከቃለአብ ጋር እንደተጨቃጨቁ ናቸው።

ሚሚ የቃለብን ጭቅጭቅ በጣም ትወደዋለች። ትዝ ሲላት ፈገግ አለች "እኔኮ መልክ እንዳለው ሰው ራስሽን ማየት መውደድሽ ነው የሚገርመኝ? አሁን ምንሽ ይታያል?" ይላታል መኝታ ቤታቸው ውስጥ ያለችውን ትንሽ መስታወት አልለቅ ስትለው።

ሚሚ ሁሉ ነገር ተመጥኖ የተሰጣት የምትመስል ነች። ትናንሽ ዓይኖቿ ስትስቅ የሚጠፉ፣ አፍንጫዋ "የሽምብራ አፍንጫ" የምትባል ዓይነት አጭር፣ ከንፈሮቿ ምግብ ለመጉረስ እንኳ የሚጠቡ የሚመስሉ፣ ጥርሶቿ ምስር የሚያካክሉ ናቸው። ግን የደስ ደስ ያላት ሁልጊዜ ታይታ የማትጠገብ አሻንጉሊት የመሰለች ናት ።

"ስምሽ ሚሚ ሆኖ የቀረው እኮ የማታድጊና ትንሽ በመሆንሽ ነው" ይላታል ቃለአብ። ሚሚና ቃለአብ በጣም ይዋደዳሉ። ገና

"ይህንንም አንብቢው" አላት፤ አጠርና ዳጎስ ያለ መጽሐፍ እየሰጣት፡፡ በመጨረሻ አንዷት ብጣሽ ወረቀት አውጥቶ "እንኳን ደስ ያለሽ ተመልምለሻል" አላት፡፡ አልገባትም መደናገሯ ገብቶታል "የኢሕአፓ የወጣት ሊግ አባል ለመሆን ብቁ ሆነሽ በመገኘትሽ ተመልምለሻል" አላት፡፡ እንዴት አድርጋ እንገቱ ላይ እንደተጠመጠችበት ስታስበው ሁልጊዜም ይደንቃታል፡፡

"እንደዕንቁ ተጠንቅቀሽ ያዣት አንብበሽ በቃልሽ መያዝሽን እርግጠኛ ስትሆኚ ቀዳደሽ ጣያት፡፡ ቀጠሮ አክባሪ መሆንሽን አውቃለሁ፤ በሰዓቱ ድረሽ" አላት፡፡ የአንተነህ ኮስተር ማለትና የነገሩም ጠበቅ ማለት ልቧን ረበሸባት፤ ትንሿን ወረቀት በጥንቃቄ ጃኬቷ ኪስ ውስጥ ከተተች፡፡

"አሁን መውጣት እንችላለን" አላት ደግሞ ለስንብት እየሳማት፡፡ አንገት ላንገት ተቃቅፈው ከአፓርትመንቱ ወረዱና አስፋልቱን አቋርጠው በትምህርት ሚኒስትር በር ላይ አልፈው የተለመደው ቦታ ድረስ ሸኛት። ታክሲው እስኪንቀሳቀስ ጠብቆ እጁን አውለበለበላት፤ አጸፋውን መለሰችለት። ታክሲው ከዕይታው እስኪሰወር ድረስ በዐይኖቹ ተከተለው።

* * * *

ግቢው የተወረረ ይመስላል፤ የበላይሁን እናትና የፍሬሕይወት እናት ነጠላቸውን ዘቅዘቅ አድርገው ከወጡ በቶሎ እንደማይመለሱ የታወቀ ነው። አዘውትረው አይወጡም እንጂ አንድ ቀን ተሳክቶላቸው ሲወጡ እንደሚቆዩ ሁሉም ይገባቸዋል።

"ሚሚ! ግቢውን እያዳመጥሽ" ብለዋት ሲወጡ ከምታነበው ወረቀት ላይ አንገቷን ሳታቀና ነው "እሺ" ያለቻቸው።

ለነሚሚ "ጎሕ" ማለት ተወዳጁ የጊዜው መጽሔት ነው። ጎሕን አግኝቶ ሳያነብ የሚያስቀምጥ ማን አለ? ጥቂት ከቆየ እንደሚወሰድና ላይመለስም እንደሚችል ስለሚገመት እጅ ከገባ ማንበብ ነው። በጎሕ መጽሔት ላይ ምን የማይወጣ ነገር አለ? ምን የማይተነተን የፖለቲካ ጉዳይ አለ? ትረካዎቹና ልቦለዶቹ



ልብን ይነካሉ፤ ግጥሞቹ ስሜት ይቀሰቅሳሉ፤ ትንታኔዎቹ ዕውቀት ያስጨብጣሉ። ብቻ እነሚሚ ጎሕ የወቅቱ የሕዝብ የልብ ትርታ የሚደመጥበት መጽሔት መሆኑን የማያምን አለ ብለው መገመት በጭራሽ የማያስቡት ነገር ነው።

ሚሚ ደግሞ ለስነጽሑፍ ያላት ስሜት ልዩ ነው፤ ማንበብ ብቻ ሳይሆን መጻፍም ትሞክራለች። እንዲያውም ለጎሕ ከላከቻቸው ጽሑፎቿ ውስጥ ሁለት ግጥሞች ወጥተውላት አንድ ሰሞን ፍንድቅድቅ ብላ ነበር። እነዛን መጽሔቶች እንዳይጠፉባት በጥንቃቄ አስቀምጣቻቸዋለች።

ሚሚ አንዴ ማንበብ ከጀመረች መቆም አትወድም፤ ለብዙ ሰዓታት ተቀምጣ የማንበብ ችሎታዋ ከፍተኛ ነው።አሁንም ማንበብ ከጀመረች ሰዓታት አልፈዋል። ትከሻዋንና ወገቧን ሲያማት ተነሳችና መንጎራደድ ጀመረች፤ ስትንጎራደድ የዕንቁላል ቅርጽ ባለው የብፌ መስታወት ውስጥ ራሷን ተመለከተች። ቤት ውስጥ የምትታወቅበት የሚሚ ሌላው ባህሪ በመስታወት ራሷን መመልከት ነው። መስታወት ከያዘች በፍጹም አታስቀምጥም፤ በዚህ ሁልጊዜ ከቃለአብ ጋር እንደተጨቃጨቁ ናቸው።

ሚሚ የቃለብን ጭቅጭቅ በጣም ትወደዋለች። ትዝ ሲላት ፈገግ አለች "እኔኮ መልክ እንዳለው ሰው ራስሽን ማየት መውደድሽ ነው የሚገርመኝ? አሁን ምንሽ ይታያል?" ይላታል መኝታ ቤታቸው ውስጥ ያለችውን ትንሽ መስታወት አልለቅ ስትለው።

ሚሚ ሁሉ ነገር ተመጥኖ የተሰጣት የምትመስል ነች። ትናንሽ ዓይኖቿ ስትስቅ የሚጠፉ፣ አፍንጫዋ "የሽምብራ አፍንጫ" የምትባል ዓይነት አጭር፣ ከንፈሮቿ ምግብ ለመጉረስ እንኳ የሚጠቡ የሚመስሉ፣ ጥርሶቿ ምስር የሚያካክሉ ናቸው። ግን የደስ ደስ ያላት ሁልጊዜ ታይታ የማትጠገብ አሻንጉሊት የመሰለች ናት ።

"ስምሽ ሚሚ ሆኖ የቀረው እኮ የማታድጊና ትንሽ በመሆንሽ ነው" ይላታል ቃለአብ። ሚሚና ቃለአብ በጣም ይዋደዳሉ። ገና

አብዮቱ በተጀመረበት ሰሞን አንድ ቀን ለሰላማዊ ሰልፍ አብረው ሄደው የሆነውን ስታስታውስ ሁሌም እንባዋ ይመጣባታል።

ያን ዕለት የነበረውን ሰላማዊ ሰልፍ መቼም ቢሆን አትረሳውም። ሚሚ ገና ትንሽ ስለሆነች ቃለአብ እንዳትሄድ ብዙ ለምኗት ነበር። ግን "እምቢ" አለችው። መንገድ ከደረሱም በኋላ እንድትመለስ ቢጠይቃት "አንተም የማትቀር ካልሆነ አላደርገውም" አለችው። እርሱ ደግሞ መቅረት በፍጹም አልፈለገም። ስለዚህ አብረው ሄዱ።

ሰላማዊ ሰልፉ የተካሄደው ባምቢስ አካባቢ ነበር፤ ሰልፉ ብዙም ሳይገፋ፤ ገና የተወሰኑ መፈክሮች እንደተሙሁ ነበር ፈጥኖ ደራሽ ወታደሮች አካባቢያቸውን ያጥለቀለቁት። አካባቢው ትርምስምሱ ወጣ፤ ወታደሮቹ አጠገባቸው ያገኙትን ሁሉ በሰደፍና በእርግጫ አጣደፉት። ሚሚና ቃለአብ ጎን ለጎን ነበሩ፤ ድንገት አጠገቧ ስታጣው ዞር አለች። ቃለአብን ወድቆ አየችው፤ ከጆሮው አካባቢ ደም ተመለከተች፤ ሮጣ አጠገቡ ስትድርስ አንድ ወታደር "ተመለሽ" ብሎ ጮኸባት። የወታደሩን ጩኸት ከምንም አልቆጠረችውም ወንድሟን ማንሳት ነበረባት። ቃለአብን ሊያነሳ የሞከረውን አንድ ወጣት በሰደፍ ሲመቱትና ሲረጋግጡት እያየች አልቆመችም። እንደምንም አጠገቡ ደርሳ ገና "ቃለ..." ብላ ስሙን ጠርታ ሳትጨርስ ያረፈባት ዱላ ራሷን አሳታት። ከዛ በኋላ ምን እንደተፈጠረ አላወቀችም።

ራሷን ስታውቅ ቃለአብ የተኛችበት አልጋ አጠገብ ተንበርክኮ እንባው በጉንጮቹ እየወረደ ተመለከተችው። ለማስታወስ ሞከረች፤ ማስታወስ የቻለችው ቃለአብ ወድቆ ማየቷን ብቻ ነው።

"የት ነው ያለነው ቃል? ምን ሆኜ ነበር?..." እያለች ጠየቀችው። መልስ አልሰጣትም፤ የሚሆነው ጠፍቶበት እንዴት አድርጎ እንዳቀፋት ስንት ጊዜ መሬቱን እንደሳመ ስትመለከት የበለጠ ግራ ገባት። ጆሮው አካባቢ በቁስል ማሸጊያ ታሽጓል፣ ግንባሩ አካባቢም ተጋግጧል።

"እስኪ ለመነሳት ሞክሪ ሚሚ" አላት ደግሞ።



ለመነሳት ስትሞክር ደረቷና ጀርባዋ አካባቢ ህመም ተሰማት፤ አልጋው ላይ ለመቀመጥ በእጇ ስትመረኮዝበት በጣም አመማት። እንደምንም ተቀመጠች።

"ተመስገን! ነቃችልህ?" አሉ አንዲት ሴት ወደነበሩበት ክፍል እየገቡ።

"አዎ ነቃች" አላቸው።

"ወንድ ልጅ ሆነህ ግን ይህን ያህል ሰፍሳፋ መሆን አያስፈልግም። ለዛሬ እግዜር አውጥቶልሃል። ለመሆኑ ለምን ወጥታ ነው?" አሉ ሴትዮዋ።

"ወደዘመድ ቤት ልንሄድ ነበር" አላቸው ለሰልፍ መውጣታቸውን መናገር ስለከበደው።

አመሻሽ ላይ ወደቤታቸው ሲመለሱ ነበር የሆነውን ሁሉ የነገራት። እርሱን ልታነሳ ስትሮጥ ወታደሮቹ እንደመቷት የነገሩት አቤታቸው አስገብተው ሕይወታቸውን የታደጓቸው ሴት እንደሆኑ አስረዳት።

ሚሚ እስከዛሬም ድረስ ሴትዮዋን ትጠይቃቸዋለች። እንዲያውም አንድ ቀን ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሲመጡ አግኝታቸው እቤት አስገብታ ከእናቷ ጋር አስተዋውቃቸው ቡና አጠጥታቸዋለች። ከእናቷ ጋርም ተቀራርበዋል።

መስታወቱ አጠገብ እንደቆመች መሆኗን ያስታወሰችው ከትውስታዋ ስትመለስ ነው። በክፍሉ ውስጥ ጥቂት ተንጎራደደችና እንደገና ወደንባቧ ተመለሰች። እያነበበች አሁንም አሁንም ሰዓቷን ትመለከታለች። ሰዓቱ እየደረሰ ነው፤ ፍሬሕይወትን የግድ ማግኘት አለባት። "ግን ባትመጣስ" አለች ለራሷ።

ሚሚ ፍሬሕይወትን የምትፈራትን ያህል እናቷን አትፈራም። ግን ለምን እንደሆነ ለራሷም አይገባትም፤ ያለፍሬሕይወት ፈቃድ

እስኪሪፕቶዋን እንኳን አትነካም፤ እናም ትንሽ መጨነቅ ጀመረች የፍሬሕይወትን ልብስ ያለፈቃዷ ለብሳ መሄድ እጅግ ከብዷታል። ልብሱ ደግሞ የግድ ያስፈልጋታል፤ የተሰጣት ማስጠንቀቂያ ከበድ ያለ ነው።

ሚሚ ሀገር አስተዳደር ሥራ ልትጀምር ነው፤ የተላላኪነት ሥራ። እዚያ መሥሪያ ቤት ውስጥ በትልቅ ኃላፊነት ላይ ላሉ ባለስልጣን ተላላኪ እንድትሆን ተመቻችቶላታል፤ እዚያ የምታከናውነው ታላቅ ድርጅታዊ ሥራም ተሰጥቷታል። ሥራውን በአግባቡ እንደምትወጣው እምነት የተጣለባት መሆኗ ሲነገራት ድንጋጤም ደስታም ነበር የተሰማት።

ሥራውን ለመጀመር ታዲያ ልብስ ያስፈልጋታል፤ ሠራተኛ ሊያስመስላት የሚችል ልብስ። የውጭው በር ሲንኳኳ ፍሬሕይወት እንድትሆን እየተመኘች በፍጥነት ወጥታ ከፈተች።

"ጎሽ ፍሬ እንኳን መጣሽ፤ እንዴት ስፈልግሽ እንደነበረ ብታውቂ" አለቻት ሚሚ ገና ፍሬሕይወት የውጭውን በር ስትገባ።

"ምነው ሚሚ ያለወትሮሽ እንዲህ ፈለግሽኝ?" አለች ፍሬሕይወት።

"ልብስ እንድትሰጭኝ ፈልጌ ነው" አለች ሚሚ እንደተቻኮለች። ሰዓቷን ተመለከተች።

"ለመሆኑ የሚሆንሽ ይኖራል?" አለች ፍሬሕይወት ሚሚን እየተመለከተቻት።

መቼም "ለምንሽ ነው፤ የት ትሄጃለሽ?" የሚባል ጥያቄ ማንሳት አይኖርም፤ ቢነሳም መልስ አያገኝም።

ፍሬሕይወት የሚሚ ሁኔታ በጣም ይደንቃታል፤ እንዳልጅ መሆን ከተወች ቆይታለች፤ የምታነባቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ ላቅ ያሉ ይሆኑባታል። የምትሰጣቸው የፖለቲካ ትንታኔዎች ይገርሟታል። ቀደም ብላ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መጀመሯን በተለያዩ



አጋጣሚዎች መገመት ችላለች። እናም በአሁኑ ወቅት የምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ከፖለቲካ እንቅስቃሴ ውጭ እንደማይሆኑ ታውቃለች። እንዲያውም በከፍተኛ ደረጃ ላይ ልትገኝ እንደምትችል ታስባለች።

"ካለው ውስጥ መምረጥ ትችያለሽ" አለቻት ፍሬሕይወት የሚሚን የቸኮለ ስሜት እያየች።

"አመሰግናለሁ ፍሬ" አለችና ወደውስጥ ገባች ሚሚ።

ሚሚ ለባብሳ ስትወጣ "እንዴት ነኝ?" አለቻት ፍሬሕይወትን።

"ወዴት እንደምትሄጂ ያጠያይቃል፤ በጣም ነው ያማረብሽ። አይገረምም? የኔ ልብሶች ለአንቺ ይሆኑሻል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር" አለቻት ፍሬሕይወት ሚሚን ሁለመናዋን እየተመለከተቻት።

"አመሰግናለሁ" አለችና ለመውጣት ራመድ ካለች በኋላ ቆም አለች ሚሚ።

"እኔ የምልሽ ዳንኤልን አግኝተሽው ታውቂያለሽ?"አለችና ጠየቀች።

"ምነው? በቅርብ ባይሆንም አግኝቼው አውቃለሁ። ምን ሆነ?"

"እሱማ ምንም አልሆነም፤ ፍሬሕይወትን ወድጃ ልሞትነው ይላል አሉ"

"ፍሬሕይወት? እኔን?" አለች ደንገጥ ብላ።

"አዎ አንቺን፤ ለማንኛውም ጠንቀቅ በይ፤ ሰፈር ውስጥ ያለውን ስም ታውቂዋለሽ። አሁንማ እርሱም ከተወራብኝ አይቀር ብሎ ነው መሰለኝ በግላጭ ከመኢሶኖች ጋር መዋል ጀምሯል። በይ ብቻ ተጠንቀቂ ረፈደብኝ" ብላት እየተጣደፈች ወጣች።

ፍሬሕይወት ስለዳንኤል ብዙም ማሰብ አልፈለገችም፤ ከአእምሮዋም ለማውጣት አልተቸገረችም።

* * * *

ፍሬሕይወት አንተነህ በሰጣት ትንሽ ወረቀት ላይ የተጻፈውን አነበበችው፤ እንደከባድ ተውኔትም ደጋገመችው፡፡ ማምሻዋን ሁሉ በሀሳቧ የሚመጣባት እሱው ነው፡፡ ዴሞክራሲያንም በፍቅር አነበበችው፡፡ የተኛችው በጊዜ ነው፤ እንቅልፍ ግን ሊወስዳት አልቻለም፡፡ ተነሳችና አንተነህ የሰጣትን መጽሐፍ ማንበብ ጀመረች፡፡ የመጽሐፉ ርእስ "እናት" ይላል፡፡ ደራሲው ማክሲም ጎርኪ፤ ዕውቁ ሩሲያዊ ደራሲ ነው፡፡ አሁንም አሁንም በተከታዩ ቀን ስለሚጠብቃት ቀጠሮ ስታወጣና ስታወርድ ሀሳቧን ሰብስባ ማንበብም አልሆነላትም፤ ማንበቡን ተወችው፡፡ ሌሊቱ መንጋቱ ስለማይቀር እንደምንም ነጋ፡፡

ጠዋት ከአልጋ ስትወርድ "ሌሊቱ የቱንም ያህል ቢረዝም ቀኑ መምጣቱ የማይቀር ነው" የሚል የማን እንደሆነ የማታውቀው አባባል በአእምሮዋ ውስጥ እየተመላለሰ ነበር።

የምትለብሳቸውን ልብሶች አዘጋጀች፤ ሰዓቷን የምትመለከተው በየደቂቃው ሆነ። የቀጠሮው ሰዓት አልደርስ እስኪላት ቸኮለች፤ ፀሑፉን በቃሏ መያዟን ለመጨረሻ ጊዜ አረጋገጠችና ትንሿን ወረቀት በጫጭቃ መፀዳጃ ውስጥ ጨመረች፡፡ ስትጨምረው ልቧ ድው ድው አለባት፤ ቢጠፋብኝስ ብላ ስለሰጋች፡፡ ያች አጭር ቃል ይህን ያህል ማሳሰቧ በጣም ደነቃት፡፡

በሀሳቧ ጠይም ረዘም ያለ ራንግለር ሱሪ የለበሰና ፈርጠምጠም ያለ ሰውነት ያለው ከስታራ ወጣት ይታያታል፡፡ ከልጁ ጋር ተገናኝተው አብረው እየሄዱ፤ የሚጠይቃትን ትመልስለታለች፡፡ የሚያወራላት ሁሉ አዲስ ነገር እየሆነባት የሚከብዳትም ይመስላታል፡፡ ይህንኑ ስታውጠነጥን ሰዓቱ ደረሰና ለቀጠሮዋ ወጣች።



ከተባለው ሰዓት በአምስት ደቂቃ ቀድማ ቀጠሮ ቦታ ደረሰች፡፡ ጊዜው የምሳ ሰዓት በመሆኑ መንገዱ በሰዎች ተጨናንቋል፡፡ ጆኪ ባርም ጢቅ ብሎ ሞልቷል፡፡ ጭንቅ አላት፡፡ "በዚህ ሁሉ ሰው መሀል እንዴት መገናኘት ይቻላል?" አለች ለራሷ፡፡ ልክ የቀጠሮው ሰዓት ሲሞላ በግራ እጇ አውራ ጣትና ሌባ ጣት በያዘችው መፋቂያ ጥርሷን መፋቅ ጀመረች፡፡ የቀኝ እጇን ሱሪ ኪሷ ከተተች፡፡ ልቧ በመጠኑ መታች፡፡ አለባበሷን ተመለከተችው፤ በፍፁም አልተሳሳተችም፡፡ የለበሰችው ጃኬትና ሱሪ ወንድ ቢያስመስላትም ረጅም ፀጉሯ ሴትነቷን ይናገራል፡፡ በድንገት ትከሻዋን ሰው ነካት በፍጥነት ዞር አለች፡፡

"መፋቂያሽ ከየት ተላከልሽ?" አላት እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ፡፡ ደንገጥ ብላ እጇን ከኪሷ አወጣችና፤

"ከጃማይካ" ብላ ጨበጠችው፡፡

ከልጁ ጋር ተያይዘው ቁልቁል ወደካዛንችስ ሄዱ፡፡ በቀስታ ፊቱን በደንብ አየችው በግምቷና በልጁ መልክ መሃል ያለውን ልዩነት ስትመለከት ፈገግ አለች ፡፡ በሀሳቧ የሳለችው ምስል ከልጁ መልክና ቁመና ጋር በፍጹም አይመሳሰልም፡፡ ልጁ በቁመቱ ከእርሷ ብዙም የማይበልጥ ሲሆን አጭር ወንድ የሚባል ዓይነት ነው፡፡ በዕድሜም ቢሆን ብዙ የሚራራቁ አይመስሉም፡፡ ፊቱ ክብ ነው፤ ትንሽ አፍንጫውም ለፊቱ ተመጥኖ የተሠራ ይመስላል፤ የተበጠሩ የሚመስሉ ቅንድቦቹ፣ ለትላልቅ ዓይኖቹ ልዩ ውበት ሰጥተዋቸዋል ጺም ወረር ያደረጋቸው ጉንጮቹ የቀይ ዳማ ቆዳውን ጠይም አስመስሎታል።

ከአንደበቱ የሚፈልቁት ቃላትና የንግግሩ ብስለት አስደነቃት፡፡ አንተነህን አስታወሳት፡፡ በመሃላቸው ያለውን የፖለቲካ ብስለት ርቀት እያሰላሰለች ተገረመች፡፡ የሚናገረውን የሸመደደው ይመስላል፤ ፈጣን ነው፡፡ ዓይኖቹ አካባቢውን የሚቆጣጠሩበት ልዩ ስልት አላቸው፡፡ ለእርሷ የሚያደርገውን ገለፃ ሳያቋርጥ ዙሪያ ገባውን የመቃኘት ችሎታውን አደነቀችለት፡፡

በዲዝኒ ላንድ መዋዕለ ሕፃናት በር ላይ አልፈው ቂልቂል ወረዱና ወደግራ ታጠፉ፡፡ አሁንም እንደገና ቁልቁል፣ ደግሞ ወደግራ ታጥፈው በታንዛኒያ ኤምባሲ በር ላይ ወደ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን አቀኑ፡፡ በተወሰኑ ሰዓታት ውስጥ የቆዩ ጓደኛሞች መሰሉ፤ አልፎ አልፎ እጇን ያዝ ትከሻዋን አቀፍ እያደረገ ኡራኤል መብራት አጠገብ ሲደርሱ ቀጠሮ ሰጥቷት ተለያዩ፡፡

ወደቤት ስትመለስ ከመቼውም ጊዜ ለየት ያለ ስሜት እየተሰማት ነበር፡፡ በሕይወት ለመኖር ታላቅ ምክንያት እንዳገኘችለት ቆጠረችው፡፡ ልትፈጽመው የሚገባትና ከእርሷ ሕይወት የሚበልጥ ዓላማ ያላት ሰው መሆኗ ዘልቆ ታወቃት፡፡ ይህን ኃላፊነት የመወጣት ጥንካሬ እና ጽናት እንደሚያስፈልጋትም ለራሷ ነገረችው፡፡

ፍሬሕይወት ማታ እንጀራ ለመጋገር ስትዘጋጅ በደመነፍስ ነበር፡፡ ሁለንተናዋን የተቆጣጠረው የቀን ቆይታዋን ማሰላሰል ነበር፤ ታናሽ እህቷ ሚሚ ስትጠራት በፍጹም አልሰማችም፡፡

"ፍርዬ ዛሬ የሆነ ነገር ገጥሞሻል አይደል?" አለቻት አጠገቧ መጥታ።

"እ... እንዲያውም ምን አየሽ?" አለቻት ደንገጥ ብላ።

"እንኳንስ ለእኔ ከሩቅ ለሚያውቅሽም ግልጽ ነው" አለችና ትታት ወጣች ሚሚ።

ጥቂት ቆይታ ደግሞ ተመለሰችና "ፍሬ! ሳልነግርሽ ሥራ ጀመርኩ" አለቻት።

"አትይኝም!" አለች ፍሬ ያልጠበቀችው ነገር ሆኖባት።

"በእውነት ጀምሬአለሁ" አለች ሚሚ እያስተማመነቻት።

"የት?" አለች ፍሬሕይወት ግራሞቷ ሳይለቃት።



"አገር አስተዳደር" አለች ሚሚ ተረጋግታ።

* * * *

ሚሚና ፍሬሕይወት ለሆቴል የሚቀርበውን እንጀራ በተራ ይጋግራሉ። እናታቸው በእንጀራ ጋገራ ውስጥ በፍጹም መግባት እንደሌለባቸው ተነጋግረውና ተራ አውጥተው ያለ ምንም ትእዛዝ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ።

ፍሬሕይወት የዕለቱ ተረኛ መሆኗን ስታስብ ለሥራ የሚያስፈልጋትን ዝግጅት ጨራረሰችና አንተነህ የሰጣትን መጽሐፍ ይዛ ጋገራዋን ጀመረች፡፡ መጽሐፉን የምታነበው እንጀራ አስፍታ እስኪበስል ባሉት ደቂቃዎች ነው፡፡ መጽሐፉ በጣም መሰጣት፤ እንጀራውን ከምታወጣበት ደቂቃ አለፍ ማለት ስላበዛች እንጀራው እንደወትሮው ቆንጆ መሆን አልቻለም፡፡ የጀመረችውን ምዕራፍ ጨርሳ ማቋረጥ እንደሚኖርባት ወሰነች፡፡ ምዕራፉን ለመጨረስ ወደንባቧ አድልታ ኖሮ የእንጀራው መውጫ ካለፈ ቆይቷል፡፡ እንጀራው በጣም ደረቀ አውጥታ ለብቻ አስቀመጠችው፡፡

ምጣድዋን በደንብ አሰሰችና ቀዝቀዝ እንድትል ኤሌክትሪኩን አጠፋችው፡፡ በድጋሚ አሰሰችና ሊጡን አስፍታና በሰዓቱ ከፍታ ጥሩ እንጀራ አወጣች፡፡ ምጣዱ ስለተስተካከለላት ደስ አላትና በፍጥነት መጋገሯን ቀጠለች፡፡ ጥቂት እንጀራዎች እንደጋገረች ድንገት መንፈሷ ወደ መጽሐፉ ሄዶ ኖሮ ሳታስበው ከባለታሪኳ እናት ጋር በዓይነ ህሊና ተጓዘች ፀጉሯ ጥቁርና ወደግንባርዋ ደፋ ያለ፣ ረዥምና ከትከሻዋ ጎንበስ ያለች ጎስቋላ እናት ጋር በሀሳቧ ሄደች፡፡ መጽሐፉን እንደገና አነሳችው፡፡

ያች እናት ልጇ ከሚያንቀሳቅሰው የሠራተኞች አመጽ ውስጥ ቀስ በቀስ እንዴት ልትገባ እንደቻለች፤ ልጇን በስስት ዐይን እያየች መከሳት መጠውለጉ እያሳሰባት ስትጨነቅ፤... የባለታሪኳ እናት ልጅና ጓደኞቹ ሚስጥራዊና የተከለከሉ መጻሕፍትን ሊያነቡ ሲሰባሰቡ የነበረውን ሁኔታ...ውይይትና ክርክራቸውን፤ ስለመጻሕፍቶቻቸውና ጋዜጣቸው... በውይይቱ ለመሳተፍ ወደዛ

ወደሠራተኞች ሠፈር ስለሚመጡት ልጃገረዶች... አነበበች ራሷን በባለታሪኮቹ ሩሲያውያን ቦታ አድርጋ ስሜታቸውን ተጋራች፤ ልክ እንደእነርሱ እርሷም ጨለማን ተገን አድርጋ በድብቅ ስብሰባ መሳተፍ እንደሚጠበቅባት አሰበች፡፡ አብረዋት እንዲሠሩ የተመደቡትን አባላት ገና ባትተዋወቃቸውም በዓይነህሊናዋ አየቻቸው፡፡ ወደፊት የሚሠሩት ሥራ ሁሉ ታያት፡፡ መጽሐፉን አስቀምጣ ደግሞ እንጀራውን አወጣች፤ አሰሰች፤ አሰፋችና ከደነች፡፡ እጇ ሳይታዘዝ መጽሐፉን እንደገና አንስቶ ማንበብ ቀጠለች፡፡

የባለታሪኳ ሩሲያዊት እናት ልጅ በፖሊስ ተይዞ ወደእስር ተጣለ፡፡ እርሱ ሲታሰር ይበተን የነበረው ጋዜጣ ከተቋረጠ ወንጀሉ ሁሉ በልጅዋ ላይ እንደሚደፈደፍ በመረዳቷ የልጇን ዕዳ ልታቃልልለት በማሰብ በህቡዕ የሚበተነውን ጋዜጣ ለመበተን ወሰነች ባለታሪኳ ሩሲያዊት እናት!

እናት ለፋብሪካው ወዛደሮች ምግብ የመሸጥ ፈቃድ ጠይቃ ሲፈቀድላት የሚበተነውን ጋዜጣ ከልጇ ጓደኞች ተረክባና ሸሽጋ ወደፋብሪካው ገ[illegible]ር ገቢ በማስገባት ውስጥ ላሉት ጓዶቻቸው ማሰራጨት ጀመ[illegible]ች፡፡ ጋዜጦቹ እንደገና መበተን ቀጠሉ፡፡ በልጇ ላይ የነበረው ትኩረትም ረገበ...

ብቻ በሃሳቧ አልም ጭልጥ ብላ ሄዳ እንጀራ እየጋገረች መሆኗንም ረስታዋለች፡፡ የተሰፋው እንጀራ እርር ብሎ ምጣዱ ጨሶ ቤቱ ታፍኗል፡፡ ከሀሳቧ የባነነችው ሲያስላት ነው፡፡ ምጣዱን እንዴት እንዳጠፋችው አልታወቃትም ክዳኑን በደመነፍስ ክፍት ስታደርገው ትንፋሹ እጇን ሲለበልባት ለቀቀችው፡፡ ለእጇ መቃጠል ብዙም ቦታ አልሰጠችውም፤ ውሀ ምጣዱ ላይ አፈሰሰችበት፤ ብቻ ተንደፋደፈች፡፡ ጭሱ እናቷ የተኙበት ድረስ ዘልቆ ኖሮ ከመኝታቸው ተነስተው ገርበብ ያለውን መዝጊያ በርግደውት ገቡ፡፡

"አፈር በሆንኩት! ልጄን ገደልኳት" ብለው ጮኹ።



"እማ ደህና ነኝ!" እያለች ልታረጋጋቸው ብትሞክርም መረጋጋት አልቻሉም፤ እንደምንም አድርጋ እንዲቀመጡ አስገደደቻቸው፡፡ እርሳቸውን እያስቀመጠች ደግሞ ባለታሪኳ እናት ትዝ አለቻት፡፡ ከብዙ ደቂቃዎች በኋላ እናቷ እንደምንም ወደራሳቸው ተመለሱና፤

"ተመስገን! ተመስገን አምላኬ" እያሉ ራሷን እያሻሹ "እንቅልፍ ጣለሽ?" አሏት በመጨረሻ፡፡ እንጀራውን ጋግራ ለመጨረስ እንደምንም እናቷን አሳመነችና ወደመኝታቸው እንዲሄዱ አደረገች፤ ምጣዱ የተቃጠለው መጽሐፍ ስታነብ መሆኑን ግን ለእናቷ አልነገረቻቸውም።

* * * *

እንደተለመደው ከጠዋቱ አስራ ሁለተ ሰዓት በሰፈሩ ውስጥ ባለው ትንሽ ሜዳ ላይ የአካል ብቃት እንቅስቃሴያቸውን ለማድረግ ወጣቶቹ ተሰባስበዋል። ጥቂት ዱብ ዱብ ብለው ወደ እግር ኳስ ጨዋታቸው ገቡ። አሁን አሁን ጨዋታቸው ረጅም አይደለም፤ ጥቂት ከተጫወቱ በኋላ ሁሉም ወደእለታዊ ተግባሩ ለመሄድ ሰዓቱን ማየት ይጀምራል፤ ሰዓት ማየት ሲደጋገም ይግባባሉ፤ ጨዋታው ይቋረጥና ወዲያው ወደየቤታቸው፣ ወደ ዕለቱ ተግባራቸው ይሄዳሉ።

ሰሞኑን በየወጣት ማህበሩና በየሰፈሩ የሚደረጉት የፖለቲካ ውይይቶች ተሟሙቀዋል። ድርጅታዊ አቋምን ለማጠናከር ጽንሰ ሀሳባዊ ብቃትን ለማጎልበት የሚደረጉት ውይይቶች ጊዜና ቦታ አይወስናቸውም፤ ብቻ ወጣት በተገናኘበት ጊዜና ቦታ ሁሉ የሚነሱት ክርክሮች ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ናቸው።

በቅርቡ የተጀመረው "አብዮታዊ መድረክ" የተሰኘው የሬዲዮ ፕሮግራም ደግሞ ለዚህ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የአንድ አካባቢ ወጣቶች ሰብሰብ ብለው ፕሮግራሙን እየሰሙ ይወያዩበታል። ውይይቱን የበለጠ ለማጎልበት በርእሶቹ ላይ ተዘጋጅቶ የሚመጣ ሰው ይመደብና እንደገና ውይይቱ ይቀጥላል።

የሬዲዮው ፕሮግራም እንደመነሻ ይሆንና በወጣቶቹ ለውይይት የሚቀርቡት ግን እጅግ በርካታ ርዕሶች ናቸው ።

በርዕሶቹ ላይ የመዘጋጀቱን ኃላፊነት የሚወስዱት በየተራ ነው። በላይሁን ታዲያ የሚያቀርበው ትንታኔ ጠንካራና ሰፊ ነው፤ ለተጠየቀው ጥያቄም መልስ እጥቶ አያውቅም። ስለዚህም ጓደኞቹ "ሌኒን" ብለው ይጠሩታል። እንደተለመደው ለሚቀጥለው ቀን ውይይት "ዴሞክራሲ" በሚል ርእስ ላይ መዘጋጀት ስለነበረበት በላይሁን ሌሊቱን ያሳለፈው እንቅልፍ የሚባል ሳይወስደው ነው። በእርግጥ የበላይሁንን ጊዜ የወሰደበት ዝግጅቱ ብቻ አይደለም፤ ችላ ይለው የነበረ ስሜቱ ሰሞኑን አስቸግሮታል። የሚደረጉት ውይይቶች ከፍርዬ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ አብሮ የመሆን አጋጣሚን ቢፈጥሩለትም ከውይይት የዘለለ አብሮነት ሊኖራቸው ግን አልቻለም፤ ከፖለቲካ ውይይትና ከቤተሰባዊ ወሬዎች ያለፈ ጉዳይ ለማንሳትም አልተመቸውም።

በላይሁን ለስንት ጊዜ ስለአንተነህ ሊጠይቃት እየፈለገ እንዳልሆነለት ሲያስብ ይገርመዋል፤ ብዙ ጊዜ ከሌሎችም ጋር ሆነ ለብቻቸው የዘመቻ ወሬ ተነስቶ ቢጫወቱም በየትኛውም አጋጣሚ ሊያነሳው ደፍሮ አያውቅም። እርሷም አንስታ አታውቅም፤ ብቻ ፍርዬ ደስተኛ ነች፤ ከሰፈር ወጣ ማለትም ታዘወትራለች፤ እናም ይጠራጠራል። "ከአንተነህ ጋር ይገናኙ ይሆን?" ይልና ራሱን ይጠይቃል። አንዳንዴ ራሱን ይታዘባል፤ "ይህን ጥያቄ ፍርዬን መጠየቅ እንዴት እንዲህ ሊከብደኝ ይችላል?" ይላል ለራሱ፤ ግን በፍጹም አልደፈረም። ሁኔታዎች ደግሞ የበለጠ እንዲወዳት እያደረጉት ነው። ያች ፖለቲካ የማይጥማት ፍሬሕይወት ዛሬ ያላት የፖለቲካ ብስለት ይደንቀዋል፤ የምትሰነዝራቸው አስተያየቶች፣ የንግግሯ ለዛ፣ የማሳመን ችሎታዋ... የሚያርፉባት ዐይኖች፤ ብቻ ሁሉም ያለውን ፍቅር ይጨምርበታል። ፍቅሩን ሊገልጽላት ግን አልቻለም።

የሌሊቱን አብዛኛውን ሰዓት በዚህ ሁኔታ ሲብሰከሰክ አድሮ ነው ጠዋት ወደ ስፖርት ሜዳው የወጣው። እንቅልፍ ያላገኙ ዓይኖቹ በደንብ አልተገለጡም። ስፖርቱን እንደነገሩ ሠራና ወደቤት



ተመለሰ፤ አሁንም በመንገዱ ላይ ስለፍሬ ማሰቡን አልተወም። "ተመልምላ ይሆን?" አለና ራሱን ጠየቀ። "መሆን አለበት፤ እንዴት ላትመለመል ትችላለች? አንተነህ መቼም ከኛም ቀደም ያለ ተሳትፎ ያለው ነው የሚሆነው..." ዘመቻ እያሉ ፍርዬ ስለአንተነህ የፖለቲካ ብስለት የጻፈችለት ትዝ አለው። ወደቤት ሲመለስ ፍሬሕይወት መጽሐፍ እንዲሰጣት ጠይቃው እንደነበር ትዝ አለው፤ እቤት ገብቶ ምንም ሳይቆይ መጽሐፉን ፈለገና ይዞላት ሄደ። ፍርዬን ደጅ ፊቷን ስትታጠብ አገኛት፤ "የት ላስቀምጥልሽ?" አላት ከሰላምታ በኋላ።

"ጠረጴዛ ላይ አድርገው" አለችውና መታጠቢን ቀጠለች። በላይሁን እንዳለችው መጽሐፉን አስቀምጠላት ተመለሰ።

"በናትህ በላይ ቁርስ አብረን እንብላ" አለችው ካጎነበሰችበት ቀና ብላ። የበለጠ ውብ ሆና ታየችው፤ አልተግደረደረም ተመልሶ ወደቤት ገባ።

"እማዬን ሰላም አትላትም እንዴ? ደግሞ እኔ ፊቴን እስከማደራርቅ ቁርስ ይዘህ ና" አለችና ትዕዛዝ ሰጠችው።

ቁርሳቸውን አብረው በሉ። እየበሉ እንደወትሮአቸው ብዙ አልተጫወቱም። በላይሁን ከተጫጫነው ስሜት አልወጣም።

"አንተ ልጅ ይህንን ቁጭ ብሎ ማደር መቀነስ አለብህ፤ ዛሬ እንቅልፍ እንዳልጠገብክ ታስታውቃለህ። ከድሉ በፊት እንዳትሞት ያሰጋል፤ እሺ ምን ተብሎ ታሪክህ ሊሰፍር ነው? ሲያነብ ነው?ሲታገል ሞተ ተብሎ የሚጻፈው?" አለችው። አልመለሰላትም።

"ምን ተዓምር የሆዴን በነገርሽ? ባንቺ የተነሳ ማንበብም እያቃተኝ መሆኑን ብታውቂ ምን ይሰማሽ ይሆን?" አለ በሆዱ። ብዙም ሳይቆይ ፍሬሕይወትን ተሰናብቷት ወጣ።

* * * *

ፍሬሕይወትና ቅዱስ (የኮድ ስሙ ነው) በተደጋጋሚ ተገናኝተዋል፤ ከሌሎቹ የኮሚቴ አባላት ጋርም አስተዋውቋታል። በሳምንት አንድ ቀን እየተገናኙ ሰፋ ያለ ሰዓት አብረው የሚቆዩበት ቦታ ተመቻችቷል። በስብሰባቸው ጊዜያት ድርጅታዊ ጉዳዮችን ይነጋገራሉ፣ ንድፈ ሃሳባዊ ውይይቶች ያካሂዳሉ፣ የተግባር ሥራዎችን ያከናውናሉ። ቅዱስ በጣም አንባቢ ነው። ይህንን ልምዱን በሚገባ አስተላልፎላቸዋል። ብዙ ከመናገር ይልቅ ማዳመጥ ይችልበታል። አዳምጦ መልስ ከመስጠትም ወደኋላ አይልም። ባጠቃላይ ድንቅ መሪ ነው ቅዱስ። አብረውት ለሚሠሩት መልካም ምሳሌ፤ በድርጅታቸው ላይ ያላቸውን እምነት እንዲያጠነክሩ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

ለድርጅታቸው የሚገባውን ወርሀዊ መዋጮ ለመክፈል አስታዋሽ አያስፈልጋቸውም። ድርጅታቸውን ለማጠናከር የሚገባውን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ የሚል የለም። ማንኛቸውም የግል ገቢ የላቸውም፤ ከቤተሰብም እንኳ በቋሚነት የሚሰጥ የኪስ ገንዘብ አያገኙም፤ ግን እንደምንም ብለው በምንም መንገድ ያገኟትን ሳንቲም አጠራቅመው፣ አሮጌ ልብሶችና ጫማዎቻቸውን ሸጠው፤... ያገኟትን ለድርጅታቸው መስጠት ከምንም በላይ ያረካቸዋል። እርስ በእርሳቸው ያላቸው መተሳሰብ ልዩ ነው። አንዳቸው ለሌላው ሀይወታቸውን እንኳ ቢሆን እስኪሰጡ ድረስ ፍቅራቸው የጠነከረ ነው።

ከቅዱስ ጋር ብዙ ጊዜ አብረው ሠሩ። ሕይወቱን ለዓላማው አሳልፎ ከመስጠቱ ባሻገር አሳቢነቱና አዛኝነቱ ፍሬሕይወትን ያስደንቃታል። ከቅዱስ ጋር ማንኛውንም ድርጅታዊ መልእክት ለመለዋወጥ ችግር የለባትም። በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ይናበባሉ፤ ቅልጥፍናው ከምትጠብቀው በላይ ነው። ከእርሱ ጋር ስትሆን ማንም በሌላ መልኩ እንደማይጠረጥራት ስለምታምን ሰውነቷ ይዝናናል።

እያደር ትግሉ እየጠነከረ፤ መስዋዕትነቱም እየተበራከተ ሄደ። በአንድ ሜይ ዴይ ሰልፍ ላይ የተከፈለው መስዋዕትነት ግን አስደንጋጭ ነበር። 1968 ሚያዝያ 23 ቀን ከሰዓት በኋላ አቧሬ ላይ የተካሄደው ሰልፍ እጅግ ደማቅ ነበር። መዝሙር ይዘመራል፤



መፈክሩ ይወርዳል፤ 'ባነሩ' ይውለበለባል፤ ወረቀቱ ይበተናል። ግድግዳዎች በቀይ ቀለም አሸብርቀዋል...

ሞቅ ባለው ሰላማዊ ሰልፍ መሃል መሳሪያ የታጠቁ ወታደሮች ከመኪናቸው ወርደው ሰልፉን ለመበተን ሞከሩ። ሰልፈኞቹ አልሸሹም ጩኸቱ ቀጠለ። ተኩስ ተከፈተ... ትርምስምስ ሆነ...የወደቀው እየወደቀ፣ የተያዘው እየተያዘ፣ የተመታው እየተመታ፣... ሌላው መሮጥ... በየቀዳዳው መሹለክ፣ በየአጥሩ መዝለል፣ ድብልቅልቁ ወጣ፣ ምድር ቀውጢ ሆነች። ዋይታ! ጩኸት...

በርካታ ወጣቶች በአንድ የእንጨት አጥር ውስጥ ሾልከው አንድ ግቢ ውስጥ ሲገቡ እንጨቱ የታሠረበት ሽቦ የፍሬሕይወትን እግር ክፉኛ ሰነጠቀው። እግሯ መድማት ጀመረ፤ ቢሆንም ማምለጥ ስለነበረባት እንደምንም ተጎትታ ፊቷ ያገኘችው ግቢ ውስጥ ገባች። ግቢው ውስጥ ማንም የለም። መዝጊያው ገርበብ ብሎ የተከፈተውን ማድ ቤት በር ገፋ አድርጋ ስትገባ ከቅዱስ ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጡ።

ቅዱስ የእግሯን ደም ተመለከተ፡ ደሙን ለማስቆም የሆነ ነገር ማድረግ ነበረበት። ጃኬቱን ገልበጥ አደረገና ገበሩን በጥርሱ ቀደደው፤ የሚደማውን እግሯን ጠቀለለና "ማምለጥ አለብን" አላት። የቅዱስ አጠገቧ መኖር ኃይል ጨመረላት። የወታደሮቹ ግርግር ጥቂት ረገብ ሲል ከነበሩበት ኩሽና ወጥተው መንገድ ጀመሩ። ብዙም ሳይጓዙ ግን ወታደሮቹ እንደገና መጡባቸው፤ የሚገቡበት ግቢ በአካባቢያቸው አላገኙም። በአቅራቢያቸው ወደነበረው የሥላሴ ጫካ ውስጥ ከመግባታቸው ተኩስና ጩኸቱ ድብልቅልቅ አለ።

ሁከቱ ሊበርድ አልቻለም፤ የጥይቱ ድምፅ አላቆመም። ጊዜው እየመሸ ሄደና ለዓይን ያዘ። ትርምስምሱ ጥቂት ጋብ ይልና እንደገና ይጀምራል። የወታደሮቹ ርምጃና ጥይቱ ይቀጥላል። የእናቶች ጩኸትና በወታደሮቹ እጅ የገቡ ወጣቶች መፈክር ያስተጋባል። ብቻ አካባቢው እንደተደበላለቀ ጊዜው በጣም መሸ፤ ባለበት ጫካ ውስጥ ከማደር የተሻለ አማራጭ አልነበራቸውም።

"ምን ይሻለናል?" አለችው ቅዱስን በቀስታ።

"አርፈን ከመቀመጥ የተሻለ ምርጫ የለም" አላት ቅዱስ።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሁሉም ነገር እንደገና ፀጥ አለ፡፡ ፍሬሕይወትና ቅዱስ ተያዩ።

"እንሞክር እንዴ" አለች ፍሬ።

"በእኔ በኩል የምሞክረው የለኝም" አለ ቅዱስ ድምጹን ዝቅ አድርጎ።

"ችግር የለም እኛ ቤት ታድራለህ" አለችው አባባሉ ስለገባት።

"እርግጠኛ ነሽ?" አለ ቅዱስ በችኮላ።

"አትጠራጠር" አለችው በሀሳቧ ለቅዱስ ማደሪያ እያመቻቸች።

ተነስታ ለመቆም ስትሞክር ሽበ የቀደደው እግሯ በጣም አመማት፡፡ ቅዱስ ደገፋትና ለመራመድ ሞከሩ ሁለት ርምጃ እንደተራመዱች በቅርብ ርቀት ላይ ድብልቅልቅ ያለ ተኩስ ተጀመረ፡፡ ጩኸቱ ተከታተለ፡፡ የፍሬና የቅዱስ ወደቤት የመሄድ ነገርም አበቃለትና ተመልሰው ተቀመጡ፡፡

"ምን ይሻለናል?" አለችው ቅዱስን እንደገና።

"እዚሁ ማደር" አላት በቀላሉ።

"ጅብ ቢበላንስ?"

"ሰዎቹ እጅ ከመግባት አይሻልም?" ነበር የቅዱስ መልስ።

ሌሊቱ ገፋ፣ አልፎ አልፎ ከሚሰማው ጢሽ ጢሽ ከሚለው የጥይት ድምጽና ከወታደሮቹ ርምጃ ኮቴ እንዲሁም ከቀጠሉ ሽሽታ



በስተቀር ሌሊቱ ረጭ አለ፡፡ ፀጥታው ደግሞ በጣም ያስፈራል፡፡ በፀጥታው መሀል የሚሰማው ማናቸውም ኮሽታ ያስደነግጣል፡፡ ያም ሆኖ ፍሬና ቅዱስ ከሃሳባቸው ጋር ነጉደዋል።

"ሌሎቹስ ልጆች እንዴት ሆነው ይሆን? ስንቶቹ ወድቀው፣ ስንቶቹ ታስረው ይሆን? ስንቶቹስ እንደእኛ መውጫ ቀዳዳ አጥተው ተደብቀው ይሆን?..." የጥይቱ እሩምታ ፀጥታውን ሰነጣጠቀው። ፍሬና ቅዱስ ተያዩ፡፡ የእግሯ ቁስል ጥዝጣዜው እየጨመረ ሄደ:: ሌሊቱ ድጋሚ የማይነጋ መሰላት::   ቅዱስ እግሮቹን ዘረጋና "እዚህ ላይ ጋደም በይ" አላት ወደጀሮዋ ተጠግቶ፡፡ ጋደም አለች፣ ጃኬቱን አውልቆ ሲደርብላት፣ ለመከራከር ሞከረች "በፍፁም!" አለ ቅዱስ፡፡

ለስንት ደቂቃዎች እንደሆነ ባታውቅም እንቅልፍ ሸለብ አድርጓታል፡፡ ከእንቅልፏ ስትነቃና ዐይኖቿን ገለጥ ስታደርጋቸው ተፈጥሮ ሕጉን ጠብቆ ሌሊቱ ለቀኑ ቦታውን ሊለቅ ተሰናድቷል፡፡ ሰማዩ በጥቂቱ ፈገግ ብሏል ወፎቹም መንጫጫት ጀምረዋል፡፡ ቀና ብላ ቅዱስን ተመለከተችው፣ እርሱም ራሱን ግንዱ ላይ ደገፍ እንዳደረገ ዐይኖቹን ጨፍኗል፡፡ ተንተርሳው ከነበረው እግሩ ላይ ለመነሳት ቀስቀስ ስትል ዓይኖቹን ገለጣቸው፡፡

"እንደምን አደሩ?" አላት ፈገግ ብሎ።

"አደርን ማለት ነው?" ነበር የእርሷ መልስ።

"በብርድ ስትጠበስ አደርክ አይደል? አለችው ራሷን እየታዘበችው።

"ገና ብዙ ይጠብቀናል መስዋእትነቱ ተጀመረ እንጂ አላለቀም፡፡ ይልቅስ እግርሽ እንዴት ነው?" አለ ያሰረውን ጨርቅ እየፈታ፡፡ ደሙ ቆሟል ቅዝቃዜው ግን ህመሙን አበረታባት፡፡ ሆኖም የለበሰችው ሱሪ በመሆኑ ማንም እንደማያይባት አረጋግጣ ዘና አለች፡፡

በመንገዱ ላይ ሰዎች መመላለስ ጀምረዋል፡፡ "እንሞክር?" አለ ቅዱስ አካባቢያዊ ቅኝት ካደረገ በኋላ። ከጫካው ወጡና በለስ ቀንቷቸው ያለችግር ሰፈር ደረሱ፡፡ ሰፈር አካባቢ በጣም ሳይጠጉ መለያየት ነበረባቸው "እናቸንፋለን! የቀጠሮ ሰዓታችን እንደተጠበቀ ነው" አለ ወደጀሮዋ ተጠግቶ፡፡ መስማማቷን በራሷ ገለጸችለት፡፡ ርምጃውን ፈጠን አደረገና ሄደ፡፡

* * * *

ወይዘሮ ስርጉት ሚያዝያ 23 ቀን "የዓለም የሠራተኞች ቀን" መሆኑን ልጆቻቸው ሲነጋገሩ ሰምተዋል። የት፣ መቼና እንዴት እንደተጀመረ ሲሰሙ "ወይ ጉድ ይህ ነገር ለካንስ በዓለም ሁሉ ላይ ነው ያለው!" ብለው ተገርመውም ነበር። ይህ ዕለት የራሱ መዝሙር እንዳለውም ሚሚ ነግራቸዋለች፤ እንዲያውም ወረቀት ይዛ ግጥሙን ጭምር ስታጠናም አይተዋታል። ቃሉ ግን ከበድ ብሏቸው አልያዙትም እንጂ አንዳንድ ስንኞች አንዳንዴ ወደአእምሮአቸው መምጣታቸውም አልቀረም።

"ምን ነበር?" አሉና ጥቂት አሰቡ።

"... ያለም መሠረት አዲስ ይሁን
ኢምንት ነን እልፍ እንሁን..." ሳያስቡት ዜማውን ለማዜም ጀመር አደረጉና ሳቃቸው አቋርጧቸው ተውት።

"ኧረ ጉድ ነው እነዚህ ልጆች እኔንም ጨምረው ሊያሳብዱኝ ነው!" አሉ ለራሳቸው።

ከሀሳባቸው መለስ ሲሉ የልጆቹ ሁኔታ ታያቸው። ቃለአብና ሚሚ እቤት አላደሩም፤ አመሻሽ ላይ ሁለቱም ተከታትለው ወጡ። ሚሚ አለባበሷም የተለየ ነበር፤ አርጀት ያለ ሱሪና ሸራ ጫማ አድርጋና ሻሽ አስራ ነጠላ ደርባ ነበር የወጣችው።

ቃለአብ ያው እንደተለመደው "ዛሬ አልመጣም ጓደኞቼጋ ነው የማድረው" ብሎ ወጣ፤ ጓደኛውም እንዲሁ አንዳንዴ እየመጣ ስለሚያድር ቤተሰብ የተቀበለው ጉዳይ ሆኖአል። .



ሚሚ ደግሞ ትንሽ ቆየችና "እማ ዛሬ እኔም አልመጣም" አለች አራሷን እያከከች።

"ደግሞ አንቺ የት ነሽ?" አሉ እናቷ። እንዲያው ለአፋቸው ጠየቁ እንጂ ሁል ጊዜም ልጆቹ አመሻሽ ላይ ከቤት ወጥተው ባደሩባቸው ጊዜያት ሁሉ በማግስቱ የሚፈጠሩትን ነገሮች ሲታዘቡ በመቆየታቸው ለምን እንደሚወጡ ገምተዋል።

የአሁኑ ግን ለየት አለባቸው፤ የልጆቻቸው ዝግጅት አላማራቸውም፤ ሁሉም በየፊናቸው የየራሳቸውን ዝግጅት ሲያደርጉ መራወጥ አብዝተዋል። ሚሚ በጠዋት መጣችና የተለመደ የሥራ አለባበሷን ለብሳ "ደህና ዋይ እማ" አለቻቸውና ሄደች። ጥቂት ቆይቶ ቃለአብ እቤት ገብቶ የቀረበለትን ምግብ በጥድፊያ ጎራርሶ ተመልሶ ወጣ።

"ኧረ ተው ልጄ ምግቡ ከጉሮሮህ ይውረድ" አሉት ወይዘሮ ስርጉት።

"እማ ጊዜ የለም፣ ማረፍ ከድል በኋላ ነው" አላቸው። ቃለአብ መቼም የድሉ ቀን የተቀጠረ ይመስል ስለ ድሉ ቀን በየአጋጣሚው ሳያወራ አያልፍም።

ወደቀን ላይ ደግሞ ፍሬሕይወት ከሄደችበት መጣች።

"እማ ብቻሽን ነሽ አይደል?" አለች የቤቱን ጭር ማለት ስታይ።

"ቡና ላፍላልሽ?" አለቻቸው ደግሞ ሰዓቷን ተመልክታ።

"አይ ማታ ይሻላል" አሏት። እንዲያው ስለጨነቃት እንጂ ቡና የማፍላት ስሜቱ እንደሌላት ታስታውቃለች።

እንደነገሩ ምሳዋን ቀማመሰችና ወደመኝታቤት ገባች። ስትወጣ ራንግለር ሱሪና ሸራ ጫማ፤ ከላይ ደግሞ ወፈር ያለ ሹራብ ለብሳለች።

"ዛሬማ የሆነ ነገር አለ" አሉ ወይዘሮ ስርጉት ለራሳቸው።

ሁኔታውን ከመከታተል በስተቀር አስተያየት መስጠት ግን አልደፈሩም። አስተያየት መስጠቱ ምን ሊፈይድ? ልጆቹ ብዙ ርቀው መሄዳቸውን በሚገባ ተረድተዋል። ልጆቹ የራሳቸውን ነገር እርግፍ አድርገው ትተው ያን ያህል ለሕዝብ ማሰባቸው ግን በጣም ይገርማቸዋል።

ከሰዓት በኋላው የዚያን ሁሉ ዝግጅት መቋጫ ይዞ ከተፍ አለ። አዲስ አበባ በጥይት ድምጽ ታጀበች። እዚህም እዚያም ተኩስና ጩኸት ሆነ። ወይዘሮ ስርጉት የሚያርፍ ልብ የሚቀመጥ ሰውነት ሊኖራቸው አልቻለም።

"ወጣ ብዬ ሁኔታውን ተመልክቼ እመጣለሁ እርስዎ ጊቢውን ይጠብቁ" አሏቸው የበላይሁንን እናት።

"አይደረግም፣ አትሄጂም፣ እዚሁ ሆነን የሚሆነውን እንጠብቃለን" አሉ የበላይሁን እናት ተንበርክከው ከሚጸልዩበት ቀና ብለው።

"ግዴለዎትም በአንድአፍታ ነው የምመለሰው" አሉና ወይዘሮ ስርጉት መልስም ሳይጠብቁ ወጡ።

አሁንም የጥይቱ ድምጽ አልፎ አልፎ ይሰማል፡ ወይዘሮ ስርጉት ነጠላቸውን ለብሰው ከቤት እንደወጡ በርከት ያለ የጥይት ድምጽ ወደሚሰማበት ወደአቧሬ ነው ያቀኑት። በመንገዱ ላይ የሚታዩት እንደእርሳቸው የተደናገጡና የሚያደርጉት የጠፋቸው እናቶች ናቸው። አንዳንድ መድረሻ ያጡ የሚመስሉ ወጣቶችም ከወዲያ ወዲህ እየተሯሯጡ ከፊት ብሎ ባገኙት ጊቢ ሁሉ ይገባሉ።

የመኪና ድምጽ ሲሰሙ ዞር አሉ፡ ሁለት በወታደሮች የተሞሉ ትላልቅ መኪናዎች ከኋላቸው ሲመጡ ተመለከቱና ድንጋጤያቸውን ተቆጣጥረው በመረጋጋት መንገዳቸውን ቀጠሉ። ከፊት ለፊታቸው ደግሞ መደበቂያ የሚፈልጉ በርከት ያሉ



ወጣቶች ወደእርሳቸው አቅጣጫ ሲመጡ ተመለከቱ። ምን እንደሚያደርጉ ግራ ገብቶአቸው እያሉ ወጣቶቹ መኪናዎቹን ከሩቅ ተመልክተው ወደየስርቻው ተበታተኑ። ወታደሮቹም ከመኪናዎቻቸው ዱብ ዱብ ብለው ልጆቹ ወደየገቡበት አቅጣጫ ሮጡ።

አሁንም ከርቀት የሚሰማው የተኩስ ድምጽ አላቆመም። በመመለስና ባለመመለስ መሀል እየመነኑ ሳሉ በአጭር ርቀት ላይ የተኩስ ድምጽ ተሰማቸው፤ የበለጠ ደነገጡ። ወዲያውኑ ወታደሮቹ አራት ያህል ወጣቶችን እያዳፉ ወደመኪናው ወረወሯቸው። ወይዘሮ ስርጉት ከዚያ በላይ መመልከት በፍጹም አልፈለጉም ገባ ብለው ከቆሙበት የአጥር ጥግ ወጥተው ወደቤታቸው ተመለሱ።

ሰፈር ሲደርሱ ብዙዎቹ እናቶች በየአካባቢያቸው ሰብሰብ ብለው ያወራሉ። እቤት ሲገቡ የበላይሁን እናት ጥቂት ተረጋግተው አገኟቸው።

"ስርጉቴ በላይ ደህና ነኝ ብሎ ደወለልኝ። እንዲያው ምን ሰማሽ?" አሏቸው።

"ጎሽ እንኳል ደወለ፤ እኔ እንኳን ምንም አልሰማሁም። ማንም ስለምንም የሚያውቅ አይመስልም" አሏቸው።

ሚሚ በሰዓቱ ከሥራ ተመለሰች። "አልመጡም?" አለች ገና ስትገባ። ሮቤል ወንበሩ ላይ ኩርችች ብሎ የእናቱን ጭንቀት የተጋራ ይመስላል።

"ልብስ ልበስ እንጂ ሮቤል" አለችው ሚሚ ሁኔታው አሳዝኗት።

"አልበረደኝም" አላት በአጭሩ።

ምሽቱ የጭንቀት ምሽት ሆነ፤ አንዳቸውም ብቅ አላሉም። ወይዘሮ ስርጉት ወታደሮቹን ባሰቡ ቁጥር ሆዳቸው ይላወሳል፤ እነዚያን የሚገቡበት ያጡ ወጣቶች ሲያስታውሱ ፍሬሕይወትና ቃለአብ

ድቅን ይሉባቸዋል። ሰዓቱ በመሸ ቁጥር ደግሞ ጭንቀታቸው ይጨምራል።

ከተቀመጡበት ተነስተው ወደደጅ ወጡ፤ ሮቤልም ተከተላቸው። ፊታቸውን ወደገብርኤል ቤተክርስቲያን መልሰው የተለመደ መማጸናቸውን ጀመሩ።

"ምነው ወላዲተ አምላክ የልጅን ነገር ስታውቂው! እባክሽን እናቴ ጭንቄን ተመልከች፣ ልፋቴንና ድካሜን አስተውይ..."

"ስርጉት" አሉ የበላይሁን እናት

"እመት" አሉ የፍሬሕይውት እናት ጸሎታቸውን አቋርጠው።

"ቃለአብ ደውሎአል" አሉ የበላይሁን እናት ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው።

"ተመስገን! ተመስገን..." አሉ ወይዘሮ ስርጉት መሬት በግንባራቸው ተደፍተው።

"እንግዲህ አንድ ምጥ ቀረ፤ ለርሷም እመቤቴ ታውቃለች ቤት ግቢ" አሉ የበላይሁን እናት።

"የእውነታቸውን ነው፤ እደጅ በመሆን ምን ታተርፊያለሽ። ደግሞ ምንም አትሆንም ጓደኞቿ ጋ ገብታ ነው የሚሆነው" አለች ሚሚ እናቷን ለማረጋጋት።

ጊዜው መሸ፤ ወደ ሌሊት እየተቃረበ ነው። ፍሬሕይወት ግን አልመጣችም፤ የእናቷ ምጥም እንደቀጠለ ነው። ሚሚና ሮቤል እንዲተኙ ለማድረግ እርሳቸውም አልጋቸው ላይ ወጡ። እንቅልፍ እንዲወስዳቸው መሞከር ዘበት ነው። እንዴት አድርገው እንቅልፍ ሊያስቡ ይችላሉ? አሳቢያቸውና የመጀመሪያ ልጃቸው ፍሬሕይወት የወደቀችበትን ሳያውቁ እንቅልፍ እንዴት ሊወስዳቸው ይችላል?



እንደተንቆራጠጡና እንደተንበረከኩ ሌሊቱ ሊነጋ ተቃረበ። ወይዘሮ ስርጉት ተኩስና ቅልጥ ያለ ጩኸት ሰሙ፤ ተፈናጥረው በሩን ከፈቱና ወጡ። በዚያው ቅጽበትም የነበላይሁን ቤትም ተከፈተ፤ የበላይሁን አባት ነበሩ።

"በይ እንዳትወጭ" አሉ የበላይሁን አባት።

"ለሁሉም ነገር መረጋጋት ያስፈልጋል፤ እንዲያው ምን እንደሆነ ሳይታወቅ ..." የበላይሁን አባት የጀመሩትን ሳይጨርሱት ተኩሱና ጩኸቱ ተከታታለ። የበለጠ መደናገጥ ሆነ።

ከንጋቱ አስራአንድ ሰዓት ተኩል አልፏል፤ ተኩሱ ራቅ እያለ የሄደ መሰለ። ጩኸቱ ግን እንደቀጠለ ነው።

የፍሬሕይወት እናት "ወንድምሽን ጠብቂው" አሉና ሚሚ በሩን እንድትዘጋ ነግረዋት ወጡ። ሚሚ ነጠላቸውን ይዛ እንዳይሄዱ ለማድረግ ያደረገችው ጥረት እንዳልተሳካላት ስታውቅ በሩን ዘግታ ሮቤልን ማባበል ያዘች። የነበላይሁን በር ሲከፈት ስትሰማ አባቱ መሆናቸውን አሰበችና ጥቂት ተረጋጋች።

ወይዘሮ ስርጉት ጩኸቱና ግርግሩ ወደተበራከተበት ሄዱ፤ በርካታ ሰዎች ወጥተው አካባቢውን ሞልተውታል፤ እዚህም እዚያም ቤት ዋይታ ሆኖአል። በሰዎቹ መሀል አልፈው ወደውስጥ ሲዘልቁ ሁለት ወጣቶች ወድቀው ተመለከቱ፡ ወንድማማቾች ናቸው። "እናታችሁ ዝርግት ትበል" አሉ ደረታቸውን እየደለቁ። ሁሉ ሰው በድንጋጤ በድን የሆነ፤ እንባውም የደረቀበት ይመስላል። እናቶች መሬቱ ላይ ይንከባለላሉ።

የበርካታ ቤቶች ደጃፎች የልጆች አስከሬን ወድቆባቸዋል። በተለይም የአንድ ቤተሰብ ሶስት ልጆች ተገድለው ከቤታቸው አቅራቢያ ተጥለዋል። የልጆቹ ወላጆች ራሳቸውን አያውቁም፤ አእምሮአቸውን ስተው እብድ ብለዋል። ሰዉ የሚያደርገው ጠፍቶት በማለዳው ብርድ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ይንገዋለላል።

“ኀበዝ አንስተን ወደየቤት አናስገባም? እጣችን ይሄ ከሆነ” አሉ አንድ ሰው።

“ማንሳት ተከልክሏል” አሉ ደግሞ ሌላ ሰው።

ወደሰማይ የተተኮሱ ሁለት ጥይቶች ሰውን ከገባበት ድንዛዜ አወጡት። “ተበተኑ” አለ ጥይቱን የተኮሰው ወታደር። በርከት ያሉ ወታደሮችም ተከታትለው ደረሱ።

የልጆቹን ወላጆች ወታደሮቹ እየገፈታተሩ ወደየቤታቸው አስገቧቸው፤ የልጆቻቸውን አስከሬን በራቸው ላይ ትተው።

ወይዘሮ ስርጉት የተፈጠሩበትን ቀን እየረገሙ ፤ እንባቸው ያለማቋረጥ በጉንጮቻቸው ላይ እየወረደ፤ ሰውነታቸው እየራደ ወደሰፈራቸው ተመለሱ።

የፍሬሕይወት እናት ከሌሎቹ እናቶች ተቀላቀሉ። ፍሬሕይወት በቀስታ እየተራመደች ወደተሰበሰቡት እናቶች ተጠጋች፤ደንግጣለች፤ ድንጋጤዋ የእግሯን ህመም አስረስቷት እርምጃዋን ፈጣን አደረገችው፡፡ እናቷን ከሴቶቹ መሃል ለየቻቸው። እርሳቸውም ወዲያውኑ አዩአትና ወደእርሷ መጡ፡፡ ዐይኖቻቸውን ማመን ያቃታቸው ይመስላሉ "እውነት ነው? ተርፈሽ መጣሽ?..." እያሉ አቀፏት፡፡

ለፍሬሕይወት እናቷ ቀስ በቀስ መርዶውን ሁሉ ነገሯት፡፡ ከትናንትናው ግርግር አመለጥን ብለው እየሮጡ ወደየቤታቸው የገቡትን እያነቁ በየቤታቸው በር ላይ ነበር የገደሏቸው፡፡ የሞቱት ወጣቶች ቁጥር ዘገነናት! እልህ፤ ንዴትና ቁጭት ደሟን ሲያመሩት ተሰማት፡፡

ከነፍሬሕይወት ሰፈር ያለቁት ወጣቶች ሁሉ አብሮ አደጎቿ ናቸው፡፡ ሀዘኑ የመረረ ሆነ፡፡ ከሰዓት በኋላ በአስር ሰዓት የካ ሚካኤል ለወጣቶቹ ቀብር በተሰበሰበ ሕዝብ ተጥለቀለቀ፡፡ እዚህም እዚያም ቀብር ሆነ፡፡ ያውም የወጣት ቀብር! እናቶች ደረታቸው እስኪቆስል ደቁት ልቅሶአቸው እጅግ መረረ። በአንድ አካባቢ



ብቻ አስር አዳዲስ የቀብር ቁልሎች ተደረደሩ፡፡ ማንም ሳያስተባብረው ሀዘንና ምሬት የፈጠረው የተቃውሞ ሰልፍ ተጀመረ፡፡ ወጣቶቹ መፈክሩን ያንበለብሉታል እናቶች እንባቸውን እያዘሩ ይቀበላሉ፡፡ እንደእናቶች አይብዙ እንጂ አባቶችም ሰልፉ ውስጥ ነበሩ፡፡

* * * *

ቅዱስ ከፍሬሕይወት ጋር ከተለያየ በኋላ ሌሎች የሚፈጽማቸው ተግባራት ነበሩት፤ ወደዚያ ከመሄዱ በፊት ግን ልብሱን መቀየር አለበት፤ እናም የግዴታ ወደቤት መግባት ያስፈልገዋል። አጋጣሚው መልካም ነበር፤ ምንም ሳትቆይ ዘጠኝ ቁጥር አውቶቡስ ባዶዋን እየከነፈች መጣችለትና ጥልቅ አለ።

የጥግ ወንበር ይዞ ተቀመጠና በአውቶቡሱ መስታወት ውጭውን ማስተዋል ያዘ። መንገዱ ጭር ብሏል፤ ወዲያና ወዲህ የሚሉ አንዳንድ ሰዎች ቢታዩም ትላልቅ ሰዎች ናችው። ወጣቱን የትናንትናው የሚይ ዴይ ሰላማዊ ሰልፍ ጉዳት ያስደነገጠው ይመስላል፤ በመንገዱ ላይ ይተራመስ የነበረ ወጣት አሁን በፍለጋ ነው ማየት የሚቻለው።
"እንዴት ያስጠላል?" አለ ቅዱስ ለራሱ። ከአውቶቡስ ባይወርድ ወደደ፤ ግን የት ሊሄድ? ምን ምርጫ አለውና! ቅዱስና የአዲስ አበባ መንገዶች እጅግ በጣም ቢተዋወቁም ለነዋሪዎቿ ግን ባይተዋር ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ ኖሯል፤ የቀበሌም መታወቂያ አለው፤ በአካባቢው ሲያልፍ ከማየት በስተቀር የቀበሌውን ውስጥ ግን አይቶት አያውቅም፤ ከቀበሌው አመራር አባላት ውስጥ አንዳቸውንም አያውቃቸውም።

"አሁን አንድ ነገር ብሆን ለእናቴ ማን ይነግራታል?" አለና ራሱን ጠየቀ።

ቅዱስ ተወልዶ ያደገው ጎሐጽዮን ነው። እንደአብዛኛው ቤተሰብ ሁሉ በወንዱ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ወላጆቻቸው በፈቀዱት ጋብቻ የተጣመሩ እናትና አባቱ ብዙ ዓመታት አብረው ኖረዋል። አባትና እናቱ በዕድሜ የሚመጣጠኑ አልነበሩም። ሁልጊዜም ይገርመዋል፤ ባልና ሚስት ሳይሆን አባትና ልጅ ይመስሉት

ነበር። ገና ልጅ ሳለ ነበር እንዴት ሊጋቡ እንደቻሉ እናቱን ጠየቃቸው።

“አባትህ ሲጠልፉኝ ገና የአስራ ሶስት ዓመት ልጅ ነበርኩ፤ ቤተሰቦቼም አላዳኑኝም፤ አባቴ ለሚሆን ሰው ሚስት እንድሆን ፈቀዱ።” አሉት። አባቱ “ማንአለብኝ” ያሉ የባለርስት ልጅ፣ የተፈሩ ሰው እንደነበሩና የእናቱም ቤተሰቦች የሰውየውን ማንአለብኝ ባይነት ፈርተውና የቤተሰቡን ሀብት ተመልክተው ይሁን ብለው እንደ አካባቢው ወግና ስርዓት ልጃቸው ሚስት እንድትሆን መፍቀዳቸውን ነገሩት።

የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ቅዱስን እያበሳጨው፤ በልጅነት አእምሮው ውስጥ እያንዳንዱን ድርጊታቸውን እየቀረፀ በማደጉ ለአባቱ ይህን ሁሉ መብት የሰጣቸውን ስርዓት በጣም ይጠላው ነበር። ለአባቱና ለስርዓቱ ያለውን ጥላቻ ዋጥ አድርጎ ቅዱስ ትምህርቱን በብርታት ተማረ፤ አንድ ቀን እናቱን ከዚያ ስቃይ ሊያወጣቸው እንደሚችል እያሰበ ለሊትና ቀን ይተጋ ነበር። አስረኛ ክፍል ሲደርስ ግን ትምህርቱን ማቋረጥ ነበረበት፤ የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በመታወጁ ምክንያት። ዘመቻው ግን ሩቅ አልወሰደውም እዚያው ጎሐጽዮን ተመደበ።

አባቱ ርስቱን በሙሉ ሸጠው ጥቂት ሲቀር ነበር መሬት ላራሹ የታወጀው። “ለማንም ጭሰኛ ከሚሰጥ እንኳን ሸጥኩት” አሉ አባቱ።

ዘመቻው ቅዱስን ከብዙ ወጣቶች አስተዋወቀው፤ ለማንበብና ለመወያየት ዕድል ከፈተለት። የፖለቲካ ንባቡንና ውይይቱን በቀጠለ ቁጥር ለስርዓቱ የነበረውን ጥላቻ አበረታበት። ለውጥን ናፈቀ፤ እናቱና እናቱን የመሰሉ ሰዎች ሁሉ የነጻነት አየር አግኝተው ጥቂት እፎይ እንዲሉ ተመኘ። በመሬት ከበርቴና በጭሰኛ መሀል ያለው ግንኙነት እንዲቀርና ሁሉም ሠርቶና ደክሞ በግንባሩ ላብ እንዲኖር ናፈቀ፡፡ እናም ትግሉ ውስጥ ሲገባ አላቅማማም። ለለውጥ የሰላ አእምሮውን ለኢሕአፓ የፖለቲካ መስመር አስገዛው፤ ቀንደኛ ከሚባሉት ፖለቲከኞች አንዱ ሆነ፡፡



ከአዲስ አበባ የመጡት ዘማቾች ወደየቤታቸው ሲመለሱ እርሱ ግን እዚያው ሆኖ የፖለቲካ ሥራውን እንዲመራ ተመቻቸ።

ቅዱስ የዘመቻ ሥራውን በማቆሙና በእያንዳንዱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የማይጠፋ መሆኑም ጭምር የሁሉም ዐይን እንዲያርፍበት አደረገው። በየአጋጣሚው ሁሉ መታሰር ተደጋገመበት፤ እናም ከአካባቢው ራቅ ብሎ መሥራት በመታመኑ ወደአዲስ አበባ እንዲመጣ ተወሰነ። እናቱን ትቶ መምጣቱ ግድ ሆነ፤ የትግሉ ጊዜ እንዲያጥርና እናቱ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን እፎይ ብለው፣ ተደስተው እንዲኖሩ እየተመኘ ወደስደት ኑሮ ገባ። በተቻለው አቅም ሁሉ ለእናቱ ደህንነቱን ለመግለጽ ይሞክራል፤ አንዳንዴ ግን አይሳካለትም። ሰሞኑን እንደምንም ብሎ ለእናቱ መላክ እንዳለበት አሰበ።

ፒያሳ ብሪቲሽ ካውንስል አጠገብ መውረድ ሲገባው በሀሳብ ተመስጦ አለፈና መሀል አራዳ ደርሶ አንድ ፋርማታ በእግሩ ተመለሰ። ሁሌም እናቱን ሲያስታውስ እንደሚሆነው መንፈሱ ታወከበት፤ እንዲህ አይነት ስሜት ውስጥ ሲገባ ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጎ ወደእናቱ መመለስ ያምረዋል።

ቁልቁል ወደወንዙ አቅጣጫ በሚያስገቡት መንገዶች በአንደኛው ታጠፈና ፈጠን ፈጠን እያለ ወረደ። እዚያ አካባቢ ሲደርስ መቼም አዲስ አበባ፤ ለዚያውም የከተማ እምብርት በሚባለው ፒያሳ ውስጥ መሆኑን ይጠራጠራል። ሹልክልክ ያሉ መንገዶችና የተሸጎጡት ቤቶች ይገርሙታል፤ ቀበሌው እነዚያን ቤቶች ማወቁ ያጠራጥረዋል። እርሱ የሚገባበት ቤት ትልቅ ነው፤ ለዚያውም ፎቅ፤ የውጭውን የብረት መዝጊያ የሚከፍትበት ቁልፍ ስላለው ማንኳኳት አያስፈልገውም። በቀስታ ከፍቶ ገባ፤ ወደትልቁ ቤት የሚያስገባውን ደረጃ ወደቀኝ ትቶ በስተግራ በኩል አጠፍ አለና በሌላ ደረጃ ቁልቁል ወረደ። ምድር ቤት ውስጥ ነው የቅዱስ ክፍል፤ የቤቱን በር በጥንቃቄ ከፍቶ ገባ።
ከላውንደሪ ቤት ያወጣውን ሙሉ ልብስ ለበሰና እየተጣደፈ ተመልሶ ወጣ። ተከታታይ ሶስት ቀጠሮዎች አሉት።

* * * *

ፍሬሕይወትና ቅዱስ በቀጠሮአቸው ሰዓት ተገናኙ፤ አለባበሱን አደነቀችለት፡፡ የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው ጥሩ መልበስ ነበረባቸውና ሁለቱም የተቻላቸውን አድርገዋል፡፡ የቅዱስ የመጀመሪያ ጥያቄ "ሠፈር እንዴት ነው?" የሚል ነበር። የሆነውን ሁሉ ነገረችው፡፡ ከሁሉም በላይ ሶስት ልጆቻቸው የሞቱባቸው ወላጆች ነገር አሰቃቂ ነበር፡፡ እናትየው ሙሉ በሙሉ አእምሯቸውን ስተዋል አባትየውም ቢሆኑ ከሴትዮዋ ብዙም አይሻሉም፡፡

መለዋወጥ የነበረባቸውን መረጃ በፍጥነት ተለዋወጡ፤ ሊፈጽሟቸው ስለሚገቡ ሥራዎችም አቅደው፤ ከመቼውም ጊዜ በላይ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ተነጋግረው ጨረሱ።

"እኔ ዛሬም ብቻዬን ስላሴ ጫካ ማደሬ አይቀርም" አለ ቅዱስ ሊለያዩ ሲሉ።

"እንዴ! ለምን እኛ ቤት አታድርም?" አለችው ፍሬ ምንም ሳታመነታ፡፡ እሱም ተስማማና ወደ አመሻሽ ላይ እንደገና ሊገናኙ ተቀጣጠሩ፡፡

ወደቤት ስትመለስ ወንድሟን ቃለአብን ስላየችው ደስ አላት፤ "ዛሬ ክፍልህን እፈልጋታለሁ" አለችው ገና ስታገኘው፡፡ ከማድ ቤቱ አጠገብ ወንድሟ የሠራትና መኝታ ቤቱ ያደረጋትን ትንሽ ግን ንፁህ ክፍል እንድትጠቀምባት ያለምንም ጥያቄ ተስማማላት፡፡ መቼም ቤታቸው ውስጥ የፖለቲካ መስመር ልዩነት ያለመኖሩ ከምንም ነገር በላይ የሚያስደስታት ጉዳይ ነው። ቤቱን ለቅዱስ አመቻቸችለትና የተቀጣጠሩበት ቦታ ሂዳ አመጣችው፡፡ በተሻለ ሁኔታ ለማደር በመቻሉ ደስ አላት፡፡

ፍሬሕይወት ሌሊቱን ብዙም እንቅልፍ አልወሰዳትም፤ ማንበብም አልሆንላትም ፤ ኮሽ በለ ቁጥር ስትደነግጥ፤ ከሀሳቧ ጋር ስትጫወት፣ ሌሊቱ ተጋመሰ፡፡ ሊነጋጋ ሲል እንቅልፍ ጥሏት ኖሮ እንድትቀሰቅሳት የሞላቻት ሰዓት ስትጮህ በድንጋጤ ባነነች፡፡ በአስራ አንድ ሰዓት ተነስታ በቀስታ ከመኝታ ቤቷ ወጣችና የጓሮውን በር ከፈተች፤ አካባቢውን ቃኘች አደረገችና ቅዱስ የተኛበትን ክፍል



መዝጊያ አንኳኳች፡፡ ቅዱስ ዝግጁ ነበር ወዲያውኑ በሩን ከፈተና ወጣ፡፡

"ግን ሌሊት አይሆንብህም?" አለችው ጨለማው ገና አለመገፈፉን ስትመለከት።

"ግዴለሽም!" አላትና ወጣ፡፡ የውጭውን በር ዘግታ ስትመለስ ቅዱስን ክፉ ነገር እንዳያጋጥመው ተመኘችለት፡፡

እያደር ሁኔታው እየከፋ ሄደ፡፡ እስርና ግድያው ተበራከተ፤ በዚያው መጠንም በየመንገዱ የሚገደሉት የመንግስት ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጣ፡፡ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳው ሥራ እየተጠናከረ በሕቡዕ የሚታገለው ፓርቲ የወጣት ክንፍ ከምንጊዜውም የበለጠ የሞት ሽረት ትግሉን ቀጠለ፡፡

1969 ዓ.ም ትግሉ ይበልጥ ምርር ክርር አለ፡፡ እንፍሬሕይወትም ያለመታከት ይባክናሉ፡፡ ትምህርት ቤቶች ቢከፈቱም ትምህርት ግን እንደወትሮው ሊቀጥል አልቻለም፡፡ ይልቁንም ት/ቤቶች የትግል ሜዳ ሆኑ፡፡ ብዙም ሳይቆይ "ትምህርት ከድል በኋላ" የሚለው መርህ ለብዙዎች ተዳረሰና አብዛኛው ተማሪ ትምህርቱን አቋረጠ፡፡

በሕቡዕ የሚታገለው ፓርቲ ራሱን ይፋ ለማድረግ ዝግጅቱ በየአቅጣጫው ተጧጡፏል፡፡ አባላት ሁሉ የዚህ ዝግጅት አካል ናቸውና ከመቼውም የበለጠ ተወጣጥረዋል፡፡ በመጨረሻ ያች እለት ደረሰችና የአዲስ አበባ ከተማ በፓርቲው አርማና በራሪ ወረቀቶች አሸበረቀ አደረች፡፡ የኤሌክትሪክ ገመዶች በትናንሾቹ የፓርቲው አርማዎች ተሞልተው የክብረበዓል ባንዲራ መሰሉ፡፡ የቀበሌ መስተዳድርና ፖሊስ ጣቢያዎች ሳይቀሩ በተበተኑ ወረቀቶች ተዳረሱ፡፡ የአጥሮቻቸው ግንቦችና የቤቶች ግድግዳዎች በቀይ ቀለም በተፃፉ መፈክሮች አሸበረቁ፡፡

"ኢሕአፓ ያቸንፋል!" "ሞት ለፋሽስቶች!" የሚሉት መፈክሮች የአላፊ አግዳሚውን ዓይኖች ማረኩ፡፡

የፖለቲካ ውጥረቱ መንግሥትን ፋታ ነሳው፡፡ ውጥረቱን ለማስታገስ ማሰነ፡፡ ያልተጠበቁ የቤት ለቤት አሰሳዎች በተደጋጋሚ ተካሄዱ፡፡ ስጋቱ የጋራ እየሆነ መጣ፡፡ እንቅስቃሴዎች የበለጠ ጥንቃቄ የተሞላባቸው ሆኑ፡፡ ፍሬና አንተነህ መገናኘት የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ተፈጠሩ፡፡ እያደር ሁኔታዎች እየተባባሱ ይሄዳሉ፡፡ ከየመንገዱ ተይዞ መታሰር፣ በመኪናዎች ሆነው በከተማው ውስጥ በሚዞሩ ታጣቂዎች መገደል በተለይም የወጣቱ የዕለት ተዕለት ገጠመኝ ሆነ፡፡ በዚያው መጠን በሕቡዕ በሚታገለው ፓርቲ የሚመቱት የመንግሥት ኃይሎች ቁጥርም ተበራከተ፡፡ በነጻነት መንቀሳቀስ ትዝታ ብቻ ሆነ፡፡ የድርጅቱ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ እየረቀቀና እየጠነከረ መጣ፡፡

ፍሬሕይወት አንተነህን ሳታየው አራት ቀናት አለፉ፤ "ዛሬስ ሳላየው በፍጹም አላድርም" አለች ለራሷ ከአንድ ቀጠሮ ወደቤቷ ስትመለስ፡፡ መንገድ ላይ ስልክ ደወለችለት፤ ስልኩን ያነሳው ራሱ ነው፤ ደስ አላት፡፡

"እንኳን ደወልሽልኝ" አላት ገና ድምጿን ሲሰማ፡፡ ወዲያውኑ መገናኘታቸው እንደሚያስፈልግ ነገራት፡፡ የተገናኙት መናኸሪያ ሆቴል አጠገብ ነው፡፡ አንተነህ የተረጋጋ ቢመስልም ዓይኖቹ ግን ከወትሮው የበለጠ ንቁ ናቸው፡፡ "ዛሬ ማታ አሰሳ ይኖራል" አላት እቅፍ አድርጎ እየሳማት፡፡ አብረው ሊቆዩ እንደማይችሉ ነገራት፡፡ እርሷም መረጃውን በተቻላት መጠን ለሁሉም ማዳረስ ነበረባት፡፡ እስከ ገብርኤል መሳለሚያ ድረስ አንገቷን እንዳቀፋት አብረው ሄዱ፡፡ ልቧን ፍርሀት ሲሰረስረው ተሰማት ዐይኖቹን እያየች ፍዝዝ አደረጋት፡፡ ሁኔታዋ እርሱንም የረበሸው መሰላት፡፡

"በጣም ቀፎኛል የዛሬን ማታ አብረን ብንሆን እንዴት ጥሩ ነበር" አለችው።

"ፍርዬ እኔም ደስ ይለኝ ነበር፤ ግን ብዙ ሥራ አለ፤ መረጃው ለብዙ ጓዶች መድረስ አለበት፡፡ ሁኔታዎች ከተስተካከሉ እንደገና እንገናኛለን፡፡ ልክ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ የተለመደው ቦታ እንገናኝ፡፡ ከሰዓቱ ግን በአንድ ደቂቃም ቢሆን መዘግየት



አይቻልም፡፡ ሻርፕ በሰዓቱ ካልተገናኘን ወዲያውኑ ወደቤት ተመለሽ፤ ምንም አታስቢ" አላት፡፡ ድምጹ ግን የወትሮው አልነበረም፡፡

ምንም ልትለው አልቻለችም፡፡ ደግሞም የጥንካሬያቸው መፈተኛ ወቅት አሁን ነው፡፡ ከፍቅር በላይ የሆነው ዓላማ መቅደም አለበት፡፡ በዚያችው ደቂቃ ብዙዎች የትግል ጓዶች በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ናቸው፡፡

"በሰላም እንደምንገናኝ እምነቴ ነው!" አለችው ሲለያዩ።

"አይዞን!" አላትና ሄደ፡፡ ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ሆኗል፡፡ ፍሬሕይወትም መረጃውን ለሁሉም እንዲደርስ የበኩሏን ለማድረግ ተጣደፈች፡፡

ወደአመሻሹ ላይ ደመናው በሰማዩ ላይ ተንጠልጥሎ የበልግ ዝናብ ሊጥል ማካፋት ጀመረ፡፡ ማድረግ ያለባትን ሁሉ አድርጋ ከአንተነህ ጋር ወደምትገናኝበት ቦታ ሄደች፡፡ ልክ በሰዓቱ ደረሰችና አካባቢውን ቃኘት አደረገችው፡፡ አንተነህ አልመጣም፤ ልትጠብቀውም እንደማትችል ታውቃለች፡፡

ካፊያው አላቋረጠም፡፡ ሽፍ ሽፍ በሚለው ዝናብ የጨፈገገው ምሽት በጣም ያስጠላል፤ አንዳች የጭንቀት መንፈስ አየሩን ሁሉ በክሎታል፡፡ ሁሉ ነገር ቅፍፍ ያለ ነው፡፡ በአላፊ አግዳሚው ላይ ዐይኖቻቸውን የሚያጉረጠርጡት ወታደሮች በጣም ያስፈራሉ፡፡ ሰፈር ስትደርስ ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሆኗል፡፡ ወደቤት ልትገባ ስትል በላይሁን ትዝ አላትና ወደእነርሱ ቤት ሄደች፡፡ በላይሁን ቤት አልነበረም፡፡ የበላይሁን እናትም ተጨንቀዋል፡፡

"እንደምን አመሹ እማማ" አለቻቸው በሩን ገባ እንዳለች።

"እኔማ ምን እሆናለሁ" አሏት ፍርሃት የጨመደደውን ፊታቸውን እያሻሹ።

"በስንት ሰዓት ነው የሄደው?" አለች ደግሞ።

"ኧረ እሱስ ቅርብ ጊዜ ነው፡፡ ካልመጣሁ አትስጊ ብሎኝ ነው የሄደው" አሉ ከተቀመጡበት ተነስተው እየተንቆራጠጡ "ደግሞ ቢመጡ እንዳትደናገጭ" ማለቱ ነው የገረመኝ፤ አባትየውስ የእርሱው ቢጤ አይደል ተቆጥቶ እንደማስቀረት ገንዘብ ሰጥቶ ሸኘው፤ እኔማ ምን አቅም አለኝ" አሉ በምሬት።

ማስተዛዘኛ ቃላት አልነበራትምና በዝምታ ወደቤቷ ገባች፡፡ ቤትም ያው ነው፡፡ ቤቱ እንዳች አዚም የያዘው ይመስላል፡፡ እና ሆኗል፤ ሮቤልን ብቻውን ኩርችች ብሎ ስተታየው አሳዘናት፡፡ ታናሽ ወንድሟ ቃለአብም ሆነ ሚሚ እቤት የሉም። ወደጓዳ ስትገባ እናቷ ይንጎዳጎዳሉ፡፡

"ምን እያደረግሽ ነው እማ?" አለቻቸው።

"ጥቂት ሰወር ቢል ብዬ ነዋ" አሏት በትልቅ ላስቲክ የሞላውን ነገር እያሳዩአት።

"ምንድነው እሱ እማ?" አለች ተገርማ።

"ምኑን አውቄው? ብቻ ስታገላብጡት የምትውሉት ወረቀታወረቀት ነው፡፡ ድንገት ከመጡ..." አሏት ቆም ብለው።

"እማ ሙች ጥንቃቄሽ በጣም አሪፍ ነው፤ ግን እሱ ሁሉ ምንም የለውም አትስጊ የትምህርት ወረቀቶች ናቸው፡፡ ግን ምን ትዝ እንዳለኝ ልንገርሽ? የማክሲም ጎርኪ "እናት" ድቅን አለችብኝ"

"ደግሞ ማክሲ የትኛው ልጅ ነው?" አሏት ቀበል አድርገው።

"ማክሲም ጎርኪ የዚህ አገር ልጅ አይደለም፡፡ የሩሲያ ደራሲ ነው፡፡ ትቆጫለሽ ብዬ ነው እንጂ ያን እለት ምባድ የተቃጠለብኝ የእርሱን መጽሐፍ ሳነብ ነበር፡፡ ባለታሪኳ እናት መስጣኝ ነበር እንጀራ መጋገሬን ረስቼ እንደዛ የሆነብኝ፡፡ ቆይ አንድ ቀን አነብልሻለሁ፡፡"

"እስኪ ዛሬን ተርፋችሁ እደሩና እኔንም አንድኛውን አብራችሁ አሳብዳችሁ ታሳርፉኛላችሁ" አሏት በትዝብት ሲሰሟት ቆይተው።



"ምንም አይመጣም አትስጊ" አለች ፍሬሕይወት፡ ውስጧ ግን ስጋት ገብቷል፡፡

ወደስድስት ሰዓት አካባቢ ዝናቡ በደንብ መዝነብ ጀመረ፡፡ አልጋዋ ላይ ተጋድማ ዐይኖቿን ጣሪያው ላይ ሰቅላ ብዙ ቆየች፡፡ ጆሮዎቿ ግን በዝናቡ ውስጥ የበርና የአጥር ኳኳታ ለማዳመጥ ቀጥ ብለዋል፡፡ "አሁን በዚህ ዝናብ እንዴት ይመጣሉ ብዬ ነው?" በማለት ራሷን ጠየቀችና ዘና ብላ ተኛች፡፡

ጥቂት ቆይቶ ዝናቡ እየቀነሰ ሄደ፡፡ ካፊያው ግን አሁንም አላበቃም፡፡ ድንገት የጥይት ድምጽ ሰማች፡፡ ተፈናጥራ ከአልጋዋ ላይ ወረደች፡፡ ተኩሱ ተደጋገመ አቅጣጫውን ለመለየት ቆመች ወደአቧሬ ይመስላል፡፡ ትንሹ ወንድሟ ሮቤል ከተኛበት ተነስቶ በድንጋጤ የሚገባበት ጠፍቶታል፡፡ እናቷ ክፍሉ መሀል ቆመዋል፡፡ ሮቤልን ለማረጋጋት ሞከረችና ወደውስጥ እንዲገባ አደረገች፡ ተኩሱ እንደገና ተንጣጣ፡ በሩን ልትከፍት አስባ ገና አንድ ጊዜ ስትራመድ እናቷ ጥርቅም አድርገው ያዙትና

"እዚሁ ሲመጡ ትደርሽበታለሽ" አሏት በቁጣ።

ልቧ በፍጹም ሊያርፍ አልቻለም፡፡ " እማ! ምናለ ብቅ ብዬ አቅጣጫውን ባዳምጥ?" አለች በማስተዛዘን።

"ምኑን ነው የምታዳምጪው? እዚያ ያሉት አነሱና አንቺም ትጨመሪልኝ?" አሉ እንድቀመጥ ገፋ አድርገዋት፡፡ "ወይኔ ልጆቼ ዛሬስ የመጨረሻ ሳይሆን አይቀርም" አሉና እንባቸው በመንታ መውረድ ጀመረ፡፡ ወለሉ ላይ ተንበረከኩ፡ ደግሞ አቅጣጫቸውን ወደገብርኤል ቤተክርስቲያን አስተካከሉና "አንተ የማቢው ገብርኤል...." እያሉ መማፀን ጀመሩ፡፡

ቃለአብ እንደተለመደው ጓደኛው ዘንድ እንደሚሄድ ተናግሮ ወጥቷል። ሚሚ ጠዋት ወደሥራ ስትሄድ "አክስቴ ጋ ነኝ" ብላ ነው የወጣችው። አክስታቸው ለሚሚ ለየት ያለ ፍቅር ስላላት አብዛኛውን ጊዜ እርሷ ዘንድ እንድትሆን ትፈልጋለች። ወይዘሮ ስርጉትም

እህታቸው መካን በመሆኗ ይህንን ጥያቄዋን መቃወም በፍጹም አይፈልጉም። ባይሆን ሚሚ አክስቷ ጋ ለማደር ተናግራ በሄደች ቁጥር እዚያ ስለማደሯ እርግጠኛ አይደሉም። ያም ሆነ ይህ ለሚሚ ይህ ሁኔታ ተመችቷት በነጻነት እንድትንቀሳቀስ አድርጓታል።

ጋብ ብሎ የነበረው ተኩስ እንደገና ቀጠለ፡፡ ድምጹ ደግሞ እየጎላና እየቀረበ የሚሄድ ይመስላል፡፡ ሮቤል እየሮጠ እናቱና ፍሬሕይወት ወዳሉበት መጣ፡፡ የከባድ መሳሪያ ድምጽ ተከተለ፡፡ እናቷ ሮቤልን ወለሉ ላይ እንዲተኛ አደረጉት፡፡ ተኩሱ ለረጅም ሰዓታት ቀጠለ በፍጹም የሚያበቃ አልመሰለም።

አምስት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ምልልሱ አቆመና አልፎ አልፎ የሚሰማው የተኩስ ድምጽ ብቻ ቀጠለ፡፡ ፍሬሕይወትና እናቷ እንቅልፍ የሚባል ሊወስዳቸው አልቻለም፤ ሌሊቱ መንጋቱን መጠበቅ ብቻ ሆነ፡፡ ሊነጋጋ ሲል የውጭው በር በኃይል ተመታ፡፡ ተፈናጥራ ከአልጋዋ ወረደችና የቤቱን መዝጊያ ከፍታ ወጣች፡፡ እናቷ ከኋላዋ ጎትተው መለሷትና እርሳቸው የውጭውን በር ከፈቱ፡፡ ታጣቂዎቹ እናቷ ገፈታትረው ወደውስጥ ገቡ፡፡ የቀበሌው አብዮት ጥበቃዎች አብረዋቸው አሉ።

እያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው በሰው ውስጥ ፍርሃት ይለቃል፡፡ "መታወቂያ" አላት አንደኛው ፍሬሕይወትን ፡፡ መለስ ብላ ደብተር አነሳችና ከውስጡ መታወቂያዋን አውጥታ ሰጠችው፡፡ በአካባቢው እምብዛም እንቅስቃሴ ስለሌላት አብዮት ጥበቃዎቹ አያውቋትም፡፡ መታወቂያዋን መልሶ ወረወረላት፡፡

"ቃልአብስ?" አለ አንደኛው አብዮት ጥበቃ።

"ትናንት እንደሄደ ነው" አሉ እናቷ ፈጠን ብለው።

"የት?" የተቆጣ ይመስላል።

"እትዬ ጋ ልኬው ነው" አሉ ተረጋግተው፤ አብዮት ጥበቃዎቹ ብዙም አላጠበቁም።



ወታደሮቹ በቤት ውስጥ ያለ አንድም ዕቃ አልቀሩቸውም፡፡ ደብተር፣ ልብስ፣ ወንበር፣ አልጋ፣ የምግብ ዕቃ... ምንቅርቅሩን አውጥተው ፈተሹ፡፡ ምንም አላገኙም፡፡

"ትምህርት ትማሪያለሽ?" አሏት ደግሞ አንደኛው።

"አዎን!" አለች ባለማመንታት፡፡ በመጡበት ሁኔታ ተመልሰው ወጡ፡፡

* * * *

ከንጋቱ በአሥር ሰዓት ሁሉም ነገር ጸጥ አለ። እነአንተነህ ህክምና ሊያገኙ ወደሚችሉበት ሲወሰዱ ሌሎቹ ለአስቸኳይ ስብሰባ እንደገና ለመገናኘት ቀጠሮ ያዙ።

በላይሁን ልብሱን መቀየር ነበረበት፤ እቤቱ ግን መሄድ የለበትም። የት ቢሄድ ልብስ ማግኘት እንደሚችል ጥቂት አሰብ አደረገና ወደጓደኛው ቤት ሄደ። የጓደኛው ቤተሰቦች መሀል ያለው የመግባባት ደረጃ ሁልጊዜም ይደንቀዋል፤ ከቤተሰቡ አልፎ መግባባቱ ለጓደኞችም ይተርፋል፤ እዛ ቤት ገብቶ ይህን እፈልጋለሁ ስጡኝ ብሎ መጠየቅ አያስፈልግም፤ ራስን መርዳት ብቻ ነው። "ምንድነው? ለምን?..." ብሎ የሚጠይቅ የለም።

ጓደኛው ቤት እንደደረሰ ወዲያውኑ ወደቁምሳጥኑ ነው የሄደው። የሚለብሰውን ልብስ እየፈለገ እህቱ ሚሮን ትዝ አለችው፤ ልብሶቹን አጥባና ተኩሳ በጥንቃቄ ነው የምታስቀምጥለት። የመረጠውን ልብስ ይዞ ለመቀየር ልብሶቹን ሲያወላልቅም ሚሮንንና እናቱን፣ ከዛ ደግሞ ፍሬሕይወትን ከሀሳቡ ሊያወጣቸው አልቻለም። አባቱን አስታወሳቸው፤ ድንገት ቢያስፈልግህ ብለው ገንዘብ ሰጥተውት ነበር ትናንት በአስራአንድ ሰዓት የወጣው። ሁልጊዜም ቢሆን የአባቱ ቃላት ከአእምሮው አይጠፉም "አካሄድህ ሁሉ በብልህነት እንጂ በግትርነት አይሁን" ይሉታል።

በላይሁን ትናንት ከቀኑ አሥራአንድ ሰዓት አካባቢ ብዙውን የዕለቱን ሥራውን አከናውኖ ሲጨርስ ስሜቱ ሙሉ አልሆነለትም ነበር። የሆነ ነገር መንፈሱን አጉድሎበት ምን እንደሆነ ለማወቅ ሲሞክር ቆየ።

አስራአንድ ሰዓት ተኩል ላይ ወደቀጠሮ የሄደው የግዱን ነበር። ከቤት ሲወጣ እናቱ በጣም ከፍቷቸው ሲያዩቸው ስሜቱን አባሰበት። የተለመደው ጥያቄያቸው አልቀረለትም "ወዴት ነው የምትሄደው ደግሞ?" ይሉታል በወጣ ቁጥር። እርሱም የተለመደ መልስ አለው። "እዚሁ ነው" ይላቸዋል። ትናንት ግን "ምናልባት ካልመጣሁ አትስጊ" ብሏቸው ነበር የወጣው። ከቤት ሲወጣ ፍሬሕይወትን ሊያገኛት ቢሞክርም አላገኛትም፤ የበለጠ ከፋው።

ቀጠሮው ቦታ የደረሰው በሰዓቱ ነበር፤ በአምስት ደቂቃዎች ውስጥ ሁሉም አባላት አቧሬ በአንደኛው ኮሚቴ አባል ቤት ተገናኙ። በዚህ ስብሰባ ላይ የተገኙት የወጣት ሊጉን አንድ ዞን የሚመሩ ወጣቶች ናቸው፤ የዞን ኮሚቴ ማለት በሊጉ መዋቅር ከላይ ወደታች ሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ከፍተኛ አካል ነው፤ በዚህ ኮሚቴ ውስጥ ከሚሠሩት እነዚህ አባላት አብዛኛዎቹ በእውነተኛ ስማቸው አይተዋወቁም። የሚጠራሩት በኮድ ስማቸው ነው።

የዚህ ዞን ሰብሳቢ ዓለም ይባላል፤ ዓለም የአንተነህ የኮድ ስም ነው። አንተነህና በላይሁን በጣም የሚግባቡ ከመሆናቸው የተነሳ የሚጠራሩት በኮድ ስማቸውም ሳይሆን በቅጽል ስማቸው ነው፤ አንተነህ በላይሁንን በቁመቱ የተነሳ "ሰቀላው" ይለዋል በላይሁን ደግሞ አንተነህን "ሳንሱር" እያለ ይጠራዋል። ይህን ስም የሰጠው አንተነህ ሳያጣራ የሚያሳልፈው ነገር ስለሌለው ነው።

ትናንት ሌሊት የተከሰተውን ነገር ሲያስብ ሰውነቱን ዝግንን አደረገው። ስልክ ተደውሎ አደጋ ላይ መሆናቸው ተነግሮአቸው ለመዘጋጀትና ለማምለጥ ምንም ጊዜ ሳያገኙ ነበር ተኩስ የተከፈተባቸው። መከላከል ነበረባቸውና አጸፋውን ተኩስ ከፈቱ፤ የተኩስ ምልልሱ ረዘም ያለ ጊዜ ወሰደ፤ የመንግሥት ኃይል ያን ያህል የመልስ ተኩስ የጠበቀ አይመስልም። በተኩስ ምልልሱ የነበሩበት ቤት ፍርስርሱ ወጥቶ እነበላይሁን ወደተሰፋ መቁረጥ ሲጠጉ የወዲያኛው ወገን ተኩስ ቆመ። በተኩሱ ውስጥ የተጎዱት ሦስት ሰዎች ቢሆኑም የሞተ ግን አልነበረም። ከተጎዱት ውስጥ አንደኛው ዓለም (አንተነህ) ነበር፤ ከትከሻው ወረድ ብሎ የመታው ጥይት ሰውነቱ ውስጥ ቀርቷል።



በላይሁን ሀሳቡን ሳይጨርሰው ልብሱን ቀያይሮ ጨረሰና ሰዓቱን ተመለከተ፤ "ሰዓቱ ከመቼው ይደርሳል?" አለ ለራሱ። ልብሱን ቀያይሮ ሲወጣ ልዩ ሰው መሰለ።

"ዛሬስ ሰርግ የምትሄድ ነው የመሰልከው" አለችው የጓደኛው እህት ከመኝታ ቤት ሲወጣ። በቁሙ የሰጠችውን ምግብ ጎራረሰና እየተጣደፈ ወጣ።

* * * *

የማታው ዝናብ አካባቢውን አጨቅይቶታል፡፡ በመንገዶቹ ላይ ብዙም ሰው አይታይም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ጋቢያቸውን ለብሰው ከቤተክርስቲያን በእርጋታ ይመለሳሉ አልፎ አልፎ ደግሞ ዝናብ የመታት ፍየል ይመስል ሽምቅቅ ያሉ ወጣቶች ገልመጥ ገልመጥ፣ ጣደፍ ጣደፍ እያሉ ይሄዳሉ፡፡

ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ፍሬሕይወት ጋቢዋን እንደለበሰች ርምጃዋን ፈጠን አድርጋ የሌሊቱን የተኩስ አቅጣጫ ተከትላ ወደአቧሬ ሄደች፡፡ የሄደችው በሰፈር ውስጥ ለውስጥ መንገድ ስለሆነ ብዙ ጊዜ አልወሰደባትም፡፡ በየጥጋጥጉ ሰብሰብ ብለው የሚንሾካሾኩ ሴቶች ስትመለከት ደነገጠች፡፡ ጠጋ ብላ ለመጠየቅም ፈለገችና ደግሞ ፈራች፡፡ እንደምንም ብላ ተጠጋችና ከተሰበሰቡት ሴቶች አንዷዋን ጠየቀች፡፡

"ተርፊዋል ብለሽ ነው ቤቱማ ያውልሽ ፍርስርሱ ወጥቷል" አሏት ሴትዮዋ፡፡ ወታደሮቹ በአካባቢው ያንገዋብባሉ፡፡ ወደቤቷ ተመለሰች፤ አንተነህን ደውላ ማግኘት እንዳለባት አሰበችና ወደአንድ ሱቅ ጎራ ብላ ሞከረች፡፡ አንተነህ ያለመኖሩ ተነገራት ተጨማሪ ማብራሪያ መጠየቅ እንደሌለባት ታውቃለች። ብትጠይቅም ማንም ምንም እንደማይነግራት የታወቀ ነው፡፡ ሆዷን እንደመቁረጥና ማቅለሽለሽ ተሰማት፡፡

ቤት ስትገባ ቃለአብን አገኘችው፤ ሚሚ ደውላ ደህና መሆኗን መናገሯን ነገራት፡፡ በላይሁን ግን አልተመለሰም፤ የአንተነህም ነገር እጅጉን እያሳሰባት ስለነበር ነፍሷ ጭንቅ አለችባት፡፡ ሁልጊዜም እንዲህ ዓይነት የመጠፋፋት ሁኔታ ሲከሰት ከአንተነህ ጋር

የሚፈላለጉበት ሰዓትና ቦታ አላቸው፡፡ እናም በዚያ ሰዓት እንደሚገናኙ ተስፋ አደረገች፡፡ በላይሁን በሰላም እንደሚመለስ ለራሷ ነገረች።

ከጠዋቱ በአራት ሰዓት ስብሰባ አላት፡፡ መቅረት አይኖርባትም፤ ድንገት ቅዱስን አሰበችው እርሱስ የት ይሆን ያደረው? ፡፡ በአራት ሰዓት ቁርጡን እንደምታውቅ አሰበች፤ እንደወትሮው ረጅም ስብሰባ አይኖርም እንጂ መገናኘታቸው አይቀርም፡፡

ልክ በአራት ሰዓት ስብሰባ ቦታ ደረሰች፡፡ ቀጠሮው እነአስቻለው ቤት ነው፤ አስቻለውን በሩ ላይ አገኘችው፤ ትላልቅ ዓይኖቹ የበለጠ ፍጥጥ ብለው ቀልተዋል፡፡ ሰላምታው በጣም ፈጣን ሆነባት፡፡ አስቻለው ምንም መረጋጋት አይታይበትም።

"ምነው አስቻለው ምን ሆነሃል?" አለችው።

"ከአባባ ጋር ተጋጭተን ነው" አላት በስጨት እንዳለ።

"አንተ ደግሞ በእርሳቸው ጸባይ ሁልጊዜ አዲስ ትሆናለህ፤ አሁን እቤት አሉ እንዴ?" አለችው ቆም ብላ።

አባቱ ያለመኖራቸውን ስለነገራት ሰውነቷ ዘና አለ፡፡ ጭስ የጠገበው የነአስቻለው ቤት ዛሬም እንደወትሮው ጨለምለም እንዳለ ነው፡፡ ረጃጅም ግድግዳዎቹ ቤቱን የበለጠ እንዲከብድ አድርገውታል፡፡

ዐይኖቿን ከጨለማው ጋር አለማመደችና ወደውስጥ ገባች፡፡ ወደአስቻለው ክፍል ለማለፍ በጓሮው በር ስትወጣ የአስቻለው እናት እሳት ለማንደድ ሲታገሉ ተመለከተች፡፡

"እንደምን ዋሉ እማማ" አለቻቸው።

"እግዚአብሔር ይመስገን!" አሏት በታፈነ ድምጽ

ከምድጃው አጠገብ ያገኘችውን ጨርቅ ጎተት አደረገችና በርከክ ብላ እሳቱን አነደደችላቸው።



"እግዚአብሔር ይባርክሽ ልጄ! እደጊ!" አሏት። የአስቻለው እናት እንዲህ ናቸው ለትንሿም ነገር ቢሆን ምርቃት ይቀናቸዋል።

"አሜን እማማ!" አለችና ወደአስቻለው ክፍል ገባች።

ስትገባ ቅዱስን አገኘችው፡፡ እንደሁልጊዜው በደንብ ለብሷል ስታየው ልቧ በደስታ ፈነደቀች፤ እቅፍ አድርጋ ሳመችው፡፡ ዘርዓይና ጋዲሳ ግን አልመጡም፡፡ ቅዱስ ለዕለቱ የተዘጋጀ ውይይት ባለመኖሩ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስቧቸው መሄድ እንዳለበት ነገራቸውና ወዲያውኑ ወጣ፡፡ ሲወጣ ስሜቱ ጥሩ አልነበረም፤ በሚቀጥለው ቀን እንዲገናኙ ፍሬሕይወትን ቀጠራት፡፡

ከነአስቻለው ቤት ስትወጣ እኩለ ቀን እየሆነ ነበር፤ ጋዲሳና ዘርዓይ ግን አሁንም ብቅ አላሉም፡፡ ከእንተነህ ጋር ያላት ቀጠሮ ገና ከሰዓት በኋላ ነው፡፡ ሌላም ቀጠሮ የላትም፡፡ ምናልባትም እንተነህም ጎረቤት ሊደውል ይችል ይሆናል፡፡ ስለስልኩ ስታስብ ርምጃዋን ፈጠን አደረገችው፡፡

ፍሬሕይወት ከቤት አልወጣችም፤ የጠበቀችው የስልክ መልዕክትም አልደረሳትም፡፡ ሀሳቧን መሰብሰብ አቅቷት እንደተጨነቀች ዋለችና አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን ከቤት ወጣች፡፡ ፈጠን ያለ እርምጃ የሰዎችን ዐይን እንዲስብባት አልፈለገችም ሰውነቷን ዘና አድርጋ በቀስታ ርምጃ ለመሄድ ሞከረች፡፡ አለባበሷን ተመለከተችው፤ የሚያሳጣ አይደለም፡፡ ሁል ጊዜም የሰው ዐይን የሚጠራባት ጫማዋም ዛሬ አጠር ያለ ተረከዝ ያለው ቆንጆ ጫማ በማድረጓ ተስተካክሏል፡፡

ወደ መድረሻዋ ስትቃረብ ደርሶ ጭንቅ አላት፡፡ ስሜቷ ሁሉ አስጠላት፡፡ መጸለይም አማራት፤ ግን እንዴት ነው የምትጸልየው? የጸለየችበትን ጊዜ ለማስታወስ ሞከረች። በትንሹ ሁለት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ አንድም ቀን የመጸለይ መንፈስ አድሮባት አያውቅም፡፡ ለመጸለይ ያደረባት ስሜት ውስጧ የቱን ያህል እንደተጨነቀ እንድታውቅ አደረጋት፡፡

በታችኛው ፍልውሀና በሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መሀል ባለው ሜዳ አቋርጣ በጊዮን ሆቴል አጠገብ አስፋልቱ ላይ ደረሰች፡፡ ከአንተነህ ጋር የተቀጣጠሩት እዚያ ነው፡፡ ዓይኖቿን ከወዲያ ወዲህ አንከራተተቻቸው፤ አንተነህ ግን የለም፡፡ ጭንቀት ጉሮሮዋን አነቃት፡፡ ዓይኖቿ መቃጠል ጀመሩ፡፡ ካለቀሰች በጣም ብዙ ጊዜ ሆኗታል፡፡ ስሜቷን በጣም ፈራችው፡፡ አንተነህን ሊገጥመው የሚችለውን ነገር ስታስበው ደግሞ ወገቧና ጉልበቷ ተንቀጠቀጡባት በቀዝቃዛው አየር ላብ ላብ አላት፡፡

የት ሄዳ ልትፈልገው ትችላለች? ያለበትን ቦታ አታውቀውም፤ በስልክም ቢሆን የመገናኘት ዕድሉ በጣም የጠበበ ነው፡፡ ቀጠሮ ቦታ አምስት ደቂቃም መቆም እንደሌለባት ብታውቅም በፍጹም መሄድ አቃታት፡፡ በሃሳቧ ስትዋዥቅ አስራ አምስት ደቂቃዎች አለፉ፡፡ በመጨረሻ እንባዋን መቆጣጠር ተሳናት፡፡ ትኩስ እንባዋ በጉንጮቿ ቁልቁል ሲወርድ በመዳፏ ጀርባ እየጠራረገች በደመነፍስ በአድቬንቲስት ቤ/ክርስቲያን በር አልፋ ሽቅብ ወደ ፍልውሀ አቀናች፡፡

ፍልውሀ በር ላይ ባለው ስልክ ዕድሏን ለመሞከር ወሰነች፡፡ አስፋልቱን ተሻግራ የስልኩን መነጋገሪያ ስታነሳ እጇ ተንቀጠቀጠ፡፡ ቁጥሮቹን ስታዞርም ጣቷ እየተንቀጠቀጠ ነው፡፡ ልቧ እየመታ የስልኩን የጥሪ ድምፅ መጠበቅ ረጅም ጊዜ የወሰደ መሰላት፡፡ ስልኩ የመያዝ ድምጽ አሰማት፡፡ ጥቂት ቆየችና እንደገና ሞከረችው፡፡ ስልኩ ጠራ የፍሬሕይወት ልብ መዝለል ጀመረች፤ አፏ የደረቀ መሰላት፡፡ ስልኩ ተነሳ ሄሎ ማለት ግን አቃታት፡፡

"ሄሎ" የሚል የሴት ድምጽ ከወዲያኛው መስመር ጫፍ ተሰማት፡፡ የአንተነህን መኖር ጠየቀች።

"አንተነህ የለም" አለች ስልኩን ያነሳችው ሴትዮ።

"ወዴት ይሆን የሄደው?" አለች መጠየቅ እንደሌለባት ብታውቅም።

"አላወቅሁም" ቆጣ ያለች መሰላት።



"አመሰግናለሁ" አለችና ስልኩን ዘጋችው።

ሌላ ምን ምርጫ አላት? ወደቤቷ ተመለሰች፡፡ ቤት ስትገባ መንፈሷ ድቅቅ ብሏል፡፡ በቀጥታ ጉብታ አልጋዋ ላይ ተዘረጋች፡፡ በጀርባዋ ተንጋላ ዓይኖቿን ወደጣራው ስትልካቸው ያልታዘዘው እንባዋ በጆሮዎቿ አልፎ ፈሰሰ፡፡ በጎኗ ተኛችና ራሷን ከትራሱ ስር ቀበረችው፡፡ እንባዋን መግታት ግን አልቻለችም፡፡ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች በለቅሶዋ መሀል ደግሞ የቅዱስ ድምጽ ተሰማት፡፡

"... ለትግሉ የምናደርገውን አስተዋጽኦ ቅንጣት ታህል የሚቀንስብን ግንኙነት ባንፈጥር መልካም ነው፡፡ ከአቅም በላይ ሆኖ ግንኙነታችን ወደፍቅር ቢያመራ ግን ከእኛ እጥፍ ድርብ ጥንካሬ ይጠበቃል፡፡ ፍቅር በምንም መልኩ ከትግሉ በላይ እንዲሆን መፍቀድ የለብንም..." ይላል ቅዱስ ሁልጊዜ የፍቅር ጉዳይ ሲነሳ።

የአንተነህን ድምጽ ከቅዱስ ድምጽ ጋር ተቀላቅሎ ሰማችው "ፍርዬ ማንንም መውደድ አልፈልግም ነበር ግን..."

እንባዋ ከመቅጽበት ከዐይኖቿ ላይ ክው ብሎ ደረቀ፡፡ ራሷን በጥፋተኝነት ወቀሰችና ከተኛችበት ተነስታ ወጣች፡፡ ፊቷን ለመታጠብ ውሃ ስትጨምር ከራሷ ጋር እየተነጋገረች ነበር፡፡ "...በእውነት ለምን ለበላይሁን፣ ለዘርዓይና ለጋዲሳ ለአንተነህ ያሰብኩትን አንድ አስረኛ እንኳ አላሰብኩም? በዛሬው ዕለት ስንት ጓዶች ምን ሊገጥማቸው እንደሚችል ማን ያውቃል?..."

ፊቷን ታጥባ የጋዝ ምድጃውን ለኮሰችና ሻይ ጣደች፡፡ መብላት እንዳለባትም በማሰብ ምግብ ለማቅረብ ጉድ ጉድ ማለት ጀመረች፡፡ ለመብላት ያደረገችው ጥረት ግን ከንቱ ነበር እንጀራውን በፍጹም ልትውጠው አልቻለችም፡፡ የጎረሰችውን እንደምንም በሻዩ አወረደችና ምግቡን መልሳ አስቀመጠችው፡፡

ምሽቱ ቀዝቀዝ ያለ ከመሆኑም በተጨማሪ ሁሉም ቤት ክትት ብለው በማምሸታቸው እናቷ ደስ ብሏቸዋል፡፡ ታናሽ እህቷ ሚሚ ከሰል አያይዛ የቡና ዕቃዎች አቀራረበች፤ ከተቋረጠ ረጅም ጊዜ የሆነው ተሰብስቦ ማምሸት ናፍቋቸው የነበሩ እናታቸው ቡናውን ራሳቸው

ማፍላት ፈልገው ከሚሚ ተቀበሏት፡፡ ቤቱ ግን እንደወትሮው ደመቅ አላለም፤ አልፎ አልፎ መነጋገር ቢኖርም ሁሉም በየራሳቸው ሃሳብ የመዋጣቸው ነገር አላስደሰቸውም፡፡

ፍሬም ብትሆን ራሷን ለማረጋጋት ያደረገችው ጥረት በመጠኑ ቢሳካላትም ብዙ ማምሸት አልቻለችም፡፡ በጊዜ ተኛች፡፡ ስትተኛ ደግሞ ጭርሱን ሃሳብ ሰፈረባት፡፡ እንቅልፍ እንዲወስዳት ያልሞከረችው ነገር የላትም፡፡ ራሷን ትራስ ውስጥ ብትቀብር፣ ጉልበቷን ኩርትም ብታደርግ፣ በደረቷ ብትተኛ፣...ትርፉ መገላበጥ ብቻ ሆነባት፡፡ መጽሐፍ ለማንበብ ሞከከረች አልሆነላትም፡፡ ሌሊቱ የማይነጋ ቀኑም ተመልሶ የማይመጣ እስኪመስላት ድረስ ረዘመባት፡፡ ሌሊቱ አልቆ ሊነጋጋ ሲል እንቅልፍ ሽልብ አደረጋት፡፡

* * * *

ሰፋ ያለ ንጹሕ ክፍል፤ ሙሉ የኦፕራሲዮን ትጥቅ ያሚላች ሀኪምና ነርስ በጸጥታና በቅልጥፍና ይሠራሉ። ሳይነጋገሩ ተግባብተው አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ይቀባበላሉ። መሳሪያዎቹ ሲጋጩ ከሚፈጥሩት ድምጽ በስተቀር ምንም ድምጽ አይሰማም። ቦታው የነሄዋን ቤት ነው።

ሀኪሟ ሥራዋን ስትጨርስ እጆቿ ላይ አጥልቃቸው የነበሩትን ጓንቶች አወላለቀችና የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛውንም አነሳችው። ወዲያውኑ መለስ አለችና ደግሞ ህመምተኛውን ተመለከተች፤ ገጽታዋ ላይ የሚነበበው ስሜት ዝብርቅርቅ ያለ ይመስላል። ነርሷ የተጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች አነሳስታ ቦታ ቦታቸውን አስያዘችና ሀኪሟን ተመለከተቻት። በአንገቷ ምልክት ሰጠቻት፤ ተከታትለው ከክፍሉ ወጡ።

ሄዋን የበሩን እጀታ በቀስታ አዙራ በሩን ከፈተችና አንገቷን ብቻ አስገብታ ተመለከተች። ምንም እንቅስቃሴ አይታይም፤ እንቅልፍ የወሰደውን ሰው ላለመረበሽ በሚደረግ ጥንቃቄ በቀስታ ገብታ በሩን ዘጋችው።



ከአልጋው አጠገብ ባገኘችው ወንበር ላይ በቀስታ ተቀመጠች፤ አንተነህን እያየችው የሆነው ነገር ሁሉ በዐይነ ህሊናዋ ታያት፤ የነበረው የተኩስ እሩምታ አሁን የሆነ ያህል በጆሮዎቿ ተሰማት። በዚያ የሞት የሽረት ትግል ውስጥ አንዳቸው ለአንዳቸው የነበራቸው መተሳሰብ ልቧን ነካው። አንተነህ እርሷን ለማዳን ባደረገው ጥረት ወደኋላ በመቅረቱ ለጥይት መዳረጉን አሰበችው። በሕይወቷ ሙሉ እንደዚያ ዓይነት ተኩስ እንኳንስ በእውን ልትመለከት በፊልም ማየቷንም ትጠራጠራለች።

ከእንደዚያ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ምንም ሳትሆን የመትረፏ ነገር ተአምር እንጂ እውነት አልመስል ብሏት ነበር። አንተነህን ትኩር አድርጋ እየተመለከተችው፣

"ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር አብሮ መሥራት እንዴት መታደል ነው?" አለች ለራሷ።

አንተነህ "ኧ..." የሚል ድምጽ አሰማና እንደመንፈራገጥ ብሎ ቁስሉ ያለበትን ቦታ በእጁ ለመዳበስ ሙከራ አደረገ። እጁን ያዘችና ቁስሉን እንዳይነካው አደረገችው። አሁንም አሁንም እያቃሰተ እጁን ሊያስለቅቃት ይሞክራል። ዐይኖቹ በሚገባ ተገልጠው ባያዩም ከቆዳቸው ውስጥ ሆነው ሲንከባለሉ በቅዠት ውስጥ እንዳለ ያስታውቃል።

በቅዠቱ ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን ማንሳት ሲጀምር ሄዋን መስኮቶቹንና በሩን ዘጋጋች። በስብሰባው ላይ የነበሩትን ሰዎች ስም እየጠራ እንዲህ ሁኑ፣ እንዲህ አድርጉ፤ ወደዚህ ጠጋ በሉ... እናሸንፋለን... ሲል ቆየና ጸጥ አለ። ከዚያ ደግሞ ጥቂት ቆይቶ እንደገና መወራጨትና መቃዠት ጀመረ።

"ኧ ... ኧ ... ፍርዬ! እስኪ ይሄንን እይልኝ... የት ነሽ?..." እያለ በእጁ መዳበሱን ቀጠለ።

"አንተነህ!" አለችው ሄዋን በቀስታ።

ዐይኖቹን በቀስታ ገለጣቸውና ተመለከታት። ደግሞ መልሶ ጨፈናቸው። "ፍሬ የት ነች? እኔስ የት ነኝ ሄዊ?" አላት ግራ በተጋባ ገጽታ።

"አይዞህ ፍሬ ትመጣለች፤ አንተም እኛ ቤት ነው ያለኸው" አለችው።

አንተነህ የሆነ ነገር በአእምሮው ውስጥ እንደመጣለት ሁሉ ጭንቅላቱን አንቃንቀና ሄዋንን ተመለከታትት። ደረቱን በእጁ ለመዳበስ ሙከራ አደረገ።

"ሄዊ ሌሎቹስ? የት ናቸው ብዙ ጓዶች ተጎዱብን እንዴ? የሞተስ አለ?" ገጽታው ሁሉ ተቀያየረ።

"ማንም አልሞተም የተጎዱትም ልክ እንዳንተ ሌላ ቦታ ህክምና እያገኙ ነው። ተረጋጋና ለመተኛት ሞክር፤ አንተ መዳን አለብህ" አለችው ሄዋን የግንባሩን ላብ እየጠራረገችለት።

አንተነህ ዐይኖቹን ጨፈናቸው፤ እንቅልፍ ግን አልወሰደውም። ትናንትን ለማስታወስ ጥረት እያደረገ ነበር፤ ብዙው ነገር ትዝ አለው። የማታው ስብሰባ፤ የተኩስ አጀማመር ... ሄዋንን ለማዳን ያደረገው ሙከራ... ከዚያ ጠፋበት። ዓይኖቹን ገለጠና ሄዋንን ተመለከታት።

"አንቺ ተመተሻል?" አላት ትኩር ብሎ እየተመለከታት።
"እኔንማ ለማዳን ስትል አንተ ተመታህ" አለችው ምን እንደምትለው ግራ ገብቷት። መልሶ ዐይኖቹን ጨፈናቸው። እንደገና ወደ ትውስታው ገባ። አሁን ፍሬሕይወትን አሰባት፣ በሀሳቡ መጣ ሄደች ስትልበት የቆየችውን ፍሬሕይወትን በዐይነህሊናው አተኩሮ ተመለከታት። ቀጠሮ ነበራቸው!

"ሄዊ" አላት ዐይኖቹን እንደገና ገልጦ

"አቤት አንተነህ" አለችው በፍጥነት

"ፍሬን እንዴት ነው የማገኛት?" አላት በሚያሳዝን ድምጽ



"አስቤበታለሁ አትጨነቅ። አንተ በደንብ አስከትነቃ ነበር የምጠብቀው። አሁን ከአንተ የሚጠበቀው ማረፍና ማንቀላፋት ብቻ ነው" አለችው በእርግጠኝነት። አንተነህ እንደገና ዓይኖቹን ከደናቸው።

* * * *

ትከሻዋን ነካ ነካ የሚያደርጋት እጅና "ፍርዬ! ፍርዬ!" የሚለው ድምጽ በስንት ስለት ካገኘችው ሽልብታዋ ቀሰቀሳትና በርግጋ ተነሳች፡፡ ፍሬሕይወት ሰሞኑን እንቅልፍ አልወስድ እያላት ሌሊቱ ሲነጋጋ ነው የምትተኛው።

"ምን አስደነገጠሽ? እኔ ነኝ" አለች ሚሚ ከአልጋው አጠገብ ቆማ።

"እሺ ምንድነው?" አለች የተጣበቁ የመሰሏትን ዐይኖቿን ለመግለጥ እየታገለች።

"ሰው ይፈልግሻል" አለች ሚሚ ተረጋግታ።

"የምን ሰው? ማነውሱ?" የበለጠ ድንጋጤ ያዛት ፍሬሕይወትን፡፡ እህቷ ውሀ ሰጠቻትና ፊቷ ላይ አፈሰሰችው፤ በመጠኑ ተረጋጋችና ተንጠራራች፡፡

"ማነው ግን?" አለች መልሳ።

"አላውቀውም፡፡ ግን የሰፈር ልጅ ነው" አለች ሚሚ ቀለል አድርጋ።

"የሞትሽ ቅድሙኑ እንዲህ አትይኝም ታዲያ" ብላት ወጣች።

የእውነትም ልጁ የሰፈራቸው ልጅ ይሁን እንጂ ንግግር የላቸውም፡፡ ለሰላምታ እጁን እየዘረጋችለት፤ ምን እንደምትለው እርሱ ቀደመና፤

"መልዕክት ነበረኝ" አላት ተረጋግቶ።

"የምን መልዕክት፤ ከማን?" በጥያቄ አጣደፈችው።

"ከአንተነህ" አላት መረጋጋቱን ሳይለውጥ ድምጹን ግን ዝቅ አድርጎ፡፡ ድንጋጤዋ እርሱንም ያስደነገጠው መሰላት "ሊያገኝሽ ይፈልጋል የሚመችሽ ከሆነ..."አላስጨረሰችውም ፤

"ይመቸኛል" አለችው።

"አሁን መሄድ ትችያለሽ?" አላት የታዘባት በሚመስል ሁኔታ።

"እንዴ በጣም! ልብሴን እስክቀይር ብቻ ታገሰኝ" አለችውና መልስ ሳትጠብቅ ቤታው ገባች፡፡

ልብሷን እየለበሰች ጥያቄዎች በአእምሮዋ ውስጥ ተመላለሱ፡፡ ግን ለምን ሰው ላከ? ለምን በስልክ አላስነገረኝም? ለምንስ ከልጁ ጋር አብሬ እንድሄድ አስፈለገ? እነዚህ ያልተመለሱ ጥያቄዎች በአእምሮዋ ውስጥ እንደተንጠለጠሉ ወጣች፡፡

ተግባረዕድ ት/ቤት አጠገብ ከታክሲ ወረዱና ወደሚቼልኮትስ የሚወስደውን መንገድ ይዘው ሄዱ፡፡ ምንም አልተነጋገሩም ሁለቱም በየግል ሃሳቦቻቸው ተውጠዋል፡፡ በአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ በር ላይ ወደ ግራ ታጥፈው ቁልቁል ወደጌጃ ሰፈር ወረዱ። በስተግራ በኩል ባሉት መንደሮች መሀል በኮረኮንች መንገድ ወደውስጥ ገቡ፡፡ ጥቂት እንደሄዱ አንድ ትልቅ አረንጓዴ የብረት በር አጠገብ ሲደረሱ ቆሙና በሩን ሦስት ጊዜ መታ መታ አደረገው ልጁ፤ በሩ ወዲያውኑ ተከፈተ፡፡

ግርማ ሞገሱ ያማረ ትልቅ ቤት ጉብ ብሏል፡፡ ግቢው ሙሉ በሙሉ በአስፋልት የተነጠፈ ሲሆን የአጥሩ ጥጋጥግ ባማሩ አበባዎች ተውቧል፡፡ ግድግዳው የተሠራበት ውድ ጠጠር ያብለጨልጫል፡፡ አድናቆቷን ሳትጨርስ ወደቤቱ በስተጀርባ አለፉ፡፡

መደዳውን ተያይዘው ከተሠሩት ቤቶች የአንደኛው በር ተከፈተና ገቡ፡፡ ከፊት ለፊቷ አንተነህ አልጋ ላይ ጋደም ብሎ አየችው፡፡ ከቶውንም ምንም ለማለት አቅም አልነበራትም፡፡ ቃላት ከአንደበቷ መውጣት ተስኗቸው በጉሮሮዋ ውስጥ እየተተረማመሱ ሳግ ፈጠሩ፡፡



ልታደርግ የቻለችው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ሮጣ አልጋው አጠገብ መንበርከክ፡፡ መታዘዝ የማያስፈልገው እንባዋ እንደፈለገው እየወረደ በጉንጮቿ ላይ ፈሰሰ፡፡ ልትከለክለው አልፈለገችም ያሻውን ያህል ወርዶ ውስጧን እንዲያጥብላት ፈቀደችለት፡፡

"በቃ! በቃ ፍርዬ! ለምን ተገናኘን ነው እንዲህ የምትሆኚው?" አላት አንተነህ በዝምታ ተውጠው ከቆዩ በኋላ።

"እንዲህ እንደሚሆን ልቤ አውቆት ነበር" አለችው እንደተንበረከከች ግንባሩን እየደባበሰች፡፡

"ምንህን ነው ግን" ድምጿ ሲርገበገብ ለራሷም ታወቃት፡፡ ልብሱን ገለጥ አድርጎ አሳያት፤ ከትከሻው ዝቅ ብሎ ደረቱ አካባቢ በፋሻ ታሽጓል፡፡

"አጥንትህን ነክቶሀል?" አለች ትንሽ ተወት አድርጋ የነበረው እንባዋ እንደገና እየወረደ፡፡

"እድለኛ ነኝ ፍርዬ፡፡ ጥይቷ ሥጋ ለስጋ ነው ያለፈችው" አላት ዐይን ዐይኗን እያየ "በናትሽ ሳሚኝ ፍርዬ! እንዴት እንደናፈቅሽኝ ብታይ፤ ልክ ራሴን ሳውቅ በአእምሮዬ ውስጥ የነበርሽው አንቺ ነበርሽ፡፡ አያንዳንዱ አጋጣሚ የቱን ያህል እንደምወድሽ ማረጋገጫ ሳይሰጠኝ አልፎ አያውቅም፡፡" አላት በቀኝ እጁ ጥብቅ አድርጎ አቅፎ አንገቱ ስር እየሸጎጣት፡፡

"ዳግመኛ የማላገኝህ መስሎኝ ተሳቅቄ ነበር" አለችው የሰሞኑ ውሎና አዳሯ ትዝ ብሏት።
በሩ በቀስታ ሲከፈት ቀና አለች፡፡ ዐይኖቿን ማመን አቃታት፤ የገባችው ሄዋን ነች፡፡ ዐይኖቿን አንዴ ወደ አንተነህ ደግሞ ወደ ሄዋን እያደረገች አንከራተተቻቸው፡፡ ሄዋንን በዚህ ዓይነት አጋጣሚ አገኛታለሁ ብላ በፍጹም አላሰበችም፡፡ ለሰላምታ ተቃቀፉ ሰላምታዋ ለፍሬ ያላትን ስሜት ያንጸባረቀላት መሰላትና ከልቧ ደስ አላት፡፡ ስለሄዋን የነበራት ግምት ትክክል ሆኖ አገኘችው፡፡ የተንደላቀቀ ሕይወቷን ለትግል የሰጠች ወጣት መሆኗን!!

## ክፍል 3
## ስደትና እስራት

የተደረገውን የቤት ለቤት አሰሳ በመቃወም የፕሮፓጋንዳ ሥራ ለመሥራት በሁሉም አካባቢዎች ዝግጅቱ ተጠናከረ፡፡ ለሥራው የሚያስፈልጉ ዕቃዎች በሙሉ ተሟልተዋል፡፡ ወጣት ሁሉ በሥራ ተወጠረ፡፡ ለአፍታ እንኳ አረፍ ሳይሉ ሲባክኑ ውለው ማደር ከጀመሩ ሰንብተዋል፡፡ እዚህ ቀጠሮ፣ እዛ ቀጠሮ፣ ማታ ደግሞ የተግባር ሥራ...

ቅድመ ዝግጅቱ በተጠናቀቀበት ዕለት ከቀኑ አስር ሰዓት ላይ ፍሬሕይወት ከድካሟ የተነሳ የማቅለሽለሽ ስሜት ተሰማት፡፡ ኪሷን ስትፈትሽ አራት ብር አገኘች፡፡ በአቅራቢያው ወዳለች ኪዮስክ ተጠጋችና ለስላሳ ጠየቀች፡፡ ለስላሳውን ከፍቶ ሲሰጣት በአንድ ትንፋሽ ጨለጠችው፡፡ የለስላሳውን ጠርሙስ ለባለሱቁ መስጠቷንም እርግጠኛ አይደለችም ብቻ ምድር ሰማዩ ዞረባት፡፡ ሆዷ ግልብጥብጥ፣ ልቧም እንደ መከዳት አደረጋት፣ በፍጥነት ተቀመጠች፡፡ የጠጣችው ሚሪንዳ እንደፈንዳ የቧንቧ ውሃ ተረጨ ምንም ነገር በሆዷ ውስጥ ሳይቀር አስመለሳት በመጨረሻ መራራ ሀሞት ወጣ፡፡ ቀና ብላ አካባቢዋን ተመለከተች ባለሱቁ ግራ ገብቶት ይመለከታታል፡፡ "ውሀ!" አለችው በደከመ ድምፅ፤ ውሀውን ጠጣች፡፡

ሲተረማመስ የነበረው ሆዷ የተረጋጋ መሰላት፡፡ በግንባሯ ላይ ችፍፍ ብሎ የነበረ ላብ ቀዝቀዝ ሲል ተሰማት ጠራረገችው፡፡

"እሮይ!" አለች በረጅሙ ተንፍሳ

"ግቢና ትንሽ አረፍ በይ" አላት ባለሱቁ በሀዘኔታ፡፡ "አይ ምንም አይለኝም እግዜር ይስጥልኝ" አለች የለስላሳውን ዋጋ እየከፈለች፡፡

በቀጥታ ወደቤቷ ተመልሳ ገብታ አልጋዋ ላይ ከተዘረረች በኋላ ነው ሰዓቷን ያየችው፡፡ ለአስራ አንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሆኗል፡፡ አንድ ሰዓት ያህል ጊዜ አላት፣ ትንሽ ማረፍ ትችላለች፡፡ ዓይኖቿን ጨፍና ሰውነቷን ዘና ለማድረግ ሞከረች፣ ሃሳቧ ግን ሊያርፍ አልቻለም፤



የሚጠብቃትም ሥራ የሚያሳርፍ አይደለም፤ ቢሆንም አልጋዋ ላይ ጥቂት መቆየት አለባት። አልጋ ሊያማት ይችላል፡፡

አስራ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን ከተኛችበት ተነስታ ወደጓዳ ስትገባ እናቷ የተለመደ ቦታቸው ላይ ተቀምጠው ምስር ይለቅማሉ፡፡

"እኔስ ተመልሰሽ የወጣሽ መስሎኝ ነበር" አሏት ቀና ብለው አይተዋት "ምነው? ፊትሽ ጥሩ አይደለም፤ ምን ሆነሻል?" አሏት የሚለቅሙበትን ሰፌድ እያስቀመጡ፡፡ እጃቸው ላይ ጋደም ብላ ራሷን እንዲያሻሿት ተመኘችና ሃሳቧ ፈገግ አሰኛት፡፡

"ኧረ ምንም አልሆንኩ ተኝቼ ስለተነሳሁ ይሆናል" አለች ቀልጠፍ ለማለት እየሞከረች፡፡ እናቷ የምትበላው ሰጥተዋት ተመልሰው ወደ ምስር ለቀማቸው ገቡ፡፡ እናቷ የሰጧትን እንጀራ ለመጉረስ እየሞከረች ሰሞኑን እንጀራ መጋገር እንኳን ሳታግዛቸው መቅረቷ ተሰማት፡፡

"እማ ሰሞኑን ሥራውን ሁሉ ተውኩልሽ አይደል?" አለች ይቅርታ በመጠየቅ ዓይነት።

"ኧረ እባክሽ ተመስገን ነው፡፡ የሚሠራው አይጥፋ፤ ምንም አልከበደኝም" አሉ ወይዘሮ ስርጉት።

"ከነገ ጀምሬ ወደመደበኛ ሥራዬ እገባለሁ፤ አግዝሻለሁ፡፡" አለቻቸው በማረጋገጥ ዓይነት።

"ምነው ችግር አለ እንዴ? ይሄን ዙረት ልትተይ ነው?" አሏት መልቀማቸውን ቆም አድርገው፡፡

"ከችግር ጋር መኖር ከጀመርን ቆየን አይደል?" አለቻቸው ባጭሩ፡፡

"ምነው ቢበቃችሁ ምን እስክትሆኑ ድረስ ነው? እርሱ እንደሆነ ነትንቅ አላለ" አሉዋት፡፡ ከእናቷ ገፅታ ላይ ጭንቀት ተመለከተች፡፡

"እማ! ከድል በፊት ምን ማብቃት አለ ብለሽ?" አለችና ወደመኝታ ክፍሏ ገባች።

ክፍሉ ውስጥ ገብታ ጥቂት ቆም አለች። የቀጠሮዋ ሰዓት እየደረሰ ነው፤ በቀጠሮ የተሞላ ሕይወት። እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ጥንቃቄ የተሞላበት ከሆነ ቆይቷል። እናም ጥቂት አሰብ አደረገችና ተስማሚ ሊሆን የሚችል ቦርሳ አውጥታ አንዳንድ ነገሮች ከተተች።

በችኮላ ልብሷን ቀያየረች፡፡ ካሊት ልብሶች የተሻለውንና ምቹውን መርጣ ለበሰች፡፡ የመኝታ ቤቷን በር ቆለፈችና ከወለሉ ላይ አንዲት ጣውላ አነሳች፡፡ ከጣውላው ስር የነበረውን ጆንያ አወጣችው፡፡ ያስቀመጠችው ዕቃ በካኪ ወረቀት እንደተጠቀለለ ጆንያው ውስጥ ነበረ፡፡ ከአንድ አባል የተበረከተች ሽጉጥ ናት፡፡ ሳንቃውን እንደነበረ መልሳ በእግሯ ረገጥ አደረገችው፡፡ ራቅ ብላ ተመለከተችው በፍጹም አያጠራጥርም፡፡ ሽጉጡ ደግሞ ለሚያስፈልጋቸው ጓዶች መድረስ አለበት፤ እናም ቦርሳዋ ውስጥ በጥንቃቄ ከትታ ዘጋችና ለመጨረሻ ጊዜ ራሷን በመስታወት ተመለከተች በሚገባ ዘንጣለች፡፡

"በይ እስኪ ተጠንቀቂ፡፡ እኔንም ጨርሳችሁ አሳበዳችሁኝ፡፡ እባካችሁ ራሳችሁን ጠብቁ!" አሏት እናቷ ስትወጣ።

ከግቢ ወጥታ ታክሲ ወደምታገኝበት ጥቂት እንደተራመደች ዳንኤልን ከፊት ለፊት ሲመጣ ተመለከተችው፡፡ ብስጭት አለች መንገዱን ቀይራ ልትሄድ የምትችልበት ምንም አማራጭ መንገድ አልነበራትም፡፡

"እንዲህ ሽክ ተብሎ ወዴት ነው?" አላት ዳንኤል ከእግር እስከራሷ እየተመለከታት።

"አመሰግናለሁ ግን ይሆን ያህል የሚታይ ነው እንዴ?" አለች አለባበሷን እየተመለከተች።

"እያሾፍሽ ነው? ይልቅስ እስኪ ዛሬ እሺ በይና ልጋብዝሽ" አላት።



"አሁን እንኳን እቸኩላለሁ ስመለስ ግን መጋበዝ እችላለሁ" አለችው በፈገግታ።

"ዛሬስ በፍፁም አትሸውጂኝም የአንቺ ችኮላ አያልቅምና ዘላለም ደጅ መጥናት አለብኝ እንዴ?" ኮስተር አለ ዳንኤል፡፡

ደቂቃዎች ባለፉ መጠን ራሷንና ቅዱስን ለአደጋ እያጋለጠች መሆኗ ተሰማት፡፡ ዳንኤል ደግሞ በወጣቱ በጠላትነት ከሚታዩ ልጆች መሀል ነው፡፡ እንድትጠነቀቅም ተነግሯታል፡፡ እርሱ ደግሞ አንዴ ችክ ካለ አይለቅም፡፡ ልቧ ጥልጥል አለችባት፡፡ ቦርሳዋ ውስጥ የያዘችውን ዕቃ አሰበችው፡፡

"እኔ እኮ በጣም ነው የምትገርመኝ፡፡ እኔ እንድጀምርልህ ነው እንዴ የምትፈልገው? ተሸወድኩ የምትለው ነገር አይገባኝም፡፡" አለችው፡፡ ዳንኤል ያልጠበቀው ነገር ሆኖበት ግራ ግብት ሲለው አየች፡፡ በዚሁ መቀጠል ነበረባት፤ እናም ዳንኤልን እቅፍ አደረገችና ሳም አድርጋው "ስመለስ እንገናኝ" ብላ ለመልስ ጊዜ ሳትሰጠው ትታው ሄደች፡፡ ከአሁን አሁን ተከተለኝ በማለት ልቧ ድው ድው ማለት ጀመረች፤ ግን ዞር አላለችም፡፡

ሰዓቷን ተመለከተች፤ ግዜ አላት፤ ታክሲ ካገኘች በሚገባ ትደርሳለች፡፡ ታክሲውን ወዲያውኑ አገኘችና እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን አጠገብ ስትወርድ አምስት ደቂቃዎች ነበሯት፡፡ ቀጠሮዋ ፍላሚንጎ ነው፡፡ ደቂቃዎቹ ይበቋታል፡፡ ራመድ ራመድ እያለች አስፋልቱን አቋረጠችና ወደ ቦሌ የሚወስደውን መንገድ ያዘች፡፡ ቀና ብላ አካባቢዋን ቃኘት ስታደርግ ክው ብላ ደነገጠች፡፡ ፍላሚንጎ አካባቢ መንገዱ ተዘግቶ አላፊ አግዳሚው ይፈተሻል፤ ይገማበራል፤ ይገፋል...

የቀጠሮ ሰዓት ማሳለፍ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አስጊ በመሆኑ በሰዓቱ መድረስ ነበረባት፡፡ "ወይኔ ቅዱስ ተበላህ!" አለች ለራሷ።

ስለቅዱስ እየተጨነቀች ደግሞ በትልቁ ቦርሳዋ ውስጥ የያዘችው ዕቃ ትገዝ/ አላት፡፡ ከያዘችው ዕቃ ጋር ብትያዝ የሚከተለውን ነገር ስታስበው ሰውነቷን ዘገነናት፡፡ አንድ ነገር ላይ ርግጠኛ ነች

በምንም ዓይነት መንገድ ይሁን ከቻለች ማምለጥ ካልሆነም... ቦርሳዋን ዳበስ አደረገችው፡፡ ወደ ፍላሚንጎ መሄዱን ተውችና ወደ ስታዲየም አቀናች፡፡ ሰው ሁሉ ይራወጣል፡፡ ከፍተኛው ለመዳን የየራሱን መላ የሚመታ ይመስላል፡፡ ማንም ማንንም የሚያይ አይመስልም። የሁሉም ትኩረት መሳሪያቸውን አንግተው ዓይኖቻቸውን እያጉረጠረጡ ሕዝቡን በሚያተራምሱት ወታደሮች ላይ ይመስላል፡፡

ቀስ ብላ የቦርሳዋን ቻርኔላ ፈታችው፡፡ እጇን ወደ ውስጥ አስገባችና የውስጠኛውንም ቻርኔላ ከፈተች፡፡ አካባቢዋን በዐይኖቿ እየተቆጣጠረች ሽጉጡ የተጠቀለለበትን ካኪ ወረቀት ቀደደችው ጣቷን በሽጉጡ ቃታ ላይ አሳረፈችና ፈጠን ባለ ርምጃ ወደፊት ቀጠለች፡፡ ቢያንስ አንዱን ይዛ ነው የምትሞተው፡፡ አሻግራ ወደስታዲየም ስትመለከት አሰሳው እዛም አለ፡፡"ዛሬስ አልቆልኛል" አለች ለራሷ፡፡ በየት በኩል መሄድ እንዳለባት እንኳን አስባ ሳትጨርስ ተከታታይ የተኩስ ድምፅና ጩኸት አካባቢውን አደበላለቀው፡፡ ፍተሻው ድብልቅልቁ ወጣ፡፡ ተኩስና ጩኸቱ ቀጠለ፡፡ አንዳንዱ ተኩሱ ወደሚሰማበት ሌላው ደግሞ ወደተኩሱ ተቃራኒ ይሮጣል፡፡

የተፈጠረውን አጋጣሚ ተጠቅማ ነጠላ ጫማዋን ከቦርሳዋ ውስጥ አወጣችና ቀየረች። ነጠላዋንም ለበሰች፡፡ በቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት በር ላይ አልፋ ወደ መሿለኪያ የሚወስደውን መንገድ ያዘች፡፡ በመሿለኪያ ወደ ፍላሚንጎ በሚወስደው መንገድ ተጠመዘዘች፡፡ አልፈው የመጣችው ፍተሻ እስከዚያ ሰዓት እንደማይቆይ እርግጠኛ ነበረች፡፡ ግምቷ ትክክል ነበር፡፡ የፍላሚንጎ አካባቢ ጭር ብሏል፡፡ ወደቦሌ የሚወስደውን አስፋልት አቋረጠችና በሰፈር ውስጥ መንገዶች እየተጠቀመች ወደሰፈሯ አመራች፡፡ ዕድል አልከዳቻትም ኡራኤል ቤተክርስቲያን በሰላም ደረሰች፡፡

ድንገት አካባቢዋን ጩኸት ሞላው፡፡ የተለመደው ሃየጥይትና የሰው ትርምስ የአካባቢውን ሰላም አደፈረሰው፡፡ በፍጥነት ተራምዳ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ገባች። አፍታም ሳይቆይ የኡራኤል ቤተክርስቲያን በተደናገጡና መሄጃ በጠፋቸው ሰዎች ተሞላ፡፡ ተከታትለው አብዮት ጥበቃዎቹ ሰዉን እየገፈታተሩ ገቡ፡፡ ቦርሳዋን ደበቀችና ነጠላዋን እንደተከናነበች መሬቱ ላይ በግንባሯ ተደፋች፡፡



ካሁን አሁን አንጠልጥለው አነሱኝ የሚለው ስጋት ቢያስጨንቃትም ባለችበት ሁኔታ ከመቆየት የተሻለ አማራጭ የላትም፡፡ ቀስ ብላ አካባቢውን ለማየት ትሞክራለች ጥበቃዎቹ የመሰላቸውን ሰው ሁሉ እያዳፉ ይነዱታል፡፡

ከተወሰነ መተረማመስ በኋላ አካባቢው ሰላም አገኘ፡፡ ከጥቂት ሰዎች በስተቀር ሰው ሙልጭ ብሎ ወጣ፡፡ ከተንበረከከችበት ተነስታ አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀመጠችና እንደገና ማሰብ ጀመረች፡፡ ምናልባት ሰፈር አካባቢም እንዲሁ ዓይነት አሰሳ ካለ እናቷ የቱን ያህል እንደሚጨነቁ ስታስበው ደግሞ የበለጠ ተረበሸች፡፡ እንደምንም ብላ መደወልና ደህንነቷን መንገር ይኖርባታል፡፡ የሕዝብ ስልክ ያለበትን ቦታ ለማስታወስ ሞከረች፤ ልታስታውስ ግን አልቻለችም፡፡ ሰዓቷን አየች፤ ጊዜው እየመሸ ነው።

የማታውን የፕሮፓጋንዳ ሥራ አሰበችው። ከዛ አልፋ ሊፈጠር ስለሚችለው ነገር ማሰብ ግን አልፈለገችም፡፡ የእለቱን ብቸኝነቷን ጠልታዋለች። ቅዱስን አግኝታው የያዘችውን ዕቃ ሰጥታው ቢሆን ቀለል ይላት ነበር። ወደቤት ለመመለስ ከተቀመጠችበት ተነሳች።

እንደገባች ራት ለመብላት ተጣደፈች ግን ምግቡን ስትጎርሰው አፏን ደም ደም አላት፡፡ ቅዱስን ለሰከንድ እንኳ ከአእምሮዋ ልታወጣው አልቻለችም፡፡ ምግቡን አነሳችና እጇንን ታጠበች::

"በልተሽ መነሳትሽ ነው" አሏት እናቷ፡፡

"ዛሬ ሥራ አለ" አለቻቸው ለጠየቋት ጥያቄ ሳትመልስላቸው

ከእናቷ ጋር ከተግባቡ ቆይተዋል፡፡ መጨቃጨቁ የትም እንደማያደርስ ስላወቁ ልጆቹ ራሳቸውን እንዲጠብቁ መምከርን ምርጫቸው አድርገውታል፡፡ "እስኪ እግዚአብሔር በሰላም ይመልስሽ" አሏት በቀስታ፡፡

አስቻለውን እመጣለሁ ካለችበት ሰዓት በማሳለፏ በጣም ተጨንቆ ሲንቆራጠጥ አገኘችው፡፡

"በደህናሽ ነው?" አላት እርሷ መሆኗን ሲያረጋግጥ።

"ለዛሬ ተርፌያለሁ" አለች ቁና ቁና እየተነፈሰች "ዕቅዳችንን ሁሉ በእጃቸው ያስገቡ ነው የሚመስሉት" አለች ተስፋ በመቁረጥ ሁኔታ።

"እባክሽን አባባም መረጃ የደረሰው ነው የሚመስለው፡፡ ልክ እንደቀበሌ ጥበቃ ጋቢውን ተከናንቦ በረንዳ ከተቀመጠ ግዜ የለውም።"

"እንዴት ይሻለናል ታዲያ? ሰፈራችን ግን ትንሽ መረጋጋት ይታይበታል፤" አለችው የገጠማትን አስታውሳ፡፡

"አንድ አማራጭ አለን፡፡ ቆሻሻውን እንደማትጠየፊ እርግጠኛ ነኝ" አላት አስቻለው።

"ከጥይት ቆሻሻ አይሻልም ብለህ ነው?" አለች አስቻለውን እየተከተለች።

በአጥርና አጥር መሀል ባለ ቀጭን መንገድ ውስጥ ገቡ፡፡ አስቻለው ጎንበስ አለና በአጥሩ ስር ባለው የቆሻሻ ፍሳሽ መውረጃ ላይ ለውሻ መከላከያ የተወነጋገረውን እንጨት እያነሳ ወደጎን አደረገው፡፡ "በይ ነይ" አላት አስቻለው በዐይኖቹም እያመላከታት፡፡ ምንም አላመነታችም እግሯን በቀስታ ወደቦዩ ሰደደችው እግሯን ሲቀዘቅዛት ቆሻሻውን ውሀ አስባ ዘግንን አላት፡፡ ምርጫ የለም ለመሹለክ ጎንበስ ስትል ትንፋገኑ በአፍና በአፍንጫዋ ገባ፡፡ እንደምንም ሾልካ ገባች፡፡ እንደገባች አስቻለውን መጠበቅ ነበረባት፡፡

“እነጋዲሳስ?” አለችው አስቻለው ሲመጣ።

“ከመጡ ቆይተዋል” አላት።

የአስቻለው አባት በረንዳቸው ላይ ተቀምጠው ቢያመሹም፤ አንድም ወጣት ወደዚያ ቤት ዝር ሳይል መቅረቱ እርሳቸው እዛ በማምሸታቸው መሆኑን ለራሳቸው ቢነግሩትም፤ በቅጥር ጊቢያቸው ውስጥ ግን ወጣቶቹ የራሳቸውን ዝግጅት ተያይዘውታል፡፡



ትንሿ የአስቻለው ክፍል በቀለምና በአልኮል ሽታ ታፍናለች፡፡ ፍሬሕይወትና አስቻለው እንደገቡ የአስቻለው እናት የክፍሉን በር ቆልፈው ወደሥራቸው ሄዱ፡፡ ፍሬሕይወትና አስቻለው ጊዜ ሳያባክኑ ወዲያውኑ ሥራቸውን ጀመሩ፡፡ ማርከሮቻቸውን አንስተው ተቆራርጠው በተዘጋጁት ወረቀቶች ላይ ትላልቅ ቀይ ፊደሎች መፃፍ ጀመሩ፡፡ ወንበር ላይ የተቀመጠው ዘርዓይ ቀለም በሌለው ስኪሪፕቶ ስቴንስሉ ላይ ይቀርፃል ጋዲሳም ወለሉ ላይ በዘረጋው ጨርቅ ላይ እንዲሁ በትላልቅ ፊደላት መፈክሮች ይጽፋል፡፡

ዘርዓይ ከወንበሩ ላይ ወደኋላ ለጠጥ ብሎ ተንጠራራና የቀኝ እጁን ጣቶች አፍታታቸው፡፡ ከኪሱ መሀረብ አወጣና እጆቹንና ፊቱን ጠራረገ፡፡ ውጭው ሙቀት ባይኖረውም የጠባቧ ክፍል የታፈነ አየር ሙቀት ፈጥሮ ፊታቸውን አወርዝቶታል፡፡ ጋዲሳም ከቆራረጣቸው ጨርቆች በአንዱ የግንባሩን ላብ እየጠራረገ ቆም ብሎ በአቡጀዲው ጨርቅ ላይ የጻፋቸውን ትላልቅ ፊደላት አዘቅዝቆ ተመለከታቸው፡፡ "ኢ.ሕ.አ.ፓ ያቸንፋል!" የሚለው መሐል ላይ ጉብ ብሎ ዐይን ይስባል፡፡ ከጨርቁ መሀል ለመሀል ከፍ ብሎ ደግሞ የፓርቲው አርማ በቀይ ቀለም ደምቋል፡፡ ማጭድና መዶሻው በሚገባቸው መልኩ ተስለዋል፡፡ ከማጭዱ ጫፍ ላይ መዋል ያለባት ኮከብ ግን ፈንጠር ብላ የተገነጠለች መሰለው፡፡ በርከክ አለ ኮከቧን ለማስተካከል ማርከሩን አነሳ፡፡

ጋዲሳ ሳያስበው ድንገት መዘመር ጀመረ፡፡

ለዘመናት በጭቆና ማጥ
በግፍ ሰንሰለት ታስሬ
ጨቋኙን ልጥል
በዝባዡን ልጥል
ተነስቻለሁ ዛሬ
ይኼው ታጥቄአለሁ ዛሬ...

"ጌታው ነፃ የወጣህ መሰለህ እንዴ?" አለ አስቻለው ከሚጽፈው ላይ አንገቱን ሳያቀና።

"ጻፋህ ለእኛም እንዳይተርፈን ጃል!" አለ ዘርዓይም ቀጠል በማድረግ፡፡ ጋዲሳ ድምጹን በጣም ዝቅ አድርጎ መዝሙሩን ቀጠለ

…በአንድ እንደሚነሳ ተበዝባዡ ሁሉ
ለማያጠራጥር ድሉ
ፍጹም ነው እምነቴ
የትግሉ ነው ሕይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና
በወደቁት ጀግኖች ፋና

አስቻለውና ዘርዓይም ሳያስቡት አብረውት መዘመር ጀመሩ፡፡ ወፈርና ለስለስ ያለው ድምጻቸው በዝግታ እንደሚወርድ ሙላት ውሀ ይፈሳል፡፡

…የሕዝቡ ታማኝ አገልጋይ ነኝ
የሠርቶ አደሩ ወታደር
ብረት አንሳሁ
ለትግል ተነሳሁ
ጠላት ይፍራ ይሸበር
ያድር ባይ ልቡ ይሰበር
ቢሰበር አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ
ላዲስ ስርዓት ልምላሜ
ፍጹም ነው እምነቴ
የትግሉ ነው ሕይወቴ…

ግድግዳው ሦስት ጊዜ ሲመታ ሁሉም ፀጥ አሉ፡፡ ሶስቱም ቀና ብለው ተያዩ፤ ተግባብተዋል፡፡ የአስቻለው እናት ድምፃቸውን ሰምተው ማስጠንቀቂያ እየሰጡ መሆኑን ለመረዳት ጊዜ የሚወስድባቸው አልነበረም፡፡

እንደገና ወደሥራቸው ተመለሱ፡፡ ዘርዓይ ስቴንስሉን ቀርፆ ሲጨርስ ማባዣውን ከአልጋው ስር አወጣ፡፡ ደስታ ወረቀቱን ወደአጠገቡ አቀረበ፡፡ የማባዣ ቀለሙን አዘጋጀ፡፡ "አደፍርስ" ሥራውን ጀመረ፡፡ "አደፍርስ" በራሳቸው የተሠራ የማባዣ ማሽን ነው፡፡



በስቴንስሉ ላይ የተቀረጸው ጽሑፍ በወረቀቶቹ ላይ እየታተመ ወጣ፡፡ ጥራቱ ዘርዓይን አስደሰተው፡፡ ከፊት ለፊቱ ላለው አስቻለው ከሩቅ አሳየው ህትመቱን፡፡ አስቻለው ጥራቱን በማረጋገጥ ዓይነት አውራ ጣቱን ከፍ አድርጎ አሳየው፡፡ ጽሑፉ በወጣት ሊጉ አባላት የሚዘጋጀው ወርሃዊ የአካባቢ ጋዜጣ ነው፡፡ የጋዜጣው ስያሜ "ፍልሚያ" ይባላል፡፡ በዕለቱ የሚወጣው ርዕሰ ጉዳይ ደግሞ "የፋሽስቶች ድንፋታ በሕዝብ አመፅ ይበርዳል!!" የሚል ነው፡፡

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ሁሉም ዝግጅት ተጠናቀቀ፡፡ የሚበተኑት ወረቀቶች በየመልካቸው ተቀመጡ፡፡ የሚሰቀሉት ባነሮችና ባንዲራዎችም ተዘጋጁ፡፡ በአጥሮች፣ በግድግዳዎችና በአስፋልት ላይ መፈክር የሚፃፍባቸው ቡሩሾችና የቀለም ቆርቆሮዎች እንደሚመቹ ተቀመጡ፡፡ ከሌሊቱ በአስር ሰዓት ተኩል ላይ ወጥተው ተግባራዊ ሥራውን ለማከናወን መንፈሳቸውን ዝግጁ አድርገው ጋደም ጋደም አሉ፡፡

ከጓዶቿ ጋር እኩል በመድረሳቸው ፍሬሕይወት በጣም ተደሰተች፡፡ ሥራቸውን ጨርሰው እጆቻቸው ነፃ ሲሆኑና የተኩሱ ድምጽ የሌሊቱን ፀጥ ያለ አየር ሲያደፈርሰው እኩል ሆነ፡፡ ከመቅጽበት አቅራቢያቸው ወደአለው የእነእሸቱ ግቢ ገቡ፡፡ ድንገተኛ አደጋ ቢያጋጥም ተብሎ የተዘጋጀው የአገባብ መንገድ ተግባራዊ ሆነ፡፡ እሸቱ አስቀድሞ ደብቆት የነበረውን መሰላል አመቻቸና ሁሉም በፍጥነት ወደግቢው ገቡ፡፡ ሁሉም ከገቡ በኋላ እሸቱ ግንቡ ላይ ወጥቶ መሰላሉን ወደውስጥ አስገባ፡፡

ግቢው ሰፊ ነው፡፡ በገቡበት በኩል የከብቶች ቤት አለ፡፡ ከከብቶቹ ቤት አጠገብ ያለችው የከብቶች መኖ ማከማቻ ቤት ምቹ ነበረች፡፡ እሸቱ ጓደኞቹን አስገብቶ የመኖ ማከማቻዋን ከውጭ ዘጋና ወደቤቱ ገባ፡፡ እሸቱ የሰጣቸውን ጋቢና ፍሬሕይወት የያዘችውን ነጠላ ለብሰው ጥግትግት ብለው ተቀመጡ፡፡ ጋብ ብሎ የነበረው ተኩስ ባሰበት፡፡ የውሾቹ ጩኸት ከተኩሱ ድምጽ ጋር ተደርቦ የአካባቢውን ሰላም በጠበጠው፡፡ በእያንዳንዱ ሌሊት የተኩስ ድምጽ መስማት የተለመደ ስለሆነ ማንም ከመኝታው አይነሳም፡፡

ፍሬሕይወት እነጋዲሳን አሰበቻቸው፤ ያሉበትን ቦታና የተኩሱን አቅጣጫ ግን ማገናዘብ አልቻለችም፤ ስታስበው ዝግንን አላት፤ ጆሮዎቿን ወደ ተኩሱ አቅጣጫ አቀናች፡፡ ድንገት ተኩሱ ረጭ አለ፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደግሞ ቀጠለ አቅጣጫውን ለመረዳት በሞከረች ቁጥር ግን ትደነግጣለች፡፡ አስቻለው አሁንም አሁንም በፊቷ ድቅን እያለ አስቸገራት፡፡ በማንኛውም ጊዜ ጭንቀት ሲበዛባት እንደሚሰማት ሁሉ መንፈሷ የሆነ መጠጊያ ፈለገ መጸለይ አማራት፡፡ የተከተለው ኃይለኛ ተኩስ ሀሳቧን በታተነባት። ቅዱስን አስታወሰችው። ልክ እንደ ቅዱስ በዚህ ጊዜ ቡድኑን ማረጋጋት እንደሚጠበቅባት አሰበች፡፡

"አይዞን!" አለች ሁሉንም እየቃኘች፡፡ በገጽታቸው ላይ የተመለከተችው ጥንካሬ እርሷን የበለጠ አጠነከራት።

ንጋቱ እየተቃረበ ነው፡፡ ያሉበት ቤት በተሠራበት ቆርቆሮ ቀዳዳዎች ብርሀን ጭል ጭል ማለት ጀምሯል፡፡ አንድ ጊዜ የተኩስ እሩምታ ተከታትሎ ወረደና ደግሞ ጸጥ አለ፡፡ የበለጠ የቀረበ መሰላቸው፤ ሁሉም ተፋጠጡ፡፡ ግማሽ ሰዓት ያህል ተቀመጡ። ተኩሱ አልተደገመም ፍሬ ልቧ ክፉኛ ፈራባት፤ እሽቱም አልዘገየም ወዲያውኑ በሩን ከፈተና "ፍጠኑ" አለ አባቱና እናቱ ሲወጡ ተመልክቶ። ከዚያ ግቢ መውጣት ግዴታ ነው፡፡ በማንኛውም ሠዓት ለከብቶች ምግብ ለመስጠት ሰው መምጣቱ የማይቀር ስለሆነ ሳይታዩ መውጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ኩርምት ብለው ያደሩ እግሮቻቸውን ጥቂት አፍታቱና በቀስታና አንድ በአንድ በዋናው በር ወጡ፡፡
የንጋቱ ተኩስ ከአእምሮዋ አልጠፋ ብሏት ፍሬሕይወት ስሜቷ አስቸገራት፡፡ ማጣራት ያስፈልጋታል፡፡ ከጃኬቷ ስር ወገቧ ላይ አስራው የነበረውን ነጠላ ፈታችና ለበሰችው፡፡ የጠዋቱን ተኩስ አቅጣጫ ተከትላ እነአስቻለው ተመድበውበት ወደነበረው ቦታ ሄደች። ሰዎች ይንጫጫሉ፡፡ እግሮቿ አልታዘዝ አሏት፣ ግን መሄድ አለባት፡፡ አንዲት አሮጊት ሴት ከወደግርግሩ አቅጣጫ ሲመጡ ተመለከተች፤ "እማማ ምንድነው ግርግሩ?" አለቻቸው የጠረጠረችውን እንዳይነግሯ እየፈራች፡፡

"እኔ ዝርግት ልበልለት! እነዚህ አረመኔዎች ዝርግት አድርገውታል፡፡" አሏት በነጠላቸው ጫፍ ዐይኖቻቸውን እየጠራረጉ፡፡ የምትሆነውን



እስከምታጣ ድረስ ደነገጠች፡፡ በሩጫ ወደግርግሩ ሄደች ከመድረሷ በፊት ግን ሩጫዋ ተገታ።

"ምን ልትጨምሪለት ነው የምትሮጪው?" አለቻት ከወደዚያው የምትመጣ ሴት።

"ማነው፤ ምንድነው?" አለች ፍሬሕይወት። ሴትዮዋ እጇን ጥብቅ አድርጋ ያዘቻትና "አስቻለው ነው፤ በይ አሁኑኑ ከዚህ አካባቢ ጥፊ አንድ ወጣት እንኳ እንዲተርፉቸው የሚፈልጉ አይመስሉም" አለቻት።

ሴትዮዋ ትግሉን በከፍተኛ ስሜት ከሚደግፉት የሴቶች ማህበራት አመራሮች አንዷ ነች፡፡ ለፍሬሕይወት በፍጹም ጊዜ አልሰጠቻትም፤ በፍጥነት ከዚያ አካባቢ እንድትጠፋ ጎተጎተቻት፡፡ በደመነፍስ የኡራኤልን መንገድ ተከትላ ሄደች፡፡ እንባዋ ዐይኖቿን አቃጠላቸው፤ ልትገታው አልቻለችም፤ ገነፈለባት፡፡

"ለስንቱ ተለቅሶ ይዘለቃል ብለሽ ነው ልጄ" አሏት አንዲት ሴት በአጠገባቸው ስታልፍ፡፡ ቀደም ሲል የጠየቀቻቸው ሴት ናቸው፡፡ እርምጃዋን ቀነስ አደረገችና አብራቸው መሄድ ጀመረች፡፡

"እማማ የሞተውን ልጅ ያውቁታል?" አለቻቸው።

"እንዴት አላውቀው ልጄ? እንዴት ያለ ቅን ልጅ መሰለሽ በሰላምታ ብቻ የሚያጠግብ የተባረከ ልጅ ነበር..." እንባቸው ንግግራቸውን አላስጨረሳቸውም፡፡ ሀሳቧን ከፊት ለፊቷ የተመለከተችው ነገር ወሰደባት፡፡ አብዮት ጥበቃዎች እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው ወደእነርሱ አቅጣጫ ይመጣሉ፡፡ በመንገዳቸው ላይ ያገኙትን ወጣት ሁሉ እያግተለተሉ ናቸው፡፡ እፊት ፊታቸው የሚሄደው ወጣት የሚገባበት ማጣቱ በደንብ ይታያል፡፡ ምን እንደሚያደርግ ለመወሰን ጊዜ እንኳ አላገኘም፤

"ቁም!" አለው አንደኛው አብዮት ጥበቃ መሣሪያውን ወደእርሱ እያነጣጠረ፡፡ ልጁ አልቆመም በግብርና ሚኒስቴር አጠገብ ባለው መንገድ ሮጠ፡፡ አብዮት ጥበቃውም ተኮሰ፤ ልጁ በደረቱ ተዘረጋ፡፡

ፍሬሕይወት ሳታስበው ወደልጁ አቅጣጫ መሮጥ ስትጀምር አሮጊቷ እንቅ አድርገው አስቀሯት፡፡ መንፈሷ ሁሉ ተረበሸ በጭራሽ መረጋጋት አቃታት፡፡ አብዮት ጥበቃዎቹ ትኩረታቸውን የተመታው ልጅ ሲስበው ከሚያግተለትሏቸው ወጣቶች መሀል የተወሰኑት አመለጡ፤ በዚህ ደግሞ ደስ አላት፡፡

ደም የለበሱ ዐይኖቻቸውን እያጉረጠረጡ አብዮት ጥበቃዎቹ መንገዳቸውን ቀጠሉና እነፍሬሕይወት አጠገባቸው ደረሱ፡፡ "ቁም! አለ የተለመደውን መግሪያውን ደግሞ"።

"ወላዲተ አምላክ! ምንድነው ጉዱ" አሉ አሮጊቷ እያማተቡ።

"ወዲህ ነይ ሽርሙጣ!" እንደብራቅ ጮኸ አብዮት ጥበቃው።

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! ምነው ልጄ እንዲህ ያለው ጸያፍ ነገር ለአፍህ አይከብድህም?" አሉ አሮጊቷ በጣም ተቆጥተው።

"አርፈው ወደ ቤተክርስቲያንዎ ይሂዱ እርስዎን ማን ፈለገ ነይ አንቺ!" አለ ጣቱን ወደፍሬ ቀስሮ።

"ልጄ አብረህ ውሰደኝ እንጂ ምን ይገባ እሄዳለሁ፡፡ ከእንቅልፏ ቀስቅሼ ከቤት አውጥቼ የት እገባለሁ" አሉት በማስተዛዘን ንዴታቸውን ሁሉ ትተው፡፡ ምንም ሳይመልስላቸው አልፏቸው ሄደ። እነርሱም ወደቤተክርስቲያን ሄዱ።

ከሰዓት በፊቱ የጭንቅ ጊዜ እንደሆነ አለፈ፡፡ ሁሉ ነገር ያስጠላል፡፡ ሰው አልቅሶ ሀዘኑን የማያወጣበት፤ ለለቅሶም መብት የታጣበት ጊዜ ላይ በመደረሱ ኀዘን ያልተሰማው ሰው አልነበረም፡፡ ፍሬሕይወት ለአስቻለው አልቅሳ ሐዘኗን ባለመከፈሏ ውስጧ መረረ፤ ስሜቷን የሚጋሯትን ጓደኞቿን ልታገኛቸው ባለመቻሏም የበለጠ ተከፋች፡፡ የአስቻለውን እናት ከአእምሮዋ ልታወጣቸው አልቻለችም።

* * * *



አንዳንዴ ከቀናት ሁሉ የተለዩ ቀናት ያጋጥማሉ። ለቅዱስ ሰሞኑ ሁሉ የስቃይ ጊዜ ሆኖበት ነው የሰነበተው፤ እቤቱ ተመልሶ ባይገባ የተሻለ እንደሚሆን ተነግሮት የተሰጠው አማራጭ መጠለያም ከአንድ ቀን በኋላ ደግሞ የሚሄድበት ሳይሆን ቀረ። በሚቀጥለው ቀን ሲያድር የሄደበት ቤትም ለመግባት አመቺ ሳይሆን በመቅረቱ ያጋጠመውን ሁኔታ ሲያስታውስ ፈገግ አለ።

ወደዛ ቤት ከመሄዱ በፊት ስለቤቱ መረጃ ቢነገረውም እንደዛ ዓይነት ሁኔታ ይገጥመኛል ብሎ አላሰበም ነበር። የተቀጠረበት ሰዓት ሲደርስ ወደተባለው ቤት ሄደ፤ የቀጠረው ሰው ሰዓቱን አክብሮ ደርሷል። መጠለያውን ካመቻቸለት ሰው ጋር ወደማደሪያው ሄዱና የውጭውን በር በተነጋገሩት መሠረት ሦስት ጊዜ መታ መታ ሲያደርገው ተከፈተ፤ በሩን የከፈተው ግን የቀጠረው ወጣት ሳይሆን አባትየው ነበሩ።

ትልቅ ነጭ ገዋን ደርበውና ነጭ ፊር ያለው ምቹ ነጠላ ጫማ ተጫምተው የሚንጎማለሉት አባት በሩን ከፍተው ያገኙትን ሰው በግልምጫ አነሱትና "ማንን ፈለግህ?" አሉት በቁጣ። የቀጠረውን ልጃቸውን ከበስተጀርባቸው ተመለከተውና "እርሱን" አለ በጣቱ እየመለከተ። ዞር ብለው ልጃቸውን ተመለከቱትና "መቼም ቅራቅንቦ አታጣ ደግሞ ይሄ ማን ነው?" አሉት ልጃቸውን። መልስ አልመለሰም በትህትና አልፏቸው ገርበብ ያለውን በር ከፍቶት ወጣ።

"ይቅርታ! ሳላስበው አባቴ ጠርቶኝ ነው" አለ ሀዘንና ጭንቀት ከገጽታው ላይ እየተነበበ።

"ይሄ እንኳ ችግር የለውም፤ ግን እንዴት መግባት ይቻላል ነው ጥያቄው" አለ ቅዱስን ያመጣው ሰው።

"አመቻችቻለሁ" አለ ልጁ ወደጓሮው እንዲዞሩ እየመለከታቸው። ተከተሉት።

ቅዱስ በሁኔታው ምንም ግራ የመጋባት ስሜት አላሳየም። ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ተመሳሳይ ገጠመኞቹ በርካታ ናቸው። ቅዱስን ያመጣው ሰው ከጊቢው ጓሮ እንደዞሩ ትቷቸው ሄደ።

"አይዞህ ምንም ችግር አይገጥምህም" አለው ልጁ ቅዱስን።

ከግቢው ጀርባ ያለችውን ትንሽ በር በቀስታ ከፈተ። በሩ የሚገኘው ከጥግ እስከጥግ በተሰሩት የሰርቪስ ቤቶች መሀል ነው። ቀስ ብለው ወደቀኝ በኩል ሄዱና አንድ ክፍል ከፍተው ገቡ። ንጹህ ክፍል ነው፤ ከፊት ለፊት ባለው ግድግዳው ጥግ አንድ የተነጠፈ አልጋ አለ፤ ከአልጋው አጠገብ ደግሞ ሁለት ወንበሮች አሉ።

"ልብስህን እስከምትቀይር እመለሳለሁ" ብሎት ወጣ ልጁ፤ መዝጊያው ከውጭ ሲቆለፍ ተሰማው። አልጋው ላይ ተጣጥፈው የተቀመጡትን ልብሶች አስተዋላቸው ፤ ሆኖም ልብሱን ለመቀየር አመነታና እወንበሩ ላይ ተቀመጠ። ጥቂት ቆይቶ ልጁ ተመልሶ መጣ።

"ለምን ልብስህን አልቀየርክም? ለአንተ እኮ ነው ያስቀመጥኳቸው" አለ ልጁ።

ቅዱስ ልብሶቹን ቀየረና ከአልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠ። በዝምታ ጥቂት ቆይቶ ልጁ ለመሄድ ተነሳ። "ምንም የሚያሰጋህ ነገር የለም፤ እዛች ውስጥ የሚያድረው ልጅ የኔ እንግዳ መሆንህን ያውቃል አያሳስብህ፤ በጠዋት እመጣለሁ" አለና ሄደ። ቅዱስ ልጁ ከሄደ በኋላ ብዙም አልቆየም፤ ተኛ።

ከእንቅልፉ ሲነቃ ገና ከሌሊቱ አስር ሰዓት ነበር፤ ሲነቃ የት እንዳለ ለማወቅ ጥቂት ማሰብ ነበረበት፤ በኋላ ትዝ አለው። የቤቱ ውስጥ በጣም ጸጥ ያለ ነው፤ ከውጭ ግን አልፎ አልፎ የሰዎች ንግግር ይሰማል። ጊዜው በጣም ተጎተተበት፤ ሰዓቱን ለማየት ሞከረ ገና አስራ አንድ ሰዓት ተኩል ነው፤ ተገላበጠ። ድንገት በሀሳብ ተሳፍሮ ያን ግቢ ትቶ ጭልጥ አለ። ሁልጊዜም ጥቂት ጊዜ ሲኖረው እንደሚያደርገው ሁሉ በሀሳቡ ከእናቱ ጋር ተገኘ። እንደወትሮአቸው ሁሉ ሲያዩት ተንሰፈሰፉ፤ የሚይዙትና የሚጨብጡት ጠፋቸው። ግንባሩን፣ ጉንጩንና አንገቱን ሳሙት፤ እንደልጅነቱ እራሱን አሻሹት… እናቱ ካያቸው ጊዜ ወዲህ በጣም አርጅተው፤ ጉስቁልናቸውም ጨምሯል… "ወይኔ!" አለ ሳያስበው።



በቅጽበት ደግሞ ቀዝቃዛ ውሃ ተደፋበትና "የ መንፈስ ርኩስ በስሙ ለእየሱስ ክርስቶስ…" የሚል ድምጽ ተሰማው፤ ቀዝቃዛው ውሀ እንደገና ተረጨበት።

"እርስዎ ግን መቼ ነው ከተንኮል አለፍ ያለ ሀሳብ የሚያስቡት?" የሚል ድምጽ ተከታትሎ ተሰማው። የልጁ ድምጽ ነው።

"ሥራዬ መሆኑን ዘነጋኸው? ኃይለ አጋንንትን መቃወም ነው ሥራዬ" አሉት ቀዝቃዛውን ውሀ የረጩት ሰው።

"በሉ እሽ ለሰጡት አገልግሎት ይህችን ይያዙና ይውጡ፤ ለአንድ ሰው ነግረው ብሰማ ግን…"

ሰውየው መውጣታቸውን ሲያረጋግጥ ቅዱስ የተሸፈነበትን ልብስ ገለጠና ልጁን አየው።

"ተንኮል በመሥራት ብቻ የሚኖር ሰው ገጥሞህ ያውቃል?" አለው ልጁ። ቅዱስ መልስ አልሰጠውም ልብሱን በፍጥነት ለባበሰና ለመውጣት ዝግጁ ሆነ። በገባበት የጓሮ በር እንዲወጣ ከፍቶለት ለስንብት ሲጨብጠው ከተጠቀለሉ ብሮች ጋር ጨበጠው። ቅዱስ ቀና ብሎ ተመለከተው፤ አመለካከቱ ጥያቄ ነበረበት።

"እባክህን እምቢ አትበለኝ" አለ ልጁ ልብ በሚነካ ሁኔታ። ተቀበለውና "አመሰግናለሁ" አለው። ልጁ በሩን ቆልፎ ሲገባ ቅዱስ ደግሞ የሚቀጥለውን ምሽት የት እንደሚያሳልፍ እያሰበ ነበር። የማይቀረው ምሽት የራሱን ታሪክ ይዞ እስከሚመጣ ድረስ ሥራውን መሥራት አለበት። የዕለቱን ተግባራት ለመፈጸም የመጀመሪያው ቀጠሮ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ነው፤ እስከዛ ያለውን ጊዜ ለማሳለፍ በአቅራቢያው ወዳለው ቤተክርስቲያን አመራ።

ቀኑ ምንም እንኳ ስጋትና ውጥረት የበዛበት ቢሆን ከሌሊቱ ፈጥኖ ያልፋል። በየመንገዱ በሚያጋጥሙ ያልተጠበቁ አጋጣሚዎች ምክንያት የሚሰናከሉ ቀጠሮዎች እየበረከቱ ቢሄዱም ተለዋጭ ቀጠሮዎችን የመጠቀም ልምድ በመኖሩ ለማካካስ ጥረት ይደረጋል። ቅዱስ ከሰዓት በፊት ከነበሩት ቀጠሮዎች አብዛኞዎቹን ተሳክተውለት

ሲያጠናቅቅ ሁለት ቀጠሮዎች ተበላሽተውበታል። ረሀብ ተሰማው፤ ጠዋት ልጁ የሰጠው ገንዘብ ትዝ ሲለው ጥሩ ምግብ የመመገብ ፍላጎት አደረበት። ሳይቆጥር ወደኪሱ የከተታቸውን ብሮች አወጣና ቆጠራቸው፤ ከግምቱ በላይ ሆነበት። “አምስት መቶ ብር!” አለ ለራሱ።

ሰዓቱን ተመለከተ፤ ከሰዓት በኋላ ከፍሬሕይወት ጋር ያለው ተለዋጭ ቀጠሮ ገና ነው። ስታዲየም ዙሪያ ካሉ ምግብ ቤቶች ወደ አንዱ ገባና ምግብ አዘዘ። ምግቡ እስኪመጣለት ድረስ በሀሳቡ የማታ ማደሪያውን ያሰላስል ገባ።

ሀሳቡን ሳይጨርሰው ያዘዘው ምግብ ቀረበለት። ከምግቡ ላይ ገና ሁለት ጊዜ እንደጎረሰ አካባቢው ትርምስምሱ ወጣ። ድንገተኛ አሰሳ ነበር፤ ወታደሮቹ ዐይኖቻቸውን እያጉረጠረጡ ሰውን ያተራምሱት ገቡ። ቅዱስ ከተቀመጠበት ቦታ ትይዩ ተቀምጠው የነበሩት ሰዎች ተደናግጠው የወታደሮቹን ሁኔታ በመከታተል ላይ ሳሉ “እጅ ወደላይ” አላቸው አንደኛው ወታደር። ከየት እንደተተኮሰ ያልታወቀ ጥይት ወታደሩን ከመሬቱ ላይ አነጠፈው። አካባቢው ቀውጢ ሆነ፤ ምግብ ቤቱ ወደጦርነት አውድማነት ተለወጠ።

ቅዱስ ወገቡ ላይ የነበረችውን ሽጉጥ ዳበስ አደረገና ሊያስወጣው የሚችል በር ፈለገ። ከመጠጥ መደርደሪያው በስተጀርባ ያለው በር ገርበብ እንዳለ ነው። እቤቱ ውስጥ ያለው ሰው ይተረማመሳል፤ ሰስት ጊዜ ተራመደና ቅዱስ እመደርደሪያው አጠገብ ደረሰ፤ ተኩሱ ከፊትለፊት በኩል ተደጋገመ፤ የቤቱ ውስጥ የበለጠ ተተረማመሰ። አንድ ወታደር ዓይኖቹን በቅዱስ ላይ አፈጠጠበት፤ ሊላው ደግሞ “እዳትንቀሳቀስ! ቁም” አለው። ቅዱስ እጁን እወገቡ ላይ ባለችው ሽጉጥ ላይ አስተካከለ፤ ወታደሩ ጠመንጃውን አነጣጠረበት። ቅዱስ ለራሱም በገረመው ፍጥነት ሽጉጡን አውጥቶ ባፈጠጠበት ወታደር ላይ አነጣጠረ፤ የሽጉጡን ቃታ ሳበው… ወታደሩ ሲወድቅ አየው… ገርበበ ባለው በር ለመውጣት ሮጥ አለ ቅዱስ። እበሩ ላይ ከመድረሱ በፊት ግን ተቀደመ፤ ጀርባው ላይ በጥይት ተመታ።



ከዚያ በኋላ የሆነው ነገር ሁሉ ቅዠት ነበር፤ ዝብርቅርቅ ያለ ቅዠት። ቅዱስ በዝብርቅርቁ ሀሳቡ ውስጥ እናቱ ጉልህ ሆነው ታዩት፤ ተጎሳቁለዋል፤ አርጅተዋል…

* * * *

ዛሬ ሚሚ በጊዜ ነው ከሥራ የተመለሰችው። ስትገባ እናቷንና ሮቤልን ሰላም ካለች በኋላ “ፍሬ አልመጣችም እንዴ?” አለችው ሮቤልን።

“አሁን ነው የወጣችው” አላት ሮቤል።

ሚሚ ወደመኝታ ክፍሏ ገብታ ቦርሳዋን አላስቀመጠችውም፤ እክፍሉ መሀል ቆመች። ግራ ግብት እንዳላት ነች፤ ምስቅልቅል ያለ ስሜት አእምሮዋን ተቆጣጥሮታል።

“ሚሚ” ብለው ተጣሩ እናቷ።

“እመት” አለችና ቦርሳዋን አልጋው ላይ ወርውራ ወደእናቷ ሄደች።

“መክሰስሽን ብይ እንጂ፤ ምነው ገብተሽ ቀረሽ?” አሏት እናቷ።

“ይቅርብኝ እባክሽ እማ፤ ልመጣ ስል ነው ሻይ የጠጣሁት” አለቻቸው። ውሸቷን ነው፤ ዛሬ ምሳዋንም ሳትበላ ነው የዋለችው።

ተመልሳ ወደመኝታ ክፍል ገባች። ውሎዋን መርሳት አልቻለችም፤ እንዴት ፈታኝ ዕለት ነበር? በመጨረሻው ግን ተሳክቶላታል፤ የተፈለገውን ሰነድ ከአገር ግዛት ጽሕፈት ቤት አውጥታ ለሚመለከተው ሰው አቀብላ ነው ወደቤት የመጣችው። ተልዕኮው ከተሳካ ለፓርቲው ትልቅ ስኬት ለመንግሥት ደግሞ ትልቅ ውድቀት ነው። ቢሳካም ባይሳካም ሚሚ ከእንግዲህ እዚያ አካባቢ መታየት አይደለም ያለችበት ቦታም ሊታወቅ አይገባውም። በሌሊት አዲስ አበባን ለቃ መውጣት አለባት።

ከአዲስ አበባ ለመውጣት የሚያስችላት ማንኛውም ሁኔታ ተመቻችቶላታል። ጫፍ ላይ ስትድርስ ግን መንፈሷ እርብሽ ብሎባታል፤ እንዴት አድርጋ ነው እናቷን፣ እህቷንና ወንድሞቿን ትታ የምትሄደው? አልጋዋ ላይ በጀርባዋ ተዘርግታ ጣሪያው ላይ አፈጠጠች፤ ድንገት አንድ መዝሙር በጆሮዎቿ ተሰማት።

"ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ
እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቸጉቬራ..." በውስጧ ዘመረችው።

በሀሳቧ የአሲምባ ተራራን ተመለከተች፣ ወጣችው ወረደችው፤ ራሷን እዚያ ካሉ ተዋጊዎች እንደአንዳቸው አድርጋ አየች፤ ከእርሷ በፊት በርካቶች መሄዳቸውን ሰምታለች። መንፈሷ ሲጠነክር ተሰማት።

"ልልፈሰፈስማ አይገባኝም!" አለች ለራሷ።

ተነሳችና ዕቃዎቿን ማዘጋጀት ጀመረች። በመጀመሪያ ወረቀቶቿን አንድ በአንድ እያወጣች መቃጠል ያለባቸውን ለየች፤ ከዚያ ደግሞ ልብሶቿን ማውጣት ጀመረች፤ ከሁለት ልብስ በላይ እንደማያስፈልጋት ተነግሯታል። ለመንገድ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ሱሪዎችና ከላይ የሚለበሱ ካናቴራዎች መረጠች። በቃ! አንድ ጠዋት ስትወጣ የምትደርበው ወፈር ያለ ጃኬት ይዛለች...

"ሚሚ" አለች ፍሬሕይወት ወደእርሷ እየመጣች።

"እመት!" አለቻት ሚሚ ወረቀቶቹን ላስቲክ ውስጥ እየከተተች።

"በደህና ነው የፈለግሽኝ?" አለች ፍርዬ ቆም ብላ ሚሚን እየተመለከተቻት።

"ደህና ነኝ..." አለች ሚሚ፤ አባባሏ የሆነ ቅላጼ አለው።

"አይመስልም!" አለች ፍሬሕይወት ድምጿን ዝቅ አድርጋ።

"መሄዴ ነው ፍሬ" አለች ሚሚ ትቷት የነበረው መረበሽ እንደገና እየተሰማት።



"የት?" አለች ድንገት፤ ጥቂት አሰብ ስታደርግ ይህን ጥያቄ መጠየቅ አያስፈለጋትም ፍሬሕይወት፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የብዙዎች የፖለቲካ ሰዎች ከአዲስአበባ መሄድ እየተለመደ ነው። ራሷን ግን ማረጋጋት አለባት። ሚሚ ልጅ ናት የታናሿ ታናሽ፤ ግን ግድ ነው፤ ብዙዎች ሄደዋል፤ ከዚያም በላይ ተሰውተዋል። ስለዚህ ሚሚን ልታበረታታት ይገባታል። እራሷን አረጋጋችና

"ፈራሽ እንዴ ታዲያ?" አለቻት ኮስተር ብላ።

"ሳይሆን እማዬን..." አለችና አንጠልጥላ ተወችው።

"እሱ ልክ ነው። ግን ባትሄጂስ የሚከተለው ምንድነው? ለእማዬ "ልጂ ተገደለች" ከማለት "ሄደች" ማለት ይቀላታል" አለቻት።

"ልነግራት ግን አልችልም" አለች ሚሚ ቀስ በቀስ የተረበሸ ስሜቷ እየተረጋጋላት።

"መንገር አይጠበቅብሽም" አለቻት ፍሬሕይወት የበለጠ ተረጋግታ።

ሚሚ አንገቷ ላይ ተጠመጠመች፤ ተቃቀፉ። ሁለቱም ላለማልቀስ ጥረት እያደረጉ ባሉበት "እናንተ ልጆች!" የሚለው የእናታቸው ድምጽ ገላገላቸው። "ምን እያደረጋችሁ ነው? ራት መብላት አልፈለጋችሁም?" አሉ እናታቸው። ሚሚና ፍሬሕይወት ተከታትለው ወደሳሎን ገቡ።

ፍሬሕይወት ስሜቷን ለመሸፈን ያደረገችው ጥረት ውጫዊ ገጽታዋን ቢቀይረውም ውስጧ ግን እንደተረበሸና በሀሳብ እንደተወጣጠረ ነው። አስቻለውን ከሀሳቧ ልታወጣው፤ ስለነዘርአይም ማሰቧን ልታቋርጥ አልቻለችም። አሁን ደግሞ የሚሚ ነገር ተጨመረበት፤ ሞትና ስደት እየተበራከተ መሆኑ አሳሰባት።

* * * *

"ስብሰባውን የምናደርገው የት ይሆን?" አለ በላይሁን እየደር እየተፈጠረ ያለውን ሁኔታ በአእምሮው እየመላለሰ። ስብሰባዎችን ማካሄድ ከባድ እየሆነ ሄዷል። ጠንካራ የነበረ የመተማመን መንፈስ ቀስ በቀስ እየተሸረሸረ መጠራጠር በቦታው እየተተካ ሲሄድ አስተውሏል።

አንተነህ ድቅን አለበት፤ የሆነውን ነገር መቀበል አልዋጥልህ ቢለውም በመዋቅሩ የደረሰውን መረጃ ያለማመን የተሰጠውንም ኃላፊነት አለመቀበል አልቻለም። ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ግን የአንተነህን ሁኔታ ከማንሳት አይቆጠብም።

"ዓለም የሀሳብ ልዩነት ሊኖረው ቢችል እንኳን በምንም መልኩ በጠላትነት ሊቆም አይችልም" ይላል ሁል ጊዜ ጉዳዩ ከተነሳ። ያም ሆነ ይህ ዓለም ከዞን ኮሚቴ ሰብሳቢነቱ ተነስቶ በአንድ ለአንድ ግንኙነት እንዲቆይ ተወስኖ ቦታውን በላይሁን እንዲይዝ ሆኖአል።

በተቻለ መጠን የስብሰባ ቦታዎችን መቀያየር እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል። የነበሩት የስብሰባ ቦታዎች ከፓርቲው ጋር የሀሳብ ልዩነት ፈጥረው የተለዩት አባላት በሙሉ ያውቋቸዋል፤ ሌሎች አዳዲስ ቦታዎችን ለማግኘት ደግሞ ጊዜው አያመችም። በላይሁን አዲስ የስብሰባ ቦታ ለማግኘት በሀሳቡ ሲማስን አእምሮው ብጥብጥ አለበት። ዛሬ የሚሰበሰቡበትን ቦታ የሚጠቀሙበት ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚሆንም ተወስኗል። እንደምንም ብሎ አንድ ለመሰብሰቢያ ሊሆን የሚችል ቦታ በአእምሮው ብልጭ አለለት። ደስ አለው።

"እርስ በእርስ መጠፋፋት ሊመጣ ይሆን እንዴ?" እያለ ራሱን የሚጠይቅባቸው ጊዜያት እየበዙ መጥተዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች የታዘባቸው ክርር ያሉ አስተያየቶች ስጋት ላይ ይጥሉታል "በፍጹም!" ይላል ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዲፈጠር የማይፈልጉ ብዙዎች መሆናቸውን ያስብና።

በዛሬው ስብሰባ ትላልቅ ውሳኔ የሚፈልጉ አጀንዳዎች ላይ መነጋገር አለባቸው። ስለአጀንዳዎቹ ሲያስብ ዳንኤል ትውስ አለው። አንዱ የመወያያ አጀንዳቸው የዳንኤል ጉዳይ ነው። ስለዳንኤል ያልደረሰ መረጃ የለም ለአካባቢ ወጣቶች መገደል፤ መታሰር እንዲሁም



ለበርካታ ወጣቶች መሰደድ ምክንያቱ እርሱ እንደሆነ የሚገልጹ መረጃዎች ከተለያዩ ኮሚቴዎች ቀርበዋል። እናም በዳንኤል ላይ መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ተነጋግሮ የውሳኔ ሀሳብ ማሳለፍ ይጠበቃል። ለዳንኤል ያለው ስሜት ይህ ነው የሚለው አይደለም፤ ከዱሮውም ቢሆን ፍቅርም ሆነ ጥላቻ የላቸውም። ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየጠላው መጥቷል፤ ፖለቲካን ከግል ፍላጎቱ ጋር አጣምሮ መረማመጃ ማድረጉ፤ በተለይም ለብዙ ወጣቶች ሞት ስጋትና ስደት ምክንያት መሆኑ አበሳጭቶታል።

በላይሁን ሰዓቱን ተመለከተ፤ ጊዜ አለው፤ ፍሬሕይወትን ማግኘት ይችላል። እቤት ከገባ ስንት ቀናት እንዳለፉ አሰበና የእናቱ ጭንቀት ተሰማው፤ ግን እየደወለ ደህንነቱን ይነግራቸዋል። አንዳንዴ አባቱ ቢሮ እየሄደ ያገኛቸዋል። ስልኩን ደወለ፤ ስልኩ ለወትሮው በፍጥነት ነው የሚነሳው፤ እናቱ እስልኩ አጠገብ ተቀምጠው የሚጠብቁ ይመስለዋል። አሁን ግን ጥቂት ዘግየት አለበትና ልቡ ፈራ። ስልኩ ሊዘጋው ሲል ተነሳ፤ እናቱን አገኛቸው።

"ምነው እማ የት ሄድሽ" አላቸው እናቱን።

"ኧረ የትም አልሄድኩ ወደጓዳ ገባ ብዬ ነው" አሉት

"ፍሬ አለች?" አላቸው አስከትሎ

"የለችም፤ ጠዋት እንደወጣች ነው" አሉት

"አይይ!" አለ ሳያስበው።

"ምነው? ደህና አይደለህም እንዴ?" አሉት እናቱ ደንገጥ ብለው።

"እኔ ደህና ነኝ እርሷን ግን እንድትጠነቀቅ ንገሪያት" አላቸው።

የፈራቸውን ጥያቄዎች አልጠየቁትም "እሺ እስኪ" አሉ እናቱ።

ስልኩን ሲጨርስ ሀሳቡ ወደስብሰባው ሄደ። በስብሰባው ሊቀርቡ የሚችሉትን መረጃዎች አሰባቸው፤ መረጃዎች በሙሉ ተሰፋ

የሚያስቆርጡ ከሆኑ ሰንብተዋል፤ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሞቱ፤ ታሰሩ እና ጠፉ የተባሉትን አባላት ቁጥር ሲያስበው ልቡን ከበደው። ከአዲስ አበባ እንዲወጡ ሁኔታዎች እንዲመቻቹላቸው የሚቀርቡ አባላት ቁጥር ከአቅም በላይ ሆኗል። በየጊዜው ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገባቸው መሆኑ የሚነገራቸው አባላትም እንዲሁ ተበራክተዋል። እናም ማን ምን ሁኔታ እንደሚያጋጥመው ማወቅ አይቻልም፤ ሁሉም በተንጠንቀቅ መንቀሳቀስ ግድ ሆኖአል።

ስብሰባ ቦታ ሲደርስ ሂዋንና ሌላ አንድ ሰው ቀድመውታል። ሂዋን አንተነህ ጋር ባላት የቀረበ ግንኙነት ምክንያት በቅርብ ክትትል እንዲደረግባት ተወስኗል። ሂዋንም በተወሰነው ውሳኔ ደስተኛ አልነበረችም። ከበላይሁን ከተል ብሎ አንድ አባል ደረሰ። ስብሰባው ላይ መገኘት የነበረበት አንድ ሌላ ሰው ዘግይቷል፤ እናም በሁሉም አእምሮ ውስጥ ጥርጣሬ ተጫረ፤ ፈጠን ብለው ተነጋግረው ከዚያ ቦታ መሄድ ነበረባቸው።

ፈጣን የሆነ ስብሰባ አካሂደው፣ ሊያደርጉ የሚገባቸውን አድርገው፣ የሚቀጥለውን የስብሰባ ቦታና ጊዜ ወስነው ተለያዩ። በላይሁን ወደሚቀጥለው ቀጠሮው መሄድ ነበረበት፤ ግን የቀጠሮው ሰዓት ገና ነው። ጊዜውን የሚያሳልፍበት ነገር እያሰላሰለ እግሩ ወደመራው ተራመደ።

* * * *

ተስፋ መቁረጥ ቢከባትም፣ ሁሉን ነገር መጥላት ብትጀምርም ፍሬሕይወት ከቅዱስ ጋር ወደ አላት ተለዋጭ ቀጠሮ መሄድ አለባት:: በተሰበረ ልብ ብትሆንም በሰዓቱ ደረሰች፤ ቅዱስ ግን የለም:: ልቧ የበለጠ ፈራባት፤ የቅዱስን ደህንነት ተጠራጠረች:: አስር ደቂቃዎች አለፉ፤ ከዚያ በላይ ግን መቆየት አደገኛ ነው:: መንገድ ለውጣ ወደሰፈር ተመለሰች:: ገጽታዋ ተስፋ መቁረጧን የሚለፍፍ መሰላት:: ቅዱስ የት እንደደረሰና ምን እንደገጠመው አላወቀችም፤ በላይ እንደወጣ አልተመለሰም፤ አስቻለው ሞቶ አስከሬኑ እንኳ እንዳይነሳ ተከልክሎ ባሳደጉት ሰዎች ደጅ ለብዙ ሠዓታት መቆየቱን ስታስበው ይዘገንናታል :: የአስቻለው እናት ድቅን



አሉባት:: እንባዋን መቆጣጠር አቃታት:: በዚህ መሪር ሀዘን ወቅት አጠገባቸው ሆና ልታጽናናቸው ብትችል ምን ነበረበት::

ገና የግቢውን በር ስትገባ የበላይሁን እናት ጠሯት። "በላይ ደውሎ ነበር" አሏት አጠገባቸው ስትደርስ።

"ምን አለ?" አለቻቸው ቸኩል ብላ።
"ተጠንቀቂ በያት አለኝ" አሏት በቀስታ። ግራ ግብት እንዳላት ወደቤት ሄደች።

እንባዋ እንዲወርድና እፎይ እንድትል ፈለገች፤ ማልቀስ ግን አልቻለችም:: ሲያስቸግራት የነበረው እንባዋ የት እንደገባ አጣችው:: ሀሳቧ ሳታዘው ስለድርጅታዊ ሥራ ማተራመስ ገባ:: የሚከተለው ነገር ምን እንደሆነ ለመገመት የሚያዳግት ነው::

"ከዚህ በኋላ ከማን ጋር ነው የምሠራው? አብረውኝ ከነበሩ የኮሚቴ አባላት የቀረነው ሁለት ብቻ ነን፤ ከበላይ አካል ጋር የነበረን ግንኙነት መቋረጡ ነው…." ከራሷ ጋር እያወራች እናቷን ወደምታገኝበት ማድቤት ገባች። ከእናቷ ጋርም ብዙ አልቆየችም።

በጊዜ ነው የተኛችው፤ እንቅልፍ ሲወስዳት አልታወቃትም። ገና ሌሊቱ ሳይጋመስ ነቃች:: ሌሊቱ በጣም ረዘመ፤ የተለመደው የተኩስ ድምጽ ግን አይሰማም፤ ቅፍፍ ያለ የብቸኝነት ሌሊት ሆነባት:: ሊነጋጋ ሲል እንደገና እንቅልፍ ወሰዳት:: ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ላይ እናቷ ሲቀሰቅሷት በድንጋጤ ተነሳች::

"የሚፈልግሽ ልጅ አለ" አሏት እናቷ፤ እናቷም እንደእርሷው ተስፋ መቁረጣቸውንና መሰላቸታቸውን ድምጻቸው ይናገራል::

ልጁን ስታየው ክው ብላ ደነገጠች። የአንተነህ መላክተኛ ነው:: መልዕክቱን ነግሯት በጥድፊያ ተመልሶ ሄደ:: አንተነህን ለስንት ቀናት ሙሉ በሙሉ ከአእምሮው እንዳወጣችው ስታስበው ለራሷም ገረማት:: "ግን እንዴት ጨካኝ ነኝ?" አለች ለራሷ "ቁስሉ እንዴት ሆኖለት ይሆን?" ከቤት መውጣት መቻሉም ደነቃት ልታየው

ቸኮለች፡፡ ደግሞ ምንም ሳንቲም የላትም፤ እናቷን ጠየቀችና አስር ብር ሰጧት፡፡

"ደግሞ ወዴት ልትሄጂ ይሆን? መቼም አታርማችሁ" አሏት ብሩን እየሰጧት።

"አልቆይም እማ ቶሎ እመጣለሁ" አለችና ወጣች።

ብሔራዊ ትያትር አጠገብ ከታክሲ ወርዳ መለስ አለችና በብሄራዊ ባንክ አጠገብ ወደ ጎማ ቁጠባ ሚወስደውን መንገድ ያዘች፡፡ ልቧ ስትመታ ተሰማት፤ ጥቂት እንደተራመደች ቆም ብላ አካባቢውን ተመለከተች፤ እንደገና ራመድ ደግሞ መልከት አደረገች፡፡ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት አጠገብ ባለችው ጠባብ መንገድ አንተነህን ብቅ ሲል አየችው፡፡ ፍርሀቷ ሁሉ በአንድ ጊዜ ለቋት ደስታ በደስታ ሆነች፤ እንዴት እንደሮጠችና አጠገቡ እንደደረሰች አልታወቃትም፡፡ አጠገቡ ስትደርስ በእጁ ሲያመለክታት ነው ቁስሉን ያስታወሰችው፡፡

ከአንተነህ ጋር ተያይዘው ወደ ጎማ ቁጠባ አቅጣጫ ሄዱ፡፡ "ከሁሉ በፊት" አለና የሆነች ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ አስጨበጣት "ግንኙነት ተቋርጦብሻል አይደል?" አለና ጠየቃት፡፡ መቋረጡን ነገረችው፤ ድርጅታዊ አወቃቀሩንና የመረጃ ፍሰቱን እያደነቀች በሀሳብ ጥርግ አለች፡፡ ቅዱስ የሆነ ችግር እንደገጠመው ገባት።

"ፍርዬ በሀሳብሽም ቢሆን ትተሽኝ እንድትሄጂ አልፈቅድም" አለ አንተነህ በሀሳብ መመሰጧን ተመልክቶ።

"የትም አልሄድኩ፤ ምንስ መሄጃ አለኝ ብለህ ነው?" አለችው፡፡ በአንተነህም ገጽታ ላይ ርቆ የመሄድ መንፈስ እያየች ነው፡፡ ፊቱ እንደመገርጣት ብሏል ድካም ያለውም ይመስላል፡፡

"ሳይድንልህ ነው የተነሳኸው አይደል?" አለችው።

"ምን መዳን አለ ፍርዬ?..." አንጠልጥሎ ተወው፡፡ በውስጡ አንዳች ነገር እየተመላለሰ መሆኑ ይታወቃል። ግን ደግሞ አጥብቃ መጠየቅም



የለባትም፡፡ ልታውቀው የሚገባ ነገር ከሆነ እንደሚነግራት እርግጠኛ ነች፡፡

"ፍርዬ" አላት አንተነህ ሳታስበው።

"አቤት አንተነህ" አለች በፍጥነት።

"አንድ ቦታ ብንቀመጥስ?" አለ ሀሳቡ ግን አሁንም ርቆ እንደተጓዘ ነው፡፡ ሰዓቷን ተመለከተች እናቷ የቱን ያህል እንደሚሰጉ አሰበችና አቅማማች፡፡

"በቃ እንዳውም እሺ በይኝና ነገ አብረን እንደር" አላት ማቅማማቷን ተመልክቶ፡፡ ድንግጥ አለች።
አልመለሰችለትም በሰንጋ ተራ በኩል ወደተግባረ ዕድ የሚወስደውን መንገድ ይዘው በፀጥታ ተጓዙ፡፡ አገሩ የተወረረ ይመስላል፡፡ እነርሱንም ዝምታው ተጋብቶባቸው ዝም ብለዋል፡፡ አንተነህ ቆም አለና ትኩር ብሎ አያት፡፡ ብቻ የሆነ ነገር እንደሚያስጨንቀው ማወቅ ቀላል ነው፡፡

"የተለየ ያስጨነቀህ ነገር አለ እንዴ ጨነቀኸኮ አንተነህ?" አለችው።

"ምን የማይጨንቅ ነገር አለ ፍርዬ ለማንኛውም አሁን ወደቤት ሂጂ፤ የነገ ማታውን እሺ እንደምትይኝ በማመን..." አሁንም ትኩር ብሎ ተመለከታት፡፡ ምንም አላቅማማችም ተስማማችለት፡፡ በአንድ እጁ በስስት አቀፈና ሳማት፡፡

"በጣም እወድሻለሁ ፍርዬ እንዳጣሽ አልፈልግም" አላት በጆሮዋ፡፡ ለአንተነህ ልቧ ደማችለት፤ ልትገታው የማትችለው ሀዘን ልቧ ውስጥ ገባ፡፡

"ነገ መገናኘት ይኖርብናል፡፡ መነገር የሚችል ከሆነ እንድትነግረኝና ጭንቀትህን እንድካፈልህ እፈልጋለሁ፡፡ በጣም እወድሃለሁ" አለችው እርሷም።

"ተጠንቀቂ" አላት በመጨረሻ ሲሰነባበቱ፡፡ ግራ ግብት እንዳላት ወደቤቷ ተመለሰች፡፡ አንተነህ ለምንም ነገር የማይሰጋ የሚመጣው ነገር ሁሉ ቢመጣ ጭንቅ የሌለው ዓይነት ሆነባት፡፡ ያልዳነ የጥይት ቁስል ይዞ ራሱን ለመደበቅም ብዙ ጥረት ሳያደርግ በእግራቸው ያን ያህል መጓዛቸው ለፍሬሕይወት እንቆቅልሽ ሆነባት፡፡ ለማንኛውም ምንም ሳያጋጥማቸው በመቅረቱ ደስ ብሏታል፤ በሰላም እንዲገባም ተመኘችለት፡፡

* * * *

እንቅስቃሴያቸው ሁሉ የወትሮው ፍጥነት ተለይቶታል፤ ቀስ በቀስ ሞራላቸው እየወረደ መጥቷል። ፍሬሕይወት ብዙ ቀጠሮዎች አልነበሯትም፤ በጊዜ እቤት ገብታ ከእናቷ ጋር ሥራ መሥራት ጀመረች። ወደአመሻሹ ላይ በላይሁን ስልክ ደውሎ ጥሩ ሁኔታ ውስጥ ያለመሆኑን ነገራትና "ነገ በጠዋት እማማ የምትሰጥሽን ገንዘብ ይዘሽልኝ ነይ" አላት። ስሜቷ የበለጠ ተመሰቃቀለባት።

ነገ የራሱን ምስቅልቅል አስከትሎ ዛሬ ሆነ፡፡ በላይሁን የቀጠራት ቦታ ሄዳ ገንዘቡን ሰጠችው። "እባክሽን ተጠንቀቂ ፍሬ" አላት በላይሁን እንደተገናኙ። ፍሬሕይወት አንተነህ በሰጣት ኮድ የምታገኘውን ሰው ለማግኘት ሰዓት እንዳያልፍባት ከበላይሁን ጋር አብረው መቆየት አልቻሉም፡፡ "በተቻለህ ሁሉ ራስህን ጠብቅ" አለችው እርሷም ስትለየው።

ቀጠሮዋ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ አለባበሱም ቦታውን እንዲመስል ተደርጓል፡፡ ጥቁር ጥለት ነጠላዋን ንጥል አድርጋ ለብሳና ጥቁር ሻሽ ሸብ አድርጋ የሰኔ ጎልጎታዋን ገልጣ ከቤተክርስቲያኑ በር በስተቀኝ ካለው ስዕል ፊት ተቀመጠች፡፡ ወዲያውኑ ሰፋ ያለ ኮት የለበሰና ካኪ ሱሪ ያደረገ ሰው ኬፑን አውልቆ ሁለት ጊዜ ተሳለመና ወደእርሷ ዞረ።

"ምልክስናሽ ዛሬ ነው?" አላት ከስተር ብሎ።

"እረ ጋብቻዬ ነው" አለች።



ሰውዬው አጠገቧ ተቀመጠ፡፡ ዳኙ ይባላል። ከፍሬሕይወት ጋር ለተወሰኑ ደቂቃዎች ተነጋሩ፤ ንግግራቸው ሁሉ አስጨናቂ ነበር፡፡ በፓርቲው ውስጥ ስለተፈጠረው ክፍፍል ጠቅለል አድርጎ አስረዳት። በፓርቲው የበላይ አካላት መሀል የፖለቲካ መስመር ልዩነት ተፈጥሮ አንደኛው ክፍል አፈንግጦ መውጣቱንና ጉዳዩ ግን ለጊዜው ከዚህ ኮሚቴ በታች መውረድ እንደሌለበትና ይህን በተመለከተ የሚነበብ ጽሑፍ እንደሚሰጣት ነገራት፡፡ እርሱ እየነገራት ሀሳቧ በሙሉ አንተነህ ጋ ሄደ፡፡ አንተነህን ምን እንዳስጨነቀው ገባት፡፡

"እንቅስቃሴያችን ሁሉ እጅግ ከፍ ባለ ጥንቃቄ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከእንግዲህ ያለው ትግል ከውጭ ጠላት ብቻ ሳይሆን ውስጣችንን አሳምረው ከሚያውቁ የውስጥ ጠላቶችም ጭምር ነው፡፡ ይህንን የሚስጥር መገናኛ ካመጣልሽ ሰው ጋርም ከእንግዲህ ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዲኖርሽ አያስፈልግም..." እስኪጨርሰው ልታዳምጠው አልቻለችም፡፡ ምድርና ሰማዩ ዞረባት፡፡ ብቻ እንደምንም ብላ ስምምነቷን በራሷ ንቅናቄ ለመግለጽ ሞከረች፡፡

የቀጠሮ ሰዓት ተነጋገሩ፡፡ የቤተክርስቲያኑን የበረንዳ ምሰሶ ተገን አድርጎ የሚነበበውን ጽሑፍ አቀበላት፡፡ የጎደለውን የኮሚቴ ቁጥር ለማሟላት እንድትችል የመገናኛ ኮድ ሰጣት፡፡ በድጋሚ "ተጠንቀቂ" አላትና ሄደ፡፡

የሰማችውን ማመንና መቀበል በፍጹም የሚሆን አይደለም፡፡ ሀሳቧ ተመሰቃቀለባት፤ አካሏም የዛለ መሰላት፡፡ አቅም እንደከዳት እመበለት ከተቀመጠችበት በግድ ነው የተነሳችው፡፡ እንደአነሳሷ በቀስታ ወደቤቷ አመራች፡፡ ጽሑፉን ለማንበብ ቸኩላለች፡፡ አንተነህንም ከአእምሮዋ ልታወጣው አልቻለችም። አካባቢዋን በጥንቃቄ መከታተል እንዳለባት በፍጹም ዘንግታለች፡፡ የአፍሪካ አዳራሽን በር አለፍ ብላ ገና አቀበቱን ስትያያዝ ከፊት ለፊቷ እነዛ መከረኛ ወታደሮች ፊስሰዋል፡፡ አእምሮዋ ከምን ጊዜው እንዳሰበው ሳታውቀው ትንፋሿን ዋጥ አድርጋ ሆዷን ነፋችው፡፡ ቀድሞ ወታደሮቹ መኖራቸውን እንዳልተገነዘበች ዓይነት ግንባሯን ቁጥር አድርጋና ፊቷን ከሶ አስመስላ በመሀላቸው ሄደች፡፡

"ስሚ! ወዴት ነው? ቁሚ!" አላት አንዱ ወታደር።

"የቱ ጋ ልቀመጥ?" አለችው አጠገቧ ያገኘችውን ሌላ ወታደር።

"ዝም ብለሽ ሂጂ" አላትና "ትለፍ ነፍሰ ጡር ነች" አለው እንድትቆም ላዘዛት ወታደር፡፡ እየተያዙ ወደመኪና ላይ የሚወረወሩትን ወጣቶች በቀስታ እያየች በትርምሱ ውስጥ አልፋ ሄደች፡፡

ነፍሷ እንደተጨነቀች መሸ። እነዛን እንደእግዚአብሔር ታያቸው የነበሩትን ሰዎች ስታስባቸው፣ በእነርሱ መሀል እንዲህ ዓይነት መከፋፈል ይፈጠራል ብላ መቀበል አቃታት። መሠረታዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የጠበቀ ትስስር ያላቸው ሰዎች ያን መሰሠረታዊ ዓላማ ለማስፈጸም መከተል በሚገባቸው ስልት ላይ መግባባት አቅቷቸው ድርጅቱን አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ ይከፋፈላሉ ብላ ለመገመት ተቸገረች።

ራስ ምታት ሲፈልጣት አድሮ ዓለም ዝብርቅርቅ ብሎባታል፡፡ ሁኔታዋን ማንም ተመልክቶ ጥሩ ስሜት እንደሌላት ለማወቅ አይቸገርም፡፡ እናቷም ጠየቋት፡፡ የምትወዳት የትምህርት ቤት ጓደኛዋ መሞቷን እንደሰማች ነገረቻቸውና አብረዋት አዘኑ፡፡ ከቤት ሳትወጣ ዋለችና ወደማታ ሄዳ ለቅሶ እንድትደርስ አስፈቀደች፡፡ ከራሷ ጋር ስትሟገት ሀያ አራት ሰዓት ሊሞላት ቢሆንም ጥርት ያለ አቋም ልትይዝ አልቻለችም፡፡ ከአንተነህ ጋር መገናኘት እንዳለባቸው ብታምንም ስለሰማችው ነገር ከእርሱ ጋር በመነጋገርና ባለመነጋገር መሀል ተወጥራ ነው አድራ የዋለችው፡፡ በመጨረሻውም ሰዓት ቢሆን አንተነህን ልትዘጋው እንደማይገባት ነፍሷ ነገረቻት፡፡

በአስራ ሁለት ሰዓት ከአንተነህ ጋር የተገናኙት መርካቶ ልደት ኬክ ቤት ነው፡፡ አንተነህ ትናንት ከነበረበት ሁኔታ ብሶበት እንደሆነ እንጂ አልተሻለውም፡፡ በማንኛም ደቂቃ የከፋ ነገር ሊደርስ እንደሚችል ነው ስሜቷ የሚያንሾካሾክላት፡፡ ከሁሉም በላይ ሰላሟን ያሳጣት በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረው መከፋፈል ነው፡፡ መተማመን በሌለበት ጥርጣሬ ጉልበት ያበጃል፣ መጠራጠር ደግሞ ኃይልን ይሸረሽራል፡፡ እርምጃቸው ሁሉ ወደሞት የሚጣደፍ ሆኖ ተሰማት፡፡



ከአንተነህ ጋር ሲጫወቱ ወትሮ የነበረው ጣዕም አልነበረም፡፡ ጥቂት ደቂቃዎች ቆይተው ወጡ፣ ወዴት እንደሚሄዱ ባታውቅም አንተነህን ተከተለችው፡፡ ወደራጉኤል መንገድ ሄዱ፣ ወደፒያሳ የሚሄደው ዋናው አስፋልት ላይ ሲደርሱ ቆሙና ታክሲ ያዙ፡፡ አራት ኪሎ ከታክሲ ሲወርዱ ለዓይን ያዝ አድርጓል፡፡ በአራት ኪሎ መንደሮች መሀል ባሉ ጨለማ መንገዶች ውስጥ ለውስጥ ሄዱ፡፡ ከተያያዙትና ጭንቅንቅ ካሉት ትናንሽ ሱቆች በስተጀርባ በጠባብ መንገድ አልፈው አንድ ግቢ በር ላይ ቆም አሉ። አንተነህ አካባቢውን ቃኘት እያደረገና እጁን አሾልኮ የውጭውን በር ከፈተው፡፡ ግቢው ጨለማ ነው፣ በቤቱ ጥግ አድርገው ወደውስጥ ዘለቁ፡፡ አቤት ጉራንጉር! ገና ቤቱ ጋ አልደረሱም። እንደገና ሌላ ግቢ መሰል ነገር አለፉና ወደውስጥ ገቡ፡፡ ጭርንቁስ ቤት ነው ፡፡ አንተነህ መክፈቻ አወጣና በሩን ከፈተ፡፡ ሁሉ ነገር የሚከናወነው በጸጥታ ነው ተከትላው እንደገባች በሩን ዘጋና ቆለፈው፡፡ ጨለማው ዐይን ቢወጉ አይታይም፣ ግትር እንዳለች ቀረች፡፡ አንተነህ በዳበሳ መብራቱን አበራው፡፡ ውስጡ ከውጭው የባሰ አስቀያሚ ክፍል ነው፣ አስጠላት፡፡ ግድግዳና ጣሪያውን ተዟዙራ ተመለከተችው፣ አንድ እንኳን ፈካ ያለ ነገር አይታይበትም፡፡ ጎንበስ ብላ የረገጠችውን መሬት አየችው፣ አፈር ነው፡፡ ሁሉም ነገር ቀፈፋት፡፡ ከፊታቸው ሲታዩ የሚብለጨለጩትን ሱቆች ታዘበቻቸው፡፡

አንተነህ ከግድግዳው ምንም የማትለይ አጭር በር ገፋ አደረጎ ከፈተና "የተሻለ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ" አላት ሁኔታዋን የታዘበ በሚመስል አነጋገር፡፡ በሀሳቧ አንተነህን ባለፈው ያገኘችበትን ሁኔታና የአሁኑን እያነጻጸረች ነበርና ለዓላማ ሲባል ሁሉንም መሆን እንደሚቻል ለራሷ አረጋገጠች፡፡

ወደክፍሉ ውስጥ ለመግባት ጎንበስ ማለት ነበረባት። በመጠኑ ሻል ያለ ክፍል ነው፡፡ በክፍሉ አንድ ጥግ ፍራሽ ተዘርግቷል፣ ብርድልብስም ተነጥፎበታል፡፡ ከፍራሹ አጠገብ አንድ ወንበር አለ፡፡ በሌላው ግድግዳ ጥግ ደግሞ አነስ ያለች ጠረጴዛ አለች፣ ጠረጴዛው ላይ የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች ተደርድረዋል፡፡

"እስከአሁን ቆመሻል እንዴ?" አላት አንተነህ የወዲያኛውን ክፍል መብራት አጥፍቶ ሲመለስ፡፡

ከፍራሹ ዳር ላይ ተቀመጠች፤ በጣም ይቀዘቅዛል እግሯን ሰብስባ ኩርትም አለች፡፡ አንተነህ ከትንሽ ሻንጣ ውስጥ ጋቢ አውጥቶ አለበሳት፡፡ ጋቢውን ሲደርብላት ቅዱስን አስታወሰችው፡፡ የት ደርሶ ይሆን? ሞቶ ይሆን ወይንስ ወደአንዱ እስር ቤት ተጥሎ ይሆን? መንፈሷ ተረበሸ። ቅዱስን ስታስብ አሁን በፓርቲው ውስጥ እየተከሰተ ያለው ሁኔታ ተደቀነባት... አቤት የሀሳቧ ያለማለቅ!

"አትኮብልይ አላልኩሽም አንቺ ልጅ?" አላት አንተነህ ጃኬቱን አውልቆ ፍራሹ ላይ እየወረወረው፡፡

"አልኮበለልኩም" አለችው። ወዲያውኑ ደግሞ አእምሮዋ ወደሌላ ሀሳብ ሄደባት፤ ወደአንተነህ። "መቼ ይሆን ቤተሰቦቹ ጋ ሄዶ የሚያውቀው?" የሚል ጥያቄ በአእምሮዋ እየተመላለሰ ቤተሰቦቹን አሰበቻቸው። "እነርሱስ ምን ያስቡ ይሆን?" አለች ደግሞ፤ በጣም ገረማት፡፡

"አንተነህ" ብላ ተጣራች ድንገት።

"እመት" አላት ሸሚዙን እየጠቀለለ።

"ምን ልታደርግ ነው?" አለች ስለቤተሰቦቹ ልትጠይቀው ያሰበችውን ትታ።

"እንዴት ዓይነት እራት እንደማበላሽ አታውቂም" አላት ጥግ ላይ ወዳለችው ጠረጴዛ እየሄደ።

"እባክህ ተወው ይቅርብን፤ ባንበላስ?" አለችው።

"አጋጣሚው ሲገኝ መብላት ነው፤ ፆም ማደሩማ የተለመደ ሆኗል" አለና ማቀራረብ ጀመረ።

ሥራውን ልትረዳው ጋቢዋን አስቀመጠችና ተነሳች፤ አልፈቀደላትም። እርሷም አልተቀበለችውም፤ ልታግዘው አጠገቡ ሆነች።

"እባክሽን ትዝታዬን እፈልገዋለሁ" አላት።



"ለትዝታውማ አብረን ሠርተን መመገባችን የበለጠ አይሆንም?" አለችው። ተስማማ። ራታቸውን አብረው ሠርተው አብረው በሉ።

የመብላት ፍላጎት ባይኖራትም በጉርሻ ኃይል በላች፤ ቆንጆ እራት ነበር። የተመገቡባቸውን ዕቃዎች ፍሬሕይወት ስታጣጥብ እርሱ ሻይ አፈላ። ደስ እያላቸው ሻያቸውን ጠጥተው ጨረሱና ፍራሻቸው ላይ ተቀመጡ።

"ሌላ ትዝታ እፈልጋለሁ" አላት አንተነህ።

"እንደእውነቱ ከሆነ ትዝታችን ተቆንጥሮ አያልቅም" አለችው ሩቅ እያሰበች።

"እውነት ነው! ዴሞክራሲያን ማንበብ ያስጀመርኩሽ እኔ ነበርኩ። ምናልባትም ለኔ የመጨረሻ የሆነውን እትም አብረን ብናነበው ደስ ይለኛል" አለ አንተነህ። እንባው እየተናነቀው እንደሆነ ገብቷታል። እንዲያለቅስ ግን በፍጹም አትፈልግም።

"ደስ ይለኛል! ነገር ግን በለቅሶ እንድንለያይ አልፈልግም" አለችው ፍርጥም ብላ።

ድምጹን ዝቅ አድርጎ የዴሞክራሲያን ልዩ እትም ማንበብ ጀመረ። የምትወደውን ድምጹን እየሰማች ወደእንቅልፍ ዓለም ብትገባ ወደደች። ዐይኖቿን ገርብብ አድርጋ ጆሮዎቿን አሰላች።

"ዛሬ እንቅልፍ የለም" አለና አንገቷ ስር ሳማት።

"በፍጹም አልተኛም! ድምጽህ እያባበለ ሲያስተኛኝ የሚሰማኝን ስሜት ማወቅ ግን ተመኘሁ" አለችው።

የቀረችውን ጥቂት ጽሑፍ አነበበና ጨረሰላት። "ምን እንዳሰብኩ ልንገርህ?" አለችው ጋዜጣውን አጣጥፎ ሲያስቀምጥ።

"እስኪ ንገሪኝ" አላት በጉጉት።

"እኔንና አንተን ከሚለያየን ምነው የትግሉ መጨረሻ ዛሬ በሆነ ብዬ አሰብኩ" አለችው።

"ፍርዬ! ምነው ለዛሬ ፍቅራችንን ቀምቶን ሕይወታችንን ባቆየልን። በሕይወት ከቆየን ስንገናኝ ፍቅራችንን መቀጠል እንድንችል" አላትና ፊቱን በእጆቹ ሸፍኖ እጉልበቷ ላይ ተደገፈ።

"በቃ ይሆናል ብለን እንመኝ" አለችና ቀና አደረገችው።

አንተነህ ከፍራሹ አጠገብ ያለ ትንሽ ቴፕ አነሳና ድምጹን ዝቅ አድርጎ ከፈተው፤ ግጥም ነበር፡፡ ኃይለኛ ግጥም!

ግጥሙ ወኔን የሚቀሰቅስ፣ ልብ የሚሞላ ነው፡፡ የግጥሙ ይዘትና የአንባቢው ድምጽ ውህደት ልዩ ነው። ልክ እንደ አንተነህ ድምጽ ተአምራዊ ኃይል ያለው ወፍራምና ዘለግ ያለ ድምፅ! ሁለቱም በየሀሳባቸው ተውጠው ግጥሙ ማለቁን እንኳ አላስተዋሉም።

"ወዴት ሄድሽ" አለ አንተነህ ቀድሞ ከሀሳቡ ተመልሶ።

"የትም አልሄድኩም፤ ግን ሁኔታው የሚቀየር ይመስልሀል?" አለችው።

"ተስፋ አንቆርጥም" አላት አንተነህ። የወትሮው ሙሉ እምነት ግን በድምጹ ውስጥ የለም።

እንደገና ዝምታ ሆነ፤ ከቅዝቃዜው ጋር ተዳምሮ አጥንት የሚሰብር ማለቂያ የሌለው ዝምታ! እንዴት ይቀፋል፡፡ ከውሾቹ ጩኸትና አልፎ አልፎ ከሚሰማው የመኪናና የጥይት ድምጽ በስተቀር ሌላ ድምጽ የለም።

"ፍርዬ" አለ አንተነህ ድንገት ዝምታውን ሰብሮ፡፡ ቀና ብላ አየችው፤ ከብ ዐይኖቹ ቅዝዝ ብለዋል፡፡ እንደምንም ብሎ ፈገግ አለና እነዛን ችምችም ያሉ ጥርሶቹን አሳየት እርሷም ፈገግ ለማለት ሞከረች።



"እንግዲህ መለያየታችን ነው" አለና ፈገግታዋን በአጭሩ አስቀረው። መለያየት የሚለው ቃል እጅግ በጣም ቢያስደነግጣትም ምን እንደምትለው ግን ግራ ገባት፡፡ በርካታ ጥያቄዎች በአእምሮዋ ውስጥ ተመላለሱ፤ የትኛውን ትጠይቀው?

"ግራ ገብቶሻል አይደል?" አላት ውስጧን ያወቀባት ይመስል።

"አዎን ግራ ገብቶኛል" አለችው።

"በማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ሊከሰት የሚችል ቢሆንም እኛ አሁን ላለንበት ሁኔታ ግን በጣም አስጊ ነው..."

"ታዲያ ለምን ይህንን አስቦ ለመፍታት አልተሞከረም..." አቋረጣት።

"በቃ ይህንን እዚህ ልንነጋገርበት አያስፈልግም አንድ ነገር ብቻ ግልጽ እንዲሆንልሽ እፈልጋለሁ። ድርጅቴን ከራሴም አስበልጨ የምወድ መሆኔን! የማደርገውን ሁሉ የማደርገው ለዓላማና ለድርጅት ስል እንደሆነ እንድትረጅልኝ ብቻ! ሊፈጠር የሚችለው ክፉ ነገር ሲፈጠር ግን እዚህ ሆኜ ማየት አልፈልግም..." ድምጹ ተርገበገበና ንግግሩን አቋረጠው።

"ታዲያ ምን ልታደርግ አስበህ ነው?"

"መለያየታችን ለዚህ መሆኑ አይደል"

"የት ትሄዳለህ?"

"ፍርዬ ይህን አትጠይቂኝ፡፡ እኔም የት እንደምሄድ አላውቀውም" አላት ከልቡ መሆኑን በሚገልጽ ቅላጼ። ከዚያ የበለጠ ውይይት የመቀጠል አቅም አልነበራቸውም፡፡ አቀርቅራ ዝም አለች። በውስጧ ግን የአንተነህን ስብእና አደነቀች።

"አንድ ነገር ቃል ትገቢልኛለሽ" አላት ደግሞ ከጥቂት ዝምታ በኋላ።

"ምን ቃል ልግባልህ አንተነህ?" አለችው።

"እስከመጨረሻው ይቅር እንድትይኝ"

"ምን አድርገሽኝ ይቅር..." አቋረጣት።

"ምን ያላደረግሁሽ አለኝ ፍርዬ፤ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ በፀፀት ስገረፍ እንደምኖር አውቀሽ ይቅር እንድትይኝ ነው የምጠይቅሽ። ሊጀመር የማይገባው ፍቅር ጀምሬ አሰቃየሁሽ፣ ለህሜት አጋለጥኩሽ..." ቀና ብላ ተመለከተችው። ካየችው ጊዜ ጀምሮ እንደዚያ ያለ ስሜት አይታበት አታውቅም። በጣም አሳዘናት።

"እሺ አንተን ካስደሰተህ ይቅር እልሃለሁ" አለችው በውስጧ ግን ሁሉም ነገር  ዝብርቅርቅ ብሎባታል።

"ፍርዬ እስኪ ምንም እንዳልተፈጠረ እናስብና ደስ ይበለን" አለና አቀፋት። ግን በፍጹም የሚሆን አልነበረም። "ማን ያውቃል ፍርዬ ልንገናኝ እንችል ይሆናል" አላት ደግሞ። ግራ ግብት እንዳለው ያስታውቃል። በአብሮነታቸው ይሰማቸው የነበረው ያ ሁሉ ደስታ ጠፍቶ ባዶነት ከበባቸው፡፡ የነገን መለየት እያሰቡ በዛሬ አብሮነታቸው መደሰት አቃታቸው፡፡ በሁለቱም ልቦች ውስጥ ያለው ግን አንድ ነገር ነው። ከግል ሕይወታቸው ለሚበልጠው ዓላማ ፍቅራቸውን መስዋዕት የማድረጋቸው ውሳኔ።

"አብሬው ብሔድስ" ድንገት ወደአእምሮዋ የመጣ ሀሳብ ነው። ሀሳቡ ራሷኑ በጣም አስደነገጣት፤ በተቻለ ፍጥነት ሀሳቡን አባረረችው፡፡ ምሽታቸው የተመሰቃቀለ ነበር፡፡ አንተነህ አንድ ጊዜ እንዳለው ፍሬሕይወትም በዚያች ደቂቃ እርግጠኛ ልትሆን የቻለችው በአንድ ነገር ብቻ ነው፤ አንተነህን በጣም እንደምትወደው!!

እንቅልፍ ምን ጊዜ እንደወሰዳት አላወቀችም፤ ጠዋት ግን ቀድማ የነቃችው እርሷ ነች፤ ከአንተነህ አንገት ስር ሽጉጥ እንዳለች ነው የባነነችው። ቀስቀስ ስትል አንተነህ በእንቅልፍ ልቡ ጥብቅ አድርጎ አቀፋት። ትኩር ብላ ተመለከተችው። በእርግጥ እንዲህ ያለ ታማኝነት ሁሉም ወንዶች ይኖራቸው ይሆን? አድናቆቷን ልትገልጽለት ፈለገችና በቀስታ ጉንጩን ሳመችው።



ሰዓቱ ለአንድ ሰዓት አሥራ አምስት ደቂቃዎች ብቻ መቅረታቸውን ያመለክታል፡፡ አንተነህን በመቀስቀስና ባለመቀስቀስ መሀል ሆና እርሱ ድንገት ነቃ፤ ሰዓቱን ነገረችው።

"እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ መቆየት እንችላለን" አለና ወደደረቱ አስጠግቶ አስተኛት፡፡ የመጨረሻዋ ሰዓት ግን ፈጥና ደረሰችና መለየት ግድ ሆነ። ተነስተው ተጣጠቡና ለመውጣት ዝግጁ ሆኑ።

"ምንም እንዳይነካሽ ምኞቴ ነው" አለና ለመጨረሻው ስንብት አቀፋት "ፍርዬ ዳግም እንደምንገናኝ ተስፋ እናድርግ" አላት።

"በፍጹም ተለያይተን እንድንቀር አልፈልግም" አለችው ሳታስበው እንባዋ እየተናነቃት፡፡ አንተነህ በግድ ይዞት የነበረው እንባ ገንፍሎ ወረደ፤ ለደቂቃዎች ተቃቅፈው ተላቀሱ።

"ፍርዬ በውስጤ ይገኛል እኖራለሁ፡፡ እስከ ዘለዓለምም ቢሆን" አላት አንተነህ በስቅስቅታ በሚቆራረጠው ድምጹ። የፊት ለፊቱ በር ሲከፈት የቁልፉ ድምጽ ተሰማቸው፡፡ እናም የመጨረሻዋ ሰዓት ሆነች፡፡

"የገባንበትን መንገድ ታስታውሽዋለሽ አይደል?" አላት አንተነህ እየተርበተበተ ልትመልስ የቻለችው በአንገቷ ምልክት ነበር። መቋቋም የምትችለው አልነበረም፡፡ ቀና ብላም ልታየው የምትችልበት አቅም አልነበራትም። ፊቷን አዞረችና ወደገቡበት በር ተራመደች። በሩን ከመክፈቷ በፊት አንተነህ  ከፊቷ ቀደመና ቆመ።

"ፍርዬ በጥንካሬሽ ሁሉንም እንደምታልፊ አምናለሁ፡፡ እባክሽን ይህንኑ አረጋግጭልኝና የልቤን ስቃይ ቀንሽልኝ" አላት አንተነህ በተረበሸ ሁኔታ።

አንተነህን ለማረጋጋት የምትችል ከሆነ ሌላም ነገር ብትጠየቅ የማትችለው ነገር እንደሌለ ተሰማት። እናም ቀና ብላ ተመለከተችው፡፡ እንባዋን ልትገታው ባትችልም ፈገግ ለማለት ሞከረች፤ ተሳካላት። አንተነህም ያንን የምትወደውን ፈገግታውን

አሳያት፡፡ ለመጨረሻ ጊዜ ተቃቀፉና ተሰነባበቱ፡፡ ከዛ በኋላ ዞር ብላ ልታየው አልደፈረችም፤ በመጡበት መንገድ ለብቻዋ ተመለሰች።

* * * *

ግቢው ጸጥ ረጭ ብሏል፤ ወይዘሮ ስርጉት መንፈሳቸው እንደተረበሸ ነው የዋሉት፤ ሥራ መሥራት እንኳ አልሆን ብሏቸው ሲወጡ ሲገቡ ቆዩና አልጋቸው ላይ ጋደም አሉ። በፍጹም የሚያርፍ ስሜት የላቸውም፤ እንደገና ተነሱና አገልግላቸውን አንስተው ወደበረንዳው ወጡ። ጥጡን በደመነፍስ ከአገልግሉ ያወጡና አረጋግፈው እክዳኑ ላይ ያስቀምጣሉ። አገልግሉ ውስጥ ያለው ጥሬ ጥጥ ሲያልቅባቸው ደግሞ መፈልቀቅ ጀመሩ።

እጆቻቸው ቢንቀሳቀሱም አእምሮአቸው ግን ከሚሠሩት ሥራ ጋር አይደለም። ሚሚን ከሀሳባቸው ማውጣት አልሆነላቸውም፤ ሁሌም በዐይነህሊናቸው የሚመለከቷት ተርባ፣ ደክሚት፣ የተቦጫጨቀ ልብስ ለብሳ... አንዳንዴ ደግሞ ወድቃ ነው። ሚሚና አብረዋት ያሉ ወጣቶች በየጫካውና በየተራራው የሚሄዱ ይመስላቸዋል። ሁሌም ከአቅሚ በላይ የሆነ ነገር ተሸክማ አደናቅፏት የምትወድቅ፤ ጓደኞቿም ሳያዩዋት ትተዋት የሚሄዱ ይመስላቸውና “ልጄን!” ይላሉ ሳያስቡት። አሁንም እዚያው ስሜት ውስጥ ገብተው “ልጄን!” ብለው ጥጡን ወርውረው ተነሱ የፍሬሕይወት እናት። በሀሳባቸው መሆኑን ሲያስታውሱ ደግሞ፡

“በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ” አሉና አማትበው ተቀመጡ፤ እንደገና ጥጣቸውን አነሱ።

ስሜታቸውን ግን ሊቆጣጠሩት አልቻሉም፤ ከወትሮው በተለየ ተረበሹ። እንባቸው የሚፈለቅቁት ጥጥ ላይ ሲንጠባጠብ ጥጡን ወርውረው ወደቤት ገቡና ተንበርክከው ተንሰቅስቀው አለቀሱ።

“ለማንኛቸው ነው የሚለቀሰው?” አሉ ለራሳቸው። ቃለአብ እቤቴ ገብቶ ካደረ ሰንብቷል፤ ከሚሚ የሚለየው አልፎ አልፎ ስልክ ደውሉ



መኖሩን መናገሩ ነው። ፍሬሕይወትም እውጭ ማደር ከጀመረች ሰንብታለች።

"... ከድሉ በኋላ..." የሚለው የቃለአብ ድምጽ ተሰማቸው።

"ምነው ድሉ ቀርቶ፤ ሁሉም ነገር ውድም ብሎ እነርሱ በደህናቸው ወደቤታቸው በተመለሱ! ኧረ ወላዲተ አምላክ ተለመኚ!" አሉና እንደገና መንሰቅሰቅ ጀመሩ። ልጆቻቸው የት ይደርሳሉ ብለው ይጠብቁ እንደነበርና አሁን ደግሞ እየሆነ ያለውን ሲያስቡት ሁሌም ይደንቃቸዋል። ምነው የተመኙት ሁሉ በቀረና ልጆቻቸው በሕይወት በቆዩላቸው፤ ክፉ ነገር ባላጋጠማቸው። ወደጣሪያው አንጋጠው ለስንተኛ ጊዜ መሆኑን ባያውቁትም ለልጆቻቸው በሕይወት መቆየት እየጸለዩ እስኪደክማቸው አለቀሱ፤ በልቅሶአቸው መሀል ደግሞ፡

"ፈጣሪዬ!እውነት ይህ ነገር ሁሉ አልፎ ልናወራው እንበቃ ይሆን?" አሉ። ከዚያ ደግሞ ተነሱና በጓሮው በር ወጥተው ቀዝቃዛ ውሀ እፊታቸው ላይ አፍስሰው መለስ አሉ።

"እማ! ማንም የለም" እንዴ?" እያለ ሮቤል ቦርሳውን እወንበር ላይ ወርውሮ ወደውስጥ ገባ።

"አለሁ! የት እሄዳለሁ?" አሉት እናቱ ፊታቸውን በነጠላቸው ጫፍ እየጠራረጉ።

"እማ! አልቅሰሻል አይደል?" አላቸው፤ ሽቅብ እየተመለከታቸው።

ዘሃ" አሉትና ተመልሰው ወደጓዳቸው ገቡ፤ ሮቤል ተከተላቸው። "እማ! ግን እኮ እኔም አንዳንዴ ማልቀስ ያምረኛል" አላቸው በሚያሳዝን ድምጽ።

"ምን በወጣህ ሮቤልዬ! የምን ማልቀስ ነው ደግሞ" አሉት ፊቱን ላለማየት እየሞከሩ።

"እኔ እንጃ! ሚሚ ስለጠፋች፣ ፍሬና ቃለአብም ሁል ጊዜ እቤት ባለመኖራቸው፤ ደግሞ እኮ ትምህርት ቤትም ሁሉም ልጆች ያወራሉ፤ ሁላችንም እናዝናለን..."

"በቃ ሮቢ! እናንተ ገና ልጆች ናችሁ፤ ስለዚህ ማሰብ አያስፈልጋችሁም። እንካ መክሰስህን ብላ ይልቅ" አሉት አንጀታቸው እየተላወሰ።

ሮቤል ተቀብሏቸው ወደሳሎን ሄደ፤ እርሳቸው እንደገና እንባቸውን አወረዱት። ድንገት ጩኸት ተሰማቸውና በድንጋጤ እንባቸውን ጠራርገው ወጡ። ጩኸቱ የሚሰማው ከነበላይሁን ቤት ነው፤ ወይዘሮ ስርጉት ወደዚያው ሮጡ።

እነበላይሁን ቤት ሲገቡ ማንን ሊጠይቁ እንደሚችሉ ጨነቃቸው፤ ብቻ "ምንድነው? ምን ተፈጠረ?" እያሉ ጮሁ።

"ጉድ ሆንኩልሽ ስርጉት፤ ልጄን ተነጠቅሁ! ልጄን እንደፈራሁት አሰሩት" አሉ የበላይሁን እናት። ወይዘሮ ስርጉት ሌላ ጥያቄ አላስፈለጋቸውም። እርሳቸውም እሪታቸውን ቀጠሉ። የሚያጽናና ሰው አልተገኘም፤ የበላይሁን አባት የወትሮው ጥንካሬያቸው አብሯቸው የለም፤ ሀዘን ጨብጧቸዋል፤ እንባቸው በጉንጮቻቸው ላይ ይወርዳል። የፍሬሕይወትን እናት ቀና ብለውም አልተመለከቷቸውም። የበላይሁንን እናት መመልከት በራሱ ስቃይ ሆኖባቸዋል። የበላይሁን እናት ወገባቸውን በነጠላቸው አስረው በእንብርክካቸው ወለሉን ያዳርሱታል፤ በግንባራቸው ይደፋሉ...

ሮቤል እናቱን ተከትሎ መጣ፤ በሩ ላይ ሲደርስ የተመለከተው ነገር አስድንግጦት ሮጠና እናቱ አጠገብ ቆመ። ግራ ተጋብቶ ሽቅብ ተመለከታቸውና የእርሱም እንባ መፍሰስ ጀመረ። "ተው" የሚል አልተገኘም፤ ቀስ በቀስ ግን ድምጻቸው እየቀነሰ ሄዶ ቤቱን ጸጥታ ዋጠው።

"በሉ ይነሱና እወንበሩ ላይ ይቀመጡ፤ እንግዲህ ምን መሆን ይቻላል? ለመሆኑ የት ነው የታሰረው?" አሉ የፍሬሕይወት እናት



ከብዙ ቆይታ በኋላ የበላይሁንን እናት ክንድ ያዝ አድርገው ለማንሳት እየሞከሩ።

"ኧረ የት እንደሆነ አላወቅሁም" አሉና ወደባለቤታቸው ዞር አሉ።

"እዚሁ ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ነው" አሉ የበላይሁን አባት የበላይሁን እናት መልስ የሚጠብቁት ከእርሳቸው መሆኑን አውቀው። "እስኪ ልብስ አዘጋጅ" አሉ ደግሞ ወደ እየሩስ እየተመለከቱ። እየሩስ እንገቷን እንደቀበረች ብትሆንም የተናገሩት ለእርሷ መሆኑ ገብቷት ተነስታ ወደ መኝታ ቤት ገባች።

የውጭው በር ሲንኳኳ ሁሉም በድንጋጤ ተያዩ። የፍሬሕይወት እናት በፍጥነት ወጥተው በሩን ሲከፍቱ ፍሬሕይወትን አገኟት፤ ዐይናቸውን ማመን አቃታቸው፤ ምን እንደሚሏትም ግራ ገባቸው።

"እማ? ምንድነው? በላይሁን ምን ሆነ?" አለቻቸው።

"ታሰረ!" አሏትና እንባቸው እንደገና መፍሰስ ጀመረ።

ፍሬሕይወት መሬትና ሰማዩ ዞረባትና መሬት ተቀመጠች። ምንም መናገር አልቻለችም፤ አቀርቅራ ቀረች። እንባዋ መሬቱ ላይ ሲንጠባጠብ ተመለከተች፤ በሃይል እንዲወርድና ውስጧን እንዲያጥባላት የፈለገች ይመስል እንባዋን ለመግታት አልፈለገችም።

እናቷ እጇን ይዘው ከመሬት አስነሷት፤ ቀና ብላ ማየት አስፈራት፤ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ገምታ፤ በበላይሁን መታሰር ብቻ ሳይሆን ቀጣዩን እያሰቡ ሲያለቅሱ መቆየታቸው ስለተሰማት እናቷን ማየት ፈራች። አንገቷን እንደደፋች ወደነበላይሁን ቤት ሳይሆን ወደቤት ገባች። እናቷ ስላልተከተሏት ደስ አላት።

ከሁለት ቀናት በፊት በላይሁንን ስታገኘው የነበረበትን ሁኔታ አስታወሰች። የተገናኙት ድንገት ነበር፤ አራት ኪሎ፤ ስታገኘው መደንገጥ ብቻ ሳይሆን ተናዳበት ነበር።

"እዚህ ምን ትሠራለህ?" ብላ ጮኸችበት።

"እማራጭ ስላጣሁ ነው ፍርዬ! ሁሉም ነገር ተበለሻሽቷል፤ በዚያ ላይ ገንዘብ የለኝም" አላት።

"እንዴ በቅርብ አልነበረም እንዴ ገንዘብ ያመጣሁልህ?" አለችው።

"በጣም በከፋ ሁኔታ ውስጥ ለነበረ ጓድ ሰጠሁት" አላት።

ቦርሳዋ ውስጥ የነበሯትን ብሮች ለቃቅማ ሰጠችውና ታክሲ ይዞ ሄደ። ወዴት እንደሄደ እንኳ አላወቀችም። ገጽታው ላይ ተመልክታ የነበረው የተስፋ መቁረጥ ስሜት ነበር፤ የወትሮው ሞራሉና ጥንካሬው አብሮት አልነበረም።

እቤት ገብታ አልጋዋ ላይ ተቀመጠች፤ በሁለት እጆቿ ይዛ ግንባሯን ጉልበቶቿ ላይ ደፍታ ተቀመጠች። እንባዋ የደረቀ መሰላት፤ አእምሮዋ ግን እንደተበጠበጠ ነው፤ የማይሄድበት ቦታ የማያስታውሰው ሰው የለውም። በአፍታ ውስጥ ያለፉትን አራት አመታት ቃኘቻቸው፤ በእነዚያ አራት ዓመታት ውስጥ አብረዋት የነበሩትን ሰዎች፣ የነበራቸውን ራዕይና ብሩህ ተስፋ... ሊከፍሉ ቃል የገቡትን መስዋዕትነት...

"ይህ ሊሆን እንደሚችል፣ መስዋዕትነት የማይቀር መሆኑን አምነን አይደል እንዴ?" ጥያቄው ለራሷ ነበር።

አልጋዋ ላይ ተጋደመች፤ ደግሞ በደረቷ ተኝታ ትራሱን ጭንቅላቷ ላይ ጫነች። መረጋጋት ግን አቃታት፤ የሆነው ሁሉ ሊሆን የሚችል መሆኑን ብትቀበልም፤ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ብትሆንም ለእንዲህ ዓይነት የሃዘን ስሜት ግን ዝግጁ አልነበረችም። የሚመጣውን ሁሉ በቀላሉ የምትቀበል ይመስላት ነበር፤ ልትቀበለው ግን አልቻለችም። በላይሁን ከዐይኖቿ አልሰወር አላት፣ አስቻለውን አስታወሰችው፤ እናቱንም አሰበቻቸው። ። ቅዱስ አብሯት እንዲሆን ፈለገች፤ አጠገቧ ሆኖ አይዞሽ እንዲላት "ያለመስዋዕትነት ድል የለም!" ብሎ እንዲያበረታታት ተመኘች። እንትነህ ግጥሞቹን እንዲያነብላት፤ የትግል ታሪኮችን እንዲነግራት... ሀሳቧ ትርምስምስ አለባት። ጋዲሳና ዘርዓይ ከሀሳቧ አልጠፉ አሏት፤ "ይሆን ጊዜ የት ይሆኑ? ምንስ እያደረጉ ይሆን?" ጥያቄዎቹ ሰላም አልሰጥ አሏት።



ትራሱን ወረወረችና ተነሳች፤ ፊቷን ጠራረገችና ሰዓቷን ተመለከተች። ወደነበላይሁን ቤት ለመሄድ ራመድ ስትል ምን ብላ እንደምታጽናናቸው ጨነቃት።

* * * *

በላይሁን ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ በመግባቱ የተሰማው ስሜት የተመሰቃቀለ ነው። በአንድ በኩል ለቤተሰቦቹ በቀላሉ ያለበትን ቦታ መንገር እንደሚችል ሲያስበው ደስ አለው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከስድስተኛ ወዴት እንደሚወሰድና እዚያ ሊጠብቀው የሚችለው ነገር ዘገነነው። ፖሊስ ጣቢያው ውስጥ በርካታ የሚያውቃቸው ፖሊሶች በመኖራቸው ለእንዳቸው የቤቱን ስልክ መስጠት ብቻ በቂ ነበር። ወደአመሻሹ ላይ ቤተሰቦቹ የሚያስፈልገውን ሁሉ አመጡለት፤ ፖሊሶቹ እናቱ ከሩቅ እንዲያዩትም ፈቀዱላቸው። እናቱና የበላይሁን እናት ለቅሶአቸውን አላቋርጥ ብለው ፖሊሶቹ በግድ ገፍተው እንዳስኬዷቸው ሲመለከት በጣም አሳዘኑት።

ከእስረኞቹ ውስጥ አንዳንዶቹ በዐይን የሚያውቃቸው ስለነበሩ ውሎውን ብዙም አልከፋውም። ሲገባ ሰላም አሉት፤ ያላቸውን ምሳ አበሉት፤ እርሱም ፖሊሶቹ ምግብ እንዲያስመጡለት ጠይቆ አስመጡለት። የመኝታ ቦታ ለማግኘትም አልተቸገረም። የታጎሩበት ጠባብ ክፍል ግን ማታ ላይ ሁሉም ወደማደሪያው ሲገባ ከግምቱ በላይ ሆነበት። በትንፋሽ የታፈነውን አየር ወደሳንባው ማስገባት ጨነቀው፤ ቁንጫውንም መቋቋም ከበደው፤ ቁንጫው መብላት ሳይሆን አቃጠለው። ከሲሚንቶ የተሠራው የክፍሉ ጣሪያ ያጠራቀመው ትንፋሽ የውሀ ጠብታዎች ሠርቶ መንጠባጠብ ጀምሯል።

በላይሁን ሀሳቡ ከዚያ ካስጠላው ክፍል ውስጥ ምንጥቅ አድርጎ ሲወስደው አላወቀውም። በተያዘበት ዕለት የነበረውን ሁኔታ አስታወሰ፤ ፍሬሕይወትን ባገኛት በማግስቱ ከአዲስ አበባ የሚወጣበት የመጨረሻው ቀን መሆኑ ተነግሮት የተዘጋጀለትን አዲስ መታወቂያና ከአዲስ አበባ ከሚያወጣው ሰው ጋር የሚገናኝበትን ኮድ ተቀብሎ ነበር ወደማደሪያው የገባው።

ብዙዎች በመኖሪያ አካባቢያቸው መቆየት ባለመቻላቸውና የመጠለያ ጥያቄ በመብዛቱ በርካቶች በአንድ ቦታ እንዲያድሩ ማድረግ ግድ የሆነበት ጊዜ ነው። ከበላይሁን ጋር የሚያድሩት አራት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ለአንድ ሳምንት ያህል በዚያ ቤት ውስጥ ቆይተዋል። ማን በምን ደረጃ ለፓርቲው እንደሚሠራ አይታወቅ እንጂ ሁሉም ለአንድ አላማ የሚታገሉ መሆናቸውን ይተዋወቃሉ። በተቻለ አቅም ለየብቻቸው ይገቡና ድምጻቸውን አጥፍተው ያድራሉ። ከሁለት ቀናት በፊት ሁለቱ ሴቶችና አንዱ ወንድ ሄደዋል፤ "የት ሄዱ?" ብሎ መጠየቅ መቹም አያስፈልግም።

በላይሁን የሚሄድበት ቀን ተቆርጦ ሲነገረው ደስ ብሎት ነበር የዋለው። ከአዲስ አበባ መውጣቱን ለፍሬሕይወት ሊነግራት አሰበና ስልክ ቢደውል አላገኛትም። የቀጠሮውን ሰዓት ሲመለከት በማግስቱ ሊደውልላት ጊዜ እንዳለው አሰበና ወደማደሪያው ገባ። ማታ ትንሿን ሻንጣውን ሲያዘጋጅ ሌላውም ወጣት እንደርሱ ሲዘጋጅ ነበር ያመሸው። "ሁለቱ ብቻ ሊቀሩ ነው ማለት ነው" አለ በላይሁን በሀሳቡ ለእነርሱም እንዲቀናቸው በመመኘት።

ለጉዞው ንቁ ለመሆን ደህና እንቅልፍ ሊያገኝ እንደሚገባው አስቦ የተኛው በጊዜ ነበር። እንቅልፍ ግን አልወሰደውም፤ የማያውቀውን የሚሄድበትን ቦታ ሲያስብ፤ የሚያገኘውን ሰው በሀሳቡ ሲስል... ስላለፈው የትግል ወቅት ሲያወጣና ሲያወርድ... የሞቱትንና የጠፉትን ጓደኞቹን ሲያስታውስ... ሌሊቱ ተገባደደ። ፍሬሕይወትን እንደምንም አግኝቶ ሊሰናበታት እንደሚገባው ወስኖ የት እንደሚቀጥራትና ምን እንደሚላት እያውጠነጠነ ባለበት ደቂቃ ያልገመተው ሁኔታ ተፈጠረ። የተኙበት ቤት የፊት ለፊት መዝጊያ ተበረገደና ትርምስምስ ሆነ።

በላይሁን እንዴት እንዳፈጠነው ባያውቀውም ሁልጊዜም ለድንገተኛ አደጋ ተብሎ ሳይዘጋ በሚያድረው የጓሮ በር ተፈተለከ። የጓሮው በር ወደሌላ ግቢ ያስገባል፤ በላይሁን በነበረበት ቤት ውስጥ ተኩሱ የተጀመረው ወዲያውኑ ነው፤ እርሱ ወደሌላው ግቢ ውስጥ ሲገባ ትልቅ ውሻ ሊቦጫጭቀው ዘሎ ጥርሶቹን አሹሎ መጣበት። ከውሻው ለመዳን የሞት የሽረቱን በአጥሩ ማገር ላይ ተንጠላጠለ፤ ውሻው ግን ሊተወው አልቻለም። ከአጥሩ ማገር ላይ አጠገቡ ወዳለው ቤት ጣሪያ ተሸጋገረና ጣሪያው ላይ በደረቱ ተኛ።



ተኩሱንም ሆነ የውሻውን ጩኸት ሰምቶ ከአካባቢው ቤቶች የወጣ አልነበረም፤ ይልቁንም አንዳንድ ቤቶች ውስጥ ይታይ የነበረው የመብራት ጭላንጭል በሙሉ ጠፋ። በላይሁን በጣሪያው ላይ በልቡ እየተሳበ በቀላሉ የማይታይበት ቦታ ላይ መሆኑን ሲያረጋግጥ እዚያው መቆየት እንዳለበት ወሰነ። ተኩሱ ብዙም አልቆየም፤ ጸጥታ ሰፈነ። ታጣቂዎቹ ከበላይሁን ጋር ያድሩ ከነበሩ ወጣቶች መሀል ሁለቱን እያዳፉ ሲወስዱቸው ተመለከተና "ሌሎቹስ አምልጠው ይሆን ወይንስ ሞተው?" አለና ራሱን ጠየቀ። ሌሎቹ ታጣቂዎች ደግሞ እነርሱ በሚያድሩበት ግቢ ውስጥ ካለው ትልቅ ቪላ ቤት ውስጥ አንድ በጎልማሳነት ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ ፒጃማ የለበሰ ሰው እያዳፉ ሲወጡ ተመለከተ።

"እባካችሁ በሽተኛ ነው..." እያለች የምትከተላቸውን ሴት እየገፈታተሩ ወደቤት እንድትመለስ አድርገዋት ሰውዬውን ይዘውት ሄዱ።

ከትልቁ ቤት ብዙም ሰዎች አልወጡም፤ አንዲት አዛውንት ሴትና ውስጥ ልብስና ነጠላ የለበሰችና የምትንቀጠቀጥ ሴት ብቻ ነበሩ፤ ሶስቱም አደጁ ላይ ኩርትም ብለው ተቀመጡ። ከአካባቢው ማንም ሊረዳቸው አልወጣም። ጥቂት ቆይቶ አካባቢው ጸጥታ ሰፈነበት፤ ትልቁ ውሻ አልፎ አልፎ ቢጮህም ቀስ እያለ ተረጋጋ።

ቀስ በቀስ ጨለማው እየገፈፈ ሲሄድ በላይሁን ስጋት ገባው፤ ሰዎች ደጃፎቻቸውን እስኪከፍቱ ድረስ እዚያ ላይ ከቆየ አደጋ ውስጥ እንደሚገባ ስለሚያውቀው እንዴትና በየት በኩል ከጣሪያው ላይ እንደሚወርድ አሰላሰለ። በጥንቃቄ በደረቱ እየተሳበ አመቺ መውረጃ ለማየት ሞከረ። በዚያው ደቂቃ ሶስቱ ሴቶች ወደቤት ገቡለት፤ ለራሱም በደነቀው ፍጥነት የአጥሩን ማገር ተጠቅሞ ከጣሪያው ላይ ወረደ።

በቀስታ ወደማደሪያቸው ገባ። ቤቱ እንዳልነበረ ሆኖ ዝብርቅርቁ ወጥቷል። ለመንገድ ያዘጋጃትን ቦርሳ ወዳስቀመጠበት ቦታ ለመጠጋት ራመድ ሲል የወደቀ ሰው ተመለከተ አብረውት ከነበሩት ወጣቶች አንዱ ነው፤ ሞቷል። ዘገነነው፤ እዚያ ቤት ውስጥ ለደቂቃም መቆየት እንደሌለበት አሰበ። ቦርሳውን ተቀዳድዳ ወድቃ አገኛት፤

በፍጹም ሊይዛት አይችልም። ባዶ እጁን ወጣ፤ ኪሱን ዳበሰና መታወቂያው መኖሩን አረጋገጠ ።

የውጭውን በር ሲወጣ የት ሊቆይ እንደሚችል እያሰበ ነበር። "አውቶቡስ ተራ! አውቶቡስ ተራ!" የሚል የታክሲ ጥሪ ድንገት እጆሮው ጥልቅ አለ። የተሻለ አማራጭ የለውም፤ ወደዚያው ሄደና ታክሲ ውስጥ ገባ። ብዙም ሳይቆይ ታክሲው ተንቀሳቀሰ፤ ካዛንችስ ቶታል ሲደርሱ ግን ሌላ ችግር ተከሰተ። ታጣቂዎች ታክሲውን አስቆሙትና ተሳፋሪዎቹ እንዲወርዱ አዘዙ። በላይሁን ከሚያውቀው አብዮት ጥበቃ ጋር ዐይን ለዐይን ተገጣጠመ። በምንም መልኩ ከዚህኛው አጋጣሚ እንደማያመልጥ አወቀ። መታወቂያውን አውጥቶ በወንበሩና በብረቱ መሀል ሸጎጠውና እንደማይታይ አረጋግጦ ከታክሲው ወረደ።

"ጎሽ! ጮማዎቹን ዲሞዎች አሳፍረህ ወዴት ልትወስድ ነው እባክህ?" አለና አብዮት ጥበቃው አፈጠጠ። መለስ ብሎ ደግሞ አብረውት ካሉት ታጣቂዎች ለአንደኛው በጆሮው የሆነ ነገር ሹክ አለው።

ወዲያውኑ በላይሁንን እያጣደፉ መኪና ውስጥ አስገቡት፤ ባለታክሲውንና ተሳፋሪዎቹን ምን እንዳደረጓቸው ሳያይ እርሱን ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አስገብተውት ሄዱ። ወደውስጥ ሲዘልቅ በሚገርም ሁኔታ በርካታ የሚያውቃቸውን ወጣቶች ተመለከተ፤ ማናቸውም ግን ምንም አላሉም፤ እርሱም ምንም ምልክት ሳያሳይ ተቀላቀላቸው። ሁሉም በየአጋጣሚው ከየመንገዱ እየተለቀሙ የታጎሩ መሆናቸውን ለማወቅ ደቂቃዎች ብቻ ነው ያስፈለገው። በወንጀል የታሰሩት በጣም ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

አጋጣሚው የሚጠበቅ ቢሆንም ከአዲስ አበባ ለመውጣት በተዘጋጀበት ሰዓት መሆኑ በላይሁንን አናደደው። ከገባበት ፖሊስ ጣቢያ ለመውጣት ያለው ዕድል የጠበበ ቢሆንም እንደምንም ብሎ ያን ታጣቂ አብዮት ጥበቃ ለማግባባት መሞከሩ አይቀርም።

አብዮት ጥበቃው ሙሉውን ቀን ሳይመጣ በመዋሉ አግኝቶ ሊያነጋግረው አልቻለም። ነገር ግን በተስፋ ይጠብቃል፤ ሰውየው በጅምላ የአካባቢውን ወጣት በሙሉ በኢህአፓነት ከመፈረጅ ያለፈ



መረጃ እንደሌለው በመገመቱ እንደምንም ጸባዩን አሳምሮ ከተለማመጠው ሊለቀው እንደሚችል ሲያስብ ነው የዋለው።

"የሰውዬውን ሥም ባውቀው ምን ነበረበት?" አለ በላይሁን ለራሱ "ጋሼ እከሌ" ብሎ ቢጠራው ልቡን ሊያራራው እንደሚችል ገምቶ።

"ግን ተሳክቶልኝ ከዚህ ብወጣ ምንድነው የማደርገው?" አለ ደግሞ የቀጠሮው ጊዜ ማለፉንና ተለዋጭ ቀጠሮ የማግኘቱም ነገር አስቸጋሪ እንደሚሆንበት አስቦ። ግንኙነቶች ሁሉ ተቆራርጠው ቶሎ መቀጠል አዳጋች እየሆነ ከመጣ ቆይቷል።

"ቢያንስ ፍርዬን ማግኘት እችላለሁ፤ ከእርሷ በላይ ላለው ሰው ሪፖርት ማድረግ ከተቻለ... ግን ሁሉም ቀላል አይሆንም። እርሷስ የት ትሆን?" አለና ጥርጣሬ ገባው።

ቢሆንም እናቱ ጠዋት ሲመጡ ይጠይቃል፤ እንደወጣ ሊያገኛት እንዲችል ያመቻቹለታል። የመሳሰለውን ሀሳብ ሲያወጣና ሲያወርድ፤ ቁንጫ እየለበለበው ሲያክ ሌሊቱ እንደምንም ነጋለት።

እስረኞቹ የተመቸ ቦታ የተኙ ያህል ሳይገላበጡ አንግተው ቀና ቀና ማለት ጀመሩ። ወደመጸዳጃ ቤት ለመሄድ ጥድፊያ ሆነ።

"ጆ! ተነሽ እንጂ በኋላ እኮ ሽታውን አትችለውም፤ በጠዋት ይሻላል" አለው አንደኛው እስረኛ ከአጠገቡ እየተነሳ።

በላይሁን ከመኝታው ተነስቶ ለብሶት ያደረውን ጋቢና ብርድልብስ አጣጥፎ አስቀመጠና ለመጸዳጃ ቤት ወረፋ ለመያዝ ወጣ። ገና ከክፍል ወጥቶ በሩ ላይ ሲደርስ ከዚያ ትናንት ካመጣው ታጣቂ ጋር ፊት ለፊት ተያዩ። በላይሁን ገና ሰላም በማለትና ባለማለት መሀል እያለ ቀድሞት

"አጅሬ ያንተ ቦታ እኮ እዚህ አይደላም፤ ለዛሬ ግዴለም ነገ ግን ትሄዳታለህ" አለው።

በላይሁን በውስጡ ተፈጥሮ የነበረው ተስፋ ሁሉ በሰከንድ ውስጥ ተነነበት። ምንም እንዳልገባው ዓይነት ዝም አለና ወረፋውን መጠበቅ ያዘ። በውስጡ ግን ነገ እንዲያልፍለት ተመኘ፤ አንድም ቀን ቢሆን ዕድሜ ነው "እዚያ..." የተባለው የት እንደሆነ አሳምሮ ያውቀዋል፤ ደርግ ጽሕፈት ቤት ነው። እዚያ ከሄደ ደግሞ የሚከተለውን ያውቀዋል፤ አበቃለት ማለት ነው። የሚሆነውን ከመጠበቅ የተሻለ ምንም አማራጭ ስለሌለው ነገን በስጋትና በጭንቀት መጠበቁን ጀመረ።

ወረፋውን እየጠበቀ፣ ከዚያም በኋላ በአእምሮው ውስጥ ያልተመላለሰ ሀሳብ አልነበረም። የትግሉ ነገር አንድና አንድ ነገር ብቻ ይቀረዋል፤ አስፈላጊ ከሆነ እስከሕይወት የሚደርስ መስዋዕትነት መክፈል! "የትግሉ ነው ሕይወቴ..." ከልብ የተባለ ስለሆነ የሕይወት መስዋዕትነት መክፈል ግድ ሊሆን ይችላል፤ ያንን በጸጋ ይቀበለዋል። እናቱን፣ አባቱንና እህቱን አሰባቸው፤ በእርሱ ሞት ምክንያት ሊደርስባቸው የሚችለውን ሃዘን ሲያስበው እንባው በአይኖቹ ግጥም አለበት፤ ብዙዎች ሲሞቱ ቤተሰቦቻቸው የደረሰባቸውን መሪር ሃዘን እስኪታክተው ተመልክቷል። ወዲያው ደግሞ ፍሬሕይወት ድቅን አለችበት፤ ለፍሬሕይወት ያለውን ፍቅር ግን እንኳንስ ሌላ ሰው እርሷም አታውቅለትም፤ ፍቅሩን እንኳ ሳይገልጽላት እስከወዲያኛው ሊለያት መሆኑ አጥንቱ ድረስ ተሰማው። "በፍጹም!" አለ በላይሁን "እንደምወዳት ሳልነግራት መሞት የለብኝም። ደግሞም ምንም ዓይነት መልእክት ለመላክ ከአሁን የተሻለ ጊዜ የለም" አለ ለራሱ።

ከመጸዳጃ ቤት እንደተመለሰ ከእስረኞቹ ወረቀት ለመነና አገኘ፤ እስኪሪፕቶ ኪሱ ውስጥ ስለነበረው ክፍሉ ውስጥ መኝታው ላይ ተቀምጦ መጻፍ ጀመረ። አዎ የመጨረሻ ማስታወሻው ሊሆን ይችላል፤ እስከአሁን ደርግ ጽሕፈት ቤት ገብቶ የወጣ ሰው አያውቅም፤ የእርሱም መጨረሻው ሊሆን እንደሚችል አልተጠራጠረም። መልዕክቱን በፍጥነት ጽፎ ጨረሰና አነበበው፤ እያነበበው እንባው ቆጠቆጠው። ከመቼ ወዲህ እንዲህ ሆደ ባሻ እንደሆነ ለራሱም ገረመው። እናቱ እንደሚመጡ እርግጠኛ ስለሆነ እናቱ መልዕክቱን እንዲያገኙ የሚያደርግበትን ዘዴ ማውጠንጠን ጀመረ።



እናቱ ምግቡን ሰጥተው ዕቃው መመለሱን ይጠባበቃሉ። ከርቀት እጁን አውለብልቦላቸው ዕቃውን ተቀብሎ በፍጥነት ወደውስጥ ገባ። በላይሁን ምግብ ለሚያመላልሰው ልጅ ዕቃውን ሲመልስ ነገ ወደደርግ ጽሕፈት ቤት ሊሄድ እንደሚችል፤ ባያገኙት እንዳይደነግጡና የሻዩን ፔርሙዝ በደንብ እንዲያጥቡት እንዲነግራቸው አስረዳው። ያንገቱን ሀብል አውልቆ ለእናቱ እንዲሰጣቸው ነገረውና "ለፍሬ ነው" ብሎ እንዲያስረዳ ነገረው። እናቱ ይህንን ሲሰሙ የቱን ያህል ሊደነግጡ እንደሚችሉ ማየት አልፈለገም፤ ልጁን ልኮት እርሱ ክፍል ውስጥ ቀረ።

ልጁ ብዙም ሳይቆይ ተመልሶ መጣ "ምን አለች" አለ በላይሁን በጥድፊያ።

"እባክህን ብቅ በልላቸውና ይዩህ" አለው ልጁ ባጭሩ።

በላይሁን እንደምንም ብሎ ብቅ አለ። "ምን ብለሃቸው ነው አንተ?" አለው አንደኛው ፖሊስ።

"ነገ ስትመጣ ድንገት ከምታጣኝ አሁኑኑ ትወቀው ብዬ እኮ ነው" አለ በላይሁን ቀለል አድርጎ።

"ምኑን ነው የሚያውቁት?" አለና ጮኸበት ፖሊሱ

"ጠዋት እኮ በአደባባይ ነው የተነገረኝ" አለ በላይሁን። ሁሉም ማንሾካሾክ ጀመሩ። ፖሊሱ አጠገብ ያለ ሌላ ፖሊስ ቀስ ብሎ የሆነ ነገር ነገረው።

"ጠጋ በልና አረጋጋቸው" አለው ፖሊሱ።

"ነገ ብታጭኝ ይሻልሽ ነበር?" አላቸው ተጠግቶ።

"እሱስ አይሻለኝም" አሉት ባጭሩ። "ሻዩ ምን ሆነብህ?" አሉት ደግሞ።

"ጣዕሙ ትክክል አይደለም፤ ክፍትፍት አድርጊውና በደንብ እንድታጥበው ለፍሬ ስጪት" አላቸው።

"እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን" አለት ዐይን ዐይኑን እየተመለከቱት።

"ምንም አልሆንም" አላቸው።

"ይበቃል ግባ" አለው ፖሊሱ።

"በቃ ግባ" አሉት እናቱም።

ዐይኖቻቸው እየተከተሉት እንደሆነ እየተሰማው ወደውስጥ ተመለሰ። ከዐይናቸው የሚሰወርበት ቦታ ሲደርስ መለስ ብሎ ተመለከተ። እንደቆሙ ናቸው። እጆቹን አወዛወዘላቸው።

"እናቴን እንደገና አያት ይሆን?" አለና ራሱን ጠየቀ።

እስረኞቹ ሁሉ ፀሐይ ለመሞቅ ውጭ ቢሆኑም እርሱ ግን ገብቶ መኝታው ላይ ተቀመጠ። በሀሳቡ ከእናቱ ጋር ወደቤቱ ሄደ። እናቱ ሊነግሩቸው የፈለገው ነገር መኖሩን መረዳታቸውን ከፊታቸው ላይ ተመልክቷል። ለፍሬ የጻፈውን ደብዳቤ እንደሚያገኙትና ከሀብሉ ጋር እንደሚሰጧት እርግጠኛ ነው።

"ግን ፍሬ ምን ይሰማት ይሆን? እንዴት እስከአሁን አይነግረኝም ብላ ትናደድ ይሆን? አሁን ምን እንዳደርግ ነው? ብላ ትቀየመኝ ይሆን? ትጠላኝ ይሆን..." ጥያቄዎቹ ማለቂያ የላቸውም።

"በላይሁን" የሚል ድምጽ ሰማ። ደነገጠ። ወዲያው ግን ራሱን አረጋጋና "አቤት" ብሎ ወደበሩ ተጠጋ። የጠራው ያ ታጣቂ ሰውዬ ነው። ለመጨረሻው ነገር ራሱን አዘጋጀና ቆፍጠን ብሎ ሰውየውን ተመለከተው።

"ና ውጣ" አለው ሰውዬው።



ለራሱም በገረመው ሁኔታ አንገቱን ቀና አድርጎና የአንድ ቀን የእስር ቤት ጓደኞቹን በጅምላ "ደህና ሁኑ!" ብሎ ሰውዬውን ተከተለው።

* * * *

ፍሬሕይወትና ዳኙ በሰዓቱ ተገናኙ፡፡ ትልቁን ኮቱን አልለበሰም ወገቡ ላይ ቡፍ ያለ ቢሆንም ቀልጣፋ ጃኬት ለብሷል። ንግግራቸው በጣም ፈጣን ነው፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ መንቀሳቀስ ያቃታቸው አባላት ከከተማ መውጣት እንዲችሉ ለማድረግ የቀበሌ መታወቂያ እንዲወጣላቸው ፎቶ መቀባበል አለባቸው።

"መታወቂያዎቹን የምትሰጫቸው አንቺ ነሽ፡፡ ፈጣን መሆን አለብሽ፤ ጊዜ መውሰድ የለብሽም በተጨማሪም ጥንቃቄ የተሞላበት ሥራ መሆን ይኖርበታል" አለና የትና በስንት ሰዓት እንደምታገኛቸው ነገራት። የሰጣትን ፎቶዎች ለዚሁ ጉዳይ በተተረተረው የቦርሳዋ ገበር ውስጥ ከተተችና የተጨማሪ ሁለት አባላትን በአካባቢው ያለመኖር አስታወቀችው። አዲሶቹን የኮሚቴ አባላት ብታገኛቸውም ገና ከጋዲሳና ከዘርዓይ ጋር አላስተዋወቀቻቸውም።

ከዳኙ ጋር ያላትን ጉዳይ ጨርሳ ስትመለስ የሰጣትን በርካታ ሥራዎች እያሰበች ነበር። ቤት ከመግባቷ በፊት የበላይሁንን እናት ለመጠየቅ ጎራ አለች፡፡ በላይሁን ጋ ሄደው እንደሆን ጠየቀቻቸውና ገና መመለሳቸው መሆኑን ነገሯት፡፡

"አዩት? እንዴት ነው?" አለቻቸው።

"አዎን አየሁት ነገ ደርግ ጽሕፈት ቤት እንደሚወስዱት ነገረኝ፡፡ ከዛ ተርፎ ይወጣል ብለሽ ነው?" አሉ በእንጨት ቢጤ መሬቱን እየቆረቆሩ።

"ማን ያውቃል?" አለቻቸውና ወደቤት ለመሄድ ተነሳች።

"ቆይ በላይ መልዕክት ልኮልሻል" አሉና ከተቀመጡበት ብድግ አሉ።

"እንዴት አድርጎ እማማ?" አለች ተገርማ።

"አንችም ይገርምሻል? ፒርሙዙን ሲመልስልኝ አመለከተኝ፡፡ ብዙም ባይገባኝም እሺ አልኩት፤ ቤት ስደርስ ከፍቼ ሳየው መልእክቱን አገኘሁት። ፊደል መቁጠሬን ወደድኩት፡፡ በዚህ መችም ደርግ ጥሩ ሰርቷል፡፡ ይህን እንድሰጥሽም ነግሮኛል" አሉና ማስታወሻውንና ያንገት ሀብል ሰጧት ደነገጠች።

"ኧረ እማማ ይህኛው እንኳን እርስዎ ጋ ይቀመጥ" አለቻቸው ሀብሉን እንዲቀበሏት እጇን እየዘረጋች። "አይሆንም" አሏት።

በላይሁን የላከውን ማስታወሻ ለማንበብ እየቸኮለች ወደቤት ሄደች፡፡ ቤት ስትገባ እናቷም ይንቆራጠጣሉ፡፡ ሰላምታ ማቅረብ እንኳን ከበዳት። "በየቱ መንገድ መጣሽ?" አሏት ግንባራቸውን ከስክሰው።

"በገብርኤል በኩል።" አለች ምን እንደሆኑ ለመገመት እየሞከረች።

"የኔ ገብርኤል ዱሮስ መች ይጥለኛል።"

"እማ የሰማሽው ነገር አለ እንዴ?" አለች በጭንቀት።

"ዳንኤል የሚባል ሰው ገዳይ ነሽ ተብሎ እየተፈለግሽ ነው አሉ" አሏት እናቷ አመዳቸው ቡን ብሎ።

"አሁኑኑ አክስቴ ቤት እሄዳለሁ። ከዛ በኋላ ደግሞ የምሆነውን መልዕክት እልክብሻለሁ" አለቻቸው እናቷን። ምንም ጊዜ አላባከነችም የእናቷን ቀሚስ ለብሳና ነጠላዋን አጣፍታ ውልቅ አለች።

አክስቷ ቤት ስትገባ በመጀመሪያ ልብሷን ከቀየረች በኋላ ነው አክስቷን ሰላም ለማለት ወደዋናው ቤት የገባችው። ከሰላምታ በኋላ ሥራዋ ያደረገችው የበላይሁንን ማስታወሻው ማንበብ ነበር፤ እንዲህ ይነበባል።

*"ፍርዬ! እንዴት ነሽ? እኔ ደህና ነኝ ልበልሽ? ደህና ያለመሆኔን ስለምታውቂው ደህና ነኝ ብዬስ አልዋሽሽም። እስካሁን ግን የደረሰብኝ አካላዊ ጉዳት የለም ምን ሊከተል እንደሚችል የታወቀ*



*ስለሆነ መጠበቁ ግን አስከፊ ነው። እዚህ ፖሊስ ጣቢያ የልጠበቅሁትን ያህል እስረኞች ማግኘቴም ያለኝን ተስፋ እያጨለመው ነው።*

*በየትኛዋ ደቂቃ ወዴት እንደምወሰድ ስለማላውቅ ይህችን ማስታወሻ ለመጻፍ ስለፈለግሁበት ጉዳይ ልንገርሽ። እንዴት ብዬ እንደምጀምረው ግን ግራ ይገባኛል። አንዳንዴም "የስቀማት ይሆን?" እልና እጨነቃለሁ። አሁን ግን፤ አዎ አሁን ግን ቁርጥ ቀን የመጣ ይመስለኛል ዳግም የመገናኘታችንም ነገር በጣም አጠያየቂ ሆኗል። እናም ላለፉት ብዙ ዓመታት በውስጤ የያዝኩትን ሚስጥር ሳልነግርሽ ወደሞት መሄዴን ሳስበው ስሜቴን መቆጣጠር አቃተኝ። ገና ወደትግሉ ስንገባ የገባነው ቃል በመሆኑ መስዋዕትነትን አልፈራሁትም፡፡ መስዋዕትነትን ባሰብኩ ቁጥር ወደአእምሮዬ የሚመጡት የልቦቻችን ዝማሬ የነበሩት ስንኞች ናቸው። "ቢሰበር አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ..." ለምን ያህል ጊዜ ደጋግሜ እንደዘመርኩ ማስታወስ ይከብዳል። እናም ሞትን ለመቋቋም ዝግጁ ነኝ።*

*ሁለት ነገሮች ግን እጅግ በጣም ከምችለው በላይ ያስጨንቁኛል ቤተሰቦቹና አንቺ። እናቴን ገና ሳስባት የምሆነው ይጠፋኛል፡፡ የእህቴ ምንም አለማወቅና በደመነፍስም ቢሆን እኛን መደገፍ መሠረቱ ለእኔ ለወንድሟ ያላት ፍቅር በመሆኑ የቱን ያህል ልትጎዳ እንደምትችል ሳስበው ልቤ ይሽበርብኛል። የአባቴን ነገር ታውቂዋለሽ፤ አባቴ ብቻ ሳይሆን ጓደኛዬም ጭምር ነውና በየደቂቃው አስበዋለሁ።*

*ፍርዬ! ይህ ሁሉ ግን ብዙዎች ሊገምቱት የሚችሉት ነው፡፡ ማንም የማያውቅልኝና ሊገምተውም የማይችለው ለአንቺ ያለኝን ስሜት ነው። ምን እንደምትይኝ አላውቅም፡፡ የፈለግሽውን ልትይኝ ትችያለሽ፡፡ በአንድ ነገር ላይ ግን እርግጠኛ ነኝ፤ ቢያንስ እንደታላቅ ወንድም ትወጂኛለሽ። እኔ ግን ከታናሽ እህቴም በላይ እወድሻለሁ፤ አፈቅርሻለሁ። ፍርዬ! ቃላት ሊገልጹት ከሚችሉት በላይ አፈቅርሻለሁ! ይህንን ስሜቴን ከማጋራት ግን ብዙ ምክንያቶች ገቱኝ፤ አንዱና የመጀመሪያው ቤተሰቦቻችን ያላቸው ግንኙነት ነው፤ በተለይም እናቴ ሁልጊዜም "እህትሁ፣ ወንድምሽ" የምትለው ነገር ይከብደኛል። ያንቺ አባትና እናት በልጅነት አእምሮዬ የፈጠሩት ስሜት ከሥጋ ዘመዶቼ በላይ እንዳያቸውና ባዕድነታቸውን*

*እንዳልቀበል አስገደደኝ። ለአንቺ ያለኝን ፍቅር ብናገር ሁሉንም ነገር የማበላሽ፣ የቤተሰቦቻችንን ጠንካራ ትስስር የምበጣጥሰው መሰለኝ። ግን እውነቱን ልንገርሽ ሁል ጊዜም "አንድ ቀን ..." የሚል ተስፋ ነበረኝ።*

*ዛሬ ላይ ሆኜ ሳየው ያ አንድ ቀን እንደማይመጣ ተሰማኝ፡፡ እናም እስከወዲያኛው ከአንቺ መለየቴን ሳስበው እንደማፈቅርሽ እንኳን ሳታውቂ መሆኑ ልቤን አደማው። ፍርዬ! እኔ ፍቅርሽን በውስጤ እንደያዝኩ የመቀበር ዕድል ካጋጠመኝ ወደመቃብሬ እወርዳለሁ። መቼም ከሞት የሚተርፉ ጥቂት ጓዶች እንደሚኖሩ እጠብቃለሁ፡፡ ከሚተርፉት ሰዎች መሀል አንዷ እንድትሆኚ ያለኝ ምኞት ከፍተኛ ነው። ሕይወትሽ ሁሉ የተቃና እንዲሆንም እመኛለሁ! በሕይወት እስካለሽ ግን እንዳትረሽኝ እፈልጋለሁ። ቢያንስ እንደወንድምሽ አስታውሽኝ። ማስታወሻዬ ይሆንሽ ዘንድ አባቴ በስምንተኛ ክፍል ፈተና ባመጣሁት ውጤት በመደሰቱ ከአንገቱ አውልቆ የሰጠኝን ሀብል ልኬልሻለሁ።*

*እስከዘለዓለም አፍቃሪሽ በላይሁን" ይላል*

"እንዴ ምን ሆነሻል?" አለች የአክስቷ ልጅ ስቅስቅታዋን ሰምታ። ሳታስበው እያለቀሰች ወረቀቱን ሰጠቻት። ዘመዶቻቸው ሁሉ እነበላይሁንን እንደዘመድ ነው የሚያዩአቸው። እርሷም ከፍሬሕይወት ጋር አብራት አዘነች።

* * * *

ሕይወት የወትሮ ቃናና ለዛውን ካጣ ሰነበተ። ወይዘሮ ስርጉት ባለቤታቸውን የሚያስታውሱባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው እንዲህ መንፈሳቸው እርብሽ ሲል ደግሞ የበለጠ ያስቧቸዋል።

"እንዴት አድለኛ ሰው ነህ፣ እግዚአብሔር የሚወድህ" አሉ አንገታቸውን እንዳቀረቀሩ። ቀና ብለው ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ፎቶግራፍ ለረጅም ደቂቃዎች ተመለከቱት። የባለቤታቸው ክስታራ ግንባር ሁሌም ቢሆን ቁጡነት ሳይሆን ጥንካሬያቸውን እንደሚመሰክር ነው የሚያስቡት።



"ሕይወትን መጋራት እንዴት ጥሩ ነበር? ለዚያውም እንዳንተ ካለ ጠንካራ ሰው ጋር?" አሉና እንባቸው በዐይኖቻቸው ግጥም አለ።

"አንተ ኖረህ ቢሆን ሁኔታው ሁሉ ሊለወጥ ይችል ነበር? ልጆቼንስ ምን ታደርጋቸው ነበር? ፖለቲካ ውስጥ ከመግባት ልታግዳቸው ትችል ይሆን?..." ራሳቸውን ነቀነቁ፤ በፍጹም በዚህ ራሳቸውን መውቀስ እንደማይገባቸው አሰቡ። "አባት ያላቸው ሁሉ ፖለቲካ ውስጥ መች ሳይገቡ ቀሩ? ደግሞም እኮ የሚያስቡትና የሚመኙት ክፉ ነገር አይደለም። የሚያነቡትንና የሚወያዩትን በተወሰነ መልኩም ቢሆን ያውቁታል..." ሁሉ ነገር የተምታታባቸው መሰላቸው።

የኑሮ ሸክም አልከበዳቸውም፤ መሥራት አልሰለቻቸውም። ፍርዬና ሚሚ ተካፍለው ይሠሩት የነበረውን ሥራ ብቻቸውን ተያይዘውታል፤ ለሆቴሉ የሚያቀርቡትን እንጀራ በፍጹም ማቋረጥ እንደሌለባቸው ወስነዋል። "ከደከመኝ የምትጋግርልኝ እቀጥራለሁ እንጂ..." እያሉ ከማሰብ በቀር ተማረው አያውቁም።

ሊቋቋሙት ያልቻሉት ጭንቀታቸውን ነው፤ እንቅልፍ ብርቅ ሆኖባቸዋል። ለልጆቻቸው መጨነቃቸውና መጸለያቸው የሁልጊዜ ተግባራቸው ቢሆንም ሰሞኑን ጭንቀታቸው አይሎባቸዋል፤ ወዴት እንደሆን ሳያውቁ የሚሚ መሄድ፣ የቃለአብ ቤት መምጣት ያለመቻልና አክስቱ ቤት መመሸግ አሁን ደግሞ የፍሬሕይወት ሁኔታ፤ ሁሉም ነገር ከአእምሯቸው በላይ ሆኖባቸዋል።

"ስርጉት! እንዴት አደርሽ?" አሉ የበላይሁን እናት።

"እግዚአብሔር ይመስገን፤ ይግቡ" አሉ ወይዘሮ ስርጉት ከተቀመጡበት እየተነሱ።

"ፍሬሕይወት የት ነች?" አሉ ገባ ሲሉ

"ኧረ የለችም"

"ብቻ ወደዚህ ሰፈር እንዳትመጣ መንገር ነው የሚሻለው፤ እነሱ እንደሆን ከጠረጠሩ በቂ ነው፤ ምስክር የለ ፍርድ! ብቻ እንዳትመጣ መንገር ነው " አሉ የበላይሁን እናት።

"ምን ይሻለናል የበላይሁን እናት?" አሉ ወይዘሮ ስርጉት ጭንቅ ቢላቸው።

"ለአንድዬ ከመንገር በቀር ምን የሚሻል ነገር አለ ስርጉት" አሉ አንገታቸውን ወደጣራው ቀና አድርገው።

"ለመሆኑ ዛሬ በላይሁንን አዩት? የኔ ነገር ብቅ ሳልል አረፈድኩ" አሉ የፍሬሕይወት እናት።

"ኧረ የለም፤ ወደ ደርግ ጽሕፈት ቤት መሄዱን ነገሩኝ" አሉ በሀዘን ስሜት።

"አፈር በሆንኩት!" አሉ የፍሬሕይወት እናት ደረታቸውን ድልቅ አድርገው።

ያለምንም ንግግር ሁለቱም በየፊናቸው ከየሀሳባቸው ጋር ጭልጥ አሉ። ከነበላይሁን እናት ቤት የተሰማቸው የስልክ ድምጽ ሁለቱንም ከገቡበት ሀሳብ አወጣቸው። ምንም ሳይናገሩ በፍጥነት ወጥተው ሄዱ የበላይሁን እናት።

"ስርጉት" አሉና ተጣሩ ወዲያውኑ። "ስልኩ ያንቺ ነው፤ ምነው ፍርዬ በሆነች" አሉ የበላይሁን እናት ለራሳቸው ብቻ በሚሰማ ድምጽ።

"ሄሎ" አሉ የፍሬሕይወት እናት የፈራ በሚመስል ድምጽ።

"አዎ ነኝ፤ ማን ልበል? እሽ" አሉና ለበላይሁን እናት ፍርዬ ነች የሚል ምልክት ሰጧቸው።

የፍሬሕይወትን ደህንነት በመስማታቸው ተደሰቱ፥ የሰፈሩ ትርምስ እየተባባሰ መሆኑን ነገሯት። "አደራሽን ተጠንቀቂ" አሏት።



"ተመስገን! አንተ እኮ ሁሌም ከኔ ጋር ነህ" አሉ ስልኩን ዘግተው ሲቀመጡ።

* * * *

ሰሞኑን አፈሳው ተጧጡፏል፡፡ በአንድ ቀን ብቻ መርካቶ አካባቢ በተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ታፍሰው ጃንሜዳ ታጎሩ። ወላጅ ጭንቅ በጭንቅ ሆነ። በተከታታይ በየአካባቢው በተደረጉ አፈሳዎች የተነሳ የግንኙነት መስመሮች ሁሉ ተበጣጠሱ፡፡ ቀይ ሽብር አገሩን አናወጠው የወላጅ እጣ ፈንታ በየእለቱ እዚህም እዛም የተጣለ የወጣት ሬሳ ማየት ሆነ ። ነፍሰጡር እናቶችም ሳይቀሩ የቀይሽብር ሰለባ ሆነው ዋይታ ከተማውን ሞላው። በከተማው ውስጥ ከሚንቀሳቀሱት መኪናዎች ውስጥ አንዳንዶቹ መንገድ ላይ የሚያገኙትን ወጣት ሁሉ እየለቃቀሙ ወደእስር ቤት መወርወር መደበኛ ሥራቸው ሆነ።

ዳኙና ፍሬሕይወት በመደበኛ ቀጠሮ መገናኘት ባለመቻላቸው ተለዋጭ ቀጠሮ መጠቀም ግድ ሆነ። የመጀመሪያዎቹን መታወቂያዎች ሰጥታው ሌሎች ተጨማሪ ፎቶዎች ሰጥቷታል። መታወቂያዎቹን ግን አልመለሰችለትም፤ መታወቂያዎቹ ደግሞ በጣም ይፈለጋሉ። የግዴታ አግኝታው መስጠት ይኖርታል።

በተለዋጭ ቀጠሮአቸው በመገናኘታቸው በጣም ደስ አላት። አክስቷ ቤት ከዚህ የበለጠ መቆየት አልነበረባትምና ተጨንቃለች። ስለሁኔታው ለዳኙ ነገረችው እርሷ ዘንድ ያለው ተስፋ መቁረጥ እርሱም ዘንድ አለ። ስትነግረው የተሰማውን ጭንቀት አስተውላለች፤ ሊያደርግላት የሚችለው ነገር እንደሌለ ሲገባት እርሷም የበለጠ ተረበሸች።

"አንድ ዕድል አለን" አላት ዳኙ ከብዙ ማሰብ በኋላ። ከአንድ ሰዓት በኋላ እንደገና ለመገናኘት ተቀጣጠሩና ተለያዩ። ሲለያዩ ዳኙን መልሳ እንደማታገኘው ተሰማት።

መቼም አማራጭ ሲጠፋ መጠጊያዋ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ አንድ ሰዓቱን ለማሳለፍ ልደታ ቤተክርስቲያን ገባች። ቁጭ ስትል እናቷን አሰበቻቸው። ቃለአብ ቤት እንደሚሄድ ስለነገራት ቢያንስ እስከዛሬ ደህና መሆኗን ይሰማሉ። ሁሉንም እናቶች አሰበቻቸው፡፡ የበላይሁን

እናት ሀዘን ከፊቷ አልጠፋም አላት፡፡ የአስቻለውን እናት ማሰብ ባትፈልግም ማስታወሷ ግድ ነው፡፡ እርሳቸውን ስታስታውስ መፈጠሯን ትጠላለች። ሰሞኑን ደግሞ ልትጠይቃቸው አልቻለችም። መንፈሷ ድቅቅ አለ፡፡ ሰዓቱ ደርሶ ዳኘን የምታገኝበት ጊዜ ናፍቋት ሰዓቷን በተደጋጋሚ ትመለከታለች። ሰዓቱ እንደምንም ብሎ ደረሰላት።

ዳኘ የመጣው ብቻውን አልነበረም። ከወጣትነት ብዙም ያልራቀ ቁመናው ረዘም ያለና በደንብ የለበሰ ሰው አብሮት አለ። ሁለቱንም ጨበጠቻቸው፡፡ ሰውዬው ታሪኩ ይባላል። ዳኘ ጊዜ አልወሰደም ታሪኩ ጊዜያዊ መጠለያ የሚሰጣት ሰው መሆኑን ነገራትና የሚቀጥለውን የቀጠሮ ጊዜ ተነጋግረው ትቷቸው ሄደ።

የታሪኩ ቤት ሩቅ አይደለም፡፡ ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት ያለው ሰፈር ውስጥ ነው የሚኖረው። ታሪኩን ተከትላ እየሄደች ለራሷ በጣም ገረማት "እንደመተማመን ምን ትልቅ ነገር አለ?" ያለ አንድ ጥያቄ ከማያውቁት ሰው ጋር ለመኖር በእምነት ተከትሎ መሄድ በእምነት እንጂ ሌላ ምን ምክንያት ሊገኝለት ይችላል፡፡

"ምነው ዝም አልሽ?" አላት ታሪኩ ጥቂት እንደሄዱ።

"እንግዳ አይደለሁ?" ነበር መልሷ።

"ምን እንግድነት አለ፡፡ ከዚህ በኋላ ከድሬዳዋ የመጣሽ ዘመዴ ነሽ" አላት። መስማማቷን በምልክት ገለጸችለት።

ቤት ሲደርሱ ማንም የለም። "ተቀመጪ" አላት ታሪኩ በሩን ከፍቶ እንደገቡ መብራቱን አብርቶ። አቅራቢያዋ ያገኘችው ወንበር ላይ ተቀመጠች። ንጹሕ ቤት ነው፡፡ ፈካ ያለው የግድግዳ ቀለም ከመብራቱ ጋር ተዳምሮ ቤቱን ድምቅ አድርጎታል፡፡ የዕቃዎቹ አዲስነትና ንጽሕና ደግሞ የአዲስ ሙሽራ ቤት አስመስሎታል። ግድግዳዎቹን ተዟዙራ ተመለከተች፤ ሆኖም አንድ እንኳን የጋብቻ ፎቶ ማየት አልቻለችም፡፡ በአንደኛው ግድግዳ ላይ ግን የታሪኩንና የአንዲት ወጣት ፎቶግራፍ ተመለከተች።



"ባለቤቴ ናት" አላት ታሪኩ ዓይኖቿን እየተከተለ እንደነበረ በሚገልጽ ሁኔታ።

"የት ሄደች?" አለችው።

"ትምህርት ቤት ሄዳ ነው አሁን ትመጣለች" አላት ሰዓቱን እየተመለከተ "እስክትመጣ ግን ሻይ ብንጠጣስ?" አለና ወደውስጥ ገባ።

ታሪኩ ወደውስጥ እንደገባ ባለቤቱ መጣች። ፍሬሕይወት ከተቀመጠችበት ተነስታ ሰላምታ ሰጠቻት።

"ጤና ይስጥልኝ መልካምሰው እባላለሁ" አለቻት።

ታሪኩ ድምጻቸውን ሲሰማ ወዲያውኑ መጣና ባለቤቱንና እንግዳዋን አስተዋወቃቸው።

"ግራ እንደገባሽ ይሰማኛል ሁኔታው ግን ለአንቺ እስከምነግር ጊዜ የሚሰጥ አልነበረምና ነው። ጊዜያዊ መጠለያ እንድንሰጣት በማስፈለጉ ነው አስቴር እኛ ቤት የመጣችው" አላት። "አስቴር" ፍሬሕይወት በመጠለያ ቤት የምትጠቀምበት ሥም ሆነ።

"እንኳን ደህና መጣሽ ቤትሽ ነው!" አለች መልካምሰው ።

መልካምሰው ልክ እንደስሟ መልካም ሴት ነች። ወዲያውኑ ለፍሬሕይወት የምትቀያይረው ልብስ ሰጠቻት። እግሯን ለመታጠብ የሚያስፈልጋትን ሁሉ አቀራረበችላትና "እንግድነት አይሰማሽ ልጄን ላምጣው" ብላት ወጣች።

የነታሪኩ ልጅ የአራት ዓመት ህፃን ነው። ሲመጣ አስቴር አክስቱ መሆኗ ተነገረው፡፡ በመጀመሪያ ለመቀበል አቅማማ "ለምን እስከዛሬ አልመጣችም?" አለና ጠየቀ።

"እማማ ያለችው ድሬዳዋ መሆኑን ታውቅ የለ?" አለው ታሪኩ።

"አውቃለሁ፤ ግን ታዲያ ለምን ከማማ ጋር አልመጣችም ነበር?" ተጨማሪ ማብራሪያ ጠየቀ።

"ያን ጊዜ ሥራ ነበራታ" አለችው እናቱ ቀበል አድርጋ።

በኋላ ላይ ተቀበለና መጫወት ጀመረ። የልጁ አነጋገርና ብስለት በጣም ደነቃት፡፡ ብዙ አነጋገሩ ከእርሱ የሚጠበቅ አይደለም፡፡ የሶሻሊስት መሪዎቹን ሥም በሚገባ ያውቃል። ሲያስቃትም ሲያስገርማትም አመሸ።

* * * *

ለፍሬሕይወት የነታሪኩ ቤት በጣም ተመችቷታል። የግቢው ሰው ሁሉ "ከድሬዳዋ የመጣች የታሪኩ ዘመድ" በማለት በጣም ተንከባከቧት። የእውነትም ዘመድ ለመምሰል ጊዜ አልወሰደባትም፤ የምትሄድበት ቦታ በሌላት ጊዜ መልካምሰውን ለማገዝ ያላት ፍላጎት፣ ሃላፊነት ወስዳ የመሥራቷ ሁኔታ፣ መልካምሰውም በሙሉ እምነት ቤቷን በኃላፊነት ሰጥታት የፈለገችበት ሄዳ መምጣቷ ዝምድናቸውን በጥርጣሬ ውስጥ ሊከት የሚችል አልነበረም። ታሪኩና መልካም የእውነትም የሥጋ ዘመዶቿ እየመሰሏት መጡ።

በአዲሱ ሰፈሯ ውስጥ እንደልቧ መንቀሳቀስ ትችላለች፡፡ ማንም ስለማያውቃት ለጊዜው ችግር የለባትም፤ ነገር ግን ስጋት አላት። በማንኛውም ሰዓት ማንም ሊያያት ይችላል፡፡ በተለይም በውስጣቸው በተከሰተው የመስመር ልዩነት ምክንያት የተፈጠረው መከፋፈል አደጋውን የበለጠ አስፍቶታል። እናም በሆነ አጋጣሚ የሚያውቃት አንጃ (ከፓርቲው በመስመር ልዩነት የወጣ ሰው) ቢኖር ሊጠቁምባትና ልትያዝ እንደምትችል እያሰበች ትሰጋለች።

ዳኙ በተገናኙ ቁጥር እንድትጠነቀቅ ይነግራታል፡፡ የተወሰኑ አንጃዎች ከመንግስት ጋር በግልጽ እየሠሩ መሆናቸውን መረጃ ይደርሳቸዋል። ደግሞም ማን መቼ የትኛውን ጎራ እንደሚቀላቀል መተንበይም አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ ሕይወታቸው በጥርጣሬ ተሞላ።



ፍሬሕይወትም በተመሳሳይ ጋዲሳን፣ ዘርዓይንና አዲሶቹን የኮሚቴ አባላት ማግኘትና ያላትን መረጃ ማስተላለፍ ይጠበቅባታል። ሁሉም በአንድነት ተገናኝተው የመወያየቱ ነገር የማይታሰብ ከሆነ ሰንብቷል፤ እናም የምታገኛቸው በተናጠል ነው። ሃላፊነቷን ለመወጣት የቻለችውን ከማድረግ ወደኋላ አትልም፤ እነርሱም እርሷን ማግኘታቸው የተስፋቸው ምንጭ በመሆኑ በናፍቆት ይጠብቋታል።

ጠዋት ከቤት ስትወጣ ከቃለአብ ጋር ቀጠሮ ነበራት፤ ሲገናኙ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልጋት ነገራት። በጣም የመረበሽ ስሜት አይታብታለች፤ ቃለአብን እያየችው የምታስበው ስለእናቷ ነበር።

"እማዬ እንዴት ትሆናለች?" አለችው ድንገት ከወሬአቸው ወጥታ።

"ፍሬ! እሱን ማሰብ አልፈልግም፤ ምንም መጨመርና መቀነስ ስለማልችል በተቻለኝ ሁሉ ላለማስታወስ እሞክራለሁ" አላት የበለጠ እየተረበሸ።

"በቻልከው አጋጣሚ ሁሉ ደውልላት፤ ቢያንስ በዚህ ልናግዛት እንችላለን" አለችው።

"ሁሉም የሚሆነው ከቆየን ነው፤ በየትኛዋ ደቂቃ ምን ሊሆን እንደሚችል ምንም መገመት አይቻልም" አላት ተስፋ መቁረጡን በሚያሳይ ሁኔታ።

"አይዞን!!" ከማለት ውጭ ማጽናኛ ቃላት አልነበራትም። ብዙም ሳይቆዩ ተለያዩ።

መሄድ ባትፈልግም ምርጫ ስላልነበራት ብቻ ወደመጠለያዋ ማዝገም ጀመረች። የሚቀጥለው ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል እያብሰለሰለች በእግሯ ልደታ ቤተክርስቲያን ደረሰች። እቤት ስትገባ የባሰ ነገር ጠበቃት፡፡ መልካምሰውና ልጁ አመድ መስለዋል፤ ገና ስታያት አንድ ችግር መፈጠሩ ገብቷተል።

"ታሪኩን ወሰዱት?" አለቻት መልካምን።

"አዎን" አለች መልካምሰው።

"ከየት?"

"ከመሥሪያ ቤት" አለችና የሆነ ብጣሽ ወረቀት እየሰጠቻት።

"ዳኙ ነው የሰጠኝ፤ እባክሽን ተጠንቀቂ! ማንን ማመን እንደሚቻል ግራ የሚያጋባ ጊዜ ነው" አለች መልካምሰው።

ዳኙና ታሪኩ ጓደኛሞች ናቸው፤ በጣም ግራ ሲገባው ነበር ታሪኩ ለፍሬሕይወት መጠለያ እንዲሰጣት በጓደኝነት የጠየቀውና የተስማማው። ሰሞኑን ታሪኩ ስጋት ውስጥ ስለነበረ ለፍሬሕይወት ሌላ ቦታ እንዲፈልግላት ነግሮት ነበር ለዳኙ። ያንን በማመቻቸት ላይ እያለ የታሪኩን መታሰር ሰማ፤ እናም አማራጭ አልነበረውም፤ ከፍሬሕይወት ጋር የነበረውን ቀጠሮ ለመጠበቅ ጊዜ የለውም ስለዚህ የተሻለውን አማራጭ ወሰደ፤ የመገናኛ ኮዱን ለፍሬሕይወት እንድትሰጥ ለመልካምሰው ሰጣት። በተፈጠረው ሁኔታ ምክንያት አንዳንድ አሠራሮች ከዲሲፕሊን ውጭ መሆናቸው ግድ ሆነ።

ፍሬሕይወት ወዲያውኑ መውጣት ነበረባት፤ ወዴት እንደምትሄድ ባታውቀውም መውጣቷ ግድ ነው። "ምሳሽን ብይ" አለች መልካምሰው ልጇን ወንበሩ ላይ እንዲቀመጥ እያደረገችው። ልጁ አንገቷን ይዞ አልለቅም አላት። ፍሬም ምግብ የመብላት ስሜት አልነበራትም።

"ምንም መብላት አልችልም፤ መልካም ደህና ሁኚ" አለች ለመውጣት እየተነሳች። ብትለምናትም በፍጹም ለመብላት አልሞከረችም። ልትወጣ ስትል ከጥግ በኩል የተቀመጠ ትንሽ የመንገድ ቦርሳ አንስታ ሰጠቻት። "መቀየሪያ ልብስ ያስፈልግሻል፡፡ ትንሽ ቆሎም አለበት። ለማንኛውም ያዥው" አለቻት መልካም። ተቀበለቻትና መልካምንና ልጇን ስማ ወጣች።

ለገሀር መኪና ተራ ስትደርስ ከቀኑ አሥር ሰዓት ሆነ፡፡ ለተሰጣት ቀጠሮ አሥር ደቂቃዎች ይቀራሉ። ተስፋና ጥንካሬ ከውስጧ ተሟጠው አልቀዋል፡፡ ከዛ በኋላ ስላለው ነገር ብዙም ጉዳይ አልነበራትም። የምታደርገውን ሁሉ የምታደርገው በደመነፍስ ነው።



"አዝመራውን ማን ይጠብቃል?" አላት አንድ ሰው መኪና ተራው ውስጥ ገብታ ጥቂት እንደቆመች።

"እረኞቹ!" አለችው ደንገጥ ብላ። ወንበር እንደተያዘላት ነገራትና ተከትላው ወደመኪናው ውስጥ ገባች።

መኪናው ሙሉ ነው፡፡ የሚጠብቀው የእሷን መምጣት ብቻ ነው። የተቀበላት ሰው "በጣም አመሰግናለሁ" ከማለቱ ሾፌሩ ሞተሩን አስነሳና ጉዞ ጀመረ። መኪናው የአውቶቡስ መናኸሪያውን ለቅቆ ሲወጣ ግንባሩን ወደቀኝ አዙሮ ስታዲየሙን አለፈና እንደገና ወደቀኝ በመታጠፍ በቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት በኩል አልፎ የናዝሬትን መንገድ ያዘ። አጠገቧ ያለውን ሰው ቀና ብላ ተመለከተች። "አይዞሽ" አላት።

ከኪሱ ውስጥ አንዲት ወረቀት አውጥቶ ሰጣት። ወረቀቱ ላይ የተጻፈው ሥሙና የአባቱ ሥም እንዲሁም የሚሄዱበት ቦታ ነው። "መታወቂያሽን ይዘሽዋል?" አለና ጠየቃት ወደ አቃቂ ሲቃረቡ። መያዟን ነገረችው። አዲሱ ጓደኛዋ ከተማ ይባላል፡፡ ጠንካራና ሙሉ ሰውነት ያለው ከወጣትነት ዕድሜ ክልል ያለፈ ሰው ነው።

አቃቂ ፍተሻው ላይ ሲደርሱ መኪናው ቆመና ሁሉም ለፍተሻ ወረዱ። እነርሱ ሲወርዱ አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ፈታሾች ወደመኪናው ገቡ። "እንዴት አደራችሁ ጓዶች!" አላቸው ከተማ ፈታሾቹን፤ ሞቅ ያለ ሰላምታ ሰጡት። ፈታሾቹ ከመኪናው ሲወርዱ ከተማ ፍሬሕይወትን አንገቷን አቀፍ አደረጋት፤ ፈታሾቹ እንዲያዩት መፈለጉ ስለገባት ጥግት ብላ ቆመች። "ጠጋ ጠጋ በለ" አለ ወንዱ ፈታሽ። ፍሬና ከተማ ጠጋ አሉ፡፡ ምንም ጥያቄ አልቀረበላትም፡፡ ሴቷ ፈታሽ የፍሬን መታወቂያ አየት አድርጋ መለሰችላትና እንደነገሩ ነካ አድርጋት አስገባቻት። ከተማ መታወቂያውን ለይስሙላ ያህል ወጣ አድርጎ ብቻ ነው የገባው። በፖለቲካ መዋቅሩ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ያለው ሰው መሆኑን የሰማችው በኋላ ነው፡፡

አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን ዱብረዘይት ደረሱ፡፡ ከአውቶቡሱ የወረዱት መኪናው መናኸሪያ ከመድረሱ በፊት ነው።

"እንሻገር?" አላት ከተማ።

"እሺ" አለች ቦርሳዋን እያነገተች።

ከተማ የያዘው ሳምሶናይት ቦርሳ ብቻ ነው፡፡ ተጨማሪ ጓዝ የለውም። "አይዞሽ እሺ?" አላት ለሁለተኛ ጊዜ። እሺታዋን በምልክት አሳየችው። የከተማ ቤት ከዋናው መንገድ ምንም ያህል አይርቅም። ጥቂት እንደተራመዱ አንድ የቆርቆሮ በር አንኳኳ። አንዲት ሴት በሩን ከፈተችላቸውና ገቡ።

"ተዋወቂያት እስቴር ማለት እርሷ ናት" አለና አስተዋወቃቸው።

"አመለ እባላለሁ" አለችና ጨበጠቻት። ተከታትለውም ወደቤት ገቡ።

የተጋነነ ባይሆንም የቤቱ ይዘት ጥሩ የሚባል ነው፡፡ በተለይ በግርግዳዎቹ ላይ የተሰቀሉት የስፌት ዓይነቶች የአመለን ሙያ ያመላክታሉ። የቤቱ ወለል እንደ አዲስ አበባ ቤቶች አያብረቀርቅ እንጂ ሳንቃ ነው። ግድግዳዎቹም ቀለም ተቀብተዋል። ሶፋ መሰል መቀመጫዎቹ በዳንቴል እጅ ሥራዎች ያጌጡ ናቸው።

"አትፍሪ አመለ የምትለመድ ጥሩ ሴት ነች" አላት።

"እሺ" አለችው ባጭሩ። በውስጧ የሚመላለሰው ሌላ ሀሳብ ነው፡፡ እንዴትና ምን እንደምትሠራ ምን ዓይነት ሰዎች ሊገጥሟት እንደሚችሉ ነበር የምታሰላስለው።

"ነገ የምታገኛቸው ሰዎች ይኖራሉ፤ እዚህ የምትቆይው ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነና የሚቀጥለው እንቅስቃሴ ምን ሊሆን እንደሚችል የምትነጋገሪው ከእነርሱ ጋር ይሆናል። እስከዚያው ግን ቤታችንን እንደቤትሽ ልትቆጥሪው ትችያለሽ" አላት ከተማ።

አመለ የቡና ዕቃዎቿን እንዳቀራረበች "ነይ ግቢ ልብሶችሽን ቀያይሪና ዘና በይ" ብላ ወደውስጥ አስገባቻት። የምትተኛበትን



ክፍል አዘጋጅታ በምትችለው ሁሉ እንዲመቻት ለማድረግ ጥረት አድርጋለች።

"እንግዲህ እንደ አዲስ አበባ ባይሆንም..." አለች የምታርፍበትን ክፍል እያሳየቻት።

"ምን ልዩነት አለው ብለሽ ነው፡፡ በጣም ቆንጆ ነው" አለቻት፤ ከልቧ ነበር።

"ብርድ ስለሆነ ሞቅ ያለ ልብስ ያስፈልግሻል" አለችና ጋቢ ሰጠቻት።

ከልጆቹ ጋር ወዲያውኑ ነው ቤተኛ የሆነችው፤ ትልቋ ልጃቸው አስር ዓመት ሲሆናት ትንሹ ደግሞ ሰባት ይሆነዋል። ለመላመድ ጊዜ አልወሰደባቸውም ወዲያውኑ አብረዋት መጫወት ጀመሩ።

በማግስቱ ከተማ የመገናኛ ኮድ ሰጣትና ከተባለው ሰው ጋር ተገናኘች። ያገኘችው ሰው በጣም የተጎሳቆለ ከመሆኑ የተነሳ ዕድሜውን መገመት ያስቸግራል። ሲራመድም ሆነ ሲናገር በጣም ፈጣን ነው፡፡ ጎድጓዳ ዐይኖቹ እረፍት የላቸውም፡፡ አንድ ቦታ ላይ አያቆያቸውም።

"ሁኔታዎች ጥሩ አይደሉም፡፡ ሰሞኑን የተላኩት ጓዶችም መንገድ ተቆርጦባቸው ከሌሎቹ ጋር መቀላቀል አልቻሉም። አንቺንም ለመላክ ሁኔታውን ማረጋገጥ ያስፈልገናል። ሁሉንም ነገር የማሳውቅሽ በስልክ ይሆናል።" አላትና ወዲያውኑ ተለያዩ።

የበለጠ ግራ ገብቷት ወደቤት ተመለሰች።
ከተማ ማታ ከሥራ ሲመጣ "ተገናኛችሁ?" አለና ጠየቃት ፍሬን።

"ተገናኘን ግን..." አለችና አቋረጠችው።

"ሁኔታዎች በጣም እየተባባሱ ናቸው፡፡ አንጃዎቹ ብዙ መረጃ ለመንግስት እየሰጡ በመሆናቸው መንቀሳቀስ ከባድ እየሆነ ነው። እንደሚሰማው ከሆነም ከዚህ በኋላ ምንም እንቅስቃሴ ማድረግ የሚቻል አይመስልም" አላት ከተማ ሃዘን ፊቱ ላይ እጥልቶበት።

የስልክ መልዕክቱን ከመጠበቅ በስተቀር ምንም አማራጭ አልነበራትም። ሁኔታው የሚፈቅድ ቢሆን እስከወዲያኛው እዚሁ ቤት ብትቆይም ደስ ይላት ነበር። የእንግድነት ስሜቷ የለቀቃት ወዲያውኑ ነው፤ ከከተማ ቤተሰብ ጋር ተላመደች። አመለንም ከተማ ካለው በላይ እጅግ ጥሩ ሰው ሆና አገኘቻት። የአካባቢው ሰውም የሚያውቀው የአመለ ዘመድ መሆኗን ነው።

እናቷን አልፎ አልፎ ስልክ እየደወለች አገኝታቸዋለች፡፡ በጣም የደነቃት እናቷ የት እንዳለች አለመጠየቃቸው ነው። የሰፈራቸው ሁኔታ በጣም እየተባባሰ መሆኑን ይነግሯታል። "ፍርዬ የትም ሁኝ ግን ድምጽሽን ብቻ አሰሚኝ" ይሏታል የስልክ ንግግራቸውን ሲጨርሱ።

እነከተማ ቤት ከመጣች አስራ አምስት ቀናት አለፉ፤ ነገር ግን ከማንም ጋር መገናኘት አልቻለችም። ከተማንም በየዕለቱ ግራ መጋባቱ ሲጨምር አስተዋለችው፡፡ እርሱም ሁኔታዎች ጥሩ ያለመሆናቸውን ይነግራታል። ሁኔታው ከሚያሳስባትና መጨረሻው ከሚናፍቃት በስተቀር ኑሮ በጣም ተመችቷታል።

"በዚህ ሁኔታ የምቆየው ግን እስከመቼ ነው?" ትላለች ለራሷ።

* * * *

አንተነህ ቤተሰቦቹ ዘንድ ከደረሰ ጥቂት ወራት ተቆጠሩ። እንደመጣ ሰሞን ናፍቆት የነበረ የቤተሰብ ጨዋታና ሳቅ ብዙውን ሀሳቡን አስረስቶት ነበር። ለቤተሰቦቹ የመጣበትን ሁኔታ በደፈናው ነገራቸውና እዚያ መቆየቱ ችግር እንደማይኖረው ገለጹለት፤ ደስ አለው። ብዙም ሳይቆይ መታወቂያ ወጣለትና ሕጋዊ ነዋሪነቱን አረጋገጠ።
አንተነህ በአባቱ አነስተኛ የልብስ ሱቅ ውስጥ መዋል ጀመረ። ምንም ጊዜ ሳይወስድበት ልብስ ስፌት በሚገባ ቻለና ሰፊዎቹ ወጣ ሲሉ ተክቶ መስራቱን ተላመደው። ለደንበኞች የነበረው አቀባበል የአካባቢውን ሰው ሁሉ ወደ ሱቁ ሳበ፤ አባቱ በጣም ተደሰቱ። ቀኑን በሥራው የሚዘነጋው ሀሳብ ግን ማታ ይጠብቀዋል፤ ሀሳቡን ለመርሳት ያነባል። እያነበበ ግን ያስባል፤ ብዙ ነገር ያስጨንቀዋል፤ መንፈሱ ይበተናል። አንተነህ ሁልጊዜም ጆሮው እውጭ ነው፤ ሁኔታዎችን ነቅቶ ይከታተላል። አዲስ አበባ ያለውን ሁኔታ ለመስማት የተቻለውን ጥረት ያደርጋል። ስጋት ተለይቶት አያውቅም፤ መቋጫው ግን ፍሬሕይወት ነች። "እንዴት ሆና ይሆን?" ይላል ሁል ጊዜ።

አንዳንዴ እንቅልፍ አልወስድ እያለው ይቸገራል፤ እናም ቀስ ብሎ ይወጣና ጊቢው ውስጥ ይንጎራደዳል። እናቱ ብዙ ጊዜ ተመልክተውት አሳስቧቸዋል፤ እንዲያውም ይጠብቁትም ጀምረዋል። አንድ ቀን ታዲያ ጭንቅ ቢላቸው ለባለቤታቸው አማከሯቸው።

"ኧረ ይሄ ልጅ የሚያሳስበው ነገር ያለ ይመስለኛል" አሏቸው

"እያስብ ነው የምትይው ታዲያ፤ በዚህ ዕድሜው እዚህ ከእኛ ጋር ቁጭ ማለቱ ብቻ አያሳስበውም ብለሽ ነው?" አሉ አባቱ።

"ታዲያ መጨረሻው ምን ሊሆን ነው?" አሉ እርሳቸውም ሀሳብ እየገባቸው።

"እኔማ ይህንን ንግድ ሰፋ አድርጎ እንዲሠራበት አለያም ሌላ ያሻውን ሥራ እንዲጀምር እያሰብኩ ነው" አሉ አባቱ እርሳቸውንም እንዳሳሰባቸው በመግለጽ።

እናቱ ይህንን ሀሳባቸውን ሊገልጹለት ተስማሙ። "ልጄ እንቅልፍ እምቢ ይልሀል ልበል?" አሉት አንድ ጠዋት እንደተለመደው እንቅልፍ እምቢ ብሎት እስከ እኩለ ሌሊት ተቀምጦ እንደነበረ አስተውለው።

"ማንበብ ስለምፈልግ ነው እማማ" አላቸው

"ይህን ያህል መረዳት ያቅታታል ብለህ ነው? ማንበብ ስትፈልግማ ምን እንደምታደርግ አውቃለሁ፤ እዚህ መጥተህ መቀመጥህ አሳስቦህ ከሆነ መፍትሄ አለው፤ አባትህ ንግዱን ሰፋ እንድታደርገው ወይንም የፈለግከውን ሥራ እንድትጀምር አስበዋል" አሉት

"ምን አሳሰባችሁ እማማ? እኔኮ ምንም አልሆንኩም" አላቸው

"ልጄ ወላጆችህ እኮ ነን ምን አስጨነቀህ? ትምህርቱ እንደሆን ቀን ሲያልፍ የትም አያመልጥህም ትደርስበታለህ" አሉት።

አንተነህ አንድ ሀሳብ በአእምሮው ውስጥ ብልጭ አለበት። "እስኪ ላስብበት" አላቸው በደፈናው።

ሌሊቱን ከሀሳቡ ጋር ሲነጋገር አደረ፤ እንቅልፍ የሚባል ሳይወስደው ፍሬሕይወትን እንዳሰበና እንደተጨነቀ ነጋለት። አንድ ቀን ወደቤተሰቦቹ እንደመጣ ስልክ ደውሎ ነበር ግን አላገኛትም። ደጋግሞ መደወሉን አልወደደውም። ዛሬ ግን ሊደውልላትና ቁርጡን ሊያውቅ ወሰነ፤ እንድትመጣና አብረው እንዲኖሩ ተመኘ።

ጠዋት ስልክ ቤቱ እስኪከፈት መቆየት አቅቶት ሳይከፈት ነው የደረሰው፤ ስልከኛዋ ገብታ ሥራ እስክትጀምር፣ መዝግባለትና መስመሩን አግኝታ እስክትጠራው ድረስ ተቁነጠነጠ፤ ገና ሲጠራ እንዴት ተፈናጥሮ እንደተነሳ ለራሱም ገረመው። የስልኩን መነጋገሪያ ሲያነሳ እጁ ተንቀጠቀጠበት

"ሄሎ" አሉ ከወዲያኛው ጫፍ ስልኩን ያነሱት ሴት።

"እባክዎትን ከጎረቤት ፍሬሕይወትን ፈልጌ ነው" አላቸው ድምጹ እንደመንቀጥቀጥ እያደረገው።

"ፍሬሕይወት የለችም" አሉት ሴትዮዋ ጥርጣሬ ባዘለ አነጋገር።

"እባክዎን ከሩቅ ነው የምደውለው ምን ባደርግ ይሻለኛል?" አለ በማስተዛዘን።

"ፍሬሕይወት የት እንዳለች እኛም አናውቅም" አሉት።

"እባክዎትን ለጥብቅ ጉዳዳይ ነው የምፈልጋት" አለ አንተነህ። "እንግዲህ ከዚህ በላይ ምንም ማለት አልችልም፤ ፍሬሕይወትን በዚህ ስልክ አታገኛትም" አሉና እቅጩን ነገሩት ሴትዮዋ።



ምን ብሏቸው ስልኩን እንደዘጋው እንኳን አላስታወሰም ብቻ ስልኩን ዘግቶ እንባው እየተናነቀው ከመነጋገሪያው ወጣ። ተስፋው ተሟጠጠበት፤ የሚጠብቀው ነገር መሆኑን ልቡናው ቢያውቀውም መቀበል አቃተው። "ፍሬሕይወት ምን ሆና ይሆን? ታስራ ይሆን? ወይስ…" ሞትን በፍጹም ሊያስበው አልፈለገም። ዐይኖቹን ጨፈናቸው፤ ላለማሰብ አእምሮውንም ቢያስቆመው በጣም ፈለገ፤ ነገር ግን አእምሮው የሚያስተጋባው ይህንኑ ብቻ ሆነበት።

ከስልክ ቤት ሲመለስ በድምጽ ማጉያ የስብሰባ ጥሪ ሲለፈፍ ሰማ። ተናጋሪው ሁሉም ሰው ለስብሰባው በነቂስ እንዲወጣ ይቀሰቅሳል። አንተነህ የሆነ ነገር በሀሳቡ ሽው አለበት። በቀስታ እየተራመደ ሰውየውን ጠበቀውና "ስብሰባው ስለምንድነው?" አለው

"አናርኪስቶችን የማጋለጥ ስብሰባ ነው፤ አካባቢው የአናርኪስቱ የኢሕአፓ ምሽግ እየሆነ ነው፤ ማጋለጥ አለብን እየተባለ ነው" አለውና ቅስቀሳውን ቀጠለ።

አንተነህ ሁኔታው አላማረውም፤ ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰላሰለ ቤት ደረሰ። እቤት ሲደርስ እናቱ "ጎሽ! መጣህ?" አሉት

"ምነው?" አላቸው፤ ምን እንዳሳሰባቸው ገብቶታል።

"በል እናቱ ሰብሰብ በል፤ ይህ ልጅ ጠንቀቅ ቢል ይሻላል ከሌላ ቦታ የመጡ ሰዎች ላይ ትኩረት እንዲደረግ ትዕዛዝ መጥቷል የሚል ነገር ስለሰማሁ ነው" አሉት።

አባቱም ያለወትሮአቸው ፊጠን ብለው ቤት መጡና ይህንን ተናገሩ። "ለተወሰነ ጊዜ ወጣ ብሎ ዘመድ ጋ ቢሄድስ?" አሉ እናቱ።

አንተነህ ሳያቅማማ ተስማማላቸው፤ አባቱም በመስማማት ተደስተው ሀሳባቸውን አደላድለው ወጡ። አንተነህ የራሱን ዕቅድ ነደፈ፤ ማስታወሻ ጽፎ በቀላሉ ሊታይ የሚችልበት ቦታ አስቀመጠና በሌሊት መንገዱን ቀጠለ፤ ወደዘመድ ሳይሆን ወደስደት።

ረፋዱ ላይ ገዋኔ ገባ፤ ወዲያውኑ በለስ ቀንቶት መኪና አገኘና ወደ አፋር አቀና። አዲስ መታወቂያ ስለያዘ ልቡ ሙሉ ነው፤ በዚያ ላይ ተስፋ መቁረጥ አደንድኖታል። አስራአንድ ሰዓት አካባቢ ዱብቲ የምትባለው ከተማ ደረሰ። ዱብቲ በአፋር ውስጥ ካሉ ከሚባሉት ከተሞች አንዷ ነች።

እንተነህ የተሳፈረበት አውቶቡስ ጎማዎቹ በአሸዋው ላይ ሲሽከረከሩ በሚያስነሱት አቧራ አካባቢውን እያለበሰውና ረጅም ጡሩምባውን እያሰማ ወደ መቆሚያው ተጠጋ። ገና ቆም ሲል ተሳፋሪዎቹ ለመውረድ ተነስተው ቆሙ፤ አንዳንዱ ያፋሽጋል ሌላው ዐይኖቹን ያሻል። እንተነህ ብቻ ከተቀመጠበት አልተነሳም፤ በመኪናው መስኮት አሻግሮ እየተመለከተ በሀሳብ ርቆ ሄዷል። ያደረገውን ኮፍያ ከራሱ ላይ ብድግ አደረገና እራሱን በእጁ አሻሸው፤ ከግንባሩ አካባቢ ጠረግ ሲያደርግ ሻከረው፤ ላቡ የፈጠረው ጨው ነው። ኮፍያውን መልሶ አደረገውና ከተቀመጠበት ተነሳ። ትንሽ የመንገድ ቦርሳውን አነገተና ከአውቶቡሱ ወረደ፤ ወዴት እንደሚሄድ ግራ ገብቶታል፤ በአካባቢው ሊታደርበት የሚችል ሆቴል መኖሩንም ተጠራጠረ።

ከመንገዱ ግራና ቀኝ የሚታዩት ቤቶች በጭራሽ ቤት አይመስሉም፤ የተከፈቱት ደጃፎቻቸው በጉብታ ላይ የሚታዩ ፉካዎች እንጂ ታስበው የተሠሩ በሮች አይመስሉም። ሁሉ ነገር አቧራ የዋጠው ነው፤ ግድግዳውም ጣሪያውም፣ ወለሉም ውጭውና ውስጡም፣ ሁሉም ነገር አፈር ነው፤ የአፈር ቤት! ከአውቶቡሱ ወርዶ እንደቆመ ላቡ በግንባሩና በአንገቱ ተንቆረቆረ፤ በጀርባው መሀል ቁልቁል ውሃ የተለቀቀበት ይመስል ላቡ ሲወርድ ተሰማው።

ወደአንደኛው ቤት ተጠጋና "አልቤርጎ የት አገኝ ይሆን?" ብሎ ጠየቀ።

"ምን አልቤርጎ አለ ብለህ ነው፤ ሁሉ እውጭ ነው የሚያድረው። እስኪ ወደዚያ ምናልባት ካለ ጠይቅ" አሉት የጠየቃቸው ሴት በእጃቸው እየመላከቱ።

ያሳዩትን አቅጣጫ ተከትሎ ጥቂት እንደሄደ የተሻሉ ቤቶች ተመለከተ። ብዙም ሳይርቅ አልጋ መኖሩ ተነገረውና ገባ። ግቢው



የተስተካከለ የቤት ወለል ይመስላል፤ እንተነህ ንጽሕናውን አደነቀ። ምንጣፎቻቸውን ዘርግተው የተቀመጡት በርካታ ሰዎች በየራሳቸው ጨዋታ ተመስጠዋል። ሰዎቹን አልፎአቸው ወደውስጥ ገባ። ራት የመብላት ፍላጎት የለውም፤ ምሳውንም እንደነገሩ ቀመሰ እንጂ አልበላም። የእንተነህ ምግብ ሀሳብ ከሆነ ሰንብቷል።

ያገኘው ማደሪያ ይህ ነው የሚባል ባይሆንም ግድ አልነበረውም፤ እንደነገሩ የተነጠፈው አልጋ ላይ ዘፍ አለና ተቀመጠ። እክፍሉ ውስጥ አየር እንዳይኖር ታስቦ የተሠራ እስኪመስለው ድረስ አየር አጠረው፤ የክፍሉ ሙቀት አያድርስ ነው። ውሃ ጥም ድብን አደረገው፤ የሚጠጣ ነገር ለመፈለግ ወጣና ቀዝቃዛ አምቦውሃ እንዲመጣለት አዞ ተመልሶ ወደክፍሉ ገብቶ ተቀመጠ።

"እንዴ! ክፍል ውስጥ እኮ ማንም አይቀመጥም፤ በጣም ይሞቃል" አለችው ቀዝቃዛ አምቦውሀ ያመጣችለት ልጅ።

"ታዲያ የት ነው የሚታደረው?" አላት ልጅቱን።

"እውጭ ነዋ! ሁሉም ሰው እውጭ ነው የሚያድረው። ፍራሹን ማውጣት ይቻላል" አለችው።

እንተነህ ፍራሹ ወጣለትና ከሰው ተቀላቀለ። የተቀላቀለው ግን በአካል ብቻ ነው። ውጭው ተመቸው፤ ፍራሹ ላይ ተንጋሎ ገደብ የሌለውን ሰማይ ሽቅብ እየተመለከተ ቀስ በቀስ በሀሳቡ ከአካባቢው ተለይቶ ወደምናቡ ዓለም ገባ። ከዓይነህሊናው ርቃ የማታውቀውን የፍሬሕይወትን ምስል በሰፊው ሰማይ ላይ ይመለከተው ጀመር። የልቡ ዝማሬ የሆነውን ፍቅሯን በተደጋጋሚ አሰበው። ደግሞ ሌሎቹን አስታወሰ፤ ሔዋን ይህን ጊዜ የት ትሆን? ወደውጭ እንድትሄድ ቤተሰቦቿ እየመቻቹላት እንደነበረና እርሷ ግን ገና ያለመወሰኗን ነበረ በመጨረሻ ሲገናኙ የነገረችው፤ ተስማምታ ሄዳ ይሆን? የት ይሆን የሄደችው? ደግሞ ሌሎቹን አሰባቸው፤ እንደርሱው ቆስለው የነበሩ ወጣቶች እንዴት ሆነው ይሆን? የተፈጠረው ክፍፍልስ... አፈሳውስ... ፍሬሕይወት በአሁኑ ሰዓት በምን ሁኔታ ውስጥ ትሆን? በተለያዩበት ሰዓት ገጽታዋ ላይ የነበረውን ሃዘንና በጉንጮቿ ላይ የወረደውን እንባ፣ እራሷን ለመቆጣጠር ያደረገችው ጥረት... እያንዳንዱን ነገር

አስታወሰ? ፍሬሕይወትን መርሳት ይችል ይሆን? እንባው ዐይኖቹን አቃጠላቸው፤ እንዲወርድና የተወጣጠረ ስሜቱን እንዲያስተነፍስለት ፈለገ፤ እንባውን አልገደበውም። በጀርባው እንደተኛ እንባው ቁልቁል በጆሮዎቹ ወረደ…

“ማን ያውቃል?” አለ ደግሞ ለራሱ “ማን ያውቃል መገናኘት ብንችልስ?” ከልቡ ተመኘ። ደግሞ ጉዞውን አሰበው፤ መረጃውን እንዴት እንደሚያገኝ፤ በምን ሁኔታ አሁን ካለበት ተነስቶ የኢትዮጵያን ድንበር ተሻግሮ ጅቡቲ እንደሚገባ አንድ በአንድ አውጠነጠነው። አዎ! ሲነጋ ያችን አምቦውሀ ያመጣችለትን ልጅ ይጠይቃታል። አዲስ አበባ እያለ ከዱብቲ ወደአፋር መሻገር ብዙ አስቸጋሪ ያለመሆኑን ሰምቷል፤ ግን አሁንም እንደዛ ይሆን? ባይሆንስ ምን አማራጭ አለው? መሞከር አለበት።

የማያውቃቸውን ድንበር አሻጋሪዎች በዐይነህሊናው ሳላቸው፤ ሸርጡን አገልድሞ ከግመሎቹ ጀርባ ልክ እንደአካባቢው ሰዎች በረጅሙ መፋቂያ ጥርሱን እየፋቀ ሲጓዝ ታየው። “ግን ስንት ሰዓት ይሆን የሚወስደው? ምን ያህል ገንዘብስ ይጠይቁት ይሆን? ያለውን ይሰጣቸዋል፤ መቼስ ከሌለው ምን አድርግ ይሉታል? “መቼም ድንበር ተሻግሮ ወጥቶ በሰው አገር ምቾት መጠበቅ አይቻልም … ቢሆንም አሁን ካለበት የስጋት ሕይወት የስደት ኑሮ መኖር ሳይሻል አይቀርም፤ ዋናው ጥያቄ በሕይወት መቆየት ነው፤ ከዚያ በኋላ… ማን ያውቃል?”

* * * *

ፍሬሕይወት “እስከመቼ ይሆን?” ለሚለው ጥያቄዋ መልስ እስከምታገኝ ድረስ እነከተማ ቤት መኖር አለባት። ተስፋ መቁረጥ ደግሞ ለማንበብ ያላትን ስሜት ገድሎባታል። አሁን አሁን የሚያስደስታት ነገር ቢኖር ከከተማ ልጆች ጋር መጫወት ነው። እነርሱ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ደግሞ ለራሷ ሥራ ፈጠረች፤ ሹራብ መሥራት።

ስትሠራ በጣም ፈጣን ነች፤ በጥቂት ቀናት ውስጥ ለትልቋ ልጅ ሠርታ ጨረሰችና ለትንሹ ልጅ ጀመረችለት። የሹራብ ሥራውን መደበኛ አደረገችው። አንድ ቀን ከተማ የምሳ ሰዓት ሳይደርስ



እየተጣደፈ መጣ። አመጣጡ አላማራትም፤ እየሠራች የነበረውን ሹራብ አስቀመጠች። ችግር መኖሩን እስኪነግራት አልጠበቀችም፤ ወዲያውኑ ተረድታዋለች። በመጣች በማግስቱ ካገኘችው ሰውዬ አነጋገር ብዙም ሳይቆይ የሆነ ነገር እንደሚከሰት እየጠበቀች ነበረ። “አዲስ አበባ መመለስሽ ግድ ሆኗል” አላት ከተማ ገና ቤት እንደገባ ወደመኝታ ቤት ጠርቷት። አዲስ አበባ ሄዳ የምትገናኝበትን ኮድ ሰጣት፤ ይህ ገንዘብ ለምታገኝው ሰው የሚሰጥ ነው፤ ከአካባቢያቸው እንዲወጡ የመጨረሻ ሙከራ የሚደረግላቸው ጓዶች አሉ ይህ የእነርሱ ፎቶ ነው። ምናልባት በመጀመሪያው ቀጠሮ ባታገኝው በድጋሚ መሄድ ይኖርብሽ ይሆናል። መልካም ዕድል ይግጠምሽ” አላት ገንዘቡንና የተጠቀለሉ ፎቶዎች እየሰጣት።

ትንሿን የመንገድ ቦርሳዋን አነሳችና ለጉዞ ተዘጋጀች። አመለ በጣም ተደናገጠች፡፡ የከተማ ሁኔታ ግራ ሲያጋባት ፍሬሕይወት ደግሞ አሳዘነቻት። “ደህና ሁኑ” አለቻቸው አመለንና ከተማን።

“መልካም ዕድል” አሏት ሁለቱም ለስንብት እየሳሟት። ልጆቻቸውን ሳታገኛቸው በመሄዷ ቅር ቢላትም አማራጭ አልነበረምና ሳትሰናበታቸው ወጣች።

እንደቀፈፋት ወደ አውቶቡስ ተራ ሄደች፡፡ በሞላ መኪና ተሳፍራ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰች። አዲስ አበባ ስትደርስ የቀጠሮ ሰዓቷ ሊሞላ ጥቂት ደቂቃዎች ቀርተዋል። ለገሀር ከመኪና ወርዳ በቀስታ እየተራመደች ኢትዮጵያ ቀይመስቀል ማህበር ስትደርስ ቆመች። ከቀጠሮ ሰዓታቸው አምስት ደቂቃዎች አለፉ። የምትጠብቀው ሰው አልመጣም፡፡ ብዙ መጠበቅም የለባትም በሚቀጥለው ቀን በዚሁ ሰዓት ተመልሳ መምጣት ነው ያለባት።

በኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና በጋንዲ ሆስፒታል መሀል ያለው መንገድ ቡላ ኩምቢ ቮክስ ዋገን መኪና መቆሙን ተመለከተች፡፡ እነዛ መኪናዎች የሚፈለጉ ሰዎችን ከየመንገዱ ለማፈን መሰማራታቸውን በሚገባ ታውቃለች። ነገሩ ያበቃ መሆኑ ቢሰማትም መሞከር ነበረባት፤ እናም መንገዱን ለማቋረጥ ራመድ ስትል የመኪናው በር ተከፈተ፡፡ የመሳሪያ መንቀጫቀጭ ድምጽም ተሰማት “ቁሚ!” የሚል ከፍ ያለ ድምጽ ተከተለ ቆመች። ደቂቃ ሳይሞላ ወጠምሻ እጆች

እያላተሙ ወደመኪናው ወሰዷት። በስርአት እስክትገባ አልጠበቋትም ገፋታትረው አስገቧት፡፡ ተንደፋደፋ ቀና ስትል ከዳኙ ጋር ዓይን ለዓይን ተገጣጠሙ፡፡ ሁሉም ማክተሙ ገባት።

ዳኙ ፀጉሩ ተንጨባሯል፣ ጉንጮቹ፣ ዐይኖቹና ግንባሩም ቊምር አባብጧል፣ የለበሰው ካናቴራ ከትከሻው ላይ ተቀዳዷል፣ እጆቹ የኋሊት ታስረዋል። ፍሬሕይወትን ለማስቀመጥ ጠጋ ሲል ፊቱ ላይ ያየችው የስቃይ ምልክት ዐይኖቿ ሁለመናውን እንዲቃኙ አደረጋቸውና ከላይ እስከታች ተመለከተችው፤ እግሮቹ ላይ ስትደርስ ያየችውን ማመን አቃታት። እግሮቹ እንደፊኛ ተነፍተዋል፡፡ እግር እንዲህ ያብጣል ብላ እስከማትገምትበት ድረስ ከመወጠራቸው የተነሳ ያብረቀርቃሉ አንዳች ነገር ነካ ቢያደርጋቸው እንደሚፈነዱ አሰበች።

ከዳኙ ጋር መኪናው ውስጥ ያለው ሌላው ወጣት ደግሞ ፊቱ የገረጣ፣ ጺሙ ያደገና ፀጉሩን የተላጨ ነው። የግንባሩ መቋጠር የውስጥ ንዴቱን ያሳብቃል፡፡ የለበሰው ያረጀ ጃኬት አንገቱ ድረስ ተቆልፏል፡፡ እጆቹ ብቻ ሳይሆኑ እግሮቹም ታስረዋል፡፡ ቦታ ለመስጠት ጠጋ ለማለት ሲሞክር እግሮቹ ላይ ያለው የእግር ብረት ተቅጨለጨለ።

የታጎሩበት ኩምቢ ቮክስ ዋገን መኪና በሀራምቤ ሆቴል በር አልፎ የመከላከያ በር ትይዩ ሲደርስ ጋቢና የተቀመጠው ሰውዬ ዞር አለና ተመለከተ "ደግሞ ቂጬ ብላ ትቁለጨለጫለች እንዴ አስተኛት! ሽርሙጣ!" ብሎ ጮኸ። ሰውዬው ገና በወጣትነት ክልል ያለ ቢሆንም የቆራጭ ፈላጭነት ስልጣኑን በየእያንዳንዱ ድርጊቱ ስለሚገልጽ ሁሉም እንዲፈሩትና እንዲሽቆጠቆጥለት ያደረገ ይመስላል። የቀሉ ዓይኖቹን በተናገረ ቁጥር ያጉረጠርጣቸዋል። ያለማቋረጥ ሲጋራ የሚምግባቸው ወፈፍራም ከንፈሮቹ ጠቁረውና ደርቀው ኩበት ይመስላሉ። "አስቀያሚ!" አለች በሆዷ።

የሰውዬውን ትዕዛዝ ለመቀበል የተጉ ወጠምሻ እጆች ማጅራቷን ጨምድደው ከወንበሩ ስር ሸንጧት፡፡ ትልቅ እግር ትከሻዋ ላይ ሲያርፍ ተሰማት። መኪናው ውስጥ ከገባች ጀምሮ ምንም ያልተናገረች ቢሆንም ይህንን ግን ዝም ብላ ማለፍ አልቻለችም። "እንዴ..."ብላ ገና ለመናገር ስትጀምር የሰደፍ ጡጫ አቋረጣት።



መኪናው በዋናው ፖስታ ቤት ታጥፎ ወደፒያሳ ማቅናቱ ታውቋታል፡፡ ሌላውን ለመርሳትና ወደየት እየተወሰደች እንደሆነ ለመገመት የመኪናውን አቅጣጫ ለመከተል ሞከረች፡፡ ወደጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የሄደ መሰላት ከዛ ቁልቁል የመርካቶን መንገድ እንደያዘ ገመተች ወዲያው ግን ወደቀኝ የታጠፈ መሰላት...
እላይዋ የተጫነው ከባድ እግር ረገጥ አደረጋትና "ሳትደርስ ሞተች እንዴ" አለ የረገጣት ሰው።

"ጥይት ከምታባክንብን ብትሞት አይሻልም ብለህ ነው" አለ ጋቢና የተቀመጠው የሚያስጠላት ሰውዬ። በውስጧ ድብን አለች፡፡ እየተከታተለች የነበረውን የመኪናውን አቅጣጫም አስጠፋባት። ወዴት እንደሄዱ መገመት ባትችልም የብረት መዝጊያ ሲከፈት ተሰማት፡፡ መኪናው ወደውስጥ ገብቶ እንደቆመ ጭኖባት በነበረው እግሩ ረገጥ አድርጓት ሰውየው ወረደ። እናም ከተደፋችበት የመኪና ወለል ላይ ቀና አለች፤ ከዚያ እግሩንና እጁን ከታሰረው ልጅ ጋር ዐይን ለይን ተጋጩ፡፡ ከንፈሮቹ ሲንቀሳቀሱ ተመለከተች "አይዞሽ"ያላት መሰላት። ከመኪናው አውርደው እያዳፉ ሲወስዱት ዐዓይኖቹ እንደሚከተሏትና ብርታት እንድታገኝ እንደሚመኙላት እርግጠኛ ነበረች።

ዳኙ እግሮቹ አላራምድ ብለውት ሲንሰፈሰፍ ከልቧ አሳዘናት። በአካባቢው ከቆሙት አንደኛው "ምን ያሽናክፍሃል" ብሎ ሲገፈትረው እግሮቹ ሚዛኑን መጠበቅ ስላላስቻሉት ተፍገምግሞ ወደቀ። በሀሳቧ አብራው ተንገላታች "አይዞህ" አለችው ሳታስበው። አጠገቧ የነበረው ሰው "ወገኛ ነገ አንቺም እንዲሁ ትሽናከፊያታለሽ" ብሎ በሀይል ሲገፈትራት ፍሬሕይወት እንደምንም የበረንዳውን ብረት ይዛ ሳትወድቅ ቆመች።

የስድብ ውርጂብኝ እያወረዱባት ወደአንድ ክፍል አስገቧት፤ የክፍሉ ሽታ ትንፋገን ይገፋተራል፡፡ ክፍሉ መሀል ቆመች፡፡ ከበስተጀርባዋ በሩን ዘግተውባት ሄዱ። የሚከተለው ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አልፈለገችም። ቤቱ ግን በጣም ይቀፋል፡፡ በወለሉ ላይ የተዝረከረኩት ነገሮች ሁሉ ቆሻሻ ናቸው፡፡ ረጅም ወፍራም ሽመል፣ የተጠቀለሉ ቆሻሻ ጨርቆች፣ የተቀዳደዱ ካናቴራና ሸሚዞች፣

ብረታብረትና አለንጋዎች፣ የኤሌክትሪክ ገመዶች፣ ባልዲ...ሁሉም ተዝረክርከዋል። ክፍሉ ይከረፋል፡፡ የቆየ የደም ጠረን ይበጠብጣል። ከክፍሉ አንድ ወገን በኩል አንድ ወንበርና ሁለት ጠረጴዛዎች ተቀምጠዋል...

መዝጊያው ተበረገደና ተከፈተ ሳታስበው ዞር አለች፡፡ ኩምቢ ኮክሱ ጋቢና የነበረው ሰውዬ ቀድሞ ሲገባ ሌሎቹ ከኋላው ተከታትለው ገቡ። አንደኛው ከኋላ ቀደም አለና አጠገቧ ከመድረሱ በጥፊ አቃጠላት፡፡ ምድር ሰማዩ ዞሮባት ስትንገዳገድ ሳቃቸው አጀባት። ራሷን ተቆጣጥራ በደንብ ሳትቆም ሌላው ደገመና በርግጫ መታት፡፡ ወለሉ ላይ ተዘረጋች።

"ገና ምኑን አይተሽ፣ ተነሽ!" አላት ያ አጉረጥራጭ ሰውዬ። ለመነሳት ተፍጨረጨረች፣ ግን አልሆነላትም፡፡ አቅሟ ሁሉ ከውስጧ ተሟጦ ያለቀ መሰላት። ከጣሪያ በላይ የሆነ ሳቃቸው አንጀቷን አሳረረው "አረመኔዎች!" አለች በሆዷ።

"ልብስሽን አውልቂ" አላት ደግሞ፣ እርሷ ገና መነሳቱም አልሆነላትም፣ አመነታች። ደግሞም ልብስ ማውለቅ ለምን እንዳስፈለገ አልገባትም።

"ምን ይለጥጥሻል አውልቂ እንጂ" አለና በያዘው አለንጋ ጀርባዋን ገረፋት፣ የሸሚዟን አንገት ጨመደደና ከመሬት አነሳት። ምንም ምርጫ አልነበራትም፡፡ ስለምንም ማሰብ አልቻለችም፡፡ የታዘዘችውን ለመፈፀም በደመነፍስ ከመንቀሳቀስ በስተቀር። ልብሶቿን አወላልቃ በጡት መያዣና በፓንት ብቻ በእነዛ ሁሉ ወንዶች መሀል መቆም አስጨንቋት የምትገባበት ቀዳዳ ባጣችበት በዚያ ሰዓት ቀጭን የሴት ሳቅ ከበስተጀርባ ሰማች።

"እጣ እየተጣጣላችሁ ነው እንዴ እናንተ 'ሽንኩርት' የምትሉት ዓይነት ነች አይደል" አለችና ከማዘፍነቷ ጋር የማይመጣጠነውን ቀጭን ሳቋን ሳቀች። ወንዶቹን ገፋ ገፋ አድርጋ ወደፍሬሕይወት ተጠጋች።



"ስሚ! አታፍሪም እንዴ" አለቻት። ፍሬሕይወት ፊቷን ወደሴትዮዋ አዞረች፡፡ የሴትዮዋ ቆንጆ የምትባል ባትሆንም የምታስጠላ አይደለችም፣ ለፍሬሕይወት ግን አስቀያሚ ሆና ታየቻት። በለበሰችው ሱሪና ኮት ላይ የደረበችው ጃኬት ቦርጯም ወንድ አስመስሏታል። የፍሬሕይወትን እጅ ሳብ አድርጋ ሁለት ጊዜ በጥፊ መታቻት ተንገዳገደች፣ ሌላው ደግሞ በእርግጫ ደገማት ሲሚንቶው ላይ በኃይል ወደቀች። የወደቀች ሳይሆን ራሷን የተመታች ነው የመሰላት፡፡ የረገጣትን ሰው ሽቅብ ተመለከተችው፣ ከወጣትነት የዕድሜ ክልል ብዙም ያለፈ አይመስልም። ዐይኖቹ ግን በጣም ቀልተዋል፣ ቁልቁል ሲመለከታት ከዐይኖቹ ውስጥ ጥላቻ ይነበባል። ከእርሱ አልፍ ብሎ ደግሞ ሌላ ሰው አለ፣ ዘለግ ያለ ቁመናውና ፈርጠም ያለ ሰውነቱ ስፖርተኛ ያስመስለዋል። እንደተጋደመች በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ሁሉ ለመቃኘት ሞከረች፣ ፈንጠር ብሎ ከወደግድግዳው ጥግ የቆመው ሌላ ሰው በእጁ መግረፊያውን እንደያዘ በሀሳብ የኮበለለ ይመስላል።

"እሰራት!" የሚል ድምጽ ሲሰማ ከሄደበት የሀሳብ መንገድ ብርግግ ብሎ ተመለሰ።

ከወደቀችበት ሳትነሳ እጆቿን በኤሌክትሪክ ገመድ ግጥም አድርገው አሰሯቸው፡፡ ከእስራቱ መጥበቅ የተነሳ ጣቶቿ ወዲያውኑ አበጡ። ሁለቱንም እግሮቿን በተመሳሳይ ሁኔታ አሰሩ፡፡ ምን ሊከተል እንደሚችል መገመት ከበዳት፡፡ ስለእስር ቤት ስቃይ ሰምታ የምታውቅ ቢሆንም ትክክለኛ ገጽታውን አታውቅም። እግሮቿን እንድታጥፋቸውና የታሰሩትን እጆቿን በጉልበቶቿ ላይ እንድታሳልፋቸው ተነገራት፡፡ የተባለችውን አደረገች፣ ረጅሙና ወፍራሙ ሽመል በእጆቿና በጉልበቶቿ መሀል እንዲገባ ተደረገ።

የሚከተለው ምን ሊሆን እንደሚችል ጠበቀች፣ የሆነውን ነገር ግን ማመን አቃታት። ከእነዛ ስታያቸው ካቅለሸለሿት መሬቱ ላይ ከወዳደቁ ካልሲና ጨርቆች መሀል ብድግ አድርጎ አመጣና ወደአፏ ጠጋ አደረገው፡፡ ማስታወክ ከጀላት።

"አፍሽን ክፈች" አላት በጩኸት።

ሊያደርገው ያሰበውን ማመን አቃታትና ቀና ብላ ተመለከተችው "ይኼማ በፍፁም አይደረግም" አለች ለራሷ።

"ክፈችው!" አለና እንደገና አምባረቀባት፡፡ በፍጹም ልትቀበለው የምትችለው ትዕዛዝ አይደለም፤ ዘገነናት አቀርቅራ ዝም አለች።

"ስቀሏት የምን ማባበል ነው" አለ አለቅዬው።

ከመቅጽበት ሽመሉን ከግራና ከቀኝ ይዘው ብድግ አደረጉት፡፡ ጭንቅላቷ ወደመሬት ተዘቀዘቀና የሽመሉ ጫፍና ጫፍ ሁለቱ ጠረጴዛዎች ላይ አረፉ። በተዘቀዘቀችበት ያን የቆሸሸና ደም የነካካው ጨርቃጨርቅ አመጣባት፡፡ አፏ ውስጥ እንዲከተት መስማማትን ግን በፍጹም የምትሞክረው አልነበረም፡፡ ጥርሶቿን ግጥም አድርጋ አልከፍትም አለች።

"ዞር በል የምን እሽሩሩ ነው" አለ ያ መሎሁ የሚወድ ሰውዬ

ወገቡ ላይ ያለውን ሽጉጥ ላጥ አደረገና አሽከረከረው፡፡ "አቃጥልሻለሁ" አለ ደግሞ ሽጉጡን ግንባሯ ላይ ደግኖ። አንዳች ስሜት ሰውነቷን ወረራት፡፡ "ግን እኮ ሞት ከዚህ ሁሉ ስቃይ አይበልጥም" እንዲያውም እረፍት ነው" አለች በሀሳቧ። በሽጉጡ አፈሙዝ አፏን ነካ አደረገው፡፡ ምን ሊከተል እንደሚችል ገና መገመት እንኳ አልቻለችም፡፡ በትልቁ ጫማው አንገቷን ረገጣት፡፡ ከንፈሮቿ ሳታዛቸው ተከፈቱና የሽጉጡ አፈሙዝ ጉሮሮዋ ውስጥ ተቀረቀረ፤ ወዲያውኑ መልሶ አወጣው አፏን ግን መልሳ ልትገጥመው አልቻለችም።

ያንን አስቀያሚ የካልሲ ኳስ ያለምንም ችግር አፏ ውስጥ ወተፈው፡፡ የታነቀች መሰላት። የተሰገሰገው የካልሲ ጥቅል እንዳይወጣ አፏን ግጥም አድርጎ በጨርቅ አሰረው፡፡ ታፈነች። ስቃዩን በቃላት መግለፅ በጣም አስቸጋሪ ነው። ዐይኖቿን ጨፍና ስቃዩን ለመርሳት ሞከረች፡፡ ለሰዓታት ያህል ከሀሳቧ ጠፍተው የነበሩ ሰዎች ሁሉ በዓይነ ህሊናዋ ፊት ተደረደሩባት። እናቷ፣ ወንድሞቿና እህቶቿ፣ አንተነህ፣ በላይሁን፣ ቅዱስ፣ ቤቲ፣ ትርሲት፣ ...



አለንጋው ውስጥ እግሯ ላይ ሲያርፍ ከገባችበት የሀሳብ ዓለም መንጥቆ አወጣት፡፡ ግርፉ ተከታተለ እስከወዲያኛው ድረስ የሚያቋረጥ አይመስልም፡፡ መፈጠሯን ጠላች ምናለበት ቢገድሉኝ አለች፡፡ "መናገር ስትፈልጊ ጣትሽን አሳይ" አላት መግረፉን ሳያቋርጥ።

"ምንድነው የምናገረው? እከሌ እከሌ እያልኩ የሰው ስም ልዘረዝር በፍጹም አላደርገውም" ከራሷ ጋር ነበር ውይይቱ "እስከሞት ድረስ እንኳ ቢሆን" ብላ ለራሷ ደመደመች፡፡

እግሯ ደንዝዞ የእርሷ እስከማይመስላት ድረስ እየተፈራረቁ ቀጠቀጧት። ዓይኖቿን ጨፈነቻቸው በዓይነ ህሊናዋ እንደገና እናቷንና ሌሎቹን አየቻቸው... ጃኬቱን እስከአንገቱ የቆለፈው ያ መኪናው ውስጥ የነበረ ልጅ ታያት፡፡ እግሮቹና እጆቹ የታሰሩበት ብረት ቅጭልጭልታ በጆሮዋ ተሰማት፡፡ ከማበጣቸው ብዛት እንደመስታወት የሚያብለጨልጩት የዳኙ እግሮች...

ቀዝቃዛ ውሀ በእግሮቿ ላይ ተደፋ፡፡ ዐይኖቿን ገለጠች ከእግሮቿ የሚወርደው ውሃ በዐይኖቿና በአፍንጫዋ ውስጥ ገባና አፈናት። በአፍንጫዋ የገባው ውሃ ጭንቅላቷ ውስጥ የገባ መሰላት፡፡ አቃጠላት ማስነጠስ ግን አልቻለችም ተወራጨች። አለንጋው እንደገና እየተከታተለ እግሮቿ ላይ አረፈ፡፡ አቤት ስቃይ! እንዲህ ዓይነት ስቃይ ይኖራል ብላ በፍፁም ገምታ አታውቅም፡፡ ሰውነቷ ሲደነዝዝ ደስ አላት፡፡ ቀስ በቀስ እንቅልፍ ውስጥ የገባች መሰላት፡፡ ሁሉም ነገር ጭልምልም አለ...

* * * *

ፈቃደ ግንባሩን እንደቋጠረ ገብቶ ፍራሹ ላይ ጥቅልል ብሎ ተኛ። በአካባቢው የሚተኙት እስረኞች ፀባዩን በሚገባ ያውቃሉ፤ እንዲህ የሚያደርገው በጣም ሲናደድ ብቻ ነው። ሌላ ጊዜ "አዝናንቻቸው መጣሁ" ይላል ወጥቶ ሲመለስ። እንዲህ እንደአሁኑ ሲኮሳተር ግን ሁሉም ራቅ ብለው ይቆያሉ እንጂ አንዳቸውም ሊያናግሩት አይሞክሩም።

ጥቂት ቆይቶ ተነሳና ተቀመጠ፤ የግንባሩ ስር ተግተርትሯል ዓይኖቹም ቀልተዋል። "የዛሬው ለየት ያለ ነው ?" አለ አንደኛው እስረኛ። ልጁ ገና ተናግሮ ሳይጨርስ ፈቃደ ከተቀመጠበት ተነሳና እግሮቹን እየጎተተ ወደ ዳኙ ሄደ።

"የማትረባ ሰው ነህ እሺ?" አለው ከዳኙ አጠገብ ቆሞ። ሁሉም ጆሮዎቻቸውን አቅንተው መስማት ጀመሩ። ዳኙ መልስ አልመለሰለትም፤ አቀርቅሮ ዝም አለ። "ትንሽ ለመቋቋም ብትሞክር ኖሮ ሊያልፍ ይችል ነበር" አለው።

"እዚህ መምጣቷ እንደሚሻል ስላመንኩ ነው ያመጣኋት" አለ ዳኙ ቀና ብሎ እየተመለከተው።

"እዚህ ከምታመጣት ራሷን እንድታድን መልዕክት አትልክባትም ነበር?" ጠየቀ ፈቃደ።

"ማንን ነው የምልክባት? ደግሞስ እንዴት ነው ራሷን የምታድነው? ከፍተኛ ወይንም ቀበሌ ሄዳ እጇን ከምትሰጥ እዚህ መምጣት አይሻልምና ነው?..."

ዳኙ ሊናገር የፈለገውን ተናግሮ የጨረሰ አይመስልም፤ ፈቃደ ግን በመጣበት አኳኋን ወደቦታው እየተመለሰ "የማትረባ!" ብሎ አጉረመረመ።

ፈቃደ ለበርካታ ጊዜ የውሸት ጥቆማ እየነገረ ይዘውት ይወጡና ምንም ሳያገኙ ይመለሳሉ። እንዲህ ባደረገ ቁጥር ይገረፋል። ጥቆማ አለኝ ብሎ ቢወጣም ባይወጣም ፈቃደ ሳይገረፍ አይሰነብትም። ስለዚህ ወደምርመራ ክፍል በተጠራ ቁጥር መገረፉ የማይቀር መሆኑን ስለሚያውቀው ይዟቸው ይወጣል።

"እስኪ ዛሬ ደግሞ ትንሽ ላንሸራሽራቸው" ይላል ሲወጣ። ሲመለስ ያው ግርፍ ይጠብቀዋል፤ ብትንትን አድርገው ገርፈው ደግሞ ይመልሱታል።



ተመልሶ ፍራሹ ላይ ተቀመጠና መጽሐፍ ማንበብ ጀመረ። ለህመሙም ሆነ ለንዴቱ ማብረጃው መጽሐፍ ነው። አሁን ግን መጽሐፉን ገለጠው እንጂ አያነበውም፤ በሀሳቡ እልም ብሏል። መኪናው ውስጥ አብራቸው የነበረችውን ልጅ ከሀሳቡ ሊያጠፋት አልቻለም። ገና እየገፈታተሩ መኪናው ውስጥ ሲያስገቧት ነው ልቡ የደነገጠው። ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከራሱ ጋር ሙግት ገጥሟል፤ "ግን እንዴት ሊሆን ይችላል? አለና ራሱን ጠየቀ።

ያን ዕለት እንዴት ሊረሳው ይችላል? እያንዳንዱ ሁኔታ ዛሬም አዲስ የሆነ ያህል ይታየዋል። አዲስ አበባ በየጎዳናዋ የወጣት ሬሳ እየተነጠፈባት መዋል በጀመረችበት ሰሞን ነበር። ወደነበረው ቀጠሮ ለመሄድ ፈጠን እያለ ይራመዳል፤ ሰዎች አጀብ ብለው ተመለከተና መንገዱን መቀየር አሰበ። ጥቂት በሌላ አቅጣጫ ከተራመደ በኋላ ሳያስበው ተመለሰ። ወደተሰበሰቡት ሰዎች አቅጣጫ ሲመለከት አሁንም አሉ። ወደዚያው ሄደ፤ ቀረብ እያለ ሲሄድ መሬቱ ላይ የሆነ ነገር መኖሩን አስተዋለ።
መሬቱ ላይ ያለው ሰው መሆኑን ዓየ፤ ርምጃውን ፈጠን አደረገና ተጠጋ። ጥቂት ራቅ ራቅ ብለው ደረታቸው ላይ "ቀይ ሽብር ይፋፋምብኝ" የሚል ጽሁፍ የተለጠፈባቸው ሦስት ወጣቶች ወድቀዋል። ሁለቱ ወንዶች ሲሆኑ አንዷ ግን ሴት ነች። ሲቷ ልጅ ረጅም ፀጉሯ መሬቱ ላይ ተበታትኖአል፤ ፊቷ ወደዚያኛው አቅጣጫ በመዞሩ አይታይም። ነጣላ ጫማዋ ፈንጠር ብሎ ወድቆ ሱሪዋ ከአንድ በኩል ተቀዷል። ሸሚዟ ከቀኝ ጎኗ በኩል ገለጥ ብሎ ሰውነቷ ይታያል። ሁሉም ከንፈሩን እየመጠጠ ሀዘኑን ይገልጻል፤ ወታደሮቹ መጥተውም እንዳይታፈስ በስጋት አካባቢውን ይቃኛል።

ፈቃደ ልቡ በኃይል እየመታችበት ቀስ ብሎ የልጅቱ ገጽታ ከሚታይበት በኩል ዞረ። ማንም አላስተዋለውም፤ መሬቱ ላይ ዝርግት ሲል ነው ያዩት። መጨጨህ ሆነ።

"ኀበዝ መጨጨህ ምን ይጠቅማል እንተጋገዝ እንጂ" አሉ አንድ ጎልማሳ። የሰውየው ቤት እዚያው አካባቢ ኖሮ ፈቃደን አንስተው ሰውየው ቤት አስገቡት። ለስንት ሰዓት እንደቆየ አያስታውስም፤ ሲነቃ ግን የማያውቀው ቤት ውስጥ እንደነበረ አስተዋለ።

የተመለከተውን ነገር ልክ እንደሀልም አስታወሰው፤ አስፋልት ላይ ተዘርግታ ያየት እህቱን ነበር፤ የሚወዳትን ትንሽ እህቱን፤ የት ትደርሳለች የምትባል እህቱን። እህቱ ይህ ነው የሚባል የፖለቲካ ተሳትፎ አልነበራትም፤ አንድ ቀን ግን እንደወጣች ቀረች። ያልተፈለገችበት ቦታ አልነበረም፤ እዚህ ቦታ ናት የሚል አልተገኘም።

በእርሷ ወጥታ መቅረት ምክንያት ቤተሰቡ እንደታመሰ ነው፤ እናቱ ታመው ሀኪም ቤት ገብተው መታከም ነበረባቸው። አባቱ ከዛ በኋላ ሥራቸውን በአግባቡ መሥራት አቅቷቸዋል፤ ብቻቸውን እየተነጋገሩ ሲሄዱ እርሱ ራሱ ዓይቷቸዋል። የሆነውን ሁሉ ለሰውየው ነገራቸው፤ የእህቱን ሞት ግን ለቤተሰቦቹ ሊነግር መድፈር አልቻለም። ቤተሰቦቹን፣ በተለይም እናቱን ማየት አቃተው፤ እናም እቤት መቆየቱ አደገኛ እንደሚሆን ተናግሮ ከቤት ወጣ። እስር ቤት በገባበት ሰሞን እናቱ መሞታቸውን ሰማ።

መኪናው ውስጥ ያየት ልጅ ቁርጥ እህቱን ነው የምትመስለው። ራሱን ተጠራጠረ፤ ተሳስቶ ይሆን እንዴ? መልክ ተመሳስሎበት ደንግጦ ይሆን እንዴ አስፋልት ላይ የወደቀችው ልጅ እህቱ የመሰለችው? በርካታ ጥያቄዎችን ደረደረ በኋላ ደግሞ በራሱ ተገረመ መኪናው ውስጥ ያየት ልጅ እህቱ ብትሆን እንዴት ዝም ልትለው ትችላለች?

መጽሐፉን አስቀመጠና እንደገና ተጋደመ። ብዙም ሳይቆይ ለሽንት የመውጫ ሰዓት መድረሱን ነገሩትና ተነስቶ ተሰለፈ። እዚያም ሆኖ መኪናው ላይ ያየትን ልጅ ከአእምሮው ሊያወጣት አልቻለም።

* * * *

በጠባቧ ግቢ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ እያሉ የሚጨዋወቱት ሴት እስረኞች የመዝጊያውን መከፈት ሲሰሙ ቆሙና የሁሉም ዐይኖች ወደአዲስ ገቢዋ ፍሬሕይወት አተኩሩ።

ግቢው መኖሪያ ቤት እንደነበረ ያስታውቃል፡፡ በስተቀኝ በኩል ሰርቪስ ቤቶች በስተግራ ደግሞ ዋናው ቤት አለ። ከትልቁ ቤት



በረንዳ ላይ ተቀመጠች። ቀኑ ወደመጨለሙ በመሆኑ ብርዱ አጥንቷ ውስጥ የዘለቀ መሰላት። ከእስረኞቹ አንደኛዋ ወደእርሷ መጣችና፤

“ባትቀመጭ ይሻልሻል ቢያምሽም እንደምንም ተራመጂበት” አለቻት። ፍሬሕይወት ግን እንደማትችል ነገረቻት።

“ግዴለሽም እኛ እንደግፍሻለን” አለች ሌላዋ ጠጋ ብላ።

ግራና ቀኝ እጆቿን ያዟት፡፡ በእነርሱ ብርታት እንደምንም ለመራመድ ሞከረች። ጊዜው በመሸ መጠን ብርዱ ይብሳል፡፡ የእጆቿ ቆዳ የዶሮ ቆዳ መሰለ። “በረደሽ አይደል?” አለችና አንደኛዋ የለበሰችውን ጋቢ አለበሰቻት። እዚያ መግረፊያ ክፍል ውስጥ ያለውን ጭካኔና እስረኞቹ ክፍል ያለውን ርህራሄ አነፃፀረችው።

“መፀዳጃ ቤት ልትወስዱኝ ትችላላችሁ” አለች አንዲት ከቤቱ ጥግ የተቀመጠች ሴት። ገና ተናግራ ሳታበቃ አጠገቧ ደረሱና ተረዳድተው አነሷት። ፍሬሕይወት የሴትዮዋን እግር አየችው፡፡የሁለት እግሮቿ ጥፍሮች በቦታቸው የሉም፡፡ የሚታየው ደም ያቾፈቾፈ ሥጋ ብቻ ነው። ውስጥ እግሮቿ ተገማምሰው ውሀ የመሰለ እዠና ደም ይተፋሉ፣ ቅልጥሞቿ ተገጣጥበው ጠገግ ያለው ቁስላቸው ይዘገንናል።

የራሷን እግሮች እያቻቸው “የኔም እንዲህ ይሆንብኝ ይሆን?” ጥያቄውን ያቀረበችው ለራሷ ነው።

“ዋጋ ለሌለው ነገር እንደ እርሷ እንዳትጎጂ ልታስቢበት ይገባል” አለቻት አንደኛዋ።

“እርሷ ለምንድነው እንዲህ ከሌላው የተለየ የተጎዳችው?” አለቻት ልጅቱን።

“ዝም” ብላ ምድረ ሲሲ (የማእከላዊ ኮሚቴ አባል) ሲለፈልፍ እርሷ ስትደርቅ አልናገርም በማለቷ ነው እንዲህ የተለተሏት” አለቻት።

“ስሚ ማነው?” ብላ ጠየቀች።

“ሚስጥረ ትባላለች” አለች ልጅቱ።

“የእውነትም ሚስጥረ ስምን መልዓክ ያወጣዋል ይባል የለ” አለች ለራሷ።

ያልገመተችውን ያህል በእግሯ ሄደችበት እብጠቱ እንዳለ ቢሆንም ከመጀመሪያው የተሻለ መርገጥ ችሎላታል። ከዚያ በኋላ እንደማይጠሯት በመገመት እህል እንድትቀምስና አረፍ እንድትል መከሯት። የሰጧትን ምግብ ለመብላት ስትሞክር እናቷ ተደቀነባት፡፡ እህሉን መዋጥ አቃታት። ይልቁንም ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ተመኘች፤ ይህ ግን በፍጹም ልታደርገው የሚገባት ያለመሆኑን ስለምታውቅ ዋጥ አደረገችው። እየታገለች የተወሰኑ ጉርሻዎችን ለመዋጥ ሞከረችና መለሰችው።

እስረኞቹ የተሻለውን ቦታ ቢሰጧትም ሊሊቱን እንቅልፍ በዓይኗ አልዞረም። እናቷን መላልሳ አሰበቻቸው፡፡ ሕይወቷን የተሻለ ለማድረግ የነበራትን የልጅነት ሕልምና ዛሬ በልጆቻቸው ምክንያት ሊደርስባቸው የሚችለውን ሐዘን… ደግሞ ከእናቷ ወደሊሎቹ… ቃለአብ እንዴት ሆኖ ይሆን? አክስታቸው ቤት መሄድ የተሻለ እንደሚሆን አስቦ መሄዱን ብቻ ነው የምታውቀው። በላይሁንስ ምን ገጥሞት ይሆን? በላይሁን ጠንካራ ልብ እንጂ ጠንካራ ሰውነት የለውም፡፡ የእጆቹ ልስላሴ ተሰማት ይህንን ግርፍ እንዴት ሊቋቋመው ይችል ይሆን? በላይሁን የላከላትን የአንገት ሀብል አሰበችው፡፡ ያን ዕለት ቤት አስቀምጣ በመውጣቷ በጣም ደስ አላት፡፡ ይህን ሁሉ ዓመት ፍቅሩን አምቆ የመያዙን ነገር ስታስበው ደግሞ ከልቧ አዘነች። አንተነህስ የት ደርሶ ይሆን? በተለያዩበት ቀን በገጽታው ላይ የነበረውን ስሜት እስከ እለተ ሞቷ ድረስ የምትረሳው አይመስላትም።…

ደግሞ ወደአለችበት ቦታ ተመልሳ ውሎዋን አስታወሰች፤ ሀሳቡ አመማት፡፡ ድንገት ሌላ ነገር ትዝ አላት፤ ቦርሳዋ፡፡ “ቦርሳዬን የት ነው ያደረጉት?” ውስጡ ገንዘብ ነበረው፤ አዎን ከአዲስ አበባ ለሚወጡ ልጆች መጠቀሚያ የሚሆን ገንዘብ፤ በርከት ያለ ገንዘብ ነው። ገንዘብ ብቻም አይደለም የልጆቹ ፎቶዎችስ? በተኛችበት ሰውነቷን አንቀጠቀጣት። ፎቶዎቹን አይተው እንዴት ዝም አሉ?



በጣም ገረማት፡፡ ያም ሆነ ይህ የሚያዋጣት መሸምጠጥ ብቻ ነው። ለመሆኑስ እነዛ ልጆች በአሁኑ ሰዓት የትና በምን ሁኔታ ላይ ይሆኑ?

በሴቶች ክንፍ አብራት ትሠራ የነበረችው ድንቅነሽ ትውስ አለቻት፡፡ ከድንቅነሽ ጋር በሚቀጥለው ቀን ቀጠሮ አላቸው። ድንቅነሽ ከፍተኛ የፖለቲካ ሚና እንደሌላት ታውቃለች፡፡ ግንኙነቶቿም ተበጣጥሰውባታል። ታዲያ በዚህ ጊዜ ውጭ መንከራተት ምን ፋይዳ አለው? ምናልባትም ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል፡፡ አጉል ቦታ መውደቅም ሊከተል ይችል ይሆናል።…

ብቻ ሊሊቱ እንዲሁ በሀሳብ እንደተተረማመሰች ለሌሎቹ ሲነጋ ነጋላት። ጠዋት ልጆቹ ሲነሱ ለእናቷ መልእክት መንገር ይቻል እንደሆን ጠየቀቻቸውና የስልክ ቁጥር ሰጠች፡፡ መቼም የት እንዳለች ቢያውቁ ይሻላቸዋል ብላ ነው።

በጠዋት ወደዛ ቀፋፊ “ቢሮ” ተጠራች፤ የገባችው ግን መግረፊያ ክፍል አይደለም፡፡ ትንሽ ቀለል አላት። “ተቀመጭ” አላት ያ መጮህ የሚወድ ሰውዬ ተቀመጠች።

“የምታውቂውን ሁሉ አንድ በአንድ ትናገሪያለሽ፤ አለበለዚያ ደግሞ ያው ነው” አላት ወረቀትና እስኪሪፕቶውን ይዞ።
በዝቅተኛ ደረጃ የምትሠራ መሆኗንና ወረቀት ከማንበብና ከመበተን የዘለለ ሥራ እንዳልሠራች ተናገረች።

“በቃ ይኸው ነው?” አለና አምባረቀባት፤ ዝም አለች።

“መሣሪያውስ?” አለ ልክ የታወቀ መሣሪያ እርሷ ጋ እንዳለ አድርጎ።

“ስለ መሣሪያ ምንም አላውቅም?” አለች ቀና ብላ ተመልክታው።

“ይህን ያበጠ እግርሽን ስገማምስልሽ ታውቂያለሽ” አለና ስኪሪፕቶውን ወርውሮ ተነሳ። ምንም ፋታ አልሰጧትም፡፡ እያዳፉ ወደዚያ የተረገመ ክፍሏ ወሰዷት። ያለምንም ተጨማሪ ጥያቄ ለድጋሚ ግርፍ ገለበጧት፡፡ ያንን ሽመል በእጅና በጉልበት መሀል አስገብተው ሁለቱ ጠረጴዛዎች ላይ የሚያንጠለጥሉትን ግርፍ “መገልበጥ” ይሉታል።

የዳግም ግርፉ ስቃይ ከመጀመሪያው የበለጠ ነው፡፡ መፈጠሯን አሰክትጠላ ድረስ ቀጠቀጧት። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁሉም ትተዋት ከክፍሉ ወጡ፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች እዚያው እንጨት ላይ ተንጠልጥላ ቆየችና "በሉ በሉ አውርዷት ሌላ ሥጋ ተገኝቷል" አለ ያ ጨካኝ ሰውዬ፤ አከታልፈው አውርደው ወረወሯት።

በድንጋጤ የፊቱ ቀለም ጨው የመሰለውን ልጅ እያዋከቡ አስገብተው ይለበልቡት ጀመር። የስቃይ ድምጹ አሰቀቃት። ጥቂት ቆይተው በሩ ተከፈተና ሁለት ገራፊዎች ተከታትለው ወጡ፡፡ እየተንደረደሩ ከበስተቀኝ ወዳለው ትልቅ መጋዘን ሄዱ፡፡ ትልቁን የብረት መዝጊያ ከፍተው ገቡ። ወዲያው ደግሞ ያንን እግሩና እጆቹ በእግር ብረት ታስሮ የነበረውን ልጅ እያንገላቱ ይዘውት ተመለሱ። እንግልቱን ሁሉ ተቋቁሞ አጠገቧ ሲደርስ በዐይኖቹ ሰላምታ ሰጧት አለፈ።

ልጁን ወደመግረፊያው ክፍል ሲያስገቡ "ይችን አስገባና ቃሏን ተቀበላት" ብሎ ትዕዛዝ ሰጠ አለቅየው። "ፍጠኝ!" አላት ከገራፊዎቹ አንዱ ገና ተናግሮ ሳይጨርስ። እየተሸናከፈች ተከትላው መጀመሪያ የገባችበት ክፍል ገባች። "እንግዲህ ብልጥ መሆን ያስፈልግሻል ፈጠን በይና መንገር ያለብሽን ብቻ ንገሪኝ" አላት ድምጹን ዝቅ አድርጎ፤ በሚገባ ተረዳችው፤ እናም ማውራት ያለባትን መናገር ጀመረች እርሱም ያለምንም ተጨማሪ ጥያቄ መፃፍ ቀጠለ።
ለልጁ ቦርሳዋ ውስጥ ስለነበረው ገንዘብና ፎቶዎች ነገረችውና የሚችል ቢሆን ፎቶዎቹን በማጥፋት እንዲተባበራት ጠየቀችው።

"ቦርሳሽ ውስጥ የነበረው ገንዘብ ተጠናቋል፡፡ አብረው ለነበሩት ፎቶዎች ብዙም ትኩረት የሰጠ የለም፡፡ እኔ እንደሚሆን አድርጌያቸዋለሁ፡፡ ስለቦርሳው እስከመጨረሻው ምንም ባትጠይቂ ይመረጣል" በማለት ሲያስጨንቃት የነበረውን የፎቶዎቹን ጥያቄ መለሰላት።

"በጣም አመሰግንሃለሁ" አለች የምትመርጠው ቃል አጥታ።

ከዚያኛው ክፍል የሚሰማው የስቃይ ድምጽ ወደመጨጨህ ተለወጠ።



"ይሄ ልጅ ደግሞ የፈረደበት ነው" አለ ቃል ተቀባዩ "ታውቂያለሽ በየጊዜው የሚመጣው ሰው ሁሉ እንደጠቆመበት እርሱም አላውቅም እንዳለ ነው" አለ። በጥድፊያ የጻፈውን አነበበላትና እንድትፈርም አስኪሪፕቶ ሰጣት፡፡ "ከዚህ በኋላ ግትርነት አያዋጣም" አላት ከወንበሩ እየተነሳ። አብዮት ጥበቃውን ጠራና ወደማረፊያ ክፍል እንዲወስዳት አዘዘ።

በማግስቱ እንደገና ወደዚያ የገራፊዎች ቢሮ ተጠራች። ስትገባ አንድ ትልቅ ሰው ተቀምጠዋል፤ ሰውየው በምን ወደዚያ እስር ቤት እንደመጡ ገረማት። እርሷ ስትገባ እርሳቸው ወደመጋዘን እንዲመለሱ ሆነ።

"አንች ደግሞ አላወጣም እንዳልሽ ነሽ አይደል?" አላት አለቅዬው ገና ከበሩ ገባ ስትል።

"አላልኩም" አለች ፈጠን በማለት

"ምን ማረጋገጫ አለሽ"

"ዛሬ አንድ ቀጠሮ አለኝ" አለች ቃል የተቀበላትን ልጅ ሰረቅ አድርጋ እያየችው፤ ትክክል ነሽ በሚል ዓይነት አውራ ጣቱን አሳያት።
በጉዳዩ ላይ ሌሊቱን ስታስብበት ነበር ያደረችው፡፡ ያሏትን ቀጠሮዎች ሁሉ አሰበቻቸው አንዳቸውንም መናገር እንደሌለባት ወስናለች፤ በሌሎቹ ቀጠሮዎች የምታገኛቸውን ሰዎች ምንነት አታውቅም በመጨረሻው ሰዓት እንድታገኛቸው የተቀጠሩ ሰዎች ናቸው። ለድንቅነሽ ግን ከደብረዘይት ከመነሳቷ በፊት ደውላላት ግራ እንደገባት ነግራታለች። ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌላትና ምን ማድረግ እንዳለባት መወሰን እንደተቸገረች አውቃለች። ስለዚህም እዚህ መምጣቷ የተሻለ እንደሚሆን አምናበታለች። "ግን እንዴት እርግጠኛ እሆናለሁ? ድንቅነሽ በኢሴትድ (የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት) የኢሕአፓ የሴቶች ክንፍ ነው የማውቃት፤ በሌላው ያላትን ደረጃ በምን አውቃለሁ?" አለች ደግሞ። "…ግን የትኛውስ ቢሆን ምን ፋይዳ አለው?" አለች እንደገና መግረፊያው ክፍል ውስጥ እየሰሩት የነበረውን መዋቅርና የገራፊዎቹን ንግግር አስታውሳ። "በቃ ሙሉው መዋቅር ሊኖረን የሚቀረው ጥቂት ነው፤ ኢሕአፓ ፈርሳለች ማለት

ይቻላል!" ነበር ያሉት። ታዲያ የፍሬሕይወት ... "ምን ትዘጊያለሽ?" አለና ሰውየው ከሀሳቧ መለሳት።

"እንሂድ አልኩ እኮ!" አለች ፈጠን ብላ። በዚያ በኩምቢ ቮክስ ዋገን ተጭና ከድንቅነሽ ጋር ወደነበራቸው ቀጠሮ ስትሄድ ግን ስሜቷ እንዳሰበችው አልነበረም። ተናደደች "ምንም ቢሆን መናገር አልነበረብኝም" አለች ለራሷ።

ፍሬሕይወት የደረሳት ዕጣ ለድንቅነሽም ደረሳት፡፡ እያካለቡ ኩምቢ ቮክስዋገኑ ውስጥ ሲያስገቧትና እርሷን ስታገኝ የቱን ያህል ፊቷ እንደተለዋወጠ መቼም ቢሆን አትረሳውም።

ወደክፍል ስትመለስ ሚስጥረን የተለመደ ቦታዋ ተቀምጣ አየቻት፡፡ ሁሉም በየክፍሎቻቸው ሆነው ግቢው ፀጥ ብሏል። ሚስጥረ አጠገብ ሄዳ ተቀመጠችና መጫወት ጀመሩ።

"እግርሽ እንዴት ነው?" አለቻት በስስ ነጠላ ሸፈን አድርጋ ፀሐይ የምታሞቀውን እግሯን እያየች።

"ደህና ነው ምንም አይል።"

"እዚህ ከመጣሽ ቆየሽ?"

"አንድ አምስት ወራት ሆኖኛል።"

"አምስት ወራት ሙሉ እንዴት ሳይድንልሽ ቆየ?"

"ትንሽ ጠገግ ሲል እየወሰዱ እየገረፉኝ እንዴት ይዳን?"

"ለምንድነው በየጊዜው የምትገረፊው?"

"ታዲያ ምን ላድርግ?"

ለጥያቄው መልስ አልነበራትም፡፡ አጠንክራ መጠየቅም ያለባትም አልመሰላትም፡፡ ሌላ ጥያቄ አነሳች።



"ሰፈርሽ የት ነው?" አለቻት።

"ኡራኤል ነው" አለች እንዳቀረቀረች።

"ምነው አመመሽ እንዴ?" አለቻት ወደጨዋታ ለማምጣት አስባ።

"የሚያመኝ የአካሌ ቁስል ብቻ መሰለሽ? የበለጠ የሚያመኝ ሀሳቡ ነው። አንቺ መቼም አሠራሩን በደንብ የምታውቂው ይመስለኛል፡፡ ሚስጥር ምን እንደሆነም ይገባሻል ብዬ አስባለሁ" አለችና ቀና ብላ ተመለከተቻት ፍሬሕይወትን። መስማማቷን በአንገቷ አረጋገጠችላት።

"ታዲያ እነርሱን የሚያካክሉ የተማሩና ፓርቲውን የሚመሩ ሰዎች እኔ ዘንድ ወታደር ይዘው መምጣት ነበረባቸው?" አለቻት ሚስጥረ።

"እነማን ናቸው?" አለቻት መገረምም ግራ መጋባትም እየተሰማት።

"ወይጉድ! እነርሱማ የፓርቲው ሰዎች ናቸው፡፡ መሣሪያዎቹ እኔ ቤት እንዲደበቁ ያደረጉት የፓርቲው መሪዎች ናቸው። ከእነርሱ ውስጥ አንደኛው ወታደሮቹን ይዞ መጥቶ መሣሪያዎቹን አስቆፍሮ አስወሰደ። ከእነዛ ሰዎች አንደኛው ደግሞ እዚህ ታስረው ኖሮ በሚቀጥለው ቀን ከዚህ ተግበስብሰው መጡና መሣሪያ ውሰጂ አሉኝ፡፡ የተወሰደውን መሣሪያ እኔ ከየት አባቴ ላምጣው? ተወስዷል ብዬ የተቆፈረውን ባሳየቸው እኔኑ ይዘውኝ መጡና ይኸው እንዲህ አደረጉኝ።

ግን ውሸትን እግዜርም አይወደው "መሣሪያው ከተወሰደ እኔ ተጠያቂ ነኝ እርሷ ምን ታድርጋለች" ብለው ወደዚህ እንዳያመጡኝ ተማጽነውልኝ ነበር። ሊያድኑኝ አልቻሉም፡፡ እዚህም ከመጣሁ ቢሆን የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያደርጉልኝ እርሳቸው ናቸው፡፡ ታዲያ እኔማ ማን ጠያቂ አለኝ?"

"አንቺ ግን መሣሪያ ለመደበቅ እንዴት ተባበርሽ?" አለቻት።

"እንዴት አልተባበርም፡፡ እነዚህ ሰዎች እኮ አንቱ የተባለ ኑሯቸውን ትተው ነው ለድሀ እናሳልፋለን ብለው መከራቸውን የሚያዩት፤ ታዲያ እንደኔ ዓይነት መናጢ ምን እንዳላጣ ነው እምቢ የምላቸው?

ደግሞም መልካም ሰዎች ናቸው፡፡ ለሰው ያላቸው አክብሮት ይገዛኛል፡፡ እነርሱ ዘንድ የበላይና የበታች የለም፤ ሁሉ እኩል ነው። ኧረ ኤዲያ ምን እንዳያቸው አላውቅም እንጂ እነርሱስ አገር ቢያስተዳድሩ እግዜርም ይታረቀን ነበር" አለች ሚስጥረ።

"ግን አንቺ አባል ነበርሽ እንዴ?" ብላ ጠየቀቻት፡፡ መጠየቅ እንደማይገባት ብታውቅም አድናቆቷን ማጋታት ስላቃታት ጠየቀች።

"እንዴታ! ነበርኩኝ፡፡ ማንበብ መጻፍ ባልችልም በምችለው መንገድ የሚፈለገውን ልሠራ ተስማምቼ ነው የተመለመልኩት። ወርሀዊ መዋጮም አጓድዬ አላውቅም፡፡ አንዳንድ ዕቃ ከቦታ ቦታ ማስተላለፍ ሲያስፈልግም አግዛለሁ፡፡ እኔን ማን ይጠረጥረኛል? ወይጉድ!" አለችና ቀና ብላ በአትኩሮት ተመለከተቻት ፍሬሕይወትን።

"እስኪ ምን ብዬ ነው ይህን ለአንቺ መለፍለፌ? ሲገርፉኝ ያላወራሁትን ለአንቺ መዘክዘኬ ምን ይባላል?..."

"እመኝኝ! በፍጹም ለማንም እንዳልተናገርሽ ልትቆጥሪው ትቺያለሽ" አለቻት።

"እስካሁን ለማንም ትንፍሽ አላልኩም..."

በሩ ድንገት በኃይል ተመታ ፍሬና ሚስጥረ በድንጋጤ በረገጉ።

"አንቺ መጥፎ! ነይ" አለ ገራፊው፡፡ ሁለቱም ለመነሳት ተንደፋደፉ።

"ኧረ አንቺኛዋ! ይህን ሊበቅል ያለ ጥፍርሽን እንደገና እነቃቅልልሻለሁ" አለ ሰውየው፡፡ የበለጠ ደነገጠች ፍሬሕይወት ለሚስጥረ ልዪ ቆሰለላት "...ጠገግ ሲል እንደገና ሲገርፉኝ..." ያለችውን አስታወሰች።

ሚስጥረ ፍሬን ዞር ብላም ሳታያት እያነከሰች ወጣች። ሚስጥረ ከአንድ ሰዓት በኋላ ተመለሰች። ፍሬ ከዚያች ቦታ ሳትንቀሳቀስ ጠበቀቻት፡፡ ሚስጥረ ስትመለስ ግን እርሷን አትመስልም፡፡ ፊቷ አባብጧል፤ አፍንጫዋ ይደማል፤ እግሮቿም ብትንትናቸው ወጥቷል።



እንደተለመደው ልጆቹ ተሸቀዳድመው ተቀበሏትና ደጋግፈው አስገቧት። እየተንሰፈሰፈች ከፍሬ አጠገብ ተቀመጠች።

ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ሚስጥረ፤ ፍሬ ልታባብላት ሞከር አደረገችና ቢወጣላት እንደሚሻል በማመን ዝምታን መረጠች። ድንገት ፀጥ አለች ሚስጥረ፤ ዞር ብላ ተመለከተቻት።

"አንዷቷን እንኳን አልነገርኳቸውም! እሞታለሁ እንጂ እስከወዲያኛውም አልነግራቸውም!" አለች በእልህ።

"ግን እኮ ጥቅምና ጉዳቱን ዓይተሽ..." አቋረጠቻት።

"በፍፁም አላደርጋትም! ከፈለገ ሌላው አውጥቶ ይስጣቸው እንጂ..."

"ሌላ መሣሪያ አምጭ ነው የሚሉሽ ማለት ነው?" አለች ደንቋት።

"አዎ! ግን አልሰጣቸውም። ማንም ሊያሳያቸው አይችልም፤ ስለ ጉዳዩ የምታውቀው ሴት እዚህ አገር የለችም፤ እኔ ደግሞ ቃል እንኳ አልተነፍስም።"

"እንዲህማ መደምደም አትችይም፡፡ ልትመጣ ትችል ይሆናል እኮ ሚስጥረ"

"ከመጣችም እንደፈለጋት! አውጥታ ልትሰጣቸው ትችላለች፡፡ ያንጊዜ እኔም እርሜን አወጣለሁ" አለች ሚስጥር ኩስትር ብላ።

እንደገና ማታም ተጠርታ ወደዚያ ቀፋፊ ክፍል ተወሰደች ሚስጥረ፤ ከዚያ በኋላ ትመለሳለች ብሎ ያሰበ ሰው አልነበረም። የሴቶች ቤት ፀጥ ረጭ ብሎ አመሸ፡፡ እራት እንኳ የበላ የለም፡፡ ሁሉም በየፍራሹ ላይ ኩርትም ብሎ የሚያወራው ስለሚስጥረ ነው። ከሌሊቱ በአምስት ሰዓት ላይ የውጭው በር ሲከፈት ሁሉም በድንጋጤ ያሉበት ጠፉቸው። የሚከተለውን ሲጠብቁ መዝጊያው ተዘጋ፡፡ ሁሉም ለመነሳት ተፍጨረጨረ።

ሚስጥረ ተመልሳ መምጣቷ ነበር። ደስታና መደነቅ ትንሿን ግቢ ሞላት። የተለመደው እንክብካቤ ተደረገላት፡፡ ብዙው ሰው ለሚስጥረ ጥንካሬ አድናቆት ቢኖረውም "ለምን ራሷን ትጎዳለች?" የሚል ንዴት ስላለበት ስለሁኔታው የሚጠይቃት የለም። በሚቀጥለው ቀን ፍሬ ስትጠይቃት ማታ ቤቷ እንደወሰዷትና መግረፊያው ተወስዶ ማግኘታቸውን እርሷ ግን መኖሩን በፍፁም እንደማታውቅ ማስረዳቷን ነገረቻት።

"የቱን ያህል እንዳስጠላኋቸው ቢታወቀኝም ማታ ስላልገረፉኝ አመሰገንኳቸው" አለች እፎይታዋን በሚያሳይ መልኩ።

"ሰው ሲቆርጥ የቱን ያህል መከራና ስቃይ እንደሚችል ያየችው ከሚስጥረ ነው። "የእርሷን ያህል ጥንካሬ ቢኖረኝ እንዴት በተደሰትኩ ነበር?" ትላለች ፍሬ ሁልጊዜ ስለጥንካሬና መስዋዕትነት ከተነሳ።

ፍሬ እንዳሰበችው ሆነ፤ ድንቅነሽ ስቃይ ሳይበዛባት በነካ ነካ ግርፋት ብቻ ታለፈች። እርሷና ድንቅነሽ እስር ቤት ውስጥ የበለጠ ተቀራረቡ የበለጠም ጓደኝነት መሰረቱ፡፡ ወራትም ተቆጠሩ። የእስር ቤቱንም ሕይወት ተላመዱት፡፡ የፍሬ የእግር ቁስል በመጠኑ ጠገግ ብሎ ቅርፊት ይያዝ እንጂ ደምና መግሉ ገና አልደረቀም።

በሦስት ወራት ቆይታ ሚስጥረን ጨምሮ ብዙ የልብ ጓደኞች አፈራች ፍሬ፡፡ እነዚህ ሴቶች ጭንቃቸውን የሚያካፍሏትና ጭንቀቷን የምታካፍላቸው ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ ምዕራፍን በሕይወቷ ሙሉ አትረሳትም። ምዕራፍ አጭርና ቀጭን ልጅ ነበረች፡፡ ልቧና ጥንካሬዋ ግን በፍጹም ከሰውነቷ ትንሽነት ጋር የማይሄድ አይበገሬ መንፈስ ነበራት። አንድ ቀን ፍራሻቸው ላይ ጋደም ብለው እየተጫወቱ ሳለ፤

"እስኪ ዛሬ ልደግፍሽና እግርሽን አለማምጂው" አለች ምዕራፍ።

"ይሆንልኛል ብለሽ ነው?" አለቻት የእግሮቿን ውስጥ ለማየት እያጎነበሰች።

"ግዴለሽም ቆሻሻ እንዳይደርስበት ካልሲ አድርጊና እንሞክር" አለችና አበረታታቻት። ለመሞከር ተነሱ።



"ስለጨነቀኝ ነው እንዘዋወር ያልኩሽ" አለች ምዕራፍ ጥቂት ለመራመድ ጥረት እንዳደረጉ።

"ምነው ምን ጨነቀሽ" አለቻት ፍሬ ጭንቀቷን ለመጋራት ከልብ በመነጨ ፍላጎት።

"እኔ እዚህ ቤት ምንም አልተናገርኩም፤ መናገርም አልነበረብኝም፤ አሁን ግን ፈርቻለሁ፡፡ ሰሞኑን ስለእኔ የሚያውቅ ልጅ እዚህ ቤት መጥቷል፡፡ እርሱ አየኝ ማለት ደግሞ አለቀልኝ ማለት ነው፡፡ ከዚህ በፊት እንደምንም ራሴን ለመደበቅ የሞከርኳቸው ሙከራዎች ተሳክተውልኝ የመጡት ሁሉ ሳያዩኝ አምልጫለሁ፤ አሁን ግን እየከበደ ይመስለኛል፤ ስለዚህ ሽፋን እፈልጋለሁ" አለች።

ስለምዕራፍ ከዚህ በላይ ማወቅ አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ይህንን ጉዳይ ለድንቅነሽና ለሌሎች ሁለት እስረኞች ነገረች። ከዛን እለት በኋላ እስረኞች የሚያውቁት ሰው ለመፈለግ ወደሴቶች ቤት ሲመጡ ምዕራፍን የመሸፈን ሥራቸውን ለመወጣት መነጋገር አያስፈልጋቸውም፡፡ ከብዙ ዓይኖችም አድነዋታል። አንድ ቀን ግን የማይሸፈን ፈላጊ መጣባት።

ከቀኑ ወደአምስት ሰዓት አካባቢ ሲሆን የብረት በሩ በኃይለኛው ተበረገደና ያ ዐዓይኑን የሚያጉረጠርጥ ሰውዬ ሌሎቹን አስከትሎ ገባ።

"የታለች ያች አይጥ" አለና አምባረቀ፤ ሁሉም አፈጠጡ።

"ማረፊያ ያሳጣሽ ምዕራፍ!" አለ። ልቦቻቸው እየዘለለ ጉሮሮአቸው ውስጥ ተወተፉ፤ እስረኞቹ ተያዩ። ምእራፍ ከነበረችበት ወደሰውየው ስትሄድ በቀስታ እጇን አውለብልባ ተሰናበተቻቸው። እንደማትመለስ አውቃው ነበር። የሚያማምሩትን ትናንሽ ጥርሶቿን ገለጥ አድርጋ በፈገግታ ቃኘት አደረገችና ወደተጠራችበት ወጣች። ሰውነቷ ትንሽ ቢሆንም የውስጥ ኩራትዋ ግርማ ሞገስ አላበሳት። አንጠልጥለው ይዘዋት ወጡ፡፡ ደርግ ጽሕፈት ቤት መወሰዷን ከመስማታቸው በስተቀር ከዛ በኋላ ስለሆነው ነገር ምንም አላወቁም፤ ከጊዜ በኋላ ግን መገደሏን ሰምተዋል። እናም ምዕራፍ ከትንሽ ሰውነቷ፣ ከመንፈስ

ኩራትዋ፣ ጥንካሬዋና ከሚያምረው ፈገግታዋ ጋር ለዘለዓለም በፍሬ ልብ ውስጥ ታትማ ትኖራለች።

* * * *

ሮቤል ሳሎን ቤት ጠረጴዛ ላይ ትልቅ ወረቀት ዘርግቶ የስዕል እርሳሶችና ላጲስ ደርድሮ በርከክ አለ። ቀና ብሎ ግድግዳ ላይ ያለውን ስዕል ሲመለከት ቆየና ትልቁ ወረቀት ላይ ስዕሉን መሥራት ቀጠለ። ቀና ጎንበስ እያለ ብዙ ቆየ። ወረቀቱ ላይ የሠራውን ስዕል ለመመልከት ከተንበረከከበት ብድግ አለና ራቅ አለ። ስዕሉ አላማረውም።

ወረቀቱን ጭምድድ አደረገና ወለሉ ላይ ወረወረው፤ እንባው በዓይኖቹ ሙልት ብሎበት ሶፋው ላይ ተቀመጠ። ሊሠራው ያሰበውን ግርግዳው ላይ ያለውን የቤተሰባቸውን ፎቶ አተኩሮ ተመለከተው። በፎቶው ላይ ያሉትን ሰዎች ቆጠራቸው ስድስት ሰዎች አሉ፤ አሁን ግን ሁለት ብቻ ናቸው እዚያ ቤት ውስጥ የሚኖሩት፤ እርሱና እናቱ። የበለጠ ሆድ ባሰው።

በፊት ትምህርት አስጨንቆት አያውቅም፤ የከበደውን ነገር የሚያስረዱት ወንድምና እህቶቹ ስለነበሩለት በልበሙሉነት ነበር የሚማረው። በተለይ ሮቤልን ድርስትና ስዕል ማሰራት የሚሚ ድርሻ ነበር። ዱሮ ዱሮ እንኳን የቤት ሥራ ኖሮበት ባይኖርበትም ቅዳሜና እሁድ ከሚሚ ጋር ስዕል መሥራት የተለመደ ውሏቸው ነበር። ስትሠራ ለሮቤል ስታሳየው፤ አላምር ያላትን ቀዳዳ ስትጥል፣ ደግሞ ሌላ ሠርታ "እስኪ ይሄንን ሥራ" ብላ ስትሰጠው፤ ቤቱ በወረቀት የሚሞላበትና ከፍሬ ጋር የሚጣሉባቸው አጋጣሚዎች፤ እርሱ ለሚሚ አግዞ ከፍሬ ጋር የሚጣላባቸው ጊዜያት ብዙ ነበሩ። ሚሚን በብዙ ነገር ያስታውሳታል። ድርሰት መጻፍ ትወድ ነበር፤ ብዙ ጊዜ አንብባለታለች፤ አስቃዋለች፣ አስለቅሳዋለች። በትዝታው ፈገግ አለ። ወዲያው ደግሞ ግንባሩን ክስክስ አደረገና ግርግዳው ላይ ያለውን ፎቶ ተመለከተው። ሚሚ የሄደችበትን ቀን አስታወሰው፤ ርብሽ ብላ ሁሉ ነገር ድንግርግር ያለባት ትመስል ነበር።



"በናትሽ ሚሚ ድርሰቴን አንብቢልኝ" አላት ተረጋግታ እስክትቀመጥ ሲጠብቃት ቆይቶ።

"እሺ ትንሽ ታገሰኝ" አለችው። እንቅልፉ ሲመጣበት ሊያስታውሳት ወዳለችበት ገባ። ወረቀት ምናምን ስታተረማምስ አገኛት።

"መጣሁ ሮቢ እዛው ጠብቀኝ፤ አምስት ደቂቃ ብቻ" አለችው ጠበቃት።

ሶፋው ላይ እንደተቀመጠ እንቅልፍ ወስዶት ኖሮ ሚሚ ስትመጣና ስትቀሰቅሰው ብርግግ ብሎ ተነሳ። ድርሰቱን እንዲሰጣት ጠየቀችውና ሰጣት፤ አነበበችው።

"በጣም አሪፍ ነው ሮቢ፤ ጎበዝ ልጅ እኮ ነህ" አለችና ሳመችው። ከዛ የሚታረመውን እንዲያርም ነገረችውና በድጋሚ ሳመችው። ለምን እንደዛ እንዳደረገች የገባው፤ የስንብት እንደነበረ የተረዳው ግን ቆይቶ ነው። እንባው ታገለው፤ ትንሽ ሲወርድ ግን በእጁ አሻሸና አስቆመው።

ፍሬን የሚመለከታት ልክ እንደእናቱ ነው፤ ከልጅነቱ አንስቶ ሁሉን ነገር የምታደርግለት እርሷ ነበረች። ሰውነቱን የምታጥበው፣ ልብሱን የምታለብሰው፣ ከእናቷ ጋር ገበያ በሄደች ቁጥር ካናቴራና ካልሲ የምትገዛለት፣ ብርቱካን፣ ሙዝና ብስኩት የምታመጣለት ፍሬ ነበረች። ከትምህርት ቤት ሲመጣ መክሰሱን የሚጠይቀው እርሷን ነበር። ትምህርት ቤት የምታስመዘግበው ለአንዳንድ ነገሮች የምትሄድለትም እርሷ ነበረች። ዘመቻ የሄደች ጊዜ እንዴት ትናፍቀው እንደነበረ አስታወሰ። አሁንም እንባው በዐይኖቹ ሞላ።

ደግሞ ቃለአብንና በላይሁንን አስታወሳቸው፤ ከእነርሱ ጋር ኳስ ሜዳ ለመሄድ ሲል በጠዋት ይነሳ የነበረውና ልብሳቸውን ይዞ የሚጠብቃቸው ሁሉ ትዝ አለው። እነርሱ ጨዋታ አብቅተው ቆም ብለው ሲያወሩ እርሱና ጓደኞቹ ደግሞ ለትንሽ ደቂቃ ይጫወቱ የነበረው ታወሰው። ከነቃለአብና በላይሁን ጋር ኳስ ይጫወቱ ከነበሩት ውስጥ አሁን ማንም የለም፤ ቃለአብና በላይሁን

ኩራትዋ፣ ጥንካሬዋና ከሚያምረው ፈገግታዋ ጋር ለዘለዓለም በፍሬ ልብ ውስጥ ታትማ ትኖራለች።

* * * *

ሮቤል ሳሎን ቤት ጠረጴዛ ላይ ትልቅ ወረቀት ዘርግቶ የስዕል እርሳሶችና ላጲስ ደርድሮ በርከክ አለ። ቀና ብሎ ግድግዳ ላይ ያለውን ስዕል ሲመለከት ቆየና ትልቁ ወረቀት ላይ ስዕሉን መሥራት ቀጠለ። ቀና ጎንበስ እያለ ብዙ ቆየ። ወረቀቱ ላይ የሠራውን ስዕል ለመመልከት ከተንበረከከበት ብድግ አለና ራቅ አለ። ስዕሉ አላማረውም።

ወረቀቱን ጭምድድ አደረገና ወለሉ ላይ ወረወረው፤ እንባው በዓይኖቹ ሙልት ብሎበት ሶፋው ላይ ተቀመጠ። ሊሠራው ያሰበውን ግርግዳው ላይ ያለውን የቤተሰባቸውን ፎቶ አተኩሮ ተመለከተው። በፎቶው ላይ ያሉትን ሰዎች ቆጠራቸው ስድስት ሰዎች አሉ፤ አሁን ግን ሁለት ብቻ ናቸው እዚያ ቤት ውስጥ የሚኖሩት፤ እርሱና እናቱ። የበለጠ ሆድ ባሰው።

በፊት ትምህርት አስጨንቆት አያውቅም፤ የከበደውን ነገር የሚያስረዱት ወንድምና እህቶቹ ስለነበሩለት በልበሙሉነት ነበር የሚማረው። በተለይ ሮቤልን ድርስትና ስዕል ማሰራት የሚሚ ድርሻ ነበር። ዱሮ ዱሮ እንኳን የቤት ሥራ ኖሮበት ባይኖርበትም ቅዳሜና እሁድ ከሚሚ ጋር ስዕል መሥራት የተለመደ ውሏቸው ነበር። ስትሠራ ለሮቤል ስታሳየው፤ አላምር ያላትን ቀዳዳ ስትጥል፣ ደግሞ ሌላ ሠርታ "እስኪ ይሄንን ሥራ" ብላ ስትሰጠው፤ ቤቱ በወረቀት የሚሞላበትና ከፍሬ ጋር የሚጣሉባቸው አጋጣሚዎች፤ እርሱ ለሚሚ አግዞ ከፍሬ ጋር የሚጣላባቸው ጊዜያት ብዙ ነበሩ። ሚሚን በብዙ ነገር ያስታውሳታል። ድርሰት መጻፍ ትወድ ነበር፤ ብዙ ጊዜ አንብባለታለች፤ አስቃዋለች፣ አስለቅሳዋለች። በትዝታው ፈገግ አለ። ወዲያው ደግሞ ግንባሩን ክስክስ አደረገና ግርግዳው ላይ ያለውን ፎቶ ተመለከተው። ሚሚ የሄደችበትን ቀን አስታወሰው፤ ርብሽ ብላ ሁሉ ነገር ድንግርግር ያለባት ትመስል ነበር።



"በናትሽ ሚሚ ድርሰቴን አንብቢልኝ" አላት ተረጋግታ እስክትቀመጥ ሲጠብቃት ቆይቶ።

"እሺ ትንሽ ታገሰኝ" አለችው። እንቅልፉ ሲመጣበት ሊያስታውሳት ወዳለችበት ገባ። ወረቀት ምናምን ስታተረማምስ አገኛት።

"መጣሁ ሮቢ እዛው ጠብቀኝ፤ አምስት ደቂቃ ብቻ" አለችው ጠበቃት።

ሶፋው ላይ እንደተቀመጠ እንቅልፍ ወስዶት ኖሮ ሚሚ ስትመጣና ስትቀሰቅሰው ብርግግ ብሎ ተነሳ። ድርሰቱን እንዲሰጣት ጠየቀችውና ሰጣት፤ አነበበችው።

"በጣም አሪፍ ነው ሮቢ፤ ጎበዝ ልጅ እኮ ነህ" አለችና ሳመችው። ከዛ የሚታረመውን እንዲያርም ነገረችውና በድጋሚ ሳመችው። ለምን እንደዛ እንዳደረገች የገባው፤ የስንብት እንደነበረ የተረዳው ግን ቆይቶ ነው። እንባው ታገለው፤ ትንሽ ሲወርድ ግን በእጁ አሻሸና አስቆመው።

ፍሬን የሚመለከታት ልክ እንደእናቱ ነው፤ ከልጅነቱ አንስቶ ሁሉን ነገር የምታደርግለት እርሷ ነበረች። ሰውነቱን የምታጥበው፣ ልብሱን የምታለብሰው፣ ከእናቷ ጋር ገበያ በሄደች ቁጥር ካናቴራና ካልሲ የምትገዛለት፣ ብርቱካን፣ ሙዝና ብስኩት የምታመጣለት ፍሬ ነበረች። ከትምህርት ቤት ሲመጣ መክሰሱን የሚጠይቀው እርሷን ነበር። ትምህርት ቤት የምታስመዘግበው ለአንዳንድ ነገሮች የምትሄድለትም እርሷ ነበረች። ዘመቻ የሄደች ጊዜ እንዴት ትናፍቀው እንደነበረ አስታወሰ። አሁንም እንባው በዐይኖቹ ሞላ።

ደግሞ ቃለአብንና በላይሁንን አስታወሳቸው፤ ከእነርሱ ጋር ኳስ ሜዳ ለመሄድ ሲል በጠዋት ይነሳ የነበረውና ልብሳቸውን ይዞ የሚጠብቃቸው ሁሉ ትዝ አለው። እነርሱ ጨዋታ አብቅተው ቆም ብለው ሲያወሩ እርሱና ጓደኞቹ ደግሞ ለትንሽ ደቂቃ ይጫወቱ የነበረው ታወሰው። ከነቃለአብና በላይሁን ጋር ኳስ ይጫወቱ ከነበሩት ውስጥ አሁን ማንም የለም፤ ቃለአብና በላይሁን

እንደታሰሩት ሁሉ ሌሎቹም ታስረው ይሆናል። ሠፈሩ በጣም ያስጠላል።

ሮቤል ትዝታው ሆድ አስባሰው፤ አሁን እንባውን ማቆም አልቻለም። አለቀሰ፤ ሁሉንም እያሰበ አለቀሰ። እንባው ጋብ ሲልለት ጨምድዶ የጣለውን ወረቀት ተመለከተው፤ ሚሚን እንደገና አሰባት። ያንን ስዕል ለምን ሊሠራው እንደፈለገ አሰበ፤ ሌላ ምንም ምክንያት አልነበረውም፤ ብቻ ሁልጊዜ ሲያየው የሚሰማው ስሜት ስላለ ፎቶውን በእጁ ቢሠራው ደስ እንደሚለው አስቦ ነው። የጣለውን ወረቀት አነሳና እንደገና ዘረጋው።

"ሮቢ!" ብለው ጠሩት እናቱ።

"እሜት እማ" ብሎ ወደውስጥ ገባ። እናቱ ይደንቁታል፤ ለአፍታ እንኳ ያለማረፋቸውና ሙሉ ቀን የመሥራታቸውና ለጸሎት የመትጋታቸው ነገር ይገርመዋል።

"የበላይሁንን እናት ቡና ጠጡ በላቸው" አሉት።

የበላይሁን እናት በጣም ያሳዝኑታል። ዱሮ ደስተኛና ጤነኛ የነበሩ ሴት አሁን ግን በጣም የሚተክዙና የሚታመሙ ሆነዋል። ሊጠራቸው ሲሄድ እውጭ የበላይሁንን እህት አገኛት። እርሷም እንዲሁ በጣም ተለውጣበታለች፤ ዱሮ በጣም ዘናጭ ነበረች። የሚፈልጓት ወንዶች ልጆች ብዛት በጣም ይገርመው ነበር፤ እርሷን እንዲጠራላቸው በላኩት ቁጥር ብስኩትና ከረሜላ ይሰጡት የነበሩትን አይረሳቸውም። አሁን ግን እንዳቸውም የሉም።

ቤት ሲገባ የበላይሁን አባት ጋቢ እንደለበሱ እሶፋ ላይ ተቀምጠዋል፤ አሁን አሁን ብዙ ጊዜ ከሥራ ይቀራሉ፤ እንደሚያማቸውም ሰምቷል። እርሳቸውም ያሳዝኑታል። ዱሮ ወደ ሥራ ሲሄዱም ሆነ ከሥራ ሲመጡ ሲያገኙት ራሱን አሸት አድርገው ግንባሩን ሳይስሙትና ስለትምህርቱ ሳይጠይቁት አያልፉም ነበር። አሁን ግን እንደዛ አይደሉም፤ ሁሉ ነገር በጣም ይገርመዋል።



"እንደምን አደሩ አባባ" አላቸው፤ የሰሙት አልመሰለውም። አለፋቸውና ወደውስጥ ገባ፤ የበላይሁን እናት አጭር ዱካ ላይ ተቀምጠው ራሳቸውን ጉልበታቸው ላይ ደፍተዋል።

"እማማ እንደምን አደሩ" አላቸው እበሩ ላይ ቆሞ።

"እንዴት አደርክ ሮቢ" አሉት ቀና ብለው። ዐይኖቻቸው ቀልተዋል፤ ባጠቃላይ ፊታቸው ተጎሳቁሏል።

"ቡና ጠጡ" አላቸው።

"ይቺን እናትህን እግዜሩ ከብረት ይሆን የሠራት ልጄ? በል መጣሁ፤ እኛማ ነገር ዓለሙን ትተነዋል" አሉ ከተቀመጡበት እየተነሱ።

ሮቤል ከነበላይሁን ቤት ሲወጣ ሚሚ ከሄደች፣ በላይሁን፤ ፍሬና ቃለአብ ከታሰሩ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ እየቆጠረ ነበር። ሚሚ ከሄደች ስድስት ወራት እነበላይሁን ከታሰሩ ደግሞ ከሶስት ወራት አልበለጣቸውም ግን ሁሉ ነገር እንዳልነበረ ሆኗል፤ ጊቢው ደስታ ኖሮበት የሚያውቅ አይመስልም።

እቤት ሲገባ እናቱ ሁሉን ነገር አቀራርበው ተቀምጠዋል። "ጠራሃቸው?" አሉት።

"አዎን ጠራኋቸው፤ ቤታቸው ግን በጣም ያስፈራል፤ ስትገቢ የሚሰማሽ ሀዘን ነው። እማ! አንቺ ግን ጎበዝ ነሽ፤ አንቺ ባለሽ ቤታችን እንደነሱ ቤት አያስፈራም። የበላይሁንም እናት ጎበዝ ነች አሉ" አላቸው።

"ብርታትን የሰጠኝ እግዚአብሔር ይመስገን!" አሉና አቀረቀሩ ሮቤል ሃዘናቸውን እንዳይመለከትባቸው የሚያደርጉትን ጥንቃቄ እያሰበ ።

ሮቤል ይህ ሁኔታ ተለውጦ የሚያይበት ቀን እየናፈቀው፤ በግቢያቸውና በቤታቸው የወትሮው ደስታ የሚመለስበት ጊዜ ቅርብ እንዲሆን ተመኘ።

* * * *

መቼም ያ የብረት መዝጊያ በተከፈተ ቁጥር መደንገጥ አይቀርም፡፡ ማን ሊጠራ ይሆን? ማን ሊመጣብን ይሆን? ማለት የተለመደ ነው። አንድ ቀን እንደልማዱ በሩ በኃይል ተበረገደ። ሁሉም ባሉበት ተደናግጠው ተቁለጨለጩ።

ከጀርባው የተገፈተረ ሰው እየተምዘገዘገ በተከፈተው በር ኸርው ብሎ ወደግቢው ውስጥ ወደቀ። ግቢው ውስጥ የነበሩ ሴት እስረኞች በድንጋጤ አፋቸውን ከፍተው የወደቀውን ሰው ተመለከቱት። ብዙዎቹ እየሮጡ ወደየክፍሎቻቸው ገቡ። ከሰውየው ኋላ ተከትለውት የነበሩት ገራፊዎች ከግራና ቀኝ አንጠልጥለው አነሱትና ደም በሚተፋው እግሩ እንዲቆም አደረጉት። ሰውየው የደነዘዘ ይመስላል በሚሰቀጥጠው እግሩ ይረግጥበታል፤ አንገቱ ጭንቅላቱን መሸከም ያቃተው ይመስል ወዲያና ወዲህ ይዝለፈለፋል። ዐይኖቹም ፈጠዋል እንጂ አያዩም፤ ብቻ በደመነፍስ ነው ያለው።

"ሻወር አስገባው ይነቃል" አለ አንደኛው ገራፊ። እያዳፉ ወደሻወር ውስጥ አስገቡት። ቀዝቃዛውን ውሃ እላዩ ላይ ለቀው በያዙት መግረፊያ ጀርባውን ይደበድቡት ጀመር። ሰውየው ድምጽ አላሰማም። ጥቂት ቆይተው ደግሞ እየጎተቱ አወጡትና ወደወንዶቹ ማደሪያ ወሰዱት።

እነርሱ ሲወጡ ያመቁትን እንባ ያወረዱ በርካታ ናቸው። ግቢው የሀዘን ጥላ እንዳጠላበት ቆየ። ወደከሰዓት በኋላ ላይ ደግሞ ያ መዝጊያ እንደገና ተከፈተ፤ ሁሉም እስረኞች ባሉበት በድንጋጤ ተፋጠጡ።

"ዲሞ ተመታ ብለሽ ነው ሁልሽም ያኮረፍሽው? ለዚያውም ለማታውቂው ዲሞ! አሁን በደንብ ታዝኛለሽ ሁልሽም" አለ በሩን የከፈተው ሰው። እስረኞቹ የበለጠ ደነገጡ።

"ፍሬሕይወት፤ ፍሬ ያሳጣሽ፤ የት ነች? ነይ ውጪ" አለ ሰውየው፡፡ ፍሬሕይወት ከው ብላ ደነገጠችና ተነስታ ወጣች። ወደዚያ ዳግም ልታየው ወደማትፈልገው ክፍል ተወሰደች። እስረኞቹ የበለጠ ተደናገጡ፤ "አለቀላት!" አሉ ሁሉም በሆዳቸው።



"እንደገና ከምገረፍስ ብሞት ይሻለኛል" አለች ፍሬሕይወት ለራሷ።

"የማሰቃያ ክፍሉን ደረጃ ወጥታ በሩ ላይ ስትደርስ ግን ያየችውን ማመን አልቻለችም። እጆቹና እግሮቹ የኋሊት ተቆራኝተው (ስምንት ቁጥር ይባላል ይህ ዓይነቱ እስር) ወለሉ ላይ በደረቱ የተደፋውን በላይሁንንና ወንበር ላይ የተቀመጠውን መንክርን ተራ በተራ ተመለከተቻቸው። ውስጧ ቆሰለ። መንክር የሰፈራቸው ልጅ ነው፡፡ የነበረውን ድርጅታዊ ተሳትፎ ባታውቅም በወጣት ማህበራት ስብሰባ ላይ በሚደረግ ተሳትፎ እንኳን የረባ ጉዳይ ሲያነሳ ሰምታው አታውቀም፡፡ እዚያ እስር ቤት ስለመሆኑም በፍጹም አልሰማችም። በላይሁንም መቼና በምን ምክንያት ወደእዚህ እስር ቤት እንደመጣ አልገባትም። እርሷና መንክር ከሰላምታ ያለፈ መግባባት ባይኖራቸውም በላይሁንና መንክር ግን የሰፈር ልጅነት ብቻ ሳይሆን ዝምድናም አላቸው።

በክፍሉ ውስጥ ሌላ ሰው የለም፡፡ ለምን እንደተጠራች ግራ ገብቷት ቆመች።

"አየሽው" አላት መንክር ወደበላይሁን እያመለከተ።

"እና ምን ይሁን?" አለችው እየተናነቃት የነበረው ንዴት ገንፍሎ።

"እንድትሰናበችው ተፈቅዶልሽ ነው" አላት በማሾፍ ዓይነት።

ውስጧ ተቃጠለባት፡፡ የበላይሁንን ስቃይ መቋቋም አቃታት። ከውስጥ ሱሪ በስተቀር ሌላ አልለበሰም። ከጉልበቱ በታች ያለው የሰውነቱ ክፍል በእሳት የተቃጠለ ይመስላል። የተፈጥሮ ቆዳውን ማየት በፍጹም አይቻልም። ውስጥ እግሩ ለማየት ይዘገንናል፡፡ ከቁርጭምጭሚቱ ላይ ያረፈው የኤሌክትሪክ ገመድ ስላጠበቀው ከውስጥ እግሩ ቁስል ላይ የደምና ውሀ ቅልቅል ፈሳሽ እየወረደ እጀርባው ላይ ተጠራቅሟል። ጀርባውና እጆቹም እንዲሁ በቁስል ተወረዋል፤ ምናልባትም ሆዱና ደረቱ ላይም ቁስለት ይኖረው ይሆናል።

በላይሁን ድምጿን ሰምቶ ቀና አለ፡፡ የግንባሩ መስመሮች ተጨማደው በጣም ትልቅ ሰው አስመስለውታል፣ የፊቱ ቆዳ ከመጥቆሩ የተነሳ ጥቀርሻ መስሏል፣ ዐይኖቹ በእልህ፣ በንዴትና በስቃይ ደም ለብሰዋል።

"እናንተ አረመኔዎች! በሰው ስቃይ ስለምትደሰቱ እንጂ ለምን አትገድሉኝም" አለና ጮኸ በላይሁን።
"እናንተ ጨካኞች!" አለች ፍሬም። ከመቅጽበት ጀርባዋ ላይ ያረፈው አለንጋና ተከታትሎ የረገጣት እግር ከበላይሁን አጠገብ በአፍጢሟ እንድትደፋ አደረጋት። እንደወደቀች ሌላ እርግጫ ወገቧን ደገማት፡፡ ከመሬቱ ጋር የተደባለቀች መሰላት።

"ተነሽ ሸርሙጣ!" አላት መንክር። ከህመሙ ሁሉ በላይ የመንክር ድምጽ ህሊናዋን ሸነቆጠው። እንደምንም ብላ ለመነሳት ሞከረች፡፡ ቀና ስትል ከአፍና ከአፍንጫዋ የሚፈሰው ደም የለበሰችውን ልብስ አጨቀየው። ገራፊዎቹ በክፍሉ ውስጥ ተበራክተዋል፡፡ ያ ጫኺ አለቃቸውም አለ፡፡ ወገቧ ላይ የተረገጠችው ርግጫ በፍጹም የምትችለው አልሆነም፤ የቱንም ያህል እልህ ቢይዛት ለመነሳት አልቻለችም። ከወገቧ በታች ያለው ሰውነቷ የራሷ አልመሰላት አላት፡፡ በጭራሽ አልታዘዝ አላት።

"እንሳና ወደዛ ጣላት" አለ ከገራፊዎቹ አንዱ። እራሷ ብኻር ማለት ጀምሯል።

"እናንተ አረመኔዎች! ከሀዲዎች!..." የሚለው የበላይሁን ድምጽ ይሰማታል።

"በረንዳው ላይ ጣሏት ይህችን ጨምላቃ፤ በኋላ እንደገና ትገባታለች" የሚለው የአለቅዬው ድምጽም ተከታትሎ እንደህልም ተሰማት፡፡ እጆችና እግሮቿን ይዘው ሲያንጠለጥሏት በስመመን ተሰምቷታል።

* * * *

የፍሬሕይወት እናት እንደተለመደው በጠዋት ተነስተዋል፤ በእንባ ብዛት የሞጨሞጨት ዐይኖቻቸው ጠዋት ሲነሱ አልገለጥም ብለው



ቢያስቸግሯቸውም ሀኪም ቤት ሄደው ለመታከም ጊዜውም ሆነ ሞራሉ አልነበራቸውም። ለብ ባለ ውሀና በሳሙና ታጥበው በነጠላቸው አደራረቁና ወደእለቱ ሥራቸው ገቡ።

ለፍሬና ለቃለአብ እስር ቤት የሚወስዱትን ስንቅ፤ ለሮቤል የሚቋጥሩትን ምሳና ቁርሱን፤ ማዘጋጀት የየዕለቱ ሥራቸው ነው፤ ሁለት ምድጃ ጥደው ተፍ ተፍ ይላሉ የፍሬሕይወት እናት። የሆነው ሁሉ ሁልጊዜም እንደገረማቸው ናቸው፤ ሥራቸውን እየሠሩ አእምሮአቸው የማይሄድበት ቦታ የለውም፤ የዱሮውንና ዛሬ እየሆነ ያለውን ያስቡና ምርር ይላቸዋል፤ እንባቸው ሳያዙት መውረድ ይጀምራል። ለቅሶ ጓደኛቸው ሆኗል።

"እስኪ በዚሁ በቃሽ በለኝ!" ይላሉ ደግሞ የባሰ እንዳይመጣባቸው እየሰጉ። ቃለአብ እስር ቤት ሲገባ ብዙ የሰፈሩ ወጣቶችም የታሰሩበት ሰሞን ስለነበር የጋራ ጉዳይ ሆኖ ነበር። ፍሬሕይወት መታሰሯን ሲሰሙ ግን የሆኑትን ነገር ሲያስቡት ይደንቃቸዋል።

ፍሬሕይወት መደወሏን ባቋረጠችባቸው ቀናት ሌሊትና ቀን አንብተዋል፤ "ምነው አምላኬ ልጆች ባትሰጠኝ ምን ነበረበት? እኔንስ ለምን እስከአሁን አቆየኸኝ? በሌላ ብትቀጣኝ ምናለበት?" እያሉ ፈጣሪያቸውን ጨቅጭቀውታል።

"እምንም ውስጥ ትሁን ብቻ እዚህ ነኝ የሚል ወሬ የሰማሁ እንደሆነ..." ብለው ለየታቦታቱ ሁሉ የስዕለት መዓት ደርድረዋል።

ታዲያ ያን ቀን የበላይሁን እናት መጥተው "ስርጉት! ፍሬሕይወት ተገኘች አሉ..." ብለው ገና ሳይጨርሱ የፍሬሕይወት እናት ዕልልታቸውን ቅልጥ አደረጉት። የበላይሁን እናት ግራ ገባቸው።

"ኧረባክሽን ስርጉት እስር ቤት እኮ ነው ያለችው" አሏቸው በግድ እያስቀመጧቸው።

በመጠኑ ተረጋግተው ራሳቸውን ሲያውቁ ድርጊታቸው ለራሳቸውም ገረማቸው። "ምናባቴን ላድርግ የበላይ እናት? አይፍረዱብኝ"

አሏቸው። "መችም እንደሚሚ የደረሰችበት ሳይታወቅ ከምትቀር ይሻለኛል" አሉ የፍሬሕይወት እናት ስለታቸውን ሁሉ እያሰቡ።

የታሰረችበትን በጥየቃ አግኝተው እየተመላለሱ ቢጠይቋትም ፍሬሕይወትን በአካል አይተዋት አያውቁም። ቢሆንም በምትልካቸው መልእክቶች በትክክል እርሷ መሆኗን አረጋግጠዋል። ቃለአብ መታሰሩንም ነግረዋታል። "አይዞሽ!" ብላ ትልክባቸዋለች ሁልጊዜም።

ዛሬም የሁሉንም ምግብ በየሳህናቸው ከተቱና ለመሄድ ተዘጋጁ። ሮቤል ግን እስካሁን አልተነሳም። የትምህርት ቤት መሄጃ ሰዓት መድረሱን ሲመለከቱ ሊቀሰቅሱት ወደ ውስጥ ገቡ። ሮቤል በጣም ዝምተኛና ምንም ነገር የማያስደስተው ልጅ ሆኖባቸዋል፤ ቤታቸው ጭር ሲልበት ሬዲዮና ቴሌቪዥኑን አንድ ላይ ከፍቶ እርሱ ግን ጥቅልል ብሎ ይተኛል። እንቅልፍ እንደማይወስደው ያውቃሉ፤ ግን ምን ይበሉት? ያሳዝናቸዋል፤ ከወንድሙና ከእህቶቹ ጋር የነበረው ጨዋታና ሳቅ ሁሉ ጠፍቶ ብቻውን ሲቀር እንዲህ ቢሆን ምን ይፈረድበታል?

ሮቤልን አልጋው ላይ እንደተቀመጠ አገኙት "ተነስ እንጂ ሮቤል ሰዓት ደርሷል እኮ" አሉት አበሩ ላይ ቆም ብለው።

"እባክሽን ዛሬ ልቅር እማ" አላቸው።

"ይሄማ አይሆንም ሮቢ ለምንድነው የምትቀረው?" አሉት

እየቀፈፈው ተነሳና ሊተጣጠብ ወደደጅ ወጣ። እርሳቸውም ቁርሱን ሊያቀራርቡለት ወደ ጓዳ ገቡ። ሮቤል እንደነገሩ ቁርሱን ቀማምሶ ሲሄድ እርሳቸውም የቃለአብንና የፍሬሕይወትን ስንቅ ይዘው ወጡ፤ ሁሌም በመጀመሪያ የቃለአብን ያደርሱና ከዚያ ደግሞ ወደፍሬሕይወት ይሄዳሉ። በየዕለቱ ሳይሄዱ በፍጹም አይቀሩም፤ የባሰ ችግር ካልገጠማቸው በስተቀር።

"ያሉበትንም አይቶ መመለስ ተስፋ ነው ብዬ እኮ ነው የበላይ እናት" ይላሉ ሁልጊዜም።



ቃለአብ የታሰረበት ቅርብ ነው፤ የሄዱ ሳይመስላቸው ደረሱና ምግቡን ሰጥተው ዕቃ ለመጠበቅ ቆሙ። ዕቃ ሳይመለስላቸው ብዙ በመቆየቱ ግራ ገብቷቸው ሳህኑን የሰጧትን ልጅ ጠብቀው "ምነው ልጄ ሳህኑን አላመጣሽልኝም" አሏት። ፊትለፊት ልታያቸው አልደፈረችም ፊቷን አዙራ ተመልሳ ወደውስጥ ገባች። ልባቸው ገነገነ፤ አንደኛውን የአብዮት ጥበቃ ሊጠይቁ ጠጋ ሲሉ ሌላኛው ከወደውስጥ ብቅ አለ፤ ምግብ ያመጡበትን ዕቃና የቃለአብን ልብሶች ይዟል። ፈጠን ብለው ተቀበሉት፤ ሳህኑ ምግብ አለው። አፋቸው ደረቀባቸው "ም...ነው ምግቡን..." ብለው ሳይጨርሱት "በቃ በቃ እርሱ የለም" አላቸው።

ከዚያ በኋላ ምን እንደሆነ በፍጹም አያውቁም፤ ራሳቸውን ሳቱ። በዚያ ሁኔታ የቆዩት ለቀናት ይሁን ለወራት አያስታውሱም። ራሳቸውን ባወቁበት ቀን ግን ሆስፒታል አልጋ ላይ ነበሩ፤ አማኑኤል ሆስፒታል። የበላይሁን እናትና ሮቤል ከአልጋቸው አጠገብ ኩርምት ብለው አዩዋቸው።

"የት ነው ያለነው? ምንድነው የሆንኩት?..." እያሉ ገና መጠየቅ ሲጀምሩ ሮቤል ተነስቶ ተጠመጠመባቸው። ተላቀሱ፤ የበላይሁን እናት ሊያጽናኑዋቸው አልቻሉም፤ አብረዋቸው አለቀሱ። እርሳቸውስ ቢሆን ያው አይደሉ? በላይሁን አለ ከመባሉ በስተቀር ደርግ ጽሕፈት ቤት ከተወሰደ ወዲህ አንድ ቀን እንኳን አይተውት አያውቁም። የበላይሁን አባት በሚያውቋቸው ሰዎች አማካይነት መኖሩን ይሰማሉ። እናም የበላይሁን እናት ሁሌም በቋፍ ናቸው፤ ለማልቀስ ሰበብ ብቻ ነው የሚፈልጉት ። ቃለአብ ደግሞ ባይወልዱትም ልጃቸው ነው፤ ለማልቀስ ሌላም ሰበብ አይፈልጉም። እዬዬ ብለው ሲያለቅሱ ነርሶቹ ከክፍሉ እንዲወጡ አደረጓቸው።

የፍሬሕይወት እናት ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሆስፒታል ሲወጡ "እማ ከእንግዲህ አታለቅሽም አይደል?" አላቸው ሮቤል።

"እሺ" አሉት እንባቸው እየፈሰሰ። ሮቤል ሊያጽናናቸው ባለመቻሉ አብሮአቸው ተንሰቀሰቀ፤ ለቅሶውን ማቆምም አልቻለም።

"እንማማል" አሉት ራሱን እያሻሹት

"አዎ" አላቸው ከመቅጽበት ለቅሶውን ትቶ።

"በቃ አሁን ፍሬ ብቻ ናት የቀረችን፤ እርሷ እንድትፈታ ብቻ እንጸልያለን" አሉት። ከዛ ወዲህ ሊሊቱን ተገን ካላደረጉ፤ ወይንም ሮቤል በሌለበት ሰዓት ካልሆነ በፍጹም አያለቅሱም።

* * * *

ፍሬሕይወት የነቃችው አመሻሽ ላይ ነው፡፡ በረንዳው ላይ እንደተጣለች ነበረች። በጭኖቿ መሀል ርጥበት ይሰማታል፤ ለመገላበጥ ስትሞክር ልብሷ ቀዘቀዛት፤ ከተጋደመችበት ለመነሳት ብትሞክርም አልሆነላትም። የሆነውን ከመገመት በስተቀር ማየት አልቻለችም። ቀስ በቀስ የሆነው ሁሉ ትዝ አላት በላይሁን ከመጣ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ መጠራቷ ነበር። መንክር ነው ያስጠራት፤ ገና ወደምርመራ ክፍል ስትገባ

"ዘውዱን አታውቂውም" አላት

"የቱን ዘውዱን?" አለችው በደከመ ድምጽ።
"ከትናንት ወዲያ እናንተ ግቢ መጥቶ የነበረውን ሰው አላየሽውም?" አላት በቁጣ።

"አይቼዋለሁ" አለችው በተሰበረ አንደበት።

"እና አታውቂውም?" አለና አንባረቀባት።

"አላውቀውም" አለችው ፍርጥም እንዳለች።

"ትቢቷ የማይበርድላት ፍጥረት እኮ ነች፤ በናትህ አስገባልኝ" አለና ከተቀመጠበት ተነሳ።

ምን እንደምትለው ጥቂት አሰበ አደረገችና "በፍጹም አልለማመጠውም! የፈለገውን ያድርግ!" አለች ለራሷ።



እንደተለመደው አስገብተው ስቃዩዋን አሳዩአት፤ ድጋሚ ራሷን እስከምትስት ድረስ። ከስንት ሰዓታት በኋላ እንደነቃች አታስታውስም የተለየ ስሜት አላት፤ በጭኖቿ መሀል የሚሰማት ቅዝቃዜ አሁንም እንዳስጨነቃት ነው።

ከማሰቃያው ክፍል ውስጥ ድምጽ ይሰማል፡፡ የራሷን ስሜት ተወት አድርጋ አዳመጠች፤ በላይሁን እዛ እንደነበረ ትዝ አላት። ድምጹን ለመለየት ሞከረች፤ የእርሱ አይደለም። ጥቂት ቆይቶ የስቃይ ድምጹ ጠፋ፡፡ አለንጋው እግር ላይ ሲያርፍ የሚያሰማው ድምጽ እና የገራፊዎቹ ጫጫታና ሳቅ ብቻ ይሰማል። ለአፍታ ያህል ደግሞ ሙሉ ፀጥታ ሰፈነ፡፡ ክፍሉ ውስጥ ሰው የሌለ እስኪመስል ድረስ!

"የለም ምንም ትንፋሽ የለውም" የሚል የድንጋጤ ድምጽ ሰማች፡፡ እንደገና ፀጥታ ሆነ።

"አውርዱና ወደዛ አድርጉት" አለ አለቅየው ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ። ወዲያውኑ የበሩ ቁልፍ ተከፈተ፤ ሲወጡ እዛው እንደተጋደመች አገኟት።

"ይህችን ውሰዱና ወደክፍሏ አስገቧት" አለና አዘዘ አለቅየው። ሊነኳት ተጠይፈዋታል፤ እንደምንም ክንድና ክንዷን አንጠልጥለው ወስደው የሴቶች ቤት በረንዳ ላይ አጋደሟት።

ሴቶቹ እስረኞች በሙሉ በድንጋጤ በዙሪያዋ ተሰበሰቡ። ወደመኝታዋ እንዲወስዷት ነገረቻቸው፤ መጸዳዳትና ልብሷም መቀየር ስለነበረባት እንደምንም ተጋግዘው ወደመጸዳጃ ቤት ወሰዱና አጣጥበውና ሊደረግ የሚገባውን ሁሉ አድርገው መኝታዋ ላይ አጋደሟት። እስር ቤት ከገባች ለመጀመሪያ ጊዜ አለቀሰች፡፡ በግንባሯ ፍራሹ ላይ ተደፍታ ተንሰቀሰቀች። በለቅሶዋ ውስጥ ከድብድባው በኋላ ከገባችበት ሰመመን ስትወጣ የሰማችው የስቃይ ድምጽና የበላይሁን ሁኔታ ይመላለስባታል፡፡ በእናቱ በኩል የላከላትን ማስታወሻ አሰበችው፡፡ "አፈቅርሀለሁ ልለው ብችል ምን ነበረበት?" አለች ለራሷ። ቀና ለማለት አልቻለችም፤ ሁሉ ነገር አስጠላት፡፡ ደምና እንባ ተቀላቅለው ፍራሹ ላይ የተነጠፈውን አንሶላ አበላሽተውታል። ያን እለት አብዛኞቹ እስረኞች አብረዋት አለቀሱ።

በሚቀጥለው ቀን አንድ እስረኛ በግርፍ ላይ መሞቱ ተሰማ፡፡ ያ ትናንትና ፍሬሕይወት በረንዳው ላይ ተጥላ ሳለ ይገረፍ የነበረው ልጅ ነው። እናቱ ጠዋት ምግብ ይዘውለት ሲመጡ ልብሶቹ ተመለሱላቸው፡፡

በላይሁንን በምን አለሁልህ ልትለው እንደምትችል ስታውጠነጥን አረፈደችና ከምግብ አመላላሾቹ አንደኛዋን አስጠራቻት። ዝኑ ነበረች የመጣችው፤ አስር ብር አወጣችና "እባክሽን ወተት አስገገርና ለበላይሁን ስጭልኝ?" አለቻት። በላይሁን ማን እንደሆነ ሁሉም አውቀዋል። ባለማቅማማት ተቀብላት ሄደች።

ዝኑ እንደወጣች ድንቅነሽ መጣችና "ዛሬ ቆንጆ ምግብ መጥቷል ለምን አንልክለትም?" አለቻት።

"ምግቡ እዚህስ ያስፈልግ የለ?" አለች ፍሬ።

"በጣም ብዙ ምግብ ነው ያለን አያስፈልገንም" አለችና ምግብ አመላላሾቹን ልትጠራ ወጣች። ቅድስትና ዝኑ በሩ ላይ ተገናኙ።

"በጣም አመሰግናለሁ ብሏል በላይሁን" አለቻት።

"በናትሽ ዝኑ ይህንንም ይዘሽለት ሂጂ?" አለቻት ድንቅነሽ። ዝኑ ምግቡን በፍጥነት ተቀብላት ለበላይሁን ይዛለት ሄደች። ከዛ ቀን በኋላ ለበላይሁን ከሴቶች ቤት ምግብ እየተመረጠ ይሄድለት ጀመር።

የበላይሁን እናት ከእናቷ ጋር አብረው ተመላልሰው መምጣታቸውን ትሰማለች። እናቷ ሊያዩዋት ባለመቻላቸው በጣም እየተጨነቁ መሆናቸውንም ምግብ አመላላሾቹ ይነግሯታል፡፡ ግን ምን ታድርግ? መነሳትና መቆም አልቻለችም። እግሯ መቆም ቢችል ኖሮ ሴቶች ክፍል የብረት በር ላይ ቆማ ቢያንስ አጇን ልታውለበልብላቸው ትችል ነበር።

አንድ ቀን ግን ከገራፊዎቹ አንዷ የሆነች ሴት የፍሬ እናት አልሄድም ብለው ሲያለቅሱ አይታቸው በሚቀጥለው ቀን ልታሳያቸው ቃል



እንደገባችላቸው ሰማች፡፡ መቆም ስለማትችል እንዴት አድርጋ ልታሳያት እንደምትችል ስታውጠነጥን ዋለች። ሴትዮዋ ወደማታ ላይ መጣችና ፍሬሕይወትን አናገረቻት።

"አንቺ ይሄ እልህ በተደጋጋሚ ያስመታሻል አይደል?" አለቻት፤ ምንም አልመለሰችላትም "ይጎዳሻል እንጂ እንደማይጠቅምሽ እወቂ" አለች ደግማ፤ ምንም ሳለመናገር ራሷን አሳመነችና ዝምታን መረጠች ፍሬሕይወት።

"ነገ ሆስፒታል ትወሰጃለሽ፤ ስትወጪ እናትሽ ውጭ እንዲጠብቁን ስለነገርኳቸው ደህና መሆንሽን እንዲያውቁ ፈካ ብለሽ ታናግሪያቸዋለሽ" አለቻት። እሺታዋን በአንገቷ ገለጸችላት።

"ይቺ ትቢትሽ እኮ ገና አልበረደችም" አለቻትና ወጣች። በሚቀጥለው ቀን እንደተባለው ፍሬ በመኪና ውስጥ እናቷ ደግሞ መሬት ሆነው በደንብ አዩአት አናገረቻቸው። እናቷ በጣም ተጎሳቁለዋል፡፡ የተሰማትን ሀዘን እንዳያዩባት ግን የቻለችውን ሁሉ አደረገች። ቃለአብና ትንሽ እህቷ እዚያው ከፍተኛ መታሰራቸውን ነገሯት። እፎይ አለች።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ምግብ አመላላሾቹ ለበላይሁን የተላከውን ምግብ መለሱትና ደርግ ጽሕፈት ቤት ተመልሶ መወሰዱን ነገሯት። ከሰሞኑ ደግሞ መገደሉን ሰማች። የተሰማትን ሀዘን በቃላት መግለጽ እስከማኪብዳት ድረስ ነበር የሆነባት፤ ብቻ መንፈሷ እንክትክትአለባት፣ ራሷን ጠላችው። በሕይወት መቆየቷን እንደወንጀል ቆጠረችው። ለሁለተኛ ጊዜ አለቀሰች። ለዚያውም ምርር ያለ ለቅሶ፤ የበላይሁንን እናት በዐይነ ሕሊናዋ እያየቻቸው ከአንጀቷ አነባች። አብሮ አደግነታቸውንና ወንድምነቱን እያሰበች አለቀሰች። በላይሁን በመጨረሻው ደቂቃ የገለጸውን ፍቅሩን እያስታወሰች አለቀሰች፤ ማልቀስ ግን የውስጥን መቃጠል ከማውጣቱ ባሻገር ምን ዋጋ አለው? ቢሆንም ትዝ ባላት ቁጥር አለቀሰች።

ከሰሞኑ ምግብ ከሚያመላልሱት ልጆች አንዷ የሆነ ወረቀት ሰጠቻት። አነበበችው "...ስለተከሰተው ሁሉ በጣም አዝኛለሁ። ብዙዎች ተሰውተዋልና ከእነርሱ ለይተሽ እንደማታይው እገምታለሁ፡፡ ከባድ

መሆኑን ባውቅም ጥንካሬሽ የበለጠ እንደሚሆን ግን አምናለሁ አይዞሽ!" ይላል መልእክቱ።

መልዕክቱ ከማን ሊሆን እንደሚችል ገመተች፡፡ ሌላ የምታውቀው ሰው ስለሌላት ከዳኙና ከዚያ መኪናው ላይ ካየችው ልጅ ሊያልፍ እንደማይችል አሰበች። ግን ማን ያውቃል እዚያ መጋዘን ውስጥ እርሷንና በላይሁንን በቅርብ የሚያውቅ ቢኖርስ? እናም ማን መልዕክቱን እንደላከላት ለማወቅ መጠየቅ ነበረባት እናም የመጣችላትን ልጅ ጠየቀች።

"የሰጠኝማ ፈቃደ ነው" አለቻት ምግብ አመላላሿ፡፡ ፈቃደን አላወቀችውም፡፡ ምልክት እንድትነግራት እንደገና አስቸገረቻትና የነገረቻት ምልክት የመለከታት ያንን መኪናው ላይ ከዳኙ ጋር ያየችውን ልጅ ነበር።

"በጣም አመሰግናለሁ በይልኝ" አለቻት።

ቀስ በቀስ የእግሯ ቁስል ጠገግ እያለ ሄደ። ያለድጋፍ ለብቻዋ መንቀሳቀስ ቻለች። ሕይወት እንዴት ይገርማል እንደገና መኖሯን እየወደደችው፣ በሕይወት የመቆየት ፍላጎት በውስጧ ሲለመልም ተሰማት፣ ገረማትም። ያ የብረት በርም በተደጋጋሚ መከፈቱ ቀነሰ፡፡ የሚያውቋት ሰው ለመፈለግና ለመጠቆም የሚመጡ እስረኞች ቁጥርም ተመናመነ መሳቅ መጫወት ተጀመረ።

እንደ ሌሎቹ እስረኞች ሁሉ ጠዋትና ማታ በሰልፍ ወደመፀዳጃ ቤት መሄድ ጀመረች ፍሬ። ሴቶች ግቢ ያለውን መፀዳጃ መራመድ የማይችሉ እስረኞች ብቻ ይጠቀሙበታል። ቀሪዎቹ ግን በቀን ሁለት ጊዜ ከግቢ ውጭ ወዳለው መፀዳጃ ቤት ይሄዳሉ። መፀዳጃ ቤቱ ያለው ወንዶቹ እስረኞች ከታጎሩበት ትልቅ መጋዘን አጠገብ ነው። በዚያ መፀዳጃ ውስጥ ሁለት እስረኞች በቀበቶዎቻቸው ተሰቅለው በመሞታቸው ምክንያት ማንም ሰው ገብቶ በሩን መዝጋት አይፈቀድለትም። እናም ሁሉም ገብተው የሚጸዳዱት መጸዳጃው እንደተከፈተ ነው።

* * * *



ጊዜው ይነጉዳል ወራት እየተቆጠሩ ወደ ዓመት ተጠጉ፡፡ የሞቱት እየሞቱ፣ የጠፉትም እየተመለሱ በየእስር ቤቶቹ ታጎሩ፡፡ በየከፍተኛው የተቋቋሙ እስር ቤቶቹ በወጣት ተጣበቡ፤ "የኢሕአፓ መዋቅር ከሞላ ጎደል መፈራረሱን አረጋግጫለሁ" አለ መንግሥት። የእውነትም ውጭውም ፀጥ ረጪ አለ፡፡

ቀስ በቀስ ለጥየቃ ከሚመጣው ቤተሰብ የመፈታት ዜናዎች መድረስ ጀመሩ። ብዙዎቹ እስረኞች የእህትና የወንድሞቻቸውን፣ የዘመድና የጓደኞቻቸውን መፈታት ሰሙ። እነርሱም የመፈታት ተስፋ በውስጣቸው ማንሰራራት ጀመረ።

ፈቃደም የእስር ቤቱ ሕይወት ሰልችቶታል፤ እስር ቤት ውስጥ ከመቆየት መውጣት የተሻለ እንደሚሆንም ያውቃል ግን አእምሮው በዚህ ተስፋ መደሰት አልቻለም። ሁልጊዜም ይተክዛል፤ ወደኋላው መለስ ብሎ የሆነውን ሁሉ ያስባል፤ በትግል ያለፉትን ዓመታት፣ ለትግሉ ሲሉ የተቀበሉትን ስቃይ፣ የተከፈለውን የሕይወት መስዋዕትነት... እያንዳንዱን ሲተነትን ለሰዓታተ በዝምታ ከራሱ ጋር ያወራል።

"እና መጨረሻው ምንድነው? ያለቁት አልቀው፣ በአካልና በመንፈስ የተጎዱት ተጎድተው... አጋጣሚ ያተረፋቸው ተርፈው መፈታት? ከዚያስ? በቃ ሕይወት ወደነበረበት መመለስ?..." ለሚደረድራቸው ጥያቄዎች መልስ የለውም። ግራ ይገባዋል፤ የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው እየሆነ በመመልከቱ ይገርመዋል። እርሱ በፍጹም ይህንን አልጠበቀም፤ ትግሉ ቢራዘምም፣ መስዋዕትነቱ ቢበዛም መጨረሻው ድል መሆኑን ተጠራጥሮ አያውቅም።

አንዳንዴ በመጋዘኑ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲያስብ "ይህን ጊዜ እኮ ትግሉ ቀጥሏል። እንደዱሮው ጠንካራ ላይሆን ይችላል፤ ከመታሰር የተረፉት ጥቂቶችም ቢሆኑ፣ ሁኔታው በቀላሉ ባያንቀሳቅስም የበለጠ ሕቡእ መሆን ቢያስፈልግም ትግሉ ግን ይቀጥላል..." ይላል ለራሱ።

አንዳንዴ ለብቻው ማሰቡ ሲያስጨንቀው ከሌሎች ጋር ማውራት ይፈልጋል፤ ሌሎቹ የሚሰማቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ይጓጓል። እናም በዚያ የመጋዘን ውስጥ የእግር ጉዞ ከአንዳንዶቹ ጋር ለመነጋገር

ይሞክራል። ብዙዎቹ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ድፍረት ሲያንሳቸው ከማየቱ በስተቀር ልክ እንደእርሱ እንደሚያስቡ መረዳት ችሏል። አንዳንዶች ደግሞ ሀሳቡ ራሱ ሲያስበረግጋቸውና ሁለተኛ እንዲህ ዓይነት ነገር እንኳንስ ማድረግ መስማት እንደማይፈልጉ ከማስጠንቀቂያ ጋር ነግረውታል።

“ከእንግዲህ የምንጠብቀው ከዚህ እስር ቤት የምንወጣበትንና የግል ሕይወታችንን የምናስተካክልበትን ጊዜ ብቻ ነው” ያሉት ብዙዎች ናቸው።

የአብዮቱ መክሸፍ ይቆጨዋል “ዓላማችንስ? እንዲቋቋም የምንፈልገው ሕዝባዊ መንግሥትስ? ሕይወታቸውንና አካላቸውን የከፈሉት ጓዶችስ...” እራሱን እስኪያመው ድረስ ያስባል። ራሱን ቢያመውም ማሰቡንና መተከዙን አያቋርጥም።

አንድ ቀን የመጋዘኑ በር ተከፈተና የእስር ቤቱ ኃላፊዎች ተከታትለው ገቡ። ሁሉም በያለበት ሆኖ ዐይኖቹን ወደ ገቡት ሰዎች ላከ። “ጸጥ ብላችሁ አድምጡ” አለ ከገቡት ሰዎች አንደኛው። ሁሉም ጆሮዎቹን አቀና፤ ሰውየው ሥም መጥራት ጀመረ። ለምን እንደሆነ መገመት ከባድ አልነበረም፤ ሰሞኑን ስለመፈታት ይናፈስ የነበረው ወሬ እውነት ሊሆን መሆኑን አሰቡ።

እንደጠበቁትም ሥም ጥሪውን ሲያበቃ ሥማቸው የተጠራው ሁሉ ለንቃት የተመደቡ መሆናቸውን ተናገረ። ከተጠሩት ሰዎች መሀል የአንዳንዶቹ ያልተጠበቀ ስለነበረ እስረኞቹ እርስበርሳቸው ተያይተዋል። ያምሆነ ይህ ስለተጠሩት ሰዎች መፈታት ደስታ ሆነ።

ኃላፊዎቹ ከወጡ በኋላ ሁሉ የየስሜቱን መነጋገር ጀመረ። ፈቃደ ቀስ ብሎ ዳኙን ጠቀሰው። ከተጠሩት ሰዎች መሀል እንደዳኙ ያሉ ሰዎች መኖራቸው እስረኞቹን ከሚያነጋግሯቸው ነገሮች አንዱ ነው።

“እንኳን ደስ ያለህ” አለው ፈቃደ ዳኙ አጠገቡ ሞጥቶ ሲቀመጥ።



“ባይገርምህ ብዙም አልተሰማኝም፤ እንዴት ሊጠሩኝ እንደቻሉም ገርሞኛል፤ ብዙ የሚጠበቁ ሰዎች እያሉ እኛ መጠራታችን ይገርማል” አለ ዳኙ ስሜቱን ገጽታው እያሳየ።

“እሱስ ትክክል ነህ ብዙዎች መፈታታቸውን የሚጠብቁ አሉ፤ እድሉን እስካገኘህ ድረስ ግን መፈታትህ ጥሩ ነው” አለ ፈቃደ ራሱን በዳኙ ቦታ አድርጎ ለማሰብ እየሞከረ።

እነዳኙ ሰሞኑን ከመጋዘን ውጭ መዋል ጀመሩ፤ እነርሱ ውለው ሲመጡ ደግሞ ወሬ ይዘው ይመጣሉ። የእስር ቤቱ መንፈስ ቀለል እያለ ሄደ፤ የመፈታቱ ተራ እንደሚቀጥልና በሚቀጥለው ዙር ደግሞ እነማን እንደሚፈቱ መናፈስ ጀመረ። ዳኙ ወጥቶ በተመለሰ ቁጥር ያጋጠመውን ሁሉ ለፈቃደ ይነግረዋል። ይህን ጊዜ ነበረ ስለሚስጥረ የነገረው። ማንበብና መጻፍ ያለመቻሏን፤ ግን የፓርቲ አባል መሆኗን ሲሰማ በመደነቅ ነው ለፈቃደ ያጫወተው። እነዳኙ ንቃታቸውን ወደማጠናቀቁ ሲደርሱ እቤታቸው ሄደው መመለስ ተፈቀደላቸውና ይህንኑ ለፈቃደ ነገረው።

“አንድ ነገር ልትቸገርልኝ ትችላለህ?” አለው ፈቃደ።

“የምችለው ከሆነ” አለ ዳኙ ሳያመነታ።

ፈቃደ የስልክ ቁጥር፣ የሚፈልገውን ሰው ሥምና የሚጠይቅለትን ጉዳይ ለዳኙ ሰጠው።

ዳኙ ያመጣለት መልስ የበለጠ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሆነበት፤ ከእስር ቤት ውጭ ያለው ሁኔታ ሁሉ ከግምቱ ጋር የማይሄድ መሆኑን ተረዳ ፈቃደ።

“ዳኙ! አንተ ግን ስትወጣ ምን ታደርጋለህ?” አለው ደግሞ ሲያስብ ቆይቶ።

“ምን አደርጋለሁ ፈቃደ! እንደማንኛውም ሰው ለመኖር ከመሞከር ያለፈ ምን ላደርግ እችላለሁ?” አለው በጥያቄ ዓይነት።

"እንደገና በሕቡዕ እንድታተገል የሚያስችልህ አጋጣሚ ቢፈጠር ማለቴ ነው" አለ ፈቃደ።

"እውነቱን ለመናገር የማደርገው አይመስለኝም" አለና እቅጩን ነገረው ዳኙ።

"በቃ ተወው" አለ ፈቃደ ተሰፋ በመቁረጥ ዓይነት።

ከዳኙ ጋር ስለዚህ ጉዳይ እንደገና አላነሱም፤ ከነዳኙም በኋላ ሌላ ቡድን ሲወጣም ከማንም ጋር አልተነጋገረም። ፈቃደ መፈታትንም ተመኝቶ አያውቅም፤ ውጭውን ሳያየው ጠልቶታል። እዚያ መጋዘን ውስጥ መኖሩም ሰልችቶታል፤ ቀሪዎቹ ወደከርችሌ እንደሚወርዱ የሚናፈሰው ወሬ እውነት ሆኖ ወደዚያው ለመውረድ ቸኮለ።

* * * *

ወይዘሮ ስርጉት እንደተለመደው በጠዋት ነው የተነሱት። ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ግን አስከፊ ቅዠት ውስጥ ነበሩ፤ በእንቅልፋቸው ከልጆቻቸው ጋር ማደራቸው የተለመደ ቢሆንም የዛሬው ግን የተለየ ነበር። ሚሚ እንደተለመደው ተርባ ተንገላታ ደክማ አዩዋት፤ ከዚያ ደግሞ ቃለአብ ከሩቅ ሆኖ ሲጠራት ወደእርሱ ስትሮጥ፤ ስትወድቅ እንደገና ተነስታ ስትሮጥ… ቃለአብ ወደእርሷ ሲሮጥ… ሲገናኙና ሲተቃቀፉ፤ እርሳቸው እነርሱ ጋ ለመድረስ ሲሮጡ… መድረስ አቅቷቸው ሲጣሩ… ቃለአብና ሚሚ ግን ዞር ብለውም ሳይመለከቷቸው ርቀው ሲሄዱ… "ሚሚ፣ ቃለአብ!" እያሉ ሲጣሩ ነው ሮቤል ቀሰቀሳቸው። ላብ በላብ ሆነዋል።

"በጣም ጮህሽ እኮ እማ" አላቸው ሮቤል፤ በእንቅልፍ ልባቸው መጣራታቸውን ቢለምደውም ያሁኑ ግን ለየት ብሎበታል።

ከአልጋቸው ወረዱና ተንጠራሩ "ቀን የማስበውን እኮ ነው የምቃዠው ሮቤል! ምንም አልሆንኩም" አሉና ራሱን አሻሽተውት ወጡ።

ሮቤልን ወደትምህርት ቤቱ ሸኝተው ወደተለመደው ሥራቸው ገቡ፤ ቅዠታቸውን ግን ከሀሳባቸው ሊያወጡት አልቻሉም። ሚሚና ቃለአብ



ተያይዘው መሄዳቸውን በሚሚ ሞት ስለተረጎሙት እንባቸውን ሊያቆሙት አልቻለም።

"ምነው የማልችለውን ነገር አሸከምከኝ? ሳለምንህ እነዚህን ልጆች ሰጠኸኝ፣ ይህን ሁሉ መከራ ብቻዬን እንድገፋ ፈረድክብኝ ምነው አምላኬ? ምን ሀጢአት ሠርቼ ይሆን? ቤተሰቦቼን ምን አስቀይሜያቸው ረግመውኝ ይሆን?" እያሉ እየተማረሩ እንባቸው በአገጫቸው ላይ እየተንቆረቆረ በሀሳባቸው የትየለሌ ተጉዘው ሄዱ።

ገና ተጫውተው ያልጠገቡ ለጋ ሳሉ ነበር ከአገራቸው ወደ አዲስ አበባ የመጡት። የእናታቸው እህት "ምነው እርሷ እንኳ ከዚህ ገጠር ብትወጣ" ብለው አመጧቸው። የነበራቸው ሙያ ከዕድሜያቸው የላቀ ስለነበር ዓይኑን ያልጣለባቸው ጎበዝ አልነበረም። አክስታቸውን ስጋት ገባቸው፤ የወጣቷን እጅ ለማን እንደሚሰጡ ግራ ግብት ሲላቸው ለባለቤታቸው አማከሩዋቸው።

"እኔ መችም ከማስረሻ የሚስተካከል ያለ አይመስለኝም" አሏቸው ባለቤታቸው። ሰውየው በሁለቱ ወጣቶች መሀል መፈቃቀድ መኖሩን ካጤኑ ሰንበት በማለታቸውና የማስረሻ ቆፍጣናነትም ስለሚያስደስታቸው ነበር ይህንን ያሉት። ባለቤታቸውም ተስማሙ።

አንድ ቀን ከማስረሻ ጋር ተገናኝተው ጥቂት ሲጨዋወቱ ቆዩና አጋጣሚውን ተጠቅመው "ይህችን ኮረዳ አንዱ ሳተና እንዳይቀድምህ" ብለው ለወጣቱ ለማስረሻ መንገድ ከፈቱ። ብዙም ሳይቆይ ሁሉም ነገር ተከናወነና ስርጉትና ማስረሻ በአንድ ጣሪያ ስር ተጠቃለሉ።

"አቤት እንዴት አንቱ የተባለ ሠርግ ነበረ! አክስቴንና ባለቤታቸውን መሬት ይቅለላቸው" አሉ ወይዘሮ ስርጉት ሳያስቡት ትዝታቸው እንባቸውን አቋረጠው። የሠርጋቸው ዘፈን ሳይቀር በእዝነ ህሊናቸው ተሰማቸው።

"ዘመናይ ናት እሷ ዘመናይ ናት እሷ
ጥልፍልፍ ጫማ አላት ሀር ነው ቀሚሷ…" እየተባለ የተዘፈነውና ሌሎችም።

"አንተንም አፈሩ ይቅለልህ" አሉ ባላቸውን እያሰቡ። "አንተስ እድለኛ ነህ ማስረሻ" አሉ ደግሞ እርሳቸው ያዩትን ሀዘን ሳያዩ በመሞታቸው በባለቤታቸው ቀንተውባቸው። "ልጅህ እንደወጣች ስትቀር ሳያሳይህ፤ የልጅህን አይሞቱ አሟሟት ሳያሰማህ የጠራህ ... ኧረ እግዚአብሄር የመረጠህ ሰው ነህ!" አሉ። እንደገና እንባቸው በዐይኖቻቸው ሙልት ብሎ ከመቼው እንደገነፈለ ሳያውቁት ጉንጮቻቸውን እያቆራረጠ ወደአንገታቸው ወረደ።

ድንገት ሀሳባቸው ወደፍሬሕይወት ሲሄድባቸው "እምላኬ ይቅር በለኝ!" አሉና እንባቸውን በነጠላቸው ጠራረጉ። ፀሐይዋ ጥርር ብላ ወጥታ ጊዜው መርፈዱን ትናገራለች፤ የያዙትን አስቀምጠው ሰዓት ለማየት ወደቤት ገቡ፤ ሰዓቱ አስደነገጣቸው፤ አራት ሰዓት ተኩል ይላል፤ ሰዓቱን አላመኑትም።

የበላይሁንን እናት ሰዓት ጠይቀው ሊያረጋግጡ ከቤት ሲወጡና ፍሬሕይወት የውጭውን በር ከፍታ ስትገባ እኩል ሆነ። የፍሬሕይወት እናት ራሳቸውን ተጠራጠሩት፤ ያመማቸውም መሰላቸው፤ ዐይኖቻቸውን ጠራረጉ። ፍሬሕይወት አንገታቸው ላይ ተጠምጥማ ሳመቻቸው፤ በደመነፍስ ሳሟት።

"እልልልል!" ብለው ጮሁ ሳያስቡት።

የበላይሁን እናት እልልታቸውን ሰምተው ሲወጡ እርስቸውም በድንጋጤ እልልታውን ተቀበሏቸው። ፍሬሕይወት ከእናቷ ወደ በላይሁን እናት ሄደች።

ትንሽ እንደመረጋጋት ሲሉ የበላይሁን እናት ከምን ጊዜው እንዳቀረቡት ሳያውቁት ቡናው መጫጫስ ጀመረ። ሕይወት ቀጠለ። በእያንዳንዳቸው ልብ ውስጥ ከባድ ሃዘን ቢኖርም ሁሉም ለመጫወት ሞከሩ፡፡ ፍሬሕይወት ስለቃለአብ መጠየቅ ቢያስፈራትም ጠየቀች፤ "ደህና ነው" አሏት ቀለል አድርገው።

የአካባቢው ሰው "እንኳን ደስ ያላችሁ" ለማለት ሲመላለስ ዋለ። እናቷ ቀኑን ሙሉ እንግዳ ሲያስተናግዱ ፍሬሕይወትም ለሰላምታ ስትነሳና ስትቀመጥ ዋለች፤ ድክም እስኪላት ድረስ። ሮቤል ከትምህርት ቤት



ሲመጣ ፍሬሕይወትን በማግኘቱ ድንጋጤና ደስታ እርሱንም ፍዝዝ አደረጉት። ጥቂት እንደቆየ እናቱ ጠቀስ አደረጉና ወደጓዳ አስገቡት።

"ስለቃለአብ መሞት እንዳትነግራት እሺ? ጠዋት ነው የምንነግራት" አሉት ። በእሽታ አንገቱን ነቀነቀና ወደፍሬሕይወት ተመለሰ። ምሽቱን ሁሉ ቤታቸው በሰው እንደሞላ አመሸ። የበላይሁን አባትም የደስታው ተካፋይ ሆነው አመሹ። ሁሉሰው ወትሮ የምታውቀው ሰው አልነበረም፤ ተለውጠዋል። ፍሬሕይወት አንድ ሰው እንኳን ስለበላይሁን ያለማንሳቱ እንደገረማትና ግራ እንደገባት አመሸች።

ሁሉም በጣም ደክሟቸው ስለነበረ እንቅልፍ ሳይፈልጉት ነው የመጣው። ማለዳው ላይ የቤቱ መዝጊያ አንድ ጊዜ "ኳ" ሲል የፍሬሕይወት እናት ተፈናጥረው ከአልጋቸው ወረዱና ወደሳሎኑ ሄዱ። የበሩ መንኳኳት ተደገመ፤ ይህን ጊዜ ነው የማታ ምክክራቸውን ያስታወሱት። በሩን ከፈቱት።

"ዛሬስ እንቅልፍ ጣለሽ" አሉ የበላይሁን እናት።

ፍሬሕይወት ከእንቅልፏ ተቀሰቀሰች፤ ተነስታ ወደ ሳሎኑ ስትገባ ገና ዓይኖቿ አልተገለጡም፤ "ቃለአብ" የሚል ሥም ስትሰማ ነው ከእንቅልፏ የነቃችው። "እማ! ቃለአብ ሞተ? አይሆንም አይደረግም!" አለች ደግሞ።

ግን ሆኗል፣ ተደርጓል፤ ታናሽ ወንድሟ ቃለአብም ሞቷል። ስሜቷን የሚገልጹ ቃላት ማግኘት በፍጹም አልቻለችም። ለቅሶዋ መራር ሆነ፤ ለሁለቱም አለቀሰች፤ ለበላይሁንና ለቃለአብ፤ በለቅሶዋ ውስጥ የበላይሁንን ሥም መጥራቷ ደግሞ ሌላ ነገር አመጣ፤ የበላይሁንን ሞት ማናቸውም አልሰሙም። ድብልቅልቅ ያለ ነገር ተፈጠረ፤ ቀስ ብለው እናቷ ጠየቋት "በላይሁን ሞቷል እንዴ?" አሏት።

"አዎን! አልሰማችሁም እንዴ?" ጥያቄያቸውን በጥያቄ መልሳላቸው እሪ አለች ፍሬሕይወት። የበላይሁን እናት ወደቁ፤ እህቱ እየሩስን መያዝ አልተቻለም። አባትዬው ሐዘናቸው የመረረ ቢሆንም ባለቤታቸውንና ልጃቸውን ለመርዳት ጥረት አደረጉ።

የአካባቢው ሰው ግልብጥ ብሎ መጣ፤ አዲስ ለቅሶ አዲስ ሐዘን! የበላይሁን ሞት የተሰወረው ከቤተሰቡ ብቻ እንጂ የአካባቢው ሰው በሹክሹክታ ሲነጋገርበት ቆይቷል። ቤታቸውን የሀዘን ጥላ ወረሰው፤ የበላይሁን እናት መጽናናት አቃታቸው፤ ኢየሩስ በአንድ ጊዜ የበለጠ ተጎሳቆለችና ሌላ ሰው መሰለች።

ፍሬሕይወት እያደር ጥንካሬዋ ሁሉ የሚሸሻት መሰለች። "ለምን እንደዛ ስደበደብ አልሞትኩም? ለምን እነርሱስ አልገደሉኝም? ፊሪና ራስ ወዳድ በመሆኔ መስዋዕትነትን በመሸሼ..." ራሷን ወቅሳ ማብቃት አቃታት። ራሷን እየወቀሰች አለቀሰች፡፡ መኖሯን እየጠላች አነባች...ራሷ የሚፈነዳ መሰላት።

* * * *

እስረኞቹ ወደክርቸሌ እንደሚወሰዱ ወሬው መናፈስ ከጀመረ ሰነበተ። የመጋዘኑ በር በተከፈተ ቁጥር እንደበፊቱ የሚመጣውን አዲስ እስረኛ ለማየት ሳይሆን "ወደክርቸሌ ለመሄድ ዕቃዎቻችሁን አዘጋጁ" የሚል ትእዛዝ ለመስማት ጆሮዎቻቸውን ያቀናሉ። እያንዳንዱ ቀን መሰላቸትን አዝሎ ይመጣል፤ እስረኞቹ በቡድን በቡድን ሆነው ቼዝ፣ ካርታ፣ ሞኖፖሊ... ይጫወታሉ ወይ ያወራሉ፤ ጊዜያቸውን ለማሳለፍ። በረጅሙ መጋዘን ውስጥ ከወዲያ ወዲህ በመመላለስ የሚታወቁም ብዙ ናቸው።

ፈቃደ ሰሞኑን በጣም የተለየ ባህሪ አምጥቷል፤ በቅርቡ ያሉት እስረኞች ወትሮም ቁጡነቱን የሚያውቁት ቢሆንም ተለይቶባቸዋል። አንዳንዴ የጀመረውን ጨዋታ ሳይታሰብ ይተወውና ተነስቶ የመጋዘን ውስጥ ጉዞውን ይጀምራል፤ ከጀመረ ደግሞ አያቋርጥም። አንዳንዴ ምሳውንም ላይበላ ይችላል። "ኧረ ነዳጅ እንዳያልቅብህ" ይሉታል ጓደኞቹ።

በመጋዘን ውስጥ ጉዞው የማያስበው ነገር የለውም፤ የትግሉን እንዲህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዳልነበረ መሆንና የኢሕአፓን መበታተን ሲያስበው ግንባሩ ላይ ቁጥር ፈታ የሚለው የደም ስሩ ይግተረተራል፤ እልህ ይይዘዋል። የኢሕአፓ መዋቅር እንዲህ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቀርቶ በዓመታት ይበተናል ብሎ አላሰበም ነበር። ከጥይት



ጋር ፊት ለፊት ይፋጠጥ የነበረ ሞራልና ወኔ እንዲህ በአጭር ጊዜ ይሟሸሻል ብሎ ገምቶ አያውቅም ነበር።

በመጋዘኑ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ እየተመላለሰ አብረውት የነበሩትን ጓደኞቹን አንድ በአንድ ያስታውሳቸዋል። እያንዳንዳቸውን እያስታወሰ "ዛሬ የት ይሆን?" ይላል። አንዳንዴ ደግሞ "ቢመጡስ?" ይላል ድንገት እርሱ ወዳለበት እስር ቤት ቢመጡና ቢጠቁሙበት ሊከተል የሚችለውን እያሰበ። "ቢሆንም" ይልና ለራሱ ይነግራል "ቢሆንም ሲመጡ የሚሆነውን እጠብቃለሁ እንጂ በፍጹም አልናገርም!" ይላል። ደግሞም ከዚህ በኋላ የመምጣታቸው ነገር የሚታሰብ አይደለም።

ድንገት ደግሞ ፍሬሕይወትን ያስባታል። አንዳንዴ ወደዚያ ወደሚጠላው የምርመራ ክፍል እንዲጠራ የሚመኝባቸው ጊዜያት እንደነበሩ አስታወሰና ፈገግ አለ፤ እንዲጠራ የሚፈልገው ግን ድንገት ፍሬሕይወትም ተጠርታ ሊያያት እንዲችል ነው። አንድ ቀን ካያት ለብዙ ቀናት በአእምሮው ውስጥ ትሰነብታለች። አሁን ግን ያም ዕድል የለም፤ እርሷ ከዚህ ግቢ ተገላግላለች። "ግን ውጭው ምን ይመስል ይሆን? መንገዱን የሚያጣብቡት ወጣቶች የት ይሆኑ? አሁን ከየከፍተኛ እስር ቤት የሚፈቱት ወጣቶች ምን እያደረጉ ይሆን?..." የማያነሳው ጥያቄ የለውም ፈቃደ።

ከመጋዘን ውስጥ ጉዞው እረፍ ሲል አንዳንዴ ከዘውዱ ጋር መጫወት ይወዳል። ዘውዱ ፈቃደ ከሚያከብራቸው ሰዎች አንዱ ነው። ርጋታውና ደግነቱ፤ አእምሮውና እንደበቱ ትህትናውና ለጋስነቱ ይገርመዋል። ዘውዱ ወደኋላ በመምጣቱ ግና ከጉዳቱ በሚገባ አላገገመም። ብዙዎች ከተሻላቸው በኋላ በመምጣቱ ግን በርካታ ተንከባካቢዎች አሉት። በአጭር ጊዜ ውስጥ የብዙዎቹን እስረኞች ቀልብ በመሳቡ ብዙዎቹ በእርሱ ዙሪያ ተሰባስበው መጫወት ይወዳሉ። "ዘውዱ ተንቀሳቃሽ መጽሐፍ ነው" ይሉታል። የሚሰነዝራቸው ሀሳቦችና የሚሰጣቸው መልሶች ሁሉ ተራ አይደሉም፤ አንዳንዶቹን ምንጭ ጠቅሶ ነው የሚነግራቸው። ፈቃደ ብዙውን ጊዜ ከዘውዱ ጋር ብቻቸውን ቢያወሩ ደስ ይለዋል፤ እናም ዘውዱ ብቻውን ሲሆን ነው አብሮት የሚሆነው። ሌሎች ጨዋታቸውን መቀላቀል

ሲጀምሩ እርሱ ይነሳና ወደቦታው ይሄዳል አሲያም የመጋዘን ውስጥ ጉዞውን ይጀምራል።

ሳምንታት ባለፉ ቁጥር የፈቃደ መነጫነጭ እየበዛ መጣ፤ ጓደኞቹ እስኪያውቁበትና እስኪታዘቡት ድረስ። በቅርብ የሚያውቁት የመነጫነጩ ምክንያት ምን እንደሆነ ቢያውቁለትም ሌሎቹ ግን ግራ ይገባቸዋል፤ በመጋዘኑ ውስጥ ጉዞአቸው ድንገት ሲተላለፉ ለማንም ደንታ የሌለው መሆኑ ያናድዳቸዋል፤ በትንሽ ነገር ሲነጫነጭ ያስጠላቸዋል። እርሱ ግን ለየትኛውም ቢሆን ግድ የለውም።

አንድ ቀን ከምግብ አመላላሾች አንዱ ፈቃደን ጠራውና ያመጣለትን ነገር ሰጠው። "ማነው የመጣው?" አለና ጠየቀ ፈቃደ።

"ከዚህ የተፈቱ ልጆች ናቸው" አለ ምግብ አመላላሹ።

"እነማን?" እንደገና ጠየቀ ፈቃደ።

"ስማቸውን አላውቀውም..."

"እንዴት?" አለና ፍ[illegible]ኸበት ፈቃደ።

"ጠይቄ እመጣለሁ" አለና ፈጥኖ ወጣ ምግብ አመላላሹ። ፈቃደ ቁጡ ቢሆንም ለሰው አዛኝና አሳቢ በመሆኑ ጩኸቱን አይቆጥሩበትም።

የልጁን መመለስ እየጠበቀ ሰጥቶት የሄደውን ዕቃ ተመለከተው፤ ሁለት ፓኮ ሲጋራ፣ መስቲካዎችና ካልሲዎች ናቸው። ሲጋራውን አነሳና ገልበጥ ገልበጥ አድርጎ ተመለከተው። "ፍሬሕይወትና ሚስጥረ" የሚል በፓኮው ላይ ተጽፎበታል። ፈቃደ እየተንደረደረ ወደበሩ ሄደ ምግብ አመላላሹን ሊፈልግ። ድንጋጤው ለራሱም ገረመው። ምግብ አመላላሹ ራሱን አሸት አሸት እያደረገ መጣና "ሄደዋል" አለው ለፈቃደ።

"ሺት!" አለ ፈቃደ ሳያስበው። "በጣም ይቅርታ!" አለው ደግሞ ልጁን ተመልሶ ሲመጣ። ልጁ የታዘበው መሰለው።



ሰሞኑን ፍቅርኛው መጥታ ጠየቀችው፤ ምን ሲሰማት መጥታ እንደምትጠይቀው ግራ ይገባዋል። የመጣችባቸውን ጊዜያት ማስታወስ ሞከረ፤ በጣት የሚቆጠሩ ቀናት ናቸው። ለረጅም ጊዜ ጠፍታ ትቆይና አንድ ቀን ደግሞ ገንዘብና አንዳንድ ነገሮች ይዛለት ብቅ ትላለች። ለፖለቲካ ያለውን ስሜት ባትወድለትም እርሱን ግን እንደምትወደው ያውቃል፤ ብታፈቅረውም አብረው መቀጠል እንደማይችሉ ወስኗል። እናም አልፎ አልፎም ቢሆን መጥታ መጠየቋ ብዙም ስሜት አልሰጠውም። ያመጣችለትን የተለያዩ ስጦታዎች፣ በመጣች ቁጥር የምትሰጠውን ገንዘብ ከምንም አልቆጠራቸውም፤ ፍሬሕይወትና ሚስጥረ ያመጡለት ካልሲዎች ከዚያ በላይ ሆኑበት።

# ክፍል 4
# ሕይወት እንደገና

የከተማው ሕይወት መረጋጋት ይታይበታል፤ እነዚያ በየምሽቱ የሚሰሙ የጥይት ድምፆች የሉም፤ ሳይታሰቡ የሰውን ግቢ በርግደው ቤት የሚያተረማምሱ አሰሳዎች ቀርተዋል። በየመንገዱ ድንገት የሚደረጉት ፍተሻዎች ተቋርጠዋል። ትምህርት ቤቶች ተረጋግተው መደበኛ ትምህርት ቀጥለዋል። አዲስ አበባ ጸጥ ብላለች።

ፍሬሕይወት መኖሯን ተቀብላለች፤ ለመኖር ግን ልታደርጋቸው የሚያስፈልጉ በርካታ እንቅስቃሴዎች አሉ። ትምህርቷን መቀጠል አለባት፣ ማህበራዊ ግንኙነትም ሊኖራት ያስፈልጋል። ወደተግባር መለወጥ ግን አልሆነላትም፤ ሁሉም ነገር ግራ ይገባታል። የሰፈሯ ልጆች ብዙዎቹ ሞተውና ተሰደው በጣት የሚቆጠሩ ብቻ ቀርተዋል። እነርሱንም ብዙም አታያቸውም፤ ሁሉም ሰው ተጠራጣሪና ፈሪ ሆኗል።

ፍሬሕይወት ከሰው መቀላቀል አልሆነላትም፤ ጨዋታው አይጥማትም፣ ውይይቱም አይገባትም። እያንዳንዱ ነገር የሞቱትንና የት እንደደረሱ ያልታወቁትን ጓዶቿን ያስታውሳታል ያሳለፈቻቸውን ጊዜያት እንድትናፍቅ ያደርጋታል። የምታልፍባቸው መንገዶችም ሳይቀሩ የትዝታዋ ቀስቃሾች ናቸው።

በቤትና በጊቢያቸው የምታደርጋቸው እንቅስቃሴዎች እንኳን በቀን ውስጥ አብዛኛውን ሰዓት በላይሁንን፣ ወንድሟንና እህቷን እንድታስታውሳቸው ይገፋፏታል። በሃሳቧ ከእነርሱ ጋር ያደረገቻቸውን ነገሮች ትደግማቸዋለች። የበላይሁንን እህት ማየት በራሱ ለእርሷ ፈተናዋ ነው። ኢየሩስ በጣም ዝምተኛ ሆናለች፤ አለባበሷ ሳይቀር ተለውጧል፣ መሽቀርቀር ትወድ የነበረችው ልጅ ዛሬ እንደነገሩ ለባብሳ ነው ወደሥራ የምትሄደው። ብቻ ሕይወት ከእስር ቤቱ ያልተናነሰ የስቃይ ቦታ ሆነባት ለፍሬ። በሕዝብ በተጣበበው ዓለም ውስጥ እየኖረች ብቸኝነት ይሰማታል።



እናቷን በቤት ውስጥ ሥራ ታግዛቸዋለች፤ አንድ ጊዜ ወደማድቤት ከገባች በፍጹም አትወጣም፤ የሚያስቸኩለውንም የማያስቸኩለውንም ስትሠራ እዚያው ትውላለች።

አንዳንዴ እንቅልፍ እምቢ ይላታል፤ አገር ሁሉ ተኝቶ ጭር ባለው ሌሊት የፍሬሕይወት አእምሮ ግን ማረፊያ አጥቶ እንደዞረ ይነጋለታል። ከዓመታት በፊት የነበሩትን የሰፈሯን ልጆች፣ ይሰበሰቡባቸው የነበሩትን አካባቢዎችና አላፊ አግዳሚውን የሚለክፉት ለከፋ፣ ሕይወቷን ወደማይመለስበት ጎዳና የመራውን ዘመቻ፣ ዘማቾቹንና አርሶአደሩን፣ ከዘመቻ መልስ በሰፈሯ ወጣቶች ላይ ያስተዋለችውን ለውጥ፣ ትግሉን፣ ለትግሉ ወጣቱ የነበረው ስሜት፣ ሰላማዊ ሰልፎቹን፣ የነበረውን መተሳሰብ፣ የከፈሉትን መስዋዕትነት፣ የነበረውን ጠንካራ ዲሲፕሊን…

አንዳንዴ የማታውቀውን የአሲምባን ተራራ በምናቧ ስትቃኘው ትቆያለች። አሲምባ የኢሕአፓ ሠራዊት አባላት የትጥቅ ትግል ማዕከል መሆኑን ከመስማት ሌላ ስለቦታው የምታውቀው ባይኖርም በሀሳቧ ታየዋለች። በፊልም እንዳየቻቸው የጦር ምሽጎች ሁሉ የአሲምባ ሕይወት ከባድ እንደሚሆን ታስባለች። የተጎሳቆሉ ግን ጠንካሮች ለምንም የማይበገሩ የሠራዊቱ አባላት በአይኔ ህሊናዋ ይታዩዋታል፤ ሚሚን ጸጉሯን አሳጥራ፣ ቁምጣ ለብሳ፣ ዝናሯን ታጥቃ፣ በረባሶ ተጫምታ በአሲምባ ተራራ ላይ ላይ ታች ስትል፣ ስትታከስ… ላቧ በግንባሯ ሲንቆረቆር… ሌሎቹ ጓዶች ሲያበረታቷት… ድንገት ደግሞ ሌላው ትዝ ይላታል "እዚያም መከፋፈል ተፈጥሮ ይሆን?" ብላ ራሷን ትጠይቃለች። ልክ እንደዚሁ እንደአዲስ አበባው እነርሱም ዘንድ ክፍፍል ሲፈጠር፣ አንዱ በሌላው ላይ መሳሪያ ሲያዞር … ዐይኖቿን ትጨፍናለች ከዚያ በኋላ ያለውን ላለማሰብ አእምሮዋን ለመግታት ትሞክራለች። ግን አይሆንላትም እንደገናም ታስበዋለች፤ በሕይወቷ ሁሉ ያን ከማሰብ የሚገታት ነገር ያለ አይመስላትም።

አንተነህ የት እንደሄደ ባታውቅም አሲምባ እንዳልሆነ ይገባታል። አንተነህ ከፓርቲው ራሱን ለይቶ ነው የሄደው። ግን እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ አንተነህን ለመፈለግ ያላደረገችው ጥረት የላትም። አብረው የሄዱባቸው አካባቢዎች ሁሉ ሄዳለች፣ በድፍረት እነሂዋን ቤት ደውላ ሂዋን ውጭ መሄዷን ብትሰማም ስለአንተነህ ግን ምንም

ሊነግሯት አልቻሉም። ከአንተነህ ጋር ይሄዱበት የነበረው አፓርትመንት፣ አራት ኪሎ ተመላልሳለች ግን ምንም አላገኘችም። ዘመቻ ጣቢያ ይቀርቡት የነበሩ ጓደኞቹን አፈላለጋ ጠይቃለች ስለአንተነህ ግን የሚያውቅ አንድ ሰው እንኳ አላገኘችም። ምናልባትም ቢያውቁም ለእርሷ ሊነግሯት አልፈለጉም ይሆናል። ሁሌም የማይቋጭ ሀሳብ! አንስቶ መጣል ብቻ!

* * * *

ወይዘሮ ስርጉት ጥረታቸው ሰምሮላቸው ደህና ይምሰሉ እንጂ ውስጣቸው ለአንድ ቀን እንኳ የተሟላ ሰላም አግኝቶ አያውቅም። በቀን ሀሳባቸው በሌሊት ሕልማቸው ሁሌም ከቃለአብና ከሚሚ ጋር ናቸው። "ምኑን ይሆን የተመታው? እንዴትና የት ይሆን የተጣለው? ... ሚሚ የት ደርሳ ይሆን? አውሬ በልቷት ይሆን ወይስ የጥይት ሰለባ ሆና ይሆን? ..." ሁሌም መልስ የማያገኙላቸውን ጥያቄዎች እንደጠየቁ፣ እንባቸውን እንዳፈሰሱ ናቸው።

የፍሬሕይወትም ነገር ያሳስባቸዋል፣ ያች ቤት ውስጥ እግሯ የማይቆይ ልጃቸው ውጭውን ለማየት መጥላቷ፣ ዝምታዋና ትካዜዋ ያሳስባቸዋል። "ምነው አምላኬ ..." ይላሉ ባዩዋት ቁጥር። "ልጆቼ አድገው፣ ራሳቸውን ችለው፣ ለወግ ለማረግ በቅተው..." ዛሬ የሚያስቡት አይደለም፣ ሕልማቸው ሁሉ እንደጉም በኖ ጠፍቷል፣ ውስጣቸውም እየደከመ መሆኑ ይሰማቸዋል። ይጨነቃሉ "ይች ልጅ እንዲህ በደመነፍስ የምትኖረው እስከመቼ ይሆን?" ይላሉ ፍሬሕይወት ለብዙ ሰዓታት በትካዜ ተውጣ ሲመለከቷት።

ከእስር ቤት ከወጣች አምስት ወራት ተቆጠሩ፣ መጪው ወር ደግሞ ትምህርት የሚጀመርበት የመስከረም ወር ነው። እርሷ ግን ስለምንም የምትጨነቅ አትመስልም፣ አንድም ቀን ስለትምህርት አንስታ አታውቅም፣ እናም ግራ ግብት ቢላቸው አንድ ቀን ሊጠይቋት ወሰኑና

"ፍርዬ!" ብለው ጠሯት።

"እመት እማ!" አለች በፍጥነት።



"ምን እያሰብሽ ነው?"

"ስለምኑ እማ!"

"ስለቀጣዩ ሕይወትሽ"

"ምን ሕይወት አለ እማ" አለቻቸው በፍጥነት። አባባሏ አስደነገጣቸው።

ሌላ ምንም ሳይናገሩ ትተዋት ወደውጭ ወጡና በረንዳው ላይ ቆሙ። በረንዳው ላይ ቆመው በሀሳባቸው ጭልጥ ብለው ሄዱ። የሕይወታቸውን ዘመናት ሁሉ በሃሳባቸው አዳረሷቸው። አጀማመሩ አስደሳች የነበረ ሕይወት፣ መተሳሰብና መተጋገዝ የነበረበትና በተስፋ የተሞላ ትዳር፣ ጤናማና ደስተኛ ልጆች ያደጉበት ቤት... ብዙም ሳይቆይ ደግሞ የባለቤታቸው ድንገተኛ ሞት ፣ መከራና ችግር... ፖለቲካ... ስደትና እስራት... የልጅ ሞት... ተስፋ የሌለውና የጨለመ ወደፊት...

"እማ እዚህ ነሽ እንዴ?" የሚለው የፍሬሕይወት ድምጽ ከሄዱበት መለሳቸው። ዞር ብለው ተመለከቷት፣ እንደዚህ ለብሳ ካዩዋት ቆይተዋል፣ ፀጉሯ ከነመፈጠሩም የረሳችው ይመስል አንድም ቀን እንደሚገባ ስታደርገው አላዩዋትም፣ አሁን ግን ያዩትን ማመን አቃታቸው፣ የፍሬሕይወት ፀጉር የዱሮው ርዝመቱ ባይኖርም ውበቱ አለ፣ የድሮዋን ልጃቸውን ተመለከቷት። በጣም አምራለች። ዐይኖቻቸውን እንባ ሲያቃጥላቸው ለመመለስ ታገሉት።

"እማ በጣም ይቅርታ! አሳዘንኩሽ አይደል?" አለቻቸው እንባ የእርሷንም ድምጽ እየቆራረጠው። "ትምህርት እጀምራለሁ፣ ልመዘገብ መሄዴ ነው" አለቻቸው።

"ጎሽ ተባረኪ፣ ሀዘንና ተስፋ መቁረጥ ቅርቤቴ ሆኑብኝ፣ አንቺ ለሕይወት ያለሽን ስሜት ስመለከት ለአንቺ ብቻ ሳይሆን ለሮቤልም ይጨነቀኛል፣ እንግዲህ ሮቤል ማንን ያያል? ከእንግዲህ ለሮቤ ያለሽው ደግሞ አንቺ ነሽ..." አሏት።

"እማ! እኔ ይህንን መስማት አልፈልግም፤ አንቺ ከሌለሽ ደግሞ ማናችንም የለንም" አለች።

"መሸሽ አይቻልም ፍርዬ ውስጤን ስለማውቀው ነው" አሏት።

"እማ! እባክሽ አንቺ ደግሞ እሺ በይኝና እንደገና ሀኪም ቤት እንሂድ፤ ይህንን "ውስጤን ስለማውቀው" የምትይውን ነገር አልወደውም" አለቻቸው።

"አይ ፍርዬ! መሸቶ በነጋ ቁጥር መድከሜ ከሚሰማኝ በስተቀር ምን ህመም አለኝ ብለሽ ነው?"

"ግዴለሽም! እኔን ደስ እንዲለኝ፣ በሙሉ ልቤም ትምህርት ቤት እንድገባ" አለቻቸው። ተስማሙላት።

"እማ አንቺ እኮ በጣም ጠንካራ ነሽ፣ ደግሞ ገና ልጅ ነሽ ለምን ስለሞት ታስቢያለሽ?" አለቻቸው ደግሞ።

"ቢሆንልኝ እኔም ባላስብ እመርጣለሁ። እስኪ እግዚአብሔር ያውቃል! አንቺ ብቻ በርቺልኝ፤ አንቺ ትምህርትሽን ከጀመርሽ እኔም እበረታለሁ" አሏት እቅፍ አድርገዋት።

"ቃል እገባልሻለሁ!" አለቻቸው።

ፍሬሕይወት ከጊቢው ወጥታ ከዐይናቸው እስከምትሰወር ድረስ ተመለከቷት። "እባክህን አበርታልኝ!" አሉ ወደሰማዩ አንጋጠው።

ቤት ገብተው ተቀመጡ፤ የፍሬሕይወት ትምህርት ለመጀመር መወሰን በጣም ደስ አላቸው። ውስጣቸውን አዳመጡት፤ ሆኖም ግን እዚህ ግባ የሚሉት ጥንካሬ አልተሰማቸውም። "ቢሆንም" አሉ ለራሳቸው "ቢሆንም ከእግዚአብሔር ጋር እስከመጨረሻዋ ዕለት እታገላለሁ" አሉ።

"ስርጉት፤ ተኝተሻል እንዴ?" አሉ የበላይሁን እናት ከውጭ።



"እመት፤ ኧረ አልተኛሁም" አሉና ፈጠን ብለው ወጡ።

"ፍሬ የለችም እንዴ?" አሉ የበላይሁን እናት።

"ትምህርት ቤት ልጠይቅ ብላ ወጣች"

"እሰይእመብርሀን! እኔስ ሀሳብ ይዞኝ ነበር። እንዲያው ነገር አለሙን ሁሉ ትታው ቤት መቀመጧ አሳስቦኝ ነበር" አሉ የበላይሁን እናት።

"የበላይ አባት እንዴት ናቸው?" የፍሬሕይወት እናት ደግሞ ጠየቁ።

"አይ ስርጉቴ! እልቅሰን የሚወጣልን እኛ እንሻላለን እኮ፤ ሀዘኑን በሆዱ አምቆ እህህ ሲል ነው የሚያድረው፤ እንቅልፍ ያለው መሰለሽ" አሉ የበላይሁን እናት እርሳቸውም እየተከዙ።

"እንግዲህ ውስጣችን እንደበሰለ መኖር እንጂ ምን ይደረጋል?" አሉ የፍሬሕይወት እናት።

"ወይ ጉድ የመጣሁበትን እረስቼው፤ ነይ እስኪ ቁርስ እንብላ" አሉ የበላይሁን እናት። መቼም የበላይሁን እናት ባይኖሩ ወይዘሮ ስርጉት በሕይወት መቆማቸውም አጠራጣሪ ነበር። ምግብ የሚቀምሱት፤ በጨዋታ ሀሳባቸውን የሚከፍሉት ከእርሳቸው ጋር ነው። ለበላይሁን እናትም ያው ነው፤ ሕይወት ሲያስጠላቸውና ሀዘን ሲበረታባቸው የሚያበረቷቸው የፍሬሕይወት እናት ናቸው። "እርሷ ባትኖር ምን ይውጠኝ ነበር" ይላሉ እርሳቸውም።

ሁለቱ እናቶች ተከታትለው ቁርሳቸውን ሊበሉ ገቡ።

* * * *

ፍሬሕይወት የእናቷ ሁኔታ አስደንግጧታል ሳታስበው በተናገረችው ነገር በጣም እንደከፋቸውና እንዳዘኑ ተመልክታለች። እርሳቸውን ለማስደሰት ስትል የራሷን ስሜት መርሳት እንዳለባት ወሰነች፤ "ደግሞስ እስከመቼ ነው በትካዜ መቆየት የሚቻለው" አለችና ራሷን ለማበረታታት ሞከረች። ለእናቷና ለሮቢ ስትል ራሷን ማስተካከል፤ መቆዘምና ማሰቧን መቀነስ ይኖርባታል፤ ግን የቀድሞው ትምህርት

ቤት ለመማር የሚችል ጭንቅላት የላትም፡፡ እዛ ግቢ ስንት የምታስታውሰው ነገር አላት? ለምን ራሷን ትበጠብጠዋለች? እናም አብረዋት ከተፈቱት ሰዎች መሀል የሁለተኛ ደረጃ አስተማሪዎች እንደነበሩ አስታወሰች፤ አንዳቸውን ለመጠየቅ ወሰነች፤ የስልክ ቁጥር ከማስታወሻዋ ላይ ፈለገችና ደወለች።

“የምችለውን ሁሉ ለማድረግ እሞክራለሁ” አላት የደወለችለት ሰው። ከሶስት ቀናት በኋላ ስልክ ደውሎ የትምህርት መረጃ እንድታቀርብ ነገራት። የዚያኑ እለት ከድሮው ትምህርት ቤት የትምህርት መረጃዎቿን አውጥታ ወሰደች። ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ተሳክቶላት ትምህርት ልትጀምር እንደምትችል ተነገራት።

“እማ ነገ ትምህርት ልጀምር ነው” አለቻቸው ማታ ራት እየበሉ።

“እፎይ!” አሉና በረጅሙ ተነፈሱ እናቷ።

“እቴትዬ እኔም ደስ አለኝ” አለ ሮቤል ደግሞ።

ፍሬሕይወት የቱን ያህል ሀሳብ ሆናባቸው እንደነበር ስታስበው በውስጧ ቃልኪዳኗን አጸናች። የምትችለውን ሁሉ በትምህርት እንደምትበረታና በውጤቷም እንደምታስደስታቸው አሰበችውና ፈገግ አለች።

ትምህርት ስትጀምር ቀላል ሆኖ አላገኘችውም፡፡ ከተማሪዎቹ ጋር ተነጋግሮ መግባባት ተጫውቶ መሳቅ አልሆነላትም፤ ተሰቃየች። ልጆቹ እንደጊዜያቸውና እንደ ሁኔታው ነው መሆን የሚችሉት እርሷ ደግሞ እያንዳንዱን ነገር የምታነጻጽረው ከድሮው ጋር ሆነና ሁሌም መደበር ሆነ ዕድሏ። እነርሱም እንደባይተዋር ቆጠሯት። ሁሉን ነገር ማድረግ የምትፈልገው ከእስር ቤት ጓደኞቿ ጋር ስትገናኝ ብቻ ነው።

ሁልጊዜም የመጨረሻው ደወል ሲደወል በጥድፊያ ነው ከክፍል የምትወጣው። ከክፍል ወጥታ ሚስጥረ ቤት ሳትደርስ በፍጹም ወደቤቷ አትሄድም፤ ፍሬሕይወት ከእስር ቤት ስትወጣ ከተደሰተችባቸው ነገሮች አንዱ የሚስጥረ ትምህርት መጀመር ነው፤ በማታው ትምህርት አንደኛ ክፍል ገብታ መማር ጀምራ ስላገኛቻት



ደስታውን አልቻለችውም። ሚስጥረን ከእናቷ ጋር አስተዋውቃታለች፤ ከትምህርት ቤት ስትወጣ ወደእርሷ እንደምትሄድም ነግራቻቸዋለች፤ እናም ከትምህርት ቤት ቆየት ብላ መምጣቷ አያሳስባቸውም።

* * * *

ወህኒ ቤት (ከርቸሌ) አዲስ ሕይወት ነው፤ ከነበሩበት ጊዜያዊ እስር ቤት በጣም የተለየ። በየዕለቱ ፀሐይን ያለስስት የሚያዩበት፤ እግር ያሻውን ያህል የሚንቀሳቀስበት የተሻለ ነፃነት ያለበት ቦታ ነው ከርቸሌ። ትልቁ የብረት በር በተከፈተ ቁጥር “ማን መጣብኝ” ብሎ የማይሳቀቁበት ቦታ ነው። አልፎ አልፎ ወደደርግ ጽህፈትቤት መወሰድ ሊኖር ይችላል፤ አንዳንዴም የጅምላ ርሸናም ያጋጥም ይሆናል፤ ቢሆንም በየዕለቱ የሚሳቀቁበት አይደለም ከርቸሌ። ቢያንስ በሳምንት አንድቀን ቤተሰብንና ጓደኛን በአካል ማየትና በሩቅም ቢሆን ማነጋገር ይቻላል። ከርቸሌ ሌላም አለ፤ ተማሪው ይማራል ለማስተማር ብቃት ያለው ያስተምራል፤ ስፖርት በሽበሽ ነው።

ፈቃደ ወህኒ ከወረደ በኋላ የተሻለ ስሜት ያለው መሰለ። እንደማንኛውም እስረኛ ቤተሰቦቹ መጥተው ስላዩት ተደስቷል። እናቱ ቢሞቱም፤ አባቱም ጤናቸው የሚያወላዳ ባይሆንም እህትና ወንድሞቹ እንዲሁም ዘመዶቹ ይጠይቁታል። በመጀመሪያዎቹ ወራት ውስጥ ተጫዋችና ሳቂታ ሆኖ የእስር ቤት ጓደኞቹ ደስ ብሏቸው ነበር። ያስተምራል፤ የእግር ኳስ ይጫወታል፤ ቀልዱና ጨዋታው በጣም ጨመረ።

ለብቻው ሲሆን ግን እናቱንና እህቱን ያስታውሳል፤ እናቱ ታመው ዘመድ ወዳጅ ጠይቋቸዋል እንደሰውም በክብር ተቀብረዋል የእህቱን መሞት የሚያውቀው ግን እርሱ ብቻ ነው፤ ይህን ባስታወሰ ቁጥር ራስ ምታት ያሰቃየዋል። እህቱን ባስታወሰ ቁጥር ፍሬሕይወትን ያስባታል። ፈቃደ ለፍሬ ያለውን ስሜት ከእህቱ ጋር ከመመሳሰል ጋር ብቻ አያይዞ ሊያልፈው አልቻለም። ከመምሰሏ ባሻገር የሚዘልቅ ስሜት አለው።

“ደግሞ እኮ ጠንካራ ልጅ ናት” ይላል ለራሱ። የመጀመሪያው ቀን ወደእስር ቤት ሲመጣ ብዙ ሰው ይደናገጥና ይርበተበታል። ከእርሷ

ላይ ግን ያን ዓይነት ስሜት አላየባትም፤ ኮስተር ብላ ለሚደርሰው ነገር ሁሉ ራሷን ያዘጋጀች ትመስል ነበር።

"ኢሕአፓ ስንት ጠንካራ ልጆች ነበሩት" ይላል ፈቃደ በቁጭት። ትውስታው ወደዚህ አቅጣጫ ከሄደ መመለስ አይሆንለትም። ስንት የሚያስታውሳቸው ወጣቶች አሉት።

አንድ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ሥራ ላይ የተከሰተውን ነገር በፍጹም አይረሳውም። ትልቅ የዕድር ስብሰባ ሲካሄድ ቅስቀሳ የማድረግ ዕቅድ ነበረ፤ ቅስቀሳውን ለማድረግ የተመደቡት ሰዎች ሲመጡ ሽፋን መስጠት አስፈላጊ ስለነበረ በተጠንቀቅ ላይ ነበሩ እነፈቃደ። "አንድ ጊዜ" የሚል የሴት ድምጽ ተሰማና ሁሉም ጸጥ አለ፤ አንድ ጎፈሬው አደግ ያለ ወጣት ወደፊት ወጣና "ሕዝባዊ መንግሥት ለምን?" በሚል ርእስ አጠር ያለ ንግግር አደረገ፤ በልጁ አነጋገርና ባነሳቸው ቁምነገሮች ተሰብሳቢው ተደምሞ ሳያበቃ ልጅቱ ደግሞ በፍጥነት ወደመድረኩ ወጣች፤ የተናገረችው ለአስራአምስት ደቂቃዎች ብቻ ነበረ፤ ሰው ሁሉ አፉን ከፍቶ አዳመጣት። "ኢሕአፓ ያቸንፋል!" አለች በመጨረሻ። ስትሄድም የነበራት ፍጥነት ልክ እንደአመጣጧ ነበር። በሰው ላይ ፈጥራው የነበረው ስሜት የሚደንቅ ነበር፤ "አሁን በሕይወት ትኖር ይሆን?" አለና ራሱን ጠየቀ።

ፈቃደ ምን የማያስታውሰው አለው? መቋጫው ግን ፍሬሕይወት ነች። ምናልባትም እዛ እስር ቤት ከገባ በኋላ በተለይም ምርመራው ክፍል አካባቢ ሴት እስረኛ ስላላጋጠመው ሊሆን ይችላል፤ ብቻ ለፍሬ ልዩ ቦታ አለው። ምርመራ ክፍል ያያቸውን ሌሎች ሴቶች በጣም ይጠላቸዋል፤ የሚናገሯቸው ቃላት እንኳ አይመቹትም፤ "መችም እነዚህ ኢሕአፓ ሆነው አያውቁም። ደጋፊም እንኳን ሊሆኑ አይችሉም" ይል ነበር ሁልጊዜ ሲያያቸው። ታዲያ በእነርሱ ዐይን እያየት ይሆን ፍሬን እንዲያ ያከበራትና በልቡ ውስጥ ልዩ ቦታ የሰጣት?

ግን ለራሱ ታማኝ መሆን አለበት፤ በማፍቀርና በማድነቅ መሀል ያለውን ልዩነት አሳምሮ ያውቀዋል። ራሱን ሊክድ በፍጹም አይችልም። ፈቃደም በተፈጥሮው ለራሱና ለስሜቱ ታማኝ ነው። አዎ! ለፍሬ ያለው ስሜት ፍቅር መሆኑን ከተረዳው ቆይቷል። ደግሞ



ፍቅረኛው ትዝ ትለዋለች፤ ፍቅረኛውን ይወዳት ነበር፤ ከፍተኛ እስር ቤት በነበረ ጊዜ ግን ብዙ አልጠየቀችውም። በጣም ይገርመው ነበር። ወህኒ ከወረደ በኋላ በተደጋጋሚ እየመጣች ስትጠይቀው መተያየታቸው የነበራቸው ፍቅር እንዲቀሰቀስ አድርጎታል። ቢሆንም፤ ልቦናውን ሲመረምረው ወደ ፍርዬ አደላበት፤ እናም በሀሳቡ ለበፊት ፍቅረኛው ይነግራታል፤ ከእርሷ ይልቅ ከፍሬ ጋር የተቀራረቡ መሆናቸውን ሊያሳምናት ይሞክራል። "ግን እርሷስ ብትሆን እስካሁን... "ይላል ደግሞ ሰበብ ሲፈልግ።

"ራሴን ማሳመን ካቃተኝ ምን ማድረግ እችላለሁ? እስከመቼ ነው አይሆንም ብዬ የምዘልቀው? ልቤና መንፈሴ ሌላ እኔ ደግሞ ሌላ መሆን አንችልም" ይላል ስሜቱን መቀበል እንዳለበት ለራሱ ሲያሳምን። ደግሞ ያለበትን ቦታ ያስባል፤ በነፃ ሰውና በእስረኛ መሀል ያለውን ልዩነት ያስታውስና "ይህን ጊዜ እኮ ስንቱ ይመኛታል፤ እንደኔ በሩቅ ሳይሆን..." ይልና ይበሳጫል። ግን መሞከርን ማን ይከለክለዋል? ማን ያውቃል...

* * * *

ዛሬም ፍሬሕይወትን የሚያስደስታት ከእስር ቤት ጓደኞቿ ጋር መገናኘት ነው፤ እነርሱ የሚግባቡበት ቋንቋ አላቸው፤ ከተነሳ የማያልቅ ትዝታቸውን ማውራት ከሁሉም በላይ ይናፍቃታል። ቢሆንም እያደር ወደመደበኛው ሕይወት የመግባት ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው። በተገናኙ ቁጥር ስላለፈው የፖለቲካ ሕይወት ብቻ ማውራት እየቀነሰ ስለዛሬው ሕይወት መጨዋወት ተጀምሯል። የእርሷ የሁልጊዜ ወሬ መስዋዕትነት ስለከፈሉ ጓዶች ነው "እኛ የእነርሱ ባለዕዳዎች ነን" ትላለች ፍሬሕይወት። እነሱ ሕይወታቸውን ከፈሉ እኛ ደግሞ ቢያንስ እነርሱ ቢኖሩ ለቤተሰባቸው ሊያደርጉ የሚችሉትን ነገር በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለማድረግ ማሰብ ይኖርብናል" ትላለች ሁልጊዜ።

"ፍርዬ የምትይው ያገባናል ግን ሕይወት እንደገና መቀጠል አለበት። የሆነው ሁሉ ሆኗል፤ እኛ የተረፍነው ግን መኖር አለብን፤ እንደ ዕድሜያችን ልናደርግ የሚገባንንም ማድረግ ይኖርብናል። ለሌሎችም ማሰብ ያለብን እየኖርን ነው!" ይሏታል።

የእሁድ የወህኒቤት ማርፈጃ አልተቋረጠም። እነፍሬ ተሰባስበው ይሄዳሉ፤ ያገኙትን ሁሉ ገዝተው ጓደኞቻቸውን ሊጠይቁ ሲሄዱ ለደስታቸው ወሰን የለውም፤ ጓደኞቻቸውም ይጠብቋቸዋል። ስጦታው ከውስጥም ይገርነደንዳል፤ እራሳቸው የሰሯቸውን የተለያዩ ቅርጻቅርጾች ይሰጧቸዋል። ሲገናኙ በርቀትም ቢሆን ተጨፋጨፈው፣ ተተራርብው... አይበቃቸውም፤ ከዚያ ግቢ ውጡ ካልተባሉ አይወጡም ።

ከወህኒ ቤት የሚሰጧቸውን ስጦታዎች በአብዛኛው የትኛው የማን እንደሆነ አያውቁትም፤ ብቻ እየተጯጯሁ እየተቀበሉ ወደቦርሳቸው መክተት ነው። አንድ ቀን ታዲያ ፍሬ ያልጠበቀችው ነገር ገጠማት። አንድ ከከርቸሌ የተሰጣትን በእጅ ሥራ ያማረ ስኪሪፕቶ አወጣችና ልትጽፍበት ከፈተችው መጻፊያ ግን አልነበረውም፤ ውስጡን ለማየት ስትሞክር ወረቀት አለበት። ወረቀቱን አወጣችው። ስኪሪፕቶውን ማን እንደሰጣትና መቼ እንደተሰጣት እንኳን አታስታውስም። ወረቀቱን ስትገልጠው ልቧ እየመታ ነበረ። ወረቀቱ ላይ የተጻፈው አጭር ነገር ነበር።

“ፍሬ! አፈቅርሻለሁ። በልቤ ውስጥ ልዩ ቦታ እንዳለሽ ተረጂልኝ” ፈቃደ ይላል ወረቀቱ ላይ የተጻፈው።

ደነገጠች፤ በጣም ደነገጠች። በሚቀጥለው እሁድ ከርቸሌ ሲሄዱ ከፈቃደ ጋር የነበራት ቆይታ ለየት ያለ ነበር። በጽሑፉ ከገለጸው የበለጠ ፍቅር ከዐይኖቹ ያነበበች መሰላት። ጓደኞቿ ምንም ጊዜ አልሰጧትም፤ ያንኑ ቀን በተረብ አጣደፏት።

ከጓደኞቿ ስትለይና ብቻዋን ስትሆን ግን ያ ሁሉ ደስታ በአንድ አፍታ ተኖ ጠፋባት። ሀሳቧ ሁሉ ተመሰቃቀለባት፤ ራሷን ከሀዲ አድርጋ ቆጠረችው። ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በዐይኗ ሳይዞር ነጋላት። በሀሳቧ ስትባክን ሌሊቱ ቦታውን ለቀኑ አስረከበ። “በፍጹም ላደርገው አይገባኝም!” አለች በመጨረሻ። በሚቀጥሉት እሁዶች ከርቸሌ ሳትሄድ ቀረች።

* * * *



“የምትመጣ ይመስልሻል?” አለ ዳኙ ሰዓቱን እየተመለከተ።

“ይመስለኛል፤ መልዕክቱ ደርሷት የምትቀር አይመስለኝም፤ አሁን ፈተና በመቃረቡ ነው እንጂ በፍጹም እኔን ሳታየኝ ወደቤቷ አትሄድም ነበር” አለች ሚስጥረ ወሣውን እየተመለከተች።

“ምን ብለሽ ነው መልዕክት የጻፍሽላት?” አለ ዳኙ።

“እንዴ ምንድነው ይሄ ሁሉ? “በጣም ስለምፈልግሽ ከትምህርት ቤት እንደወጣሽ በኔ በኩል እንድትመጭ ብዬ ነዋ!” አለችው እየገረማት።

“ፈቃደ መፈታቱን ሰምታለች እንዴ?” አለ ደግሞ ዳኙ።

“ከኔ ጋር አልተገናኘንም፤ ማን ይነግራታል?” ጥያቄውን በጥያቄ መለሰችለት።

“ስለፈቃደ ምን ነግራሽ ታውቃለች?” አላት ዳኙ ሚስጥረን እየተመለከታት።

“መቼ? ውስጥ እያለን እንደምታደንቀው ነግራኛለች...” አቋረጣት ዳኙ “ኧረ በቅርብ ጊዜ” አላት።

“እንዲያውም! ምንም ነግራኝ አታውቅም፤ ምነው? አሁንስ ግራ እያጋባኸኝ ነው። ከእስር ቤት ሰው ሲፈታ ለማግኘት ያጓጓል እንጂ ያስጠላል እንዴ?” አለችው ግራ ተጋብታ።

“ፈቃደ ፍሬን ይወዳታል፤ እንደሚወዳትም ታውቃለች። እናም እርሱ እዚህ ቤት እንደሚመጣ ካወቀች ላትመጣ ትችላለች ብዬ ነው” አለና እቅጩን ነገራት።

“እንድጠራት የፈለግከው ለዚህ ከሆነ በጣም ልክ አይደለህም ዳኙ፤ ፍሬ እንዲህ ዓይነት ግንኙነት መመስረት አይደለም ሀሳቡም እንዲነሳባት የምትፈቅድ ያለመሆኗን አውቃለሁ። ለምን እንዲህ ዓይነት ነገር ውስጥ ትከተኛለህ?” አለችው ኮስተር ብላ።

"አሁንም ውሳኔው የግሏ ነው፤ በመሸሽ ሳይሆን በንግግር መግባባት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ከተገናኙ በኋላ ቁርጥ ያለ መልስ ስትሰጠው እርሱም ሀሳቡን ሊተወው ይችላል..." ዳኙ በሩ ሲንኳኳ ንግግሩን አቋረጠ።

የመጣው ፈቃደ ነው፤ ከሚስጥረ ጋር ተሳስመው ሲያበቁ "አልመጣችም እንዴ?" አለ።

"አልመጣችም" አሉት ሁለቱም።

ፈቃደ ሀሳብ ገባው፤ "እንደምመጣ ግን አውቃለች?" ብሎ ለጥያቄው መልስ ሳያገኝ

"ዛሬ ደግሞ ትምህርት ቤት ድረስ መልክት የተላከው ለምንድነው?" እያለች ፍሬሕይወት እበሩ ላይ ሆና።

"ይልቅስ ግቢ" አለቻት ሚስጥረ ከውስጥ ሆና።

የሳሎኑን በር ከፊት አድርጋ ስትገባ በመጀመሪያ ያየችው ፈቃደን ነበር። የት እንዳለች እስኪጠፋባት ደነገጠች። በቅርብ ጊዜ ከወሀኒ የተፈቱ ሰዎች መኖራቸውን እንኳን አልሰማችም። እሁድ ከርቸሌ ከሄደች ሁለት ወር አካባቢ ይሆናታል። ከድንጋጤዋ በቶሎ መውጣት አልቻለችም፤ ሚስጥረ ተነስታ እየሳመቻት "ደነገጥሽ አይደል?" አለቻት በጆሮዋ። የምትመልሰው አልነበራትም። ለፈቃደ እጇን ለሰላምታ ዘረጋችለት ፤ እርሱም ከእርሷ ባልተናነሰ ሁኔታ ደንግጧል። እጃን ዘረጋ ፤ ተጨባበጡ።

"እንዴ! እንዲህ ነው እንዴ ሰላም የምትባባሉት?" አለች ሚስጥረ።

"እንኳን ደስ ያለህ!" አለችው ፍሬሕይወት።

"እንኳን አብሮ ደስ አለን" አላት እንደቆመ።



ዳኙን ሳመችውና ተቀመጠች፤ ሚስጥረን ለምን እንደፈለገቻት መጠየቅ አላስፈለጋትም። ለምን እንደተፈለገች ገብቷታል፤ ግን ጨንቃት፤ ምን ብላ ወሬ ትጀምር?

ሚስጥረም ከእርሷው እኩል ጨንቋታል፤ እንዳትቀየምባትም ሰግታለች።
"ተጫወቱ" አለችና ወደ ጓዳ ገባች። ፍሬም ተከትላት ገባች "ምነው ሚስጥረ?" አለቻት በወቀሳ ዓይነት።

"ሌላ ጊዜ አወራልሻለሁ" አለቻት በአጭሩ።

ፍሬ ወደሳሎን ተመለሰችና ተቀመጠች። "ትምህርት እንዴት ነው?" አላት ዳኙ።

"ምንም አይልም፤ ጥሩ ነው" አለችው ፍሬሕይወት።

"የት ትምህርት ቤት ነሽ" አለ ፈቃደም ቀጠል አድርጎ። ነገረችው። "ስንተኛ ክፍል ገባሽ?'

"አስራ ሁለተኛ?"

"ለብሔራዊ ፈተና እየተዘጋጀሽ ነዋ?" አላት ፈገግ ብሎ።

"ይመስላል" አለችው እርሷም ፈገግ ብላ። ቀስ በቀስ የቤቱ አየር ቀለል አለ።

ሚስጥረ ሻይና መክሰስ ይዛ መጣች። ሻዩን እየጠጡ ዝምታ ሰፈነ።

"ልሂድ አይደል? እናቴ ትሰጋለች" አለች ፍሬሕይወት ሻዩን ጠጥታ ስትጨርስ።

"ስልክሽን ብትሰጭኝ ደስ ይለኛል" አላት ፈቃደ ሊሰናበታት እየተነሳ። ስልክ ቁጥሯን ሰጠችው።

"ምንድነው የሚያስደስታት?" አለ ፈቃደ ፍሬ ከወጣች በኋላ።

“እኔ እንኳን ለትግሉ ከነበራት ቁራጥነት ያለፈ ዕውቀት የለኝም” አለ ዳኙ ሚስጥረን እየተመለከተ።

“ሚስጥረ መቼም በሚገባ ታውቂያታለሽ” አለ ፈቃደም እርሷኑ እየተመለከተ።

“ፍሬን በጣም አውቃታለሁ ብዬ አስባለሁ። ዛሬም ቢሆን ስላደረገችው ፖለቲካዊ ተሳትፎ ደስተኝነት የሚሰማት፣ የትግሉ ግብ ሳይመታ መጨናገፍ በጣም የሚቆጫትና ከእስር በኋላ ሁሉን ረስቶና እንዳልነበረ ቆጥሮ በግል ሕይወት ላይ ብቻ ማተኮር ትክክል ያለመሆኑን የምትናገር፣ ቢያንስ ለትግሉ ሕይወታቸውንና አካላቸውን የሰጡ ጓዶችን መርሳት እንደማይገባ የምታምን ናት። ወደግል ሕይወቷ ስመጣ ፍሬ በብዙ መልኩ የተጎዳችና እህት፣ ወንድም፣ ፍቅረኛና ጓደኛ ያጣች ሰው ነች። አፍቃሪ ልቦና እንዳላት ባውቅም አሁን ባለችበት ሁኔታ ወደፍቅር ዓለም ለመግባት ዝግጁ አትመስለኝም” አለቻቸው ሚስጥረ።

“ባገኘሽው አጋጣሚ ሁሉ ግን እንደምወዳት ንገሪልኝ” አለና ፈቃደ ለመሄድ ተነሳ። ዳኙም ተከተለው።

* * * *

ፈቃደ ለፍሬሕይወት በተደጋጋሚ ደወለላት። በስልክ ሲያናግራት በሚገባ ትቀበለዋለች፣ የፈለገውን ያህል ታነጋግረዋለች። “ለምን አንገናኝም?” ሲላት ግን አይሆንም ትለዋለች።

አንድ ቀን ደወለላትና “ኧረ በፈጠረሽ ሻይ አብሮ ለመጠጣትም ቢሆን እሺ በይኝ” አላት ጠንከር ብሎ።

“በፍጹም አልችልም” አለችው እርሷም ፍርጥም ብላ።

ፈቃደ የፍሬን ስልክ ዘጋና ለሚስጥረ ደወለላትና ሊያገኛት እንደሚፈልግ ነገራት። በምሳ ሰዓት ተገናኙና ምሳቸውን አብረው በሉ። ምሳ እየበሉ ስለትግል ሕይወትና ስለእስር ቤት ቆይታቸው



አወሩ፤ ዳኙ ስለሚስጥረ ብዙ የነገረው ቢሆንም ፈቃደ ታሪኳን ከራሷ አንደበት ሲሰማ በጣም ደስ አለው። በተለይ ስለደረሰባት ስቃይ ስትነግርው በመገረም ነው የሰማት።

“ጀግና ነሽ!” አላት ካዳመጣት በኋላ።

“በእርግጥ የፖለቲካ ዕውቀት ሳይኖረኝ በእምነት ብቻ የከፈልኩት መስዋዕትነት ትልቅ ሊመስል ይችላል። ጀግና ሊባሉ የሚገባቸው ግን እንደምዕራፍ የመሰሉ ሕይወታቸውን የከፈሉ ናቸው፤ በሕይወቴ የማልረሳት ልጅ ነች” አለችው።

“ባውቃት ደስ ይለኝ ነበር፤ ባላውቃትም ያለኝ አክብሮት ከፍ ያለ ነው። ትግባባ ነበር? ” አላት።

“በጣም! እንዴት ዓይነት ልጅ ነበረች መሰለህ? ፈገግታ ከፊቷ ላይ ጠፍቶ አያውቅም፤ አጠገቤ መጥታ አነጋግራኝ በሄደች ቁጥር ትሰጠኝ የነበረው ጥንካሬ ዛሬም ይሰማኛል። ለማድነቅ የተፈጠረች እስኪመስለኝ ድረስ አድንቃኝ አታበቃም ነበር፤ መልፈስፈስን አጥብቃ እንደምትጠላ ትነግረኝና “የእግርሽ ቁስል ይድናል፤ የማያስፈልግ ነገር ተናግረሽ የምታተርፊው የህሊና ቁስል ግን እስከወዲያኛው አይሽርም፤ ስለዚህ ውሳኔሽ ትክክል ነው” ትለኝ ነበር።

ከፍሬ ጋር የነበራቸው መግባባት ደግሞ ልዩ ነበር። አብረው ሆነው ሳያቸው በጣም ደስ ይለኝ ነበር፤ ምዕራፍ የሄደች ቀን ፍሬ የሆነችውን ሳስታውስ የሆነ የሚጋሩት ነገር የነበራቸው ይመስለኛል። እንደማትመለስ አውቃው ነበር መሰለኝ ሁላችንን ተሰናብታን ነበር የወጣችው፤ በዐይኖቿ ፍሬን ፈለገቻትና ከዐይን ላይ በማይጠፋ ፈገግታዋ ተመለከተቻት፤ ልዩ መግባባት የነበራቸው መሰለኝ” አለችው በተመስጦ።

“ፍሬ አስቸጋሪ ልጅ ነች” አላት ድንገት ከነበረችበት ትዝታ አውጥቶአት።

“አስቸጋሪ ሆና እንኳን አይመስለኝም” አለችው በቀላሉ።

"ከዚህ የበለጠ ማስቸገር አለ እንዴ? ስንት ጊዜ እንደደወልኩላት ታውቂያለሽ? በስልክ በደንብ ታነጋግረኝና እንገናኝ ስላት ብልጭ የሚል ነገር አለባት። ሁሉን ነገር ታበላሸዋለች" አለ ፈቃደ።

"ቀስ በቀስ ካልሆነ ፍሬወሕይወትን በአንድ ጊዜ መለወጥ ይቻላል ብዬ አላስብም፤ ትዕግስት ብታደርግ ነው የሚሻለው" አለችው ሚስጥረ።

"ፍቅር ይዞሽ ያውቃል?" አለና አስደነገጣት።

"ፍቅር? እንጃ!"አለችው እየገረማት።

"ይቅርታ! ስሜቴን የቱን ያህል ልትረጂልኝ እንደምትችይ ለማወቅ ብዬ ነው" አላት። ዝምታ ሰፈነ። ሁለቱም በየሀሳባቸው ተጓዙና ደቂቃዎች ተቆጠሩ።

"አሁን ግን ምን እየሠራሽ ነው?" አለና ዝምታውን ሰበረው ፈቃደ።

"ይሄ ነው የምለው ሥራ የለኝም፤ ያገኘሁትን እሠራለሁ። ለአንድ ሆዴ ብዙም አልጨነቅም፤ አሁን በጣም የሚያስደስተኝ የማታ ትምህርት መጀመሬ ነው" ነው አለችው።

"ምንድነው የምትማሪው?" አላት ደግሞ።

"አታውቅም እንዴ ገና አንደኛ ክፍል መጀመሬ ነውኮ" አለችው።

"ሥራ መቀጠር ትፈልጊያለሽ?" አላት።

"እንዴ! ምን ጥያቄ አለው? አግኝቼ ነው?" ከልቧ መለሰችለት።
"ሥራ እንደማትመርጭ እተማመናለሁ" አላት ትኩር ብሎ እየተመለከታት።

"ልሠራው እስከቻልኩ ምንም ቢሆን እሠራለሁ"

"በቃ! ነገ እነግርሻለሁ፤ ጽዳትም ይሁን መላላክ ለመጀመር ተዘጋጂ" አላት ቀለል አድርጎ።



"እየቀለድክ ነው?" አለችው ማመን አቅቷት።

"በዚህ የምቀልድ ይመስልሻል? አሁን እንሂድ" አለና ተነሳ።

ሚስጥረ ከፈቃደ ጋር ተሰነባብታ ስትለያይ በአዲስ ተስፋ ተሞልታ ነበር። ፈቃደ ገረማት "በጣም ቀናና ደግ ሰው መሆን አለበት" አለች ለራሷ። ፍሬሕይወትን ስለምትወዳት ከፈቃደ ጋር ጓደኝነት እንድትጀምር ተመኘች።

ቤቷ ከመግባቷ በፊት ለዳኙ ስልክ ደወለችለትና "ልንገናኝ እንችላለን?" አለችው።

"በሚገባ! የት ነሽ?" አላት ዳኙ።

"ፍላሚንጎ" አለችው።

"በቃ መጣሁ፤ እዚያው ጠብቂኝ" አላትና ስልኩን ዘጋው። ዳኙ ገና መደበኛ ሥራ አልጀመረም፤ በሚቀጥለው ዓመት ያቋረጠውን የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ሊቀጥልም ያስባል።

ሚስጥረ ስልኩን ዘጋችና ተመልሳ ፍላሚንጎ ገባች። ከፈቃደ ጋር ተቀምጠውበት የነበረው ቦታ ባዶ ነው፤ እዚያው ተቀመጠች። ዳኙ ብዙ አልቆየም "ምን ተገኘ?" አላት ከሰላምታ በኋላ።

"መጀመሪያ ተቀመጥ" አለችው እርሷ እየተቀመጠች።

"ፈቃደን አግኝቼው ነበረ" አለችው

"እና ምን አለሽ?" አላት በጥድፊያ።

"ፍሬ እምቢ እንዳለችውና እርሱ ደግሞ በጣም እንደሚወዳት ነገረኝ" አለችው እያዘነች።

"ታዲያ ምን እናድርግ ብለሽ አሰብሽ?" አለ በሀሳቡ ሊያደርግ የሚችለውን እያውጠነጠነ።

“እኔማ ከእኔ ይልቅ አንተ ብትጠይቃት ምናልባት እሺ የምትል ከሆነ ብዬ ነበር” አለችው።

“መሞከር እችላለሁ” አለ ዳኙ እንደሚያሳምናት እየገመተ።

“እንዲህ እንደምትለኝ እርግጠኛ ነበርኩ” አለችው በማመስገን ዓይነት። ቀጠል አድርጋ ደግሞ።

“ዕውነቱን ለመናገር ይህን ለማድረግ ያሳሰበኝ ፍሬ ጥሩ ሰው እንዲገጥማት ባለኝ ምኞት ነው” አለችው።

“ይህን ለማለት የተለየ ምክንያት አለሽ?” አላት ዳኙ፤ ይህን ያህል ፈቃደን ታውቀዋለች ብሎ ስላልገመተ።

“መቼም ቀናነትን መገመት አያስቸግርም፤ ለእኔ ብዙም ለማያውቀኝ ሰው ሥራ ሊፈልግልኝ ማሰቡ ቀናነቱን ነው የሚያመለክተው”አለችው።

“የምን ሥራ ነው የሚፈልግልሽ?”

“የተገኘውን ነዋ! ዋናው ነገር ማሰቡ ነው” አለችው።

“በእርግጥ በአንድ ነገር ብቻ የሰውን ማንነት ማወቅ ያዳግታል፤ የፈቃደን ቀናነት ግን እኔም እመሰክራለሁ። ለማንኛውም ለምን ለፍሬ እንደውልላትም” አለ ዳኙ።

ከፍላሚንጎ ወጡና በሕዝብ ስልክ ለፍሬ ደወሉላት።
“በጣም አስቸኳይ ነው? እያጠናሁ ነበር” አለችው ፍሬ ዳኙ ሲያነጋግራት።

“ብዙ አትቆይም፤ ደግሞም ትንሽ እረፍትም ያስፈልጋል። ሚስጥረም አብራኝ አለች” አላት።

“እሺ እመጣለሁ” አለችው። ወደሱፐር ማርኬት አካባቢ ጠጋ እንደሚሉላት ተነጋገሩ።



“ዛሬ የሚገርም ነው ፤ ለምን እንደፈለጋችሁኝ ለማወቅ ቸኩያለሁ” አለቻቸው ገና ሲገናኙ።

“መችም ለዱሮው ጉዳይ እንደማይመስልሽ እርግጠኛ ነኝ” አላት ዳኙ እየቀለደ።

“ለዚያ ቢሆን የሚከፋኝ ይመስልሃል?” አለችው።

በሱፐር ማርኬት ህንጻ ስር ካሉት በአንደኛው ካፌቴሪያ ውስጥ ገብተው ተቀመጡና ጨዋታቸውን ቀጠሉ። ሚስጥረና ዳኙ ተያዩ።

“እኔ የምልሽ ፍሬ” አለ ዳኙ ድንገት በጨዋታ መሀል። ፍሬሕይወት ቀና ብላ በጥያቄ ዓይነት ተመለከተችው።

“ምን ሆነሽ ነው ፈቃደን እምቢ ያልሽው?” አላት በቀላሉ።

የፍሬሕይወት ፊት ሲለዋወጥ ተመለከቱና ሁለቱም ደነገጡ፤ “ልመናና ምልጃ የምፈልግ ሰው እመስላችኋለሁ? ወይንስ የምግደረደር?” በንዴት ነው ጥያቄውን ያቀረበችው።

“ይቅርታ! አንቺ ባሰብሽው መንገድ አልሄድንም፤ ይህን ያህል እንደሚያናድድሽ ባለመገመታችን ይቅርታ” አለ ዳኙ ሚስጥረንም በመወከል።

“ሁለተኛ ስለዚህ ጉዳይ ባናወራ ደስ ይለኛል” አለች ፍሬሕይወት።

ብዙም ሳይቆዩ ተለያዩ። ሚስጥረና ዳኙ የፍሬን ንዴት ያልጠበቁት ስለነበረ ግራ ገብቷቸዋል።

“ዳኙ በጣም ይቅርታ የኔ ጥፋት ነው” አለች ሚስጥረ ፍሬ ከሄደች በኋላ።

“የጋራ ስሚታችን እኮ ነው፤ ይቅርታ ልትጠይቂኝ አያስፈልግም” አላት ዳኙ ለማረጋጋት።

“መቼም ይሁን መቼ ምክንያቷን እንድታስረዳኝ መጠየቄ አይቀርም” አለች ሚስጥረ ከዳኙ ጋር ሲሰነባበቱ።

* * * *

የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች መመዝገቢያ የመጀመሪያ ዕለት ነው። ከሬጂስትራር መስኮት ግራና ቀኝ በረጅሙ የተዘረጋውን ሰልፍ ጨርሰው ወረፋ የደረሳቸው አስፈላጊውን ከፈጸሙ በኋላ “ግቢውን ጎብኙ” የተባሉ ይመስል በግቢው ውስጥ ይተረማመሳሉ። አብዛኞዎቹ አንድ ዓይነት ስሜት ይነበብባቸዋል፤ የስኬታማነት መንፈስ!

ፍሬሕይወት ለምዝገባው የመጣችው ብቻዋን ነው፤ ረጅሙ ሰልፍ መጨረሻ ቆመችና ወረፋዋን መጠባበቅ ጀመረች። ወረፋ እየጠበቀች በሀሳቧ ከአካባቢው ርቃ ሄዳለች። በጊቢው ውስጥ ከወዲያ ወዲህ የሚተራመሱትን ወጣቶች እያየች የተሰደዱትንና የሞቱትን፤ የምታውቃቸውንና የማታውቃቸውን ወጣቶች አስታወሰች “ትውልድ ማለት ጎርፍ ነው!” አለች ለራሷ “አዎን ያለማቋረጥ የሚፈስ ጎርፍ ነው” አለችና ደመደመች።

በሰልፉ ውስጥ ያሉትንና በጊቢው ውስጥ ወዲያና ወዲህ የሚተራመሱትን ወጣቶች በሚገባ አስተዋለችና ወጣቶቹን ለሁለት ከፈለቻቸው፤ ከምታያቸው አብዛኞዎቹ በአንድ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙና ከእርሷ ዕድሜ የሚያንሱ ናቸው፤ “እነዚህ የአዲሱ የትውልድ ጎርፍ አባላት ናቸው” አለችና ሌሎቹን ደግሞ አስተዋለች በቁጥር እንደፊተኞቹ ባይበዙም በሰልፉ ውስጥ ተሰባጥረው የሚታዩት ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፤ “እነዚህኞቹ ደግሞ ያለፈው ትውልድ ጎርፍ ቅሬቶች መሆናቸው ነው” አለች በሀሳቧ፤ አንዳንዶቹ ከእርሷ ይበልጣሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ከእርሷ እኩል ይሆናሉ፤ ያም ሆነ ይህ እራሷን ከእዚህኛው ቡድን ጋር ፈረጀች። ትምህርት ያቋረጠችባቸውን ዓመታት ቆጠረቻቸው፤ አምስት ናቸው። “አምስት አመት ቀላል ጊዜ አይደለም” አለች ለራሷ።

“አንደኛ ዓመት ናችሁ?” አላት አንድ ወጣት ወደእርሷ ጠጋ ብሎ።



“አዎ” አለችውና የየትኛው ቡድን አባል መሆኑን ወዲያውኑ ገመተች፤ የእርሷ ዕድሜ ክልል ተጋሪ ሊሆን እንደሚችል አሰበች።
እርሷ ይህንን “የኔ ቡድን” ያለችውን ትውልድ ለምን እንደተቀላቀለች ታውቀዋለች፤ “የሌሎቹስ ምን ይሆን?” አለች ደግሞ መጠየቅ በማይታክተው አእምሮዋ። እያንዳንዱን ሰው የየትኛው ዕድሜ ተጋሪ መሆኑን በመገመት አእምሮዋን ሥራ ስላስያዘችው ሰልፉ ሳይሰለቻት ነው ተራዋ የደረሳት።

ምዝገባዋን አጠናቀቀች፤ ሌሎች ልታደርጋቸው የሚገቧትን ነገሮችም ፈጸመች። ፍሬሕይወት ይህን ሁሉ ስታደርግ አንዴ እንኳን ስለወደፊት የግል ሕይወቷ አላሰበችም ሕይወቷን የምትኖረው ለራሷ መሆኑን ተቀብላ አታውቅም። ሁሌም መኖሯን የምትቀበለው ለእናቷና ለትንሹ ወንድሟ ለሮቤል ስትል ብቻ መሆኑን ነው የምታስበው። ለምዝገባ ዩኒቨርሲቲ ስትሄድ፣ መኝታ ክፍል እንዲሰጣት ስትጠይቅ፣ ትምህርት ተጀምሮ ክፍል መግባት ስትጀምር፣...ሁሉንም ያደረገችው በደመነፍስ ነው። ብቻ የእርሷን ዘመን ተጋሪዎች ባየች ቁጥር ይህን ትውልድ የመቀላቀላቸው ምክንያት ምን እንደሆነ ራሷን ሳትጠይቅ አልፋ አታውቅም።

ክፍል ስትገባ የምትቀመጠው የፊተኛው ወንበር ላይ ነው። የትምህርት አሰጣጡ ከሁለተኛ ደረጃው የትምህርት አሰጣጥ ከመለየቱ በቀር ትምህርት በፍጹም አልከበዳትም። እንዲያውም ለእርሷ አብዛኞዎቹ ኮርሶች የክለሳ ያህል ናቸው፤ በፖለቲካ ትግሉ ወቅት በፍላጎት ይወያዩባቸው የነበሩ እንደ ፍልስፍናና ፖለቲካል ኢኮኖሚ የመሳሰሉትን ትምህርቶች የእድሜና የታሪክ ተጋሪዎቿ ማስተማርም የሚችሉ ናቸው። የአዲሱ ትውልድ አባላት ግን እነዚህ ትምህርቶች አይጥሟቸውም፤ አይገቧቸውም። የሁለቱን ትውልድ ጎራ ለመለየት ተጨማሪ መመዘኛ ፈጠረላት። እናም በእነዚህ ክፍለጊዜዎች የተማሪዎቹን ተሳትፎ እየተከታተለች “ይህ የእኛ ትውልድ ነው...” እያለች መፈረጇን ተያያዘችው። እርሷ ግን በትምህርት ሂደቱ ውስጥ የመሳተፍና የመናገር መብቷን የተገፈፈች ይመስል ዝምታን መረጠች።

እንደዩኒቨርሲቲው ደንብ ማደሪያ ክፍል ቢሰጣትም ፍሬሕይወት አድራበት ስለማታውቅ የመኝታ ቤት ተጋሪዎቿን እርሷም አታውቃቸውም እነርሱም አያውቋትም። በአንድ የመኝታ ክፍል ውስጥ ስድስት ሴት ተማሪዎች መመደብ የተለመደ ነው፡፡ በክፍሉ ውስጥ አራት አልጋዎች ሲኖሩ እነርሱም የሚሰጡት ከአዲስ አበባ ውጭ ለመጡ ተማሪዎች ነው። በተጨማሪ ደግሞ ሁለት ፍራሾች ይገቡና የአዲስ አበባ ተማሪዎች ይመደባሉ።

አንድ ቀን ከክፍል ስትወጣ "ለምን የመኝታ ክፍሌን አላየውም?" አለች ለራሷ። ወደቤት መሄዱን ትታ ወደመኝታ ሕንጻ አመራች። በሩን ያንኳኳችው በቀስታ ነው፤ ተከፈተላት።

"ማንን ፈለግሽ?" አለች የከፈተችው ልጅ።

"መኝታ ክፍሌ እዚህ ነው" አለቻት።

"ፍሬሕይወት ነሽ?" ጠየቀች ልጅቱ በመገረም ዓይነት።

"አዎን ፍሬሕይወት ነኝ" አለች። ልጅቱ ፍሬሕይወት እንድታልፍ መንገድ ለቀቅ አደረገችላትና በሩን ዘግታ ወደ ውስጥ ገባች።

"እመቤት እባላለሁ ተገናኝተን አናውቅም" አለች ልጅቱ ፍራሹ ላይ ተመቻችታ እየተቀመጠች።

"አዎን ተገናኝተን አናውቅም" አለችና ፍሬሕይወት ወንበሩ ላይ ተቀመጠች።

"በፍራሽ ነው የተመደብሽው አይደል?" ሌላ ጥያቄ አስከተለች ልጅቱ።

"አዎ በፍራሽ ነው የተመደብኩት" አለቻት።

ፍሬሕይወት "የኔ ዘመን ተጋሪ" የምትለው ትውልድ አካል እንደሆነች እመቤትን ገምታታለች። "ለምን ይሆን እርሷስ እንደኔ ዘግይታ ዩኒቨርሲቲ የገባችው?" ብላ ራሷን ጠየቀች።



"እዚህ ማደር ጀምረሻል?" አለቻት እመቤትን ከጥቂት ዝምታ በኋላ።

"አዎን ጀምሬአለሁ"

"ልጆቹ ጥሩ ናቸው?"

"ምንም አይሉም" መለሰች እመቤት።

ክፍሉ ጸጥ አለ። እመቤት ከምታገላብጠው ወረቀት በስተቀር ሌላ የሚሰማ ነገር የለም፤ ፍሬሕይወት አልቆየችም፤ ወዲያውኑ ከመኝታ ክፍል ወጥታ ወደቤቷ ሄደች። በመንገዷ ላይ ስለእመቤት እያሰበች ነበር።

* * * *

ፍሬሕይወት ወጥታ ስትሄድ ዝምታቸው ፈጥሮት የነበረው ከባድ አየር ቀለል ሲል ተሰማት እመቤት። ያላገኘቻትን የመኝታ ተጋሪዋን ለማየት በጣም ጓጉታ ነበር ፤ አራቱን አልጋዎች የያዙቸው ልጆች በዕድሜ ከእርሷ ያነሱ ከመሆናቸው ባሻገር በሕይወት ተሞክሮአቸው እርሷን የሚመስሉ አይደሉም። ፍሬሕይወትን ስታያት በአንድ ነገር እርግጠኛ ሆነች፤ በእድሜ የሚቀራረቡ መሆናቸውን። እንደምንም ብላ ፍሬሕይወትን በደንብ ማወቅ እንዳለባት አሰበች፤ በደንብ ያወቀቻት ዕለት ወይ እሮይ ብላ ትቀመጣለች አለያም የመኝታ ክፍሉን ጥላ ትወጣለች።

"እስከመቼ ይሆን?" አለችና ራሷን ጠየቀች። እመቤት በስቀቀን መኖር ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል። ጊዜው እየቆየ ቢሄድም ሁሉም ነገሮች ትናንት የተደረጉ ያህል በአእምሮዋ ውስጥ ግልጽና ሕያው ናቸው። ከወንድሟ ጋር ለመኖር የመጣችበት ጊዜና ሕይወት ባላሰበችው ሁኔታ አቅጣጫውን የቀየረበት ጊዜ! ወደኋላ ብዙ ዓመታትን ቆጠረችና ከወንድሟ ጋር ለመኖር የመጣችበትን ጊዜ አስታወሰች። አቤት! ያኔ እንዴት ልጅ ነበረች።

ወንድሟ የባንክ ሠራተኛ ነበር፤ ሥራው ጥበቃ ደሞዙም ለወቅቱ ኑሮ በቂ ነበር። የእመቤት ወንድም ሩቅ አሳቢ፤ ታናናሾቹን ማስተማር

የሕይወቱ ዓቢይ ዓላማ አድርጎ የተቀበለ ሰው ነበር። በዕቅዱ መሠረት እመቤትን አብራው እንድትኖር ከቤተሰቦቿ ለይቶ አመጣት። ቤተሰቦቿም በሙሉ ፈቃደኝነት ነበር የላኳት። እመቤትና ወንድሚ ቀበና አካባቢ በተከራዩአት ትንሽ ግን ንጹህ ቤት ውስጥ ኑሮአቸውን ተያያዙት።

እመቤት በ1967 ዓ.ም ዘጠነኛ ክፍል ገባች እርሷም ወንድሚም ደስ አላቸው። አገራዊው የስርዓት ለውጥ እምብዛም ሳያሳስባቸው ሕይወት እንደወትሮው ቀጠለ። እንዲያውም ገበሬዎቹ ቤተሰቦቻቸው ባለመሬት የሚሆኑበት ጊዜ በመምጣቱ ተደስተው ነበር። ከሞላ ጎደል በተረጋጋ ሁኔታ ዓመቱ አለቀና እመቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪ ሆነች፤ በጣም ተደሰተች። ያ ዓመት ግን ወንድሚ ከቤተሰባዊ ጉዳይ ይልቅ ለፖለቲካዊ ጉዳዮች ትኩረት የሰጠበት ጊዜ ሆነ። ጓደኞቹ ሲመጡ ወሬያቸው ሁሉ ፖለቲካ ላይ አጠነጠነ፤ ከፖለቲካ ውይይት ባሻገር ሚስጥራዊነቱ የበዛ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመሩ። ወንድሚ አብዛኛውን ጊዜ እቤቱ ሳይመጣ ማደር ጀመረ።

አንድ ማታ እንደተለመደው ወንድሚ ሳይመጣ ቀረ፤ ያን ሌሊት የነበረው ተኩስ ደግሞ የተለየ ነበር፤ እመቤት በስጋት ስትናጥ አደረች። ሊነጋጋ ሲል፤ ወደ አስራአንድ ሰዓት አካባቢ የቤቱ መዝጊያ በቀስታ ተንኳኳ፤ እመቤት አፏን ወደበሩ አስጠግታ "ማነው?" አለች። የወንድሚ ድምጽ መሆኑን ለመለየት አንድ ቃል ብቻ በቂዋ ነበረ፤ በሩን በቀስታ ከፈተችለት። ወንድሚ እንደምንም ተጎትቶ ገባና ወለሉ ላይ ተዘረረ። እመቤት የምትሆነውን አጣች፤ ተብረከረከች።

"ምንድነው የሆንከው? ምንህን ነው?" እያለች ማልቀስ ብቻ እንጂ የመጀመሪያ እርዳታ እንኳን ልታደርግለት አልቻለችም። ወደውስጠኛዋ ክፍል እንዲገባ እንድታግዘው ምልክት አሳያት፤ እጁን ይዛ ልታነሳው ስትሞክር በእጁ ጨብጦት የነበረውን ጎኑን አስለቀቀችውና በደም የተበከለውን እጁን ተመለከተች። እንዳትጮህ በእጁ ምልክት ሲሰጣት ልብሷን አፏ ውስጥ ሰግስጋ ተንበረከከች።

ገርበብ ያለውን መዝጊያ ከፍተው ጓደኞቹ ተከታትለው ገቡ፤ እመቤት የማታውቀው ሌላ ሰውም አብሯቸው አለ። ከወለሉ ላይ አንስተው አልጋ ላይ አስተኙትና እንግዳው ሰው ለተመታው ጎኑ ህክምና



አደረገለት። ሁሉ ነገር የሚከናወነው በጥድፊያ ነው፤ እመቤት ፊልም የምታይ እንጂ የዕውነት እየሆነ ያለ ነገር አልመሰላት አላት። የህክምና እርዳታው ሲያልቅ በመጡበት አኳኋን እየተጣደፉ ወንድሚን ይዘውት ወጡ።

"አይዞሽ!" ሊላት ሞከረ በደከመ አንደበቱ። እመቤት ግራ በመጋባት እበሩ ላይ እንደቆመች ቀረች።

"ወንድምሽን ልታድኚው ከፈለግሽ ይህንን ለማንም መናገር የለብሽም" አላት አንደኛው ጓደኛው መለስ ብሎ። መልሷን አልጠበቀም፤ በሩጫ ወጥቶ ሄደ።

ወደረፋዱ ላይ መልዕክት ደረሳት፤ ወዲያውኑ ቤቷን ቆልፋ ሄደች። የተነገራትን ቦታ በምልክት እየፈለገች ደረሰችበት፤ በተነገራት መሰረት የውጭውን በር ሁለት ጊዜ ብቻ መታች። የወንድሚ ጓደኛ ነበር የተቀበላት፤ በተከረከመ ጽድ የተሸፈነ ጠባብ በር ከፍቶ አስገባት። በሩ ወደሚቀጥለው ጊቢ ይወስዳል፤ ጊቢው ሰው የሚኖርበት አይመስልም፤ ጋራዥ የሚመስል ነገር ተመለከተች በዚያ ውስጥ አለፉና መከደኛ የመሰለ ብረት ከፍቶ እንድትገባ ምልክት ሰጣት በጠባቡ ደረጃ በቀስታ ተከታትለው ወረዱ፤ ጭልምልም ያለ ነው። ቀደም አላትና ከበስተቀኝ በኩል ያለ መዝጊያ ከፍቶ አስገባት። ከፊትለፊቷ ወንድሚን ተኝቶ አየችው። ጠዋት ከነበረው ሁኔታ የተሻለ ይመስላል። ገና አጠገቡ ስትደርስ በእንባዋ ታጠበች።

"እሙ! እንድታለቅሽ አልፈልግም፤ ይልቅስ እንድትረጂኝ እፈልጋለሁ" አላት።

"በምችለው ሁሉ!" አለችው።

"የሚያጋጥምሽ ምንም ይሁን ምን ያየሽውንና የሆነውን ሁሉ እንዳልነበረ መቁጠር ይጠበቅብሻል፤ አለበለዚያ በእኔ ላይ ሞት እንደፈረድሽ ዕወቂ" አላት። በፍጹም ወንድሚ አልመሰላሽ አላት። እንዲህ ዓይነት ማስፈራሪያ ቀርቶ ጠንከር ያለ ንግግር ተናግሯት አያውቅም።

"በአንቺ ላይ ያለኝ እምነት የጸና ነው!" አላት ደግሞ።

"ምንድነው የማደርግልህ?" አለችው ግራ እንደተጋባች።

"እርሱ የሚልሽን ሁሉ" አላት ወደጓደኛው እያመለከታት።

"እንሂድ" አላት ጓደኛው። ለመሄድ ራመድ ካለች በኋላ ዞር ብላ ወንድሟን ተመለከተችው። "ይቅናሽ! እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ" አላት። ተመለሰችና ግንባሩን ሳመችው። ሌላ ቃል ግን አልተናገረችም።

ከጓደኛው ጋር በመጡበት መንገድ ተመልሰው ወጡ፤ ከጉድጓዱ ሲወጡ አንዲት ታክሲ ቆማ አየች። የምትወስጂውን ዕቃ እዚች መኪና ውስጥ ታገኛለሽ፤ መኪናው ሲያወርድሽ ዕቃውን በጀርባሽ ተሸክመሽ በግራ በኩል ያለውን መንገድ ተከትለሽ መስቀለኛ መንገድ እስከምታገኚ ድረስ ትሄጃለሽ። የቀኙን ቅያስ ተከትለሽ ጥቂት ስትራመጂ የሚጠብቅሽ ሰው አለ፤ የያዝሽውን ዕቃ ነካ አድርጎ "ወፍሬም ቤቱን ታውቂዋለሽ?" ይልሽና መልስ ሳይጠብቅ ይሄዳል ተከተይው፤ ዕቃውን ይቀበልሻል። ዕቃውን ከሰጠሽው በኋላ በመጣሽበት መንገድ አትመለሽም፤ ወደፊትለፊት ስትሄጂ ታክሲ መሳፈሪያ ታገኛለሽ የምታውቂውን ቦታ በሚጠራ ታክሲ ተሳፍረሽ ወደቤትሽ ተመለሽ" አላት። የተባለችውን ሁሉ አድርጋ ወደቤቷ ተመለሰች።

እመቤት ማታ ብቻዋን ኩርትት ብላ ትንሿን ቴሌቪዥን ከፍታ ብቸኝነቷን ለመርሳት ሞከረች። ልክ ስትከፍተው "ፀረ አብዮተኞች የባንክ ዘረፋ አካሄዱ..." የሚል ዜና ስትሰማ መብረቅ የመታትን ያህል ደርቃ ቀረች። ቴሌቪዥኑን የዘጋችው ሳታስበው ነው፤ ዝርዝሩን ሳትሰማው አመለጣት፤ ባትሰማውም ግድ የላትም፤ በዘረፋው ውስጥ እርሷም አለችበት። ያደረሰችው ዕቃ ምን እንደሆነ እርግጠኛ ሆነች። የወንድሟ አባባል በጆሮዎቿ አስተጋባ፤

"የሚያጋጥምሽ ምንም ይሁን ምን ያየሽውንና የሆነውን ሁሉ እንዳልነበረ መቁጠር ይጠበቅብሻል፤ አለበለዚያ በእኔ ላይ ሞት እንደፈረድሽ ዕወቂ" ነበር ያላት።



እንቅልፍ በዐይኗ ሳይዞር ሌሊቱ ተጋመሰ። መገላበጥ ብቻ፤ ሀሳብና ጭንቀ ብቻ... ምን ታድርግ፤ የሆነውን ነገር ለቤተሰቦቿ መንገር ይጠበቅባት ይሆን? በፍጹም! ወንድሟ የሆነውን ሁሉ እንዳልነበረ እንድትቆጥረው ነግሯታል።

የቤቱ በር በሃይል ተመታ፤ ያለችበት እስኪጠፋት ድረስ ደነገጠች። ተደገመ። "አቤት" አለችና ተነሳች። በሩን ከፈተችው፤ በርከት ያሉ ሰዎች አልፈዋት ገቡ፤ ከቆመችበት አልተንቀሳቀሰችም።

"የት ነው የሄደው?" ብሎ አንባረቀባት አንደኛው።

"ሥራ" አለች ፍርጥም ብላ።

ሳታስበው በሰደፉ ትከሻዋን መታት አንደኛው። ሌሎቹ ቤቱን ዝብርቅርቁን አወጡት፤ ምንም ነገር አላገኙም፤ ተናደዱ። ሌላው በሰደፉ ደገማት። "ቅደሚ" አላት ሌላው፤ አንድም ቃል ሳትተነፍስ ቀደመች።

"ቤቱን ትቆልፍ" አለ አንዱ፤ ተመልሳ እንድትቆልፍ ፈቀዱላት። እያዳፉ መኪና ውስጥ አስገቧት፤ ወዴት እንደተወሰደች አላወቀችም። እንደደረሰች የተፈጠረችበትን ቀን እስከምትረግም ድረስ ተገረፈች፤ እርሷም በአቋሟ ጸናች፤ "ምንም አላውቅም ብላ ችክክ አለች"።

በሚቀጥለው ቀን እንደገና ተጠራች፤ የምርመራ ክፍል በረንዳ ላይ እያለች አንድ ሰው ወደአጠገቧ መጣና "ማንም የለም፤ አንቺም ምንም አታውቂም" አላት። በግልምጫ አነሳችው በፍጥነት ትቷት ሄደ። ምርምራ ክፍል ስትገባ የቀረበላት ጥያቄ የትናንትናው ነው። "ወንድምሽ የት ነው? የዘረፈውን ገንዘብ የት አደረገው?" አሏት።

የእርሷም መልስ ያው ነው "ምንም አላውቅም" ብቻ። እንዳልነበረች አድርገው እንደገና ገረፏት። የፈላ ዘይት እግሮቿ ላይ ደፉባት፤ እመቤት ግን "አላውቅም" ብላ ድርቅ አለች ። ምርር ሲላት ተናግራ እፎይ ማለት ያምራታል፤ ግን ወንድሟስ? እርሱ ከሚሞትባት እርሷ ስቃዩን ብትቋቋም መረጠች። እናም የወረደባትን መከራ ሁሉ ችላ በአቋሟ ጸናች፤ ወንድሟን ለማዳን።

ምግብና ተቀያሪ ልብስ ማን እንደሚያመጣላት አታውቅም። በየቀኑ ሳህን እንድትቀበል ትጠራና እርሷ ቁስለኛ በመሆኗ ወጥታ መቀበል ስለማትችል ጠባቂዎቹ ያመጡላታል። እግሮቿ ክፉኛ ተጎድተዋል፤ በዘይት የተጠበሰ ቆዳቸው ያመረቅዛል፤ ህመሙ አይጣል ነው። እዛ ውስጥ ያሉ እስረኞች ግን በጣም ጥሩዎች ናቸው፤ ይንከባከቧታል፤ ያስታምሟታል። መድሀኒት እንዲገባላት በመፈቀዱ ስቃይዋን ቀንሶላታል። ስጋት ቀንሶላታል፤ ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ወደእዛ ምርመራ ክፍል ተጠርታ አታውቅም።

እግሯ ጠገግ ካለላት በኋላ አንድ ቀን ምግቧን ማን እንደሚያመጣላት ለማወቅ ጓጉታ ስሟ ሲጠራ ወጣች። የሆነ ሰው ከሩቅ ሆኖ እጁን አውለበለበላት፤ ማን እንደሆነ አላወቀችም፤ እርሷም እጇን አውለበለበች። የሆነ ምልክት አሳየት፤ ብዙም አልገባትም። ሳህንና ልብስ ተቀብላ ተመለሰች። ምግብ ገለበጠችና ሳህኑን መለሰች። ሰውየውን ስላላወቀችው እያደር ግራ ይገባታል፤ ማን ይሆን እንዲህ በቋሚነት የሚጠይቃት?

ሌላ ጊዜም እንዲሁ የመጣላትን ምግብ ለመቀበል ስትወጣ ያመጣውን ሰው ለማወቅ ጥረት አደረገች። በፍጹም ልታውቀው አልቻለችም። ከሳህኑ ጋር አዲስ ቱታም ተልኮላታል። ምግቡን ገልብጣ ሰጠችና ወደክፍሏ ተመለሰች፤ ወደቤት ልትገባ ስትል ያ አንድ ቀን የሆነ ነገር ሹክ ያላት ሰው ጠራት፤ የሆነ ነገር በምልክት ሊነግራት እንደፈለገ ተመለከተች፤ ሊነግራት የፈለገው ነገር የገባት መሰላት። እክፍሏ እንደገባች የገባትን ነገር ሞከረችው። ትክክል ነበረች በቱታው ጃኬት የእጅ እጥፋት ውስጥ የሆነ ወረቀት መኖሩን አወቀች። ጃኬቱን አጣጥፋ አስቀመጠችው፤ ሁኔታው ተመችቷት አውጥታ እስከምትመለከተው ድረስ።

ጃኬቱን መጸዳጃ ቤት ስትሄድ ለበሰችውና በቀላሉ ወረቀቱን አወጣችው። አመቺ ጊዜ ስታገኝ አነበበችው፤ በሕይወቷ ሙሉ እንደዛን ዕለት ተደስታ አታውቅም። የወንድሟ እጅ ጽሑፍ ነው፤ "በስቃይሽ አዝኛለሁ፤ በአንቺነትሽ ግን ኮርቻለሁ። ዛሬ በሕይወት ለመኖሬ ምክንያቷ አንቺ ነሽ። ማን ያውቃል? አንድ ቀን በአካል ተገናኝተን እናወራው ይሆናል። ለአሁኑ ግን በጥንካሬሽ ነፃ የምትሆኝበት ቀን ቀርቧል፤ ወዳጆችንን እመኝው" ይላል። ምን ለማለት እንደፈለገ የገባት መሰላት፤ "ወዳጆችን" ማለት ያ አንዳንድ መልዕክት ሊያስተላልፍልኝ የሚሞክር ሰው መሆን አለበት" አለች ለራሷ።

ከእመቤት ጉዳይ ጋር በተገናኘ ብቅ ያለ ሰው የለም፤ "ምናልባት" ተብሎ እንድትቆይ ተደረገ፤ ግን ማንም አልመጣም። ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ ተፈታች፤ በተፈታችበት ዕለት ያ አንዳንድ ነገሮችን ሊያስተላልፍላት የሚሞክር ሰውዬ ጠጋ ብሎ ስልክ እንደሚደውልላት ነገራት። በሶስተኛው ቀን ደወለላትና ቀጠራት። ከሰውየው ጋር ተገናኙ፤ አዲስ ነገሮች ሲከሰቱ እንደሚያሳውቃትና መልዕክቱ ከእርሱ መሆኑን የምታውቅበትን ኮድ ነገራት።

"መዘናጋት የለብሽም፤ ሁልጊዜ በጥንቃቄ ኑሪ" አላት ሲለያዩ።

እግሮቿን ለመታከም የተለያዩ ሀኪሞችን ብታይም የእግሮቿ ጠባሳዎች የሚድኑ አልሆኑም። ጠባሳ ከተበተባቸው እግሮቿ ጋር እስከሕይወቷ ፍጻሜ መኖር እንደሚኖርባት አመነች።

ከእስር ቤት የወጣችው በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ በመሆኑ ጊዜ ሳታባክን ትምህርት ቤት ለመግባት ወሰነች። ከትምህርት በፊት ግን ቤተሰቦቿን አይታ መምጣት ነበረባትና ሄደች። ወላጆቿ ወንድሟ ያለበትን ትክክለኛ ቦታ ባያቁም በሕይወት መኖሩን እንደገለፀላቸው ነገሯት፤ በጣም ተደሰተች።

አስራሁለተኛ ክፍል ሳያዳግታት አለፈችና ዩኒቨርሲቲ ገባች፤ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ ከፍሬሕይወት አገናኛት።

* * * *

ዳኙ ፈቃደ ፍሬሕይወትን እንዲረሳት ነገረው። ፈቃደም መተዉን አረጋገጠለት። በልቡ ግን የፍሬሕይወት ሁኔታ እልህ ውስጥ አስገብቶታል። ብዙ ቀን ደውሎላት እንደማይመቻት እየነገረችው ሳይገናኙ ቀርተዋል።

"ዛሬ ለመጨረሻ ጊዜ እደውልላታለሁ፤ የተለመደውን መልስ ከሰጠችኝ ግን... " አለና ከራሱ ጋር ተማከረ። እንደመከረው ደወለላት።

ስልኩ ሲነሳ ግን ልቡ መታበት፣ የፈራውን "አልችልም" እንዳይሰማና በንዴት ያልሆነ ነገር እንዳይናገራት ፈራ። ስልኩ ተነሳ፣ ያነሳችው ደግሞ ራሷ ነች። "ሄሎ" አለች ፍሬሕይወት።

"እሺ የጠፉ ሰው! እንዴት ነሽ?" አላት ቀለል አድርጎ።

"እኔ እንኳን አልጠፋሁም" አለችው እርሷም ቀለል አድርጋ።

"ዛሬ አልችልም የሚል መልስ መስማት አልጠብቅም። የለመድነውም ፊት ለፊት ተገናኝቶ ማመን ወይ ማሳመን እንጂ መሸሽ አይደለም" አላት።

ከወዲያኛው መስመር መልስ አልተሰጠም፣ ፍሬሕይወት ዝም አለች። ያልጠበቀችው እንደሆነባት ገመተ። "ሄሎ! እየሰማሽኝ ነው?" አለ ፈቃደ።

"እየሰማሁህ ነው ግን የተረዳኸኝ አልመሰለኝም" አለችው በተከፋ ድምጽ።

"እንድረዳሽ እኮ ነው ተገናኝተን እናውራ የምልሽ፣ አንቺ ለምንድነው ከኔ ጋር ለመገናኘት የጠላሽው?" አሁምን ጠንከር ባለ አነጋገር።

"እሺ መቼ እንገናኝ" አለችው ፍሬሕይወት።

"ብትችይ አሁንም ቢሆን በጣም ደስ ይለኛል"

"የት?" አለችና አስድነገጠችው።

ሀራምቤ ሆቴል ቀጠራት፣ ገብታ እንደማታውቅ ነገረችውና ውጭ እንደሚጠብቃት ነገራት። ሆቴሉ ጸጥ ያለ መሆኑና የወንበሮቹ አቀማመጥ ለጥንዶች ግላዊ ጨዋታ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑ ስለሚሰማው ነው እዚያ እንዲገናኙ የፈለገው።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ እንደምትድርስ ነገረችው፣ የፈቃደ ልብ በደስታ መታች፣ መደሰቱን ግን እንድታውቅበት ማድረግ እንደሌለበት አሰበ።



ወዲያውኑ ነው ሀራምቤ የደረሰው፣ እዚያው አካባቢ ጠበቃት። እርሷም በሰዓቱ ነው የደረሰችው፣ ከሩቅ ሲጠብቃት ቆይቶ አንድ ደቂቃም ሳያሳልፍ አጠገቧ ደረሰ። ሰላምታቸው ሞቅ ያለ ነበር፣ ተሳሳሙ።

ፈቃደ ጨዋታውን ሁሉ ወዳለፈ ሕይወታቸው ወሰደው፣ በዚያ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ በመሳተፉ፣ ለትግሉ ሕይወትን እስከመስጠት ድረስ መስዋእትነትን ለመክፈል በመወሰኑ፣ በመታሠሩና በመሰቃየቱ ዛሬም የሚሰማውን ኩራት ነገራት። ያ ሁሉ መስዋዕትነት ግን ፍሬ ሳይሰጥ በመቅረቱ ግን ልቡ ሁሌም እንዳዘነ እንደሚቆይ አወራላት።

"በእርግጥ እኔ ዕድለኛ ነበርኩ ማለት እችላለሁ፣ አብረውኝ ከነበሩት አብዛኞዎቹ በሕይወት መኖርና ያለመኖራቸውን ባላውቅም በእስር ቤት እያለሁ አልመጡም። እናም ይሄው ለመውጣት በቃሁ" አላትና ትካዜ ይዞት ጭልጥ አለ።

ፍሬሕይወትም ሳታስበው የልቧን ስሜት ሁሉ አጫወተችው፣ አዳመጣት። ማዳመጥም ብቻ አይደለም አደነቃት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያያት የነበረውን ግምት ትክክለኛነት ማረጋገጡን ነገራት።

ቀስ እያለ ደግሞ ከትግል ሕይወት ወደማህበራዊ ሕይወት ወሰዳት። ስለቤተሰቡ ነገራት፣ የእህቱን አሟሟትና ከዛ ተከትሎ በቤተሰባቸው ላይ የደረሰውን ቤተሰባዊ ምስቅልቅል አጫወታትና ሳያስበው መንፈሱን ሀዘን ተጫጫነው። ስሜቱ የጋራ መሆኑን ለመንገር አላመነታችም፣ ስለእርሷም ቤተሰብ ነገረችው፣ ግን ያው ነው የተካፈሉት አሳዛኙን ቤተሰባዊ ገጽታ ነው። ሁለቱም በዝምታ ተሸበቡ።

ይህን የሀዘን ድባብ የቀየረው ፈቃደ ነው። ስለዩኒቨርሲቲ ጠየቃትና ብዙም እንደማይጥማት ነገረችው። እርሱም ስላለፈ የዩኒቨርሲቲ ሕይወቱ ነገራት፣ ሦስተኛ ዓመት ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ሳያጠናቅቅ እንደታሰረና ብዙዎቹ ጓደኞቹ በሕይወት ያለመኖራቸውንና ዩኒቨርሲቲ ገብቶ መማርንም እንደማይሞክረው፣ ከእስር ቤት ከወጣ በኋላ አነስተኛ የግል ሥራ መጀመሩን ነገራት።

ሰዓቱ ሄዷል ፍሬሕይወት ድንገት ሰዓቷን ስትመለከት አየች፤ አስራሁለት ሰዓት ሆኗል።

"አይገርምም?" አለችው።

"መሸ አይደል?" አለና ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰው።

"ብንሄድ አይሻልም?" አለችው ለመነሳት እየተዘጋጀች።

ፈቃደ አስተናጋጁን ጠራና ሂሳብ ከፍሎ ለመውጣት ዝግጁ ሆነ። የሀራምቤ ሆቴልን ደረጃዎች ሲወርዱ ሁለቱም በየራሳቸው ሀሳብ ተውጠው ነበር።

"ወዴት ነሽ?" አላት ከሆቴሉ ሲወጡ።

"ገብርኤል ሰፈር" አለችው ሳታስበው።

"ለምን አልሸኝሽም ታዲያ፤ ቅርብ ናት" አላትና መራመድ ጀመረ። ተከተለችው።

ፍልውሀን አልፈው የኢዮቤልዩ ቤተመንግስትን ዳገት ሲወጡ ብዙም አላወሩም። ፈቃደ የፍሬሕይወትን ትከሻ ማቀፍ ተመኘ፤ ግን ፈራ። መልካም ቁይታቸውን ድንገት የሚያደፈርስ ሁኔታ እንዳይፈጠር እየሰጋና ሰረቅ አድርጎ እየተመለከታት በቀስታ እርምጃ ተጓዘ። ውስጡ ደስ ብሎታል የፍሬሕይወት ስሜት መለሳለሱንና አስቸጋሪ እንደሆነች እንደማትቀጥል ቁይታቸው ነግሮታል። ባነሷቸው ጨዋታዎች ሁሉ ደስ ብሏት ዘና ብላ መቆየቷ የዚህ ሁሉ ምልክት መሆኑን ተቀብሏል።

ፍሬሕይወትን ቀስ ብሎ ተመለከታት፤ ከሀሳቧ ጋር ሙግት የያዘች መሰለችው። ሃሳን እያሰበች እንደሆነ መገመት አላቃተውም፤ ግን ምንም ሊላት አልፈለገም፤ የቤት ሥራ ይዞ መሄዱን ፈልጎታል።

"ወዴት ሄድሽ?" አላት ፈቃደ።



"የትም" አለችው ድንግጥ ብላ።

መናፈሻውን ተሻግረው በሂልተን ሆቴል አጠገብ ሽቅብ ወደገብርኤል እየወጡ ነበሩ። የሂልተንን በር አልፈው አጥሩን ሲጨርሱ ቆም አለችና "ይበቃሃል" አለችው።

"ቤትሽ ቅርብ ነው?" አላት ድንገተኛ ስንብቷ ያልጠበቀው ሆኖበት።

"በዚች ገባ ብሎ ነው" አለችው በሂልተን አጥር ጥግ ወደቀኝ የምታስገባውን ኮረኮንች መንገድ እያመላከተችው።

"ሩቅ ከሆነ ግን ልሸኝሽ" አላት እጁን ለስንብት እየዘረጋ።

"በፍጹም" አለች ፍርጥም ብላ።

ጨበጣትና ቆየት አለ "አብረን በመቆየታችን ደስ ብሎኛል" አላትና ጉንጪን ሳታስበው ሳማት። ድንጋጤ ቢያይባትም ንዴት አልነበራትም።

ሁለት ሰዓት ሲሆን ደወለላትና "ደህና መግባትሽን ለማወቅ ነው" አላት።

"ደህና ገብቻለሁ፤ በጣም አመሰግናለሁ" አለችው። ድምጿ የመደናገር ስሜት አለው።

* * * *

ሚስጥረ የጀመረችው ሥራ በጣም ተስማምቷታል፤ ታታሪ ሠራተኝነቷም ቀጣሪዎቿን አስደስቷል። ቦታው መሀል ከተማ መሆኑ ደግሞ ከብዙዎች ጋር እንድትገናኝ አድርጓታል፤ እንዲያውም ለብዙዎቹም መገናኛ ሆኖአል። ሦስት ራዴቨን የእስር ቤት ሰዎች የቀጠሮ ቦታ ሆነ። አንዳንዴ ሁሉም ለየግል ጉዳዩ ይመጣና ለስብሰባ የተገናኙ እስኪመስል ድረስ ቁጥራቸው ይበረክታል። ደግነቱ ማንነታቸውንና የት እንደሚተዋወቁ ሌሎች ሰዎች ያለመረዳታቸው ነው። ውስጥ አዋቂ ቢያጋጥም ግን እንደገና ወደእስር ሊከታቸው ይችላል።

ሚስጥረ ለአፍታ ሳታርፍ ነው የምትውለው፤ ሰላምታ ስትሰጥ ስታስተናግድ፣ ስታጸዳ ያላት ቅልጥፍና ተገልጋዩንም ባለቤቶቹንም ያረካቸዋል። ከራንዴቩ ባለቤቶች ስለሚስጥረ የሚሰጠው አስተያየት ፈቃደ እንዲኮራባት አድርጎታል። ተገልጋዩ የሚሰጠው ጉርሻ ከምን ጊዜውም በላይ በመሆኑ አብረዋት የሚሠሩት አስተናጋጆችም የደስታው ተካፋይ ሆነዋል።

ፈቃደ ሚስጥረን ሊያናግራት ሲፈልግ በስንት ሰዓት እንደሚመጣ ያውቀዋል፤ እርሷም የሚመጣበትን ሰዓት ተመልክታ ፈቃደ ለምን እንደመጣ ይገባታል።

“ስሚ ጉዳዩ እኮ በድል ተጠናቀቀ” አላት አንድ ቀን በተለመደው ሰዓት መጥቶ። ወንበር ሳብ አደረገችና ተቀመጠች ሚስጥረ።

“አታደርገውም!” አለችው ገጽታዋ በፈገግታ እየበራ።
“ሆኗል ተደርጓል” አላት ደረቱን ነፋ አድርጎ።

“እንኳን ደስ ያለህ” አለችው ከተቀመጠችበት ተነስታ እየሳመችው።

ከስራ ስትወጣ ለፍሬ ደወለችላት፤ ፍሬ ራሷ እንድትነግራት ስለፈለገች በቶሎ አላነሳችባትም። እንደጠበቀችውም ፍሬ ቀድማት አነሳችው።

“እቤት የምትገቢበትን ሰዓት እየጠበቅሁ ነበር” አለች ፍሬ ከሰላምታ በኋላ።

“ምነው በደህና?” አለች ሚስጥረ ምን እንደሆነ ቢገባትም።

“ራንዴቩ መጥቼ እንዳልነግርሽ ድፍረት አጥቼ ነዋ!” አለች ፍሬ ዳር ዳር በማለት።

“አቦ ሆዴን አታስጨኚው ምንድነው የምትነግሪኝ” አለች ሚስጥረ ሳቋ እየመጣባት።
“እንደማትቀየሚኝ ቃል ግቢልኝና” አለች ፍሬ።



“ምነው እንዲህ ያገር ጉዳይ አደረግሽው” አለች አሁንም ሚስጥረ ሳቋ እያስታወቀባት።

“እንዲያውም ሰምተሽዋል መሰለኝ፤ አንቺ ጋ ሳይደርስ እንደማያድር አውቀዋለሁ” አለች ፍሬም ሳቋ እየመጣባት።

“ለማንኛውም ደስ ብሎኛል” አለቻት በመጨረሻ።

“አመሰግናለሁ ሚስጥረ፤ ለዚህ እኮ ነው የምወድሽ” አለቻት ደስታዋን ድምጿ እያሳበቀ።

“እንዴት እንደምወድሽ ታውቂ የለም ፍርዬ፤ በጣም ደስ ብሎኛል። ፈቃደ ጥሩ ሰው ነው” አለች ሚስጥረም።

“ያንቺስ ይሁን ዳኙን ግን እንዴት አድርጌ ነው ይቅርታ የምጠይቀው?” አለች ፍሬ ወዲያውኑ የድምጿ ቅላጼ እየተለወጠ።

“እኔ እያለሁልሽ? አትጨነቂ ይደውልልሻል” አለቻት።

የፍሬን ስልክ ዘግታ ወደዳኙ ደወለች ሚስጥረ። “መልካም ዜና ልነግርህ ነው” አለችው ገና ስልኩን አንስቶ እርሱ መሆኑን ስታረጋግጥ።

“ዜናው ቀድሞ ደርሶኝ ቢሆንስ?” አላት እየሳቀ።

“ፈቃደ ተደስቷል ማለት ነው! ላንተም ነገረህ?” አለችው ሚስጥረ እየገረማት።

“ስሚ እንጂ በአማላጅነት መከራዬን ሳይ ሰንብቼ ባይነግረኝ እኮ ነው መግረም ያለበት” አላት ዳኙ።

“እኔ መቼም በጣም ደስ ብሎኛል” አለችው ሚስጥረ።

“ማለቱን እኔም ደስ ብሎኛል፤ ግን የእኛ ነገር እየገረመኝ ነበር” አለ ዳኙ ድምጹን ዘለግ አድርጎ።

"ምኑ ነው የገረመህ?" አለችው ሚስጥረ አባባሉ ስላልገባት። "ራሳችንን በአማጭነት ብቻ መመደባችን ነዋ!" አላት።

"አልገባኝም!" አለች ሚስጥረ ግራ መጋባቷ እየስታወቀ።

"ስንገናኝ እነግርሻለሁ፤ ግን ከሞኝ ደጅ መፈር ይቆረጣል እንዳይሆንብኝ ሰግቻለሁ" አላት

ምን ለማለት እንደፈለገ የተረዳች መሰላትና ደነገጠች። ድንጋጤዋን እንዲያውቅባት አልፈለገችም። "ስንገናኝ ታስረዳኛለህ፤ ለፍሬ ግን ትደውልላታለህ አይደል? እንዴት አድርጋ ይቅርታ እንደምትጠይቅህ ግራ ገብቷታል" አለችው።

"እደውልላታለሁ፤ ባይሆን እርሷም አማላጅነት በመሄድ ውለታዋን እንድትከፍል ሊጠበቅባት ይችላል" አላት። ሚስጥረ አሁንም ደነገጠች። ግን ምንም አልመለሰችም።

"አመሰግናለሁ ዳኙ፤ እንዴት እንደማሳምንህ ለእኔም ከብዶኝ ነበር" አለችው፤ የዚያን ዕለት የፍሬን ንዴትና የዳኙን ድንጋጤ አስታውሳ።

"አትጨነቂ አሁኑኑ እደውልላታለሁ" አላት።

ስልኩን ከዘጋች በኋላ የዳኙን አባባሎች እንደገና አውጠነጠነቻቸው። በፍጹም ወደልቦናዋ መጥቶ የማያውቅ ነገር ነው፤ በጭራሽ ስለፍቅር አስባ አታውቅም።

"አሁንስ ቢሆን?" አለች ደንገጥ ብላ። ዳኙን በጥሩ ሰውነቱ ታከብረዋለች፤ ትወደዋለችም ግን በፍጹም ለፍቅር ልታስበው አይገባትም። ምናልባትም በዕድሜ እኩያ ሊሆኑ ይችላሉ። "ይሄ እንኳን ቀላል ነው" አለች ደግሞ። "ግን እኔ ገና ፊደል የምቆጥር፤ ከመሀይምነት ያልወጣሁ..." ሀሳቡን ከአእምሮዋ ልታወጣው ሞከረች። "የታሪክ አጋጣሚ አገናኝቶን ጓደኛቸው ብሆን ይህንን ማሰብ አለብኝ እንዴ?" አለችና ራሷን ጠየቀች። በራሷም ተናደደች።



ሀሳቡ በየደቂቃው ወደአእምሮዋ እየመጣ ቢያስቸግራትም ለመርሳት ሞከረችና ተኛች። ጠዋት በተለመደው ሰዓት ሥራዋ ስትገባ ትኩረቷን ሁሉ የሚቆጣጠረው ሥራዋ ሁሉን አስረሳት።

ዳኙ ባልተለመደ ሰዓት መጣ፤ ስታየው ደነገጠች። ሰላምታቸው የወትሮው ቢሆንም ሚስጥረ ስሜቷን ታዘበችው።

"ዛሬ ከሰዓት ሥራ የለሽም አይደል?" አላት ዳኙ።

"አዎ የለኝም" አለችው

"ምሳ አብረን እንበላለን" አላት ሳያቅማማ።

"ደስ ይለኛል" አለች ሚስጥረም ሳታመነታ።

"የዛሬ ምሳችን ፊንፊኔ አዳራሽ እንዲሆን እፈልጋለሁ" አላት፤ ከገጽታው ላይ ልዩ ስሜት ተመለከተች።

"እኔ እንዲህ ዓይነት ቦታ ገብቼ አላውቅም ዳኙ፤ እፈራለሁ" አለችው።

"አዲሱ ፍልውሀ በር ላይ እንገናኝና አብረን እንገባለን" አላትና ነገሩን አቀለለው።

ዳኙ ከሄደ በኋላ ከአእምሮዋ ሳታወጣው ነው የቆየችው፤ ባሰበችው ቁጥር ልቢ እንደመረበሽ እያለባት ነው የዋለችው። ልክ ስድስት ሰዓት ሲሆን ተረኛ ሠራተኞች ሲገቡ ሥራዋን አስረከበችና የሥራ ልብሷን ቀያየረች። ከሥላሴ ራንዴቩ ፍልውሀ ያለው መንገድ ታክሲ አያስፈልገውም፤ በእግርም ቢሆን አስር ደቂቃም አይወስድም። ሰዓቷን ተመለከተች፤ ሀያ ደቂቃ አላት። በቀስታ መራመድ ጀመረች፤ በእርምጃዋ ልክ ልቧም ትመታለች። በጣም ገረማት እስር ቤት ሆነው ለንቃት ከተመደቡበት ጊዜ ጀምሮ ነው ከዳኙ ጋር የተግባቡት። ከእስር ከተፈቱ፡ በኋላም ዘወትር ይገናኛሉ፤ አንድም ቀን ግን እንዲህ ዓይነት ስሜት ተሰምቷት አያውቅም።

ዳኙን ከሩቅ አየችው፤ እንዲህ ለብሶ በፍጹም አይታው አታውቅም፤ የበለጠ ግራ ገባት። የለበሰው ሙሉ ልብስ ሙሽራ አስመስሎታል፤ የምታውቀው ዳኙ አልመሰላሽ አላት። ከሩቅ ሲያያት ደግሞ ፈገግታው ልዩ ሆነ፤ እርሷ ወደእርሱ እየሄደች እርሱም ወደእርሷ መጣ። ቀረብ ሲል እጆቹን ዘረጋላት፤ ሳይገናኙ ብዙ የቆዩ ይመስል ሰላምታው የጠበቀ ነበር። ሌላም ጊዜ እንዲህ ተቃቅፈው ሰላም ተባብለው ያውቃሉ፤ ሚስጥረን ግን እንዲህ ዓይነት ስሜት ተሰምቷት አያውቅም።

ተያይዘው ወደፊንፊኔ አዳራሽ ገቡ፤ ከጥግ በኩል ቦታ ያዙና ተቀመጡ። የዳኙ ፈገግታ ከገጽታው ላይ አልጠፋም፤ ሚስጥረም በዐይኗ ሙሉ ልታየው መድፈር አቃታት። ዳኙ ስሜቷን እንዳያውቅባት ሰግታ ከራሷ ጋር ታገለች። "እስኪ የፈለገኝ በፍጹም ለማይገናኝ ጉዳይ ቢሆንስ?" አለችና ራሷን ጠየቀች።

አስተናጋጁ የሚጠጡትን ከፍቶላቸው ተመልሶ ሄደ። "ምንን በማስመልከት እንደሆነ ቢነገረኝ" አለችው ዳኙን ለራሷም በገረማት ድፍረት።

"ድንገት ከእንቅልፉ የሚነቃ ሰው አጋጥሞሽ ያውቃል?" አላት።

"አዎ ያውቃል" አለችው።

"እኔም ልክ እንደዛ ሆንኩ፤ ድንገት ስነቃ ደነገጥኩ፤ እናም መቸኮል ነበረብኝ። ጊዜ ማጓተት እንደማያስፈልገኝና እቅጬን ማወቅ እንዳለብኝ አወቅሁ፤ እናም ተጣድፌ አጣደፍኩሽ" አላት።

ካወቀችው ጊዜ አንስቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዐይኖቹ ውስጥ ፍቅር ማንበብ ቻለች። ያሰበችው ትክክል ነበር ማለት ነው። የምትመልስለት ግን አልነበራትምና አቀርቅራ ዝም አለች።

"ይህ አባባሌ ለሚስጥረ አልገባትም ለማለት በፍጹም አልደፍርም" አላት ዝምታዋን ለመስበር።

"ገብቶኛል ግን ትክክል አልመሰለኝ አለኝ" አለችው።



"ምኑ ነው ትክክል አልመሰለሽ ያለሽ ሚስጥረ?" አላት ዳኙ ለመስማት እየቸኮለ።

"እኔኮ' አጋጣሚ ከእናንተ ያገናኘኝ ሰው ነኝ፤ ምንም ያልተማርኩ መሀይም..." ዳኙ አቋረጣት።
"በቃሽ ሚስጥረ ከዚህ በላይ እንድትናገሪ አልፈቅድልሽም፤ ከማንም በላይ መስዋዕትነት ስትከፍይ ያለመማርሽ መች አገደሽ? እሱን እርሺው፤ ለመሆኑ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ልትቀድሚን እንደምትችይስ አስበሽው ታውቂያለሽ? አሁን አንድ ነገር ብቻ ነው እንድትነግሪኝ የምፈልገው። ትወጂኛለሽ?" አላት።

ቀና ብላ ተመለከተችው፤ ዐይኖቿና ገጽታዋ ባጠቃላይ መልስ ሰጡት። "ለፍቅራችን!" አላት ለስላሳ የተቀዳበትን ብርጭቆ አንስቶ፤ እርሷም ብርጭቆዋን አነሳች።

ምሳቸውን እየተጎራረሱ በሉ፤ ብዙ ጊዜ አብረው በልተው ተጎራርሰው ያውቃሉ የዛሬው ስሜት ግን ልዩ ነው።

"ግን ድንገት እንድታስበው ያደረገህን ምክንያት ልትነግረኝ ትችላለህ?" አለችው ሚስጥረ።

"መንስኤዎቹ ስለፈቃደ ጉዳይ ከፍሬ ጋር በተነጋገርንበት ቀን የተጠቀምሽባቸው ቃላት ናቸው። ዱሮም እንደምወድሽ ታውቂያለሽ፡ መውደዴ ግን ከወንድምነት የመነጨ ነበረ። ያን ዕለት ግን ስለፍቅር ያለሽን አመለካከት አሳየኝ፤ እናም በልዩ ዐይን እንዳይሽ አደረገኝ" አላት ዳኙ።

"ታዲያ ምን አጣደፈህ አትይኝም?" አላት ዝም ስትለው።

"እሺ ምን አጣደፈህ?" አለችው እየሳቀች።

"ፈቃደ ፍሬሕይወት "እሺ" እንዳለችው ሲነግረኝ ስለእንቺ የተሰማኝን አዲስ ስሜት ስነግርው የሰጠኝ መልስ ነው ያባነነኝ" አላት።

"ምን አለህ?" አለችው እርሷም ለመስማት እየቸኮለች።

"እኔ አንተን ብሆን አንድ ቀን እንኳን አላድርም፤ አንዱ ቀድሞህስ እንደሆን ምን ታውቃለህ? ያለችበት ቦታ ከስንት ሰውጋር እንደሚያገናኛት አታውቅም?' አለና አስደነገጠኝ፤ ከዚያ እንቅልፍ አጣሁ" አላት ዳኙ።

* * * *

እመቤትና ፍሬ ቀስ በቀስ ተግባቡ ስሜታቸው ተጣጣመ፤ ቢሆንም ያለፈ ሕይወታቸውን ስንክሳር አልተገላለጡም። አንዳቸው ስለሌላዋ የማወቅ ፍላጎት ቢኖራቸውም አልተጠያየቁም። ፍሬ ወደተመደበችበት መኝታ ክፍል አዘውትራ በመሄዱም ሌሎቹን የመኝታ ክፍሉን አባላት ተዋወቀቻቸው ሁሉም በእድሜ ታናናሾቿ ናቸው፡፡ የዕድሜያቸው ልዩነት ግን ተግባብተው ከመኖር አላገዳቸውም። ከመግባባታቸው የተነሳም ሁለቱ የመኝታ ክፍሉ አባላት ተዳብለው አንድ አልጋ ላይ ለመተኛት ተስማምተው ለፍሬና ለእመቤት አንደኛውን አልጋ ለቀቁላቸው። ከዛ በኋላ ፍራሾቻቸው የሁሉም የጥናት ቦታዎች ሆኑ።

አንድ ቀን ፍሬ ወደ ዶርም ስትሄድ መከፈቻው የሚቀመጥበት ቦታ ላይ አልነበረም፤ የከፍላቸውን በር ጠምዘዝ አደረገችው በሩ ተከፈተላትና ዘው አለች። ፍሬና እመቤት ተፋጠጡ፤ እመቤት በጣም ደነገጠች፤ ልብሷን አውልቃ ልትቀይር ስትል ነው የገባችባት።

"ወይኔ! በሩን አልቆለፍኩትም?" አለች እመቤት እንደደነገጠች።

"ደግነቱ እኔ ነኝ" አለቻት። እመቤት መልስ ሳትመልስላት ልብሷን በፍጥነት ለበሰች።

"ከእንግዲህማ መጨነቅ አያስፈልግሽም" አለች ፍሬ ጭንቀቷን ልታቀልላት በማሰብ።

"ለምኑ" አለች እመቤት እንዳልገባት በመሆን።

"ስለእግሮችሽ" አለቻት በቀላሉ፤ እንደገና ደነገጠች። ፍሬ ግምቷ ትክክል በመሆኑ ደስ ብሏታል፤ "ከእንግዲህ ድብብቆሹ ይበቃናል" አለቻት መልሳ። በጣም የሚያማምሩት የእመቤት እግሮች በጠባሳ ተሸፍነዋል "ስለእግሮችሽ በጣም አዝናለሁ" አለች ሳታስበው።



"ሕይወታቸውንስ የከፈሉት? መቼም ጠባሳ ከሕይወት አይበልጥም አይደል?" አለች እመቤት። ፍሬሕይወት በመስማማት አንገቷን ነቀነቀች።

"በጣም እድለኛ ነኝ" አለች እመቤት ከጥቂት ዝምታ በኋላ።

"ዕድለኞች ነን" አለች ፍሬ ራሷንም ጨምራ።

ጓደኝነታቸው እየደረ ጠነከረ፡፡ ለብዙዎች እስከሚደንቅ ለጓደኝነት ምሳሌ እስከሚሆን ድረስ ተዋደዱ። ፍሬ እመቤትን ከእናቷና ከወንድሟ ጋር አስተዋወቀቻት፤ በጣም ተግባቡ። ቀስ በቀስ ሕይወት መነቃቃት ጀመረና ፍሬና እመቤት የልቦቻቸውን ድብቅ ሚስጥሮች ማውራት ጀመሩ፡፡ ያልተቋጨትን የፍቅር ጅምሮቻቸውን ሁሉ ተጨዋወቱ።

እመቤት ከዩኒቨርሲቲ ውጭ ብዙ ቦታ መሄድ አትወድም፡፡ በዛ ቢል እነፍሬ ቤት ደርሳ ብትመጣ ነው። ፍሬም "ለምን?" ብሎ አጠንክሮ የመጠየቅ ልምድ የላትም።

ከእመቤት ጋር የተማሩት ለአንድ ሴሚስተር ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ሴሚስተር ፈተና በተፈተኑ በሳምንቱ ፍሬሕይወት ወደቤት ስትሄድ እመቤት ዘመድ ጠይቃ እንደምትመጣ ነግራት ሄደች። ማታ ስትመጣ ፊቷ ሁሉ ተቀያይሮ ጥቁርቁር ብላ ተመለሰች።

"ምነው ምን ሆንሽ?" አለች ፍሬ ገና ስትገባ።

"ፍርዬ! ጉድ መጣልሽ"

"የምን ጉድ እሙ?" ልቧ የጠረጠረው ነገር እንዳይሆን ሰጋች።

"ሰምቼ መጣ!" አለቻት። እነማን እንደሆኑ ስለገባት መጠየቅ አላስፈለጋትም።

"ታዲያ ምን ይሻላል?"

"መሄድ! መጥፋት ብቻ!" አለች እመቤት ማዶ ማዶ እያየች።

"እዚህ ሆኖ ማሳለፍ አይቻልም?"

"አይሆንም ፍርዬ! እነዚህ እግሮቼ እንዲህ እስኪሆኑ ድረስ በፈላ ዘይት የተጠባበሱት፣ ወገቤን የተሰበርኩት...የን ሁሉ ስቃይ የተቀበልኩት ለራሴ ስል ሳይሆን የወንድሜንና የጓደኞቹን ሕይወት ለመታደግ ስል ነበር። እንዳቸውም ሳይመጡ በመቅረታቸው ነበር ከእስር ቤት ልወጣ የቻልኩት። ፍርዬ! ተመልሼ ያንን ስቃይ መቀበል፣ ወደወህኒ መወርወርና ለማንም የማይጠቅም የሕይወት መስዋዕትነት መክፈል አልፈልግም" አለች እመቤት የእስር ቤቱ ስቃይ ትዝታ እያንገፈገፋት።

"ያገኘሽው መረጃ ግን የተረጋገጠ ነው?"

"አዎ ፍርዬ ከታመነ ምንጭ ነው የተነገረኝ። አንደኛው የወንድሜ ጓደኛ በአሁኑ ሰዓት ያለው ቤተመንግሥት ነው። ሌላው ደግሞ በቅርብ ቀን እንደሚመጣ ይጠበቃል። የሚቀረው የኔ ወንድም ብቻ ነው፤ እርሱን ለማግኘት ዋና መንገዳቸው ደግሞ እኔን መያዝ ነው። የኔ ዳፋ ወደአንቺም እንዳይደርስ ግን አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጌያለሁ፡፡ ትምህርት ቤት ሲከፈት ለተወሰኑ ቀናት ዶርም ላለማደር ሞክሪ" አለቻት።

ፍሬሕይወት ነገሩ የማያወላዳ መሆኑ ገባት "መቼ አሰብሽ ታዲያ?" አለቻት በትካዜ።

"በጣም መፍጠን አለብኝ ፍርዬ! ነገ በሌሊት እሄዳለሁ"

እንባዋ ሳታስበው መፍሰስ ጀመረ፡፡ እመቤትን ማጣት ሞት መስሎ ታያት፡፡ በፍጹም ልታጣት አትፈልግም።

"በሕይወት መለያየት አይሻልም ፍርዬ?" ጠንካራ ጥያቄ ነበር። በእመቤት ድምጽ ውስጥ የድሮው ወኔ ይሰማል፡፡



ቀስ ብለው ሁኔታውን ለፍሬ እናት ነገሯቸው፡፡ እናቷ በጣም ደነገጡ፤ ስቅስቅ ብለውም አለቀሱ። "ተስፋ አድርጌ ነበር፡፡ ልጄ እህት አገኘች ብዬ ተደስቼ ነበር፡፡ የወደፊት ሕይወታችሁ እንኳ ተስፋ የሚጣልበት ይሆናል ብዬ ነበር" አሉ በስቅስቅታቸው ውስጥ።

ፍሬሕይወት እንደምንም ራሷን አበረታትታ የሁለተኛ ሴሚስተርን ትምህርት ጀመረች። ብቸኝነቱን ግን መቋቋም አቃታት፡፡ በእመቤት ተሞልቶ የነበረው መንፈስ ባዶ ሆነባት። ክፍል ብቻዋን፣ ምግብ ቤት ብቻዋን፣ ላይብረሪ ብቻዋን፣... ብቸኝነት ትምህርቷን ሊያስተዋት ሆነ። ግን እናቷን እያሰበቻቸው እርሳቸውን ለማስደሰት ብቻ ትምህርት ቤት ትመላለሳለች።

* * * *

ወይዘሮ ስርጉት የጤናቸው ሁኔታ እየከፋ መሄዱ ውስጣቸውን ባዳመጡ ቁጥር ይሰማቸዋል። ሕይወት ባይጥማቸውም መኖር ግን ይፈልጋሉ፤ ለፍሬሕይወት ሲሉ ሕይወታቸው እንዲቆይ ይመኛሉ። እርሷ ደህና ከሆነች የሮቤልን ነገር በእርሷ ላይ ሊጥሉት ይችላሉ።

"አምላኬ ሆይ ይህች ልጅ አንድ ደረጃ ላይ እስከትደርስ እድሜ ስጠኝ" ብለው ይጸልያሉ ሁልጊዜም።

አንዳንድ ጊዜ ድንገት ሁሉ ነገሯ ተቀያይሮ ሐዘን የሚወራትን፣ ዝምታ የሚውጣትንና እንባዋ የሚቀርባትን ልጃቸውን ሲመለከቷት ሕይወትን የመጋፈጥ አቅሟ ስለሚያሳስባቸው መኖራቸው በጣም እንደሚያስፈልጋት ይረዳሉ።

ሮቤል ገና ልጅ ነው፤ የቤተሰብ ድጋፍ ያስፈልገዋል። ከፍሬሕይወት ጋር ተቀምጠው ሲጫወቱም ሆነ ስለትምህርት ሲነጋገሩ ማየት ለወይዘሮ ስርጉት ተስፋቸው ነው።

"ፍሬ ካለች ሮቤል ምንም አይሆንም" ይላሉ ሲያዳምጧቸው ይቆዩና።

"አንተ የኔ ገብርኤል እባክህን ይህችን ልጅ ጠብቅልኝ" ይላሉ በሆዳቸው የፍሬሕይወትን ድንገተኛ ትካዜና ተስፋ መቁረጥ ሲያስቡት።

ከቀኑ ውስጥ ብዙውን ሰዓት የሚያሳልፉት ተኝተው ነው፤ የልጆቹ ከትምህርት ቤት መምጫ ሰዓት ሲደርስ ግን ከመኝታቸው ይነሳሉ እንዳይጨነቁ ለማድረግ። የበላይሁን እናት የወይዘሮ ስርጉት ጤንነት ያሳስባቸዋል፤ ይጨነቃሉም። ብዙ ጊዜም ሀኪም ቤት እንዲሄዱ መከረዋቸዋል።

"ከእንግዲህ ምን ሊፈይድልኝ ብለው ነው የበላይ እናት፤ ይልቅስ ይጸልዩልኝ እንዲሁ ሆኜ ለእነዚህ ልጆች ጥቂት እንድቆይ እግዚአብሔር እንዲረዳኝ" ይሏቸዋል።

"እግዚአብሔር ራሱ መጥቶ አያድንሽ፤ መቼስ ሀኪሞቹን መፍጠሩ በእነርሱ በኩል እንዲፈውሰን አይደል? እባክሽን እሺ በይኝና እንሂድ" ብለው ሲጨቀጭቋቸው አንድ ቀን አብረው ወደሆስፒታል ሄዱ።

ወይዘሮ ስርጉትን የመረመራቸው ሀኪም "ምንዎት ናቸው?" አላቸው ወይዘሮ ስርጉት ሲወጡ የበላይሁንን እናት አስጠርቶ።

"ኧረ ዝምድናስ የለንም፤ ግን ጉርብትናችን ከዝምድና በላይ ነው" አሉት።

"ተስፋ የሚጣልበት ሁኔታ የላቸውም፤ እቤት ውስጥ በተቻለ አቅም እንክብካቤ ቢያገኙ መልካም ነው። ለህመም ማስታገሻ የሚሆን መድሀኒት አዝገናላቸዋለሁ" አላቸው ገጽታው ላይ ሀዘን እየተነበበ።

"ተስፋ የላትም እያልከኝ ነው ዶክተር?" አሉ ደንግጠው።

"እንደዛ ሳይሆን ህመማቸው በቶሎ የሚድን አይደለም" ለማለት ነው" አለ ሲያጽናናቸው።

ከሆስፒታል ሲወጡ ወይዘሮ ስርጉት በውስጣቸው የነበረችው ትንሽ ተስፋ ሙጥጥ አለችባቸው። የበላይሁን እናትም የሚያጽናኑበት አቅም አልነበራቸውም። በትካዜ እንደተዋጡ ወደቤታቸው ተመለሱ።

የፍሬሕይወት እናት ልጆቻቸውን ባዩ ቁጥር እንባቸውን መቆጣጠር እያቃታቸው ተቸገሩ። እናም ሁል ጊዜ መሸፋፈንና መተኛት



መረጡ። ልጆቹ ደግሞ ተሸፋፍነው መተኛታቸውን አይወዱትም። አሁንም አሁንም ይጠሯቸዋል።

አንድ ቀን ፍሬሕይወት እቤት ስትውል "እሰኪ ባንክ ቤት እንሂድ" አሏት።

"ለምን?" አለቻቸው ደንገጥ ብላ።

"እንግዲህ እንደልቤ መሄድ እያቃተኝ..." የጀመሩትን መጨረስ አልቻሉም፤ እንባቸውን መቆጣጠር አቃታቸውና ተሸፋፈኑ።

"እማ ምንድነው? አመመሽ?..." የምትጠይቃቸው ጠፋት። የተሸፋፈኑበትን ልብስ እንደምንም ገልጣ ተመለከተቻቸው። የእናቷ እንባ የተደፋ ውሀ ይመስል በጉንጮቻቸው ላይ ተንቆረቆረ። ፍሬሕይወት አብራቸው ማልቀስ ጀመረች። የሚከለክል በሌለበት ሁለቱም አለቀሱ፤ ምርር ያለ ለቅሶ ነበር።

"በይ በቃሽ፤ እንዲያው ለምን ተነካሁ ብዬ አንቺንም አስለቀስኩሽ" አሉና ከአልጋው ለመውረድ ሞከሩ። ጥርሳቸውን ነክሰው እንዳላቃታቸው ሊያሳዩዋት ሞከሩ። ደገፈቻቸው።

"እማ ብዙ ስለተኛሽ እኮ ነው የሚደክምሽ፤ ትንሽ ትንሽ መንቀሳቀስ ያስፈልግሻል" አለቻቸው እንባዋን እየጠራረገች።

"የግድ ግን ዛሬ መሄድ አለብሽ?" አለቻቸው ደግሞ ድካማቸው አሳስቧት።

"አዎ ፍሬ መሄድ አለብኝ፤ እየባሰ እንጂ እየተሻለ አይሄድም" አሏት ያሉበትን ሁኔታ ሊያስረዷት ፈልገው።

"እማ ተስፋ አትቁረጭ እንጂ፤ መድሀኒትሽን በደንብ ከወሰድሽ ይሻልሻል" አለቻቸው።

ባንክ ቤት ሄደው ገንዘቡ በሙሉ እንዲወጣ ሲነግሯት ደነገጠች "እማ ለምንሽ ነው?" አለቻቸው።

"ግዴለሽም መልሰን እናስገባዋለን" አሏት። የተወሰነ ገንዘብ ብቻ አስቀርተው ሁሉንም በፍሬሕይወት ሥም አስገቡት። ፍሬሕይወት ተረበሸች። ከባንክ ቤት ሲመለሱ ምንም አላወራችም፤ ውስጧ እንደተጨነቀና የእናቷም አዝማሚያ እንዳሳሰባት ነው እቤት የገቡት።

"እንግዲህ ፍሬ አደራሽን ትንሽም ብትሆን ትጠቅማችኋለችና የሮቢን ነገር የምተወው ላንቺ ነው" አሏት እቤት ገብተው አልጋቸው ላይ አረፍ ሲሉ።

ፍሬሕይወት እንባዋን መቆጣጠር አቃታት፤ ስቅስቅታዋ ቤቱን ሞላው። አልጋው አጠገብ በርከክ ብላ ራሷን ደረታቸው ላይ አስደግፋ አለቀሰች፤ እራሷን በደከመ እጃቸው እየደባበሱ አባበሏት። የራሳቸውን የውስጥ ስሜት ለመቆጣጠር እየታገሉ አባበሏት፤ መጭውን ጊዜ እያሰቡ ከራሳቸው ይልቅ ለእርሷ እየዘኑ ተጨነቁላት።

* * * *

ተማሪዎቹ የሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ መምህር እስኪገቡ ድረስ ፀሐይ ለመሞቅ በየቦታው ቆመው ይጨዋወታሉ። ታረቀኝ ከአንዱ ቡድን ጋር ተቀላቅሎ ከጨዋታው በመቋደስ ላይ ሳለ ድንገት ዐይኖቹ ራቅ ብላ ከቆመች ተማሪ ላይ አረፉበት። በአካል ከቡድኑ ጋር ቢሆንም በሀሳቡ ግን ተለይቷቸዋል። ልጅቱ የምዝገባ ጊዜ ከፊቱ ተሰልፋ የነበረች ልጅ ነች።

በጣም ትገርመዋለች፤ አንዳንዴ በጣም ተጫዋች ሌላ ጊዜ ደግሞ እጅግ ኩስታራ ትመስለዋለች። በአንደኛው ሴሚስተር በፍጹም የማትለየት ጓደኛ ነበረቻት፤ ከጓደኛዋ ጋር የተማማሉ እስኪመስሉ ድረስ አንዳቸውን ያለአንዳቸው ማግኘት የማይታሰብ ነበር። አንዳንዴ በተመስጦ ሲያወሩ ለተመለከታቸው በከፍተኛ የሀገር ጉዳይ ላይ የሚነጋገሩ ይመስላሉ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሳቃቸው የሌሎቹን ተማሪዎች ሁሉ ቀልብ እስከሚገዛ ድረስ ረጅምና ነፃ ይሆናል። ግርም ይሉታል ታረቀኝን። ታረቀኝ ስማቸውን ለማወቅ ጊዜ አልወሰደበትም ፍሬሕይወትንና እመቤትን ለይቶ ያውቃቸዋል።

ፍሬሕይወትና እመቤት ለምንም ነገር ደንታ ያላቸው አይመስሉትም፤ ተማሪው የፊት ወንበሮችን ለመያዝ በክፍል በር ላይ ሲታገል እነርሱ



ዳር ቆመው ይመለከታሉ። ተማሪው ሁሉ ገብቶ ከተቀመጠ በኋላ ገብተው መጨረሻው ወንበር ላይ ይቀመጣሉ። አንዳንዴ ክፍልም ላይገቡ ይችላሉ፤ የመጀመሪያዎቹ የክፍል ፈተናዎች በተሰጡበት ጊዜ ተማሪ ሁሉ በጥያቄና መልስ መከራውን ሲያይ እነርሱ ግን የሚታዘቡ ይመስሉ ነበር። ሁኔታቸው ትቢተኛ ስለሚያስመስላቸው አንዳንዴ ታረቀኝን ያናድዱትና "ምን ይለጥጣቸዋል?" ይላል ለራሱ። ቢሆንም ዐይኖቹን ከሚስቡት ተማሪዎች መሀል ሊያወጣቸው አልቻለም።

አንደኛ ሴሚስተር አልቆ፤ በገና የሚሸኙት ተሸኝተው የፈተና ውጤታቸው ትምህርታቸውን ለመቀጠል ያስቻላቸው ሁሉ ተመልሰዋል። ታረቀኝ በሁለተኛው ሴሚስተር እመቤት ያለመመለሷን ከሁሉ ሰው ቀድሞ ነው ያስተዋለው። ፍሬሕይወት ሌላ ጓደኛ ለመያዝ ሙከራም አላደረገችም፤ በብቸኝነቷ ገፋችበት። ክፍል መግባትና መውጣት አንዳንዴ ምግብ ቤት ገብታ ለብቻዋ መመገብ ከዚያ ደግሞ ላይብረሪ መግባት ብቻ። አንዳንዴ በሀሳብ ጭልጥ ብላ መሄዷን በሚገባ ተመልክቷል።

በጣም በተወሰኑ አጋጣሚዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ስትነጋገር አስተውሏታል፤ ምንም ዓይነት ዐይንአፋርነት አላየባትም፤ በሚገባ ትጫወታለች። አካሄዷ ራሱ ልበሙሉነቷን ይናገራል፤ ከአንገቷ ቀና ብላና ራሷን ከፍ አድርጋ በእርጋታ ስትራመድ በራስ መተማመኗን የሚመሰክር ይመስላል። ግርም ይለዋል ታረቀኝን "ጓደኛዋ የት ሄደች? የገና ተመራቂ ሆና ይሆን?" ይላል ለራሱ ብቻዋን ባየት ቁጥር።

ብቻዋን ሲያያት እያደር እያሳዘነችው ተቸገረ። አንዳች ነገር እንዲያስብላት ያደርገዋል፤ በተለይ በየክፍለጊዜው መሀል ብቻዋን ስትሆን አብሯት መሆን ያሰኘዋል። ግን ስለእርሷ የሚያውቀው አንዳቸም ነገር ስለሌለው ይፈራል። በጣም አልፎ አልፎ ከምትቀላቀላቸው ልጆች መረጃ ማግኘት ፈለገና አብሯቸው መሆን አዘወተረ። በወሬ መሀል አንዳንድ ጥያቄዎችን ጣል በማድረግ የተወሰነ መረጃ አገኘ። "አይገርምህም፤ ስታያት ትቢተኛ ቢጤ ትመስላለች እንጂ እንዴት ምስኪን መሰለችህ። ደግሞ በትምህርት እንዴት ጎበዝ እንደሆነች ብታይ፤ የማዕረግ ተማሪ እንደሆነች

ታውቃለህ?" አለችው አንደኛዋ ልጅ። መረጃው የበለጠ ሊየውቃት የመፈለግ ስሜቱን አበረታበት።

ታረቀኝ ደህና ገቢ ያላቸውና የተደላደለ የሚባል ኑሮ ከሚኖሩ ቤተሰቦች የተወለደ የቦሌ ልጅ ነው። ቦሌ የኑሮ መለኪያ ነው፤ ማንነታቸውን መደበቅ የሚፈልጉ የድሀ ልጆችም ሰፈራቸው ቦሌ መሆኑን መናገራቸው የተለመደ ነው። ታረቀኝ ግን ሰፈሩ ብቻ ሳይሆን አለባበሱና ሰውነቱ የኑሮ ሁኔታውን የሚመሰክሩለት ልጅ ነው። የሚቆጠርለት መልክ ባይኖረውም ጎረድረድ ያለ ወንዳወንድ መልኩ ከመካከለኛ ቁመቱ ጋር ሲታይ የሴቶችን ቀልብ የሚስብ ነው። በተለይም የተጠቀለለ የሚመስለው ጥቁር ዞማ ፀጉሩን የማትመኝ ሴት የለችም። ከሁሉም በላይ ግን በፀባይ የታደለ መሆኑ የሴቶችን ልብ በአንድ ጊዜ ያሸንፍለታል። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ በዙሪያው የሚያሰልፋቸው ሴቶች በርካቶች ነበሩ።

ቤተሰቦቹ ዕድገት በሕብረት እንዳይዘምት ወዲያወዲህ ብለው አመቻችተውለት እንጂ ዘመቻ መሄድ ነበረበት። ዘመቻ አለመሄዱን በደስታ ነበር የተቀበለው፤ እናም ጓደኞቹን ሸኝቶ እርሱ አዲስ አበባ ቀረ። በመቅረቱም ሥራ አልፈታም፤ አባቱ በአንድ ትልቅ መሥሪያ ቤት ሥራ እንዲያገኝ አደረጉ።

ጓደኞቹ ከዘመቻ ሲመለሱ በናፍቆት ነው የተቀበላቸው፤ በብዙዎቹ ላይ ያስተዋለባቸው ለውጥ ታዲያ ዘመቻ ባለመሄዱ እንዲቆጭ አድርጎታል። መልካም ባህሪው ረድቶት ለውጣቸውን ለመጋራትና መንገዳቸውን ለመቀላቀል ጊዜ አልወሰደበትም። ጓደኞቹ የሚሆኑትን ሆኖና የሚያደርጉትን አድርጎ ከትግሉ መሀል ገብቷል።

ታረቀኝ የህይወት መንገዳቸው በአጭሩ ካልተቀጨባቸው ወጣቶች አንዱ ቢሆንም ያለፉት ጥቂት ዓመታት መንፈሱን ጎደሎ የሚያደርጉበት በርካታ ነገሮችን ትተውበት አልፈዋል። የሚወዳቸው ጓደኞቹ ለሞትና ለስደት ተዳርገውበታል፤ እንደነፍሱ ይቆጥራት የነበረች ፍቅረኛውንም መስዋዕትነት ተቀብሏል። እናም ሰው ሲተክዝና ብቸኝነት ሲያበዛ ይጨንቀዋል። ፍሬሕይወትንም ከሀሊናው ሊያወጣት አልቻለም፤ እንዲያውም እንደምንም ብሎ ሊተዋወቃት ወሰነና ጊዜና ሁኔታ ይጠባበቅ ጀመረ።



ልደት አዳራሽ ከጓደኞቹ ጋር ምሳ ሲበላ ፍሬሕይወትን በርቀት አያት። መቼም ሁልጊዜም አበላሏ አያስደስተውም፤ ስትበላ ምግብ የምትመገብ ሳይሆን የሆነ ነገር የምትልቅም ነው የምትመስለው። ፍሬሕይወት በዚያን ቀን ከሰዓት በኋላ ላይብረሪ መግባት ፈልጋ ስለነበረ ነው ወደቤት ሳትሄድ የቀረችው። ላይብረሪ ከመግባቷ በፊት ምሳ ለመብላት ወደአዳራሽ መግባት ነበረባት፡፡ ምሳዋን ተሰልፋ ብትወስድም፤ ልደት አዳራሽ በተማሪ ቢሞላም ለእርሷ ግን ብቸኝነቷን አልቀነሰላትም። ምሳዋን ለመብላት ተቀመጠች፤ ምግቡ ግን አስጠላት። የዩኒቨርሲቲ ምግብ እንኳንስ ለከፋው ለማንም ያስጠላል "የዩኒቨርሲቲ ምግብ ማባያው ጨዋታ ነው" ይባል የለ። ዳቦውን እንደነገሩ መቆነጣጠር እንደጀመረች ምግብ ቤቱ ውስጥ አገልግሎት ከሚሰጡት ልጆች አንዱ መጣና "በዚህ ብይ ተብለሻል" ብሎ ሹካ ሰጣት።

"ማነው ያለኝ" አለችው ቀና ብላ።

ልጁን በእጁ አመለከታት። ካሳየት ልጅ ጋር ንግግር ባይኖራቸውም በዐይን ይተዋወቃሉ። በአንገቷ ምስጋና አቀረበች። ልጁ ከምግብ ቤት ስትወጣ ውጪ ጠበቃት።

"ታረቀኝ እባላለሁ" አላት እበር ላይ ጠብቋት።

"ፍሬሕይወት..." ብላ ስሟን ለማስተዋወቅ ስትሞክር፤

"አውቀዋለሁ" አላት "ብቸኝነትሽ ስላስጨነቀኝ ነው የምተዋወቅሽ" አለ ቀጠል አድርጎ።

"አመሰግናለሁ፤ ግን ብቸኛ መሆኔን በምን አወቅህ?" አለችው።

"ስለራሴ የማውቀውን ያህል ስላንቺ የማውቅ ይመስለኛል" አላት በእርግጠኝነት።

"ያጋነንከው አይመስልህም?" አለችው ትንሽ በስጨት በማለት።

"ከመሰለሽ..." እንጠልጥሎ ተወው። ለማንኛውም ፍሬና ታረቀኝ ከዛን ቀን በኋላ እየተቀራረቡ ሄዱ።

* * * *

የሴሚስተሩ ትምህርት ገና በደንብ ሳይጀመር የወይዘሮ ስርጉት ጤንነት ማጣት እየተባባሰ ሄደ፡፡ በስንት ልመና እንደገና ሆስፒታል ለመሄድ ፈቃደኛ ሆኑ። ሀኪሞቹ ቀስፋ እንደሌላቸው ነገሩዋቸውና ወደቤት መለሷቸው። ፍሬ አንድ ሳምንት ያህል ክፍል ሳትገባ ቀረችና በሁለተኛው ሳምንት የበላይሁን እናት አላስቀምጥ ሲሏት ሄደች።

ትምህርት ቤት ስትሄድ ለምን እንደቀረች የጠየቃት የመጀመሪያው ሰው ታረቀኝ ነው፤ ነገረችው፤ በጣም አዘነ። ክፍል ገብታ ትምህርት መከታተል አልቻለችም ወዲያውኑ ወደቤት ተመለሰች። ወደቤት ስትመለስ ታረቀኝ ለማንኛውም ስልክ እንድትሰጠው ጠየቃት።

ታረቀኝ በየሰስቱ ቀኑ ይደውላል፡፡ ችግሯን ለአስተማሪዎቿ እንደነገረላት ነገራትና እንዳትጨነቅ መከራት። አመሰገነችው። ብዙም ሳይቆዩ እናቷ ሞቱ፡፡ እርሳቸው ሲሞቱ ሰማይ መሬቱ ተደፋባት። ትንሹን ሮቤልን የሚያጽናና ኃይል አልተገኘም። ባየችው ቁጥር ከማልቀስ ያለፈ ልታደርግለት ተሳናት። በአጋጣሚ እናቷ በሞቱ ሰሞን ፈቃደ አዲስ አበባ አልነበረም፤ ከአስራአምስት ቀናት በኋላ ከሄደበት ሲመለስ ከሚስጥረ ጋር ቤት መጣ።

ታረቀኝ በለቅሶው ሰሞን ተመላልሶ አስተዛዘናት። በተለይም ከሮቤል ጋር ልዩ ግንኙነት ፈጠሩና ለሁሉ ሰው ያሸነፈው ሮቤል በመጠኑ መረጋጋት ቻለ፣ ታረቀኝ ባለውለታቸው ሆነ፡፡ ፀባዩም ቢሆን የሚወደድ ሆኖ አገኘችው፡፡ ለስለስ ያለና ግልጽ ነው። በቀላሉ ተግባቡ፤ ቤተኛነታቸው ጠነከረ።

እናቷ ከታመሙ ጀምሮ ከርቸሌ ሄዳ አታውቅም፡፡ ጓደኞቿ እንድትሄድ ሲጠይቋት ብዙም አላንገራገረችም፤ ፈቃደም ተጨምሮ ተሰባስበው ሄዱ። እርሷ ከርቸሌ ሄዳ ታረቀኝ ቤት መጥቶ ሲያጣት መልዕክት ትተውላት ከሮቤል ጋር ፊልም መግባታቸውን አወቀች። ደስ አላት።



ታረቀኝና ሮቤል ከፊልም ሲመለሱ ቤት አገኙዋት። ከርቸሌ ማንን ልትጠይቅ እንደሄደች ሮቤል ነግሮት ታረቀኝ ስለፍሬ ማንነት ከሞላ ጎደል አውቋል። ቀስ በቀስ ከታረቀኝ ጋር ከአንድ ወንዝ የተቀዱ መሆናቸውን ተዋወቁ። ከእርሷ ጋር ተመሳሳይ የኋላ ታሪክ ላላቸው ሰዎች ደግሞ ልዩ ግምት አላት።

ታረቀኝ ትምህርቷን መከታተል እንድትችል በጣም አገዛት። ለሮቤል ስለምታስፈልገው ሙሉ ለሙሉ ከአዳሪነት ወደተመላላሽነት ተቀየረች፡፡ ዶርም ያሉ ዕቃዎቿን ጠቅልላ ቤቷ ገባች። በእናቷ ህመምና ሃዘን ያመለጣትን ትምህርት ታረቀኝ እያስረዳት ከተማሪዎቹ ጋር እኩል መራመድ በመቻሏ ተደሰተች። አንዳንዴ በትምህርት መሀል ስለሌሎች ጉዳዮች አንስተው መጫወትም ጀመሩ።

ፍሬ ጓደኝነትን የምታይበት ልዩ መነጽር አላት፡፡ ጓደኛ ማለት ለእርሷ የሚስጥር ተካፋይ ማለት ነው። ከሚስጥሮቿ አንዱ ደግሞ የፍቅር ሕይወቷ ነው። ለታረቀኝ አንድም ሳትደብቀው አጫውታዋለች፤ ስለአንተነህ እንባ እየተናነቃት አውርታለታለች፤ አሁን ደግሞ ከፈቃደ ጋር ስለጀመረችው ፍቅር ስሜቷን ሳትደብቅ ትነግረዋለች፡፡ ቀስ በቀስ ለአንተነህ ያላትን ስሜት በማንነቷ ውስጥ አርቃ ደብቃው ፈቃደን የቱን ያህል እንደምትወደው፣ እንደምትናፍቅ...ምንም ሳይቀራት ታጫውተዋለች።

ጓደኝነታቸው በጣም እየጠነከረ በሄደ መጠን ግንኙነታቸው አቅጣጫውን እንዳይስት ስጋት ሲያድርባት የበለጠ ስለፈቃደ ማውራቷን ቀጠለች። እርሷ የበለጠ ግልጽ በሆነች መጠን ግን ለታረቀኝ ጎልቶ የሚታየው የእርሷ ስብዕና እንጂ ለፈቃደ ያላት ፍቅር አልሆነም። እናም ታረቀኝ በልቡ ፍቅር ቋጠረ፡፡ ሊደብቀው፣ ሊያምቀው ቢሞክርም አሸነፈው እቅጩን ነገራት።

"እንዴት ይሆናል ታረቀኝ! እየነገርኩህ!" አለችው።

"ፊልጌ ይመስልሻል?" ነበር መልሱ።

እርሷም ብትሆን ታረቀኝን በጣም ትወደዋለች። እንዲያውም ሁለት ሰዎችን በአንድ ጊዜ ማፍቀር እንደሚቻል የተገነዘበችበት አጋጣሚ

መሰላት። ቢሆንም "ፍቅር ውሳኔ ነው" የሚል ፍልስፍናዋን ታምንበታለች፡፡ እያንዳንዱ ሰው የተለያዩ ባህሪያት አሉት፤ በሁሉም አንፃር መልካም የሚሆን ሰው ይኖራል ብላ አትገምትም፡፡ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚደነቅ ሰው በሌሎች ደግሞ ደካማ ሊሆን ይችላል። እናም አንድን ሰው በተወሰኑት ባህሪያት ሌላውን ደግሞ በሌሎቹ ማፍቀር ይቻላል ታዲያ የፍቅር ውሳኔነት የሚመጣው እዚህ ላይ ነው።

የፍቅር ውሳኔነትና የግለሰብ ጠንካራነት የሚለካው በዚሁ ነው ብላ ታምናለች። ሆኖም በተመለከተቻችው ውሱን ባህሪያት አንድ ጊዜ ያፈቀረችውን ፈቃደን ...ያን አሮጌ ጃኬቱን እስከአንገቱ ቆልፎና ግንባሩን ኮስትሮ የታሰረበትን ሰንሰለት እያቅጨለጨለ "አይዞሽ" ያላትን ፈቃደን በሌላ ላትለውጠው ወሰነች፡፡ ለእርሷ የፍቅር ትርጉም ይሄው ነው፡፡ ለራስ የገቡትን ቃል ሳያፈርሱ በጽናት መኖር። እናም ለታረቀኝ የፍቅር ማመልከቻ ጀርባዋን ሰጠች።

ያም ሆነ ይህ ጊዜ ቀመሩን አይስትም፤ በዚሁ ሁኔታ ሁለተኛው ሴሚስተር ተጠናቀቀ። ዕድሜ ለታረቀኝ ውጤቷ አመርቂ ባይሆንም ጥሩ የሚባል ሆነ። ውጤታቸውን አይተው ሲመለሱ "እንዴት አድርጌ ላመስግንህ ታረቀኝ?" አለችው ፍሬ።

"ለምኑ?" አላት

"እዚህ ግቢ መቆየት የቻልኩት ባንተ መሆኑን አጥተኸው ነው?" አለችው ዐይን ዐዓይኑን እየተመለከተች።

"ምን ያደርጋል ውለታ መመለስ አታውቂበት" አላት ትኩር ብሎ እየተመለከታት።

"ውለታ መመለስ ባለመቻሌ የሚቀርብኝ እኔ መሆኔንም አውቀዋለሁ" አለችው ደግሞ።

"ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?" አለ ታረቀኝ እያሾፈች መስሎት።



"የእውነቴን ነው ፍቅር የመርህ ጥያቄና የውስኔ ጉዳይ ባይሆን ኖሮ ያንተ ለመሆን አላመነታም ነበር" አለችው በቀላሉ። "ያንተ በምትሆነው ልጅ ሳላውቃት እንደምቀናባት ብታውቅ ምን ትላለህ" አለችው።

ታረቀኝ የፍሬሕይወት ነገር አንዳንዴ ግራ ይገባዋል፤ የተሰማትን መደበቅ የለ፤ ሚስጥር የሚባል ቃል በመዝገበ ቃላቷ ውስጥ ያለ እስከማይመስለው ድረስ ግልጽነቷ ይገርመዋል። የምታወራለት ደግሞ ድንገትና በቀላሉ ነው።

"ግን ሰዎች እንዴት ጨካኞች ነን?" አለችው ስለአንተነህ የነገረችው ቀን።

"በምን?" አለ ታረቀኝ።

"አሁን እኔ ከአንተነህ ሌላ ሰው መውደድ ነበረብኝ?" አለችው ራሷን እየወቀሰች።

ፍሬሕይወት ስሜቷን ሳትገልጽ በፍጹም አታልፍም፤ "ታረቀኝ ጉዴ ፈላ" አለችው አንድ ቀን ደግሞ ከክፍል አካባቢ እግንቡ ላይ እንደተቀመጡ።

"ምነው ምን አጋጠመሽ?" አላት።

"እንቅልፍ ሳይወስደኝ እኮ ነው የማድረው" አለችው በማስተዛዘን።

"ለምን?" አላት።

"ለፈቃደ ያለኝ ፍቅር እየባሰብኝ ሳይሆን አይቀርም" አለችው።

"ያላችሁት አብራችሁ ማፍቀርሽ ምን ያስጨንቃል?" በግዴለሽነት መለሰላት።

"እኔ እንጃ፤ ብቻ ለደቂቃ እንኳ ባንለያይ እፈልጋለሁ" አለችው ስሜቷን ለማጋራት እየጣረች። ብሽቅ አለ ታረቀኝ።

"ታዲያ መፍትሄው ቀላል አይደለም እንዴ? መጋባት ይቻላል" እንደተናደደ መለሰላት።

"የሞትክ እንዲህ ዓይነት ምክር ጠይቄሃለሁ?" አለችው።

"በቃ ሌላ ጨዋታ አምጭ" አላት ታረቀኝ፣ ሁልጊዜም በፈቃደ ይቀናበታል፣ እንደፍርዬ ዓይነት ፍቅረኛ በማግኘቱ የታደለ ሰው መሆኑን እያሰበ።

* * * *

1976 ዓ.ም.፣ ግንቦት ወር ዕለቱ ቅዳሜ ከረፋዱ አምስት ሰዓት ነው፡፡ የተለመደ የቀጠሮ ሰዓት፡፡ ፍሬ ለቀጠሮ በመዘጋጀት ላይ ሳለች ግን የተለየ ስሜት ተሰማት፡፡ የመፍራት ይሁን የማዘን ምንነቱን ያልለየችው የሆነ ስሜት ሰላም አልሰጥ እያለ አስጨነቃት፡፡

ለባበሰችና ከቤት ወጣች፡፡ ሰዓቱ አምስት ሰዓት ተኩል ሆኗል፡፡ ለቀጠሮዋ ግማሽ ሰዓት ያህል ይቀራታል፡፡ ታረቀኝን አስታወሰችው፣ ትናንት ዛሬ ከፈቃደ ጋር ስላላት ቀጠሮ ስትነግረው ገጽታው ላይ ያየችው መከፋት ውስጧን ረበሸው። ግን ምን ማድረግ ትችላለች?

ብዙ ሳትቆም ታክሲ አገኘችና ገባች፣ ሰላም አልሰጥ ያላት ስሜቷ አልተዋትም፡፡

"ግን ለምን? ለምን የመንግስት ሥራ አስፈለገው? ለዚያውም ደግሞ ክፍለ ሀገር! ገና ስድስት ወር እንኳ ሳይሞላ? የጀመረውን ሥራውን በደንብ ሳይሞክረው?" አለች ለራሷ ከሁለት ቀናት በፊት ለፈቃደ ስልክ ደውላ የነገራትን አስታውሳ፡፡ ስልክ ስትደውልለት

"ሥራክ አገኘሁ" አላት ፈቃደ የምሥራች የሚነግራት ይመስል።

"የምን ሥራ?" አለችው ደንገጥ ብላ



"የመንግስት ነዋ"

"መቼ ፈልገኸው?"

"አንዳንዴ ሳያስቡት ነው የሚገኘው"

"ስለተገኘ ብቻ ይገባል እንዴ?"

"ለውጥ ያስፈልጋል"

"ለማንኛውም ስንገናኝ እናወራለን" ብላው ነበር ስልኩን የዘጋችው፡፡

"ያ ይሆን እንዴ ይህንን ስሜት የፈጠረብኝ? ወይንስ የታረቀኝ ነገር ነው ያሳሰበኝ?" አለች ለራሷ ታክሲ ውስጥ ተቀምጣ መንገድ ስትጀምር፡፡ ፒያሳ ልክ ከታክሲ ስትወርድ ፈቃደን አገኘችው፡፡

"እዚህ ነበር እንዴ ቀጠሮአችን" አለች ገርሟት።

"የፃድቃን ቀጠሮ ሆኖ ነው" አላት እየቀለደ፡፡ የት እንደሚሄዱ መነጋገር አያስፈልጋቸውም፣ ሁልጊዜም ቅዳሜ ምሳ የሚበሉት ጣይቱ ሆቴል ነው፡፡ አቅጣጫዋን ወደዚያው ስታደርግ ግን ቆም አደረጋትና "ዛሬ ለውጥ ያስፈልገናል" አላት የቀኙን መንገድ እየያዘ።

"እንዴት ነው የዚህ ሰሞን ለውጥ? ብቻ እኔንም እንዳትለውጠኝ" አለችው በምፀት።

"መጠርጠር መልካም ነው" አላት አንገቷን እያቀፋት።

አዲስ አበባ ሬስቶራንት እንደወትሮው ሁሉ ግጥም ብሎ ሞልቷል፡፡ ትልቁን አዳራሽ አልፈው ወደውስጥ ገቡ፡፡ እዚያም ቢሆን ቦታ የለም፡፡ ወደ ሌላው ክፍል ገቡ፡፡ ቀንቷቸው ሁለት ዱካዎች አገኙና ተቀመጡ፡፡ ቤቱ የንጉሳውያን ቤተሰብ ግብር የሚያበሉበትን አዳራሽ ይመስላል፡፡ ቁርጥ፣ ጎድን ጥብስ፣

ዝልዝል ጥብስ፣ ክትፎ፣ ዶሮ ወጥ... ጠጅ፣ ቢራ... ብቻ ሁሉም እንደየስሜቱ ያዛል፣ ያስቀርባል፣... ይበላል ፣ይጎራረሳል... ያወካል፡፡

ያዘዙት ምግብ ሲመጣ ፊታቸው ቀይ ልብስ ለብሶ ጉብ ያለው ሞሰብ ተከፈተና ትሪው ተቀመጠበት፡፡ ምግባቸውን እየተጎራረሱ መብላት በመጀመር ከታዳሚው ተቀላቀሉ፡፡

"ዛሬ ቢራ ጠጭ" አላት ፈቃደ።

"ከመቼ ወዲህ" አለችው።

"ለለውጥ ያህል" አላት እየሳቀ።

"ለውጥ የወቅቱ መፈክርህ መሆኑ ነው?"

"አዎ ደስ እንዲለኝ አንድ ጠጭ" ተስማማችለት፣ ትኩር ብሎ ተመለከታት።

"ምነው?" አለችው

"ነገ እኮ ነው የምሄደው"

"የት ነው የምትሄደው?"

"ሥራ አገኘሁ አላልኩሽም"

"ስለሱማ መነጋገር አለብን"

"ጊዜ ግን የለንም"

"ምን ማለት ነው?" ድንገት ተቆጣች

"ማለቴማ መነጋገር የምንችለው ዛሬ ብቻ ነው"



"አሁንም አልገባኝም"

"አውቀሽ ነው አይደል?" አለ ፈርጠም ብሎ።

ፈቃደ ትልቅ የሚባል ባይሆንም መጠነኛ የግል ሥራ አለው፡፡ ቤተሰቦቹ ከእስር ቤት ወጥቶ ሁለት ወር ሳይቆይ ነበር የግል ሥራ እንዲጀምር ገንዘብ የሰጡት። እናም ከጓደኛው ከኤፍሬም ጋር የእንጨት ቤት ከፈቱ።

እንጨት ሥራው የሚያኩራራ ባይሆንም ትልቅ ከሚባል ደሞዝ ያላነሰ ትርፍ እንደሚያስገኝ እርግጠኛ ናት፡፡ የሚኖረው ከቤተሰቦቹ ጋር በመሆኑ ወጪ የለበትም፡፡ ከጓደኛው ጋር ጥሩ መግባባትና መተማመን እንዳላቸው ነው የምታውቀው፡፡

"ቆይ! በሥራ ላይ የተፈጠረ ችግር አለ?" አለችው በጣም እየገረማት።

"የለም" አለ ባጭሩ።

"ከኤፍሬም ጋር ተጣላችሁ?" አለች ደግሞ፣ ዝም አላት።

"ንገረኝ እንጂ! ደህና ሥራህን የሚያስተው ምን ተፈጠረ?"

"እኔ ታማኝነትን ከሁሉ በላይ ነው የማየው፡፡"

"ታዲያ ማን እምነት አጎደለብህ?"

"ኤፍሬም ድርሻውን እስከአሁን አላሟላም"

"ለምን እንደሆነ ጠይቀኸዋል?"

"ብዙ ጊዜ ነግሬዋለሁ"

"ግን ደሞዙን ይወስዳል አይደል?"

"አሳምሮ"

"ታዲያ በዚያ መደራደር ይቻል አልነበረም፡፡ ድርሻውን መክፈል ካልቻለ ለተወሰነ ጊዜ ያለደሞዝ በመሥራት ሊያካክሰው ይችል አልነበር፡፡"

"ይከፍላል ብዬ ስላሰብኩ ይህንን አላደረግሁም"

"ወደፊትም ማድረግ ይቻላል"

"ሥራውን ሊተወው ያስባል"

"ታዲያ ሁላታችሁም ሥራውን ትታችሁትስ?"

"በቃ አሁን እሱን እንርሳው" አለ ፈቃደ ብስጭት ብሎ።

ከአዲስ አበባ ሬስቶራንት ወጥተው ወደፒያሳ ተመለሱ፡፡ "ትያትር ብናይስ?" አለችው ድንገት ማዘጋጃ ቤቱን ስታየው ትዝ ብሏት፡፡

"የራሳችንን ጨዋታ እንድንጫወት ነው የምፈልገው" አለና ቁልቁል ወደ ክሪያዚስ ወረዱ፡፡ ቡና በመጠጣት ላይ እያሉ

"ዛሬ መችም እምቢ እንደማትይኝ እርግጠኛ ነኝ" አለ የቡና ስኒውን እጠረጴዛው ላይ እያሽከረከረ፡፡

"ምኑን?" አለችው ድንገተኛ ጥያቄው አስደንግጧት።

"ምን እንደሆነማ ታውቂዋለሽ! ይኸው በልምምጥ ስድስት ወራት አለፉ"

"ግን ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ? አብረን ስንሆን እንደርስበት የለ?"



"ገና ከሦስት ዓመታት በኋላ? ወይንስ አሁን እንድንጋባ ፈቃደኛ ነሽ?"

"የምንጋባ ከሆነ ትቀራለህ?"

"የመንግስት ሠራተኛ ለማግባት ፈቃደኛ አይደለሽም ማለት ነው?"

"ስለዛ እንኳን አስቤ አላውቅም፡፡ የማገባው ደግሞ አንተን እንጂ ሥራህን አይመስለኝም"

"ወደማልፈልገው ነገር እየገፋሽኝ መሆኑ ግን ይግባሽ" በጣም ኩስትርትር አለ "ዛሬውኑ ውሳኔሽን እፈልጋሁ እኔ ግን አብረን በመዝለቃችን ላይ እምነቱ ካለን ሌላውን ጉዳይ ለምን መቀበል እንደሚያቅተን አይገባኝም፡፡ ያም ሆነ ይህ ዛሬ ቁርጡን ማወቅ እፈልጋለሁ"

"በውሳኔዬ ላይ ጥርጣሬ አለህ ማለት ነው?"

"ሌላ ምን ትርጉም ልሰጠው እችላለሁ? ለመጋባት ከወሰንን በሌላው ላይ የማንስማማበት ምክንያት ሊዋጥልኝ አይችልም"

ከእርሱ ሌላ የማግባት ሀሳብ እንደሌላት እንዲረዳላት ትፈልጋለች፡፡ በጣም እንደምታፈቅረውም ጭምር! "ግን ለምን አያምነኝም" አለች ለራሷ።

"ችግር ካለ በግልፅ እንድትነግሪኝ እፈልጋለሁ" አለ ከጥቂት ዝምታ በኋላ።

"ለምን ግን አታምነኝም?" አለችው በውስጧ የነበረውን ጥያቄ።

"ጥርጣሬ ያለብሽ አንቺ ነሽ"

"እንዴት?" ሳታስበው ተቆጣች።

"ባትጠራጠሪኝማ ይሄን ያህል ደጅ መጥናት አያስፈልግም ነበር፡፡ የልቡን ሲያደርስ..."

"በቃ ባላሰብኩት መንገድ አትሂድ፡፡ ይህ ዓይነት ሀሳብ ለሰከንድ እንኳን መጥቶብኝ እንደማያውቅ እንድትገነዘብልኝ እፈልጋለሁ" ቁጣዋ ለራሷም ተሰማት፡፡

በርካታ ጥያቄዎች በአእምሮዋ ውስጥ ተመላለሱ፡፡ ፈቃደን ተመለከተችው፤ እንደዚያ እለት ከፍቶት አይታው አታውቅም፡፡ አሁንም ቡና የጠጣበትን ስኒ ማሽከርከሩን አልተወም፡፡

"በናትህ አሁን ይሄ ጉዳይ እንዲህ ያስተክዛል?" አለችው ዝምታው ሲረዝምባት።

"በቃ ተይው ስሜቴን ልትረጂልኝ ባለመቻልሽ አዝናለሁ" አለና አስተናጋጁን ሂሳብ እንዲወስድ ጠራው።

"ይህ ነገር ለፈቃደ ይህን ያህል ትልቅ ከሆነ..." አለች ለራሷ።

ወደአመሻሹ ላይ ዝናቡ ማጉረምረም ያዘ፡፡ የክረምቱ ወር እየተቃረበ ቢሆንም ከዋለው የግንቦት ወር ቃጠሎ አኳያ ዝናቡ የተጠበቀ አልነበረም፡፡ ፍሬና ፈቃደም ዝናብ ከመጀመሩ በፊት ውሳኔያቸውን ሰጥተው ማደሪያቸውን መያዝ አለባቸው፡፡

"እሺ አዳር የት ነው?" አለችው ደግሞ ድንገት ሳያስበው፡፡

"ሁሉ ነገር ተመሰቃቅሎብኛል፡፡ በፍፁም ያልጠበቅሁት ነገር ነው፡፡ በቃ ደህና እደሪ" ትቷት ሊሄድ ተነሳ።

"እንዲህ ነው የምንሰነባበተው ማለት ነው? ነገ እንደሚገናኝ ሰው?"

"በናትሽ ግራ አታጋቢኝ ፍሬዬ..."



"በቃ እሺ አብረን እንደር..." በምን ዓይነት ፍጥነት እንዳቀፋት መግለጽ ይከብዳታል፡፡ ብቻ መንፈሱ ሙሉ በሙሉ ተቀይሮ ድብርቱ ሁሉ ወዲያውኑ ለቀቀው፡፡

አጋጣሚው ገረማት እለቱ ሮቤል እንደተለመደው አክስታቸው ቤት የሚያድርበት ቀን በመሆኑ ምቹ ነበር። ፈቃደ የጉዞ ሻንጣውን ይዞ ሊመጣ ወደቤቱ ሲሄድ እርሷ ስልክ ደወለችና ለበላይሁን እናት ትምህርት ቤት እንደምታድር ነገረቻቸው።

ሆቴል ስታድር በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፡፡ ልቧ በጣም ትመታለች ሰው ሁሉ እርሷን ብቻ የሚመለከት መሰላት፡፡ በዚያ ላይ የሚጠብቃትን ነገር ታስበዋለች፡፡ ፈቃደን ስታየው ገጽታው ከደስታ በስተቀር ምንም አይታይበትም፡፡ ልዩነታቸው ገረማት፡፡ የእርሷ ልብ ሰዓቱ እንዲርቅ የእርሱ ደግሞ እንዲቀርብ ይፈልጋሉ።

ክፍሉ በጣም ንጹህ ነው፤ ግን አስጠላት፡፡ ዝም ብላ ቆመች ስሜቷ ዝብርቅርቅ አለባት፡፡ ፈቃደ እጇን ይዞ እስኪያስቀምጣት ድረስ አልተንቀሳቀሰችም፡፡

"አታሳምመኝም አይደል?" አለችው፤ ጥያቄውን ሳታስበው ነው የጠየቀችው።

"እወድሻለሁ እኮ ፍሬዬ" አለ ፈቃደ፤ ድምፁ ለየት ያለ ቃና አለው። "እንዲህ እንድትጨነቂ በፍጹም አልፈልግም"።

ፈቃደ ግርግዳው ላይ ያለውን መጥሪያ ተጫነው፡፡ አስተናጋጁ ወዲያውኑ ከተፍ አለ፡፡ የአስተናጋጁን ፊት ማየት አሳፈራት፡፡ እንዳመጣጡ ትእዛዙን ተቀብሎ በፍጥነት ሄደና ሶስት ቢራዎችና አንድ አምቦ ውሀ ይዞ መጣ፡፡ አስተናጋጁ ሲወጣ ፈቃደ በሩን ቆለፈና ተመለሰ፡፡ ፍርሀቷ ጨመረባት ከምታውቀውና ከምትወደው ሰው ጋር ያለች መሆኗን እስከምትዘነጋ ድረስ መንፈሷ ተረበሸ፡፡

"ምነው ፍርዬ" አለ ፈቃደ ሁኔታዋን ተመልክቶ፡፡ ቢራውን ከፍቶ ሰጣት ሳታንገራግር ተቀበለችው፡፡ "አስገድጄ እንዳመጣሁሽ ያህል ተሰማኝ እኮ ፍርዬ ተጫወቺ እንጂ" ፈቃደንም ግራ ገባው፡፡ እንዴት እንደጀመሩት ሳታውቀው ሌላ ጨዋታ ውስጥ ገብተው ለረጅም ሰዓት አወሩ፡፡ ፍርሀቷ ሁሉ ለቀቃት፡፡

ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ ሀይለኛ ዝናብ መጣል ጀመረ፡፡ "በዝናብ አልጋ ውስጥ መሆን አትወጂም?" አላት ፈቃደ ተነስቶ ልብሱን እያወላለቀ፡፡ እንደገና ፈራች ልብሶቿን ማውለቅ አልቻለችም፡፡ ፈቃደ እንደትንሽ ልጅ ልብሷን አወላልቆ አልጋ ውስጥ አስገባት፡፡

ዝናቡ ዶፉን ያወርደዋል የፈቃደ ሰውነት ግሏል፡፡ የፍሬ ልብ ደግሞ በፍርሀት ትናወጣለች፡፡ ተቃቅፈው ተኙ፤ ፈቃደ እንደህፃን ልጅ እያሻሸ የሚያባብላት መሰላት፡፡ ቶሎ አድርጎት እንዲወጣላትም ተመኘች፡፡ ድርጊቱ ባላሰበችው ጊዜ ከመፈፀሙ ባሻገር ከፈቃደ ጋር ይህንን በማድረጓ ምንም የሚሰማት ነገር የለም፡፡ አብሮነታቸው እስከወዲያኛው ሊዘልቅና በትዳር ሊተሳሰሩ ቃል የተገባቡት ገና በመጀመሪያው ዕለት ነበር፡፡ እናም ልቧን አደፋፍራ ራሷን ዘና አደረገችው፡፡
ዝናቡ መጣሉን አላቋረጠም የፈቃደም ሰውነት መፋጀቱን ጨምሯል፤ ፍቅሩን የሚገልጽበት ቃላት ያጠሩት ይመስላል፡፡ እርሷ ደግሞ በተዘበራረቀ ስሜት ውስጥ ነች፡፡ ቀስበቀስ ስሜቱን እንድትጋራው አደረጋት፡፡ ፍርሀቷን አጠፋው በስሜቱ ግለት እርሷንም አሞቃት፡፡ በጆሮዎቿ የአንደበቱን የፍቅር ቃላት እያዳመጠች ሰውነቷ የወንድነቱን ጥንካሬ እንዲቋቋም ለማስቻል ራሷን አዘጋጀች፡፡ ህመሙን ሳይሆን ፍቅሩን ለማሰብ ጥረት አደረገች ስሜቱን ልታበላሽበት እንደማይገባት ራሷን አሳመነችው፡፡

"ፍርዬ የለም!" አላት ፈቃደ በደከመ አንደበቱ።

"ምኑ? "አለችው ግራ ተጋብታ።



"ለማንኛውም በጣም ተደስቻለሁ" አለና በቀስታ ሳማት፤ አቀፋት፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የነበረው ጥንካሬ በጭራሽ የለም፡፡ በጣም ገረማት፡፡

"ይህን ያህል ያደክማል እንዴ?" የጠየቀችው ራሷን ነበር።

ዝናቡ ጋብ ብሏል እንጂ አላባራም፡፡ "ፍርዬ የለም!" የሚለው የፈቃደ ድምፅ ተደጋግሞ ተሰማት፤ የበለጠ ግራ ገባት፡፡ የፈቃደን ፊት በቀስታ ዳበስ አደረገችው፡፡ አልቦታል፡፡ እግሯን ቀስቀስ አደረገችው የህመም ስሜት ተሰማት፡፡ ድንገት ትዝ አላትና መብራቱን አበራች፡፡

"ምነው ፍርዬ?" አለ ፈቃደ በደካማ ድምፅ።

"መታጠብ እፈልጋለሁ" አለች፡፡ ለማየት የፈለገችውን ማየት አልቻለችም፡፡ "የእውነትም የለም!" አለች ለራሷ፡፡ ደነገጠች፤ የበለጠም ግራ ገባት፡፡ እግሯን እንደገና አንቀሳቀሰችው በጣም አመማት፡፡

"ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ታገሽኝ አብረን እንታጠባለን" አላት ፈቃደ።

ከአልጋ ወርዳ ለመራመድ ስትሞክር አቃታት፡፡ እግሮቿ እንደወትሯቸው አይደሉም እየጎተተቻቸው ወደመታጠቢያ ቤት ስትሄድ ፈቃደ ደርሶ ደገፍ አደረጋት፡፡ ሰውነታቸውን እየታጠቡ በጭንቅላቷ ውስጥ የሚመላለሰው ሃሳብ አስጨነቃት፡፡ ሲወራ የሰማችውን ያህል ባይሆንም ህመሙ አለ። "ግን ደሙን ምን ወሰደው?" ድንቅ አላት። መንፈሷ ተረበሸ፤ ፈቃደንም መጠየቅ ፈራች፡፡

"ስላደረግሽው ተፀፀትሽ እንዴ?" አላት ፈቃደ ለመጀመሪያ ጊዜ።

"አንተ ግን ደስ ብሎሀል?" አለችው ጥያቄውን በጥያቄ በመመለስ።

"አዎ ፍርዬ ደስ ብሎኛል" አለ የድምፁ ቅላፄ ግን ደስተኝነቱን አልገለጸላትም። ፍቃደን ደስ ሲለው ታውቃለች።

"ከልብህ ነው?" አለች ፊቷን ወደእርሱ አዙራ።

"ለምን ዋሸሽኝ?"

"በፍፁም አልዋሸሁህም" አለችው በሚርገበገብ ድምፅ፤ የጠበቀችው ጥያቄ ነበር፡፡ የበለጠ ግራ ተጋባች ስሜቷም የበለጠ ተመሰቃቀለባት፡፡ ፈቃደ የሆነውን ነገር በደንብ እንዲያስረዳት ተመኘች ለመጠየቅ ግን ድፍረት አጣች፡፡

"አምንሻለሁ ፍርዬ ከልቤም ተደስቻለሁ" አለ ደግሞ ፈቃደ።

ታጥበው ጨርሰው ሰውነታቸውን እያደረቁ ሳሉ ፋቃደ ትኩር አድርጎ ተመለከታት፤ ዐይኖቿን አሸሸችው። አቀፋት...በጣም ጥብቅ አድርጎ አቀፋት ሳማት...የበለጠ ግራ አጋባት፡፡ ከሰማቻቸው ታሪኮች አንጻር የፈቃደ ድርጊት በጣም ተለየባት፤ እና ለማቀፉም ሆነ ለመሳሙ አፀፋውን አልመለሰችለትም በራሷ ሃሳብ ውስጥ ጠፋች፡፡

"ደስታዬን እንድታበላሽብኝ አልፈቅድም" አለ ፈቃደ ፊቷን ወደእርሱ እያዞረ።

"ልታስረዳኝ ግን ትችላለህ? በምን ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ልትነግረኝ ትችላለህ?" አከታትላ ጠየቀች።

"የባለሙያ መልስ የለኝም፤ ግን እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል" የመለሰላት ተረጋግቶ ነው።

"እኔ ግን አዝኛለሁ"

"ፍርዬ እርግጠኛ እንድትሆኚ እፈልጋለሁ በጣም ደስ ብሎኛል ደግሞም በጣም አምንሻለሁ" ሊያረጋጋት ሞከረ።



ተመልሰው ተኙ፤ የፈቃደ ሰውነት በጣም ያቃጥላል፡፡ "ከውሀ ውስጥ የወጣህ አትመስልም" አለችው፡፡ እንደገና አቀፋት፤ ሳማት...

"ምንኛ የታደልኩ ነኝ? ንፁህ እኮ ነሽ ፍርዬ" አላት በጆሮዋ፤ ትንፋሹ ጆሮዋንሞቃት፡፡ ምን እንደሚያደርጋት ግራ የገባው ይመስል ቀና ብሎ ተመለከታት፡፡ ስላመናት ደስ አላት፡፡

ጠዋት ዝናቡ ሙሉ ለሙሉ አላቆመም፡፡ የዝናቡ ካፊያ ጣሪያና ኮርኒሱን ዘልቆ ባይሰማም በመስኮቱ መስታወት ውስጥ ይታያል፡፡ አንድ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ ይላል ሰዓቱ። የክፍላቸው መዝጊያ በቀስታ ተንኳኳ።

"አቤት! አምስት ደቂቃ ብቻ" አለ ፈቃደ እየተነሳ፡፡

"ማነው?" አለችው ፈቃደን በቀስታ።

"ሾፌሩ ነው፤ እዚህ መሆኔን ማታ ነግሬዋለሁ" አለ ወደመታጠቢያ ቤት እየገባ።

ልብሶቿን በፍጥነት ለባበሰች፡፡ ከአልጋው አጠገብ ያለው ከመዲኖ ላይ ያለው የአምቦ ውሀ ጠርሙሱ አልተከፈተም፤ ስታየው ውሀ ጥም ተሰማት ከፈተችና ግጥም አድርጋ ጠጣችለት፡፡ የአምቦ ውሀው ጋዝ ዐይኖቿ እምባ እንዲያቀሩ አደረጋቸው፡፡ ፈቃደ እየተጣደፈ ተዘገጃጅና ለመሄድ ተነሳ፡፡

"አልሸኝህም እንዴ?" አለችው እምባዋ በዐይኖቿ እየሞላ።

"መኪናው እዚሁ ነው" አለ በአንደኛው እጁ ጎተት አድርጎ እየሳማት። "ደህና ሁኝልኝ ፍርዬ! እወድሻለሁ" አላትና ወጣ።

"መቼ ነው የምንገናኘው?" አለችው።

"እፅፍልሻለሁ"

"እሺ ደህና ሁን" አለች በተከፋ አነጋገር፡፡ መውጣቱን ትቶ ተመለሰና ሻንጣውን አስቀምጦ እንደገና አቀፋት፤ ሳማት እንደሚወዳት ነገራት፡፡ "በቃ ሂድ!" አለችው የመኪናውን መቆም አስባ፡፡

"ያላንቺ መኖር እንደማልችል አውቀዋለሁ" አለ የበሩን እጀታ እንደያዘ።

"ደህና ግባ" አለችው ከእንባዋ እየታገለች።

* * * *

ሚስጥረ ልብስ መቀየሪያው ክፍል ገብታ የሥራ ልብሷን ያወለቀችው በደመነፍስ ነው። ከሰዓት በኋላ ከዳኙ ጋር ወዳላቸው የተለመደ ቀጠሮ ለመሄድ ነው የምትሰናዳው። ሁልጊዜም እሁድ ከሰዓት በኋላ የምትለብሳቸው ልብሶች ልዩ ናቸው። የሥራ ባልደረቦቿ እነዚህን ልብሶቿን በሚገባ ያውቋቸዋል፤ ከሰዓት በኋላ የት እንደምትሄድም ያውቃሉ። ዳኙንም ያውቁታል።

"ታድለው!" ይላሉ ሁልጊዜም ተሰናብታቸው ስትወጣ።

ዛሬ ግን የወትሮው ደስተኝተኝነትና መረጋጋት አይታይባትም። የተረበሸች ትመስላለች። የሥራ ጓደኞቿ ሁኔታዋን አይተው በመጠየቅና ባለመጠየቅ መሀል እያሉ "ደህና ዋሉ" አለችና ለጥያቄም ጊዜ ሳትሰጥ ወጣች። ስሜቷን መቆጣጠር ባለመቻሏ በራሷ ተናደደች። መንገዷን ሁሉ ስለፍሬና ስለፈቃደ እያሰበች ነበር።

እንደተለመደው ዳኙ ቀድሚት ደርሷል፤ አጠገቡ እስክምትድርስ በትኩረት ተመለከታት። "ምን ሆነሻል?" አላት እየሳማት። ጊዜያቸውን እንዳታበላሸው በመስጋት ላትነግረው ፈለገችና "ምንም" አለችው ወንበሯን አስተካክላ እየተቀመጠች።

"አውቅሻለሁ! 'ምንም' መልስ አይሆንም" አላት ትከሻዋን እየደባበሰ።



"ጊዜያችንን ማበላሸት አልፈልግም፤ ወደቤት ስንሄድ ብነግርህስ?" አለችው።

"ምንም ቀጠሮ አያስፈልግም፤ ተነጋግረንበት ስናበቃ እንዳልተፈጠረ ልንቆጥረው እንችላለን፤ ካልሆነ ግን ቆይታችን ሁሉ አይጥምም" አላት እንደተረጋጋ።

"ዳኙ!" አለችው ድንገት።

"አቤት!" አላት ደንገጥ ብሎ፤ ሁኔታዋ አላማረውም።

"አንድን ሰው ባልጠበቅከው ቦታ ብታገኘው ምን ታደርጋለህ?" አለችው፤ በትኩረት እየተመለከተችው።

"እንደሁኔታው ነው" አላት በደፈናው።

"እሺ! አንድ ሰው ሁለት የማይገናኝ ባህሪ ሊኖረው ይችላል?" አለችው ደግሞ።

"ምናልባት! ጥያቄሽ ግን አልገባኝም፤ ለምን ለመጠየቅ የፈለግሽውን በቀጥታ አትጠይቂኝም?" አላት ግራ ገብቶት።

"ስለጨነቀኝ ነው ዳኙ! የፈቃደ ነገር በጣም ገርሞኝ…" ዳኙ አቋረጣት።

"ፈቃደ ምን አለሽ?" አለ በቁጣ።

"እኔንማ ምን ይለኛል፤ ከሌላ ሴት ጋር ስለማየው ከራሴ ጋር እየታገልኩ ነው" አለችና ገላገለችው።

"ከሌላ ሴት ጋር መሆን ማለት ታዲያ…" አቋረጠችው።

"ዝም ብዬ ተጠራጥሬ እንዳይመስልህ፤ አብሮ ማየት ብቻ ሳይሆን የግንኙነቱን ዓይነት በሚገባ ተመልክቼ ነው። በተለይ የዛሬ

ሳምንት ያየሁት ዐይን ያወጣ ነበረ፤ በጠዋት ወደሥራ ስገባ አብረው ሳገኛቸው ትንሽ እንኳን አላፈረም። ጭራሽ ትናንት ደግሞ ይዟት መጣ። ስሜቴን መቋቋም አቅቶኝ ወዲያውኑ ለፍሬ ልነግራት ፈልጌም ነበር። በእውነት ነው የምልህ ወንድ እንድጠላ ነው ያደረገኝ" አለችው ስሜት ውስጥ ገብታ።

"ማጠቃለያ መስጠት እንኳን አይቻልም። ሁላችንንም ጨፍልቀሽ እንደአንድ ሰው ልትመለከቺን ከሆነ ታላቅ ስህተት እየሰራሽ ነው" አላት ተኮሳትሮ።

"እሺ! በልቤ ውስጥ ትልቅ ቦታ የምሰጠውን ፈቃደን በእንዲህ ዓይነት ጉዳይ ላይ ውርድ ብሎ ሳገኘው ምን ልበል" አለች ሚስጥረ ግራ እንደገባት።

"ፈቃደን የምታውቂው ግን በምንድነው?" አላት ዳኙ።

"የማውቀው በትግል ጥንካሬው ቢሆንም ቢያንስ ፈቃደ ፍሬን እንዴት እንደሚወዳትና እርሷን ለማግኘት የሆነውን አውቃለሁ" ቆጣ አለች ሚስጥረ።

"ያልተረዳሽው ነገር ቢኖር ፍቅር ቀመር ያለመሆኑን ነው። ፍቅር ለሁላችንም አንድ ዓይነት ትርጉም እንዲኖረው ቀመር መሆን አለበት፤ ምክንያቱም በሂሳብ አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ከመሆን ያለፈ ውጤት የለውም። ለፍቅር ግን ይህ አይሠራም፤ ፍቅር ሁሉንም የሚያስማማ አጠቃላይ መገለጫ ቢኖረውም እያንዳንዱ ሰው ደግሞ ለፍቅር የሚሰጠው የራሱ ትንታኔ ሊኖረው ይችላል። በእርግጥ ለፍቅር ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሰዎች ሲገናኙ ተመሳሳይ መንገድ ሊከተሉ ይችላሉ..." አቋረጠችው።

"ፍልስፍና አታድርገው እንጂ! እንደምትለው ቢሆን እንኳ የፍቅር ግንኙነት ከመጀመር በፊት አቋምን መገላለጽ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። እርግጠኛ ነኝ ፈቃደና ፍሬ ተመሳሳይ ፍልስፍና ሊኖራቸው አይችልም። ፍሬ እንኳንስ አብራ ሆና ለተለየቻቸውም ሰዎች ታማኝ ለመሆን የምትፈልግ ሰው ነች።" አለችው።



"እንግዲህ ልናደርግ የምንችለው ነገር ካለ እንነጋገርና ወደራሳችን ፍቅር እንመለስ፤ ስለሰው ፍቅር ስንጨነቅ የራሳችንን እንዳንተወው እሰጋለሁ" አላት።

"ያየሁትን ልንገራት?" አለችው ድንገት።

"ቀደም ቢል ምንም አልነበረም፤ አሁን ግን ፍሬ ፈቃደን ያፈቀረችው ይመስለኛል እንዳትጎዳ እፈራለሁ" አላት።

"እያወቅሁ ዝም ልበላት ማለት ነው?" አለች ጥፋተኝነት ተሰምቷት።

"ይመስለኛል!" አላት ዳኙ።

"ያንተ የፍቅር ፍልስፍና ግን ምንድነው?" አለችው ሳያስበው።

"አትጠራጠሪኝ! የፍቅር ኮክቴል ጥሞኝ አያውቅም" አላት።

"የፍቅር ኮክቴል ደግሞ ምንድነው?" አለችው፤ ያልገባትን ሳትጠይቅ የማታልፈው ሚስጥረ።

"የኮክቴል ግብዣ እየተዟዟሩ ከዚያም ከዚያም መቀማመስ አይደል? በፍቅር ጉዳይ መልክስከስ አልወድም ማለቴ ነው" አላት።

"አምንሃለሁ!" አለችው።

"ወደራሳችን ጉዳይ እንግባ?" አላትና ተስማማች።

ዳኙ ስለወደፊት ሕይወታቸው ያሰበውን ነገራትና በሰፊው ተወያዩ፤ ብዙም ሳይቆዩ አብረው መኖር እንዲጀምሩ፣ የራሳቸውን ትንሽ ሥራ በጋራ እንዲሰሩ፤ ሁለቱም ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ተስማሙ።

ሚስጥረ ከዳኙ ጋር ያሳለፈችው ጊዜ ያስደሰታት ቢሆንም ቤቷ ስትገባ ሀሳቧ ወደፍሬ ሄደባትና ደስታዋን ከፈለባት። ፍሬን ስታስባት አመሸች።

* * * *

ፍሬሕይወት "ፍርዬ የለም!" የሚለው የፈቃደ ድምፅ ከአእምሮዋ ሊጠፋላት አልቻለም፡፡ "ለምን?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ባደረገችው ፍተሻ ሀሳቧ የኋሊት እየገሰገሰባት ትናንት ስትበጠበጥ ውላለች፡፡

ሙሉ ቀን መተኛትም ሆነ መቀመጥ ቢያስጠላት፣ ማንበብም አልሆን ቢላት ቤት ማጽዳት ጀመረች፣ ሥራው ጊዜውን ገፋላት፣ ስትጨርስ ሰባት ሰዓት አልፏል። ምሳ የመብላት ፍላጎት አልነበራትም፣ መብላት ቢኖርባትም ምግብ መስራት ነበረባት። ሁሉም የሚሆንላት አልነበረም፣ ገባችና ጋደም አለች፣ ሀሳቧ ግን ወደማትፈልገው ጉዳይ መሄዱን አልተዋትም። ልብሷን ቀያየረችና ከቤት ወጣች።

በውስጧ የሚጉላላውን ነገር ተናግራ ትንሽ መተንፈስ እንዳለባት እያሰበች ሚስጥረን ለማግኘት ተጣደፈች። ፖስት ራንዴቩ ስትደርስ ስምንት ሰዓት ተኩል ሆኖአል፣ ቤቱ ጭር የሚልበት ሰዓትነው፣ ከሚስጥረ ጋር ለማውራት ምቹ መሆኑን እያሰበች ተቀመጠች። አስተናጋጆቹ ስለሚያውቋት ወዲያውኑ መጥተው ሰላም አሏት።

ሚስጥረ ከሰዓት ረፍት መሆኗን ስትሰማ በሸቀች። ጭንቅላቷ በሌሎች ነገሮች ተይዞ ዘንግታ ነው እንጂ እሁድ ከሰዓት በኋላ ከዳኙ ጋር እንደምትሆን ታውቃለች። ሳትፈልግ ማኪያቶ ጠጥታ ብዙም ሳትቆይ ነበር ወደቤት የተመለሰችው። ከሮቤል ጋር መንገድ ሲገናኙ ትንሽ ቀለል አላት።

ዛሬ ትምህርት ቤት መሄድ ነበረባት፣ ግን ጭንቅላቷ እንደተበጠበጠ ነው። በመጀመሪያ ሚስጥረን ማግኘትና ሀሳቧን ማከፈል አለባት። ገና ሥራ ለመጀመር ሲዘጋጁ ነው ፖስት ራንዴቩ የደረሰችው፣ ሚስጥረ ከሩቅ ስታያት ደነገጠች።



"ምነው ፍሬ በደህና ነው?" አለቻትና የሚቀመጡበት ቦታ አመቻቸች ሚስጥረ።

"በደህና ነው፣ መናፈቅ አይቻልም" አለች ፍሬ ለመሳቅ እየሞከረች።

"መናፈቅን አግኝቼው ነው?" አለች ሚስጥረም እየቀለለደች።

"ፈቃደ እኮ ሄደ" አለች ፍሬ ድንገት።

"ነገረኝኮ' ከትናንት ወዲያ መጥቶ ነበረ" መለሰች ሚስጥረ ሲፈታተናት የነበረው ነገር በአእምሮዋ እየተመላለሰ።

"ቅዳሜ ዕለት አብረን ነበረ ያደርነው" አለች ፍሬ በቀስታ።

"አታደርጊውም!" አለች ሚስጥረ፣ ሳታስበው ደንግጣ ፍሬንም አስደነገጠቻት።

"ምነው ሚስጥረ?..." አለች ፍሬ ልትናገር የፈለገችውን ነገር ሁሉ ትታው። "ፍሬ የለም" የሚለው የፈቃደ አነጋገር በአእምሮዋ ውስጥ እንደተንጠለጠለ ነው።

"አይገርምም! እስኪ ምን ይህን ያህል አስደነገጠኝ? በእርግጥ አስቤው አላውቅም፣ አብሮ ማደርን ከጋብቻ ጋር ብቻ ስለማያይዘው ሊሆን ይችላል። ይቅርታ ፍሬ አንቺንም አስደነገጥኩሽ" አለች ሚስጥረ ራሷን ለማረጋጋት እየሞከረች።

"ለነገሩ እኔም አስቤው ያደረግሁት አልነበረም፣ ፈቃደን ታውቂዋለሽ አንድ ጊዜ ያለው ነገር ካልተፈጸመ እረፍት አይሰጥም..." ንግግሯን አቋረጠችው።

"ታዲያ እንዴት ነበር?" የሚስጥረ ጥያቄ ነበር።

"እኔ እንጃ! ብቻ አልተደሰትኩም ማለት ይሻላል... ያልተዘጋጀሁበትም ስለሆነ ሊሆን ይችላል... እንጃ!" ፍሬ እነዛን ቃላት አውጥታ ለሚስጥረ መንገር አልሆነላትም።
"ሚስጥረ ግን... በቃ ተይው እባክሽ..." አለች ፍሬሕይወት።

ሚስጥረም ነገሩ ሁሉ በፈቃደ ላይ ቢያዘችው ነገር የተነሳ ተመሰቃቅሎባታል። ፍሬ የፈለገችውን ነገር አውጥታ እንድትናገር የሚያበረታታ ሁኔታ አልፈጠረችላም። በመሀላቸው ዝምታ ሰፈነ።

"በቃ ልሂድ" አለችና ተነሳች ፍሬ። ሚስጥረም እንድትቆይ ለማድረግ የሚያስችል አቅም የላትም። ሚስጥረ ስህተት እንደፈጸመች ተሰማት፤ ፍሬ የሆነ ነገር ልትነግራት እንደመጣች ብታስብም የራሷን ስሜት አሸንፋ ለፍሬ ተገቢውን የጓደኝነት ድጋፍ ልታደርግ ባለመቻሏ በራሷ ላይ ተናደደች።

ፍሬሕይወት ከፖስት ራንዴቩ ስትወጣ ወደትምህርት ቤት የመሄድ ሀሳቧን ሰርዛ ወደቤቷ ተመለሰች። ቤት ስትገባ ከቦርሳዋ ውስጥ እስኪሪፕቶና ደብተር አወጣችና ወንበር ስባ ከጠረጴዛው ፊት ተቀመጠች፡፡ ስትቀመጥ የፈቃደ "ፍርዬ የለም!" የሚሉ ቃላት በአእምሮዋ ውስጥ እንዳሉ ናቸው። አሁንም በዚህ ምክንያት ነው ማለትና መልስ መስጠት አልቻለችም። "ሳይንሳዊ ትንታኔ መስጠት ባልችልም ሊያጋጥም ግን ይችላል" የሚለውን የፈቃደን አባባል መቀበል ነበረባትና ተቀበለችው።

የሚያጋጥሟትን አንዳንድ ለየት ያሉ ስሜቶች የመጻፍ ልምድ የነበራት ቢሆንም ከተወችው ረጅም ጊዜ ሆኗታል። ዛሬ ግን አዲሱን ያጋጠማትን ነገር ትውሰታ ለማስቀረት መጻፍ ጀመረች። ጽፋ ስትጨርስ "ለምን የዛሬውን ብቻ?" የሚል ጥያቄ በአእምሮዋ ውስጥ ቦታ ያዘና ልታወጣው አቃታት።

ማስታወሻና እስኪሪፕቶውን አስቀምጣ ለጥቂት ደቂቃዎች አሰበች፡፡ ሊፃፍ የሚገባው መሆኑን አመነች፤ እናም የሕይወት አጋጣሚዋን ሁሉ ከመነሻ እስከመድረሻ ልትጽፈው ለራሷ ቃል ገባች፡፡ መድረሻው ግን የቱ ይሆን? መድረሻው ገና ነው፤



ቢሆንም ስትደርስበት ትጽፈዋለች! ያለፈውን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱንም ጭምር ለመጻፍ ወሰነች!

ውስጧ አንዳች ኃይል ሲፈጠር ተሰማት፡፡ በየአጋጣሚው እየጻፈች ያስቀመጠቻቸው ብጥስጣሽ ወረቀቶች ትዝ አሏት፡፡ ወረቀቶቹን ለመፈለግ አልጋ ስር ከተከተተ የቆየውን ካርቶን አወጣችና ማገላበጥ ጀመረች። ወረቀቶቹን እያገላበጠች ሀሳቧ ወደ ፈቃደ ሄደባት። ፈቃደን እንደምታፈቅረው ይሰማታል ከፈቃደ ጋር ስትሆን የሕይወት ትዝታዋ በውስጧ ይኖራል፤ በእያንዳንዱ ዕለት፣ ሰዓትና ደቂቃ ፈቃደን ባሰበች ቁጥር ያለፈ ሕይወቷን ትዝታ ታስታውሳለች ... ፈቃደ ለእርሷ የሕይወቷ አሻራ ነው ። ከዚያ የሕይወቷ ትዝታ መለየት በፍጹም አትፈልግም።

* * * *

ፈቃደ ገጠርን ከዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ውጭ አያውቀውም። ያኔ ደግሞ ብቻውን ሳይሆን ከብዙዎች ጋር ነበር፤ መንግስት ባዘጋጀው መጠለያ ውስጥ ነበር የኖረው። አሁን ግን ለብቻው ነው የሄደው፤ ለዚያውም በሥራ። ገጠር ከመሆኑ በስተቀር ጠለቅ ያለ መረጃም አልነበረውም። ምንም ነገርም ይዞ አልሄደም።

አካባቢውን ሲያየው ትንሽ መደንገጡ አልቀረም፤ ከጠበቀው የባሰ ሆኖ አገኘው። የገባ ዕለት አልቤርጎ ማደር ነበረበት፤ ቢያስጠላውም የትም መሄድ አይችልም የጎረጎደው የሽቦ አልጋ ሲቀመጥበት መሬት የነካ መሰለው። ጋቢውን ብቻ ተከናንቦ አልጋው ጫፍ ላይ ተንጠልጥሎ አደረ።

ጠዋት ሾፌሩ መሥሪያ ቤት ወሰደና ከሥራ አስኪያጁ ጋር አስተዋውቆት ወደአዲስ አበባ ተመለሰ። ብዙ ነገሮችን ከአዲስ አበባ ሳይወጣ መጠየቅ እንደነበረበት ቢሰማውም ከሥራ አስኪያጁ ጋር መነጋገር ነበረበት።

ሥራ አስኪያጁ አጠቃላይ ገለጻ አደረገለት፤ ለሥራ የሚሆን ሞተር ብስክሌት እንደሚሰጠው፣ ቤትን በተመለከተ መሥሪያ ቤቱ የሠራተኞች መኖሪያ እንዳለውና የሚያስፈልጉትን ቁሳቁስ ግን ማሟላት እንደሚኖርበት ነገረው። የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር

መኘታ መሆኑንና ለመግዛት ለንዲተባበሩት ጠየቀ። ሾፌር እንደሚታዘዝለትና ሄዶ ሊገዛ እንደሚችል ሲነገረው በመጠኑ ተረጋጋ።

መደበኛ ሥራውን የጀመረው አንድ ሳምንት ከመሙላቱ በፊት ነው። ፈቃደ ሥራውን አልጠላውም፤ ኑሮውን ተቀብሎ መሥራት እንደሚኖርበት ራሱን አሳምኗል። ከሥራው ጋር እስኪላመድ ድረስ የሚፈጠሩበትን ጥያቄዎች ሁሉ ከመጠየቅ ወደኋላ ብሎ አያውቅም፤ ካጠበቀው በላይ ፈጥኖ ሥራውን በሚገባ ለመደው።

ብዙው ሥራ መስክ የሚወስደው በመሆኑ ብዙውን ጊዜውን የሚያሳልፈው እዚያው ነው። በጠዋት ሞተር ብስክሌቱን ይዞ ከወጣ የሚመለሰው ማታ ነው። ምሳውንም ሳይበላ የሚውልባቸው ቀናት አሉ። ማታ ከሥራው ሲመለስ ሰውነቱን ይተጣጠብና ራቱን በልቶ ወደመኝታው ይገባል። እቤት ሲገባ ግን ያስጠላዋል፤ ከአልጋው በስተቀር ሌላ ነገር የሌለው ቤት ሕይወት አልባ ይሆንበታል። ቀስ በቀስ አምሽቶ መግባት ጀመረ። ሲያመሽ ደግሞ መጠጣት ይኖራል፤ ሲጠጣ ሞቅ ይለዋል፤ ሞቅ ሲለው ሌላ ፍላጎት... ዐይኖቹ እንስት ማየት ጀመሩ።

በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ሁሉም ነገር ያበሳጨው ነበር፤ አራሱን እያሳመነው ሄደ "ለመሥራት መቼም መኖር ያስፈልጋል፤ ለመኖር ደግሞ መሠረታዊ ፍላጎት መሚላት ይኖርበታል፤ አእምሮም እረፍት ያስፈልገዋል። ይህን ለመፍጠር ደግሞ ባለው አማራጭ ከመጠቀም ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል?" ብሎ ሊያደርግ የሚገባውን እያደረገ መሆኑን አመነበት።

አንድ ቀን ከመስክ ሲመጣ መንገድ ላይ አንዲት ሴት አጋጠመችውና እንዲያፈናጥጣት ለመነችው። እምቢ ማለት ከበደው፤ ከተማ ድረስ አመጣትና "የት ነው የምትሠሪው?" አላት ስትወርድ። የምትሠራበትን በምልክት ነገረችው። አንድ ቀን እንደተለመደው ለእራት ሲወጣ ያች ሴት ትዝ አለችውና በምልክት የነገረችው ቦታ ሄደና አገኛት። በመጠኑ ከጠጣ በኋላ ሴትዮዋን እቤቱ እንድትሄድለት ጠየቃት። እስካሁን ካገኛቸው ሴቶች የተሻለች ሆና ስላገኛት ደስ አለው። በተደጋጋሚ አብራው አደረች።



ያን ሰሞን አእምሮው ምቾት ሊያገኝ አልቻለም፤ በየሰዓቱ ፍሬሕይወትን ማሰብ አበዛበትና ጨነቀው። "ፍሬሕይወትን በጣም እወዳታለሁ፤ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ አብሬአት መኖር እፈልጋለሁ። ግን እስከዛው መኖር አለብኝ፤ ሰው በመሆኔ ደግሞ ተፈጥሮአዊ ፍላጎት አለኝ፤ ይህ ፍላጎት መርካት አለበት፤ ከሌላ ሴት ጋር የምሄደውም ይህንን ጊዜያዊ ፍላጎቴን ለማርካት ነው" አለ ለራሱ።

ቢያንስ አንድ ነገር ማድርግ እንዳለበት ግን ተሰማው፤ የሚፈጥረው ግንኙነት ሁሉ ጊዜያዊ መሆን እንዳለበት። በመሆኑም ከሴትዮዋ ጋር የጀመረውን ግንኙነት ማቋረጥ እንዳለበት ወሰነ። ውሳኔውንም ተግባራዊ አደረገ። አንድ ጊዜ ለስብሰባ አዲስ አበባ ሄደና ፍሬሕይወትን አገኛት፤ ደስ አለው ከገመተው በላይ ነበር የናፈቀችው፤ እናም አዲስ አበባ ገብቶ ሳያገኛት ማደር አቅቶት ደጋግሞ ደውሎ አገኛት።

ለሶስት ቀናት ብቻ ነው አብሯት መቆየት የቻለው፤ ወደሠራው ተመለሰ። ፈቃደ ሥራ ጀመረ ማለት ሁሉን ነገር ረሳ ማለት ነው። ነገሮችን የሚያስበው ማታ ከሥራ ገብቶ አረፍ ሲል ነው፤ ወዲያውኑ ደግሞ ይረሳዋል። አንድ ቀን የሬድዮ መልእክት እንዳለው ተነገረው፤ ፍሬሕይወት መሆኗን ሲያውቅ ደነገጠ።

"ምነው?" አለችው ደህንነቱን ከሰማች በኋላ።

የሚመልስላት አልነበረውም፤ ትክክል መሆኗን አመነ። በሶስት ወራት ውስጥ ያገኛት አንድ ጊዜ ነው። ለዚያውም ለሶስት ቀናት ብቻ። ወደሥራ ቦታው ሲመለስ ስልክ ሊደውልላት ተስማምተው ነበር። በእርግጥ ያለበት ቦታ ስልክ የለውም፤ ከታሰበበት ግን ወደከተማ ወጣ ብሎ መደወል ይቻላል።

"ፍሬ ይቅርታ አድርጊልኝ፤ ጥፋተኛ ነኝ" አላት። ከፍሬሕይወት ጋር የሚገባውን ያህል የመልእክት ልውውጥ እንዳላደረገ ያውቀዋል። ከዚያ በኋላ በየሳምንቱ ወደከተማ እየወጣ ስልክ ደውሎ ሊያገኛት ተነጋገሩ።

አንድ ቀን ከዋናው መሥሪያ ቤት ደብዳቤ ደረሰው፤ ለአጭር ጊዜ ስልጠና ወደአውሮፓ የመሄድ ዕድል እንደተመቻቸለት የሚገልጽ መልእክት ነበር። ብዙም አላስደሰተውም ግን በዕድሉ ለመጠቀም ወሰነ። ጉዞውን ለማመቻቸት ወደአዲስ አበባ መሄድ ነበረበት። አዲስ አበባ የገባ ዕለት ዩኒቨርሲቲ ሄዶ ለፍሬ መልዕክት ላከ። ባጋጣሚ መልዕክቱ በሰዓቱ ደረሳትና ተገናኙ። ፈቃደ አዲስ አበባ ከሆነ እንድትለየው አይፈልግም። ባላት ሰዓት ሁሉ አብራው ብትሆን ደስተኛ ነው። ሲጫወቱ ቆዩና ወደ አስራአንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን፤

“ብሄድ ምን ይመስልሀል?” አለችው ፍሬሕይወት።

“ትሄጂ?” አላት ሰዓቱን እየተመለከተ።

“ሮቢ ብቻውን አይደል?” አለች።

“አንድ ነገር ልነግርሽ ነበር ፍርዬ!” ፈገግታና ሐዘን የተቀላቀለበት ገጽታ ነበረው።

“ምን ፈቃደ? ምንድነው የምትነግረኝ?” አለች በችኮላ።

“ወደውጭ ልሄድ ነው” አለ።

“መቼ? ለምን ያህል ጊዜ?” ድንግጥ ብላለች።

“ከሳምንት በኋላ እሄዳለሁ፡፡ ለስድስት ወራት ነው የምቆየው” አለ ፈቃደ ቀለል አድርጎ።

“ዝም አለችው”

“የማያስደስትሽ ከሆነ ቢቀርም ግድ የለኝም” አላት። ከልቡ ነበር።

“ምን ለውጥ አለው፤ ባትሄድስ የት እንገናኛለን፤ በዕድሉ ብትጠቀምበት ነው የሚሻለው” አለችው። አዲስ አበባ የቆየበትን አንድ ሳምንት አልተለያዩም፤ ያላትን ጊዜ ሁሉ አብረው ነው ያሳለፉት።



ፈቃደ አውሮፓ ከሄደ በኋላ በየአሥራ አምስት ቀኑ ደብዳቤ ይልክላታል፡፡ እወድሻለሁና ናፍቄአለሁ ከደብዳቤዎቹ ውስጥ ቀርተው አያውቁም፡፡

* * * *

የሴሚስተር አጋማሽ ፈተና ተቃርቧል፤ የማይፈቀዱ ቢሆንም ለጥናት የሚያግዙ ማነቃቂያዎች በተለያየ መንገድ ወደ ዩኒቨርሲቲው ግቢ ይነጉዳሉ። አብዛኛው ተማሪ “ጫት ካልተቃመ የኮሌጅ ትምህርት አይሰምርም” የተባለ ይመስል ወደአመሻሹ ላይ ወደ ውጭ ወጣ ብሎ በጀርባውና በካልሲው ውስጥ ጫት ሸጉጦ ይመለሳል። ሌሊቱን ቁጭ ብሎ የሚያነጋው የተማሪ ቁጥር ይጨምራል።

ታረቀኝ ጫት አይቅምም፤ ማጥናት ያለበትን ያህል ያጠናል ይተኛል በቃ! ውጤቱ ደግሞ ከፍተኛ ነው። አድናቂዎቹም ብዙ ናቸው፤ ለተወሰኑ ሰዓታት አብሮአቸው ሆኖ እንዲያጠኑ የሚመኙት ሴቶች ቁጥር በርካታ ነው። ማታ በአብዛኛው አልጋው ላይ ሆኖ ነው የሚያጠናው። ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ግን የጸባይ ለውጥ እያዩበት የመኝታ ክፍል ተጋሪዎቹን እያሳሰባቸው ነው። ከሚያጠናበት ጊዜ ይልቅ አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋሎ በሀሳብ ጭልጥ ማለት አብዝቶአል። ዛሬም ጥቂት ካነበበ በኋላ ደብተሩን ከትራሱ ስር ሲያስቀምጥ ሀሳቡ ወደማይፈልገው አቅጣጫ ሄደበት። ማሰብ፤ መተከዝ... ጓደኞቹ ሆነዋል።

ውጤቱ እየደር እየቀነሰ የመሄዱ ነገር በእጅጉ ያሳስበዋል። ግን ምን ያድርገው? ዘንድሮ ራሱን ማሸነፍ አቅቶታል። ስንት ቀን የሚገናኙበትን ጊዜ መቀነስ እንዳለባቸው ተነጋግረዋል፤ ላለመገናኘትም ፍሬሕይወት ወደቤት እንድትሄድ ይስማማሉ። እቤት ገብታ አንድ ሰዓት ሳትቆይ ግን ታረቀኝ ይደውልላታል፤ “አንድ መጽሐፍ አግኝቻለሁ አብረን እናንብበው” ይላታል። እርሷም በፍጹም እምቢ ልትለው አትችልም፤ ተመልሳ ወደዩኒቨርሲቲ ትመጣለች። አብረው ሲሆኑ ደስ ይለዋል፤ መንፈሱ ሰላም ያገኛል።

አንድ ቀን የሆነው ነገር ትዝ አለው፤ ያን ዕለትም እንደተለመደው ደወለና ጠራት፤ ብዙም ሳትቆይ ከተፍ አለች። ስትመጣ ድክም እንዳላት ታስታውቃለች። "እንኳን ጠራኸኝ" አለችው ስታገኘው።

"ለምን?" አላት እቅፍ አድርጎ እየሳማት።

"የቤቱ ሥራ አላልቅ ብሎ ጊዜውን ሁሉ ወሰደብኝ" አለችው ቁና ቁና እየተነፈሰች።

"ወገኛ ይህን ጊዜ ቤት ጠርገሽ ይሆናል" አላት እየሸፈ።

የሠራችውን ደረደረችለት፤ አሁንም ድካሟ አልወጣላትም። ኬኔሩ ላይብረሪ ሊገቡ ደረጃውን መውጣት ጀምረው ነበር። ድንገት ከክንዱ ሸርተት አለችበት፤ መጽሐፍና ደብተሩን ወርውሮ ደገፈና ወደጥላ ስር ወሰዳት። ደጋግሞ ቢጠራትም ልትመልስለት አልቻለችም። ግንባሯ ላይ ላብ ችፍፍ ብሏል፤ ከንፈሮቿ ከፊት ብለዋል። በአቅራቢያው ያሉ ሁሉ ተሰባሰቡ። ታረቀኝ የሚይዝና የሚጨብጠውን አጣ፤ ከልጆቹ ጋር ተረዳድተው ተሸክመው ወደ ተማሪዎች ክሊኒክ ወሰዷት። ያን ዕለት ፍሬሕይወት ምርመራ ክፍል በቆየችበት አጭር ጊዜ የቱን ያህል እንደተጨነቀና እንዳዘነ ሲያስበው ይገርመዋል።

ተፈናጥሮ ከአልጋው ላይ ወረደና ያወለቀውን ልብሱን ለበሰ። ፍራሽ ላይ ተቀምጠው የሚያጠኑት ጓደኞቹ ደነገጡ። "አጅሬው ሶስት ሰዓት ሆኖአል" አለው አንደኛው።

"አውቄአለሁ" አለ ታረቀኝ በተረጋጋ አነደበት።

* * * *

ያ ማታ ሮቤል አክስታቸው ቤት ሄዶ ለብቻዋ ማደር የነበረባት ጊዜ ነው፡፡ ደብሯታል፤ ፈታደም ናፍቋታል። ማጥናት ሞክረችና አልሆን ሲላት ሁሉንም አስቀምጣ ሶፋው ላይ ጋደም አልችና ከሀሳቧ ጋር መጫወት ያዘች። ሁልጊዜም እንዲህ ዓይነት ሃሳብ ውስጥ ላለመግባት ጥረት ታደርጋለች ከገባች መውጫ እንደሌላት ስለምታውቀው በጣም ትጠነቀቃለች። ያን ዕለት ግን ተሸነፈች፤ እናቷን፣ ወንድሟንና እህቷን፣ አንተነህንና በላይን፣ አነቅዱስንና አስቻለውን፣ ዘርዓይንና ጋዲሳን፤ እመቤትን፣... ሁሉንም እያስታወሰች በሀሳብ ባሕር ውስጥ ገብታ ስትንቦጫረቅ ስንት ሰዓት እንኳን እንደሆነ ሳታውቀው ነጎደ።

ድንገት በሩ ሲንኳኳ ከተኛችበት ዘላ ተነሳችና "ማነው?" አለች። "እኔ ነኝ" አላት ያንኳኳው ሰው። ጆሮዋን ማመን አቃታት፡፡ በፍጹም ሊሆን አይችልም! "ማነው?" አለች እንደገና፤ መቼም በድጋሚ የሰማችውን ድምጽ መጠራጠር አትችልም። እናም በሩን ከፈተችለት። ከከፈተች በኋላ ነው ሰዓት የተመለከተችው፤ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ይላል።

"እንዴት ልትመጣ ቻልክ?" አለች ሰላም ከማለቷ በፊት። በሩን ዘጋችው።

"ማጥናት እኮ አልቻልኩም ፍርዬ!" አላት ቅዝዝ እንዳለ።

የምትናገረው ጠፋት ምን እንደምትለው ግራ ገባት። "ታዲያ እዚህ ማጥናት ይቻላል?"

"ግራ ስለገባኝ ብቻ ነው"

"እሺ አሁን እንዴት ይሁን?"

"ትንሽ ለማጥናት እንሞክርና ከዛ እንተኛለን"

"ትቀልዳለህ ታረቀኝ! እንዴት ነው እዚህ ቤት እኔና አንተ ብቻ የምናድረው?"

"እንደምወድሽ ታውቂያለሽ አይደል? ለሚወዱት ሰው የሚገባ ቃል አይታጠፍም፤ ለዚህ ቃል እገባልሻለሁ፤ ታምኚኛለሽ?" አላት ኩስተር ብሎ።

"እሺ አንተንስ ልመንህ ሰው ምን ይላል?"

"ለዚህ እንኳን አያገባኝም" በጣም ተኮሳተረ።

ለተወሰኑ ሰዓታት አጠኑ፤ በመሀሉ ደግሞ ወሬያቸውን ሲያወሩ ቆዩ፤ ከዛ እንደገና ለማጥናት ሞከሩ። ፍሬ ብዙ መቆየት አልቻለችም፡፡

"እኔ ልተኛ ነው" አለች ዐይኖቿን እያሻሸች።

"ተኚ" አላት በቀላሉ።

"አንተ ሮቤል አልጋ ላይ ትተኛለህ" አለችው እየተነሳች።

"እዚሁም ቢሆን ልተኛ እችላለሁ" አለ ሶፋውን እያመለከታት።

"አልጋው ይሻልሃል፤ ደህና እደር" አለችው።

"ደህና እደሪ፤ መልካም እንቅልፍ"

"ትቼህ በመተኛቴ ይቅርታ" አለች ቆም ብላ።

"ምንም ችግር የለበትም" አላት።

ጋደም ስትል እንቅልፍ ወሰዳት፡፡ የነቃችው አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን ነው። ጥቂት ስትቆይ ማታ ታረቀኝ መጥቶ እንደነበረ ትዝ አላት፡፡ የመብራት ጭላንጭል ተመለከተችና ተነስታ ወደ ሳሎን ሄደች።

"አልተኛሁም እንዳትለኝ ብቻ"

"ሞክሬ ነበር አልቻልኩም"

"ሀሳብ የሌለው ሰው ሆንኩብህ አይደል?" አለች ራሷን እየታዘበች።

"በምኑ ነው ሀሳብ የሌለሽ?"

"አንተ ቁጭ ብለህ ተዝናንቼ መተኛቴስ?"



"አመንሽኝ ኃላፊነቱን ሁሉ ለኔው ተውሽው፤ እናም እንቅልፍ ወሰደሽ፤ ይህ ደግሞ ፍቅር ምን እንደሆነ ማወቅሽን ነው የገለጸልኝ። በፈቃደ ቀናሁበት" አለ ከልቡ መሆኑን በሚገልጽ ሁኔታ።

* * * *

ሚስጥረ በጠዋት ተነስታ ዳኙን ቀሰቀሰችው፤ ለምን እንደምትቀሰቅሰው ገብቶታል።

"እባክሽን አንቺ ሂጂ" አላት ዳኙ አንሶላና ብርድልብሱን ወደ ግርጌው እየገፋ።

"ምነው ዳኙ ማታ ተነጋግረን፤ እኔ መደበኛ ሥራዬን እንደምሠራ አይደል የተስማማነው" አለችው ሚስጥረ እመኝታ ቤቱ በር ላይ እንደቆመች።

"የአንቺን ሥራ እኔ እሸፍናለሁ፤ ሰው መቅጠሬን ረስቼው ነበር ማታ" አላት።

በሀሳቡ ተስማማችና ሚስጥረ ወደአትክልት ተራ ሄደች። ዳኙ ሌሊቱን ጥሩ እንቅልፍ አልወሰደውም፤ የሰማው ሆነ ያነበበው ነገር ሲገርመውም ሲያናድደውም ነው ያደረው። ምግብ ቤት ውስጥ ረስተውት የወጡትን ፖስታ ሚስጥረ ሳትገባ በፊት ማንሳት አለበት። ሚስጥረ እንደወጣች ወዲያውኑ ነው ወደ ሥራ ቦታ የሄደው።

ሚስጥረና ዳኙ መሀል አራት ኪሎ ምግብ ቤት ከፍተዋል፤ ምግብ ቤታቸው በጣም ከመለመዱ የተነሳ በምሳ ሰዓት ቦታ እስከሚጠፋ ድረስ ነው ደንበኞች ያሉት። ገበያውን ለመያዝ እንዲችሉ ከጎናቸው ያለውንም ክፍል እንዲጨምሩላቸው ባለቤቶቹን ጠይቀው ቤቱን ቀላቅለው ትልቅ የምግብ አዳራሽ ለመክፈት ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል።

ዳኙ የምግብ አዳራሹን ለማሠራት ዕቅድ ሲነድፍ ሞላ ትዝ አለው። ሞላ እስር ቤት አብሮት የነበረ አናጺ ነው፤ እናም ሊያማክረው ፈለገና

ለተወሰኑ ሰዓታት አጠኑ፤ በመሀሉ ደግሞ ወሬያቸውን ሲያወሩ ቆዩ፤ ከዛ እንደገና ለማጥናት ሞከሩ። ፍሬ ብዙ መቆየት አልቻለችም፡፡

"እኔ ልተኛ ነው" አለች ዐይኖቿን እያሻሸች።

"ተኚ" አላት በቀላሉ።

"አንተ ሮቤል አልጋ ላይ ትተኛለህ" አለችው እየተነሳች።

"እዚሁም ቢሆን ልተኛ እችላለሁ" አለ ሶፋውን እያመለከታት።

"አልጋው ይሻልሃል፤ ደህና እደር" አለችው።

"ደህና እደሪ፤ መልካም እንቅልፍ"

"ትቼህ በመተኛቴ ይቅርታ" አለች ቆም ብላ።

"ምንም ችግር የለበትም" አላት።

ጋደም ስትል እንቅልፍ ወሰዳት፡፡ የነቃችው አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን ነው። ጥቂት ስትቆይ ማታ ታረቀኝ መጥቶ እንደነበረ ትዝ አላት፡፡ የመብራት ጭላንጭል ተመለከተችና ተነስታ ወደ ሳሎን ሄደች።

"አልተኛህም እንዳትለኝ ብቻ"

"ሞክሬ ነበር አልቻልኩም"

"ሀሳብ የሌለው ሰው ሆንኩብህ አይደል?" አለች ራሷን እየታዘበች።

"በምኑ ነው ሀሳብ የሌለሽ?"

"አንተ ቁጭ ብለህ ተዝናንቼ መተኛቴስ?"



"አመንሽኝ ኃላፊነቱን ሁሉ ለኔው ተውሽው፤ እናም እንቅልፍ ወሰደሽ፤ ይህ ደግሞ ፍቅር ምን እንደሆነ ማወቅሽን ነው የገለጸልኝ። በፈቃደ ቀናሁበት" አለ ከልቡ መሆኑን በሚገልጽ ሁኔታ።

* * * *

ሚስጥረ በጠዋት ተነስታ ዳኙን ቀሰቀሰችው፤ ለምን እንደምትቀሰቅሰው ገብቶታል።

"እባክሽን አንቺ ሂጂ" አላት ዳኙ አንሶላና ብርድልብሱን ወደ ግርጌው እየገፋ።

"ምነው ዳኙ ማታ ተነጋግረን፤ እኔ መደበኛ ሥራዬን እንደምሠራ አይደል የተስማማነው" አለችው ሚስጥረ እመኝታ ቤቱ በር ላይ እንደቆመች።

"የአንቺን ሥራ እኔ እሸፍናለሁ፤ ሰው መቅጠሬን ረስቼው ነበር ማታ" አላት።

በሀሳቡ ተስማማችና ሚስጥረ ወደአትክልት ተራ ሄደች። ዳኙ ሌሊቱን ጥሩ እንቅልፍ አልወሰደውም፤ የሰማው ሆነ ያነበበው ነገር ሲገርመውም ሲያናድደውም ነው ያደረው። ምግብ ቤት ውስጥ ረስተውት የወጡትን ፖስታ ሚስጥረ ሳትገባ በፊት ማንሳት አለበት። ሚስጥረ እንደወጣች ወዲያውኑ ነው ወደ ሥራ ቦታ የሄደው።

ሚስጥረና ዳኙ መሀል አራት ኪሎ ምግብ ቤት ከፍተዋል፤ ምግብ ቤታቸው በጣም ከመለመዱ የተነሳ በምሳ ሰዓት ቦታ እስከሚጠፋ ድረስ ነው ደንበኞች ያሉት። ገበያውን ለመያዝ እንዲችሉ ከጎናቸው ያለውንም ክፍል እንዲጨምሩላቸው ባለቤቶቹን ጠይቀው ቤቱን ቀላቅለው ትልቅ የምግብ አዳራሽ ለመክፈት ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል።

ዳኙ የምግብ አዳራሹን ለማሠራት ዕቅድ ሲነድፍ ሞላ ትዝ አለው። ሞላ እስር ቤት አብሮት የነበረ እናጺ ነው፤ እናም ሊያማክረው ፈለገና

ደወለለት። ሞላ ወዲያውኑ ነበር የመጣው። ስለቤቱ ተነጋግረው ሲያበቁ የዱሮ ወሬ ጀመሩና ብዙ ተጫወቱ።

"እኔ መችም እንደፈቃደ ዕድለኛ ሰው ያለ አይመስለኝም" አለ ሞላ በጨዋታቸው መሀል።

"በእርግጥ ሁላችንም ዕድለኞች ነን" አለው ዳኙ።

"ስልሀ ፈቃደ መዝናናት ይወዳል ይሳካለታልም" አለ ሞላ።
"ማለት? አልገባኝም" አለ ዳኙ ግራ ገብቶት።

"የጻፈልኝን ደብዳቤ ብታየው ሊገባህ ይችላል" አለና ከኪሱ ደብዳቤ አወጣና አስነበበው። በደብዳቤው ላይ ያልተጻፈ ነገር የለም።

"... ኑሮው በጣም ጥሩ ነው፤ እዚህ እስካለሁበት ድርስ በሚገባ ተደስቼ መመለስ እፈልጋለሁ። ስለዚህም መጠጣት፤ መጨፈርና ከሴቶቹ ጋር መደሰት ሆኗል ሥራዬ። ሴቶቹ እንዴት አሪፎች እንደሆኑ ልነግርህ አልችልም፤ ከእኛ ሴቶች ጋር ሳነጻጽራቸው ልዩነታቸው ያገርመኛል፤ ተደስተው በማስደሰት የተካኑ ናቸው። በአንድ ጊዜ ነው ፍቅር የሚያስይዙህ፤ አንዳንዴ እዚሁ እንዳያስቀሩኝ እሰጋለሁ..." የሚል አነበበና ገረመው።

ሞላ ደግሞ ስለፈቃደ የሚያወራው በተመስጦ ነው፤ ከደብዳቤው የበለጠ ከፈቃደ ጋር በስልክ ስላወሩት ነገር ለዳኙ ተረከለት። ዳኙና ሞላ ለረጅም ጊዜ ነበር ያወሩት። በወሬ ተጠምደው ደብዳቤውን እዛው ቦታ ረስተውት መውጣታቸውን ያስታወሱት ከራቁ በኋላ ነበረ። ዳኙ ደብዳቤውን እንዲያስቀምጥለት ነግሮት ሄደ ሞላ።

ከሞላ ከተለየ በኋላ ዳኙ ለብቻው ብዙ አሰቦበታል። "እነፈቃደ ሴቶቹ ተመሳሳይ ነገር ቢፈጽሙ ይቀበሉት ይሆን?" አለና ራሱን ጠየቀ። ይህንን ነገር ለሚስጥረ በመንገርና ባለመንገር መሀል መወሰን አቅቶታል። ለማንኛውም ደብዳቤውን ማየት የለባትም፤ ስለዚህ ነው ቀድሟት ወደምግብ ቤት ለመሄድ የፈለገው።



ምግብ ቤቱን ከፋፈተና ወረቀቱን ከተቀመጠበት አንስቶ ኪሱ ከተተ። ሌሎቹ ሠራተኞች ከመግባታቸው በፊት ሚስጥረ ልትሠራ አስባ የነበሩትን ሥራዎች መስራት ጀመረ። የሚስጥረ አሳብ ሁልጊዜም ይገርመዋል። "ሠራተኞቹ ሲገቡ ሁሉም ነገር ንጹሕ ሆኖ ሊያገኙት ይገባል" ትላለች።

"የተቀጠሩት ሊሠሩ አይደለም? እነርሱ ለምን አያጸዱትም?" ብሎ ጠየቃት አንድ ቀን።

"ሁሉም የሥራ ድርሻ አለው፤ ማታ ስለሚመሽ አጽድቶ ለመውጣት አይቻልም። ጠዋት ሲገቡ ደግሞ ለቁርስ የሚመጣው ሰው ወዲያውኑ ነው የሚሞላው፤ እናም በደንብ አጽድቶ ሥራ መጀመር አያመችም። ለዚህ ደግሞ የሥራ ድርሻው ጽዳቱን መሥራት የሆነና ሌሊት ሊገባ የሚችል ሰው ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ አልተቻለም፤ ስለዚህም ይህን ሥራ እኔ ወሰድኩ። የምፈልገውን የንጽሕና ደረጃ ደግሞ እኔ ሠርቼ ካላሳየሁ እነርሱ እንዲያደርጉት መጠየቅ ይከብደኛል" አለችው።

የሀሳቧን ትክክለኛነት ተመልክቷል። ቤቱ ሙሉ ቀን ንጹሕ እንደሆነ የሚውለው በዚህ ምክንያት መሆኑን አውቋል።

ዳኙ ሚስጥረ የምትሠራውን ሥራ በሙሉ አከናወነና ቆም ብሎ ተመለከተ። "በትክክል ተሠርቷል" አለና ለራሱ አረጋገጠ።

ሚስጥረ ስትመጣ በአድናቆት ተመለከተችው። "ለዚህ እኮ ነው ዕድለኛ ነኝ የምልህ፤ እኔም እንደዚህ አጽድቼው አላውቅም" አለችና አድናቆቷን ገለጸችለት።

"ሁለታችንም ዕድለኞች ነን!" አላት።

* * * *

ፍሬሕይወት ማታ ከትምህርት ቤት ስትመለስ ሮቤል ቀድሟት ገብቶ አገኘችው። ወትሮውንም ሰላምታቸው ሞቅ ያለ ነው፡፡ ያን ዕለት ግን ለየት አለባት። ገጽታውን ስታየው የተመሰቃቀለ ስሜት ተመለከተች፤

"ምን ሆነሃል ሮቢ?" አለችው። መልስ አልሰጣትም የሆነ ወረቀት ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠላትና "ተመልከችው" አላት፤ ፊቷን ለማየት አቅም ማጣቱ ያስታውቃል።

ወረቀቱን አንስታ ተመለከተች እያገላበጠች አነበበችው፤ እያነበበች መንፈሷ መረበሽ ጀመረባት። ቀና ብላ ቤታቸውን በዐይኖቿ ቃኘችው በጆሮዎቿ አዳመጠችው፤ ጭርታው የከፋ ሆነባት። ለአፍታ ያህል አባታቸው በሕይወት እያሉ ቤታቸው እንዴት እንደነበረ ከአባታቸው ሞት በኋላ፤ ከዘመቻ ስትመለስ፣ በትግሉ ወቅት፣ ከእስር በኋላ፣ ከእናታቸው ህመምና ሞት በኋላ፣... ከዚህ በላይ መሄድ አልቻለችም።

ሕይወትን ከሮቤል መሄድ በኋላ ስታስበው ስለሚያቅታት ነበር ወደ ውጭ ለመሄድ ለሚያደርገው ጥረት ጆሮ ዳባ ልበስ ያለችው። አክስታቸው ኑኑ ሮቤልን እንድትወስድ የጀመረችውን ጥረት ለመቃወምም አቅም አልነበራትም፡፡ የእርሷን በጎ ሀሳብ ላለማደናቀፍና በተለይም ሮቤል ለመሄድ የነበረውን ፍላጎት ስታስተውል ጥረቱን መቃወም አልቻለችም። እንዲህ በአጭር ጊዜ ይሳካል ብላም አልጠበቀችም፡፡ ምን ደረሰ እያለች መከታተልም መሄዱን የተቀበለች መሆኗን እንዳያስረዳ ስለምትሰጋ አላደረገችውም፤ ሮቤልም ስሜቷ ስለሚገባው ሂደቱን በየጊዜው አልነገራትም።

ዛሬ ግን ግድ ሆነባት፡፡ ዐይኖቿን ማየት እንኳ አቅቶት ወረቀቱን እፊቷ አስቀምጦላት ገባ። አሁን መበርታት ያለባት እርሷ ናት፡፡ እናም ቀስ ብላ ወለሉ ላይ ተንበረከከች ምንም እንኳ በእናቷ ህመምና ሞት ስትጨነቅ ለመፀለይ ሙከራ ያደረገችባቸው ጊዜያት ቢኖሩም ከሰባት ዓመታት በኋላ እጅግ በጣም በተሰበረ ልብ ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ወደቀች። ሕይወትን ልቋቋም የምትችልበትን ኀይል እንዲሰጣት ተማፀነችው። ያለችበትን እስከምትዘነጋ ድረስ ለደቂቃዎች ያህል በመንፈስ ኮበለለች። ከዛ ስትነሳ የተረጋጋች መሰላት፡፡ ሮቢን ልታናግረው ኃይል ያላት ሆኖ ተሰማት፤ እናም ወደመኝታ ቤት ገባች።

መኝታ ቤት ስትገባ ሮቤል ትራሱን እራሱ ላይ ጭኖ በደረቱ ተኝቷል፡፡ እንቅልፍ የወሰደው መሰላት ጥቂት ቆም ብላ ተመለከተችው ሰውነቱ ይንቃንቃል እያለቀሰ መሆኑ ገባት።



"ሮቢ!" አለችው ድምጿን ለማረጋጋት እየጣረች አልመለሰላትም። ደግማ ጠራችው አሁንም ስቅስቅታው ጨመረ እንጂ አልመለሰላትም።

"ሮቢ! እህትህ እንድትኖር ትፈልጋለህ?" አለችው በጠንካራ አንደበት። ከመቅጽበት ብድግ አለና ተመለከታት

"ምን ዓይነት ጥያቄ ነው እቴት?" አለ። ዐይኖቹ ቀልተው አብጠዋል።

"እንግዲህ ከአንተ ሌላ ማን አለኝ ሮብ? የቱን ያህል እንደምወድህስ ታውቀው የለ..." አቋረጣት ሮቤል።

"አዎ እቴትዬ ይህንን ሳስበው እኮ ነው የተሰማኝ፡፡ ይቅር በይኝ እቴትዬ፤ በቃ እቀራለሁ አንቺን ትቼሽ በፍፁም አልሄድም።" አለና አንገቷ ላይ ተጠምጥሞ አለቀሰ።

"ሀሳቤና ሀሳብህ አልተገጣጠሙም ሮቢ የኔ ሀሳብ ካንተ በጣም የተለየ ነው። እህትህ እንድትኖር ከፈለግህ ላታባባት እንድትሞክር ነው የምጠይቅህ። ያገኘኸውን ዕድል እንድትጠቀምበት እፈልጋለሁ ይህን ለማድረግ ግን ሁለታችንም መጠንከር ያስፈልገናል። ከዚህ በኋላ ስታለቅስና ስትተክዝ ማየት አልፈልግም፤ እኔም እንደዚያ አላደርግም። ለዚህ አሁኑኑ ቃል ግባልኝ" አለችው።
የሮቤል እንባ አቆመና በምትኩ ገጽታውን መደነቅ ዋጠው፡፡ በፍጹም የጠበቀው አልነበረም። ከዛ በኋላ ለብዙ ሰዓት ተነጋገረው ሮቤል ዳግም ስለመቅረት እንደማያስብ ቃል እንዲገባላት አደረገችው።

የሮቤል ጉዞ ፈጣን ነበር፡፡ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ መብረር ነበረበት። አንድ ቀን ለሮቤል መገዛት ያለባቸውን ነገሮች ገዝዝተው ተመለሱና ማውራት ጀመሩ፡፡ ለመሄጃው የቀሩት ሦስት ቀናት ብቻ ነበሩ።

"እቴትዬ አንድ ነገር ብጠይቅሽ ትቀየሚኛለሽ?" አላት።

“ለምንድነው የምቀየምህ ይልቁንስ የምቀየምህ ልትጠይቀኝ ሲገባህ ሳትጠይቀኝ ከሄድክ ነው” አለችው ሊነግራት ያሰበውን ነገር ለመገመት እየሞከረች።

“ታረቀኝን አትወጂውም?” አለና ዐይኖቿን እንዳያይ ማዶ ማዶ ማየት ጀመረ። እንደእውነቱ እርሷም በጥያቄው በጣም ደንግጣለች። ሮቤልን ስምንት ዓመታት ትበልጠዋለች፤ ገና የአስራ አራት ዓመት ልጅ ነው።

“ለምን ጠየቅከኝ” አለችው ተረጋግታ።

“እንድትዋደዱ ስለምፈልግ። እኔ ታረቀኝን በጣም እወደዋለሁ፤ ደግሞም በጣም ጥሩ ሰው ነው” አለና ድንገት በዝምታ ተዋጠ።

“እወደዋለሁ ሮቢ!” አለችና ከዝምታው መለሰችው።

“እርሱም በጣም ይወድሻል”

“ደግሞ ይሄንን በምን አወቅህ?” አለች እየገረማት።

“ነግሮኛል፤ በጣም እንደሚወድሽና ጥሩ ሰው በመሆንሽ እንደወደደሽ፤ እህቴ በመሆንሽ እድለኛ መሆኔንም ነግሮኛል” አላት ሮቤል።

ሮቤልን እናት ሆና ወደአሜሪካ የምትወስደው ኑኑ የአክስታቸው ልጅ ናት። ላለማልቀስ የገባችለትን ቃል ለመጠበቅ ከራሷ ጋር ባደረገችው ትግል ዕንባዋን ሳታሳየው ሸኘችው። ሁሉንም ሸኝዎች ጥቂት መቆየት እንደምትፈልግ ነግራ ተሰናበተቻቸው፡፡ የበላይሁን እናት ግን ለመሄድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው አብረዋት ቆዩ።

ብቻዋን ስትሆን ታምቆ የነበረ ዕንባዋ እየገነፈለ መንታ መንታ እየሆነ ቁልቁል በጉንጮቿ ላይ ተሽቀዳደመ። የበላይሁን እናት አልከለከሏትም፤ እስከሚበቃት እንድታለቅስ ተዋት፤ እርሳቸውም በሆዳቸው ውስጥ የተቀበረውን ሀዘናቸውን የእርሷ ለቅሶ እየኮረኮረው ሳግ እየተናነቃቸው አለቀሱ። ከእርሳቸው ለቅሶ ባሻገር ቃለአብንና



በላይሁንን እንዲሁም ሌሎቹን ሁሉ እያስታወሰች እምቅ ብሶቷንና ናፍቆቷን በእንባዋ አጠበችው።

ሮቤልን የያዘው አውሮፕላን የበረራ ሰዓት ደርሶ አውሮፕላኑ የቦሌን ምድር እስኪለቅ አልተንቀሳቀሱም፡፡ ሰዓቱ ሲያልፍ መረጃ ጠይቀው መሄዱን ሲያረጋግጡ ፍሬና የበላይሁን እናት ወደቤታቸው መመለስ ግዴታቸው በመሆኑ ብቻ ቦሌን ለቀቁ። ቤት ሲገቡ የበላይሁን እናት ቡና እንድትጠጣ ቢጋብዟትም ጥቂት ማረፍ እንደምትፈልግ ነግራቸው ወደቤት ገባች።

* * * *

ስድስት ወራት የስድስት ቀናት ያህል ፈጥነው አለቁበት። በተለይ በመጨረሻዎቹ ቀናት በርካታ ቀጠሮዎች ተደራረቡበት። በኮርሱ ላይ የነበሩት ተሳታፊዎች ልዩ የአዳር ዝግጅት ጋብዘውታል። ሁለቱ አውሮፓውያን ሴት ጓደኞቹ ፋታ ሊሰጡት አልቻሉም። ዝብርቅርቅ ብሎበት ነበር። መደዳውን ሶስት ቀናት ጭፈራ አድሮ በአራተኛው ቀን ተዝለፍልፎ አልጋው ላይ የመውድቅ ያህል ነው የተጋደመው።

ስልኩ ሲጠራ ቢሰማውም ሊያነሳው ግን አልቻለም፤ ከዚያ በኋላ ሳይሰማው ስንት ጊዜ እንደተደወለ አያውቅም፤ የሚያውቀው ለረጅም ሰዓታት መተኛቱን ነው። እንቅልፉን ጨርሶ ሲነቃ ቀኑና ሰዓቱ ተደነጋግሮት ነበር። ለማንኛውም ብሎ ሻንጣውን ማዘጋጀት ጀመረ። ልብሶቹን ከቶ ሳይጨርስ ስልኩ አንቃጨለ። አነሳውና “ሄሎ” አለ።

“ሀይ! አሁንስ ተገኘህ፤ ለመሆኑ ይህን ሁሉ ጊዜ የት ነበርክ?” አለችው ከወዲያኛው ጫፍ ያለችው ሴት።

“ተኝቼ ነበር” አላት በቀላሉ።

“መምጣት እችላለሁ?” አለችው።

“እንዴ በሚገባ እንጂ” አላት

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የክፍሉ ደወል ተደወለና በሩን ከፈተላት። ገብታ ተንጠለጠለችበት፤ እስኪሰለቸው ድረስ ሳመችው። ያመጣችለትን ስጦታ ሰጠችው። አመስግኖ ተቀበላት። ሻንጣውን እያገዘችው አዘጋጅና ጨረሰ።

"ለጓደኛዬ ስጦታ ልታጋሪኝ ትችያለሽ?" አላት

"አሳምሬ!" አለችውና ተነሳች። ፍሬን ያስደስታታል ያለውን ስጦታ ገዝተው ተመለሱ። ወደቤቷ አልሄደችም "ለመጨረሻ ጊዜ አብሬህ ማደር እፈልጋለሁ" አለችው።

"አሁን ያችኛዋ ብትሆን ምን አደርግ ነበር?" አለ ለራሱ፤ እርሷ በዕድሜ የምትበልጠው ትልቅ ሴት ነች፤ ቁጭ ብሎ ማውራት ነው የሚያስደስታት። ሁለቱ ሴቶች በምንም አይገናኙም። ይህችኛዋ በጣም ወጣት ነች፤ መዝናናት በጣም ትወዳለች። ሁለቱም በጣም እንደሚወዱት ይነግሩታል፤ አብረው እንዲሆኑ ይጠይቁታል። አብረው በቆዩበት ጊዜ ውስጥ በተቻለው መጠን ሁለቱንም ለማስደሰት ሞክሯል። ከሁለቱም ጋር ግንኙነት ሲመሰርት የተለመደውን አመለካከቱን ምክንያት በማድርግ ነው።

በመጀመሪያ የተገናኙት ከወጣቷ ጋር ነበር፤ ሀሉ ነገሯ አስደሰተው። ለተወሰኑ ሳምንታት አብረው ሲወጡ ሁሉን ነገር አስረስታ አዘናጋችው። እንዲያውም ሳያገኛት ሲቀር ትናፍቀው ጀመር፤ እናም ስጋት ያዘው። ግንኙነታቸው ከጊዜያዊነት ማለፍ እንደሌለበት ወሰነ። ለሕይወት ጓደኛ ልትሆነው የምትችል ሰው ፍሬ ብቻ መሆኗን አምኗል፤ እርሷን ሊለውጥ የሚችል ሰው አይፈልግም። ያለውን ግንኙነት ለመቀነስ በማሰብ ከሌላ ሴት ጋር መውጣት ጀመረ፤ ከትልቋ ሴት ጋር። እንዳሰበውም ሆነለት፤ ሊያገኝ የሚገባውን እር ካታ ሳያጓድል ሊፈጠር የነበረውን አደጋ አስቀርቷል። ተደሰተ።

የማደር ጥያቄዋን አልተቃወማትም፤ እንዲያውም ደስ አለው። በአውሮፓ የሚያደርገውን የመጨረሻ አዳር ተደስቶ ማሳለፍ ይፈልጋል። አብረው አድረው አውሮፕላን ጣቢያ ድረስ ሸኘችው፤ ለመጨረሻ ሲለያዩ እንባዋ ሲመጣባት ገረመው "ኢትዮጵያ እመጣለሁ" አለችው።



አውሮፕላን ላይ ሆኖ ትቷት ስለመጣው ፈረንጅ ማሰብ አልፈለገም። ፍሬሕይወትን አሰባት፤ በጣም ናፈቀችው። አዲስ አበባ ሲደርስ የመጀመሪያ ሥራው ፍሬሕይወትን ማግኘት ነው የሚሆነው። የፍሬሕይወት ፍቅር ልዩ ነው፤ ለፍቅር የምትሰጠው ግምት ያስደንቀዋል፤ ቃል አክባሪነቷን ይወደዋል። ሁል ጊዜ ግን ይሰጋል፤ ፍሬ አንድ ቀን እንኳ ወደሌላ ወንድ ከሄደች የምትመለስ አይመስለውም፤ ሊያጣት ደግሞ አይፈልግም። ለእርሱ ግን ከሌላ ሴት ጋር መሆን ምንም ማለት አይደለም፤ አብሯቸው የሚሆነው ለጊዜው ብቻ መሆኑን ነው የሚያስበው፤ ያም ሆኖ ግን አንዳንድ ጊዜ ጠንከር ያለ ግንኙነት ውስጥ የገባ ሲመስለው ፍሬሕይወትን ያስብና ወዲያውኑ ያቋርጣል።

አዲስ አበባ ሲገባ ከቀኑ አስር ሰዓት ነው፤ ከአውሮፕላን ማረፊያው ሲወጣ ማንም ይጠብቀኛል ብሎ ስላልገመተ ወደቤቱ የሚያደርሰው ታክሲ ብቻ ነበር የሚፈልገው።

"እባክህን ሰላም በለኝ" አለችው ፍሬሕይወት ሳያስበው። ፈቃደ በድንጋጤ ጋሪውን ገፈተረውና ወደእርሷ ዞረ። እንዴት አቅፎ ከመሬት እንዳነሳት አላወቀውም፤ በአካባቢው ያሉ ሰዎች እስኪገርማቸው ድረስ አሽከረከራት።

"እሺ. በድንጋጤ ብሞትስ?" አላት ትንሽ ሲረጋጋ። የልቡን ምት በእጇ እንድታየው እጇን ደረቱ ላይ አስደገፈው። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ማለቱን አላቆም አለው።

"በፍጹም ትመጪለሽ ብዬ አላሰብኩም፤ እቤት ደርሼ ስልክ እስክምደውል ቸኩዬ ነበር" አላት ጥብቅ አድርጎ እያቀፋት።

"አስችሎኝ የምቀር ይመስልሃል? ላይህ እንዴት እንደጓጓሁ አላወቅህም ማለት ነው። እወድሀለሁኮ' ፈቃደ" አለችው እርሷም ዐይን ዐይኑን እያየችው።

"መቼም የኔን ያህል አይሆንም" አላት።

ሻንጠው ታክሲ ላይ ተጫነና ሾፌሩ ሲገባ "መቼ ነው የምንገናኘው?" አለችው።

"እቤት አብረን እንሂድ እንጂ" አላት ፈቃደ እጇን ይዞ።

"እቤት እንኳን አልሄድም፤ ማታ ደውልልኝ" አለችው።

"እቤትሽ እናድርስሽ" አላት ደግሞ።

"እቤት አልሄድም እዚሁ አካባቢ ከሰው ጋር ቀጠሮ አለኝ" አለችው። በጣም እየከፋው ስሟት ታክሲው ውስጥ ገባ።

ፍሬ የፈቃደን የፍቅር አገላለጽ በጣም ትወደዋለች፤ አይሰለትም። ታክሲው ከአጠገቧ እስኪርቅ ድርስ በዐይኗ ተከተለችው፤ እጆቿንም አወዛወዘችለት።

በእርግጥ ቀጠሮ አልነበራትም፤ ታክሲው ውስጥ አብራው ከገባች እቤት እንድትሄድ ሊያሳምናት እንደሚችል አስባ ነው። እቤቱ ደግሞ መሔድ አትፈልግም። ታክሲ ያዘችና ወደቤቷ ሄደች።

አንድ ሰዓት ሲሆን ፈቃደ ደወለላት፤ እየጠበቀችው ነበር። "ፍሬ ጨካኝ ነሽ!" አላት ስልኩን ስታነሳው።

"ጨካኝ ነኝ ብዬ ገምቼ አላውቅም" አለችው እየሳቀች።

"አልናፈቅሁሽም ማለት ነው?"

"መናፈቄን እንዴት አድርጌ እንደማሳይህ አላውቅም። ልቀበልህ የመጣሁት ስለናፈቅከኝ መሰለኝ"

"በጣም እንደምወድሽ ግን ታውቂያለሽ?" አላት ፈቃደ

"መመዘን የሚቻል ቢሆን የማናችን እንደሚበልጥ ማየት እንችል ነበር። እንደኔ ግን እንደማትሆን እርግጠኛ ነኝ" አለችው አጸፋውን ለመመለስ።



"ነገ የት ነሽ?"

"ከሰዓት በኋላ ትምህርት አለኝ"

"እንግዲያው ጠዋት ሶስት ሰዓት ቤት እመጣለሁ"

"ሰዓቱ እስከሚደርስ እቸኩላለሁ"

"እወድሻለሁ! ደህና እደሪልኝ"

"በሰላም ያገናኘን" አለችውና ስልኩን ዘጋችው።

እንቅልፍ እስኪወስዳት ድረስ ስለፈቃደ ስታስብ ነው ያመሸችው፤ ካየችው በኋላ ደግሞ የበለጠ ናፈቃት። ስለፈቃደ ይህን ያህል በማሰቧ ደስ አላት፤ እስከምታገኘው መቸኮሏ ተፈጥሮአዊ ነው፤ ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ ለእርሱ ያላት ፍቅር በመሆኑ ማፍቀሯን ወደደችው። እስከሕይወቷ ፍጻሜ ድረስም እንደምታፈቅረው እርግጠኛ ነች።

ድንገት እነዚያ ቃላት በአእምሮዋ ውስጥ ሲመጡ ስሜቷን አበላሹባትና ተናደደች። "ፍርዬ የለም!" የሚረብሻት አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ፈቃደ በእርሷ ላይ ያለውን እምነት ያጎድለው ይሆናል ብላ ማሰቧ!

ፈቃደ ከእርሷ በፊት ከሴቶች ጋር ግንኙነት እንደነበረው ታውቃለች ከእርሷ ጋር ከሆነ ወዲህ ግን የእርሷ ብቻ መሆኑን በሙሉ ልቧ ነው የምታምነው። እርሱም እንዲያምናት ትፈልጋለች። ግን ምክንያቱን ያላወቀችው ነገር ታማኝነቷን ያሳጣት መሰላት። "ምነው ልጃገረድ ነኝ ባላልኩት ኖሮ" ትላለች ሁልጊዜም ያንን ዕለት ስታስታውስ።

ድንገት ስልኩ ጮኸና አስደነገጣት፤ አነሳችና "ሄሎ" አለች።

"ምነው ፍሬ ዛሬ ጠፍተሽ ዋልሽ?" አላት

“ውይ ታረቀኝ እንደምን ዋልክ? ፈቃደ እንደሚመጣ ነግሬህ አልነበረም” አለችው።

“እና እርሱ ከመጣ ትምህርት ቤት አትመጭም ማለት ነው?”

“ነገ ከሰዓት እመጣለሁ፤ ይልቅስ እንኳን ደስ ያለሽ አትለኝም?”

“ይቅርታ እንኳን ደስ ያለሽ፤ አጉል ለምጄሽ ስትቀሪ ይደብረኛል” አላት ታረቀኝ ከልቡ።

“ነገ አልቀርም እመጣለሁ” አለችው እያዘነች።

ስልኩን ዘግታ ስለታረቀኝ አሰበች፤ ሁሌም እንደምታደርገው ትምህርት ቤት ውስጥ ከምታውቃቸው ሴቶች ልጆች ለታረቀኝ የምትሆን መፈለግ ያዘች።

* * * *

ትምህርት ተጠናቆ የፈተና ዝግጅት ተጀምሯል፤ ታረቀኝ ግን ሰሞኑን ብስጩነቱ ብሶበታል፤ የመኝታ ክፍል ጓደኞቹ በእርሱ ምክንያት የሚፈልጉትን ያህል ማጥናት አቅቷቸዋል። የታረቀኝ ጎበዝ ተማሪነትና መልካም ጓደኝነት “የራሱ ጉዳይ” ብለው እንዲተዉት አላደረጋቸውም። እናም ሰሞኑን የመነጋገሪያ አጀንዳቸው ሆኗል። አንዳንዶቹ ከታረቀኝ ጋር በግልጽ ለመወያየትና ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት ሞክረዋል፤ ግን የተገኘ ውጤት የለም።

ከመኝታ ክፍል ጓደኞቹ በጣም የሚቀርበው ልጅ ከታረቀኝ ጋር ለመወያየት ተደጋጋሚ ሙከራ ማድረጉን አላቋረጠም። “ኧረ በናትህ ታረቀኝ እኛንም ግራ አጋባኸንኮ' ምናለ ብታናግረኝ?” አለው አንድ ቀን ብቻቸውን ሆነው።

“ምን ልነግርህ እችላለሁ የማታውቀው ጉዳይ አለ?” አለው በመሰላቸት።



“እሺ! የማውቀው ነገር አለኝ ልበል፤ የተሻለ ሁኔታ ለመፍጠር ምን ላደርግልህ እችላለሁ? ይሄንን አድርግ ብትለኝ የምችለውን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ አልልም” አለው ከልቡ።

“ቆይ ምን አድርግ ልበልህ? ፍሬ መጥታ አብራኝ እንድታጠና አድርግልኝ ብልህ ልታደርግልኝ ትችላለህ?” አለው ታረቀኝ።

“አዎ! የምችለውን እሞክራለሁ” አለ ጓደኛው።

“እባክህን አትቀልድ፤ ፍሬከ ፍቅረኛዋ መጥቶ ከእርሱ ጋር ለመሆን ነው የማትመጣው”

“አንተስ ለምን ልትርሳት አትሞክርም ታዲያ…” አቋረጠው ታረቀኝ።

“በናትህ ተወኝ እኔ አሁን እንዲህ ዓይነት ምክር አልፈልግም” አለና ትቶት ወጣ።

የታረቀኝ ጓደኛ ተናደደ፤ ሰው ለፍቅር እንዲህ መሆን እንደሌለበት የሚያምን በመሆኑ በታረቀኝ በጣም አዘነበት። “ግን ምን ያድርግ ደግሞ ፈልጎ አልተቸገረ” አለ ደግሞ።

ወደአመሻሽ ላይ “የፍሬሕይወትን ስልክ ልትሰጠኝ ትችላለህ?” አለው።

“ትቀልዳለህ? ለምንድነው የምሰጥህ? ታረቀኝ ባንቺ ፍቅር ምክንያት ማጥናት ስላቃተው እባክሽን ነይና አባብይው እንድትላት” አለ ታረቀኝ እየሾፈ።

“በፈጠረህ ታረቀኝ፤ እኔ እየቀለድኩ አይደለም፤ የምለውን አላታለሁ። ብቻ ስልኳን ስጠኝ። አለው ጓደኛው።

“ግን ስሜን እንድታነሳላት አልፈልግም” አለና ቁጥሯን ሰጠው።

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ለፍሬሕይወት ደወለላት፤ ስልኩ ወዲያው አልተነሳም። "በናትሽ አንሺው" አለ የታረቀኝ ጓደኛ ስልኩን እጆሮው ላይ እንዳደረገ። ድንገት ስልኩ ተነሳና ተደናገጠ።

"ጤና ይስጥልኝ" አለ እንደምንም ራሱን አረጋግቶ

"ጤና ይስጥልኝ ማን ልበል?" ፍሬሕይወት መሆኗን ወዲያውኑ ነው ያወቀው።

"የታረቀኝ ጓደኛ ነኝ..."

"ምነው በደህና? ታረቀኝ ምን ሆነ?" ድንጋጤዋ ያስታውቃል።

"ደህና ነው ልበልሽ? ወይንስ ደህንነቱን መጥተሽ እንድታይው ልጠይቅሽ?" አላት።

"በናትህ አታስጨንቀኝ፤ ምን ሆነ?"

"ሰሞኑን ትምህርት ቤት መጥተሽ አታውቂም አይደል?"

"አዎ አልመጣሁም"

"በቃ! ያለመምጣትሽ ነው ችግር የፈጠረው፤ እባክሽን ነገ ነይ" አላት በማስተዛዘን።

"ኧረ "እባክሽ" መባል ያለብኝ አይደለሁም፤ ለምን ግን ታረቀኝ አልደወለልኝም?" አለችው።

"ነገ ስትመጭ ምክንያቱን ይነግርሻል። በእርግጠኝነት ነገ ትመጫለሽ አይደል?"

"በእርግጠኝነት እመጣለሁ" አለችው።

"በስንት ሰዓት?"



"በሁለት ሰዓት"

"ኬኔዲ በር ላይ ይጠብቅሻል፤ በጣም አመሰግናለሁ" አላትና ስልኩን ዘጋው።

ስልኩን ዘግታ እራሷን በእጆቿ ይዛ ለብዙ ደቂቃዎች ቆየች። ትምህርት ቤት ከሄደች አንድ ሳምንት ሆኗታል። በእነዚህ ቀናት ውስጥ ከታረቀኝ ጋር በስልክም አልተገናኙም። ራሷን በታረቀኝ ቦታ አድርጋ ስታስበው በጣም አዘነች። ስልክ ለምን እንዳልደወለ ገባት፤ እርሱ ይህን ያህል ሲያስብላት እርሷ ግን ለደቂቃ እንኳን አላሰበችለትም። ራሷን ታዘበችው። ፈቃደን ሽኝታ እንኳ መሄድ ነበረባት።

ለሁለት ሩብ ጉዳይ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው በር ገባች ፍሬሕይወት። እንደገባች ዐይኖቿ ወደ ኬኔዲ ላይብረሪ በር ማተኩ፤ ታረቀኝን አየችው፤ ሮጠች። አጠገቡ ስትደርስ "ይቅርታ አድርግልኝ" ብላ ተጠመጠመችበት። ከሰላምታ በኋላ "ይቅርታ አድርገህልኛል?" አለችው እንደገና።

"ምን አጥፍተሽ?" አላት

"በመጥፋቴ ነዋ!" አለችው።

"አንቺ ልትነግሪኝ የሚገባሽን ሁሉ ነግረሽኛል፤ አቋምሽን አሳውቀሽኛል፤ መቀበል ያቃተኝ እኔ ነኝ። ይቅርታ ልትጠይቂኝ አይገባሽም" አላት ኮስተር ብሎ።

"ቢያንስ ጓደኛህ ነኝ ላስብ ይገባኝ ነበር፤ ለራሴ ብቻ ባላስብ ኖሮ በመሀል መምጣትም ነበረብኝ፤ በናትህ ይቅር ብዬሻለሁ በለኝ" አለችው።

"እሺ! ደስ የሚልሽ ከሆነ፤ይቅርታ አድርጌያለሁ" አላት ታረቀኝ። ጉንጩን ሳመችው።

"አሁን ጥናት መጀመር እንችላለን፤ የት እንሁን?" አለችው።

እስከፈተና ድረስ ባሉት ቀናት የተቻለውን ያህል ለማጥናት ሞክረዋል ውጤት ግን አጥጋቢ አልሆነም። የታረቀኝ ሁኔታ ይረብሻታል፣ ያሳዝናታል... ምን መደረግ እንዳለበት ታስባለች። ሁኔታውን ለመለወጥ ምን ልታደርግ እንደምትችል እየውጠነጠነች ባለችበት ሁኔታ አንድ ቀን ያ የታረቀኝ ጓደኛ ስልክ ደውሎ እንደሚፈልጋት ነገራት።

በሚቀጥለው ቀን ከልጁ ጋር ተገናኙና "ታረቀኝ ትምህርት ሊያቋርጥ ነው" አላት በትካዜ። ደነገጠች ፍሬ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች አፍጥጣ ተመለከተችውና

"ከእኔ ለመራቅ ነው አይደል?" አለችው አንገቷን ደፍታ።

"አዎ!" አላት ጓደኛው።

"እኔ ትምህርቱን ብተወውስ?" አለችው ቀና ብላ እያየችው።

"ለፈቃደ ብለሽ?" አላት ደንገጥ ብሎ።

"ጓደኛው እኮ ነኝ፣ ይህንን ማድረግ ትልቅ ነገር አይደለም፣ እናንተ ስትመረቁ ተመልሼ ልገባ እችላለሁ" አለችው።

የታረቀኝን ሕይወት ማበላሸት እንደሌለባት አሰበች፡፡ በፍቅር ለተሰቃየ ልቡ ልታደርግ የምትችለው ነገር ባይኖራትም ከአጠገቡ ራቅ ልትልለት እንደሚገባት ወሰነች። አዎ! አጠገቡ ሆና ሲሰቃይ ከምታይ መራቅ ይሻላታል። ታረቀኝን ትወደዋለች፣ እናም የራሱ ጉዳይ ማለት አልቻለችም። እዛ ግቢ አብረው እስካሉ ድረስም መለያየት የሚታሰብ አይደለም ሁሌም አንገት ላንገት ተቃቅፈው ነው የሚገኙት።

"እኔ ግን ይህን እንድታደርጊ መፍረድ እቸገራለሁ፣ ብታስቢበት ደስ ይለኛል" አላት ሲያስብ ቆይቶ።



"ግዴለህም፣ ሳስብበት ነው የቆየሁት። ታረቀኝን ለመሰለ ጓደኛ ደግሞ ይህችን ታህል መስዋእትነት መክፈል ከባድ አይደለም" አለችው በቁርጠኝነት። ሁለቱም በየሀሳባቸው ተመሰጡና ዝምታ ሰፈነ።

"መገናኘታችንን ግን አትንገረው" አለችው ከጥቂት ዝምታ በኋላ።

"በጣም አዝናለሁ፣ በሕይወትሽ ላይ እንዲህ ዓይነት ውሳኔ ስትሰጭ መመልከት ከብዶኛል" አላት ልጁ።

"ሀሳብ አይግባህ፣ ይህን ሳልሰማ ታረቀኝ ትምህርቱን አቋርጦ ቢሆን ኖሮ ምን ላደርግ እንደምችል ማሰብ ይከብደኛል። እኔም የማቋርጥ ይመስለኛል። በጣም ነው የማመሰግንህ በሕይወቴ ሙሉ የምደሰትበትን ውሳኔ እንድሰጥ እንዳደረግከኝ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ" አለችው።

ጥቂት ሰንበትበት ብሎ "ፍሬ ትምህርት ላቋርጥ ነው አለችኝ" አለው ታረቀኝ ለጓደኛው።

"ለምን?" አለው ጓደኛው።

"እርግጥ'ለሁ" አለችኝ።

"ምን አልካት ታዲያ" አለው በሰጠችው ምክንያት እየተገረመ።

"እንድታስወጣው ስነግራት በጣም ተቆጣች፣ በፍጹም እንደማታደርገው ነገረችኝ" አለ ታረቀኝ በትካዜ።

"ለበጎ ነው ብሎ ማሰብ ይሻላል፣ ለአንተ ደግሞ አጋጣሚው መልካም ይመስለኛል። በራሷ ጊዜ ከዚህ ጊቢ መራቅ ካለባት ታረቀኝ ትምህርት ማቋረጥ አያስፈልገውም" አለው ጓደኛው የታረቀኝን ስሜት እየተመለከተ።
"ይሳካልኛል ብለህ ነው?" አለ ታረቀኝ በጥርጣሬ።

"የማንስማማው እዚህ ላይ ነው" አለ ጓደኛው በቁጣ።

ታረቀኝና ጓደኛው ብዙ ተከራከሩና በመጨረሻው ታረቀኝ ትምህርት ባለማቋረጡ ተስማማለት። የታረቀኝ ጓደኛ ይህንኑ ለፍሬሕይወት ነገራት። ከሰሞኑ ትምህርት ለማቋረጥ ልታሟላ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ስታደርግ እንደወትሮአቸው ከታረቀኝ ጋር ነበሩ።

በመጨረሻ ሲለያዩ "ፍሬ! እንደወደድኩሽ እኖራለሁ፤ ተሳክቶልኝ ጓደኛ መያዝ ብችል እንኳን የምረሳሽ አይመስለኝም" አላት።

"እኔም አልረሳህም ታረቀኝ፤ በሕይወቴ ሙሉ እንዳንተ ዓይነት ጓደኛ ይኖረኛል ብዬ አላስብም። ከአንተ ጋር በፍቅር የምትጣመድ ሴት ዕድለኛ ነች" አለችው።

* * * *



## ክፍል 5
## የትዳር ሕይወት

ሰሞኑን እንቅልፍ እምቢ ይላታል፤ የሌሊቱን አብዛኛውን ሰዓቶች በመገላበጥ ነው የምታሳልፋቸው። አንዳንዴ ተነስታ ትቀመጣለች፤ አለያም ከአልጋዋ ወርዳ ትቆማለች። የወሰነችው ታላቁን የሕይወት ውሳኔ ነው። የራሷን ሕይወት በራሷ መወሰን እንዳለባት ያላት እምነት ፅኑ ነው፡፡ እናም ወደአዋሳ ስትሄድ ባህሉና ወጉ በማይፈቅደው መንገድም ቢሆን ወደትዳር እየገባች መሆኑን ታውቀዋለች።

"ግን ፈቃደ ባይስማማስ?" ድንገት ወደአእምሮዋ የመጣ ጥያቄ ነው፤ እስካሁን አላሰበችውም።

እናም ለፈቃደ ስልክ ደወለችለትና "ልመጣ አስቤ ነበር" አለችው።

"ትምህርት ቤት ተዘጋ እንዴ?" አላት እርሱም።

"ሳይሆን ትምህርቱን ልተወው ነው..."

"እየቀለድሽ ነው?"

"እየቀለድኩ ሳይሆን የምሬን ነው"

"እኔ በዚህ ውሳኔ አልስማማም" አለ ኮስተር ማለቱን ለመግለጽ እየሞከረ።

"ካልተስማማህ ችግር የለውም፤ "ሳትነግሪኝ" እንዳትለኝ እፈልጋለሁ አለችው እርሷም ያላትን ቁርጠኝነት በሚገልጽ ሁኔታ።

"እሺ ትንሽ ላስብበት..."

"ትችላለህ" አለችው እስኪጨርስ ሳትጠብቀው። የስልክ ንግግራቸው በዚሁ አበቃ።

በሚቀጥለው ቀን ቤት አልዋለችም፤ ከብዙዎቹ የእስር ቤት ጓደኞቿ ጋር እምብዛም አይገናኙም፤ አልፎ አልፎ የሚገናኙት ከሚስጥረ ጋር ብቻ ነው። አሁን ግን መሄድ አለባት፤ ውሳኔዋን ልትነግራቸው እንደሚገባት አምናበታለች። በመጀመሪያ ሚስጥረን ለማግኘት ወሰነችና ወደዚያው ለመሄድ ወጣች።

"ፍርዬ ከየት ተገኘሽ?" አለቻት ሚስጥረ ስታያት።

"ልጠይቅሽ መጣሁ አንቺ ባትፈልጊኝ እኔ ልፈልግሽ አልችልም?" አለች እንደቀልድ።

"ጉረኛ! አንቺ ፈቃደ እያለ ማን ይታይሻል ደግሞ?" አለቻት የተለመደውን ተረብ በመጀመር።

ልታደርግ የወሰነችውን ነገረቻት፤ "አይሆንም አይደረግም!" አለች ሚስጥረ። "ፍርዬ ግን ምን ሆንሻል? አላበዛሽውም እንዴ አግባኝ እያልሽው እኮ ነው" አለቻት ከምሯ እየተናደደች።

"ሊሆን ይችላል፤ እኔ ብጀምረው ምናለበት" አለቻት እየቀለደች።

"ፍሬ እባክሽን አስቢበት፤ በጣም የቸኮልሽ ይመስለኛል" አለች ሚስጥረ ስለፈቃደ ያላትን ስሜት ሳትነግራት ፍሬሕይወት እንዲህ ያለ ውሳኔ ላይ በመድረሷ ጥፋተኝነት እየተሰማት።

"ሳልናገር መሄድ ስላልፈለግሁ ነው የመጣሁት፤ ውሳኔዬ የማይታጠፍ ነው" አለች ፍሬ ኮስተር እንዳለች። ሚስጥረም ከዚያ በኋላ ምንም ለማለት አልደፈረችም። ጥቂት ተጫዋወቱና ተሰነባበቱ።

ፍሬሕይወት እንዳሰበችው ልትሰናበታቸው ያሰበቻቸውን ሁሉ አዳርሳ ስትጨርስ ድክም አላት። ብዙዎቹ በውሳኔዋ ባይስማሙላትም ስለነገረቻቸው አመሰገኗት።

ቤት ስትገባ የበላይሁንን እናት ደጅ አገኘቻቸውና ስልኩ ሙሉ ቀን ሲጮህ መዋሉንና በመጨረሻ እነርሱ ቤት ተደውሎ መልእክት



እንደተቀበሉ ነገሯት። የደወለው ፈቃደ ነው ነገ በጠዋት እደውላለሁ ነው መልእክቱ። እንዳለውም በጠዋት ደወለ።

ፍሬሕይወት ስልኩን አነሳችና "ሄሎ!" አለች።
"ምነው ፍርዬ እንዲህ አሰቃየሽኝ?" አለ ፈቃደ ከሰላምታ በፊት።

"በደንብ እንድታስብበት ብዬ እኮ ነው" አለችው የእርሷ ባልሆነ አነጋገር። አነጋገሯ ለራሷም ገርሟታል።

"ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?" አለ በብስጭት።

"ቀልድ ትተሃል መሰለኝ አንተ ልጅ አሁን ይሄ ምን ያስቆጣል? እሺ ምን ወሰንክ?" አለችው።

"መቼ ለመምጣት አስበሻል?" አለ፤ ጥያቄዋን በጥያቄ እየመለሰላት።

"እኔኮ የእርስዎን መልስ ነው የምጠብቀው ጌታዬ!" አለች ለመጀመሪያ ጊዜ እየቀለደች።

ያንኑ ዕለት ለበላይሁን እናት ሥራ ማግኘቷንና ወደ ክፍለሀገር ልትሄድ መሆኑን ነገረቻቸው፤ በጣም ደነገጡ።

"እንደፈራሁት ቤቱ ሊዘጋ ነው?" አሏት።

"አይዘጋም! እመለሳለሁ እማማ። ለጊዜው የሚገቡ ሰዎች ተነጋግሬያለሁ መጥተው ያነጋግሩዎታል፤ ስማቸውና የስልክ ቁጥራቸው ይሄውና" አለቻቸው ወረቀት እየሰጠቻቸው።

"ሁሉን ነገር ጨርሰሻላ?" አሏት።

"አዎን ጨርሻለሁ እማማ" አለቻቸው።

የመጨረሻው ቀን ደረሰ፤ "ከዚህ በኋላ እዚህ ቤት ውስጥ የማድረው ለአንድ ቀን ብቻ ነው። ነገን ብቻ!" አለች እንደልማዷ እንቅልፍ አልወስድ ብሏት ከአልጋዋ ወርዳ መንጎራደድ ስትጀምር። ሁልጊዜም

ከስድስት ቤተሰብ ብቻዋን የመቅረቷን ነገር ስታስበው መጮህ ያምራታል። አሁን ደግሞ እርሷም ትታው ልትሄድ ነው። "አዎ ከነገ በኋላ ይህ ቤት ሌላ ቤት ይሆናል፤ ከእንግዲህ እነዚህ ሁሉ በዚህ ቤት ውስጥ አይታዩም" አለች ሳሎን ገብታ እግርግዳ ላይ የተሰቀሉትን ፎቶግራፎች እየተመለከተች። ፎቶዎቹን በሙሉ አወረደቻቸውና ጠረጴዛው ላይ በጥንቃቄ አስቀመጠቻቸው። መጠቅለል ከጀመረች በኋላ እንደገና ፈታችና ቤተሰቡ በሙሉ ያሉበትን አንድ ፎቶግራፍ ለብቻው አስቀመጠች። "ቢያንስ ይህ አብሮኝ መሆን አለበት" አለች ለራሷ። በልብስ ጠቀለለችና ሻንጣዋ ውስጥ ከተተችው። ቤቱ ውስጥ የሚገቡት ሰዎች የቤቱን ዕቃ እንደሚጠቀሙበት ቢነጋገሩም አንዳንዶቹን ዕቃዎች አንድ ክፍል ውስጥ አስገብታ ማሸግ ስለሚያስፈልግ በመልክ በመልኩ ስታደራጅ ሌሊቱ አለቀ።

ትንሽ ረፈድ ሲል ነጠላዋን ነጠል አድርጋ ለበሰችና ቤቱን ዘግታ ወጣች፤ በመንገዷ ላይ ሁለት ሻማዎችንና ሁለት አበባዎችን ገዛችና በፈጣን እርምጃ እየተራመደች ወደኡራኤል ቤተክርስቲያን ሄደች። ለእናትና ለአባትዋ ውሳኔዋን ልትነግር፤ በመንፈስም ቢሆን አይዞሽ እንዲሏትና በእዝነህሊናዋም ቢሆን "ተባረኪ!" የሚለውን ታላቅ ምርቃት ልትቀበል ነበር የምትሄደው።

ሁሌም እንደሚሆነው መቃብሮቹን ስታያቸው የልቧ ምት ጨመረ፤ ቆመችና አማተበች፤ እራሷን ለማረጋጋት ለጥቂት ደቂቃዎች ዐይኖቿን ጨፈነችና ገለጠቻቸው። የእናትና አባቷ መቃብሮች አጠገብ ላጠገብ መሆናቸው ያስደስታታል፡፡ አንዳንዴ የሚነጋገሩ ሁሉ ይመስላትና ስለዕድለኛነታቸው ታስባለች፤ ትቀናባቸዋለች። ከመቃብሮቹ በስተግርጌ እመሀል ባለው ጠባብ ቦታ ላይ ተንበረከከችና ጸሎቷን አድርሳ ቀና ስትል ዐይኖቿን እንባ አቃጠላቸው። "ዛሬ ማልቀስ የለብኝም" አለች ለራሷ።

* * * *

ፍሬሕይወት አዋሳ ስትደርስ ፈቃደ በሚገባ ተዘጋጅቶ ጠበቃት፤ ከጓደኞቹ ጋር እራት አዘጋጅተው ጋበዟት። ኑሮ "ሀ" ተብሎ



ተጀመረ፡፡ ምቾት ያለው ቀላል አጀማመር ነበር፡፡ በአዋሳ ሀይቅ ዳርቻ ላይ በተሠራው ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ውስጥ ካሉት ቪላዎች በአንዱ ውስጥ ነበር ፈቃደ የሚኖረው። ለጊዜው አስቸጋሪ ነገር አልነበረም፡፡ ቤቱ ለመኖር በሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የተደራጀ የሆቴሉ ሠራተኞችም አስፈላጊውን ግልጋሎት የሚሰጡበት ሁኔታ ነበር።

ሕይወት በጣም ቀላል ሆነላት፤ በዚያ ላይ ያለችው ከምታፈቅረው ሰው ጋር ነው፤ ተደሰተች። ፈቃደ ደመወዙን አምጥቶ ያስረክባታል፡፡ በጀታቸውን አብረው ይሰራሉ፤ ገንዘባቸውን ይመድባሉ፤ መተሳሰብና ሰላም ያለበት አዲስ ሕይወት መሠረቱ። ወግና ልማድን ያልተከተለ ቢሆንም ትዳር ተመሠረተ፡፡ ብዙዎች የሚቀኑበት በፍቅር የደመቀ ሆነ ቤታቸው።

ማሕበራዊ ግንኙነታቸው ሰፊ ነው፤ የፈቃደ መሥሪያ ቤት ጓደኞች፤ በሆቴሉ ውስጥ እንደነሱው ተከራይተው የሚኖሩ ሰዎች፤ ብቻ ከበርካታ ሰዎች ጋር ተዋወቀች። ሰብሰብ ብለው ሲጫወቱ ፍርዬ አንዳንዴ በሀሳብ ጭልጥ ትላለች እለያም የተሰበሰቡትን ሰዎች ትገመግማለች። ብዙዎቹ የሚመቻትና ተመሳሳይነት ያለው ባህሪ አላቸው። "እነዚህ" ትላለች ለራሷ "እነዚህ የዘመን ተጋሪዎቻችን ናቸው፤ አይ እነዚህ እንኳ አይመስሉም..." ትላለች ለራሷ፤ ለብቻቸው ሲሆኑ ፈቃደን ትጠይቀዋለች "እነእንትና የኛ ሰዎች ናቸው እንዴ?" ትለዋለች።

"ልክ ነሽ፤ ግን በምን አወቅሽ?" ይላታል እየገረመችው።

"ታውቃለህ አንድ የሆነ የሚያመሳስለን ነገር አለ፤ ልገልጸው ግን አልችልም" ትለዋለች።

ታረቀኝን ሳታስታውስ የዋለችበት ቀን አልነበረም፡፡ "እንዴት ሆኖ ይሆን?" ትላለች ባስታወሰችው ቁጥር። ያለበትን ሁኔታ ማወቅ በጣም ትፈልጋለች፤ ግን እንዴት አድርጋ? ቤተሰቦቿን፤ ያሉትንም የሞቱትንም ታስታውሳለች፤ አንዳንዴ ብትተክዝም ትካዜዋ አጭር ነው። ፈቃደ ሲመጣ ሁሉን ያስረሳታል።

ፍሬ በተቻላት አቅም ሁሉ ከእስር ቤት ጓደኞቿ ላለመለየየት ትጥራለች፤ ያለችበትን ሁኔታ ትጽፍላቸዋለች። እነርሱም ይጽፉላታል አንዳንዴም ይደውሉላታል። አንድ ቀን ሰብሰብ ብለው ያለችበት ቦታ ድረስ መጥተው ጠይቀዋት ፍንድቅድቅ ብላለች። አዲስ አበባ እያለች ትጠይቃቸው የነበሩ ሰዎችንም መጠየቋን አላቋረጠችም፤ ስልክ ትደውላለች። ለአስቻለው እናት ወደአዲስ አበባ የሚሄድ ሰው ፈልጋ መላክ የምትችለውን ያህል ትልክላቸዋለች። "አይዞዎት!" የሚል መልእክት ትልክባቸዋለች። ፈቃደ ደግሞ በዚህ ወደኋላ የሚለው ነገር የለውም "ሕይወታቸውን ለከፈሉ ጓዶቻችን ገንዘባችንን መክፈል ካቃተንማ..." ይላታል፤ የልቧን ይሞላላታል። ሕይወት አስደሳች ሆነ።

"ዛሬ እንግዳ ይዤ እመጣለሁ" አላት ፈቃደ አንድ ቅዳሜ።

"በደስታ እቀበልሃለሁ" አለችው።

ፈቃደ እንደወጣ እርሷም ለእንግዳ ማስተናገጃ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለመገዛዛት ወጣች። ከገበያ ስትመለስ ወዲያውኑ ሥራ ጀመረች፤ እየሠራች ደግሞ ስለእንግዳው አሰበችና ስለማንነቱ አንዳችም ጥያቄ አለማቅረቧ ትዝ አላት። "ሲመጣ ማን እንደሆነ አውቅ የለ? ምን አስቸኮለኝ" አለች ለራሷ።

አዘጋጅታ ስትጨርስ ሰዓቷን ተመለከተች፤ ለፈቃደ መምጫ ሰዓት የቀሩት ሰላሳ ደቂቃዎች ብቻ ናቸው። ፈጠን ብላ ወደመታጠቢያ ቤት ገባች። ተጣጥባና ልብሶቿን ቀይራ የምግብ ጠረጴዛውን በማዘጋጀት ላይ እያለች የሳሎኑ በር ተንኳኳ።

"ይግቡ" አለች ፍሬሕይወት። በሩ ተከፈተና ፈቃደና እንግዳው ተከታትለው ገቡ። ፍሬ ደነገጠች፤ ይህን መልክ ታውቀዋለች፤ በሚገባ ታውቀዋለች፤ ግራ ገባት።

"ዘውዱ ይባላል፤ እስር ቤት አብሮን የነበረ ጓደኞችን ነው" አለ ፈቃደ። እንደምንም ሀሳቧን አሰባስባ ከእንግዳው ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ እንግዳው እንዲቀመጥ ጋበዘችው።

"የማውቅህ መስሎኝ ነው የደነገጥኩት" አለችው።



"እስር ቤት ተያይተን ይሆን?" አላት ፈቃደ እዚያ እስር ቤት የነበረች መሆኗን እንደነገረው አስታውሶ።

"አንተ እንኳን ሳትሆን እኔ አይቼሃለሁ፤ ያ መልክና መገረፊያው ክፍል የሰማሁት ሥም አሁን ካየሁት ሰውና ከተነገረኝ ሥም ጋር ተገጣጠሙብኝ" አለች።

"እንዴት ልታይውና ስሙን ልትሰሚ ቻልሽ?" አላት ፈቃደ። ሁኔታውን ነገረቻቸው። ሴቶች ክፍል ተገፍትሮ ሲወድቅ የነበረውን ሁኔታ፤ በሚቀጥለው ቀን መግረፊያ ክፍል ተጠርታ ስለዘውዱ መጠየቋንና የተጠየቀችበት ምክንያት ከበላይሁን ጋር ሊዛመድ እንደሚችል የነበራትን ግምት ሁሉ ነገረቻቸው።

እንደማንኛውም ጊዜ የዚያ ዘመን ተጋሪዎች እንደሚያደርጉት ውሎዋቸው ሁሉ ከዚያ ክልል ሊወጣ አልቻለም፤ ግን ለእነርሱ አስደሳች ነበር። በትግሉ ወቅት የነበሩትን ሁኔታዎች ሲያነሱና ሲጥሉ፤ በትግሉ ውስጥ ሕይወታቸውን የሰጡትን ጓዶች ሲያደንቁ፤ የነበረውን መተማመንና አንዳቸው ለሌላው ሕይወት መትረፍ እስከሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉበትን ዘመን ሲዘክሩ በአንጻሩ ደግሞ ባለዕዳነታቸውን ሲያስቡና ሲቆዝሙ... ጊዜው ሳያስቡት ሮጦ ወደአመሻሹ ላይ ዘውዱን ሸኙት።

* * * *

ከአዲስ አበባ ለሄደ ሰው የክፍለ ሀገሩ ኑሮ እንደአዲስ አበባ ወከባ የለበትም። ብዙ ማህበራዊ ትስስር ስለማይኖራቸው የእረፍት ቀናቸውን በጋራ የማሳለፍ ልማድ አላቸው።

አንድ ቀን ዘውዱ "ለምን እነፈቃደን አንድራቸውም?" አለ ሰብሰብ ብለው ሲጫወቱ።

"እውነት እኮ ነው፤ ለምን የሆነች ዝግጅት አድርገን ጋብቻቸውን አናከብርላቸውም?" የሌላው ሀሳብ ነበር።

"እኔ ዝግጅቱን ሠርግ የማስመሰሉን ኃላፊነት እወስዳለሁ" አለች የአንደኛው ጓደኛቸው እጮኛ። በዚሁ ተስማሙ።

የፈቃደ ጓደኞች ለፈቃደና ለፍሬሕይወት ጋብቻ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ፕሮግራም አዘጋጅተው ፈቃደንና ፍሬሕይወትን ጋበዟቸው። በመጀመሪያ የሄዱት አንደኛው ጓደኛው ቤት ነበር። ቤቱ ውስጥ ሲገቡ አድናቆታቸውን ሊገቱ በማይችሉበት ሁኔታ ደነገጡ። ቤቱ በጣም አሸብርቋል፤ እሳሎኑ መሀል ወንበሮች ላይ የተቀመጡት የሰርግ ቬሎና የወንድ ሙሉ ጥቁር ሱፍ ከነጭ ሸሚዝ ጋር፤ በትንሽ ጠረጴዛ ላይ በሁለቱ የሠርግ ልብሶች መሀል የተቀመጠው አበባ ለቤቱ ልዩ ውበትን አጎናጽፈውታል።

ፈቃደና ፍሬሕይወት በድንጋጤ ፈዘው እንደቆሙ ጓደኞቹ በአንድ ላይ "መልካም ጋብቻ" አሏቸው። ማመን እስኪከብዳቸው ድረስ፤ ደስታ ዐይኖቻቸውን በእንባ እስኪሞላቸው ድረስ ነበር የፈቃደና የፍሬሕይወት ስሜት። ሁለቱም እርስ በእርሳቸው እየተያዩ ፍዝዝ አሉ።

"ልብሶቻችሁን ልበሱ" አለቻቸው የጓደኛው እጮኛ። በሩን መለስ አድርገውላቸው ወጡ።

ፈቃደና ፍሬሕይወት የሰርግ ልብሱን ለብሰውና በጓደኞቻቸው ታጅበው በሆቴሉ ግቢ ውስጥ ወዳለው የዋና ቦታ መሄድ ነበረባቸው። እነርሱ የተባሉትን መፈጸም እንጂ ስለፕሮግራሙ ምንም ዓይነት አስተያየት ሊሰጡ እንደማይችሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው። ምስጋና ለማቅረብ እንኳ ጊዜ አልነበራቸውም፤ የዕለቱን ፕሮግራም የሚመራው ዘውዱ ነው። ለዚያ ሰዓት የመዋኛ ሥፍራው ነጻ እንዲሆንላቸው ከሆቴሉ ጋር ተነጋግረዋል። ልክ ሲደርሱ መዋኛው ለፍሬና ለፈቃደ ብቻ ተለቀቀላቸው። ለስለስ ያለ የሰርግ ዘፈን እየተሰማ ሁለቱ ሙሽሮች ወደ መዋኛው እንዲገቡ ተነገራቸው። ገቡ፤ ዋናውን ተያያዙት የውሀው ድምጽና የሙዚቃው ቃና በሁለቱም ልቦች ውስጥ ልዩ ስሜትን በመፍጠሩ የተነሳ ሁለቱም በተመስጦ በቀስታ መዋኘታቸውን ቀጠሉ። በዚያች ቅጽበት ፍሬሕይወት ሀሳቧ ወደአንተነህ ኮበለለባት።



"እንዴ ዋናውን የደስታ አድርጉት እንጂ!" አላቸው ዘውዱ ጮክ ብሎ።

ፈቃደና ፍሬሕይወት ተቀራረቡ፤ እየዋኙ መጫወት ጀመሩ፤ መሽቀዳደም፤ መደፋፈቅ... ሳቅ... የዋናው ቦታ የብዙዎችን ቀልብ ሳበ።

ከመዋኛው ሥፍራ ጥቂት ራቅ ብለው የሞቀ ጨዋታ የያዙት ሰዎች ግን በመዋኛው አካባቢ የሁሉን ቀልብ የሳበውን ሁኔታ አላስተዋሉም።

ውሀው ውስጥ ከገቡ ብዙ ደቂቃዎች ቢያልፉም ፈቃደና ፍሬሕይወት ምንም የደከማቸው አይመስሉም። እልፎ አልፎ ሁለቱም ውሀው ውስጥ ይሰጥሙና ሰውን ያስደነግጣሉ፤ ደግሞ ብቅ ይላሉ። ሁኔታቸው የዋና ስፖርተኛ እንጂ ተራ ዋናተኛ አላስመሰላቸውም። በመደፋፈቅ ላይ እያሉ እርሱ ሊደፍቃት ሲል ስታመልጠውና ሳያስበው ስትደፍቀው በአካባቢው የነበሩት ሁሉ ሳቁ። ሳቁ በጨዋታቸው ውስጥ ሰምጠው ለአካባቢው ትኩረት ያልሰጡትን ሁለት ሰዎችም ከገቡበት የግል ጨዋታቸው ጎትቶ አወጣቸው።

ሁለቱም ሰዎች የሳቁን መንስኤ ለመመልከት ወደዋናው ስፍራ መጥተው ከሰዎቹ ተቀላቀሉ። ፈቃደና ፍሬሕይወት ለየብቻቸው መዋኘት ጀምረዋል ፍሬሕይወት በጀርባዋ ተንጋላ እየዋኘች እዳር ደረሰችና ብረቱን ያዝ አድርጋ ቆም ከማለቷ "መልካም ጋብቻ" አላት ዘግይቶ የመጣ ጓደኛቸው።

"እናመሰግናለን" አለችው ፈቃደንም በመወከል።

በዋናው ቦታ አካባቢ የተፈጠረው ድምጽ ስቧቸው ትዕይንቱን ከተቀላቀሉት ሁለት ሰዎች አንዱ አንተነህ ነው። አንተነህ የተመለከተውን መልክና የሰማውን ድምጽ ማመን አቅቶት ዐይኖቹን አሸት አሸት አደረጋቸው፤ ያደረገውን ኮፍያ ወደግንባሩ ደፋ አደረገና ፊቱን ከእይታ ከለለ። ከእይታ የበለጠ ለመራቅ የቆመበትን ቦታ ቀየረ። እነዚያን ዐይኖችና በውሀው ተነክሮ አንገቷን የሙጢኝ ብሎ የተጠመጠመውን ወርቃማ ጸጉር ሊጠራጠር አልቻለም። መነጽሩን አወለቀና ትክ ብሎ ተመለከታት፤ እብረቱ ላይ ተቀምጣ በእግሮቿ ከውሀው ጋር የምትጫወተውን ፍሬሕይወትን።

ጓደኛው አድራጎቱን ሲከታተል ቆይቶ "ምን ነካህ?" አለው ወደጆሮው ተጠግቶ።

"ፍሬሕይወት!" አለው አንተነህ በጣም በደከመ ድምጽ ዐይኖቹን ካነጣጠሩበት አቅጣጫ ሳይመልስ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንገቱን እንደሰበረ ከዋናው አካባቢ ለመራቅ ጉዞውን ጀመረ።

ጓደኛው የአንተነህ ሁኔታ ግራ እያጋባው ተከተለው። ኋላና ፊት ሆነው ጥቂት ተራመዱና ከዋናው ሥፍራ ዕይታ ተሰወሩ።
"እኮ ለምንድነው አጋጣሚዎች እንዲህ የሚፈታተኑኝ?" አለና በጩኸት ጠየቀው አንተነህ ጓደኛውን። ጓደኛው በድንገት የጮኸበት የአንተነህ ድምጽ አስድንግጦት ወደኋላው እንደማፈግፈግ አለና ቆመ። ለቅጽበት ያህል ከአንተነህ ጋር ተፋጠጡ።

"እርሷን ፍለጋ አዲስ አበባ ውስጥ፤ ያላደረስኩት ቦታ የለኝም፤ ይሆናል ያልኩት ቦታ ሁሉ አልቀረኝም፤ አጣኋት። ታዲያ እንደአጣኋት ብቀር ምን ነበረበት? የሌላ ሰው መሆኗን እያሰብኩ እንድቃጠል ለምን ይፈርድብኛል?..." ጓደኛው አቋረጠው።

"ለሁሉም ረጋ ማለት ያስፈልጋል አንተነህ! መንፈስህን ለማረጋጋት ሞክር፤ በጥሞና ለማሰብ ትችል ዘንድ ስሜትህን በረድ አድርገው፤ ከዚያ በኋላ ብቻ ነው ረጋ ባለ አእምሮ አስፈላጊውን ትንተና መስጠት የሚቻለው" አለ ጓደኛው የአንተነህ ድንገተኛ ለውጥ እየገረመው።

ጎን ለጎን ሆነው ጥቂት ተራመዱና አንተነህ ቆም ብሎ ጓደኛውን ተመለከተው። ትክሻውን እንደማራገፍ አደረገና "ይቅርታ! ሳታስበው፣ አንተም ብቻ ሳትሆን እኔም ሳላስበው በተፈጠረ ሁኔታ ስላስጨነቅኩህ ይቅርታ" አለው። "ይመስለኛል፤ ታሪኩን አጫውቼሀለሁ። ከዘመቻ ... ጀምሬ..." አቋረጠው ጓደኛው።

"ታዲያ ለምን አታናግራትም?" አለው ጓደኛው።
"ምን ብዬ ነው የማናግራት? ባልሽን ተይውና ከኔ ጋር እንሁን ብዬ ነው የማናግራት?" ጮኸ አንተነህ።



"ግን አንተ የምትወዳትን ያህል እርሷ እንደምትወድህ እርግጠኛ ነበርክ?" ሌላ የሚያናድድ የጓደኛው ጥያቄ ነበር።

"ስንት ዓመት እንደሆነና በምን ሁኔታ ውስጥ እንደተለያየን ታውቃለህ?" አለና አፈጠጠበት።

"እና ቢሆንስ አንተም ሆንክ እርሷ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለፋችሁት፤ እርሷ ነገር ዓለሙን ሁሉ ትታው ትዳር ስትመሰርት አንተ እንዲህ እንደአዲስ ፍቅረኛ ካልሞትኩ ማለት አለብህ? የምትለው ዓይነት ጠንካራ ፍቅር ቢኖራት ነው እንዲህ የምትሆነው? እኔኮ የሆሊውድ አክተር ነው የመሰለችኝ" አለው በማሾፍ።

አንተነህ የበለጠ ተናደደ። "በቃ አንተ ስሜቴ በፍጹም ሊገባህ አይችልም" አለና ባገኘው ጥላ ስር ዘፍ አለና ተቀመጠ።

"ስማ አንተነህ ከሞተ ዓመታት ያስቆጠረ ፍቅር እያነሳህ እዬዬ ስትል አብሬህ እንዳለቅስ የምትጠብቅ ከሆነ ተሳስተሃል። በጣም እየገረምከኝ መሆኑን ባወቅህ! እንኳን አንተን ሆኜ ላስብው" አለውና ጓደኛውም መቀመጫ ቦታ ፈልጎ አረፍ አለ።

"አየህ" አለ አንተነህ "አየህ አንተ እንደምትለው ቀላል አይደለም። ለኔ የነበራትን ፍቅር እንድጠራጠር የሚያደርገኝ ሃይል የለም። ስንለያይ ግን የመገናኘት ዕድላችን የመነመነ ነበር። እርግጠኛ ነኝ "አንተነህ ሞቷል" ብላ ነው የምታስበው። ይህን እያሰበች ደግሞ ዓለም በቃኝ ብላ ካልመለከሰች በስተቀር ሌላ ከማፍቀር መከልከል የለባትም፤ ፍቅሯን በእርሷነቷ ውስጥ ቀብራም ቢሆን ለማፍቀር መሞከሯ ሊያስኮንናት አይችልም። እኔስ ብሆን መቼ ከዚህ ውጭ ነኝ? ፍቅር ለመጀመር ያልሞከርኩት ሙከራ አለኝ? እኔን ፍቅሯ የተቀበረበትን ድንጋይ እየፈነቀለ እንደሚያስቸግረኝ ለእርሷም እንዲሁ ሊሆን ይችላል። ታዲያ የኔ በዚህ መሀል መገኘትና ማነጋገር በሁለት እሳት መሀል ሊጥላት እንደሚችል እያወቅሁ እንዴት ነው ይህ እንዲሆን መንገድ የምከፍትው? ደግሞምኮ ልጁም እኔ የወደድኳትን ያህል ሊወዳት ይችላል..." ጓደኛው አቋረጠው

"ቦታ የሚያዋጣህ ምን እንደሆነ ልንገርህ? እራስህን አሳምነህ "መልካም ጋብቻ!" ብለህ ከዚህ አካባቢ መጥፋት ብቻ!" አለው።

አንተነህ ፊቱ ተለዋወጠበት። "ዕድል እንዳልሰመረልኝ ተቀብዬ እንደቀለድከው "መልካም ጋብቻ" ለማለት ብችል ደስታዬ ነበር። ግን አንተ እንዳቀለልከው አይደለም። ይህን ሁሉ አገር አቋርጬ የመምጣቴ ምክንያት ከሆኑት አቢይ ጉዳዮች አንዷ ፍሬሕይወት በመሆኗ ነገሩን ቀለል አድርጎ መተው እንደማልችል ልትረዳልኝ በተገባህ ነበር" አለው በጓደኛው ላይ የምሩን እየተቆጣ።

ጓደኛው ሙከራው ሁሉ እንዳልሰራለት ሲያውቅ ዝም አለ። ቅድሙንም ቢሆን የአንተነህን ስሜት ላለማባባስ እንጂ ጉዳዩ ቀላል ነው ብሎ አስቦ አልነበረም።

"እሺ ምን ለማድርግ ታስባለህ?" አለው ጓደኛው ኮስተር ብሎ።

"መሄድ! በአስቸኳይ ወደመጣሁበት መመለስ" አለው አንተነህም ፍርጥም እንዳለ።

ዐይኖቹ እንባ ማቅረራቸውን ሲመለከት ጓደኛው የበለጠ አዘነና ከአጠገቡ ራቀ። አንተነህ ዐይኖቹ ላይ ተንጠልጥለው የነበሩ የእንባ ዘለላዎች ቁልቁል በጉንጮቹ እየወረዱ እሽሚዙ ላይ ሲንጠባጠቡ ዝም አላቸው።

"ምነው ፊጠን ባልኩ ኖሮ!" አለና ራሱን ወቀሰ። ወደኢትዮጵያ ተመልሶ ለመግባት ይችል እንደሆነ ለማጣራት የወሰደበት ጊዜ ረጅም ነበር። የፈለገውን መረጃ በፍጥነት ሊያገኝ ባለመቻሉ መቆየቱ ግድ ሆኖበት ነበር የዘገየው።

ድንበር አቋርጦ ሲወጣ የደረሰበትን ስቃይ፣ የአውሮፓን ኑሮ ለመልመድና የተረጋጋ ሕይወት ለመጀመር ያለፈበትን ውጣውረድ ሁሉ አሰበው፤ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ፍሬሕይወት አብራው ነበረች። ተስፋ በቆረጠባቸው ጊዜያት ሁሉ የሚጽናናው እርሷን ሲያስብ ነበር። በጓደኞቹ ግፊት እንደ ወጣት መሆን የሞከረባቸውን አጋጣሚዎች አስታወሳቸው፤ በጓደኞቹ አማካይነት የተዋወቃቸውንና አብረውት



የነበሩትን ሴቶች አሰባቸው... በዚህ ሁሉ ውስጥ ፍሬ በልቡ ውስጥ ያላትን ቦታ የነካው አልነበረም። እንባውን ሊያቆመው አልቻለም።

ከጥቂት ቀናት በፊት ወደኢትዮጵያ ሲመለስ ትንሽም ቢሆን ተስፋ ነበረው። የመጀመሪያ ሙከራውን ያደረገው በገባ በሰዓታት ውስጥ ነበር፤ የፍሬን ቤት ባያየውም አካባቢውን ስለሚያውቀው ወደዚያው አቀና። በመናኸሪያ ሆቴልና በግቢ ገብርኤል መሀል ያለውን አካባቢ አዳርሶ ሳይሳካለት ተመለሰ። ዱሮ ይቀጣጠሩባቸው የነበሩበት አካባቢ ሁሉ እየሄደ እንደሞኝ አላፊ አግዳሚውን ሲመለከት የቆየባቸው ቀናት ጥቂት አልነበሩም።

ወደቤተሰቦቹ ከመሄዱ በፊት ሌላ ሙከራ ለማድረግ አስቦ መንፈሱን ለማረጋጋትና ከፍሬሕይወት ትዝታ ጋር ለመሰንበት ወደአርባምንጭ ሄደ፤ የዘመቻ ጣቢያቸውን ለማየት፣ ከፍሬሕይወት ጋር የሄዱባቸውን መንገዶችና ተቀምጠው የተጫወቱባቸውን ሜዳዎች ለመመልከት... ያሰበውን ሁሉ አደረገ፤ በትዝታ ባሕር ውስጥ ሰጠመ፤ ለፍሬሕይወት ያለውን ፍቅር ጨመሩበት። ጓደኞቹን አስታወሰ፤ ከዩኒቨርሲቲ እስከ ዘመቻ፤ ከዘመቻ እስከ ተጧጧፈው የፖለቲካ ትግል... ትዝታው የትግል ጓዶቹን እያሰበ እንዲተክዝ አደረገው።

ወደአዲስ አበባ በተመለሰበት ዕለት "ለምን እግር መንገዳችንን አዋሳ ጎራ አንልም?" አለው ጓደኛው ። አንተነህ በሀሳቡ ተስማማና ወደአዋሳ አቀኑ።

"ከአርባምንጭ የተረፍከው መረጋጋት ሳይሆን የበለጠ መረበሽ ነው ፤ አዋሳ እንግባ " አለው ጓደኛው። አንተነህ ሀሳቡን ተቀበለና አዋሳ ገቡ። አዋሳ ደግሞ በፈረስ የተሻለ መዝናናት ትችላለህ" አለው።

የአዋሳ ቆይታው ግን ያልጠበቀው ነገር ላይ ጣለው ሲፈልጋት የሰነበተውን ፍሬሕይወትን በጋብቻ ደስታዋ ላይ እንዲያገኛት አደረገው፤ በውስጡ ያለውን ትንሽ ተስፋ አሟጦ ባዶነትን አስታቀፈው፤ ሕይወትን ጠላት።

* * * *

ፈቃደና ፍሬሕይወት ጓደኞቻቸው ባደረጉላቸው ነገር ተገርመው አላበቁም። በየእለቱ ያነሱታል፤ ባነሱት ቁጥር ይገርማቸዋል። በየዕለቱ ፎቶግራፎቻቸውን ያዩዋቸዋል አሁንም ይደንቃቸዋል።

"ግን ይህ ዓይነት ሀሳብ እንዴት ሊመጣላችሁ ቻለ" አለችና ጠየቀች ፍሬሕይወት አንድ ቀን ሁሉም በተሰበሰቡበት የረፍት ቀን።

"ሀሳቡን ዘውዱ አመነጨ፤ ከዚያ ሁላችንም ተስማማንበት። አፈጻጸሙን ደግሞ ማን እንዳሳመረው ታውቂያለሽ" አላት አንደኛው ጓደኛቸው። ዘውዱን ዞር ብላ ተመለከተችውና "ብቻ እድሜ ልኬን ሲደንቀኝ የሚኖር ነገር ነው አለች" ፍሬሕይወት።

"ምንም የሚደንቅ ነገር እኮ የለውም ፍሬ፤ ለሠርግ የማንጨነቀው እኛ ወንዶቹ ነን እንጂ ለሴቶች ግን ትልቅ ትርጉም የሚሰጥ መሆኑን ከሕይወት አጋጣሚ ማወቄ ነው ይህንን ሀሳብ እንዳቀርብ ያደረገኝ። አንዷት ያለሠርግ ያገባች ዘመዴ ከባለቤቷ ጋር ሠርግ ተጠርተው በሄዱ ቁጥር የምታለቅሰው እንባ መቼም የምረሳው አይደለም" አለና ነገራቸው።

ፍሬ በዘውዱ ውስጥ ብዙዎችን መልካም ሰዎች የምታይ ይመስላታል፤ እርሱ የትናንት አሻራ ነው። አመለካከቱ ይደንቃታል፤ ለዓላማ ያለው ጽናት ይገርማታል፤ "ለአገር መሥራት በፖለቲካ ብቻ ነው ያለው ማነው? በሕይወታችን እያንዳንዱ ቀን አንድ በጎ ነገር ማበርከት መቻል ላገር መሥራት ነው!" ይላል ሁልጊዜም ሰዎች ተስፋ የመቁረጥ አዝማሚያ ሲያሳዩት። በእርሱ ውስጥ ብዙዎቹን ታያቸዋለች፤ አንተነህን፣ በላይሁንን፣ ቅዱስን... ይገርማታል።

ከሌሎቹም የፈቃደ ጓደኞች ጋር እጅግ በጣም ተቀራረበች፤ በጣምም ተግባባች፤ ወደደቻቸው ወደዷት። በእያንዳንዱ አጋጣሚ ለፍሬ ሥራ ለመፈለግ የማይሞክር የለም ግን ሊሳካ አልቻለም። ሥራ ባለመግባቷ ብዙም አላዘነችም እንዲያውም ተመልሳ ወደትምህርት ቤት ለመግባትም እያሰበች ነበር።

አንድ ቀን "በሚቀጥለው ዓመት ትምህርት ቤት ብመለስስ? ሥራው እንደሆነ አልተገኘም" አለችው ፈቃደን።



"አንቺን ከተመቸሽ ለኔ ችግር የለውም" አለ ፈቃደ።

አንዳንዴ ሕይወት በሚገርሙ አጋጣሚዎች ትሞላለች። ሲያስቡበት የከረሙት ነገር ይቀርና በጭራሽ ያልገመቱት ነገር ይከሰታል። ፍሬንም የገጠማት ነገር እንዲህ ዓይነት ሆነ። አንድ ሰሞን ድንገት ጤና የማጣት ስሜት ተሰማት፡፡ ደነገጠች። ጠዋት ከእንቅልፏ ስትነሳና ቁርሷን ስትበላ ያለመደሰት፤ ብቻ መብሰክሰክ ጀመረች።

"ልጅ ሊመጣ ነው" አላት ፈቃደ። ደስታው ከገጽታው ላይ ሲፍለቀለቅ አስተዋለች።

ጤና ማጣቱና መነጫነጩ ቀጠለ፡፡ ክሊኒክ ሄደችና ተመረመረች መጸነሷን አረጋገጠች፤ ቀስ በቀስ ሀሳብ ገባት። ጊዜውን አሰላችው የምትወልድበት ጊዜ የሚቀጥለው ዓመት ትምህርት በሚጀመርበት ወቅት ነው። ትምህርት ቤት መግባት እንደማትችል ስታውቀው ሀሳቧን ደመደመች።

ተፈጥሮ የራሱን ቀመር ይከተላል የሚሆነው ሁሉ መሆን እስካለበት ጊዜ ድረስ ይቀጥላል፡፡ የፍሬ መነጫነጭ መበሳጨት ሕይወትን ከማነሳቆል ያለፈ አስተዋጽኦ የለውም። ፈቃደ "ምን ያምርሻል? ምን ባደርግልሽ ይመችሻል?" ይላታል እርሷን ለማስደሰት የማያደርገው ጥረት የለም።

ወራት ተቆጠሩ ሆዷም እርግዝናዋን ማሳበጥ ጀመረ። የሕይወቷን የመጀመሪያ ምእራፍ አጠናቅቃ ከልጅነት አልፋ የልጅ እናት ወደ መሆን እየተሸጋገረች መሆኗ ልዩ ስሜት ፈጠረባት። እያንዳንዱ ተፈጥሮአዊ ለውጥ እናቷን ያስታውሳታል፣ ያስቆዝማታል፣ አንዳንዴም ያስለቅሳታል። ሮቢን ማስታወስ ስለእርሱ ማሰብ የዘወትር ተግባሯ ነው፡፡ ሮቢል ወንድሟ ሳይሆን ልጇ ነው የሚመስላት፤ እርሱም እንደዛው ነው የሚያያት ልክ እንደ እናቱ። አንዳንዴ ከአእምሮዋ አልወጣ ይልና በጣም ያስጨንቃታል።

የምትቀርባቸው ሰዎች ወደአዲስ አበባ በሄዱ ቁጥር የፖስታ ሳጥን ከፍተው ደብዳቤ እንዲያመጡላት ታደርጋለች። ሮቢልም መጻፍ አይታክትም፤ ሁል ጊዜም ይጽፍላታል። ስለትምህርት ቤቱ፣

ስለጓደኞቹ፣ ስለአኗኗሩ፣ ስለቤታቸው፣ ስለኑሮ... ብቻ ምን የማይጽፍላት ነገር አለው? ናፍቆት ግን ከኑሮው ምቾት ሁሉ ልቆ እንደሚሰማውና ሁሌም እረፍት እንደሚነሳው ይነግራታል። ስለ ታረቀኝ ይጠይቃታል።

ለሮቤል የሆነውን ሁሉ ገለጸችለት፡፡ ትምህርት ማቋረጧንና ማግባቷን ማርገዟንም ጭምር ጻፈችለት። እስከመቼ ልትደብቀው ትችላለች? እርሱም በሁኔታው በጣም ማዘኑንና መናደዱን ጻፈላት፡፡ ከዛ በኋላ ግንኙነታቸው እንደበፊቱ ሊሆን አልቻለም። ሮቢን አልተቀየመችውም ልጅ ነው፤ በዚያ ላይ ታረቀኝን በጣም ይወደዋል፡፡ ታረቀኝ እንዴት እንደሚወዳትም ያውቃል፡፡ ከታረቀኝ ጋር ብትሆን በጣም ይፈልግ ነበር። ስለዚህ ያለውን ቢላት አልገረማትም፡፡ አንድ ቀን የሕይወት ምስቅልቅልነት ሲገባው ይረዳታል። ማን ያውቃል አንድ ቀን ሲገናኙ ሁሉንም ልትነግረው ትችል ይሆናል።

* * * *

አንተነህ ሊቆይ የፈለገውን ያህል ሳይቆይ ወደ "አገሩ" ተመለሰ። ለጓደኞቹ የሆነውን ሁሉ ነገራቸው። ሊመክሩትና ሊያበረታቱትሞከሩ፤ ሙከራቸው ሁሉ ግን የአንተነህን ልብ ሊያሸንፍ አልቻለም። የአንተነህ ምርጫ ራስን በማደንዘዝ ስቃይን መርሳት ሆነ። ድንዛዜው ሲለቀው እንደገና ሊበሳጭ፤ የበለጠ ሊሰቃይ ራሱን በመጠጥና በሲጋራ ማደንዘዙን ቀጠለበት።

የሊሊቱን አብዛኛውን ሰዓት ከመጠጥ ጋር አሳልፎ የማያረካ እንቅልፉን ተኝቶ ሲነሳ ራስ ምታት ይፈልጠዋል፤ ከምግብ ይልቅ የህመም ማስታገሻ መውሰድ ይቀናው ጀመር፤ እንክብሎቹን ይወስድና ወደሥራው ይሄዳል። የሥራ ባልደረቦቹ የሚመለከቱበትን የጸባይ ለውጥ በዝምታ ማለፍ ባለመቻላቸው ችግሩን ጠየቁት፤ አድበስብሶ አለፈው።

በሥራ ሰዓቱ ሁልጊዜም ከራሱ ጋር ይነጋገራል፤ የጀመረው መንገድ የሚያዛልቀው እንዳልሆነም ያውቀዋል። እናም ለራሱ ቃል ይገባል፤ ሁለተኛ ላይጠጣ፤ ራሱን ላይቀጣ ይወስናል። ከሥራ ሲወጣ ግን እግሩ በቀጥታ ወደመሸታ ቤት ይወስደዋል "ለዛሬ ብቻ" ይላል አንተነህ እግሩ ወደመራው እየሄደ።



አንዳንድ ቀን ደግሞ ውሳኔውን ያከብርና ከእግሮቹም ከራሱም ታግሎ ወደቤቱ ይገባል። እቤት ሲገባ የተዝረከረከ ቤቱ ያስጠላዋል፤ እናም ወንበሩን ይይዝና ወደበረንዳ ይወጣል። በሀሳቡ ከፍሬሕይወት ጋር ይውሉበት የነበረውን የአራት ኪሎውን አፓርትመንት ያስታውሳል። የዕቃዎቹ አቀማመጥና ንጽሕናው ወለል ብሎ ይታየዋል። ከሀሳቡ ጋር ብዙ ቢቆይ የሚያመው ይመስለዋል፤ ሁሉን ነገር ሊረሳ ይፈልጋል። እናም ከበረንዳው ላይ ይነሳና ውሳኔውን አፍርሶ ወደመሸታ ቤቱ ይሄዳል፤ እንደገና ሊደነዝዝ ራሱን ሊረሳ...

አንድ ቀን እንዲሁ ከሀሳቡ ጋር ተሟግቶ ውሳኔውን አፍርሶ ከቤቱ ወጣ። ወደተለመደው ቤት መሄድ ግን አልፈለገም፤ ከጓደኞቹም መቀላቀል አላሰኘውም። ጭቅጭቃቸው አስመርሮታል። ከሚኖርብት ሕንጻ ወጣና የለመደውን ጎዳና ትቶ በሌላ መንገድ እግሩ ወደመራው ሄደ። ለግማሽ ሰዓት ያህል ሲሄድ የት እንደሚገባ አላሰበም፤ ብቻ ዝም ብሎ ይራመዳል፤ ቀና ብሎ እንኳን ሳይመለከት አንገቱን አቀርቅሮ እርምጃውን የሚቆጥር ይመስል ይላወሳል።

ከፊት ለፊቱ የሚመጡትን ሰዎች አላስተዋለም፤ ድምጻቸው በርከት ሲልበት ቀና አለ፤ ለመጋጨት ጥቂት ሲቀረው ነው ቀና ያለው ፤ ላለመጋጨት ሲሞክር ተደነቃቀፈና ተግተርትሮ ቆመ።

"አላልኩሽም!" የሚል የአማርኛ ንግግር ሲሰማ የበለጠ ደነገጠ።

"ኢትዮጵያዊ ነህ?" አለችው አንደኛዋ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከታቸውና በአንገት ምልክት ኢትዮጵያዊ መሆኑን ነገራቸው። ቀና ብሎ አተኩሮ ሲመለከት ከሴቶቹ ውስጥ አንደኛዋ "እኔ አላምነም!" ብላ ጩኸቷን ለቀቀችው። "እኔ አላምንም! አንተነህ!" ብላ እንደገና ጮኸች። ሁሉም በድንጋጤ አፋቸውን ከፍተው ቀሩ።

"እየቃዠሁ ነው ልበል?" አለ አንተነህ የራሱን ጤንነት የተጠራጠረ ይመስል። ሄዋን አንገቱ ላይ ተጠመጠመችበት፤ ተቃቀፉ፣ ተላቀሱ የሄዋን ጓደኞች ከድንጋጤአቸው አልወጡም። ሄዋንና አንተነህ ይላቀቁና ይተያያሉ፤ እንደገና ደግሞ ይተቃቀፋሉ፤ ደቂቃዎች

አለፉ፤ ሁለቱም ወደ ትክክለኛ ማንነታቸው ለመመለስ አልሆነላቸውም። አጠገባቸው ያሉትን ሰዎች ዘንግተው በራሳቸው ትዝታ ውስጥ ቆዩ።

"ፍሬሕይወትስ?" አለች ሂዋን ሳታስበው። አንተነህ ምንም መልስ ስላልሰጣት ደነገጠች። "ምናልባት ሞታ ቢሆንስ?" አለችና በመጠየቋ ተናደደች።

"ለምን ተቀምጣችሁ አትጫወቱም?" አለች አንደኛዋ የሂዋን ጓደኛ። ሳይነጋገሩ ተስማሙና በአካባቢው ባገኙት መዝናኛ ውስጥ ገቡና ተቀመጡ፤ የሂዋን ጓደኞች እስካሁን የአንተነህን ማንነት አላወቁም። በኋላ ሂዋን ወደራሷ ስትመለስ "አንተነህ ይባላል፤ ጓደኛዬ ነው" አለቻቸው። "እነርሱም ጓደኞቼ ናቸው" አለች ደግሞ ወደአንተነህ ዞራ። ጓደኞቿ "ጋደኛዬ" የሚለው ነገር ግራ አጋብቷቸው እርስ በእርሳቸው ተያዩ። "ጓደኛዬ ስላችሁ ሊደንቃችሁ ይችላል፤ ዩኒቨርሲቲ አብረን የተማርን፣ አብረን ብዙ መከራ የተቀበልን የትግል ጓዴም ነው" አለቻቸው ስሜታቸውን ተረድታ። እንደገና ተያዩ፤ እነርሱ በዚያ ሕይወት ውስጥ ያላለፉ በመሆናቸው ብዙም ባይገባቸውም ብዙውን ጊዜ ስለእዛ የትግል ወቅት ሲነሳ የሂዋን ስሜት የሚለዋወጥባቸውን ጊዜያት ስለሚያውቁ ተቀበሏት።

"ከእነርሱ ጋር የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሳለን አብረን ነበርን፤ እነርሱ ቀደም ብለው ወደአሜሪካ በመሄዳቸው ስለአብዮት የሚያውቁት ነገር የላቸውም፤ ለዚህ ነው ግራ የገባቸው" አለችና ለአንተነህ አብራራችለት። ቀጠል አድርጋም ከጓደኞቿ ጋር ለሠርግ ወደፈረንሳይ መምጣታቸውን ነገረችው። የሆነ ያልሆነውን እያነሱ ሲያወሩ አብረው አመሹና በቀጣዩ ቀን ሊገናኙ ከሂዋን ጋር ተቀጣጥረው ተለያዩ።

አንተነህ እንቅልፍ አልወሰደውም። የሂዋንን እጮኛ ያስታወሰው እንቅልፍ አልወስድ ብሎት ሲገላበጥ ነው። ደህንነቱንና አብሯት መጥቶ እንደሆን ሳይጠይቃት በመቅረቱ ልትታዘበው እንደምትችል አሰበና ሃፍረት ተሰማው።



በሚቀጥለው ቀን ሂዋንና አንተነህ የተገናኙት ብቻቸውን ነው። ሲገናኙ የመጀመሪያው ጥያቄ ስለእጮኛዋ ነበር። "አይ አንተነህ!" አለችና ዝም አለች። አንተነህ በድንጋጤ ዝም አለ። "ይቅርታ" አላት ደግሞ ከጥቂት ቆይታ በኋላ።

"ለምኑ አንተነህ?" አለች ቀለል ባለ መንፈስ።

"ምንም መረጃ ስለሌለኝ..." አረፍተነገሩን ሊጨርሰው አልቻለም።

"እኔን ትናንት ያስደነገጠኝ ሀሳብ አስደንግጦህ ከሆነ አትጨነቅ፤ ተለያይተናል" አለችና ነገረችው።

አንተነህን ቀለል አለው። "አንችን ምን አስደነገጠሽ?" አላት።

"ትናንት ስለፍሬሕይወት ስጠይቅህ..." እርሷም አንጠልጥላ ተወችው።

"አገርቤት ሂጄ ነበር" አላትና ዝም አለ።

"መቼ?" አለችው በጥድፊያ።

"በቅርብ ጊዜ ነው የሄድኩት፤ አጋጣሚዬ የከፋ ሆኖብኝ እረፍቴን ሳልጨርስ ተመልሼ መጣሁ።

"አሁንም ጥቆማ አለ እንዴ?" አለችው የሚነግራትን ነገር ለመስማት በመጓጓት።

"ጥቆማ ቢሆን ሳይሻለኝ ይቀራል ብለሽ ነው?" አላት ቅዝቅዝ ባለ አነጋገር። ሂዋን ግራ ተጋባች።

"እግሬ ሲያንቀለቅል ወስዶኝ በፍሬሕይወት የጫጉላ ሽርሽር ላይ አደረሰኝ" አለና እቅጩን ነገራት።

"አታደርገውም!" አለችና ጮኸች። የተሰማት ስሜት ደስታ ይሁን ሀዘን መለየት አልቻለችም። ግን ድንጋጤ ተሰምቷታል።

ለደቂቃዎች ያህል በዝምታ ቆዩ፤ ሁለቱም በየራሳቸው ሀሳብ ውስጥ ነበሩ። ዝምታውን የሰበረችው ሂዋን ነበረች።

"እኔ ግን ይህ ሁሉ አጋጣሚ የሆነ መልዕክት እንዳለው ተሰማኝ" አለችው። ቀና ብሎ ዐይኖቿን በትኩረት ተመለከታቸው። "ይህን አባባሌን ግን ከጭካኔ እንዳትቆጥርብኝ፤ በወቅቱ ሊሰማህ የሚችለው ስሜት እንዲሰማኝ ብዙ ማሰብ አያስፈልገኝም፤ የቱን ያህል ከባድ ሆኖብህ እንደነበረም እንድታስረዳኝ መጠየቅ ያለብኝ አይመስለኝም። ግን በአንድ ነገር እንዳምን አእምሮዬ እየነገረኝ ነው፤ እኔም ላንተ አንተም ለእኔ የተፈጠርን መሆናችንን" አለችው እርሷም ትኩር ብላ እየተመለከተችው።

አንተነህ መልስ አልነበረውም፤ ዝምታን መረጠ። በአባባሏ እንዳልተናደደና እንዳላዘነባት ግን እርግጠኛ ነበረች።

* * * *

ፈቃደ ሁልጊዜም ከሰዓቱ ቀደም ብሎ ወደ ቢሮው ይገባ እንደሆን እንጂ አንድ ቀን እንኳ ሲያረፍድ ታይቶ አያውቅም። ብዙውን ሰዓቱን የሚያሳልፈው በሥራ ነው፤ ሥራው የሚፈልገው ከሆነ ሌሊትም ቢሆን በሥራ ላይ ይገኛል። የክፍሉ ሠራተኞች ብቻም ሳይሆኑ የድርጅቱ ሠራተኞች በሙሉ ይህን ያውቁለታል። በተለይ ከበታች ሠራተኞች ጋር ያለው ግንኙነት መልካም ነው ግን ይቆጣል፤ በተለይ በሥራ ላይ የሚያለምጥ ሰው በክፍሉ ውስጥ እንዲኖር አይፈልግም፤ ሠርቶ ያሠራቸዋል። ደግሞ ችግራቸው ችግሩ ነው፤ ያደምጣቸዋል፣ ገንዘብም ቢሆን ከማገዝ ወደኋላ አይልም። "ሁሉም አለቃ እንደርሱ ቢሆን" ይላሉ የበታቾቹ።

ፈቃደ እንደተለመደው በጠዋት ነው ቢሮ የገባው። የዕለቱን ተግባራቱን በማስታወሻ ደብተሩ ላይ በመጻፍ ላይ እያለ ስልኩ ጮኸና አስደነገጠው። በዚያ ሰዓት ማን እንደሚደውል ስለሚያውቅ በፍጥነት አነሳውና "ሄሎ" አለ። እህቱ ነበረች፤ ለረጅም ሰዓት ተነጋገሩ። በመጨረሻ ስልኩን ዘግቶ ግንባሩን ጠረጴዛው ላይ አስደገፈና ለብዙ ደቂቃዎች ቆየ።



ያንን ዕለት ለብዙ ጊዜ ረግሞታል። አሁንም ለስንተኛ ጊዜ ረገመው፤ ከእህቱ ጋር ብዙ ጊዜ ተጨቃጭቀውበታል አሁንም ተጨቃጨቁ። ለእህቱ ዐይኔን ግንባር ያድርገው ብሎ ቢክድም ራሱን ግን ሊክድ አይችልም። የሆነውን ነገር አሳምሮ ያውቀዋል፤ ግን ማመን አልፈለገም ዛሬም ከእህቱ ጋር እስከመጨረሻው ድረስ ተከራከረ።

ደገመና ያንን ቀን ረገመው፤ ቀኑ ያስገደደው ይመስል ምንም ያላደረገውን ቀን ደጋግሞ ረገመው። ክርክሩ እንደማያዋጣው አውቆታል፤ እህቱ በመጨረሻ ስልኩን ስትዘጋ "ይዤልህ እመጣለሁ" ነበር ያለችው። ሳያስበው "ይዤልህ እመጣለሁ?" አለና ደገመው። ራሱ የሚፈነዳ መሰለው፤ ተነስቶ ተንጎራደደ፤ ተመልሶ ተቀመጠ፤ የሚሆነው ሁሉ ጠፋበት። ፍሬሕይወትን አሰባት፤ እነዛን የነጭ ሴቶች ፎቶግራፎች አስታወሳቸው፤ የዛሬው ግን በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም። ፍሬ ዛሬ ነፍሰጡር ነች፤ እንክብካቤ የሚያስፈልጋት፤ መበሳጨት የሌለባት ሰው። ታዲያ እንዴት አድርጎ ነው ይህንን ጉድ የሚነግራት። መጮህ አማረው፤ እራሱን በሁለት እጆቹ ጥፍር አድርጎ ያዘና እጠረጴዛው ላይ ተደፋ።

ሰዓቱ እየሄደ ነው፤ መወሰን አለበት። የስልኩን መነጋገሪያ አነሳው ቁጥሮቹን አዞራቸው፤ ከመጥራቱ በፊት ዘጋው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንደገና ደወለ፤ ·አሁን ግን እስኪጠራ ድረስ ጠበቀው። የእህቱ ድምጽ መሆኑን ሲያረጋግጥ "እመጣለሁ" አላት ባጭሩ።

"መቼ" አለችው በአሸናፊነት·መንፈስ።

"በማንኛውም ቀን"

"ከሚቀጥለው ሳምንት ካለፍክ ግን..." አንጠልጥላ ተወችው።

ስልኩን ዘጋውና ተነሳ መኪና አዘዘና ወደመስክ ወጣ። መስክ ላይ ግን የወትሮው እንቅስቃሴው አልነበረም። ቆም ማለትና ማሰብ፣ በንግግር መሀል መዘናጋት አብዝቷል።

"ጋሼ ዛሬ አሞዎታል እንዴ?" አለው ሾፌሩ መንገድ ላይ እያሉ የጠየቀውን ነገር ሳይመልስለት በመቅረቱ ዞር ብሎ ሲመለከተው ፍዝዝ ማለቱን በማስተዋሉ።

መስክ ላይ ጥቂት እንደቆዩ ደግሞ "ወደቤት ብትገባ ይሻላል፤ ዛሬ ትክክል አይደለህም። አንዳንዴ እኮ እረፍትም ያስፈልጋል" አለው የመስክ ሠራተኛው ከወትሮው የተለየ ሁኔታ በመመልከቱ።

ቤት ሲደርስ ዘጠኝ ሰዓት ሆኖአል። ከመኪና ወርዶ ወደቤት ሲገባ ልቡ ፈራበት፤ የፍሬሕይወትን ዐይን እንዴት አድርጎ እንደሚያይ ጨነቀው። የሳሎኑን በር ከፍቶ ሲገባ ፍሬሕይወት ሹራብ ስትሠራ አገኛት። ግንባሯን በመሳም የተለመደ ሰላምታ ሰጥቷት ሶፋው ላይ ዘፍ አለ።

"ልታጠብ አይደል?" አላት ድንገት ብድግ ብሎ።

"ታጠብ፤ እስከዛ እኔ ምሳ አቀርባለሁ" አለችውና ቀድማው ተነሳች። ከጀርባዋ እየተመለከታት ተጨነቀ፤ ያን ሰዓት ተዓምር ተፈጥሮ ሁኔታዎች ቢቀየሩ ተመኘ። "ፈቃደ" የሚለው የፍሬ ድምጽ ተሰማው። "እመት" አለና ተነስቶ ወደውስጥ ገባ። የሚቀይራቸውን ልብሶች አዘጋጅታለት ነበር። "ዛሬ ግን በጣም ደክሞሃል" አለችው ልብሶቹን እያቀበለችው።
ሰውነቱን የታጠበው እንደነገሩ ነው፤ በደመነፍስ ተለቃልቆ ወጣ። እርሱ እስኪታጠብ ድረስ ምሳቸውን አቀራርባ ጠበቀችው። ፈቃደን ድብርቱ አልቀለለውም፡፡ ጉርሻውን ባይተወውም ከጉርሻው ጋር የነበረው ቀልድና ጨዋታ ግን የለም። ፍሬ ዐይን ዐይኑን አየችው፤ የበለጠ ጨነቀው።

ምሳ የበሉባቸውን እቃዎች እንደተለመደው ተጋግዘው አነሳሱና አጣጠቡ ሁሉም እንቅስቃሴ ግን ዝምታ የከበደው ሆነ። ሁሌም ከምሳ በኋላ እንደሚያደርጉት ለጥቂት ጊዜ ጋደም ለማለት ወደመኝታ ቤት ገቡ።

"ትንሽ ሽለብ ያድርገኝ?" አለና ፈቃድ ጠየቃት። ተስማማች። እርሱ ሲተኛ እርሷ ግን ወደሳሎን ተመለሰች። ፈቃደ እንቅልፍ



አልወሰደውም ፊቱን ወደግድግዳው አዙሮ ተኛና እንቅልፍ የወሰደው መሰለ። ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ ፈቃደ እየተንጠራራ ከመኝታ ቤት ሲወጣ ሊያልቅ ትንሽ የቀረውን የልጇን መቀበያ ሹራብ እየሠራች አገኛት። "እስኪ ፊትህን ታጠበው" አለችውና እንዳለችው አደረገ።

"ፍርዬ እንውጣ?" አላት ፊቱን ታጥቦ ሲመለስ።

"ለምን እዚሁ አረፍ አትልም ድካሙም የለቀቀህ አትመስልም" አለች።

"ግዴለሽም ስወጣ ይለቀኛል"

"በናትህ እኔም ይችን ሹራብ ዛሬ መቁረጥ ፈልጌያለሁ" አለች ደግሞ።

"ግዴለሽም ነገ ያልቃል" ብሎ ሹራቡን ከእጇ ወሰደና አስቀመጠው።

ተያይዘው ወጡ፡፡ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ የአዋሳ ሀይቅ ዳር ሆቴሎች በሰው ይሞላሉ። የዋናው አካባቢ በሰዎች ሙልት ብሏል፡፡ የሆቴሉ በረንዳ አንድ እንኳን ባዶ መቀመጫ አይታይበትም። ባለሞተርና ሞተር አልባ ጀልባዎች በሀይቁ ላይ ተበታትነዋል፡፡ እነርሱን መመልከት የሚወደውና ሀይቁ ላይ ለመንሸራሸር ወረፋ የሚጠብቅ ሰው በሀይቁ ዳርቻ ተኮልኩሏል።

እነፈቃደም ሁሉንም አልፈው ሂዱና ራቅ ካለው የሀይቁ ዳርቻ ድንጋዮች ላይ ለመቀመጥ ተዘጋጁ። ሁሌም እንደሚያደርግው ፈቃደ ለፍሬ መቀመጫ የሚሆን ትራስ ይዞላታል፤ አመቻቸላትና ተቀመጠች፤ እርሱም አጠገቧ ተቀመጠ። አሁንም ዝምታውን የሚገፍላቸው ጨዋታ አላገኙም። ቀስ ብሎ የፍሬሕይወትን ፊት ተመለከተው፤ በሃሳብ ርቃ የሄደች መሰለችው።

"የሆነ ነገር... ብነግርሽስ?። አለና ከሄደችበት የሃሳብ ጉዞ መለሳት።

"እንዴ ንገረኛ" አለችው ፊቷን ወደእርሱ መልሳ።

"በቃ ተይው ረፍታችንን መረበሽ አያስፈልግም" አላት ዳግም፤ ስሜቱ ተለዋወጠ።

"መተው አይቻልም ብትነግረኝ ነው የሚሻለው ነፍሰጡር ሴት ጭንቅ አትችልም" አለችው ለመቀለድ እየሞከረች።

"እሺ ሌላ ወሬ አምጭ"

"እንዲህ ዓይነት ነገር እንደማልወድ ታውቃለህ አይደል? ለምን አትነግረኝም" ተነጫነጨች።

"ቃል ከገባሽልኝ እነግርሻለሁ"

"ምን ብዬ ቃል ልገባልህ?"

"እንደማትጠይኝ"

ግራ የመጋባት ስሜት ተመለከተባት፡፡ ሊነግራት ያሰበውን ነገር ከአፉ ላይ መለሰው።

"አፉ! ብቻ በጣም ይከብዳል" አለ ዳግሞ።

"በቃ ተወው፤ እንዲያውም ከዚህ በኋላ መስማት አልፈልግም" አለችና ከተቀመጠችበት ተነሳች። መልሶ አስቀመጣት።

"ል...ጅ" የሚሉት ሁለት ፊደላት በትግል ከአፉ አፈትልከው ወጡ።

"ልጅ! ምን?" የሚከተለውን መፈለጓንና ያለመፈለጓን እንኳን እርግጠኛ አይደለችም። ተደበላለቀባት፤ በትክክል መስማቷን ተጠራጠረች።

"ግን በትክክል ተረድቼሃለሁ?" አለችው እንደምንም።

"አዎን ፍርዬ ተረድተሽኛል..." ከዚያ በኋላ የተናገረውን በትክክል አልሰማችም፡፡ የተቀመጠችበት ምድር የከዳት መሰላት፣ የልቧ ምት



ፍጥነቱ የጨመረ፣ ከንፈሮቿም የደረቁ፣ ምጥም የጀመራት መሰላት። አቅሟ ሁሉ በውስጧ የሌለ ያህል ድክም አላት፡፡ ፈቃደ የሚያደርገው ሲጠፋው ይታያታል፤ ግን ከማሳዘን ይልቅ ጠላችው፡፡ ሊደግፏት የሚሞክሩትን እጆቹን ተፀየፈቻቸው።

"ግን ለምን? ለምን በዚህ ሁኔታዬ ላይ መንገር አስፈለገህ? አላሳዝንህም?" አለች በደከመ ድምጽ።

"ምርጫ ስለሌለኝ ነው ፍርዬ! ደብቄሽ እንድሄድ ደግሞ ህሊናዬ አልፈቀደልኝም፡፡ ባስቸኳይ ሄጄ ካላየሁ ደግሞ ልጁን ይዛ እንደምትምጣ እህቴ ነገረችኝ" አለ ሁኔታውን ለማስረዳት።

"ደብቀኸኝ ብትሄድ ይሻለኝ ነበር" አለችው በዚያው በደከመ ድምጽ፤ ምን ያህል እርግጠኛ እንደሆነች ግን አታውቅም፡፡ እርግጠኛ የሆነችው እንዲህ ዓይነቱ ነገር መፈጠሩን መስማት የማትፈልግ መሆኗ ላይ ብቻ ነው።

በመከራ ከተቀመጠችበት ተነሳች፡፡ ቡዝዝ ባሉ ዐይኖቿ ወደመጥለቂያዋ የምታሽቆለቁለው ፀሐይ የሚያምር ቀይ ጨረር በአዋሳ ሀይቅ ላይ አርፎ የፈጠረው ሕብር የመድረክ ላይ ዝግጅት፣ የተንጣለለው የአዋሳ ሀይቅ ውሀም የትርኢት መድረክ፤ ደብዛዛው ብርሀን የአሳዛኙ ተውኔት መገለጫ መሰሏት። "ሁሉም ነገር ከንቱ ነው!" አለች ለራሷ።

ለመራመድ አንድ እግሯን ስታነሳ ተንገዳገደች፣ ዐይኖቿ ጨለሙባት፣ ጉልበቶቿም ተሸከመዋት መቆም ተሳናቸው ፣ተመልሳ መቀመጥም ደከማት። በሀሳቧ ግን ከንፎች አውጥታ መብረርና ከፈቃደና ከዓለም ፊት መጥፋት ተመኘች። እንዲህ ዓይነቱ ጥቃት ከሚደርስባት፣ ይህን ክህደት ከምትሰማ ይልቅ መሞት እንደሚሻላት አሰበች።

"ምነው ለትግል ጓዶች ያለኝ አክብሮት ሳይጎድል፣ መንፈሴን ከሞላው ፍቅርና ኩራት ጋር አብሬ በሞትኩ ኖሮ?" አለች ለራሷ። ያ አሮጌ ጃኬቱን እስከአንገቱ ቆልፎ በሰንሰለት የታሰረውና ከስታራው ፊቃደ በዐይነህሊናዋ ፊት ተደቀነባት። አጠገቧ ያለው ፈቃደ በምንም

መመዘኛ ያንን ፈቃደን ሊመስላት አልቻለም፡፡ ስቃይና ጥይትን በጽናት የሚቋቋም መንፈስ እንዴት ይህንን መቋቋም ያቅተዋል? አስደመማት።

ትንሽ ለመራመድ ሞከረች፡፡ ሰውነቷ ከቁጥጥሯ ውጪ ሲሆንባት እንደህልም ተሰማት… በቃ ሁሉም ነገር አበቃ። ከዛ በኋላ ምን እንደተፈጠረ አታስታውስም፡፡ ለቀናት ይሁን ለሰዓታት ለምን ያህል ጊዜ ራሷን ስታ እንደነበረ አታውቅም ፡፡ ራሷን ስታውቅ ግን ሆስፒታል አልጋ ላይ ነበረች። በነቃችበት ጊዜ ሆስፒታል መሆኑን እስከምታውቅም ደቂቃዎች ወስዶባታል። በተኛችበት ክፍል ኮርኒስ ላይ ተተክለው የነበሩትን ዐይኖቿን ነቅላ አካባቢዋን ለመቃኘት ሙከራ ስታደርግ ሦስት አልጋዎች መኖራቸውን አስተዋለች።

በአንደኛው አልጋ ዙሪያ በርከት ያሉ ሰዎች ተሰብስበዋል፣ በሌላው አልጋ ለይ የተኛችው ህመምተኛ ደግሞ በእጇ ላይ ግሉኮስ የተሰካላት የደከመች ሴት ነች። ከሴትዮዋ አልጋ አጠገብ ወንበር ላይ ተቀምጦ ራሱን አልጋዋ ላይ እንዳስደገፈ እንቅልፍ ሸለብ ያደረገው ሰው ግሉኮስ የተሰካበትን እጇን እንደያዘ ነው። ሌላኛው አልጋ ግን ባዶ ነው።

አካባቢዋን እያየች በአእምሮዋ ውስጥ ጥያቄዎች ይመላለሳሉ፡፡ “መቼ ነበር የመጣሁት? ምን ሆኜ ነበር? እንዴት ነበር የመጣሁት?…” ፈቃደ ላቡን ከግንባሩ ላይ እየጠራረገ ሲገባ አየችው በድንጋጤ ሆዷን ዳበሰችው። እንደነበረ ነው በሰከንድ ውስጥ ሁሉም ነገር ትዝ አላት፡፡ ሁሉም ነገር በአእምሮዋ ውስጥ ፍንትው ብሎ ታያት። ፈቃደን እንዲያናግራትና እንድታናግረው አልፈለገችም፤ ተሸፋፈነች።

ቀስ በቀስ ወደ ልቦናዋ ስትመለስና በትክክል ማሰብ ስትጀምር ወደአእምሮዋ የመጣው የመጀመሪያ ጥያቄ “እሺ ምናባቴን ላድርግ?” የሚል ነበር። ልጅ ይዛ የቤተሰቦቿን አና ቤት ከፍታ መግባት? “ዲቃላ ልጅ ይዛ መጣች” እየተባለች መጠቋቆሚያ መሆን? የወላጆቿ ስም ዝንተዓለም በመጥፎ ምሳሌነት እንዲጠራ ማድረግ? ልጅ ይዛ ሌላ ባል ማግባት ለልጇ የእንጀራ አባት ፊት ማሳየት?…” ሁሉም ቢሆን አማራጭ የሚሆን አይደለም። ሰዎች ባዩአት ቁጥር ሲንሾካሾኩ የማየትና የመስማት ትዕግስት የላትም፡፡ የሌላ ወንድ ሰውነት



የሚያስተናግድ አካልም የላትም። “ደግሞስ ከፈቃደ ያልተገኘ ዕምነት…” አለች ለራሷ።

እንጀራ እናት መሆንን መረጠች። ከሆስፒታል ከመውጣቷ በፊት ራሷን አዘጋጀች፡፡ መጪውን ሁሉ እንዳመጣጡ ለመቀበልና ልጇን ለማሳደግ ከራሷ ጋር ውል ገባች።

“ተሻለሽ?” አላት ፈቃደ።

“ደህና ነኝ” አለችው።

ጥቂት ቆይተው ሀኪሞቹ ገቡ መደረግ ያለበትን ሁሉ አድርገው ሲያበቁ “ዕድለኛ ልጅ ነሽ፤ ሁሉም ነገር በትክክለኛ ሁኔታ ላይ ነው፤ መውጣት ትችያለሽ” አሏት። ከሆስፒታል ወጣች።

ቤታቸው ገቡ፡፡ ፈቃደ ሠራተኛ እንዲፈለግ ነግሮ ኖሮ ጓደኛው ወዲያውኑ ይዞ መጣ። ፈቃደና ጓደኛው ለልጅቱ ሁሉንም ነገር አሳዩአት። ሥራዋን ቡና በማፍላት ጀመረች። ፍሬ ልጅቱን ወደደቻት።

ይንጋል ይመሻል ቀን ቀንን እየተካ አንድ ሳምንት ሆነ። የፍሬና የፈቃደ ግንኙነት ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት ነው። ሁሉ ነገር ሕግና ደንብ ተከትሎ የሚከናወን ይመስላል። አዲስ አበባም አልሄደም፡፡ የልጁን ነገር ምን እንዳደረገ ማሰብ ጀመረች፡፡ “ተከታዩ ሕይወት እንዴት ዓይነት ይሆን?” አለች ለራሷ።

“ለምን አዲስ አበባ አትሄድም?” አለችው አንድ ቀን። ደነገጠ።

“ተውኩት” አላት በአጭሩ።

“ለምን? እኔ ስለታመምኩ?”

“በቃ ተውኩት ሁለተኛ ስለዚህ ጉዳይ ማንሳት አልፈልግም” ብድግ አለ።

"ይሄ ራስን ማታለል ይባላል፡፡ አዲስ አበባ መሄድህን በመተውህ ልጅ አልተወለደም የሚል ትርጉም ይሰጣል? እኔስ ከዚህ በኋላ ፈቃደ ልጅ የለውም ብዬ ለራሴ ልነግር እችላለሁ? ልጅ እኮ የመጣው በአጋጣሚ ነው ዋናው ጉዳይ ያለው ሲጀመር ግንኙነቱን መፍጠሩ ላይ ነው..."

"ያን ቀን እኮ አላስጨረስሽኝም ፍርዬ..."

"ዛሬም እንድትጨርስልኝ አልፈልግም። ምንም ዓይነት ምክንያት ልትሰጠኝ ትችላለህ ለኔ ግን አንድ ትርጉም ብቻ ነው ያለው። ልጃችንን አብረን እንድናሳድግ የምትፈልግ ከሆነ እባክህን ሄደህ ማድረግ ያለብህን አድርግ" አለችው።

"እሺ ላስብበት" አላት።

"እንግዲያው ከእኔ ጋር ያለንን ግንኙነት እንጨርሳለን" አለችውና ጋደም ካለችበት ቀና ብላ ተቀመጠች።

"ኧረ በፈጠረሽ ፍርዬ ትንሽ እንድረጋጋ እንኳን ፍቀጂልኝ" አላት።

"ሁለት ቀን እሰጥሀለሁ ከዛ በኋላ ግን ከውሳኔዬ እንደማልመለስ እንድታውቅልኝ እፈልጋለሁ" አለች ፍርጥም ብላ።

ፈቃደ የፍሬሕይወት አዝማሚያ አላማረውም፤ አዲስ አበባ ሄዶ ተመለሰ፡፡ ምን እንዳደረገ ጠየቀችውና ቤተሰቦቹ ህፃኗን ሊያሳድጉለት መስማማታቸውን ነገራት። በቃ ከዛ በኋላ የልጅቱ ጉዳይ የሁለቱ አጀንዳ ሆኖ አልተነሳም።

ሕይወት ግን ቀጠለ ፍሬም ሥራ ፍለጋዋን አላቋረጠችም። የተከሰተው አጋጣሚ ያደረሰባት የመንፈስ ጉዳት ሳያንሳት እጇ ላይ ደርሶ የነበረውን የሥራ ዕድል ስላጨናገፈባት ንዴቷን እጥፍ ድርብ አደረገው። ላመለከተችበት ሥራ ለፈተና መቀመጥ ሲገባት እርሷ ግን ባልጠበቀችው አጋጣሚ ሆስፒታል መተኛት ኖረባት።

መጽናኛዋ የአዋሳ ሐይቅ ሆነ። በአዋሳ ሐይቅ ዳር ተቀምጣ ሀሳቧ እንዳሻው እንዲሆን ትለቀዋለች። ከውሀው እንቅስቃሴ ጋር መቆሚያ



በሌለው ሞገድ እየተላጋ ወዳለፈ የልጅነት ሕይወቷ ያስገባታል፡፡ ያስደስታታል፣ ያሳዝናታል...ብቻ እንደፈለገው ያደርጋታል። አንዳንዴ ትንንጎራደዳለች ሌላ ጊዜ ደግሞ ከጥላ ወደጥላ እየተዟዟረች ትቀመጣለች። ሀሳቧና የአዋሳ ሀይቅ ወዳጅነታቸው ጠና። ልክ እንደሠራተኛ ጠዋት የወጣች ለምሳ ወደቤት ትገባለች ከሰዓት በኋላ እንደገና ትወጣለች።

ቀኑ ወደማለቂያው ሲደርስና ፀሐይ ወደቤቷ ለመግባት ስታዘግም ለወትሮው በናፍቆት ትጠብቀው የነበረ የፈቃደ ከሥራ የመመለሻ ሰዓት ጥላቻን ይዞባት ይመጣል። ሁልጊዜም ቀን ቢሆንና ከአዋሳ ሀይቅ ጋር ብቻ እየተያየች ...እየተጫወተች ብትዘልቅ ደስ ይላታል። የአዋሳ ሀይቅ ባለውለታዋ ነው፡፡ ከሚያናድደው የገሀዱ ዓለም ሕይወት ይነጥላታል፡፡ በምትወደው የትላንት ሕይወት ትዝታ ውስጥ ይከታታል።

* * * *

የለበሰውን ኮት አውልቆ እላይኛው አልጋ ላይ ወረወረና እታችኛው አልጋ ላይ በጀርባው ተዘረጋ። ታረቀኝ ይሄን ሰሞን ሰላም የለውም። በጀርባው እንደተንጋለለ ዐይኖቹን በላይኛው አልጋ ርብራብ ላይ ተከላቸው። ዐይኖቹ የሚመለከቱት ግን የአልጋውን ርብራብ ሳይሆን ፍሬሕይወትን ነው።

ሰሞኑን የሰላም እንቅልፍ ተኝቶ አያውቅም፤ ይቃዣል አንዳንዴ በቅዠቱ ደንግጦ እየጮኸ ከእንቅልፉ ይነቃል። ጓደኞቹ በነጋታው መሳቂያ ያደርጉታል። በተለይ ትናንት ያየውን ህልም ከአእምሮው ሊያወጣው አልቻለም። ፍሬሕይወትን በአዋሳ ሀይቅ ላይ ስትንሳፈፍ ያያት፤ በመደነቅ ወደሀይቁ የሚቀርብ ይመስለዋል፤ እየቀረበ በሄደ መጠን ፍሬሕይወት አንዲት እንጨት ነገር ላይ ተንጠልጥላ እንደተንሳፈፈች ይመለከታል። የሀይቁ ውሃ በንፋሱ እየተገፋ ፍሬሕይወት የያዘችውን እንጨት ሊቀማት የደረሰ መሰለው። የውሀው ሞገድ እያንገላታት የያዘችው እንጨት ሊያመልጣት ሲልና አጥብቃ ለመያዝ ስትታገል ያያታል፤ ይደነግጣል። "ፍሬ አይዞሽ! በርቺ!" እያለ ከነልብሱ ውሀው ውስጥ ዘሎ ይገባል፤ ዋኝቶ ሊደርስላትና ሕይወቷን ሊያተርፍ። ቀና ሲል ግን ውሃው እያንገላታ ፍሬን

ወደሀይቁ መሀል ወስዷታል፤ ሊደርስላት በፍጥነት እየዋኘ ትንፋሹ እየተቆራረጠበት ሊጠራትና ሊያበረታታት ሲሞክር ድንገት ነቃ።

ሲነቃ ጓደኞቹ ያጠናሉ፤ መስማታቸውን የሚያመለክት አንድም ምልክት ባለማየቱ ደስ አለው። ድምጹ እንዳልተሰማ ገባው። ፍሬሕይወትን ግን ከአእምሮው ሊያወጣት አልቻለም። ሙሉ ቀን ሲያስባት ዋለ፤ ማሰብ ብቻ ሳይሆን የመነጫነጭ ስሜት ነበረው።

የመመረቂያ ጽሑፉን ሊያጠናቅቅ የቀረው የመጨረሻ ማስተካከያ ብቻ ነው። አማካሪ መምህሩ እንዲያስተካክል የነገሩትን ክፍል ለመሥራት የሚያስችለውን መረጃ ለማግኘት ጥናቱን ወደሰራበት መሥሪያ ቤት መሄድ ግድ ስለሆነበት እንጂ ዛሬ ከማንም ጋር ባይነጋገር ይወድ ነበር። መሥሪያ ቤት ደርሶ የሚፈልጋቸውን የሥራ ኃላፊ ለማነጋገር ጸሐፊዋን ማስፍቀድ ነበረበት።

ገና ሰላምታ ሰጥቷት መግባት ይቻል እንደሆነ ሲጠይቃት በአግባቡ ሳትመለከተው እንኳን ያለመኖራቸውን ነገረችው ።

"ዛሬ ይገቡ ይሆን?" አላት

"እኔ እንጃ አላወቅሁም" አለችው እየተቆናጠረች።

"ምን ጊዜ ብመጣ የማገኛቸው ይመስልሻል?" አላት ተስፋ ባለመቁረጥ።

"እየተመላለስክ መጠየቅ ነዋ!" አለችው። ከዚህ በፊት አይቷት የማያውቅ እስኪመስለው ድረስ ገረመው። እዚህ መሥሪያ ቤት ሲመላለስ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ወራት ናቸው የቀሩት፤ እንዲህ ተመናጭቃበት አታውቅም።

"ዛሬ ልጅቱን ምን ነካት?" አለና ራሱን ጠየቀ። ከዚያ በላይ ሊያነጋግራት አልፈለገም። ወደዩኒቨርሲቲ ተመለሰ።

መንገድ ላይ ደግሞ ሁሉን ትቶ ሀሳቡ ፍሬሕይወትን ደቀነበት፤ አሰባት። "ምን ሆና ይሆን?" አለ። "ይህን ጊዜ" አለ ደግሞ "ይህን ጊዜ



ትምህርቷን ባታቋርጥ እርሷም የመመረቂያ ጽሑፏን ትሠራ ነበር" አለ። የመመረቂያ ጥቁር ጋዋን ለብሰው በልደት አዳራሽ ውስጥ ጎን ለጎን ተቀምጠው በሀሳቡ ታየው። ስለልደት አዳራሽ ሲያስብ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነጋገሩበትን ሁኔታና ቦታ አስታወሰ። "ምነው ባላወቅኋት ኖሮ" አለ ታረቀኝ በስጨት ብሎ።

አዎን! ፍሬሕይወት በልቡ ውስጥ ባትኖር በጓደኞቹ ገፋፊነት የተዋወቃትን ልጅ አያስቀይማትም ነበር። ያስቀየማት ሆን ብሎ አልነበረም፤ ብዙ ጊዜ አብረው ሲሆኑ ስለፍሬሕይወት ስለሚያወራላት ነበር ልጅቱ የተናደደችበት። ብዙ ጊዜ "ሁለተኛ ስለፍሬሕይወት አላነሳም" ብሎ ለራሱ ቃል ይገባና ሳያስበው በሆነ አጋጣሚ ፍሬሕይወትን ያስታውስና ማውራት ይጀምራል። ልጅቱ ትናደዳለች፤ በኋላ ከታረቀኝ ጋር የመሰረተችውን ጓደኝነት እርግፍ አድርጋ ተወችው። ታረቀኝም ከዚያ በኋላ ከሌላ ጋር ለመተዋወቅ አልሞከረም።

ሁሉን ነገር ትቶ የፍሬሕይወት መንፈስ ከሰፈነበት ከዚያ ግቢ ለመውጣት ሆነ ጥረቱ። ከዚያ ግቢ ስለመውጣትም ሲያስብ ግን በሀሳቡ ውስጥ ፍሬሕይወት አለችበት። አቤት! ምን ያላወሩት ነበራቸው? ስላለፈውም ሕይወታቸው ሆነ ከዩኒቨርሲቲ ትምህርት ባሻገር ሊኖራቸው ስለሚገባው ሕይወት ስታወራለት ልቡን ትሰቅለው ነበር። ስላለፈው ስታነሳ እርሷ ራሷን የምትወድ በመሆኗ መትረፏ እያናደዳት በቁጭት ስታወራለት የነበራትን ስሜት ሲያስተውስ ይገርመዋል።

"ምን ማለት እየፈለግሽ ነው ፍሬ? በሕይወት የተረፍነው ሁሉ መትረፍ የማይገባን ከሆነ እንድ ትውልድ ለወሬ ነጋሪ እንኳ ሳይቀር ማለቅ ነበረበት እያልሽ እኮ ነው" ይላት ነበር ታረቀኝ።

"እንደሱ እንኳን ለማለት አይደለም፤ እነቅዱስ እነበላይሁን ሞተው እነአንተነህ እነ ሚሚ ተሰደው እኔ መትረፌ አንድም ቀን ሰላም ሰጥቶኝ ስለማያውቅ ነው" ትለዋለች።

"ቢያንስ በሙያችን ለዓላማ የምንኖር መሆን አለብን፤ ለሕዝብ እስቦ ሕይወቱን የሰዋ ትውልድ አካል በመሆናችን ፖለቲካው ባይሳካልንም

በሙያችን የጓዶቻችንን ዓላማ ተከትለን ለሕዝብ አገልጋይ መሆን ከቻልን ባለዕዳነታችንን ከሕይወት መስዋዕትነት በመለስ ለመክፈል እንችላለን..." ይላታል። ታረቀኝ ከፍሬሕይወት ጋር ሲያወሩ ውለው ቢያድሩ አይሰለቸውም ነበር።

የመመረቂያው ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ ታዲያ ሊረሳት የሞከረውን ያህል አልሰምርለት ብሎት በየሰዓቱ ያስታውሳት ይዟል። ይባስ ብሎ ይህን ሰሞን የሚያያቸው ሕልሞች ጭንቀት ጨምረውበት ስለፍሬሕይወት እንዲያስብ አስገድደውት ተቸግሯል።

"ለምን ግን ደብዳቤ አልጽፍላትም?" አለና ራሱን ጠየቀ። ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ ጽፎላታል እርሷም መልስ ሰጥታዋለች፤ ደብዳቤዋ ስለረበሸው መልሶ አልጻፈላትም። ደብዳቤ ከተለዋወጡ አንድ ዓመት ሊሆን ነው "ጊዜው እንዴት ይሮጣል?" አለ በመገረም።

ስለፍሬሕይወት የማወቅ ፍላጎቱ ባልገመተው ሁኔታ እየጨመረ የመምጣቱ ነገር አሳሰበው። "እስኪ የመጨረሻ ዓመት የመጨረሻ ሴሚስተር ላይ ሆኖ እንዲህ በሌላ ሀሳብ መወጠር ምን ይባላል?" ብሎ ከራሱ ጋር ተነጋገረ። ዩኒቨርሲቲ እንደደረሰ ደብዳቤውን ጽፎ ፍሬሕይወትን ከአእምሮው ለማውጣት ቸኮለ።

መኝታ ክፍል ሲገባ ግን ደብዳቤ የመጻፍ ፍላጎቱ ጥፍት አለበት። እነሆ አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋሎ ግን የሚያስበው ስለእርሷው ነው። እንደምንም ብሎ ከአልጋው ላይ ተነሳና ወደመስኮቱ ሄደ፤ በመስኮቱ አሻግሮ ሲመለከት ብዙ ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆነው ይጫወታሉ፣ ይሳሳቃሉ... ቀናባቸው። ድንገት በርካታ ዓረፍተነገሮች በአእምሮው ውስጥ መሰካካት ጀመሩ፤ ወረቀትና እስኪሪፕቶውን አንስቶ ደብዳቤውን መጻፍ ጀመረ።

* * * *

እንደወትሮው ሁሉ ምግብ ቤቱ በሰው ተጨናንቆ መተላለፊያ የለውም። አስተናጋጆቹ ትንፋሽ ሳያገኙ በጠረጴዛዎቹ መሃል ይሮጣሉ፤ ያቀርባሉ ያነሳሉ እንደገና ይታዘዛሉ... ማንም ማንንም የሚሰማ አይመስልም። ሚስጥረና ዳኙ እንደወትሯቸው ሁሉ



በጎደለበት ይሞላሉ፣ መመሪያ ይሰጣሉ፣ ደንበኞቻቸው መርካታቸውን ይመለከታሉ።
አንድ ሰው ወደምግብ ቤቱ ሲገባ የሁለቱንም ቀልብ ሳበውና ሁለቱም ሳያስቡት ወደርሱው ሄዱ።

"ይቅርታ በሥራ ላይ መጣሁ፤ ከግማሽ ሰዓት በኋላ እመለሳለሁ" አላቸው ሞቅ ካለ ሰላምታቸው በኋላ። ምሳ እንዲበላ ቢጠይቁትም ሲመለስ እንደሚደርስ ነገራቸውና ወጣ።

ዘውዱ አዲስ አበባ መጥቶ ከአቅሙ በላይ ሆኖበት ጊዜው ካልተጣበበት በስተቀር ዳኙንና ሚስጥረን ሳይጠይቃቸው አይሄድም። እዚያ ከመጣ ደግሞ የናፈቁትን ሰዎች ማግኘት እንደሚችል እርግጠኛ ነው። ለሁለትና ሶስት ዓመት የጠፉበትን ጓደኞቹን ሲጠይቅ አንዱ አንዱን ይጠይቅና እዚያው ድረስ ይመጡለታል። ከረጅም ጊዜ በኋላ ሲገናኙ ታዲያ ተለያይተው የሚያውቁ ሰዎች አይመስሉም።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ያ ወከባ የነበረ ቤት ተረጋጋና ሰላም ወረደበት። በምሳ ሰዓት የተተራመሰው ቤት ወዲያውኑ ተጸዳድቶና ተዘጋጅቶ ልዩ ይሆናል። አስተናጋጆቹ አንዲት ቆሻሻ ጠብ ስትል ማለፍ አያውቁም፤ በዚያ ላይ ትሁት ናቸው።

ዘውዱ ተመልሶ ሲመጣ ሚስጥረና ዳኙ የተለመደው ቦታቸው ላይ ተቀምጠው አገኛቸው። ገና ሲያዩት ሁለቱም ብድግ አሉና ተቀበሉት።

"ደስ ብሎናል እንኳን ደስ ያላችሁ" አለና እንደገና ሳማቸው።

"ወጣ ብለህ ምን አገኘህ" አለ ዳኙ።

"ፍሬ ወለደች" አለ ዘውዱ በደስታ። እንደገና ተቃቀፉ።

ምሳ እየበሉ ጨዋታቸውን ጀመሩ። መቼም ቢሆን የጨዋታው መጀመሪያ ሳይገኙ የቀዩ ሰዎችን ሁኔታ መጠየቅ ስለሆነ ዕድሉ ሁሉ የዘውዱ ነው። ዘውዱ ሁሉንም በየተራ ሲጠይቅ ቆዩና ቆም አደረገ።

"ፍሬ ግን እንዴት ነች?" አለች ሚስጥረ መቼ በጨረሰ ስትል የቆየች ይመስል።

"ደህና ነች" አለ ዘውዱ።
"ፈቃደስ?" አለች ደግሞ ቀጠለችና።

"እርሱም ደህና ነው" አለ። ዳኙ ግን በሀሳቡ አብሯቸው ያለ አይመስልም፤ ሚስጥረ ሰረቅ አድርጋ ተመለከተችው እርሱ ግን አላስተዋላትም።

የእውነትም ዳኙ በሀሳቡ ርቆ ሄዷል፤ ፈቃደ ከአውሮፓ ሲመለስ እዚሁ ምግብ ቤት መጥቶ ጠይቋቸው ነበር። ዳኙ ያንን እንደትላቅ ጀብዱ ለሞላ ያስነበበውን ደብዳቤ እያስታወሰ ነበር ከፈቃደ ጋር ሲያወሩ።

"አውሮፓ እንዴት ነበር?" አለው ዳኙ ፈቃደን።

"ጥሩ ነበረ" አለ ፈቃደ።

"መቼም ተመችቶህ እንደነበር እገምታለሁ" አለ ዳኙ።

"ጥሩ ነበር፤ የፍርዬ ነገር ሆኖብኝ ነው እንጂ..."

"ልትቀር አስበህ ነበር እንዴ?" አለ ዳኙ ፈጠን ብሎ።

"እንደማልቀር እንኳን ታውቀዋለህ፤ ሴቶቹ ግን..."

"እና የፍሬሕይወት ነገር ባይሆንብህ ኖሮ ሚስት ልታመጣ ነበር ማለትነው" አለ አሁንም ዳኙ።

"ለፍሬ ያለኝን ፍቅር እያወቅከው?"

"ብታመጣ ይሻላት ነበር ለፍሬሕይወት" አለ ዳኙ ቀበል አድርጎ።



"ምን ለማለት ፈልገህ ነው? ለፍሬ ያዘጋጀህላት ሰው ነበረህ ማለት ነው?" ፈቃደ ለመቀለድ ቢሞክርም ንዴቱ ይታወቅ ነበር።

"እኔ ለፍሬ ሰው የማዘጋጅበት ምክንያትም ፍሎጎትም የለኝም፤ ግን ፈቃደ አንተ ወጣ ባልክ ቁጥር እንደምትሆነው ፍሬም እንደዚያ ብታደርግ አይከፋህም?" አለው ዳኙ የፍቃደን ስሜት ቢመለከትም።

ያን ዕለት ዳኙና ፈቃደ አንድ ሁለት ሲባባሉ ተካረው በጸብ ነበር የተለያዩት። ከዚያም ወዲህ አልተገናኙ።

ስለፍሬሕይወት መውለድ ሲወራ ዳኙ የሚያስበው ይህንኑ ነበር። በዚህ ዙሪያ የፍሬና የፈቃደ አመለካከት በጣም የተለያየ መሆኑን በተለያየ ሁኔታ በማወቁ በአብሮነታቸው ፍሬ እንዳትጎዳ ይሰጋ ስለነበር ነው አሁን በሀሳብ ትቷቸው የሄደው። ሚስጥረ ያየችውን ነገር ለፍሬ ባለመንገሯ ሲቆጫት እንደነበረ ስለሚያውቅ ከፈቃደ ጋር መጋጨታቸውን ሳላልነገራት አሁን ብትሰማ ምን ልትለው እንደምትችል እያሰበ ነበር።

"ምነው ዳኙ አብረኸን አይደለህም እኮ" አለ ዘውዱ የዳኙን በሀሳብ መመሰጥ ተመልክቶ።

"ምን የነጋዴ ነገር ይሄው አይደል፤ በመሀል ስንቅር የሚል ነገር አይጠፋም" አለ ዳኙ በመቀለድ።

"መኪና አለህ እንዴ ዘውዱ?" አለች ሚስጥረ ስታስብ ቆይታ።

"አዎ አለኝ" አላት በአጭሩ።

"ቦታ ይኖርህ ይሆን አብሬህ ብሄድና ፍሬን ባያት" አለች ሚስጥረ ቀጠል አድርጋ።

"ማመቻቸት እችላለሁ" አለ ዘውዱ።

"ሌላ ጊዜ ብትሄድ አይሻልም?" አለ ዳኙ።

“መሄዴ ካልቀረማ አሁኑኑ ነው የሚሻለው” አለች ሚስጥረ።

ሚስጥረ ከዘውዱ ጋር አብራ እንደምትሄድ ተነጋገሩና ጠዋት መጥቶ እንደሚወስዳት ተቀጣጥረው ዘውዱ ሄደ። ዳኙ ስሜቱ ጥሩ እንዳልሆነ በመመልከቷ ሚስጥረ ዘውዱ እንደሄደ “ምን ሆነህ ነው ዳኙ እንዲህ የሆንከው?” አለችው ።

“ምን ሆንኩ?” አላት ጥያቄዋን በጥያቄ መልሶ።
“ስንተዋወቅ ዳኙ!” አለች ሚስጥረ።

“አንዳንዴ ባትፈልጊም ወደውስጥሽ የሚገባ ነገር የለም?” አላት።

“መኖሩማ ገብቶኛል፤ ያ ነገር ምንድነው ማለቴ ነው” አለችው።

“የፍሬ ነገር ያሳስበኛል፤ ያን ጊዜ በፈቃደ ላይ ያየሽውን ከነገርሽኝ ጀምሮ አስባታለሁ፤ ወዳልሆነ አቅጣጫ የመራናትና በገባችበትም ሕይወት የምትጎዳ ስለሚመስለኝ ይጨንቀኛል” አላት እየተከዘ።

“በእርግጥ በእኛ ምክንያት ሳይሆን በራሳቸው ጊዜ ነው ወደ ፍቅር የገቡት፤ ቢሆንም እኔንም ያሳስበኛል፤ ግን ደግሞ እድሜም ያስተምራልና ፈቃደ ሊለወጥ ይችላል” አለችው።

“አይመስለኝም የሚያሳስበኝም ያ ነው፤ አውሮፓ ሄዶ ሲቀብጥ ሰንብቶ መምጣቱ ሳያንሰው አንተ የምታደርገውን ፍሬ ብታደርገውስ? ብለው ተጣላን... እና ያ ባህሪ አብሮት ይዘልቅ ይሆናል ብዬ እሰጋለሁ” አለ ዳኙ የበለጠ ሃዘን እየተሰማው።

“እስኪ ፍሬን ሳገኛት ሁኔታውን ለማየት እሞክራለሁ። ስለነገርከኝ አመሰግናለሁ” አለችው ሚስጥረ።

* * * *



ፍሬሕይወት የጊዜው ፈጥኖ ማለፍ ሁሌም እንደደነቃት ነች፤ ዛሬን በነገ እየተካ የሆነው ሁሉ እያለፈ፤ ሌላ ዛሬ ...አዲስ ተስፋ...አዲስ ኩነት እያመጣ መንጎዱ ይገርማታል። ልጇ አደገችላት፤ ወራት ተቆጥረው ዓመት ሞላ ልጇም ወንከር ወንከር ማለት ጀመረች። ልጇ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለ ድጋፍ በእግሯ መቆም የጀመረችበት ዕለት በፍጹም አይረሳትም። ልጇ በአዲሱ የሕይወት ደረጃዋ ፍንድቅድቅ ስትል አብራት ፈነደቀች አብራት ወንከር ወንከር...ስትወድቅ አብራት ውድቅ...እንደገና ብድግ እጇን ያዝ...ዳዴ...ስትል ዋለች።

ማታ ፈቃደ ከሥራ ሲመለስ የምስራቹን ልትነግረው ቸኩላለች፡፡ ልጃቸው በእግሯ ስትሄድ እንዲያያትም ጓጉታለች። ገጽታው ግን ለዚህ ሁሉ የሚጋብዝ አልሆነም፡፡ ደስታዋን ሁሉ አጠፋው።

“ምነው አሞሃል እንዴ?” አለችው ገብቶ እንደተቀመጠ። በቃላት ሳይሆን የሆነ ወረቀት በመስጠት መለሰላት።

ወረቀቱ ደብዳቤ ነው፤ የቅያሬ ደብዳቤ። ፍሬሕይወት ደነገጠች። “የቅያሬ ደብዳቤ ድንገት ነው እንዴ የሚሰጠው?” አለች ደብዳቤውን አንብባ ስትጨርስ።

“ተነግሮኛል፤ እየተከራከርኩ ስለነበረ ይቀራል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነው ያልነገርኩሽ” አላት ፈቃደ።

“ምን ይሻለናል ታዲያ?” አለችው።

“እሄዳለሁ...”

“ማለት ብቻህን?” በጥያቄ አቋረጠችው።

“አዎን ብቻዬን እሄዳለሁ፤ ህፃን ልጅ ይዘሽ እንድትንገላች አልፈልግም” አላት። ብዙ ተነጋገሩ፡፡ ፈቃደ ሥራ ከፈታ መኖር የሚያስችል ምንም ገቢ በሌለበት መኖር ስለማይቻል ቅያሬውን መቀበል ግድ ነው። እናም ፈቃደ ወደተቀየረበት ቦታ ሔደ።

በትልቁ ቤታቸው ውስጥ ፍሬ፣ ልጇና ሠራተኛዋ ለብቻቸው መኖር ጀመሩ። ሕይወት በጣም ከበዳት፤ በተለይ በዚያ ትልቅ ቤት ውስጥ ማደሩን እንደጦር እየፈራችው ተቸገረች። ገና ምሽቱ ሲቃረብ ጨለማው ከመምጣቱ በፊት ፍርሀቷ እየቀደመ አስቸገራት። ሰው ሁሉ ተኝቶ እንቅስቃሴ ሁሉ ፀጥ ረጭ ሲል ጣሪያ ላይ የሚያርፍ ቅጠል የሚፈጥረው ኮሽታ፣ የንፋሱ ግፊት በበሩ በመስኮቱና በጣሪያው ላይ ታከክ ብሎ ሲያልፍ የሚፈጥረው ቃቃታ እንኳ እያስበረገጋት ተቸገረች።

እንቅልፍ በዐይኗ ሳይዞር የሚነጉት ሌሊቶች በርካታ ናቸው። እንቅልፍ እምቢ ሲላት ለማንበብ ትሞክራለች ሃሳቧ ያለው ውጭ ስለሚሆን ያነበበችውን በፍጹም አታስታውሰውም፤ ትናደዳለች።

"ለምንድነው ፈሪ የሆንኩት?" ትላለች እየደነቃት። ዱሮ እኮ እንኳን ልትፈራ ፍርሀት መኖሩንም አታስብም ነበር። ደፋር ነበረች ለምንም የማትደነግጥ ደፋር! "ታዲያ ዛሬ ያ ሁሉ ድፍረት ወዴት ሄደብኝ?" ራሷን ትጠይቃለች። "የምፈራው ለራሴ መኖር በመጀመሬ ይሆን? ምናልባት መውለድ ፈሪ ያደርግ ይሆን? ለልጄ ሕይወት እየሳሳሁ ይሆን?" ትላለች። እነዚህ ሁሉ መልስ የማታገኝላቸው ጥያቄዎች ናቸው።

ፈቃደ አንድ ወር ሳይሞላ ተመልሶ መጣ። "አሞሽ ነበር እንዴ?" አላት ገና ሲገባ።

"እንዴ,የውም! ምን ሆንኩ?" አለች ደንገጥ ብላ።

"ከስተሻል፣ ተጎሳቁለሻል..." አላት ሀዘኑ እየታየበት።

"አዲስ አበባ ብመለስስ?" አለችው።

"እኔስ?"

"አሁንስ መቼ አብረን መኖር ቻልን?"

"ልወስዳችሁ እኮ ነው የመጣሁት" አለና እቅፉን አሳወቃት።



"ይሄ እንኳን የሚሆን አይመስለኝም ህፃን ልጅ ይዞ መንከራተት ትክክል አይደለም..." አቋረጣት ፈቃደ።

"ብታምኝም ባታምኝም ካለእናንተ መኖር አልችልም አንድ ወር አንድ ዓመት እንደሆነብኝ ብታውቂ ይህንን አትይም ነበር። አልሄድም የምትይኝ ከሆነ ሥራውን ከመተውና አብሬያችሁ ከመሄድ ወደኋላ አልልም" አለ ፍርጥም እንዳለ።

ፍሬሕይወት፤ ደነገጠች የራስህ ጉዳይ ነው ማለት አትችልም፡፡ ሁለት ሥራ የሌላቸው የቤተሰብ ኃላፊዎች እንዴት አድርገው ቤታቸውን ሊመሩ ይችላሉ? ፈቃደ ደግሞ ያለውን ከመፈጸም ወደኋላ እንደማይል ታውቃለች። እናም ኀዟን ጠቅልላ ከፈቃደ ጋር አስላ መሄድ ሆነ ምርጫዋ።

አዲስ አካባቢ! አዲስ ሕይወት! በእርግጥ ሕይወት ከባድ አልሆነባትም። መልካም አጋጣሚ ተፈጠረና ፈቃደ የሥራ እድገት አገኘ የተሻለ ገቢ ኖረ። በጥቂት ወራት ውስጥ ቤታቸውን የበለጠ አደራጁና በተሻለ ሁኔታ መኖር ጀመሩ።

ልጃቸው አንድ ዓመት አልፏታል። "ልክ የዛሬ ሁለት ዓመት ትምህርቴን እቀጥላለሁ" አለች ለራሷ። ፈቃደ ደግሞ ሌላ ዕቅድ ይዞ ቀረበና ብዙ ተከራከሩበት።

"ገና ልጅ ነሽ ፍርዬ! ከዚህ በኋላ ሶስት ዓመት እንኳ ብትጨምሪ ገና ሀያአምስት ዓመት ነው የሚሆንሽ፤ ስለዚህ ትምህርትሽን ለመቀጠል ከባድ አይሆንብሽም" አላት። ተስማማችና ሁለተኛ ልጅ የመውለድ ፕሮጀክት ታቀደ።

* * * *

ያን ዓመት የልማት ባንክ በርካታ አዲስ ሠራተኞች ተመድበውለታል። እነዚህ አዲስ ሠራተኞች ወደየቅርንጫፎቹ ከመላካቸው በፊት አንድ የመተዋወቂያ ስብሰባ እንዲካሄድ ተወሰነ። ለዚህ ስብሰባ የየቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶቹ ኃላፊዎች እንዲገኙ ጥሪ

ተላለፈላቸው። ዘውዱ ከቅርንጫፍ ኃላፊዎች አንዱ በመሆኑ ለስብሰባው ሊታደም ወደአዲስ አበባ መጣ።

ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ላይ አዳራሹ ጢም ብሎ ሞላ። የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ስብሰባውን ከፈቱና ትውውቅ ተጀመረ። ከፊተኛው መቀመጫ ተጀምሮ እያንዳንዱ ሰው ሥሙን የሥራ ኃላፊነቱንና የሚሠራበትን ቅርንጫፍ ማስተዋወቅ ያዘ።
ታረቀኝ በአዲስ ሠራተኝነት ከተመደቡት መሀል ነው፤ የሚያስተዋውቁትን ሰዎች በጥንቃቄ ሲያዳምጥ ቆየ። ዘውዱ ተራው ሆነና ተነስቶ ስሙንና የሥራ ድርሻውን ተናግሮ የሥራ ቦታውን ሲጨምር ታረቀኝ ልቡ ዘላ ጉሮሮው ውስጥ የተወተፈች እስኪመስለው ድረስ መታችበት። ከዚያ በኋላ የተደረገውን ትውውቅ እንደመጀመሪያው በትኩረት አልተከታተለም። ብቻ የሻይ ሰዓት ደርሶ ያን ከአዋሳ መጣሁ ያለውን ሰው እስኪያነጋግር ቸኮለ።

የጠበቀው የሻይ ሰዓት ሲደርስ እንደምንም ተሹለክልኮ ዘውዱ ወዳለበት አካባቢ ተጠጋ። ድንገት አንድ ጥያቄ በአእምሮው ውስጥ ገባ "አሁን ከአዋሳ ስለመጣ ብቻ አዋሳ የሚኖር ሰው መጠየቅ ልክ ይሆናል?" የሚል። አዋሳ ምን ዓይነት ከተማ እንደሆነች እንኳን አያውቅም፤ ቢሆንም ከአዲስ አበባ በጣም እንደምታንስ መገመት ቀላል ነው።

"እንዴ አጠገቡ ልድረስ እንጂ ጥያቄዬን በዘዴ ማቅረብ አያቅተኝም" አለ ለራሱ። ለራሱ ሞራል ሰጠና ቀስ በቀስ ዘውዱ ወዳለበት ተጠጋ።

"ታረቀኝ እባላለሁ አዲስ ሠራተኛ ነኝ፤ ምድቤ ዋናው መሥሪያ ቤት ነው" አለ ዘውዱን ለመጨበጥ እጁን እየዘረጋ። ዘውዱ ቀልጠፍ ብሎ ጨበጠው።

"ወደ መሥሪያቤታችን እንኳን ደህና መጣህ፤ ዘውዱ ከአዋሳ" አለው። ዘውዱ የሚከብድ ሰው አይደለም። ታረቀኝ ወዲያውኑ ስለአዋሳ መጠየቅ ጀመረና አዋሳ ጠባብ ከተማ መሆኗንን ነዋሪውም ብዙ ያለመሆኑን አወቀ።



"ሰው ብጠይቅህ ምናልባት ታውቅ ይሆን? መቼም ጠባብ ከተማ ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች ለመተዋወቅ አይከብዳቸውም" አለ ደግሞ ታረቀኝ ልቡ እየዘለለችበት።

"ማን ያውቃል? ላውቅ እችል ይሆናል?" አለ ዘውዱ።

ታረቀኝ በጣም መቸኮሉ ቢሰማውም የጀመረውን ጥያቄ መቀጠል ስለነበረበት "ፍሬሕይወት ትባላለች..." ብሎ ሳይጨርስ።

"የምትላት ፍሬሕይወት እኔ የማውቃት ከሆነች..." ብሎ ሳይጨርስ "ባለቤቷ ፈቃደ ይባላል" አለ ታረቀኝ በችኮላ።

"በቃ እርሷው ነች" አለው ዘውዱ።

ልክ እራሷን ያገኛት ያህል ቢሰማውም ታረቀኝ ምን ማለት እንዳለበት ጠፍቶበት ተጨነቀ፤ የሻይ እረፍቱ በማለቁ እሮይ አለና ወደመቀመጫው ሄደ። ከተቀመጠም በኋላ ሀሳቡን መሰብሰብ አልቻልም፤ እዛና እዛ እንደረገጠበት የምሳ ሰዓት ደረሰ። አሁንም እንደምንም ብሎ ከዘውዱ አጠገብ ተቀመጠ። ምን እንደሚያወራለት አስቀድሞ አስቦበታል። ዘውዱም ቢሆን ከፍሬሕይወት ጋር የት እንደሚተዋወቁ ሊጠይቀው ፈልጎ ኖሮ አጠገቡ እንዲቀመጥ ይፈልግ ነበር።

"ጎረምሳው! ና እስኪ እዚህ ተቀመጥ" አለ ዘውዱ ታረቀኝን ገና ሲያየው። ታረቀኝ ዘውዱ አጠገብ ተቀመጠ።

"ለመሆኑ የት ነው ከፍሬሕይወት ጋር የምትተዋወቁት" አለና ጠየቀ ታረቀኝ አጠገቡ እንደተቀመጠ።

ታረቀኝ ከፍሬሕይወት ጋር ዩኒቨርሲቲ አብረው እንደነበሩ በአጭሩ ነገረው። "ፍሬሕይወት ጥሩ ልጅ ነች" አለ ዘውዱ።

"በጣም እንጂ" አለ ታረቀኝም ዘውዱ ያለውን በማረጋገጥ። በርካታ ጥያቄዎችን አከታተለ ፤ ስለልጇ፣ ስለጤናዋ፣ ስለትዳርዋና ሥራ አግኝታ እንደሆነ ጠየቀው ታረቀኝ። ዘውዱም መለሰለት።

"እንዳገኘኸኝ ባትነግራት ግን ደስ ይለኛል" አለው ደግሞ ጥቂት ቆየት ብሎ። ዘውዱን ግራ ሲገባው ተመለከተ።

"መመረቃችንን ስታስበው ትምህርቷን ያለመጨረሷ እንዳያናድዳት ብዬ ነው" አለ ታረቀኝ ዘውዱ ሳይጠይቀው።

"አትስጋ" አለው ባጭሩ።

* * * *

"ሕይወት እንዴት ዝብርቅርቅ ነች?" ትላለች ፍሬሕይወት እንዲሆን ትመኘው የነበረውንና እየሆነ ያለውን እያነጻጸረች። ቀስ በቀስ ሕይወት የምታቀርብላትን አማራጮች መቀበልን እንደቀላል ነገር መውሰድ ስለ ጀመረች ፈቃደ እንደገና ወደሌላ ቦታ የመቀየሩን ዜና በቀላሉ አስተናገደችው።

የአሰላን ኑሮ ገና በሚገባ ሳትለምደው ሌላ ቅያሬ መጣና ፈቃደ ወደ ባሌ ጎባ መቀየሩን በምሬት ነገራት። ልጃቸውን ማንከራተት እንደሌለባቸው ተስማሙና እርሱ ወደተቀየረበት ቦታ ሲሄድ እርሷ ወደአዋሳ ተመለሰች። አዋሳን የትውልድ አካባቢዋን ያህል ትወዳታለች እናም ወደአዲስ አበባ ከመሄድ ይልቅ ወደአዋሳ መመለሱ ቀለላት።

ፈቃደ በየመሀሉ እየመጣ ይጠይቃቸዋል፡፡ ፍሬ ኑሮውን ለመደችውና ብዙም አያስከፋትም። ወንድ ልጅ ወለደች፤ ደስ አላት፡፡ ፈቃደም እጅግ በጣም ተደሰተ፡፡ ስትወልድ መጥቶ ለተወሰነ ጊዜ አብሯቸው ቆይቶ ሄደ፡፡ ልጃቸውንም ማቴዎስ ብለው ሰየሙት። ፈቃደ ኃላፊነቱን በሚገባ ተወጣ፤ ከመውለዷ በፊት መደረግ ያለባቸውን ነገሮች ሁሉ ያለምንም ቀስቃሽ ኃላፊነቱን ወስዶ አከናወነ። ቤተሰቦቹ ሁሉን እንዲያደርጉ አመቻቸና አስፈላጊው ነገር በሙሉ ተዘጋጀ። ቤተሰቦቹን ግን ፍሬሕይወት እስከአሁን ድረስ በአካል አታውቃቸውም።



"ለምን ትጨነቃለህ ፈቃደ! ሠራተኛዋ ልታዘጋጀው ትችላለች እኮ" አለችው ፍሬ ፈቃደ ለቤተሰቦቹ ደውሎ መንገሩን ስትሰማ።

"ፍርዬ! እነዚህ ሁሉ የኔ ድርሻዎች ናቸው" አላት በቀላሉ። ሁሉም ነገር እንደሚገባው ሆነና ደስ ብሏት የአራስ ቤት ቆይታዋን አጠናቀቀች።

ፈቃደ መለስ ቀለስ እያለ እያያቸው ተለያይቶ መኖሩን ተላመዱት። ትልቋ ልጅ ሩት አራት ዓመት ሆናትና መዋዕለ ሕፃናት ገባች። ትንሹ ማቴዎስ አንድ ዓመት ሞላው፡፡ ልጆቿን ለማሳደግ ሙሉ ጊዜዋን ሰጠችና ለትምህርቷ የነበራትን ስሜት ችላ አለችው። ብቻ ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ሕይወትም አቅጣጫውን እየቀየረ ፍሬም የቤት እመቤትነቱን ሕይወት እየተላመደችው ሙሉ ስሜቷን ማህበራዊ ሕይወቷና ልጆቿ ወሰዱት።

ዓመታት ተቆጠሩ ከአዋሳ የመውጣቱ ነገርም እንደሰማይ እየራቀ ሄደ፡፡ ተደላድላ ተቀመጠች። ትንሹ ልጅ ማቲ እድሜው ደረሰና ትምህርት ቤት ገባ። የፈቃደም በተወሰኑ ጊዜያት ብቅ እያለ መሄድ ልክ እንደ ቀንና ሌሊት መፈራረቅ ተፈጥሮአዊ ሕግ እየሆነ ሄደ። ልጆቹ "አባታችንስ?" ብለው የሚጠይቁት በበአላት አካባቢ ብቻ ነው፡፡ ዘመን መለወጫ፣ ልደትና ትንሳኤ ሳይመጣ አሳልፎ አያውቅም። ፍሬም ብትሆን አእምሮዋ ውስጥ የነበራትን የሕይወት ስዕል እንዳልነበረ ትታው የሆነውን ከተቀበለች ሰንብታለች።

ለቤተሰቡ ያለው የአንድ ሰው ገቢ ለሁለት ቦታ ተከፍሎ የልጆች ወጪም ታክሎበት ብዙም የሚያወላዳ አልሆነም። ቤት መሥራትና ሳይሳቀቁ መኖር የሁልጊዜም ህልሟ እንደሆነ ቀርቷል። ብቻ እያደር ሁሉም ነገሮች ወደአልጠበቀችው አቅጣጫ እየመሩ የመሆናቸው ነገር ያሳስባታል፡፡ ከቤተሰቦቿ ኑሮ ያልተሻለ ሕይወት መቀጠሏ ይገርማታል። ደግሞ ሁሉም ሆኖ ከፈቃደ ጋር ያላት ግንኙነት እንኳ ቢያስደስታት ምን ነበረበት? ግን አልሆነም እያደር ብዙ ነገሮች እየተለወጡ ነው።

ፈቃደ እንደተለመደው የትንሳኤን በዓል አብሯቸው ሊያሳልፍ መጣ፤ ሁሉም በጣም ደስ አላቸው። አሁን ሩታ የስድስት ማቲ ደግሞ

የአራት ዓመት ልጆች ሆነዋል። ፈቃደ ሲመጣ የሚጋራት ዋነኛ ሥራ የልጆቹን ትምህርት መከታተል ነው፡፡ የቤት ሥራ ያሰራቸዋል፣ ያስነብባቸዋል፣ የሕፃናት መጽሐፍ ያነብላቸዋል። ልጆቹ በጣም ይደሰታሉ።

"አንተ ሁል ጊዜ ለምን አትመጣም? እማማ እኮ ብዙ ሥራ ነው የምትሠራው፤ ከዛ ደግሞ የቤት ሥራ መስራትና ሁል ጊዜ ደግሞ ለእኛ መጽሐፍ ማንበብ ይደከማታል" ትለዋለች ሩታ።

"እመጣለሁ ሩታዬ እኔ ደግሞ ገንዘብ ማምጣት ስላለብኝ እኮ ነው ሁልጊዜ ወደሥራ የምሄደው" ይልና ይመልስላታል።

"ለምንድነው እማማስ ገንዘብ ማምጣት የማትችለው? እሷስ በትምህርት ጎበዝ አልነበረችም? ግን አንድ ቀን እናትሽ ጎበዝ ተማሪ ነበረች ብለህ አልነበር?" የሩታ ጥያቄ ማቋረጫ የለውም።

ብቻ ፈቃደ ሲመጣ ቤቱ ሞቅ ይልና ነፍስ ይዘራል፡፡ ትዳርም የእውነት ትርጉም ይኖረዋል። ኃላፊነትን፣ ፍቅርንና ቤተሰባዊ ደስታን መጋራት አይደል ዋናው የትዳር ትርጉሙ?

* * * *

አንተነህ ዛሬ እረፍት ነው፤ ሁልጊዜም በእረፍቱ እንደሚያደርገው ቤቱን ማጽዳትና የተዘበራረቀ ቁምሳጥኑን ማስተካከል ነው የዛሬ ሥራው። ወጥቤቱን ማጽዳት ጀመረና ዕቃዎቹን ለማጠብ ወደማጠቢያ ገንዳው ውስጥ አስገባቸው። እጆቹ ሥራቸውን እየሠሩ አእምሮው ግን ከቤቱ ወጥቶ በቅጽበት ውስጥ አዲስ አበባ፤ አራት ኪሎ እጓደኛው አፓርትመንት ውስጥ ተገኘ።

ከፍሬሕይወት ጋር የተመገቡባቸውን ዕቃዎች ሲያጥቡ፣ ቤቱን ሲያጸዱ፣ በየመሀሉ ሲተቃቀፉና ሲላፉ፣ ሲሳሳሙ… "ወይኔ!" አለ አንተነህ የዕቃ ማጠቢያ ስፖንጁን የእጁ የደም ስር እስኪግተረተር ጭምቅ እያደረገ። የመጨረሻ መለያያቸው ዕለት ደግሞ ታወሰው፤ ያደሩባት የጠቋቆረች የሮቶ ማጠቢያ ክፍል፣ የተኙበት ፍራሽ፣ ያዳመጡት ግጥም፣ የተላቀሱት እንባ፣ ወጥታ ስትሄድ የተሰማው ስሜት… ከዚያ ደግሞ የአዋሳው ትዕይንት ተደቀነበት… እራሱን ብርጭቆ ውስጥ በመደበቅ እርሱነቱን ለመርሳት የሞከረባቸው



ወራት… ከሄዋን ጋር የተገናኙበት ምሽት… ትዝታውን መቋቋም አቃተው፤ የሚያጥበውን ዕቃ አስቀመጠና ወጥቤቱ ወንበር ላይ ተቀመጠ፤ ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ያዘና ጉልበቱ ላይ ተደፋ።

አብረው በመሆንና ባለመሆን፣ አሜሪካ በመምጣትና ባለመምጣት ከሄዋን ጋር የተጨቃጨቁባቸውን ቀኖች በፍጹም አይረሳቸውም። የሄዋን ትዕግስትና ያለመታከት መመላለስ በጣም ይደንቀው ነበር።

"ለምን ሄዋ?" ይላታል አንተነህ ከአሜሪካ እርሱ ወደሚኖርበት ፈረንሳይ ተመላልሳ ትጠይቀው በነበረበት ጊዜ ሁሉ "ለምን አትተይኝም ሄዋ? ለምንም የማልሆንና የማልጠቅም ሰው መሆኔን ተረድተሽ ለምን አትተይኝም?" ይላት ነበር።

"ይመስልሀል? አንተነህ ለምንም የማይሆንና የማይጠቅም ሰው ሆነ ብዬ ለራሴ ልነግር የምችል ይመስልሃል? ይልቅስ አንተ ለራስህ ልትነግረው ይገባሃል፤ የስንት ጓዶችን መስዋዕትነት የተቀበለ አእምሮ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ከፍቅረኛ መለየትን የዓለም መጨረሻ አድርጎ እንዲህ መቸገሩ ታላቅ ድክመት መሆኑን ለራስህ ልታሳምን ይገባሃል" አለችው አንድ ቀን።

"አንቺም?" አላት አንተነህ "አንቺም ፍሬሕይወትን የምታውቂያት ሰው እንዲህ አልሽኝ?" አላት ድምጹ እየተንቀጠቀጠበት።

"አዎ! ፍሬሕይወትን አውቃታለሁ፤ ግን ዛሬ የአንተ አይደለችም። የሌላ ሰው መሆኗን ደግሞ በዐይንህ አይተህ መጥተሃል። አንተነህ እኔስ? እኔስ ለምን አልታይህም? በስህተት አጥቼህ የሌላ ሰው ስትሆን ራሴን አሳምኜ ተቀበልኩ፤ ቢሳካልህና እስከወዲያኛው አብራችሁ ብትሆኑ ደስ ባለኝ፤ ግን አልሆነም። ዛሬ ደግሞ አጋጣሚ እንዳገኘህ ፈቀደ፤ የተገናኘነው ደግሞ ከሁለታችንም ግምት ውጭ በሆነ ሁኔታ እንጂ ተፈላልገን አልነበረም። ግን ዛሬ ነጻ ሰው ነህ፤ እና ለምን የከፈልኩትን መስዋዕትነት አታስበውም? የምትጠላኝ ከሆነ እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ። ከዚያ በኋላ አጠገብህ አልደርስም" አለችው።

አንተነህ ደነገጠ፤ ሄዋንን በፍጹም አይጠላትም፤ እንደምትወደውም በሚገባ ያውቃል። "ግን ፍሬሕይወትስ?" አለና ራሱን ጠየቀ።

"ፍሬሕይወትማ አግብታለች" መለሰ ሌላው ሀሳቡ።

"ከሄዋን ጋር በነበረን ግንኙነት ድሮም ጥርጣሬ ስለነበራት አሁን አብረን መሆናችንን ብትሰማ ያታለልኳት ቢመስላትስ?" አሁንም ከራሱ ጋር ተሟገተ።

"ዕውነታውን መንገር ብቻ!" ሌላው ሀሳቡ በፍጥነት መለሰ። "ትንሽ ጊዜ ልትሰጭኝ ትችያለሽ ሄዊ? ከራሴ ጋር እስክታረቅ ድረስ ጊዜ ያስፈልገኛል" አላት።

"የፈለግከውን ያህል ጊዜ ልሰጥህ እችላለሁ፤ ግን እየመጣሁ አይሃለሁ" አለችው። ተስማሙ። የእውነትም ተመላልሳ ጠየቀችው፤ አንድም ቀን "ምን ወሰንክ?" አላለችውም።

አንድ ጊዜ ልትጠይቀው ስትመጣ ከራሱ ጋር እየታገለም ቢሆን አሜሪካ ለመሄድ መስማማቱን ለሄዋን ነገራት። ከመቼው ተነስታ አንገቱ ላይ እንደተጠመጠመችበት ባስታወሰው ቁጥር ፈገግ ያሰኘዋል።እናም አንተነህ አሜሪካ ከመጣ ዓመታት ተቆጥረዋል። ሄዋንን የተለየች ፍጥረት ሆና አገኛት፤ ድሮም የሚዋደዱ ጓደኞች ነበሩ፤ አሁን ደግሞ ለፍቅር የምትሰጠውን ክብርና ስስት የሌለበት አፍቃሪነቷን አድንቆ ማብቃት አቅቶታል።

እርሱም የምትሰጠውን ፍቅር ሊሰጣት ያደረገው ጥረት ተሳክቶለታል፤ መንፈሱ ተረጋግቶለታል፤ ቤታቸው ሰላም የሰፈነበት፣ ኑሮአቸው በብዙዎች ዘንድ "የሚያስቀና" ተብሎ የሚፈረጅ ሆኗል። ቢሆንም ግን አንዳንዴ ፍሬሕይወትን ማስታወሱና መብከንከኑ አልቀረም፤ ሄዋን እንዳታውቀበትና ደስታዋን እንዳይሸርፍባት ይጠነቀቃል። እንዲህ እንዳሁኑ ብቻውን ሲሆን ብቻ ነው ከትዝታው ጋር የሚፋጠጠው።

አሜሪካ ሲመጣ ደግሞ ሀሳቡን የሚከፍልለት ለየት ያለ ነገር ገጥሞታል። ብዙ የሚያውቃቸውን ሰዎች አግኝቷል፤ ከስደተኛ የኢሕአፓ አባላት ጋር ተዋውቋል። አብሯቸው የሚያሳልፋቸው



ጊዜያት ይናፍቁታል፣ እንደልቡ ይናገራል፣ ስሜቱን ይገልጻል... ከእነርሱ ጋር ሲሆን ነጻነት ይሰማዋል፤ አንዳንዴ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ እስኪመስለው ድርስ ከኢትዮጵያውያን ጋር ውሎ ያድራል...

"እፎይ!" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰና ሰዓቱን ተመለከተ፤ የሄዋን መምጫ ደርሷል። ከተቀመጠበት ተነስቶ ፊቱን ተጣጠበና በፍጥነት ዕቃዎቹን ማጠቡን ቀጠለ።

* * * *

እንደተለመደው ፈቃደ ሊጠይቃቸው መጥቶ የሚሄድበት ቀን ደረሰ፤ ፍሬ የፈቃደን የጉዞ ሻንጣ ማዘጋጀት ነበረባትና ውስጡ ያሉትን ልብሶች አወጣጥታ ለማራገፍ ዘቅዘቅ አድርጋ መታ መታ አደረገችው፤ የሆነ ወረቀት ዱብ አለ። ወረቀቱን አነሳችው፤ ፎቶ ግራፍ ነው፡፡ መስከ ላይ ጋደም ያለች የሴት ምስል! ደንገጥ አለች፡፡ መገረም ይሁን ንዴት ውስጧን ረበሸው።

"አቤት! እንዴት የተለያየን ሰዎች ነን" አለች ለራሷ። ደግሞ እውነቱን ሳታረጋግጥ በዚህ መንገድ በመደምደሟ ራሷን ወቀሰች። በውስጧ ቅሬታ ከማስቀምጥ ልትጠይቀው እንደሚገባትም ወሰነች።
"ይሄ ፎቶ የማን ነው?" አለችው ፈቃደን። ቀለል አድርጎ መለሰላት፤ ዱሮ ተማሪ እያለ ያውቃት እንደነበረና በአጋጣሚ አግኝቷት እንደሰጠችው ነገራት። ከዱሮ ትውውቃቸው ባሻገርም ሲገናኙ የነበራቸውን አብሮነት መደበቅ አላስፈለገውም። ለእርሱ ብቻውን በሚኖርባቸው ጊዜያት ተፈጥሮአዊ ስሜቱን ማርካት ምንም ስህተት የለበትም፡፡ ለእርሱ የሚፈጽመውን ድርጊትም ከፍሬ መደበቅ መሸፋፈን እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም። ይህ ሁኔታው በጣም ይገርማታል፤ ደግሞም እምነቷን ይሸረሽርባታል።

"አሁን እኔም ተመሳሳይ ድርጊት ብፈጽም እንዲሁ ያቀለው ይሆን? ሁሉም ወንዶችስ ከሚስቶቻቸው የሚጠብቁትን ታማኝነት ሚስቶቻቸው ከእነርሱ እንደሚጠብቁ አይረዱም ይሆን? ለመሆኑ ብዙዎቹ ወንዶች ስሚታቸው ያዘዛቸውን ለመፈጸም ወደኋላ የማይሉት ልምን ይሆን ለትዳራቸው ሲሉስ ስሜታቸውን መግታት ግዴታቸው ሊሆን እንደሚችል የሚያስቡት መቼ ይሆን?" የሚሉት ጥያቄዎች

በአእምሮዋ ውስጥ ይመላለሳሉ፤ ሁሌም መልስ የማታገኝላቸውና የሚፈትኗት ጥያቄዎች!

እርሷ ተመሳሳይ ድርጊት ብትፈጽም በቀላሉ እንደማያልፋት የተረዳችበት አጋጣሚ ትውስ አላት። ያን ዕለት የሩታ ክርስትና ዋዜማ ነበር፡፡ ፍሬና ፈቃደ በየፊናቸው ሥራውን ተያይዘውታል። እርሱ ቤት ያዘጋጃል ፍሬ ደግሞ ማዕድ ቤት ትንጎዳጎዳለች፤ ፈቃደ እቤት ሆኖ ሲጣራ ሰማችው "አቤት" ብላ ወደቤት ገባች፤ ፈቃደ በእጁ አንድ ፓስታ መያዙን ስትመለከት ለምን እንደጠራት ወዲያውኑ ነበር የገባት።

"ጠራኸኝ?" አለችው መኝታ ቤት በር ላይ ቆም እንዳለች።

"ይህን ደብዳቤ ማን ነው የጻፈልሽ?" አላት የፖሊስ ጥያቄ በሚመስል አነጋገር።

"አድራሻው እላዩ ላይ አለልህ አይደል?" አለችው በቀላሉ።

"እላይ ያለው አድራሻና የውስጡ ይዘት ግን አይመሳሰሉም" አለ ቁጣው እየጨመረ።

"ሌላ ጊዜ ብንነጋገርበት አይሻልም?" አለችው። ዝም አለና ፖስታውን ወደ መሳቢያው መለሰው።

ፈቃደ ፊቱ ሳይፈታ፤ እንግዶቻቸውን በሚገባው መልኩ ሳያስተናግዳቸው የልጃቸው ክርስትና እንደነገሩ አለፈ። ያን እለት ወደማታ ስለ ደብዳቤው ይጠይቀኛል ብላ ብትጠብቀውም ሳያነሳው ቀረ፡፡ እንደተኳረፉ አደሩ። የሚቀጥሉትም የሥራ ቀናት እንዲሁ በዝምታ ቀጠሉ፡፡ እርሷም እልህ ያዛት ነገሩን እርሱ ካላነሳው ላለማንሳት ወሰነች።

እሁድ ወደረፋዱ ላይ ከቤተክርስቲያን መልስ ቡና ጠጥተው ሲያበቁ ሁለቱም ደስተኞች አልነበሩም። ፍሬ መደበቂያ አላት ልጇ! መልስ ከማትሰጣት ከልጇ ጋር ታወራለች፤ ትጫወታለች...



"ስለዚያ ደብዳቤ እንድንነጋገር እፈልጋለሁ" አለ ፈቃደ።

ፍሬ ሁኔታውን ለማስረዳት ጥረት አደረገች የሆነውን ሁሉ ምንም ሳትደብቅ ነገረችው። የፈቃደ ቁጣ ግን እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልሄደም።

"ሰማኝ ፈቃደ የአንተን ፍቅር በሌላ ላለመለወጥና ቃሌን ላለማጠፍ ስል እምነቴን ሳላጎድል ትምህርቴን መስዋዕት ማድረጌ ወደአንተ መምጣቴ የሚገልጽልህ ታረቀኝን መውደዴን ከሆነ እንደፈለገህ ማድረግ ትችላለህ" አለችው እርሷም ተቆጥታ '...የአንተ ልሆን ስለማልችል አትውደደኝ ብትይኝም እኔ ግን ከማፍቅር ወደኋላ ማለት አቃተኝ...' የሚለው ዓረፍተነገር ለእርሱ ምን እንደነገረው እንዲያስረዳትም ጠየቀችው።

ፈቃደ ሊያምናት ባለመቻሉ በጣም ተናደደች። ንዴት ደግሞ ያለችበትን ሁኔታም አስረሳት፡፡ ሕፃን ልጇን ይዛ ወዴት ልትሄድ እንደምትችል እንኳ አላሰበችም።

"የማታምነኝ ከሆነ ዛሬውኑ መለያየታችንን እመርጣለሁ። ከሌላ ወገን የተገለጸ ፍቅር ይህን ያህል የሚያደርግህ ከሆነ ከእኔ ጋር እያለህ ከሌላ ሴት ልጅ መውለድህን ስትነግረኝ ስሜት የሌለኝ ግኡዝ አድርገኸኝ ነበር ማለት ነው? ወይንስ "በሚስትና በእርስት..." የሚለውን ያባቶችህን ተረት እያስታወስክ? ይህ ዓይነቱ አመለካከት ካለህ አሁኑኑ ምርጫችንን ማስተካከል ያለብን ይመስለኛል" አለችው።

ፈቃደ ምንም ሳይናገር ትቷት ወጣ ሲመለስም ስለጉዳዩ አላነሳም። ብቻ ቀስ በቀስ ሁኔታውን እየተወ ወደወትሮው ግንኙነታቸው ተመለሱ። ከዚያ በኋላም አንስቶት አያውቅም።

ፍሬ ያሳለፉቻቸውን አጋጣሚዎች ስታስባቸው በጣም ይገርማታል። የፈቃደን ልጅ መውለድ ከሰማች በኋላ ታረቀኝን አግኝታው ይቅር እንዲላት ብትጠይቀው ምኞቷ ነበር። ምናልባትም ያን ጊዜውኑ አግኝታው ቢሆን ኖሮ ምን ታደርግ እንደነበረ ስታስበው ትደነግጣለች። ቢሆንም ፈቃደን ደህና ሁን ብላው ከታረቀኝ ጋር ትሆን እንደሆነ እንጂ ከታረቀኝ ጋር ጊዜያዊ ግንኙነት መፍጠርን

የማታስበው ጉዳይ ነው። ይቅር ብላ ኑሮዋን መኖር ከጀመረች በኋላም ከታረቀኝ ጋር ባልጠበቀችው ሁኔታ ሲገናኙ ለሁለተኛ ጊዜ ፍቅሩን ገፍታ ያስቀየመችው ለትዳሯ ያላትን ታማኝነት ለማረጋገጥ ስትል ነበር።
አንድ ጊዜ ትምህርት ባቋረጠች በሁለተኛው ዓመት የትምህርት መረጃዋን ለሥራ ውድድር ፈልጋ ቤት ውስጥ ልታገኘው ባለመቻሏ የግድ ዩኒቨርሲቲ ሄዳ ማምጣት አስፈላጊ ሆነ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ደጅ ስትረግጥ ታዲያ ያስታወሰችው የመጀመሪያው ሰው ታረቀኝ ነበር። በጣም አሰበችው አብረው የተቀመጡባቸውን ቦታዎች ሳይቀር አሰበቻቸው። ቢሆንም ታረቀኝን ፈልጋ ለማግኘት ፍላጎት አልነበራትም፡፡ ብታገኘው ጠልታ ሳይሆን እንዳትረብሸው በመፈለግ ነበር።

በቀጥታ የሄደችው ሬጂስትራር ነበር፡፡ በመስኮት በኩል ለማናገር ስትሞክር ማንም የለም። በበሩ በኩል ዞረችና ወደውስጥ ገባች። ረጅሙ አሮጌ ሕንፃ ውስጡ በቂ ብርሀን የለውም፤ ወደውስጥ ገብታ ሰው ያለበት ክፍል ለማግኘት ሞካከረችና ማንንም በማጣቷ ተመልሳ ወጣች።

ጊዜው ስድስት ሰዓት መሆኑን ያየችው ከሬጂስትራር ከወጣች በኋላ ነበር። የት እንደምትቆይ ግራ ግብት አላት፡፡ ይህንኑ እያሰበች ቀስ ብላ እየተራመደች ላውንጅ ደረሰችና ጎራ ብላ ተቀመጠች። ምን እንደምትፈልግም  እርግጠኛ አይደለችም፡፡ መጥቶ የጠየቃትም የለም፤ ለአካባቢው ባእድነት ተሰማት። እነዛን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማረችባቸውን ዓመታት አሰበቻቸው ቀስ በቀስ በትዝታ ስመመን ውስጥ ገባች።

"መስሎኝ መሆን አለበት!" የሚል ድምጽ ከገባችበት ትዝታ ውስጥ መንጥቆ አወጣት። እርሷም ዐይኖቿን ማመን አልሆነላትም ዕይታዋ የትዝታዋ ክፍልም መሰላት። ከታረቀኝ ጋር ተፋጠጡ ከዛ ደግሞ ተቃቀፉ በአካባቢው የነበሩ ሁሉ በትዝብት እስከሚመለከቷቸው ድረስ መተቃቀፋቸው ረጅም ሰላምታቸውም የጠበቀ ነበር።

ከሰላምታቸው በኋላ አልተቀመጡም አንገቷን እንዳቀፋት በአምስተኛ በር በኩል ወጡ፡፡ ወዴት እንደሚሄዱ አልተነጋገሩም ብቻ ቆም



ይሉና ይተያያሉ እንደገና ይተቃቀፋሉ ከዛ መንገዳቸውን ይቀጥላሉ። የራስ መኮንን ድልድይን አልፈው ወደ ቲ ሩም ዘለቁ ምቹ የሆነ መቀመጫ ፈልገው ተቀመጡና ምሳቸውን አዘዙ።

"እሺ. ፍርዬ! እስኪ ስለሁሉም ነገር እንደድሮው አውሪልኝ። የትዳር ዓለም ይጥማል? ፍቅርስ ከትዳር በኋላ እንደድሮው እንደሞቀ ነው ወይስ..." አለ ታረቀኝ ገና ሲቀመጡ።

ስለፈቃደና ስለልጇ አወራችለት።

"በቃ?" አላት የተገረመ በሚመስል መልኩ።

"ሌላ ምን ላውራልህ?" አለች ትዝታዋ ገጽታዋን ለውጦት።

"ፍርዬ! ሕይወት ያንን ግልጽነትሽን አጥፍቶት ከሆነ በጣም አዝናለሁ። ለእኔ እኮ ፍርዬ ማለት የታማኝነትና የግልጽነት ምሳሌዬ ናት" አለ ታረቀኝ።

እርሷም ያን ለጉዳት የዳረጋትን የፈቃደን ልጅ መውለድ ለታረቀኝ በመንገርና ባለመንገር መሀል እየዋለለች ነበር። እናም ነገረችው፤ በጣም የምታምነው ፈቃደ ከእርሷ ጋር እያለ ከሌላ ሴት ልጅ መውለዱን ሳትደብቅ አወራችለት።

ምሳቸው ቀረበ፤ ታረቀኝ አሁንም አሁንም ያጎርሳታል እርሷም ትቀበለዋለች። "ለምን አታጎርሽኝም?" አለ ለጉርሻው አፀፋውን ባለመመለሷ። አጎረሰችው እየተጎራረሱ ያላነሱት ጉዳይ የለም።

"እስኪ እንደድሮሽ ዐይኖቼን እያየሽ አውሪልኝ" አለ ታረቀኝ ድንገት። ቀና ብላ ዐየችው ግን መቆየት አልሆነላትም።

"ታውቂያለሽ ፍርዬ?" አለ ከጥቂት ዝምታ በኋላ "አንገትሽን ቀና አድርገሽና ትከሻሽ ቀጥ ብሎ ስትራመጂ ሳይሽ በውስጥሽ ያለው በራስ መተማመንና ኩሩነትሽ ነበር የሚታየኝ። ታዲያ ዛሬ ያ ሁሉ የት ሄዶ ነው ፍርዬ እንዲህ አንገተ ሰባራ የሆነችው? የባሰ ቁጭት ውስጥ እንድትገቢ ለማበረታታት ፈልጌ አይደለም ግን የማውቃት

ፍርዬ ይህን ዓይነት ጥቃት ትቀበላለች ብዬ በፍጹም አልገመትኩም" አላት።

"አዝናለሁ ታረቀኝ እንዲህ እንድትናደድብኝ አልነበረም የነገርኩህ" አለችው።

"ብናደድም አትፍረጂብኝ እንደ ዕንቁ የምቆጥራትን ፍርዬን ስትጎዳ ማየት ስለማልችል ነው። እመኚኝ ዛሬም ለአንቺ ያለኝ ስሜት አልተለወጠም፡፡ ፍርዬ እኔኮ መመዘኛዬ አንቺ ሆነሽ ከሌላ ሴት ጋር ዓላማ ያለው ጥምረት መፍጠር ያቃተኝ ሰው ነኝ። ዛሬም ሳስበው እኔ ላንቺ አንቺም ለእኔ የተፈጠርን ይመስለኛል። ልጅ የመውለድሽ ጉዳይ ደግሞ ለእኔ ምንም አይደለም፡፡ አንቺ እሺ ብለሽ ከመጣሽልኝ እጆቼን ዘርግቼ እቀበልሻለሁ" አላት።

የታረቀኝ አባባል ልቧን ንዶባት ነበር፡፡ አብራው ብትሆን ደስተኛ እንደምትሆንም ታውቃለች፤ "ግን ቃሌስ? አንድ ጊዜ ይቅር ብዬ መኖር ጀምሬ ይቅር የተባለበት ስህተት አንስቼ እንዴት ጥዬው እሄዳለሁ?" ከራሷ ጋር ተጨቃጭቃ እራሷን አሸነፈች።

እናም ዛሬ ፈቃደ ያደረገውን ስትመለከት ከሌላ ሴት ጋር የፈጠረውን ግንኙነት እንደቀላል ነገር ሲነግራት በጣም ደነቃት። ከመገረም አልፋ ግን ምንም ለማለትም ሆነ ለማድረግ ወኔው የላትም። በእንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች ሁሉ ታዲያ ሚስጥረን ታስታውሳታለች፤ በእንዲህ ዓይነት ጉዳዮች ከሚስጥረ በላይ ሊረዳት የሚችል ያለመኖሩን ብታውቅም፤ ስለፈቃደ የጠየቀቻትን ሁሉ ደብቃ ደህና ነኝ ስላለቻት እየደር ራሷን ከሚስጥረ ስላሸሸች ቀስ በቀስ ተለያይተው ቀርተዋል። ሚስጥረን ስታስብ አእምሮዋ ስለሚበጠብጥባት በተቻላት መጠን እንደተለየቻት መኖርን መርጣለች። እናም ችግሯን ሁሉ ብቻዋን ለመወጣት ሆኗል ጥረቷ።

አንዳንዴ የፈቃደ ነገር በጣም ግራ ያጋባታል፡፡ ሲያሻው ካገኛት ሴት ጋር ሁሉ በቀላሉ ሲወዳጅ ሌላ ጊዜ ደግሞ ካላንቺ መኖር አቃተኝ ተለያይቶ መኖር መረረኝ ይላታል። አንድ ሰሞን ይህን ዓይነቱ ደብዳቤና ስልክ ሲበዛባት ሄዳ ልታየው ወሰነችና ተዘጋጀች።



እስከምትመለስ ድረስ ከልጆቹ ጋር የምትሆንላት የጎረቤት ልጅ አነጋገረች።

ልትሄድ በተዘጋጀችበት እለት ወደማታ ላይ ዘውዱ እቤት መጣ። ወደፈቃደ ለመሄድ መዘጋጀቷን ነገረችው። እርሱም ፈቃድ ወስዶ ወደቤተሰብ ለመሄድ የተነሳ መሆኑን ነገራት። ከዘውዱ ጋር አብረው አዲስ አበባ ድረስ ሄዱ።

ፈቃደ ልትጠይቀው በመሄዷ በጣም ተደሰተ። ስለልጆቹ፣ ስለጎረቤትና ስለጓደኞቹ በተለይም ስለዘውዱ ጠየቃት። የሁሉንም ደህንነት ነገረችውና ከዘውዱ ጋር አዲስ አበባ ድረስ አብረው መምጣታቸውንም አወራችለት። እየነገረችው የፈቃደ ፊት ሲለዋወጥ ተመለከተች።

"አዲስ አበባ የት አደርሽ?" አላት ደግሞ።

"ምነው ጠየቅከኝ?" አለች ጥያቄውን በጥያቄ በመመለስ።

"የአንቺን መምጣትና የዘውዱን እረፍት ምን እንዳገጣጠመው ገርሞኝ"

"ምን ለማለት ፈልገህ ነው?" አለችው ስሜቱ ስለገባት።

ፈቃደ ግን ከዚያ በኋላ ምንም አላለም፤ ወይ ይቅርታ አልጠየቀ አሊያም በጥርጣሬው አልገፋበት፤ በዝምታ አለፈው።

ፈቃደ ዐይታው ከተመለሰች በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሊያያቸው መጣ። በጓደኛው በዘውዱ ከጠረጠራት ወዲህ ያላት ስሜት ሁሉ እንደወትሮው መሆን አልቻለም። ትዳራቸውን እንደማንኛውም ባህላዊ ትዳር ራሷንም የባሏን እጅ ጠብቃና ኢኮኖሚያዊው ጥገኝነቷ ስብእናዋንና ማህበራዊ ማንነቷን ወስኖት አንገቷን ሰብራ እንደምትኖር እንደማንኛዋም ባህላዊ ሴት መቁጠር ጀምራለች።

ይህ ሁኔታ የሕይወት አቅጣጫዋን በጥልቀት እንድትመረምር አደረጋት። እናም እንደማንኛዋም "የቤት እመቤት" የፈቃደን እጅ ጠብቃ የእርሱን ቸርነት ተገን አድርጋ መኖር የምትቀጥል ከሆነ

የማይታየውንና በገንዘብ የማይተመነውን የቤተሰብ ኃላፊነት የምትሸከምበት ጫንቃዋ እየጎበጠ፣ በሕይወት ውስጥ የሚኖራትም ወሳኝነት እየተመናመነ፣ በብሶት የታመቀ እኔነት ይዛ መቅረቷ የማይቀር መሆኑን አመነች።

ይህ ደግሞ በፍጹም የምትቀበለው ጉዳይ አይደለም። የታገለችው ትግል የማንንም ሕይወት መለወጥ ቢያቅተው ቢያንስ ራሷን ማዳን ይኖርበታል። ወጣትነቷ ከህሳቧ አልወጣ አላት፡፡ እንደእናቶቿ ሆና መኖር በጭራሽ አትፈልግም። የዘመረቻቸው የቅስቀሳ መዝሙሮች ትውስ አሏት፤

"ወጣቷ ድርብ ታጋይቷ ሴት
በርቺ ታገይ ለኩልነት ላርነት..."

መዝሙሩን ሲዘምሩ የነበረው ስሜት ተሰማት፤ የእያንዳንዳቸው ገጽታ ታያት። ትዝታውን ከራሷ ለማውጣት የፈለገች ይመስል ጭንቅላቷን አነቃነቀችው። ይህን ማሰላሰል ባበዛች ቁጥር ደግሞ ልታስበው ወደማልትፈልገው ትውስታ እየከተታት ተቸገረች። ምንም ፋይዳ ላትሠራ በትዝታ ብቻ መብሰክሰክ ምን ዋጋ አለው። ቢሆንም ግን ባለችበት ሁኔታ ውስጥ እንዳትቆይ፣ ራሷን እንድትለውጥ የሚያነሳሳ ኃይል ሆናት ትዝታዋ።

ፈቃደ ሊጠይቃቸው በመጣበት ወቅት አብረው በሚሆኑባቸው ጊዜያት ጨዋታቸው እንደወትሮው አይሞቅም፡፡ ያጥርባቸው የነበረውም ቀን እየረዘመ ልጆቹ ከትምህርት ቤት እስኪመለሱ ድረስ እርሷም ወደጓዳ ሥራዋ እርሱም ወደመኝታ ቤቱ መግባት የተለመደ ሆነ።

ፈቃደ ወደሥራው ለመመለስ ጥቂት ቀናት ሲቀሩት ሥራ ለመፈለግ ማሰቧንና ሥራ የምታገኝ ከሆነም ትምህርቷን መቀጠል እንደምትፈልግ ነገረችው። አልተቃወማትም እንዲያውም አበረታታት። እርሱም ቅያሬ እየሞከረ መሆኑንና የበለጠ ሊረዳዱ እንደሚችሉ ነገራት።

ዕቅዷን ለልጆቿ የነገረቻቸው ዕለት የተደሰቱት መደሰት ያልጠበቀችው ነበር። "ብራቮ እማ! ወንዳታ" አላት ማቲ ገና ተናግራ



ሳታበቃ። "በጣም አሪፍ ነው እማ፤ የነቤቢ እናት ሥራ ሄደው ሲመለሱ እንዴት እቀናለሁ መሰለሽ። አንቺም ከእንግዲህ ሥራ ትሄጃለሽ ማለት ነው!" አለች ሩታም እንደማቲ ተደስታ።

"ገና እኮ ሥራ ልፈልግ ነው አላገኘሁም" አለቻቸው ሥራ ማግኘት ባይሳካላት የልጆቿ ስሜት እንዳይጎዳባት ሰግታ።

"ኧረ እባክሽ ለምን ታጫለሽ በትምህርት ከቤቢ እናት እንደምትበልጪ የማላውቅ መሰለሽ?" አለች ሩታ በእርግጠኝነት።

"በምን አወቅሽ ሩታዬ?" አለቻት በመገረም።

"ቤቢ ናታ የነገረችኝ። አባቷና እናቷ ሲያወሩ ሰምታ 'ታድለሽ እናትሽ ለካ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበረች' አለችኝ እኔም በጣም ደስ አለኝ። አንቺ ግን ነግረሽኝ አታውቂም" አለች ሩታ በቅሬታ።

"ምን ዋጋ አለው ሩታዬ ጥቅም ላይ ያልዋለ ትምህርት ስለሆነ እኮ ነው" አለቻት በተሰበረ አንደበት።

"ቢሆንስ የቤት ሥራችንን የምታሰሪን አንቺ አይደለሽ? የቤቢ እናት እኮ ሥራ ብትሄድም የቤቢን የቤት ሥራ ማሠራት አትችልም" አለች ኮራ ባለ አነጋገር።

ሌላው ሁሉ ቢቀር እንኳን የልጆቿን ስሜት ለመጠበቅ ስትል ሥራ መግባት እንዳለባት አስባ ፍለጋውን ተያያዘችው። በለስ ቀናት፤ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሥራ አገኘችና ገባች። እርሷም ቢሮ ውሎ የመግባት ወጉ ደረሳት። ሥራዋን ወደደችው፤ በአዲስ ጉልበት ሥራውን አጣደፈችው። ትምህርቷን ለመጀመር ደግሞ መስከረም እስከሚደርስ ከመቸኮሏ የተነሳ ከወዲሁ ማንበብ ጀመረች።

ራሷን ወደተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ታጥቃ ተነሳች። አዋሳ እርሻ ኮሌጅ በማታው ፕሮግራም ለመማር ተመዘገበች፤ አቤት ያን ዕለት የተሰማት ደስታ። የተመዘገበችው ለዲፕሎማ ፕሮግራም ቢሆንም በጣም ደስ አላት። ልጆቿም አብረዋት ተደሰቱ፡፡ አብረው እንደሚያጠኑም ተነጋገሩ።

ትምህርቱ ተጀመረ፡፡ የምታውቀው ሰው ስላልነበራት ብቸኝነት ከብዷት ነበር። ክፍል መግባት በጀመረችበት ሳምንት እመቤትን፤ የአንድ ሴሚስተር የዩኒቨርሲቲ ጓደኛዋን ከአእምሮዋ ማውጣት ተቸግራ ሰነበተች። እመቤት የት ደርሳ ይሆን? እመቤት ልታገኛት የምትችልበት
ምንም ዓይነት አድራሻ ስለሌላት ደህና ብትሆን እንኳን ሊገናኙ የመቻላቸው ጉዳይ ያለቀለት መሆኑን ስታስበው ታዝናለች። በየአጋጣሚው ግን ሕይወቷን ሙሉ ስታስታውሳት ትኖራለች። እመቤትን ስታስታውስ የበላይሁን እናት ትውስ አሏት። ሰሞኑን ልትደውል እያሰበች ሳትደውል ቆይታለች። "እንዲያውም እደውልና ምናልባት እመቤት ከመጣች አድራሻዬን እንዲሰጧት እነግራቸዋለሁ። ማን ያውቃል!" አለች ለራሷ።

* * * *

ታረቀኝ በጠዋት ተነስቶ በቀዝቃዛው ውሀ ተጣጥቦና ሽሚዙን አጥልቆ ከመልበሻው መስታወት ፊት ቆመ። ለሊቱን ብዙ እንቅልፍ አልወሰደውም፤ አለቃው የሰጡትን ሥራ ጨርሶ ቅዳሜና እሁድን በነጻነት ማሳለፍ በመፈለጉ እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ድርስ ምሽቶ ነው የተኛው።

እንቅልፍ ያልጠገቡት ዓይኖቹ በደንብ አልተገለጡም፤ በድጋሚ በቀዝቃዛው ውሀና በሳሙና ሙልጭ አድርጎ ፊቱን ታጠበና ተመልሶ በመስታወቱ ፊቱን ተመለከተ፤ ዐይኖቹ ከመቅላታቸው በስተቀር ገለጥ ብለዋል። ሰዓቱን ተመለከተና እንደገና በመስታወቱ ውስጥ ወዳለው የራሱ ምስል አስተዋለ። አለባበሱን እንደገና ሲቃኝ የሽሚዙን ቀለም አልወደደውም፤ ፀጉሩ እንደገና በጠር በጠር አደረገና በእጁ አስተካከለ። ሽሚዙን አወለቀና ነጭ ሽሚዝ አውጥቶ ለበሰ፤ በላዩ ላይ ጠቆር ያለ ሰማያዊ ጃኬት ደረበበት። ከፊቱ የቆመውን ምስሉን በየምወድሽ ዐይን ተመለከተውና ደስ አለው፤ ሳያስበው ፈገግ አለ።

ከየምወድሽ ጋር መውጣት ከጀመሩ አንድ ዓመት ሊሆናቸው ጥቂት ቀናት ብቻ ቀርተዋል። ፍቅርን እንዴት እንደጀመሩት ሲያስታውስ



ደግሞ የበለጠ ፈገግ አለ። ወደዚያች የመጀመሪያ የፍቅር ዕለት በሀሳቡ ተጓዘ።

ታረቀኝ ከዘውዱ ጋር ከተዋወቀ በኋላ ስለፍሬሕይወት በየጊዜው ይሰማል፤ ዘውዱ ስለፍሬሕይወት እንኳን ተጠይቆ ሳይጠየቅም ቢያወራ ደስ ስለሚለው ለታረቀኝ የሚነግረው ያለውን አድናቆትም ጭምር ነው። ይሄ ደግሞ የበለጠ እንዲያስታውሳት፤ እንዲያስባት አደረገው። ባሰባት ቁጥር ደግሞ የበለጠ እየወደዳት ተቸገረ። ከትምህርት ቤት ጓደኞቹ ጋር ይገናኛሉ፤ አብረውም ያመሻሉ። እንደ አዲስ ሠራተኛነታቸው መገባበዝና መዝናናት ያዘወትራሉ። ቀስ በቀስ ታረቀኝ በመጠጡ ገፋ ማድርግ ሲጀምር አንዳንድ ጓደኞቹ ሊገስጹት ሞከሩ፤ ከእነርሱ እየሸሸ ወደመጠጡ ከሚያደላ ጓደኛው ጋር መሆን አዘወተረ።

አንድ ሰኞ ወደሥራው ሲገባ ያደረ የመጠጥ ስሜት ሙሉ በሙሉ አልቀቀውም። ተኝቶ ቢያረፍድ በወደደ ነበር ሆኖም አለቃው ሁልጊዜ ስለሚጠይቁ እንዲያጡት አልፈለገምና ቢሮ ገባ። ቢሮው ገብቶ ወረቀቶቹን ገልበጥ ገልበጥ ሲያደርግ ቢቆይም ያን ዕለት ግን አለቃው አላስጠሩትም። መኖራቸውን ሊጠይቅ ወደጸሐፊያቸው ቢሮ ሄደ።

ጸሐፊያቸው የምወድሽ ማንም ሳይቀድማት ቢሮ የምትገባ፣ በሥራዋ ቀልድ የማታውቅ ኮስታራ ሽቅርቅር ልጅ ነች። አለባበሷን የማያደንቅላት ሰው በቢሯቸው አይገኝም። የምትለብሳቸው ልብሶች እላይዋ ላይ የተሰፉ ይመስል ከሰውነቷ ጋር የተስማሙ ናቸው፤ የምታደርጋቸው ጫማዎች ለተመልካች የሚከብዱ ረጃጅሞች ቢሆኑም እርሷ ግን ዘና እያለች ስትራመድ እነዛ ረጃጅምና የሚሰበሩ የሚመስሉ ቀጫጭን ተረከዞች ላይ የቆመች አትመስልም።

ቢሮውን የሞላውን የምወድሽን የሽቶ መዓዛ ሳብ አደረገው ታረቀኝ ወደ ቢሮዋ ሲገባ። "ታረቀኝ! ዛሬ እንዲህ የተረበሽ ከተማ መስለህማ አለቃህ እንዲያዩህ አያስፈልግም" አለችው ገና ሰላም ሳትለው።

"ምን ሆኚ ነው የተረበሽ ከተማ የመሰልኩት?" አላት እየሳቀ። ለሰላምታ ጉንጭ ለጉንጭ ሲሳሳሙ ደግሞ

"መች አጣሁት ይሂዋ አድረህበታል፤ የጠጣህ ሳይሆን የተጠመቀብህ ነው የሆንከው" አለችው።

"አሁንስ አበዛሽው" አላት ኮስተር ለማለት እየሞከረ።

"ያበዛሁት እኔ ሳልሆን አንተ ነህ፤ አለቃህ በአንተ ላይ ያላቸውን እምነት እንድታበላሸው አልፈልግም፤ እርሳቸው እንዴት ቆፍጣና አለቃ እንደሆኑ ታውቅ የለ? አንተም የእርሳቸውን ፈለግ እንድትከተል ይፈልጋሉ። እና ለአንተ ብዬ ባይሆንም የእርሳቸውን ስሜት ለመጠበቅ ስል እንዲህ ሆነህ ባያዩህ እመርጣለሁ" አለችው።

ግልጽነቷ እየገረመው ትኩር ብሎ ተመለከታትና "እሺ ወደቤቴ ልሂድ?" አላት በመቀለድ።

"አዎን ሂድና እረፍ፤ በዛውም ከዚህ ከመጠጥና ወደፊት ከሚጠብቅህ መልካም እድል የቱ እንደሚበልጥብህ አስብና ወስን" አለችው አሁንም ኮስተር ማለቷ ገርሞው።

"እሺ መሄዱን ልሂድ፤ እሳቸው ምን ይላሉ..." አላት

"እርሱን ለኔ ትተወዋለህ፤ ገብተህ እንደነበረና ብርቱ ጉዳይ አጋጥሞህ እንደሄድክ እነግራቸዋለሁ። ይልቅስ ፍጠን አራት ሰዓት እንደሚገቡ ነግረውኛል" አለችው ሰዓቷን እየተመለከተች።

ታረቀኝ ምንም ሳይመልስላት ከቢሮዋ ወጥቶ የራሱን ቢሮ ዘጋና ወደቤቱ ተመለሰ። በመንገዱ ላይ የምወድሽን ከአእምሮው አላወጣትም፤ ቤቱ እስኪደርስ ልብሱን ቀያይሮ እስኪተኛም ድረስ በሀሳቡ ውስጥ ተመላለሰች።

ጋቢ ለበሰና አልጋው ላይ ተኛ፤ ዐይኖቹን ጨፍኖ እንቅልፍ እንዲወስደው ተለማመጠ፤ ከእንቅልፍ ይልቅ የምወድሽ በግዝፈት ትታየው ጀመር። በጀርባው ተንጋለለና ኮርኒሱ ላይ ዐይኖቹን ተከላቸው፤ በሀሳቡ ወደመሥሪያ ቤቱ፣ ወደየምወድሽ ነጎደ።



አንድ ቀን ከመሥሪያ ቤት ጓደኞቹ ጋር ለምሳ ወጥተው ሳሉ ስለሴቶቹ ማውራት ተጀመረና የመሥሪያ ቤታቸውን እንስቶች አብጠለጠሏቸው። በመሀል የምወድሽ ስም ተነሳና "አይ እሷን ለቀቅ ብታደርጓት ይሻላችኋል" አለ አንደኛው። ከዚያ በኋላ የቆዩትን ጊዜ በሙሉ ስለየምወድሽና ስለፈላጊዎቿ እንዲሁም ስለእርሷ ኮስታራነት አወሩ። ሁሉም ተስፋ ቆርጦ አፉንና እግሩን እንደሰበሰበ ተነገረ።

ታረቀኝ አልጋው ላይ ተንጋሎ ይህንን ሁሉ አስቦ እርሷና እርሱ ስላላቸው መግባባት ደግሞ ማሰብ ጀመረ። በጣም ይቀራረባሉ፤ ይከባበራሉ። የዛሬው በጣም ተለየበት እንጂ እንደምታስብለትም ያውቃል። ከሥራ ግንኙነታቸው ውጭ አንድም ቀን በሌላ መልኩ አስቧት አያውቅም፤ በጣም ገረመው።

"ወይ ፍሬሕይወት! በሌለሽበት በቁጥጥርሽ ስር አውለሽኝ አጠገቤ ያለውን ውበት እንዳላይ አድርገሽኛል ለካ" አለ በሀሳቡ።

በደመነፍስ ስልኩን አነሳና ቁጥሮቹን ማዞር ከጀመረ በኋላ መልሶ አስቀመጠው። "እስኪ አሁን ምን ልላት ነው?" አለና ራሱን ጠየቀ። ግን አሁንም የምወድሽን ከሀሳቡ ሊያወጣት አልቻለም። እንደገና ስልኩን አነሳ፤ ቁጥሮቹን አዙሮ ጨረሰ። ስልኩ ሲጠራ የእርሱም ልብ ከበሮዋን ትደልቅ ገባች። ስልኩ ሲነሳ ልቡ ከደረቱ ውስጥ ዘላ የወጣች እስኪመስለው ድረስ መታችበት። ራሱን ለማረጋጋት ሞከረ "ጤና ይስጥልኝ..." የሚለውን የምወድሽን ድምጽ ሲሰማ ደግሞ ባሰበት።

"አለቃችን ገቡ እንዴ?" አላት ድምጹን ለማስተካከል ጥረት እያደረገ።

"እንዴ ቆይተዋል እንጂ፤ አራት ሰዓት እንደሚገቡ አልነገርኩህም" አለችው።

"ምን አሉ?"

"ምንም! ያው ስለምትናፍቃቸውና አንተን ካላዩ ሥራ ስለማይጀምሩ ጠየቁ፤ ነገርኳቸው። ምን እንደገጠመህ ጠየቁኝ፤ ዝርዝሩን እንደማላውቅ ገለጽኩላቸው፤ በቃ!" አለችው።

"ሳላመሰግንሽ በመምጣቴ ተጸጽቼ ላመሰግንሽ ነው የደወልኩት፤ በጣም ነው የማመሰግንሽ፤ ይህን ያህል ለሰው የሚያስብ ሰው በመኖሩ ተደንቂያለሁ፤ እንዲህ ዓይነት ሰው መሆንሽን ይህን ያህል ጊዜ ባለመረዳቴ ራሴን ታዘብኩት" አላት

"ይህን ያህል ምን አደረግኩልህ? እኔም የአለቃዬ ተጋብቶብኝ ነው መሰለኝ..." ዓረፍተነገሩን ሳትጨርስ አንጠልጥላ ተወችው።

ታረቀኝ የበለጠ ደነገጠ፤ የሚለው ጠፋበት "በናትሽ ዓረፍተነገሩን ጨርሽው?" አላት ሳያስብው።

"እወድህለሁ መሰለኝ" አለችው።

"ሙት በይኝ እስኪ?"

"ሙት ከምልህ እጅህን ብመታልህ አይሻልህም" አለችው።

"እጄን እንድትመችልኝ ታዲያ ለምን አንገናኝም?" አላት ከየት የመጣለት ዘዴ እንደሆነ ሳይገባው።

"ይልቅስ አርፈህ ተኛና ዋል፤ እጅ መምታቱ ሌላ ቀንም ይደርሳል" አለች የምወድሽ በተረጋጋ አንደበት።

"ቀኑን ሙሉ አርፌ ከሥራ ስትወጭ ብንገናኝ ታዲያ ምን አለበት? በናትሽ እሺ በይኝ" ልምምጡ ለራሱም ተሰማው።

"እሺ" አለችው። ነፍሱ ተነጥቃ የወጣች መሰለው። የሚገናኙበትን ቦታና ሰዓት ተነጋገሩና ስልኩን ዘጋው። በቃ! ከዛን ቀን በኋላ ከልቡ የማይወጣት ፍቅረኛው ሆነች ። አሁንማ ፍቅራቸው አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ሆነ። በአንድ ጣሪያ ስር መኖር ሊጀምሩም ዝግጅታቸውን ተያይዘውታል።

የስልኩ ድምጽ ከገባበት ሀሳብ አወጣው፤ ስልኩን ከማንሳቱ በፊት ሰዓቱን ተመለከተ፤ ለቀጠሮዋቸው ሀያ ደቂቃ ይቀራል። ስልኩን አንሳው ማን ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛ ነው።



"ተዘጋጅተሃል?" አለችው የምወድሽ።

"ተዘጋጅቼ ከመስታወቱ ፊት ቆሜ በሀሳብ ጭልጥ ብዬልሻለሁ"

"የምን ሀሳብ ነው ደግሞ፤ ይልቅስ ቶሎ ና ናፍቀኸኛል" አለችው።

"እንደኔ አትሆኝም፤ አሁኑኑ መጣሁ" አላትና ስልኩን ዘግቶ በጥድፊያ ወጥቶ የምወድሽን ወደሚያገኝበት ቦታ ሄደ።

* * * *

ፍሬሕይወት ሥራና ትምህርት መጀመሯ ሕይወቷን ለወጠው፡፡ በሥራዋ ያገኘችው ተጨማሪ ገቢ ከለወጠው ቁሳዊ ሕይወቷ ይልቅ መንፈሳዊ እርካታዋ ከፍ ያለ ሆነ። በመሥሪያ ቤትና በትመህርት ቤት ከበርካታ ሰዎች ጋር እንደመዋሏ የማህበራዊ አድማሷ እየሰፋ መጣ፡፡

እንደተለመደው ሁሉ ምዘናዋ አይቋረጥም፤ በሚሰጡ አስተያየቶች፤ በሚቀርቡ ጥያቄዎች፤ በሚሰነዘሩ ግምቶች... ለሰዎች የምትሰጣቸው ቦታ የተለያየ ነው። እናም ከሰዎች ጋር ያላት ግንኙነት የሚመሰረተው በምዘናዋ ላይ ነው። ለፍሬሕይወት ይህ ምዘና የሚያገለግለው የቀረበ ግንኙነት ለመፍጠር እንጂ ለማህበራዊ ኑሮዋ ለየት ያለ መርህ አላት፤ "መንፈሰ ጠንካራ ሰው ከሰይጣንም ጋር መኖር ይችላል" የሚለውን ትከተላለች፤ ከማንም ሰው ጋር ለመኖር ትችላለች። ፍሬ ስለዕድሜ አትጨነቅም፤ ከሁሉም ጋር እንደሁኔታው መኖር ትችልበታለች። ከታላላቆቿም ሆነ ከታናናሾቿ ጋር መግባባት ለእርሷ በጣም ቀላል ነው።

በእረፍት ቀናትና በአንዳንድ አጋጣሚዎች ወደነፍሬ ቤት የሚመጡ ሰዎች በርከትከት እያሉ ሄደዋል፤ ልጆቿ በዚህ በጣም ተደስተዋል። የፍሬ ልጆች እንደአጎታቸው የሚያዩት ዘውዱን ነው፤ ከተወሰኑ ሌሎች የፊታደ ጓደኞች ሌላ የሚያውቁት ጎረቤቶቻቸውን ብቻ ነበር። አሁን ግን አንዳንዶቹ ሰዎች አልፎ አልፎ ልጆቻቸውን ማምጣት ጀምረዋል፤ ሩታና ማቲ ከጎረቤት ልጆችና ከትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ተጨማሪ ጓደኞች ኖሯቸው።

እቤት የሚመጡ ሰዎች ሰብሰብ ሲሉ የማይነሱ ጉዳዮች የሉም፤ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቡናዊ ጉዳዮች እስከጥግ ድረስ ይወራሉ። አንድ ነገር ላይ ብቻ ሳይነጋገሩ ስምምነት ላይ የደረሱ ያህል ዘለቅ ያለ ወሬ አይወራም፤ ፖለቲካ ክልክል ይመስላል። አንዳንዴ ፍሬሕይወት ድንገት እስኪላት ድረስ መመሳሰል ታያለች፤ "ማን ያውቃል? ይሄ ሁሉ ሰው ከአንድ ምንጭ የፈለቀና በአንድ መንገድ የተጓዘ፤ ወቅት ያስከተለው መከራና ሰቆቃ የፈጠረው ፍርሃት አፉን የሸበበው ትውልድ ይሆናል" ትላለች። የእውነትም ብዙዎቹ፤ እርሷንም ጨምሮ "እርም ፖለቲካ!" ያሉ ይመስላሉ።

ፍሬሕይወት የመሥሪያ ቤትም ሆነ የትምህርት ቤቷ ሰዎች መጥተው ሲጫወቱ ደስ ይላታል። ብዙውን ጊዜ መጥተው ሲሄዱ እርሷ ደግሞ ወደ ትዝታዋ ትገባለች። በየቦታው እንዲህ እንደነርሱ ሳይነጋገሩ ተግባብተው ቢያንስ ተመሳሳይ ጉዳዮች አንስተው ሊወያዩ የሚችሉ ፍርዬ "የእኛ ሰዎች" የምትላቸው ሰዎች መኖራቸው ደስ ይላታል።

"ግን አንተነህ የት ደርሶ ይሆን? በሕይወት ይኖር ይሆን?" በማለት መልስ የማታገኝለትን ጥያቄዋን ትጠይቃለች። ግን ያውቃል እነአንተነህም እንዲህ እንደእርሷ በያሉበት ቦታ የየራሳቸውን ማህበራዊ ቡድን መስርተው ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል።

"እማ! ለምንድነው ሰዎቹ ሲሄዱ የምታዝኚው?" አለቻት ሩታ አንድ ቀን ሰዎቹ ሲሄዱ ፍሬ በሀሳብ ጭልጥ ስትል ተመልክታት።

"አዝናለሁ እንዴ ሩታዬ?" አለቻት ደንገጥ ብላ።

"አዋ! ሁልጊዜ ትተክዢለሽ፤ አይታወቅሽም?" አለቻት።

"አባቴ፣ እናቴ፣ ወንድሜ ሞተውብኛል ብዬ ነግሬሽ የለ? እነሱ ትዝ እያሉኝ ነው" አለቻት። ሩታ ነገሩ ባይገባትም ሌላ ጥያቄ አላቀረበችም።

"ደግሞ ጓደኞቹም ሞተውብኛል" አለቻት ግራ መጋባቷን ተመልክታ።

"ምን ሆነው? ብዙ ናቸው እንዴ?" አለች ሩታ እያዘነች።



"አዎ ብዙ ናቸው። ለምን እንደሞቱ ሌላ ግዜ እነግርሻለሁ" ምስቅልቅል ያለው ሀሳቧ ሌላ ለማለት አላስቻላትም።

ለማንኛውም ፍሬሕይወት ኑሮዋም ሆነ ማህበራዊ ሕይወቷ ወደ ተሻለ አቅጣጫ እየሄደ መሆኑ ይሰማታል። በተለይ ትምህርት መጀመሯ ለብዙ ነገሮች ወሳኝ መሆኑን ታስባለች፤ ስትጨርስ ዕድገት ልታገኝ ትችላለች ከዛ ትምህርቷን ለመቀጠል ይመቻታል... ጊዜው ይርዘም እንጂ በሕይወት ያለመችውን እንደምትደርስበት እርግጠኛ ነች። አዎ ዕድሜዋ ገና ነው፤ ብዙ መሥራት ትችላለች የሕይወትዋ ዓላማዋን ለማሳካት ጊዜው አይረፍድባትም።

* * * *

አንድ ቀን ፍሬሕይወት ለምሳ ወደቤት ስትገባ ፈቃደን ቤት አገኘችው፤ እንደሚመጣ አልነገራትም "ተቀየርክ?" አለችው ገና ስታየው።

"አልተቀየርኩም" አለ የተሰላቸ በሚመስል ሁኔታ።

"ምነው ደህና አይደለህም እንዴ?" አለችው ደግሞ ሰላምታውም ቀዝቀዝ ስላለባት።

"ቤት ስገባ ሰላላገኘሁሽ እንዴት እንዳስጠላኝ" አላት ጥቂት ቆይቶ።

"ሥራ መጀመሬን ታውቅ የለ?" አለችው ምሳ እንድታቀርብ ለሠራተኛዋ ነግራ።

ምሳ በልተውና ቡና ጠጥተው እንደጨረሱ ወደሥራ ለመሄድ ተነሳች፡፡ ፈቃደ መከፋቱ ከፊቱ ላይ እየተነበበ ወደመኝታ ቤት ገባ። ተከትላው ገባችና ተሰናበተችው፡፡ እርሷም ብትሆን ትታው ስትሄድ ቅር እያላት ነበር።
ፈቃደ ወደሥራ ሳይመለስ ከጠበቀችው በላይ ቆየ። ግራ ቢገባትም ለምን ብዙ እንደቆየ አልጠየቀችውም። ልጆቹም አባታቸውን በማግኘታቸው ደስታቸው ከፍተኛ በመሆኑ እንዴት ቆየህ ማለት የእነርሱንም ደስታ መቀማት ሆነባት። ቢሆንም ዘወትር ከሀሳቧ አውጥታው አታውቅም።

ሁልጊዜም እሁድ እነፍሬ ቤት ለየት ያለ ነው፡፡ ጠዋት ቤተክርስቲያን ሄደው ከተመለሱ በኋላ ሁሉም የየራሳቸው ሥራ አላቸው። ሩታና ማቲ መኝታ ቤታቸውን ያጸዳሉ፣ ልብሶቻቸውን በተገቢው ቦታ ይከታሉ፣ ደብተርና ወረቀቶቻቸውን ያስተካክላሉ፣ ካልሲዎቻቸውን ያጥባሉ። ፍሬ ደግሞ ለየት ያለ የእሁድ ምሳ ለማዘጋጀት ከሠራተኛዋ ጋር ጉድ ጉድ ትላለች። ፈቃደ ቤት ሲኖር ደግሞ መኝታ ቤታቸውን ያጸዳል ቁምሳጥናቸውን ያስተካክላል።

ሰባት ሰዓት ሲሆን ሁሉም የሥራ ድርሻውን ጨርሶ የምግብ ጠረጴዛው ላይ መገናኘት ነው። በደስታ ምሳቸውን ይበላሉ፣ ከዚያ በረንዳ ላይ ወጥተ ከጎረቤቶቻቸው ጋር ቡና ይጠጣሉ። ቡና እየጠጡ ጨዋታቸው ሞቅ ይላል። ጥላ በረድ ሲል ወጣ ብለው አሲስ ይሄዱና መሽትሽት እስኪል ይቆያሉ።

አንድ እሁድ ታዲያ እንደተለመደው አሲስ ሄደው እንደተቀመጡ ልጆቹ በራሳቸው ጨዋታ ሲጠመዱ እንደምንም ራሷን አበረታታችና "እረፍትህ እስከመቼ ነው?" አለችና ጠየቀችው ፈቃደን።

"የምን እረፍት?" አለና ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰላት።

"እንዴት? የመጣኸው ለእረፍት መስሎኝ" አለች በመጠኑ ደንገጥ አድርጓት።

"ተመልሼ የምሄድ እንኳ አይመስለኝም" አላት ቅዝቅዝ እንዳለ።

"አልገባኝም ሥራ ለቀሃል ማለት ነው?"

"ምን ችግር አለው አንቺ እየሠራሽ አይደል?"

"ከምርህ ነው? ወይስ በደሞዜ ትንሽነት እያሾፍክ"

"ቀልዱ ቀልድ ነው ቅየሬዬን ካልጨረሱልኝ ተመልሼ አልሄድም" ፈርጠም አለ ፈቃደ። ቅየሬ እየሞከረ መሆኑን ስለምታውቅ ብዙም አልገረማትም።



ቅየሬው ሳይሳካ ወራት ተቆጠሩ፡፡ ፈቃደን እልህ ያዘውና መልቀቂያ አስገባ። መሥሪያ ቤቱ መልቀቂያውንም መስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ሁኔታውን በትእግስት መያዝ እንዳለባቸው ተነጋገሩ፤ የፍሬ ትምህርት መጀመር ለፈቃደ ሥራ ስለፈጠረለት ጊዜውን በማንበብ ያሳልፋል፤ ከሥራ ስትመለስ ያነበበውን ያስረዳታል። ለእርሷ ሕይወት በጣም ቀለላት። ለልጆቹም ጥሩ አስተማሪ ሆናቸው፤ እናም ደስታቸው አልጎደለም።

ጊዜው በረዘመ መጠን ግን ያለቻቸውን እየወጡ መኖር አሳሳቢ እየሆነ መጣ፤ የፍሬ ደሞዝም ብዙውን ወጪ መሸፈን አይችልም። ፈቃደም መበሳጨት ጀመረ። መልቀቂያ ባይኖረውም አንዳንድ መሥሪያ ቤቶች የሥራ ማመልከቻ አስገባ፤ ሆኖም መጨረሻው ያው ነው፤ መልቀቂያ ይጠይቁታል በዚያ ምክንያት ሥራው ለሌላ ይሆናል።

አንድ ቀን ጠዋት ፍሬ ወደሥራ ለመሄድ ስትወጣ "ዛሬ አሰላ እሄዳለሁ ካልመጣሁ አታስቢ" አላት ፈቃደ።

"ምነው ምን አገኘህ?" አለችው።

"ጓደኛዬ ጭላሎ እርሻ ልማት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ ሥራ ካለው እጠይቀዋለሁ" አላት።

"ነገ ግን ትመጣለህ አይደል?" ብላ የመምጫውን ጊዜ አረጋገጠች።

"ምን እሠራለሁ? እመጣለሁ" አላት።

ፈቃደ እመጣለሁ ባለበት ሰዓት አልመጣም፤ ፍሬ ተጨነቀች። ሁኔታውን ልትጠይቅ የምችልበት ምንም መንገድ የላትም። የምትገባበት ጠፋት፤ ጭንቅ ሲላት መቼም የምታስታውሰው ዘውዱን ነው፡፡ ቤት ሄደችና ሁኔታውን አስረድታ አሰላ ለመሄድ ማሰቧን ነገረችው። ቢሮ ደውሎ አስቸኳይ የቤተሰብ ጉዳይ እንደገጠማት እንዲነግርላትና ልጆቿን እንዲያዳምጥላት ነገረችው።

"አይ ፍሬ! አንችኮ የምታስቢው እንደሚስት ሳይሆን እንደእናት ነው" አላት ዘውዱ።

ወደቤት ስትመለስም ጭንቀት አልለቀቃትም። በሃሳቧ የሚመጣባት ነገር ሁሉ የሚዘገንን ቢሆንም ሰላም እንዲሆን እየተመኘች ቤት ገባች። ሳሎን ስትገባ ግን የፈቃደን ድምጽ ሰማች፡፡ በደስታ ዘልላ ወደመኝታ ቤት ገባች። ፈቃደ ለማቲ ሂሳብ እያስረዳ አገኘችው።

"በደህናህ ነው ፈቃደ?" እያለች ለሰላምታ አጠገቡ ስትደርስም ማስረዳቱን ቀጠለ።

"እንዴ ሰላም በለኝ እንጂ" አለች ንዴትም ቁጣም በተቀላቀለበት አነጋገር።

"የት ሄደሽ ነው?" ሰላምታዋን ችላ በማለት ጠየቃት። ማቲ ቀስ ብሎ ወጣ።

"ሰላምታው አይቀድምም?" አለችው ጠጋ እያለች።

"ከዚህ ሰው ጋር ያለሽን ግንኙነት መተው አትችይም ማለት ነው?" አለና የበለጠ አናደዳት።

"ስማ ፈቃደ አሁንስ በጣም ያበዛኸው አይመስልህም? ጭንቅ ሲለኝ የምሄድበት ሰው ያስፈልገኛል አንድ ያለን የጋራ ጓደኛ ደግሞ እርሱ ነው። ዛሬም ጥርጣሬ አለህ ማለት ነው?"

"ባይገርምሽ ለእርሱም በቀጥታ እነግረዋለሁ" አላት እርሱም ተናዶ።

"ጤነኛ ካልሆንክ ብቻ ነው ይህንን የምታደርገው?" አለችውና ከመኝታ ቤት ወጣች።

ሳሎን ገብታ ተቀመጠች፤ እንደገና ደግሞ ወጣችና በረንዳ ላይ ቆመች። እርሷ በእነዚህ ሁለት ቀናት ስለእርሱ በማሰብ ያሳለፈችውን ጭንቀትና እርሱ የሚሄድበትን መንገድ እያሰበች ተብሰለሰለች። ፈቃደ በእንዲህ ያሉ ጉዳዮች ላይ ያለው ባህሪና ሌላው ስብእናው



ሁልጊዜም አይጣጣምላትም። እንዲህ ዓይነቱን የትዳር ሕይወት ደግሞ እንኳንስ ለራሷ ለማንም ሰው አትመኘውም። እንዴት አድርጋ ነው ለፈቃደ ልቧን ልታሳየው የምትችለው? በምን መንገድ ነው ሊግባቡስ የሚችሉት?...

መኝታ ቤት እንዳለ ሲጠራት ሰማችው፤ ለጥሪው መልስ መስጠት አስጠላት። ልጆቿ መኝታ ቤታቸው መኖራቸውን ታውቃለች፤ ምን ሊሰማቸው ይችላል? ወደመኝታ ቤት ገባችና "ምነው?" አለችው።

"ቁጭ በይ" አላት አልጋውን እየመለከታት። ማቲ ተቀምጦበት የነበረው ወንበር ላይ ተቀመጠች።

"አጠገቤ መቀመጥ አስጠላሽ?" አላት።

"ምን በደልኩህ ፈቃደ ለምንድነው እንዲህ አእምሮዬን የምትበጠብጠኝ?" አለችው። ተነስቶ ወደአጠገቧ መጣና ቆመ።

"የቱን ያህል እንደምሰስትልሽ ታውቂያለሽ? ያ ስስት ነው እንዲህ የሚያደርገኝ። ከሌላ ወንድ ጋር የመሆንሽን ነገር ገና ሳስበው ያመኛል..."

"አንተ ብቻ ነህ ለወደድከው ሰው የምትሳሳው? ምነው ከሌላ ሴት ጋር ስትሆን ራስህን በእኔ ቦታ አታደርገውም? ወንድ ስለሆንክ ለአንተ ይፈቀዳል እኔን ግን ባልፈጽመውም ገና ስላሰብከው ብቻ እንደፈለገህ ትናገረኛለህ። ያ በዚያ መከራ ውስጥ በጥንካሬው ያደነቅሁት ፈቃደ እንዲህ ይሆናል ብዬ በፍጹም አስቤ አላውቅም..." በውስጧ የታጨቀውን ነገር ለመናገር ገና ስትጀምር አቋረጣት።

"በቃኝ ፍርዬ! ይበቃኛል። ትክክል ያለመሆኔ ተሰምቶኝ እኮ ነው ይቅርታ ለመጠየቅ የጠራሁሽ፤ እባክሽ ተረጂኝ። ሁለተኛ እንዲህ ዓይነት ነገር አላነሳም" አላት። ከዝምታ የተሻለ ምርጫ የላትም እናም ዝም አለችው። ይኼ ደግሞ በጣም ይገርማታል ይቅርታ ለመጠየቅ ያለው ፍጥነት! ግን ደግሞ ተመሳሳይ የሆነ ስህተት ከመፈጸም ራሱን አይገታም። እናም የፈቃደ ነገር በጣም ግራ ያጋባታል፤ ከምን ጎራ እንደምትመድበው እስከሚጠፋት ድረስ።

" ሰኞ እሄዳለሁ" አላት ደግሞ ጥቂት ቆይቶ። "የት" ብላ ለመጠየቅ የሚያስችል ሞራል አጣች። ሁኔታው ከዝምታዋ የሚመልሳት ሊሆን አልቻለም።

"እባክሽን አናግሪኝ፤ ትናንትም መምጣት ያልቻልኩት አዲስ አበባ መሄድ ስለነበረብኝ ነው"

"እሺ ይሁን" አለችው እንደምንም ተጣጥራ። እንደነገሩ ስለአዲሱ ሥራው ተነጋገሩ።

ፍሬሕይወት ፈቃደ ወደአዲሱ ሥራው በመሄዱ ደስ አላት። አብረው ሆነው ሰላም ከሚያጡ መሄዱ በጣም የተሻለ ነው። እርሱ ሲሄድ ሕይወት እንደሚከብዳት ብታውቀውም መሄዱን መረጠችው።

ፈቃደ እንደተለመደው በበዓላት መጣ እያለ እየጠየቃቸው ሕይወት ቀጠለ፤ ልጆቻቸውም አደጉ እርሷም በሥራዋ በረታች። ሩታ አሥራ ስድስት ማቲ ደግሞ ወደ አስራ አራት ዓመት እየተጠጉ ነው። አይታ የማትጠግባቸው ልጆቿ የደስታዋ ሁሉ ምንጮች ሆኑ፡፡ ጉዳቷን ሁሉ የተካሰችባቸው፣ የሕይወትን አስቀያሚ ገጽታዎች ሁሉ የምትረሳባቸው የሕይወቷ ፈርጦች ናቸው ልጆቿ።

ፍቅርና ትዳር ግን የጠበቀችውን ያህል ሆኖ አላገኘችውም። ለሌሎች ምሳሌ ይሆናል ያለችው ትዳር እንኳንስ ምሳሌ ሊሆን እንደማንኛውም ትዳር የሚታይ አልመስልሽ አላት። ቀስ በቀስ ፈቃደ ለአራትና ለአምስት ወራት ሳይመጣ መቆየት ያዘ። "ምን ሆኖ ይሆን?" እያለች መጨነቁ ባሰባት። በየወሩ የሚልክላት ገንዘብም ጊዜውን ጠብቆ መድረስ አቃተው። የምትጽፋቸውም ደብዳቤዎች መልስ አለባነት እየተደጋገመ መጣ።

በዓላት መጥተው አለፉ፤ ፈቃደን የበላ ጅብ ግን አልጮህ አለ። ማሰብ ብቻ ሳይሆን መበሳጨትም ጀማመረች። አንዳንዴ ሀሳብ፣ ንዴትና ብሶት ሲበዛባት ወረቀትና እስኪሪፕቶ አንስታ ስሜቷን ትጽፋዋለች። ስሜቷን ወረቀት ላይ ብታሰፍርም፤ በአእምሮዋ የሚመላለሱ ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑም ከፈቃደ ጋር ተነጋግረው መፍትሔ ሊሰጧቸው



አልቻሉም። ከሁሉ በላይ እረፍት የሚነሳት ደግሞ በዚህ ዓይነት ሁኔታ እስከመቼ መዝለቅ እንደሚቻል ስታስበው ነው።

እግዚአብሔር ላለፈው እንዲጠብቃት ተማጸነች "ለወደፊቱ ግን" አለች ለራሷ። "ኸረ በፍጹም ተለያይቶ መኖር አያስፈልግም! በቃ ፈቃደ ለአዲስ አመት ከመጣ መወሰን አለብን" ብላ ደመደመች።

* * * *

ፈቃደ አዲሱን የሥራ ቦታውን ወዶታል፤ የወደደው ግን ተመችቶት ሳይሆን ብዙ ሊሠሩ የሚችሉ ሥራዎች በመኖራቸው ነው። የእርሱን ሙያ የሚጠይቅ ሥራ ኖሮ ለነገ ብሎ የሚያሳድረው ነገር የለውም። ሠራተኞቹን ወደዳቸው፤ ሠርቶ የሚያሠራ አለቃ የናፈቃቸው ይመስል የፈቃደን እረፍት አልባ ሥራ ያለማጉረምረም ተቀበሉለትና ደስ አሰኙት። እርሱም ቢሆን ለእነርሱ የማያደርገው ነገር የለም፤ ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ጠይቀው "የለም" የሚል መልስ እንዲሰጣቸው አይፈልግም፤ በሠራተኝነታቸው የሚገባቸው መብትም እንዲጓደልባቸው አይፈቅድም። እናም ሥራ ዋጠውና ቤተሰቡን ሄዶ የመጠየቁን ነገር ረሳ።

ሌላ ነገር የሚያስበው ማታ አልጋው ላይ ሲጋደም ብቻ ነው። ተኝቶ ሳይሄድ የቆየባቸውን ወራት ይቆጥራል፤ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት...ይደነግጣል። የአሁኑ ደግሞ ለየት ያለ ነው፤ ረፍት ሊሞላ ያስብና ሥራውን ሲመለከት "ይችኛዋ እስክትጠናቀቅ..." ይልና ወደሥራው ይመለሳል።

አንዳንዴ ደግሞ የፍሬሕይወትንና የልጆቹን ደብዳቤዎች ያወጣና ያነባል፤ መልስ ያልሰጣቸው ደብዳቤዎች መኖራቸው ያስጨንቀዋል፤ ሊጽፍ ሲሞክር ያቅተዋል "ስሄድ ሥራ የቱን ያህል እንደሚበዛብኝ እነግራታለሁ" ይልና ደብዳቤዎቹን ሰብስቦ ያስቀምጣቸዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ደሞዝ ሳይልክ የቀረባቸውና የፍሬሕይወት መልእክት ሲደርሰው የደነገጠው ድንጋጤ ትዝ ይለዋል "ሁለተኛ አይለምደኝም" ብሎ ስንት ጊዜ ለራሱ ቢነግርም በተከታዩ ወር በመድገሙ ፍሬሕይወት ምን ሊሰማት እንደሚችል አስቦታል።

"አሁንስ ደርሼ መምጣት አለብኝ" ብሎ ወሰነ አንድ ወቅት። ወደቤት መሄድ ሲወስን አንዳች ነገር ከበደው። ዘውዱን አስታወሰ፤ ዘውዱን ባሰበ ቁጥር ስሜቱ ዝብርቅርቅ ይልበታል፤ የዘውዱን ጥሩ ሰው መሆን አንድም ቀን ተጠራጥሮ አያውቅም፤ እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ ዘውዱ ይመክረው የነበሩ ምክሮች ከብዙ ነገሮች አድነውታል። ዘውዱ ደግና ተጨናቂ፤ ለሰው ሲል ብዙ ማይል የሚጓዝ ሰው መሆኑንም ከእርሱ በላይ ሊመሰክር የሚችል የለም። የፍሬሕይወትንና የዘውዱን መቀራረብ ግን ከዚህ አንጻር ብቻ መመልከት አልቻለም። ለበርካታ ጊዜያት ከራሱ ጋር ተጨቃጭቋል፤ ፍሬሕይወትንም ሆነ ዘውዱን እርሱ በሚያስበው መልኩ ማሰብ ሀጢአት እንደሚሆን ለራሱ በተደጋጋሚ ነግሯል። ግን ድንገት ዝብርቅ ይልበታል፤ ራሱን መቆጣጠር እስኪያቅተው ድርስ ያበሳጨዋል፤ ጥቂት ቆይቶ ይቅርታ ሊጠይቃት የማይሆን ነገር ተናግሯታል ፍሬሕይወትን።

እንዲህ ዓይነት ሀሳብ ከአእምሮው አልወጣ ሲለው ከቤቱ ወጣ ይላል። አንድ ቀን በዚሁ ስሜት ከራሱ ጋር ሲነታረክ ቆየና ከቤት ወጣ። ራሱን ለማዝናናት በመፈለግ መጠጥ ወሳስዶ ሳለ ያገኛትን ሴት እንደቀልድ አነጋገራት። ስሟን ጠየቃት "መሠረት እባላለሁ" አለችው። ሲጫወቱ አመሹና አብረው አደሩ። አብሮነታቸው ቀጠለና ተቀራረቡ፤ መቀራረብ ደግሞ ወዳላሰበው አቅጣጫ ይዞት ጭልጥ አለ፤ ፈጠን ብሎ ራሱን መመለስ አልሆነለትም። ሁሉንም ነገር ትቶት ከሴትዮዋ ጋር የጠበቀ ወዳጅነቱን ቀጠለ፤ ሥራ ያዘገየው ሳያንስ አዲሱ ግንኙነት ደግሞ የባሰውን ከቤተሰቡ ለየው።

አንዳንዴ ትውስ ይለውና ወሬቱን ይቆጥራል፤ ስምንት ወሬት ሲቆጥር ዘግነነው። ወደቤት ለመሄድ አስቦ ለመሠረት ሲያማክራት ተንሰቅስቃ አልቅሳ መሄድ እንደሚችል ትነግረዋለች፤ ሀሳቡን እርግፍ አድርጎ ይተውና ይቀመጣል። ልጆቹና ፍሬሕይወት የቱን ያህል እንደሚጠብቁት ቢያውቀውም ብቅ ሳይል በርካታ በዓላት አለፉ።

ሁልጊዜም ግን ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ የዘውዱና የፍሬሕይወት የጠበቀ ግንኙነት መሆኑን ያስባል። ለጥርጣሬው ምክንያት ሊሆን የሚችል ማረጋገጫ ባይኖረውም ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገባ ስላደረጉት ያማርራቸዋል።



አንዳንዴ ወደኋላ መለስ ብሎ ታሪካቸውን ሲያስታውስ ያቺ እዚያ መኪና ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየት ፍሬሕይወት ድቅን ትልበታለች፤ የራሱ ሊያደርጋት የቱን ያህል እንደተመኘ ሲያስበው ራሱን ይወቅሳል። ፍሬሕይወት ያው የዱሮዋ ፍሬሕይወት መሆኗንም አይክድም፤ ዛሬም ቢሆን የጥሩ ሚስት ምሳሌው ነች… አንዳንዴ ግን የበዛ ግልጽነቷ ያናድደዋል፤ መጠራጠሩን ያባሰበትን ያን ወቅት እንዴት ይጠላዋል፤ "ምነው ባልጠየቅኋት ኖሮ? እርሷስ ከዘውዱ ጋር አብረው አዲስ አበባ ድረስ መሄዳቸውን ባትነግረኝ ምን ነበረበት?" ይላል ግራ ሲገባው። ወደኋላ ተመልሶ ከዘውዱ ጋር አንድ አካባቢ እንዲሠሩ ያደረጋቸውን አጋጣሚም ይወቅሳል፤ ሁሉም ግን ትርጉም አልባ ይሆንበታል።

* * **

የቅዱስ ዮሃንስ በዓል ደርሶ ሁሉም የበዓል ዝግጅቱን ተያይዞታል፡፡ የተለመደው የፈቃደ መምጫ ጊዜም ተቃርቦ ቀናት ብቻ ቀርተዋል። ፈቃደ ለአዲስ ዓመት በፍጹም ከጳጉሜ ሦስት አልፎ አያውቅም፡፡ ልጆቹም በናፍቆት ይጠብቁታል እርሱን ብቻ ሳይሆን ሲመጣ የሚገዛላቸውን የአዲስ አመት ስጦታም ይጠብቃሉ።

ፍሬሕይወት በአሁኑ አዲስ ዓመት ፈቃደ ሲመጣ የወደፊቱን ሕይወታቸውን በአዲስ መልክ ለመጀመር ሊወስኗቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች እንደሚኖሩ አስባለች። ውሳኔዎቻቸው ደግሞ ትዳራቸውን የሚያጠነክሩ ሊሆኑ እንደሚገባቸው ታምናለች። መጭውን አዲስ ዓመት በአዲስ መልክ ለመጀመር አስባ ለራሷና ለፈቃደ ስጦታ ለመግዛት ስትዘጋጅ ነው የሰነበተችው። ፍሬሕይወትና ፈቃደ የጋብቻ ቀለበት የላቸውም፤ ስለዚህ ለአዲስ ዓመት ለሁለቱም የሚሆኑ ቀለበቶች ገዝታ፣ በአዲስ ዓመት አዲስ ቃል ተገባብተው ትዳራቸውን እንዲያድሱ የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር ስታስብ ሰነበተች። ቀለበቱን ገዝታ በስጦታ ወረቀት ጠቅልላ ስትሰጠው፤ በጣም ቸኩሎ ሲከፍተው፤ ቀለበቱን ሲመለከትና ሲደነግጥ፤ ዐይኖቹ የደስታ እንባ ሲያቀሩ… እቅፍ አድርጎ ሲስማት፤ የሚያደርገው ሲጠፋው… በዐይነህሊናዋ ሲታያት የራሷ ዐይኖች እንባ አቀረሩባት። ፈቃደ ሁልጊዜም ለበዓል አሥራአምስት ቀን ሲቀር ይመጣል፤ እርሷም እንደመጣ ስጦታውን ትገዛለች፤ የልጆቹን ስጦታዎች ግን አብረው ይገዛሉ። ገንዘቡን አሰናድታ አስቀመጠች።

ቀናት አለፉ ፈቃደ ግን አሁንም አለመጣም፤ "ምን ሆኖ ይሆን? ለመሆኑ ደህና ነኝ ባለመምጣቱ አታስቢ ማለት ማንን ገደለ? ምን ይሻለኛል?" ትላለች ፍሬ በጭንቀት። ቀኑ ሲቃረብ ዓውድ ዓመት መጣሁ መጣሁ እያለ አካባቢው ልዩ ስሜት ፈጥሯል፤ የፍሬ ልብ ግን እንዳዘነ ነው። ሁል ጊዜ ማዘን ብቻ ምን ይጠቅማል? ጊዜው እንደሆነ ከተፈጥሮ ቀመሩ ዝንፍ አይል፤ ጳጉሜ ገባች።

የልጆቹን ስሜት ለመጠበቅ ስትል ጳጉሜ አምስት በአውደ ዓመቱ መባቻ ቀን ለብቻዋ ሄዳ ለልጆቿ የሚያስፈልጋቸውን ገዛዝታ መጣች። የገዛችላቸውን ልብስና ጫማ ድንገት ላይሆናቸው ቢችል አለችና እንዲለኩት አደረገች፡፡ በምርጫዎቿ በጣም ደስ ሲላቸው በማየቷ እርሷንም ደስ አላት።

"እማ ያንችስ?" አለች ሩታ የራሷን ለክታ ስትጨርስ።

"የእውነቷን ነው ለአንቺ የገዛሽውን አሳይን" አለ ማቲም ከተል አድርጎ።

"ለእኔማ ፈቃደ ሲመጣ ይገዛልኛል" አለቻቸው በቀላሉ።

"መቼ?" አሉ ሁለቱም በአንድነት።

"ዛሬ ይመጣል" አለቻቸው

አሁንም ተስፋ አልቆረጠችም፤ ዕለቱ እየተገባደደ ሲሄድ ግን ጭንቀቷን መቆጣጠር አቃታት፡፡ በደህናው ይቀራል ብላ ለማሰብ መሞከሩም አልሆነላትም። የምትሆነውን አጣች። ወደ አስር ሰዓት አካባቢ ከቤት ወጣች፡፡ መረጃ ለማግኘት ነበር የወጣችው። መንገድ ላይ ትርሲትን አገኘቻት።

"ወዴት ነው ፍርዬ እኔ ወደአንቺ ስመጣ?" አለቻት

"ኧረ እኔም ወደአንቺ እየመጣሁ ነበር። ታደለ አልመጣም እንዴ?" አለቻት የትርሲት ባለቤት ታደለና ፈቃደ አብረው ነው የሚሠሩት።



"ዛሬ ገባ፡፡ መልእክት አምጥቷል" አለችና ፖስታ ሰጠቻት። ከትርሲት ተለይታ መልእክቱን እስከምታነበው ቸኮለች።

እቤት ስትገባ በችኮላ ፖስታውን ቀደደችው፤ መልእክቱ የተጻፈው በትንሽ የማስታወሻ ወረቀት ነው። አምስት መቶ ብሮች ከማስታወሻው ጋር አገኘች። መልእክቱ ሦስት መስመር ነው።

"ውድ ቤተሰቦች እንደምን አላችሁ? እኔ እንደነገሩ ደህና ነኝ። ለዓመት በዓል መምጣት አልቻልኩም። ከመስከረም አሥር እስከ አስራ አምስት ባለው ጊዜ እመጣለሁ" ይላል መልዕክቱ። ወሽመጧ ተበጠሰ፡፡ ሐዘንና ንዴት በደምስሮቿ ሲሰራጭ ተሰማት። ብጣሽ ወረቀቱን እንደገና ተመለከተችው የተጻፈበት ቀን ነሐሴ አስራ ስምንት ይላል።

አዘነች ፤ በጣም አዘነች። "ያላንቺ መኖር አልችልም፣ ላጣሽ አልፈልግም፣ አንቺ የሌለሽበት ሕይወት ባዶ ነው፣..." ይላት የነበረ ሰው ሳይገናኙ አንድ ዓመት ሞልቶ በአዲስ ዓመት መባቻ እንዲህ ዓይነት ማስታወሻ ሲልክላት ምን ሊሰማት ይችላል?

በቤት ውስጥ የጎደለ ነገር የለም፡፡ ጎዶሎ የነበረው የፍሬ መንፈስ ነው። የልጆቹን "አባታችንስ?" ጥያቄ መስማት አስጠላት። እንደማይመጣ ነገረቻቸው ቤቱ በዓል አልመስል ብሎ ጭር አለ። ልጆቿን ለማስደሰት ግን ደስተኛ መምሰል ነበረባትና የምትችለውን ጥረት አደረገች። ካሏት ልብሶች ውስጥ ጥሩውን እንዲመርጡላት ለልጆቿ ነገረቻቸውና በሁለቱ ጭቅጭቅ ቤቱ ደመቅ አለ። በኋላ የሁለቱንም ምርጫ እንደምትቀበል ነገረቻቸው፤ ለዋዜማና ለበዓሉ። እነርሱም ለዋዜማ የመረጡትን እንዲለብሱ ለበዓል አዲሱን እንዲያስቀምጡ ተስማሙ፤ በዓሉን በዓል ለማስመሰል ጥረት አደረገች። የእውነትም በአሉን በደስታ አሳለፉት፡፡ ውስጧ ቢያዝንም፣ የፈቃደ ሁኔታ ቢያሳስባትም ከልጆቿ ጋር ግን ለመደሰት ያደረገችው ጥረት ተሳካላት።

በዓሉ አለፈና መስከረም አስርን መጠበቅ ያዘች። መስከረም አለቀና ጥቅምት ገባ፤ ፈቃደ ግን ሳይመጣ ቀረ። ግራ ተጋባች። ወደአእምሮዋ ሲመጡ የምታባርራቸው ሀሳቦች ሁሉ አሁን አእምሮዋን ማጨናነቁን

ተያይዘውታል። ደህና መሆኑን ትሰማለች እርሱ ግን የውሀ ሽታ ሆነ። ከሄደ አንድ ዓመት ሊሞላ የቀረው ጊዜ አንድ ወር የማይሞላ ነው፤ ነገሩ እንቆቅልሽ ሆነባት። ደብዳቤ ለመጻፍ ወሰነችና እስኪሪፕቶና ወረቀት አነሳች። ደብዳቤውን ጽፋ ስትጨርስ ደጋግማ አነበበችው፡፡ በወቅቱ የነበራትን ስሜት በደንብ ባይገልጽላትም ደብዳቤው እንዲህ ይነበባል፤

*"ለውድ ባለቤቴ እንደምን አለህ? እኔም ሆንኩ ልጆቼ በጣም ደህና ነን። ከተለያየን አንድ ዓመት መሙላቱን አወቅህ? አዎን አንድ ድፍን ዓመት ሊሞላ ነው። ሁሉም ነገር እንዲሁ ፈጥኖ ያልፋል። መጥፎውም፣ መልካሙም፣ ችግሩም፣ መከራውም... ብቻ ሁሉም ማለፉ አይቀርም። እኛ በሕይወት እስካለን ድረስ ሁሉንም እያሳለፍን እንኖራለን፤ ግን ዕድሜአችንም አብሮ ያልፋል። ትልቁም ነገር ያለው እዚህ ላይ ነው! ዕድሜን ወደፊት እንጂ ወደኋላ አይመለሱበትም፤ ካለፈ አለፈ ነው በቃ! ችግርን አሳልፈን ወደደስታ አለያም ከተደላደለ ሕይወት ወደ ችግር አዘቅት ... ደግሞ ተመልሰን ወደቀድሞው ...እንደየሁኔታው በሕይወት ዘመናችን ልንመላለስበት እንችላለን። ልንመልሰው ... እንደገና ልናልፍበት የማንችለው ዕድሜን ነው። ግን እንዴት ያሳዝናል? የንተን እንጃ እንጂ እኔ በጣም ነው የማዝነው።*

*አቤት! የወጠነውን ጅምር ሕይወት በወጉ ሳናደርገው ስንት ዓመታት ተቆጠሩ? ትዳራችን የትዳርን ስሙን እንጂ ወጉንና ጣዕሙን ካጣ ስንት ዓመታት አለፉ? ግን ዓመታቱ ፈጥነው ባለፉበት ወቅት ዛሬ የማይባቸው መልክ አልነበራቸውም፡፡ ያኔ ዓላማና ተስፋ ነበረኝ አንዱ ዓመት ሲያልፍ ተከታዩን በተስፋ እጠብቅ ነበር፤ ዓላማዬን ከግብ ለማድረስ ጥንካሬ እንደሚያስፈልገኝ እየተሰማኝ ራሴን አበረታትቼ በተስፋ ቀጣዩን ዓመት በአዲስ ጥንካሬ ለመቀበል እወስን ነበር።*

*ያለቀውን ዓመት ስንጀምር ያቀድነው ዕቅድ ትዝ ይልሀል? እቅዳችንን ተግባራዊ ለማድረግ በኔ በኩል የምችለውን ሁሉ ከመፈጸም ወደኋላ አላልኩም። አንተ ግን የውሀ ሽታ ሆነህ ቀረህ፤ እንኳንስ የተሻለውን አፈጻጸምህን ልታሳየን ዓውድ ዓመትንም አብረኸን ለመዋል ጊዜ አጣህ። ኸረ እኔ ግራ ገብቶኛል!*

*ልንገርህ! ትዳራችን ትዳር የሚያሰኘውን ሁኔታ ሳያሟላ፣ የቤተሰብን ትክክለኛ ትርጉም ሳይዝ፣ የልጆቻችን የወደፊት ሕይወታቸው መሰረት የሚገነባበትን ወሳኙን የዕድሜ ክልል ሊያልፉ በመሆናቸው ያሳዝኑኛል። ሕይወት ገንዘብ ማግኘት ብቻ አይደለም፤ እኔና ልጆቼ ከምንጊዜውም በላይ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሕይወትን ያካተተ ቤተሰባዊ ሕይወት እንፈልጋለን።*

*ስለዚህ ፈቃደ እንድትመጣና እንድነጋገር ያስፈልጋል።*

*መልካም አዲስ ዓመት እንዲሆንልህ እመኛለሁ"*

ደብዳቤውን በትርሲት ባለቤት በታደለ ልትልክለት ነበር የጻፈችው ስሜቷ ግን አልፈቅድ አላት። ደብዳቤውን መላክ ሽንፈት መሰላት፤ እናም አስቀመጠችው።

* * * * *

ሰሞኑን ፈቃደ ወደቀልቡ የተመለሰ ይመስላል፤ ሁሉን ነገር ረስቶትና ትቶት ከሰነበተ ወራት በዓመት ሊተኩ መሆኑ ያሳሰበው ጀምሯል። ልጆቹንና ፍሬን ሳያያቸው ይህን ያህል ጊዜ መቆየቱ ትክክል ያለመሆኑ ቢሰማውም፤ በሕይወቱ ውስጥ ለጊዜያዊ ፍላጎት ማርኪት ሲል ከሚመሠርታቸው ግንኙነቶች ወጣ ማለቱንና ስህተት እየሠራ መሆኑን አስቦት ቢያውቅም የጀመረው አዲስ ግንኙነት ያመዝንና እርግፍ አድርጎ ይተወዋል። ሕይወት አስከፍቷት ራሷን ለማጥፋት ጥቂት ቀርቷት ለነበረችው ለመሰረት በሕይወት እንድትቆይ ምክንያት በመሆኑ፤ ለተጎዳ ልቧ መጽናናትን ሰጥቶ ደስተኛ እንድትሆን በማድረጉ ደስ ብሎት ነው የቆየው።

በዚህ ሰሞን ግን ህሊናው እረፍት ነስቶታል፤ ወደቤት መሄድ እንዳለበት፤ ልጆቹን መጠየቅ እንደሚያስፈልገው ይጎተጉተዋል። ግን

ፍሬ ምን ትለዋለች? እርሱስ ምን ይላታል? ከሌላ ሴት ጋር ፍቅር ጀምሬ ጠፋሁ ወይስ ምን? ያም ሆነ ይህ የሆነውን ነገር እንዳልተፈጠረ አድርጎ ፍሬን ሊያሳምናት አይችልም። እውነቱን ነግሯት ይቅርታ መጠየቅ እንደሚሻለው አሰበ። ግን እንዴት አድርጎ ነው ይቅርታ የሚጠይቃት? የሆነውን ሁሉ በአንደበቱ ሊያወራላት አቅም እንደማይኖረው ያውቀዋል እናም ማስታወሻና እስኪሪፕቶ አነሳና መጻፍ ጀመረ፤ "ሰው ሲቸገር" ብሎ ርእስ ሰጠው።

"ሰው ሲቸገር"

" ...ባለቤቴን አፈቅራለሁ ልጆቼንም እንደዛው፤ ግን ያለገንዘብ መኖር አይቻልም፤ ፍቅር ብቻውን አያኖርም። በመሆኑም የቤተሰብ ኃላፊነቴን ለመወጣት የውዴታ ግዴታ ሆኖብኝ ከቤተሰብ ርቄ ለመኖር ተገድጃለሁ ..."

"... በአፍላ ዕድሜዬ ጊዜው የፈቀደልኝን ሁሉ አድርጌያለሁ፤ አሁን በትውስታ ስመለከተው ይደንቀኛል። አሁን ወደአዲሱ የሥራ ቦታዬ ከመጣሁ በኋላ አንድ ሁኔታ ተፈጠረ።

አንድ ቀን በፕሮግራሜ መሠረት ራሴን ለማዝናናት ወደከተማ ወጣሁ። ራሴን ከመጠጥ ሱሰኝነት ነፃ ካወጣሁ ስምንት ዓመታት ተቆጥረዋል ያን ዕለት ግን ደስተኝነት ስላልተሰማኝ ሰውነቴን ፈታ ለማድረግ ከእራት በኋላ ትንሽ መጠጥ ወሳሰድኩ። ከዛ በኋላ አልጋ ወደያዝኩበት ሆቴል ሳዘግም አብረውኝ የነበሩ ሰዎች አገኘሁና እግረመንገዴን ወደሌላ ቡናቤት ጎራ አልኩ። ጥቂት ቆይቼ ወደማረፊያዬ ሄድኩ፡፡ ሰዓቱ ጊዜ ስለነበረ አምቦ ውሀ ይገፍ በረንዳ ላይ እንደተቀመጥኩ አንዲት ሴት በአጠገቤ አለፈች።

በረንዳ ላይ መቀመጥ ሲሰለቸኝ ተመልሼ በመውጣት ወደሌላ ቡና ቤት ገባሁ። በመጠኑ አልኮል ጠጥቼ ወደመኝታዬ የተመለስኩት ወዲያውኑ ነበር። የጊቢውን በር አልፌ ወደውስጥ ስዘልቅ አንዲት ሴት ከዛፍ ስር ተቀምጣ አየሁ። ተጠግቼ ሳያት ቀደም ሲል በረንዳ ላይ በነበርኩበት ጊዜ ያየኋት ሴት ነች።

"መቀመጥ ይቻላል?" አልኳት



"ይቻላል" አለችኝ ቀልጠፍ ባለ አነጋገር

"እንግዳ ነሽ መሰለኝ" አልኳት

"አዎን እንግዳ ነኝ ከአዲስ አበባ ነው የመጣሁት አለችኝ ሴትዮዋ

ቀረብ ብዬ ስመለከታት ገጽታዋን የማውቀው መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ የቅርብ ትውውቅ ባይሆንም አንድ ኬክ ቤት ውስጥ በገንዘብ ተቀባይነት ስትሠራ በዐይን ነበር የማውቃት።

"የት ነበር የምትሠሪው?" አልኳት ለማረጋገጥ

"ፒያሳ" አለችኝ

ችግር፣ ሀሳብና ጭንቀት ግን መልኳን ለውጦታል። አንድ ባነበብኩት መጽሐፍ ላይ "...ሰው ሲቸገር ፣በቃ! አለቀ ደቀቀ ብሎ ተስፋ ሲቆርጥ የሚፈልገውን እርዳታ ማድረግ ለአድራጊውም ሆነ ለሚደረግለት ምን ያህል ደስታ ይሰጣል?... የሚል ሀረግ ትዝ አለኝ።

"ምንም ማድረግ አልችልም" አልኩ ለራሴ

"እህት ስለአንቺ ማወቅ የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ እዚህ ሆቴል አልጋ ይዤለሁ፤ ነገር ግን ሴት ስለቀጠርኩ አንቺ መኝታ ቤት ምሽቱን አብረን ብናሳልፍስ?" በማለት ጠየኳት

"ደስ ይለኛል" አለች ባለማመንታት

"...የሴትዮዋ ሁኔታ በጣም አሳዘነኝ። እኔም በብዙ ችግሮች ውስጥ አልፌአለሁ፤ በዚያ በችግር ወቅት ታዲያ ምን እንደተሰማኝና እንዴት እሆን እንደነበር ድቅን አለብኝ። በክፍሉ ውስጥ በነበረችው አልጋ ላይ አረፍ ብዬ በአምፖሉ ብርሃን ተመለከትኳት። ይህን ፊት እንዲህ ቀለሙ ተለዋውጦና ቆርፍዶ አልነበረም የማውቀው።

“ቲሞ” በይ እንጂ” አልኳትና ተቀመጠች “ለመሆኑ ይህን ዓይነቱን ሥራ ልትሠሪ ከአዲስ አበባ ድረስ እንዴት መጣሽ?” አልኳት እንደማውቃት ሳልገልጽ።

“ሰው ሲቸገር የትም ይሄዳል ሰይጣንም ቤት ይገባል። የእኔ ግን የተለየ ነው። እዚህ የመጣሁት እራሴን ከማጥፋት እዚህ ሞት ራሱ በቅርብ ይገኛል ሲባል ስለሰማሁ ነው” አለችኝ።

ሰውነቴን ዝግንን አለኝ። እኔም በአንድ ወቅት ችግርና ጭንቀት ሲበዛብኝ ሕይወቴን ለማጥፋት ያሰብኩበት ጊዜም ነበር። ያ ሁኔታ ትዝ አለኝ። ቢሆንም “ከመኖር ተስፋ አለ፤ ካለመኖር ግን ምንም!” የሚለው አባባል መልሶኝ እዚህ ደርሻለሁ።

“እህት የችግር ቀንበር ከሰው ልጅ ትከሻ ላይ ወርዶ አያውቅም ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ሰው ሆኖ ችግር የማይደርስበት የለም። ለችግር ዋነኛ መድሀኒቱ ራሱ ችግር የደረሰበት ሰው ሲሆን የሚረዳው ሰው ካገኘ ደግሞ ተጨማሪ መፍትሄ ይሆናል” በማለት የራሴን ተሞክሮዎች በትንሹ ገለጽኩላት። ሆኖም የምናገረው ሁሉ ግንባሯን ገጭቶ ሲመለስ አስተዋልኩ። ችግር ውስጥ የወደቀ ሰው መፍትሄው በቁሳቁሳዊ መልኩ ካልቀረበ እምብዛም እንደማያረካው አውቃለሁ።

ጥቂት ተንፈስ አልኩና “ላደርግልሽ የምችለው አንድ ነገር አለ። አንተዋወቅም እንጂ ከምትቀመጭበት የካሸር ባንኪ ውስጥ ሆነሽ ነው የምትታይኝ ...ብቻ አወቅሁሽ አላወቅሁሽ የእኔ ዓላማ አሁን ካለሽበት ችግር በምችለው አቅም ለማውጣት ነው። ምናልባት አሁን የምጠረጥረውን ሙያ ያልሆነ ሙያ ልትማሪበት ...” እራሴን ከሴትዮዋ ጋር እያነፃፀርኩ እንባዬ ተናነቀኝ።

“ሴተኛ አዳሪነትን?” አለችኝ ተናግሬ ሳልጨርስ። “ለዚህ ብዬ ከአዲስ አበባ ድረስ አልመጣሁም፤ አሁንም ደግሜ ልግለጽልህ እዚህ ሞት ቅርብ ነው ስላሉኝ መጣሁ” አለችኝ

“እንግዲያው በአቅሜ ልረዳሽ የምችለው በአካባቢው የማውቃቸውን ሰዎች አጠያይቄ ሥራ እንዲፈልጉልሽ ማድረግ ነው” አልኳት።



ከዚህ ሁሉ ቆይታ በኋላ ፍላጎቴ ተቀስቅሶ ከችግሯና ከስነስርዓት ጠባቂነቷ አንፃር እንደመውደድ ተሰምቶኝ አብሬያት አደርኩ...”

“... ጠዋት በተቻለኝ ሁሉ እንደምረዳት በድጋሚ ቃል ገብቼላት ወደሥራዬ ሄድኩ። ከእርሷ ከተለየሁ በኋላ እንዴት እንደምረዳት ሳውጠነጥን ቆየሁ። በአጭር ጊዜ መፍትሔ ካላገኘች ምርጫዋ ሴተኛ አዳሪ መሆን አሊያም ራሷን ማጥፋት ብቻ ነው። መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን በሀሳቤ ሳወጣና ሳወርድ ቆየሁና ጠበቅ ያለ ትውውቅ ወደነበረኝ የመሥሪያ ቤት ኃላፊ ሄጄ ተስፋ አገኘሁ።
አንድ ቅዳሜ አጣዳፊ ሥራ ላይ ሳለሁ ሰው እንደሚፈልገኝ ተነገረኝ። የልቤ ምት ጨመረ፤ ከአዲስ አበባ ይመጣል ብዬ የምጠብቀው ሰው ስላልነበረኝ እየተጣደፍኩ ወጣሁ። ያገኘሁት መሠረትን ነበር። ከሩቅ ሳያት ደነገጥኩ ቀረብ ስላት የተቸገረ ሰው ችግሩን ወደሚካፈለው ሰው ሲመጣ የሚያሳየውን የደስታ ፊት ስመለከት ችግሯን ለማቃለል ያደረግሁት ጥረት ዝቅተኛነት ተሰማኝ።

ወደቤት ይዣት ሄድኩ፤ በጨዋታችን መሀል ያልጠበቅሁት ሌላ አጋጣሚ ተፈጠረ። መሠረት የቅርብ ጓደኛዬ የአክስት ልጅ ሆና ተገኘች። የሁኔታው መገጣጠም አስገረመኝ። የመሠረት የአጎት ልጅ በሥጋ ባይዛመደኝም እንደወንድሜ የማየው የነበረ ጓደኛዬ ነበር። ከመሠረት ጋር የፈጸምኩት ግንኙነት ትክክል እንዳልሆነ ተሰማኝ። መሠረት በሀብትም ሆነ በስነምግባር ወደዚህ ዓይነት ተግባር ከሚገፋፋ ቤተሰብ የተገኘች አይደለችም ። በመሆኑም ይህም እንደተጨማሪ ሆነና መሠረትን ከገባችበት ችግር ለማውጣት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንዳለብኝ ወሰንኩ። ሙሉ ቀን አብረን ውለን አብረን አደርን።

ጠዋት ከእንቅልፋችን ነቅተን ጋደም እንዳልን “ፈቃደ ባለፈው ሳምንት አንተን አግኝቼ ያደረግህልኝን እርዳታ ባላገኝ ኖሮ ወንዝ ውስጥ ገብቼ ሕይወቴን ባጠፋሁ ነበር” ብላ ሊሊቱን ሲያነባ ያደረውን ዐይኗን የበለጠ በእንባ እንዲታጠብ አደረገችው በሥራ አካላቴ የሆነ ነገር ተተረማመሰብኝ አዘንኩ። ተፈጥሮዬ ሆነና በቃላት ሰውን ማረጋጋት አይሆንልኝም። ብቻ ችግርን በራስ ስለማውቀው እንዴት ራስን ከችግር ማውጣት እንደሚቻል የሀሳቤን ሁሉ አወራሁላት።

መሠረትን ችግርና በጅምር ያለው ፍቅር እየተፈራረቁ እንባዋን ያጎርፉታል። እንደምንም አረጋጋኋትና ከአልጋ ወርደን ቁርስ በላን።

"ፈቃደ ሎንችን እንዳያመልጠኝ" ስትለኝ የፍቅር ንዝረት ሰውነቴን ወረረኝ። በቅርቡ የወጣ አንድ ዘፈን ትዝ አለኝ "ፍቅር አገረሸብኝ" አልኩ።

ለትዳሬ የምሰጠው ፍቅር ብቻ ሳይሆን ለትዳር መሰጠት ያለበትን ክብር አውቃለሁ። ሀሳቤ ከሁለት ተከፈለ፡፡ ልቤ ፈነቀለኝ ከልቤም ተሸነፍኩ ከአእምሮዬም ጋር ትግል ያዝኩ።

መሠረትም ልትቋቋመው ያልቻለችው ፍቅር ፈንቅሏት "እኔ አልችልም" በማለት በስቅስቅታዋ ውስጥ ደጋግማ ተናገረች። ዐይኖቹ እንባ አቅርረው ዝም አልኳት። ሰው ሲቸገር ከሚደረግለት ሌላ በፍቅር ለተንጠለጠለ ልብ መሰጠት ያለበትን መልስ ለመግለጽ ተገደድኩ።

ወትሮውንም ፀባዬ በመሆኑ በግልጽ ልነግራት ፈለግሁ። የቤተሰብ ኃላፊነቴን ገልጬ ካየኋት ቀን እስከዚያን ዕለት ግን ሰውነቴ በፍቅር እንደተሸነፈና ልወዳትም እንደተገደድኩ ነገርኳት"...

ማስታወሻውን አስቀመጠና ወዲያ ወዲህ ተንጎራደደ። ወደአዲስ አበባ መሄድን ከአእምሮው ሊያወጣው አልቻለም። ጭንቅላቱ ብጥብጥ አለበት፤ የልጆቹ መልክ አሁንም አሁንም እየታየውና ድምጻቸው እየተሰማው ናፍቆት አስቸገረው።

"የግዴታ መሄድ አለብኝ፤ ሁሉንም እንዳመጣጡ መቀበል ግዴታዬ ነው" አለ ለራሱ። ቢሮ ሲገባ የመጀመሪያ ሥራው ፈቃድ መሙላት ሆነ።

* * * *

ፈቃደ በተመቸው ጊዜ መጣ፡፡ ውስጧ ደስተኛ ባይሆንም ፍሬ በሰላም ተቀበለችው። ልጆቹ አባታቸውን በማግኘታቸው ፍንድቅድቅ ሲሉ በማየቷም ደስ አላት። ፈቃደ በመጣ በሦስተኛው ቀን ልጆቹ



ወደትምህርት ቤት ሲሄዱ መነጋገር እንዳለባቸው አነሳችበትና ገና መነጋገር ሲጀምሩ "ምን መሰለሽ መሲ..." አላት። ያለችበት ጠፋባት ለተወሰኑ ደቂቃዎች ምን ማድረግ እንዳለባት ሳታውቅ ዝም አለችና።

"ማን አልከኝ ግን?" ብላ ጠየቀችው በጣም ከመደንገጧ የተነሳ በሙሉ ዐይኖቿ ልታየው አቃታት፤ ቀጥሎ ልትሰማ የምትችለውን ነገር ፈራችው። ዝምታው እንደድንጋይ ከባድ ሆነባት፤ ጨነቃት፤ እርሱም መልስ ሊሰጣት አልቻለም።

"ለምን አትነግረኝም ከዚህ በኋላ መታገስ የምችል ይመስልሃል?" አለችው ዝምታውን ሰብራ።

ፈቃደ ተነሳና ሻንጣውን ከፍቶ አንድ ማስታወሻ አወጣና ሰጣት። "ፈቃድሽ ከሆነ ይህን አንብቢውና ከዚያ በኋላ እንነጋገር" አላት። ተቀበለችው፤ ግራ ቢገባትም ማንበብ ጀመረች "ሰው ሲቸገር" ይላል ርእሱ።

ጥርሷን ነክሳ አንብባ መጨረሻው ላይ ስትድርስ ፍሬሕይወት አንዳች ስሜት ሰውነቷን ተቆጣጠረው፤ ማስታወሻውን ወርውራለት ፊቷን ተሸፈነች። በፍጹም የሆነ ድርጊት የምታነብ አልመሰላሽ አላት፡፡ አጠገቧ ያለውን ፈቃደን ተጠየፈችው። ከዚህ ድርጊቱ በኋላ ገላዋ ከገላው መነካካቱ አናደዳት።

ደግማ ደጋግማ ያነበበችው ይመስል እያንዳንዱ ዓረፍተነገር በጭንቅላቷ ውስጥ የሚያስተጋባ፤ በዚያ ወቅት በዓለም ላይ ያሉ አስቀያሚ አባባሎች ሁሉ ከአፏ ለመውጣት የሚሽቀዳደሙ መሰላት። አንድም ቃል ግን ከአንደበቷ አልወጣም። ቆይታ ግን ከት ብላ ሳቀች። የንዴት ሳቅ!

"በጣም ጎበዝ ደራሲ ነህ። ግን ምን ላድርገው?" አለችው። መልስ አልነበረውም። እንደገና ሳቀች፤ የሳቋ ብዛት ለራሷው ደህንነቷን እስከሚያጠራጥራት ድረስ። በኋላ ደግሞ እንባዋ ድንገት ይገነፍል ጀመር። ስቅስቅታዋ ቤቱን ሞላው፡፡ ፈቃደ ለማረጋጋት ቃጣው እጇን መንጭቃ ወረወረችው። በጽሑፉ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ቃል

አጥንቷን የሰበረው መሰላት። ጽሑፉ ባደረገው ድርጊት መፀፀቱን የሚገልጽ አንድ እንኳን ቃል የለውም።

"ይህ ሰው ግን ጤነኛ ነው ማለት ይቻላል?" አለች ለራሷ "እና ቆይ እስኪ ምን ይሁን ነው የምትለው? ሌላ ሴት አፈቀርክ! ምን ላድርግህ? ማፍቅርህንም ነገርካት፤ መቀጠል ነዋ!..."

"አይደለም እኮ ጽሑፉ ስላላለቀ ገና ይቀጥላል መሲ ..." ፈቃደ ጽሑፉን እንዳልጨረሰው ትዝ ሲለው በጣም ደነገጠ፤ ማስታወሻውን ሲያጠናቅቀው መተውን አስታወሰ።

የጠራው ሥም ገና ወደጆሮዋ ሲደርስ ተፈናጥራ ከአልጋው ወረደች፤ ፈቃደ ትራሱን በቡጢ አቀመሰው።

"ገና ወደፊት ነው የምትፀፀተው? ያን ጊዜ ደግሞ ስለመፀፀትህ የፃፍከውን አነብልሃለሁ" አለችው።

ዓለም ሁሉ ተገለባብጠባታል። ምንም ነገር ሊያጽናናት የሚችል አልመስልሽ አላት፤ ትንፋሿ ያቃጥላታል፤ አንጀቷ ድብን ማለቱ ይሰማታል፤ ጉሮሮዋና ምላሷ በየደቂቃው ይደርቅባታል በውሀ ትጉመጠመጣለች። ጭንቅላቷ ተወጥሮ ከአሁን አሁን የሚፈነዳ መሰላት ጥቃትና ንቀት ተሰማት።

"አቤት! እንዴት ክፉና ጨካኝ ነው?" አለች ለራሷ "ለእውነተኛ አፍቃሪ ይህ መልስ ይሰጣል እንዴ? መላ ሰውነትንና ልብን ለአንድ ሰው አስረክቦ ዓለምን ችላ ማለት ያስነውራል እንዴ? እራስን ተወት አድርጎ ለትዳርና ለልጆች መኖር ያስንቃል?..." በርካታ ጥያቄዎች በአእምሮዋ ውስጥ ተመላለሱ።

ወይ ጉድ! ለዚህ ትዳርና ፍቅር ምን ያልሆነችው ነበራት፤ በፈቃደ ላይስ የቱን ያህል እምነት ጥላበት ነበር? ባጠፋው ጥፋት ተፀጽቶ ከአንዴም ሁለቴ ይቅርታ የጠየቀ ሰው እንዴት በድጋሚ ተመሳሳይ ስህተት ይሠራል ብላ ትገምት? ምን ያህል ሞኝ ናት! ፈቃደ ያለፈውን አመኔታ ማጉደሉን ለወደፊት ፍፁም ታማኝ በመሆን ይሽረዋል ብላ መገመቷ እንዴት የዋህ ብትሆን ነው? በፍፁም ራሷን



የዋህ አድርጋ አስባው አታውቅም... የቱንም ያህል እንደምታፈቅረው ብታውቅም እንደ አለት የፀናና የማይሰበር እምነት ማሳደሯ ስህተት ነበር፡፡ አንዴ እምነት ከተሸረሸረ በኋላስ ተመልሶ እንደነበረ ይሆናል ብሎ ማሰብ ምን ይባላል?"

ድንገት ታረቀኝ ድቅን አለባት፡፡ "አቤት የፍቅር አምላክ! ግፍ ሰርቼ ነበር ማለት ነው? ይቅር በለኝ ታረቀኝ!" አለች ለራሷ። አልጋው ላይ የተኛውን ፈቃደን በትዝብት አስተዋለችው፡፡ ንዴቷ ጨመረ! በጥርሷም በጥፍሯም ልትቦጫጭቀው አማራት።

"እሺ ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልገው? ለፍቅራችሁ ቡራኬ እንድሰጥ ወይንስ ሰርግ እንድደግስ? ከኔ የምትፈልገው ምንድነው?" አለችው። መልስ የለም።

"እንግዲያው በእኔ በኩል ፍቺ እፈልጋለሁ" አለችው፤ ከእርሱ መልስ ስታጣ። በድንጋጤ ተነስቶ ተቀመጠ።

"በቃ ውሳኔሽ ይሄው ነው?" አላት አፍጥጦ እየተመለከታት።

"በጣም ደፋር ነህ ሌላ ምን ነበር የጠበቅከው እባክህ?" አለችው።

በራሷ የመተማመን ባህሪዋ ዛሬም አለ፡፡ የመንፈስ ኩራቷም አብሯት ነው። መናቅንና ጥቃትን አሜን ብሎ የሚቀበል ህሊናም የላትም። ፈቃደን ትኩር ብላ ተመለከተችው፤ ገጽታውን እየተመለከተች ያሳለፈችውን ሕይወት አሰበችው። አዎ በራስ የመተማመን ባህሪዋ በርቺ እያላት ያፈቀረችውን ሰው የራሷ ማድረግ እንደምትችል እያንሾካሾከላት፤ ለዚያ ደግሞ ሴትነቷ እንቅፋት መሆን እንደሌለበት እያሳመናት...እስከዚያ እስከመጨረሻው ዕለት እንዳደረሳት አሰበች።

በሌላ በኩል ደግሞ ማህበረሰቡን ፈርታ የቤተሰቦቿን ስም ለመጠበቅ ብላ እርግዝናዋ ሊያስከትልባት የሚችለውን ማህበራዊ እንከን አስባ የተቀበለችው የመጀመሪያው ስህተት ታወሳት።

ዛሬ ደግሞ ሌላ ጉድ ተከሰተ፡፡ ራሱን ተቆጣጥሮ ሞራሏን ሊጠብቅ ተሳነውና ከእርሷ ጋር ሆኖ የሌላ ሴት ሥም በቁልምጫ እስኪጠራ ድረስ እራሱን ሳተ። ታዲያ ከእርሷ ጋር ተኝቶ ሌላ ሴት ከሚያልም ሰው ጋር ምን ሕይወት ይኖራታል? ይህ ማለት እኮ ነፍስ ከተለየው በድን ጋር እንደመኖር ነው። ራሷን ስትፈትሸው ጠብታ ፍቅር በውስጧ የለም።

ድንገት "እባክሽን አንድ ዕድል ብቻ ስጭኝ" አለ ፍቃደ።

"የምን ዕድል" አለችው በፍጥነት።

"ለአሁኑ ብቻ ይቅር በይኝ! ሁለተኛ ግን ይህን ዓይነት ስህተት እንደማልደግም በምወዳት እናቴ ሥም ቃል ልግባልሽ። እባክሽን ይቅር በይኝ" አላት።

"ዛሬስ እናትህንም መውደድህን እጠራጠራለሁ..."

"እናትህንም መውደድህን?" በማለት አቋርጧት ጮኸ።

"አዎ! የእናቴ ምትክ ነሽ የምትለኝ ሰው ነበርክ እናትህን እንደከዳህ ልትቆጥር ይገባህ ነበር" አለችው።

ትራሱ ላይ ተደፍቶ አምርሮ አለቀሰ፡፡ ሁለቱም ለየግላቸው አለቀሱ። እያለቀሰች ልጆቿን አሰበቻቸው። እስከአሁን ለፍቅር ራሷን መስዋዕት እንዳደረገች ከዚህ በኋላ ደግሞ ለእነርሱ ስትል እንደምትኖር ለራሷ ቃል ገባች። ለመጀመሪያ ጊዜ ደካማነት ተሰማት። ልፋቷና ጥረቷ ሁሉ ከንቱ እንደሆነባት አመነች።

"አ! አምላክ ሆይ ከእንግዲህ ወዲያ ያለውን አንተ እንደፈቃድህ አድርግ፡፡ በውሳኔዬ ሁሉ አንተ ተጨመርበት ብቻዬን ስሆን ረዳቴ ስደክም አጋዤ ሁን" አለች።

ፈቃደን ዞር ብላ ተመለከተችው፡፡ ትራሱ ላይ በግንባሩ ደገፍ እንዳለ እንቅልፍ ወስዶታል። ቀስ ብላ አልጋው ላይ ወጣችና እርሷም ጋደም



አለች። ውስጧ መረጋጋት ያለው መንፈሷም ሰላምን ያገኘ መሰላት፡፡ ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሰላም እንቅልፍ ወሰዳት።

ጠዋት ዐይኖቿን ስትገልጥ ያየችው ፈቃደን ነው፤ ምንም አልተሰማትም።

"ምን አልሽኝ ታዲያ?" አላት።

"የተደመደመ ጉዳይ ነው" አለችው በተረጋጋ መንፈስ።

በቃ ከፈቃደ ጋር በዚሁ ተለያዩ፡፡ ተመልሶ ወደሥራው ከሄደ በኋላ አልመጣም፤ ዐይን ለዐይንም አልተያዩም። የሚቀዱትም የጋብቻ ውል፣ የሚያጓጓ ንብረት አልነበራቸውምና ፍቺውን በየልቦቻቸው አፀደቁት። በቃ!

ማን እንዳለው ባታስታውስም አንድ አባባል ሁል ጊዜ በአእምሮዋ ይመላለሳል "...ሕይወት ፈተና ነው ውጣ ውረድ ጣጣ..." የእውነትም ሕይወት ፈተና ነው፡፡ ፈተናውን ማለፍ ደግሞ የእያንዳንዱ ተፈታኝ ፋንታ ነው።

"እኔ ግን በአንዱ ፈተና ወድቂያለሁ። አዎ! መልካም ትዳርን የመመሥረት ፈተናውን አላለፍኩም። ትዳርን ትዳር በማድረግ ፈተና ብወድቅም ሕይወት ግን እዚያ ላይ አያበቃም ይቀጥላል። ማን ያውቃል የሕይወት ፈተና ገና ሊሆን ይችላል እናም ሌሎች በርካታ ፈተናዎችም ሊገጥሙኝ እንደሚችሉ ከወዲሁ ማሰብ ይኖርብኛል" አለች ለራሷ።

የተፈጠረውን ሁኔታ የነገረችው የመጀመሪያና የመጨረሻ ሰው ዘውዱ ነው። ዘውዱ በጣም አዘነ። ለልጆቿ ግን ሕይወት ብዙም ለውጥ አልነበረውም፡፡ የአባታቸውን ያለመኖር ጉዳይ ከወትሮው የተለየ አድርገው አልወሰዱትም። እርሷም እንዲያውቁት አልፈለገችም ወደፊት ሊያውቁት ይችላሉ፤ ምንስ የሚያስቸኩል ነገር አለ?

## ክፍል 6
## የመጨረሻው ቀን ሲመጣ

የመጨረሻው ቀን ጅማሬ እጅግ ፈጥኖ ደረሰ። አንድ ቀን ፍሬ ቢሮ ገብታ ገና ሥራ ሳትጀምር ስልክ ተደወለ፡፡ ሰዓቷን ተመለከተች፤ ለቢሮ መግቢያ ሰዓት አሥር ደቂቃዎች ይቀራሉ። ስልኩን አነሳችው፤ የሴት ድምጽ ሰማች።

"ጤና ይስጥልኝ..." አለች መነጋገሪያውን እንዳነሳች።

"መልዕክት ነበረኝ" አለች በወዲያኛው ጫፍ ያለችው ሴት።

"ከየት ነው?" ድንጋጤ ቢጤ በውስጧ አለፈ።

"ከፈቃደ"

"ፈቃደ ከእኔ ምን ጉዳይ አለው?" ድንጋጤዋ ወደንዴት ተለወጠ። ካለች በኋላ ግን በራሷ ተናደደች።

ፈቃደ የልጆቹን ደህንነት እንኳ ከጠየቀ ሁለት ዓመታት አልፈውታል። ለተወሰነ ጊዜ የገንዘብ ተቆራጭ ሲያደርግ ቆይቶ ሁሉም ነገር ሙሉ ለሙሉ ከተቋረጠ ሁለት ዓመታት አልፈዋል።

"በጣም ይፈልግሻል?" አለች ሴትዮዋ።

"ለምንድነው የሚፈልገኝ?" ፍሬ ግራ ተጋባች።

"እርሱን ስትመጭ ታውቂዋለሽ"

"የት ነው የምመጣው? ደግሞስ ለምን ራሱ አያናግረኝም?"

"ማናገር ስለማይችል ነው፤ ግን ይሞክር" ለተወሰነ ጊዜ ፀጥታ ሆነ፡፡



የፍሬ ልብ መምታት ጀመረች። በስልኩ ውስጥ ድምጽ ሰማች፡፡ የፈቃደ ድምጽ ነው ብላ ለመቀበል ግን በፍጹም አልደፈረችም። ያነጋገረቻትን ሴት ድምጽ እንደገና ሰማችው።

"ምን ሆኖ ነው?" አለቻት ሴትዮዋን።

"ታሟል ልጆቹን እንድታሳይው ግን ይፈልጋል" አለች። ምንም ሳታቅማማ አድራሻውን ብቻ ጠየቀቻትና በመጀመሪያ ግን ብቻዋን እንደምታየው ነገረቻት።

"እባክሽን አትዘግይ" አለች ሴትዮዋ።

ፍሬ የዚያኑ ዕለት አዲስ አበባ ሄደች። በተሰጣት አድራሻ መሰረት ያለምንም ችግር ፈቃደ ያለበትን ቤት አገኘችው። ዐይኖቿን ግን ማመን አቃታት፤ ፈቃደ ነው ብላ ለመቀበል ጊዜ ወሰደባት። ከአልጋው አጠገብ ትንሽ መቀመጫ ላይ ተቀምጣ ለደቂቃዎች ተመለከተችው፡፡ ከአፏ የሚወጡ ቃላት ግን አልነበሯትም። የፈቃደ ዐይኖች እንባ ማፍሰስ ጀመሩ፤ በፊት ለፊት ሊያያት አልደፈረም ጣሪያውን እየተመለከተና እንባው በጉንጮቹ እየወረደ

"ይቅርታ ልጠይቅሽ አልደፍርም፤ ግን..." ሳግ ተናነቀው፤ መናገር አልቻለም፤ ስቅስቅታው ስጋ የሌለውን ሰውነቱን ናጠው። እርሷም ልትቋቋመው አልቻለችም፡፡ በእርሱ ውስጥ ራሷን አየችው። መድፈር እንዳለባት ራሷን አሳመነች።

"ምን ሆነህ ነው?" አለችው።

"እንደምታይኝ ነው የሆንኩት ቤተሰቦቼ ግን አያውቁም" አላት። "ብዙ የምቆይ አይመስለኝም..." እንደገና እንባው አቋረጠው።

"ተመርምረሃል?" አለችው ደግሞ።

"አዎን ተመርምሬአለሁ፤ እባክሽን እንቺም..." ንግግሩን ሊጨርሰው አልቻለም። ዝምታ በመሃላቸው ሰፈነ እርሷም በሀሳቧ አጠገቡ

አልነበረችም ሀሳቧ ወደ ልጆቿ ገሰገሰ። ልጆቿን አየቻቸው። ነገን አሰበችው መረራት።

“ምን እንዳደርግ አስጠራኸኝ” አለችው ድንገት ከሀሳቧ ጉዞ ተመልሳ።

“ለልጆቹ ብዬ አስጠራሁሽ! የአንቺንማ ምን እላለሁ ከአንቺ ሳይሆን ይቅርታውን ከእግዚአብሔር እየጠየቅሁ ነው፤ ይቅር የሚለኝ ባይመስለኝም” አለ ፈቃደ። ብዙ መቆየት አልቻለችም አልነበረባትምም። ሁለንተናዋ በጥላቻ የተመረዘ መሰላት፤ እናም ከፈቃደ አጠገብ መራቅ ነበረባት። እንደምንም ብላ ከራሷ ጋር ተሚግታ ለመውጣት ስትነሳ

“እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ!” አለችው።

“ልትሄጂ ነው?” አለ ለመጀመሪያ ጊዜ በፊት ለፊት እያያት። እርሷን እያናገራት ከአልጋው ራስጌ ያለውን ደወል ተጫነው። አንዲት በእድሜ ከፍሬ ታናሽ ልትሆን የምትችል ሴት ገባች “እህቴ ናት” አለ ፈቃደ ለማስተዋወቅ።

“ፍሬሕይወት እባላለሁ” አለቻት ለትውውቅ እጇን ዘርግታ።

“አውቅሻለሁ” አለቻት እየጨበጠቻት “መጥተሽ ስላየሽው ደስ ብሎኛል፡፡ ስለአንቺ ሳያነሳ ውሎ አያውቅም የእውነትም ጥሩ ሰው ነሽ፡፡ በጣም አመሰግንሻለሁ” አለች ሴትዮዋ ከእንባዋ ጋር እየታገለች።

“አመሰግናለሁ” አለች ፍሬም እንባዋ እየመጣባት።

“ያንን የሰጠሁሽን አምጭው” አላት ደግሞ ሴትዮዋን። ዐይኖቿን እየጠራረገች ወጣች።

“አሁን የምሰጥሽ ለአንቺ ነው። ለልጆቹ የሚሆነው እዚሁ ይቀመጣል” አለ ፈቃደ በደከመ ድምጽ። እያደር ድምጹ እየቀነሰ የመጣ መሰላት።



“ለእኔ አያስፈልገኝም” አለችው ጠንከር ባለ ድምጽ።

“እባክሽን ፍርዬ በሰላም እንድሄድ እርጂኝ እባክሽ!” ድምጹ የበለጠ ቀነሰ። እሺታዋን በአንገቷ ገለጸችለት፤ ፈገግ ለማለት ሞከረ።

እህቱ የጠየቃትን ይዛ ተመልሳ መጣችና ሰጥታው ወጣች። “ትንሽ ናት፤ ቢሆንም…” አለና ፖስታውን ሰጣት ለፍሬ።

* * * *

ከፈቃደ ተለይታ ስትወጣ ሰው መሆን አስጠላት። “ለምን ተፈጠርኩ? ለምንስ ያን ሁሉ ስቃይ አልፌ ለዚህ ቀን ደረስኩ?…” ተክለኃይማኖት ቤተክርስቲያን አጠገብ መድረሷን ያወቀችው የመኪና ክላክስ ሰምታ ቀና ስትል ነው። ሳታመነታ ገባች፡፡ ተንበርክካ ስለሕይወቷና ስለልጆቿ ፀለየች እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ለፈቃደም ፀለየችለት። ምን ያህል እንደቆየች ትዝ አላላትም፤ ጸሎቷን ስትጨርስ ወጥታ በእግሯ ወደ ፒያሳ አቀናች።

ፈቃደን ከአእምሮዋ ልታወጣው አልቻለችም፡፡ ከእርሷ ሌላ ብዙ የለመደ ገላው ብዙ መዘዝ ይዞ መጣ። መቼ ራሱን እንዳወቀ ሳትጠይቀው በመቅረቷ ተናደደች። ያም ሆነ ይህ አልጋ ከያዘ ስድስት ወራት ማለፋቸውን እህቱ ነግራታለች። መመርመር እንዳለባት ወሰነች፡፡ “ተመርምሬ ቫይረሱ በደሜ ውስጥ መኖሩን ባውቅ ምን አደርጋለሁ? ለመሆኑ ማን ነው ሊንከባከበኝ የሚችለው? እናት የለኝ እህት የለኝ…” ሐዘን መንፈሷን ሰበረው።

እየለፈለፈ እርቃኑን የሚሮጥ እብድ አይታ ነው ወደገሀዱ ዓለም የመለሳት። አካባቢዋን ቃኘት አደረገችው፤ ከእብዱ ልትደበቅበት የምትችልበት ቦታ በመፈለግ። “ግን ለምንድነው ወደፒያሳ የምሄደው?” ራሷን ጠየቀች። መሄድ ያለባት ወደአውቶቡስ ተራ ነው፡፡ ወደመጣችበት ተመለሰችና ወደ ሲኒማ ራስ በሚወስደው መንገድ ታጠፈች፡፡ ዞር ብላ እንኳን ለማየት ስለፈራች በፍጥነት ተራመደችና ያገኘችው ታክሲ ውስጥ ገብታ ወደአውቶቡስ ተራ ሄደች።

አውቶቡስ ተራ ስትገባ የአዋሳ መኪና አላገኘችም፡፡ የሻሸመኔ መኪና ከፊት ለፊት ይጣራል። ሳታቅማማ ገባችና ባገኘችው ወንበር ላይ ተቀመጠች። ውሀ ጥም ድብን አደረጋት፡፡ ከንፈሮቿ መድረቃቸው ተሰማት፡፡ የሰውነቷም ትኩሳት የጨመረ መሰላት ፈራች! "ሊያመኝ ይሆን እንዴ?" ራሷን ጠየቀች። "አምላኬ ሆይ እባክህን ጽናትን ስጠኝ!" አለች ደግሞ ወደአውቶቡሱ ጣሪያ አንጋጣ።

ሀሳቧን መሰብሰብ አልቻለችም ድንገት ጋዜጣ ሻጭና ለስላሳ የያዘ ልጅ ተከታትለው መኪናው ውስጥ ገቡ። ለጥማቷ ለስላሳ ለተበተነ ሀሳቧ ማሰባሰቢያ ይሆናት ዘንድ ደግሞ ጋዜጣ ገዛች። በመጀመሪያ ለስላሳውን በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አደረገችውና ጠርሙሱን መለሰችለት። የጋዜጦቹን ዋና ዋና ርዕሶች እያየች ሳለች አንድ ሰው አጠገቧ ተቀመጠ። አንዱን ጋዜጣ አስቀርታ ሌሎቹን መመለስ ነበረባት፡፡ የአንዱን ዋጋ ከፍላ ሌሎቹን ስትመልስ
"እኔም ማንበብ ስለምፈልግ ላዋጣ!" አላት ሰውዬው። ቀና ብላ አየችውና "ግድየለም ሳታዋጣ ታነበዋለህ" አለችው።

ለጥቂት ደቂቃዎች ጋዜጣውን ተመለከከተችና ድንገት አጣጥፋ አስቀመጠችው፡፡ አፍታም ሳይወስድባት በሀሳብ ጭልጥ ብላ ተጓዘች። ሰውዬው ምናልባትም ገርሟው ሊሆን ይችላል።

"ለዚሁ ነው እንዴ የገዛሽው?" አላት

"ውይ ይቅርታ" አለችና ጋዜጣውን ሰጥታው ተመልሳ ወደሀሳቧ ሄደች። ለተወሰኑ ደቂቃዎች ሲያነብ ቆየና ደግሞ
"ምነው ሀሳብ የያዘሽ ትመስያለሽ?" አላት በቀስታ። ፈቃደ ችግር ለገጠማት ሴት የሰጠው መፍትሄ ትዝ አላትና ተናደደች ሰውዬውን ጠላችው። ምንም አልመለሰችለትም ፊቷን ወደመስኮቱ አዙራ ዝም አለች።

"ችግርን መናገር የመፍትሔውን ግማሽ እንደማግኘት መሆኑን አታውቂም?" አላት ደገመና።

በብሶት የታጨቀውን ሆዷን ከፍታ ያሳየችው እስኪመስላት ድረስ ተናዘዘችለት ከአንድ ነገር በስተቀር። በወሬዋ መሀል ደግሞ



"ለአንዲት ሆድ ለባሳት ሴት ሊቀርብ የሚገባው መፍትሄ ግን የፍቅር ጥያቄ መሆን የለበትም" አለች። ድንጋጤውን ከገጽታው ላይ አነበበች፤ ግራም የተጋባ፤ ጤናም የሌላት አድርጎ የገመታት መሰላት። ይቅርታ ጠየቀችው፤ እያወራችለትም ራሷን መቆጣጠር እያቃታት አነባች። ሕይወቷ...ልጆቿ...ቤተሰቦቿ...ማን የማይደቀንባት አለ፤ ሁሉም በዐይነ ህሊናዋ ፊት አለፉ። ልቧን መሪር ሀዘን አጎሳቆለው።

ሊያጽናናት ሞከረ፡፡ ከቆይታ በኋላ እንደምንም ራሷን ተቆጣጥራ ወደ እርሱ ዞር አለች፤ በጣም ማዘኑን ከገጽታው ላይ ብትመለከትም ፈገግ ለማለት ሞከረ።

"አይዞሽ እንጂ እያንዳንዱ ነገር ማለፉን እያወቅሽ? ሁሉም ያልፋል! አንቺ ደግሞ ጠንካራ መሆንሽን መገመት አልተቸገርኩም፤ ሕይወትም ለብዙዎቻችን እንዲሁ ናት። በፈጠረሽ ለሚያልፍ ነገር ራስሽን አትጉጂ..." ሲላት አቁመው የነበሩ የእንባ ዘለላዎች ተከታትለው ወረዱባትና ፊቷን እንደገና ወደውጭው አዞረች።

"እባክሽን እኔንም ሆድ አታስብሽኝ" አለ ሰውዬው ትክሻዋን ነካ አድርጎ። በእሺታ አንገቷን ነቀነቀችለት።

ውጭው መምሸት ጀምሯል እነርሱም ሻሸመኔ ሊደርሱ ጥቂት ቀርቷቸዋል። "አዋሳ ገብቼ ማደር እችል ይሆን?" አለችና ሰውየውን ጠየቀችው። "በፍጹም ልጆቼን ትቼ ማደር አልፈልግም" ለጊዜውም ቢሆን" አለች ደግሞ መልሱን ሳትጠብቅ።

"ለምንድነው እንዲህ የምታከብጂው? ለምንድነው ራስሽን የምትጎጂው?" አላት ሰውዬው።

"መሆኑ ላይቀር ከወዲሁ ልቀበለው ብዬ እያሰብኩ እኮ ነው..." አለችው ሳታስበው።

"ምኑ ነው መሆኑ የማይቀረው?" አለና ጠየቃት ግራ ተጋብቶ።

“ኤች.አይ.ቪ. መመርመር እፈልጋለሁ” አለችው ደግሞ። መሆኑ የማይቀረው ምን እንደሆነ ፍንጭ መስጠቷ ያስደሰተው ይመስላል።

“ታዲያ ምን ችግር አለው እኔ አግዝሻለሁ” አላት ምንም ባለመደነቅ።

“ለምን አልገረመህም?” አለችው ከሁኔታው ምንም ለውጥ ስላላየች።

“ለምን ይገርመኛል፤ ከነገርሽኝ ታሪክ ይህንን መገመት እኮ በጣም ቀላል ነው፡፡ እንዴት አድርጌ እንደምጀምርልሽ እያሰብኩ ስለነበረ ነው እንጂ ማንሳቱ የማይቀር ነበር”

“ሀኪም ነህ እንዴ?” ብላ ጠየቀችው።

“ሀኪም እንኳን አይደለሁም ግን በኤች.አይ.ቪ. ዙሪያ መሥራት ከጀመርኩ ዓመታት ተቆጠሩ” አላት። ሲለያዩ ስሙንና መሥሪያ ቤቱን ነገራት። ዘሪሁን ይባላል።

በማግስቱ ጠዋት በቀጠሯቸው መሠረት ሄደች፤ ዘሪሁንን አገኘችው። ሊደረግላት የሚገባውን ሁሉ አመቻቸላት። ውጤቷ እስከሚነገራት አልተለየትም፤ ምንም ይሁን ምን የሚመጣውን ውጤት እንድትቀበል ሲመክራት ቆየ። በመጨረሻ የተጠበቀው ውጤት መጣ፤ ሊሆን እንደሚችል ብትገምትም እርግጠኛው ውጤት ሲመጣ ግን አቅም አጣች፡፡ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደሟ ውስጥ አለ ብላ ለመቀበል ተቸገረች።

* * * *

ታረቀኝና የምወድሽ ዛሬ በጠዋት ተነስተዋል፤ እንደወትሯቸው እሁድን እስከረፋዱ ድረስ መኝታ ቤታቸው ውስጥ ላለመቆየት የወሰኑት ትናንት ነበር። ቅዳሜ የቢሮው መደበኛ የሥራ ቀን ባይሆንም ታረቀኝ ግን ቅዳሜ ሥራ ሳይገባ ውሎ አያውቅም። ይህን ልምድ እንዲያዳብር ያደረጉት የበፊት አለቃው ነበሩ።

“ቅዳሜ የሳምንቱን ሥራህን በነጻነት የምትገመግምበት ዕለት ነው። የቢሮህን በር የሚያንኳኳ ሰው በሌለበት፤ ስልኩ አሁንም አሁንም በማይጮህበት፤የስብሰባ ሰዓት ደረሰ ብለህ በማትዋከብበት ቀን አእምሮህ በእርጋታ ብዙ ተግባራትን ሊያከናውን ይችላል። ያለፈውን ሳምንት አፈጻጸም ተመልክተህ ለሚቀጥለው ሳምንት የተሻለ ሥራ ለመሥራት ታቅዳለህ። ስለዚህ ቅዳሜ ከሰዓት በፊትን ቢሮህ ገባህ ማለት ቀሪ የእረፍት ጊዜህን ድንገት ስንቅር እያለ ከሚያስቸግርህ የሥራ ጉዳይ በመከላከል ሰላማዊ ጊዜ ላማግኘት ይረዳሃል፤ ሰኞ ሥራ ስትጀምር ከመዋከብ ያድንሃል” ይሉት ነበር።

ታዲያ ታረቀኝ ይህንን የእርሳቸውን ልምድ ተጋርቶ ሁልጊዜም ቅዳሜ ጠዋት ቢሮው ይገባል። ቅዳሜ ከሰዓት በኋላና እሁድ የቤተሰብና የማህበራዊ ጉዳዮች ጊዜያት መሆናቸውን የታረቀኝና የምወድሽ ያልተጻፈው የቤተሰብ ሕግ ይደነግጋል። የምወድሽ በተቻለ አቅም ሁሉ እነዚህ ጊዜያት የልጆቻቸው እንዲሆኑ ትፈልጋለች። ታረቀኝም ቢሆን አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመው በቀር ለልጆቹ የተመደበውን ሰዓት ለሌላ ጉዳይ ላለማዋል ጥረት ያደርጋል።

የትናንቱ ቅዳሜ ግን የተረጋጋ ስሜት እንዲኖረው አላደረገውም። ወደቤት ሲመለስ ድፍርስ ካለ መንፈስ ጋር በመምጣቱ የምወድሽ ያመመው መስሏት ደነገጠች።

“ምን ሆንክ?” አለችው ገና ሲገባ። እንደገባ ሶፋው ላይ ዘፍ አለ የተለመደውን ሰላምታውን እንኳ ሳያደርስ።

“ተይኝ የምወድሽ! ዓለምን በጣም ጠላኋት” አላት መረበሹ እየባሰበት።

“እንዴ ምን ተፈጥሮ ነው እንዲህ የመረረ ነገር የምታወራው?” የእርሱ ጭንቀት የተጋባባት ይመስል እርሷም ተጨነቀች።

“ለዘውዱ ደውየለት ነበር…”

“እና! ዘውዱ ምን ሆነ?” በጥያቄ አቋረጠችው።

“ዘውዱ እንኳ ምንም አልሆነም…”

"በናትህ ታረቀኝ አታስጨንቀኝ" ትእግስቷ አለቀባት።

"የፍሬሕይወት ባለቤት መታመሙን ነገረኝ"

"ታዲያ ይሄ ነው እንዲህ የረበሸህ፤ መታመም አዲስ ነው እንዴ? ደግሞስ ተሩተዋል አላልከኝም?" ጥያቄዎቿን ደረደረችለት።

"እንዳልሽው ምንም አዲስ ነገር የለም። ግን ህመሙ ለእርሷም እንደሚደርስና የልጆቿንም ነገር ሳስበው ነው እረፍት የነሳኝ" አለ ታረቀኝ ማዶ ማዶ እየተመለከተ።

የምወድሽ የፊቃደ ህመም ኤች.አይ.ቪ. መሆኑን ለመረዳት እንደገና መጠየቅ አላስፈለጋትም። በዝምታ ተዋጠች። ፍሬሕይወትንና ፊቃደን በአካል አይታቸው ባታውቅም በጣም የምታውቀቸው ይመስሏታል። በተለይም ፍሬሕይወት ታረቀኝ አንስቶ የማይጠግባት መሆኗ ልዩ ሥፍራ እንድትሰጣት አድርጓታል። ታረቀኝ ስለፍሬሕይወት ዘውዱ የሚነግረውን እያንዳንዱን ነገር ይነግራታል። የምወድሽ ነገር ታዲያ ሁሌም ይገርመዋል ታረቀኝን።

"ታውቂያለሽ የምወድሽ" አላት አንድ ቀን ታረቀኝ።

"ምኑን?" አለችው።

"በጣም እድለኛ ሰው ነኝ ብዬ የማምን መሆኔን"

"ለምን?" አለችው።

"ሀሳቤንና ስሜቴን በቀላሉ የምትረዳልኝ ሚስት በማግኘቴ!" አለና እቅፍ አድርጎ ሳማት።

"አንተ ደግሞ ጉረኛ ነህ! አሁን ይሄ ይህን ያህል ዕድለኛ መሆንን ይጠይቃል?" አለችው ፈገግ በላ።

"የእውነቱን ልንገርሽ ለኔ ትልቅ ስጋት ነበር፤ ማግባት የማልችል እስኪመስለኝ ድረስ ነበር የምጨነቀው..." አቋረጠችው



"አንተ ዛሬ ምን ሆነሃል?" አለች በመገረም።

"ዩኒቨርሲቲ እያለሁ ከነበረችኝ ጓደኛ ጋር የተለያየነው ሳትረዳኝ በመቅረቷ ነበር፤ እናም በጣም አሳስቦኝ ነበር፤ አንቺን እስካገኘሁበት ዕለት ድረስ" አላት አሁንም እያቀፋት።

"እስኪ ንገሪኝ ስንቶቹ ሚስቶች ናቸው ስለሌላ ሴት መልካምነት ሲተረክላቸው የመስማት ትዕግስት ያላቸው፤ ስንቶቹስ ናቸው ይህን እየሰሙ እምነታቸው እንደጸና መቆየት የሚችሉ? አንቺ ግን በነጻነት ስለፍሬሕይወት እንዳወራ፤ ስለጥሩ ሰውነቷ እንድመሰክር፤ ዛሬም እንደምጨነቅላት እንድነግርሽ ነጻነት ሰጠሽኝ። ወደ ጥርጣሬ ከመግባት ይልቅ የማታውቂያትን ፍሬሕይወትን እኔን ሆነሽ ማየት ጀመርሽ። ታዲያ ከዚህ በላይ መታደል ምን ይገኛል?" አላት ደግሞ የውስጡን ስሜት በሚገልጽ አድናቆት።

"እኔም ዕድለኛ ነኝ! ነገርህ ሁሉ እንድትታመን የሚያደርግህ በመሆኑ ነው ያመንኩህ። ፍቅርህ የሚያረካኝን ያህል ግልጽነትህ ይደንቀኛል። የሰጠሁህን ነጻነት በአግባቡ መረዳትህ ደግሞ ትልቁ አቅምህ ነው። ምናልባትም ሌላ ሰው ቢሆን ይህን ነጻነት አለመጋፋቱን ከጅልነት ሊቆጥረውም ይችል ይሆናል። ለማንኛውም የጥሩ ሰው ምሳሌዬ መሆንህን ብታውቅ እንዲህ አትልም ነበር። ስናቻችለው ታዲያ ሁለታችንም እድለኞች ነን" አለችውና እቅፍ አድርጋ አጸፋውን መለሰችለት። ይህን በመነጋገራቸው አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ያላቸው እምነት እየጠነከረ ፍቅራቸው እየሰመረ ሄደ።

"እንዲህ እናድርግ?" አለችው ከሀሳቧ መለስ ስትል።

"እንዴት?" የታረቀኝ ጥያቄ ነበር።

"የልጃችንን ልደት ነገ በጠዋት እቤታችን እናክብር፤ የፍሬን ባለቤት ለመጠየቅ ስንል የነገ ሽርሽራችንን እንሰርዘው፤ ዘውዱ አዲስ አበባ ከሆነም እናግኘውና ለፍሬሕይወት መደረግ ስለሚገባቸው ነገሮች እንነጋገር" አለችው።

“ለዚህ እኮ ነው የማደንቅሽ! ታዲያ ከኔ በላይ የታደለ ይኖራል? እንዴት አድርጌ ላመስግንሽ?” አላት ልባዊ በሆነ አነጋገር።

“እንድታመሰግነኝ አያስፈልግም፤ ለነገርከኝ ፍሬሕይወት ማዘን የማይችል ልቦና ሊኖረው የሚገባ ሰው መኖር ያለበት አይመስለኝም። በቃ! ይልቅስ አሁን ትካዜ አያስፈልግም፤ ተነስና ልጆቻንን ለማስደሰት የልደቱን ዝግጅት ከወዲሁ እንጀምረው” አለችው እየተነሳች።

“እስኪ አሁን ፊቴን ተመልከችው?” አላት ያዝ አድርግ።

“ምኑን?” አለችው።

“ስገባ የነበረኝን ገጽታና አሁን ያለሁበትን ስሜት! የእውነት መድሀኒቴ እኮ ነሽ!” አላትና እርሱም ከተቀመጠበት ተነሳ። “በመጀመሪያ ለዘውዱ ደውዬ ሀሳባችንን ልንገረው?” አላት ደግሞ ለዘውዱ ስልክ ለመደወል ስልኩን እየነካካ።

* * * *

ፍሬሕይወት አንድ ጠዋት ዘውዱን እንደምትፈልገው ነገረችው። “እቤት እመጣለሁ” አላት። ከሥራ መልስ እቤት ሲመጣና ልጆቹን ሲስማቸው የሆነ ስሜት አነበበችበት፤ የሚያውቀው ነገር ይኖረዋል ብላ ተጠራጠረች።

“ስለፈቃደ የሰማኸው ነገር አለህ እንዴ?” አለችው ልጆቹ ወደ መኝታ ቤት ሲገቡ።

“አዎን ፍርዬ! ስልክሽን የሰጧቸው እኔ ነኝ። ሂጂም ጠይቂዋለሁ” አላት። ምን እንደምትቀጥል ግራ ገባትና ዝም አለች።

“መቼ ልትሄጂ አሰብሽ?” አላት



“ሰሞኑን እሄዳለሁ። እኔም ተመርምሬ ራሴን አውቄአለሁ” አለችው። በድንጋጤ አፍጥጦ ተመለከታት። ምን እንደሚላት ግራ እንደገባው ተረድታለች። “ቫይረሱ በደሜ ውስጥ አለ” አለችና አረጋገጠችለት።

“ምናልባት ከጥቂቶቹ አንዷ ልትሆኚ ብትችይስ? የሚል ተስፋ ውስጤ ስለገባ እንጂ እንደሚሆንማ...” ዘውዱ አንጠልጥሎ ተወው።

“ለልጆቹ ያሰበውን ነገረሽ?” አለ ደግሞ ጥቂት ቆየት ብሎ።

“ያስቀመጠላቸው ገንዘብ እንዳለ ነግሮኛል” አለችው።

“ልጆቹን ዘመዶቹ ወደውጭ እንዲወስዷቸው አመቻችቷል” አላት ዘውዱ። የተሰማት የተቀላቀለ ስሜት ነው፡፡ ሀዘንና ደስታ! እንባዋን መግታት እስኪያቅታት ድረስ ፈሰሰ፡፡ ፈሶ የማያልቀው እንባዋ ብቻ ነው መሣሪያዋ።

በሚቀጥለው ቀን ልጆቿን ወደአባታቸው ወሰደቻቸው፤ ሲያዩት ምን እንደሚሰማቸው ስታስብ ልቧ እንደተጨነቀች ደረሱ። ልጆቹ በቀላሉ ሊያውቁት አልቻሉም፡፡ በፍጹም ሊጠጉት ፈቃደኛ አልሆኑም። ፈቃደ ከአንጀቱ አዘነ፤ ያዘነው ግን በራሱ እንጂ በልጆቹ አልነበረም። ከቤተሰቡ ጋር የመቻቸውን ነገራት።

ከዚያ በኋላ ለአንድ ወር ብቻ ነው የቆየው ማረፉን ሰማች። ቀብር ግን እንደማትሄድ ወስና ስለነበረ አልሄደችም። ዘውዱ ውሳኔዋን ስትነግረው አልተከራከራትም። ቤተሰቦቹም አልጠበቋትም። እርሷና ልጆቿ ቤታቸው ሆነው ተላቀሱ፡፡ ዛሬን ሳይሆን ትናንትን እያሰበች፣ ያንን እስከአንገቱ ድረስ ጃኬቱን ቆልፎ ያየችውን ኮስታራውን ፈቃደን እያስታወሰች፣ ፍቅሩን ሲገልጽላት ከአንደበቱ ማር ጠብ ይል ይመስላት የነበረውን ፈቃደን በዐይንህሊናዋ እያየች አለቀሰችለት፣ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለራሷም አለቀሰች፤ ሳያስቡትና ሳይገምቱት ወላጅ ለሚያጡት ልጆቿም አዘነች።

* * * *

ከፈቃደ ቀብር በኋላ ዘውዱ፣ ታረቀኝና የምወድሽ ቡና እየጠጡ ለመነጋገር ወደአንድ ቦታ ጎራ አሉ። የሚፈልጉትን ካዘዙ በኋላ

በመሃላቸው የማይጣስ የሚመስል ዝምታ ሰፈነ። ሁሉም ግን የሚያሰላስሉት ስለፈቃደ፣ ስለፍርዬና ስለልጆቿ ነበር።

“ፈቃደን ጠላሽው?” አለ ዘውዱ ድንገት ዝምታውን ሰብሮ። የምወድሽ ድንግጥ ብላ ቀና አለችና በትኩረት ተመለከተችው ዘውዱን።

“እኔ እንጃ!” አለችው ስሜቷን ማወቅ እየሞከረች።

“አትጥይው!” አላት ጠንከር ብሎ “ሁላችንም የየራሳችን ድክመት አለን፤ ድክመቶቻችን እንደየስብእናችን ይለያያሉ። አንዳንዶቻችን የሚደርስብንን ከፍተኛ ፈተና የመጋፈጥ ጥንካሬ ሲኖረን፤ እራሳችንን የማሸነፍ አቅማችን ደካማ ይሆናል። ፈቃደን ልገልጸው የምችለው በዚህ ነው፤ በትግሉ ወቅት ለብዙዎቻችን የከበዱንን ፈተናዎች በልበሙሉነት የተጋፈጠ፤ የዓላማ ጽናቱ ማንንም ያስደነቀ… ብቻ በብዙ መመዘኛ ጠንካራ የሚባል ሰው ነበረ። ነገር ግን ራሱን ማሸነፍ አልቻለም፤ ስሜቱን መቆጣጠር አለያም ተጠንቅቆ የራሱንና የቤተሰቡን ሕይወት አልጠበቀም። ስለዚህ ይህንን እንደማንኛውም ድክመት መውሰድ እንጂ የተለየ ተዓምር አድርጎ መውሰድ ስህተት ነው። አንቺን የጠየቅሁበት ምክንያት ደግሞ “ወንዶች!” የሚል የመፈረጅ ነገር ስላለ በዚያ መልኩ እንዳትወስጅው ነው” አለ ዘውዱ።

“እንግዲህ ምን ማለት ይቻላል? እንዲህ እንደፍሬሕይወት ደግሞ ሊሆን የማይገባውን ጉዳት የመሸከም እጣም ያጋጥማል። ፍሬሕይወትና ፈቃደ የማይመለሱበትን መንገድ ተጉዘውታል፤ ወቀሳውም እርምት አይሆንም። ለፍሬሕይወትና ለልጆቻቸው ምን ማድረግ እንደሚቻል መነጋገሩ ነው የሚሻለው” አለ ታረቀኝ እንደሁልጊዜው እንባው በዐይኖቹ እየሞላ።

“እውነትህን ነው!” አለች የምወድሽ ጆርባውን አሸት አሸት እያደረገችና በስስት እየተመለከተችው።

“ዘውዱ! ይህ ሁሉ የሆነው፤ ለፍሬሕይወት ልናደርግ የሚገባንን ለማድረግ የቻልነው አንተ ድልድይ ስለሆንከን ነውና በጣም ነው የምናመሰግንህ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ሁሉም ነገር ካበቃ በኋላ ብሰማ



ሕይወቴን ሙሉ በጸጸት እየተለበለብኩ እንደምኖር ሳስበው ላደረግከው ሁሉ የተሰማኝን ስሜት በምን ቋንቋ እንደምገልጽልህ ይጨንቀኛል” አለ ታረቀኝ ሊሆን ስለሚገባው ነገር ተነጋግረው ሲያበቁ።

“አመሰግናለሁ ታረቀኝ፤ በዕድሜ ታናሾቼ ብትሆኑም ከናንተ ብዙ ተምሬአለሁ፤ ትዳሬን የማከብር ሰው ብሆንም ከእናንተ አንጻር ሳየው ብዙ የሚጎድሉ ነገሮች እንዳሉ አስተምራችሁኛልና እኔም አመሰግናለሁ” አላቸው ዘውዱ።

* * * *

ፍሬሕይወት አባታቸው በሞተ ሰሞን ቀስ ብላ በኤች.አይ.ቪ. መሞቱን ለልጆቿ ነገረቻቸው። ስትነግራቸው የተሰማቸውን ስሜት መግለጽ በጣም አዳጋች ነበር። ለመቀበል በጣም ተቸግረዋል፤ ሆኖም የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቃቸው ግድ ነበርና ጠየቋት።

“እማ አንችስ ተመረመርሽ እንዴ?” አለች ሩታ ስሜቷን ለመቆጣጠር የምታደርገው ጥረት እየታየባት፤ ማቲ ጥያቄውንም ሆነ መልሱን መስማት እንደከበደው ያስታውቃል።

“አዎን ተመርምሬአለሁ፡፡ በመጀመሪያው ምርመራ ቫይረሱ በደሜ ውስጥ እንዳለ ተነግሮኛል…” ስሜታቸውን መቋቋም አቃታቸውና ሁለቱም ትተዋት ወደ መኝታቤታቸው ገቡ። እንዲረጋጉ ጥቂት ጊዜ ሰጠቻቸውና ቆየት ብላ እርሷም ገባች። ገርበብ ባለው የመኝታ ቤት በር ወደውስጥ ተመለከተች፤ ያየችው ሁኔታ የተቀላቀለ ስሜት ፈጠረባት ደስታና ሀዘን። ሩታ ማቲን ደረቷ ላይ ደገፍ አድርጋ ራሱን ታሻሽዋለች፤ እንባዋ ግን ይፈሳል። ሩታ ማቲን ለማጽናናት ያደረገችው ነገር ለፍሬ አስደሰታት ኃላፊነቷ ደግሞ አሳዘናት።

“ሩታ” ብላ ተጣራች በሩን ሳትከፍተው ወደሳሎን እየተመለሰች።

“አቤት እማ” አለች ወዲያውኑ መጥታ። ሩታ እርሷንም ለማጽናናት እየሞከረች መሆኑ ገባት።

“ማቲንም ጥሪው” አለቻት። ተያይዘው መጡ። መኖር እንደሚቻል ልትነግራቸው ሞከረች። ምሳሌዎችን ሰጠቻቸው፤ እርሷም ረጅም ዕድሜ ለመኖር እንደምትችል አረጋገጠችላቸው።

ከዚያ በኋላ አብረው በቆዩባቸው ጊዜያት ሁሉ ከኤች.አይ.ቪ ራሳቸውን እንዲጠብቁ አበክራ ነግራቸዋለች። ይህን በማድረጓ አንድ ትልቅ ኃላፊነትን የተወጣች አድርጋ ቆጠረችው።

ከሦስት ወራት በኋላ እንደገና ተመረመረችና ቫይረሱ በደሟ ውስጥ መኖሩን አረጋገጠች። መድሀኒት መፈብረኩን ብትሰማም በጣም ውድ መሆኑንም ታውቃለች፡፡ እኛ አገር ጥቂት ሰዎች ብቻ ተጠቃሚዎች መሆናቸውንም ሰምታለች፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ተስፋ የሚሰጥ ነገር አላገኘችም፡፡ ዛሬ ባይሆንም የዛሬ ዓመት ከፈጠነም በወራት ውስጥ ፈቃደን ልትከተለው ትችል ይሆናል። እናም ልጆቿ ወደዘመዶቻቸው በመሄዳቸው አመነችበት። ከልጆቿ መለየቷን ስታስበው ወደሞቷ እየተጣደፈች መሆኗ ይሰማታል፤ ግን ማድረግ አለባት፡፡ ልጆቿ ወደተሻለ ሕይወት መሄዳቸውን ማረጋገጥ አለባት፡፡ ተጎሳቁላ ከማየታቸው በፊት በጤንነቷ እያለች እንዲሄዱ መፍቀድ አለባት።

ወንድሟን ሮቤልን በየሰዓቱ ታስበዋለች፤ ከተለያዩ ቆይተዋል። ማናቸውም ስለማናቸው አያውቁም። ኑኑንም አሰበቻት ለወንድሟ እናቱ እንደሆነችው ለልጆቿም እናት ብትሆናቸው ምን ነበረበት? ፍሬና ኑኑ ግን ላለፉት ረጅም ዓመታት ዐዓይን ለዐይን መተያየት ያልቻሉ በፖለቲካ መስመር ልዩነት የተነሳ ዳግም ላይገናኙ ወስነው የተለያዩ ሰዎች ናቸው። ኑኑ መኢሶንን ከአንጀታቸው ከሚወዱና ለዓላማው ከሚታገሉ ሰዎች አንዷ ነበረች። ከፍሬ ጋር በጣም ለረጅም ጊዜ ተከራክረዋል ግን መተማመን አልቻሉም እናም ሁለቱም በየመስመራቸው ተጓዙ፤ ኑኑ መኢሶን ከመንግሥት ሲጣላ ከአገር ወጣች። ፍሬሕይወት ኑኑን ከአእምሮዋ ለማውጣት ሞከረች።

ግን ትውስታዋን ወደዛሬው ሕይወቷ መመለስ ይከብዳታል። ቤተሰቦቿንና የወላጆቿን ቤት በላይሁንን እና የበላይሁንን እናት፣ ዘመዶቻቸውን…ማን የማታስታውሰው ይገኛል? ከአንተነህ ጋር ሁልጊዜ በህልሟ አብራው ታድራለች፤ ሁል ጊዜም በተለያየ ሁኔታ ታየዋለች አንዴ ተመችቶት ሌላ ጊዜ ደግሞ ተጎሳቁሎ፤ ተመችቶት



ያየችው እለት ተደስታ ትውላለች። ታዲያ በሕልሟ ባየችው ቁጥር አንድም ቀን እንደሚወዳት ሳይነግራት ተለይቷት አያውቅም። ታረቀኝን በህልም እንኳ ማየት በጣም ይከብዳታል፤ በህልሟ ባየችው ቁጥር በእንቅልፍ ልቧ ብቻ ሳይሆን ከነቃችም በኋላ ትሸማቀቃለች።

“እንግዲህ ምን ቀረኝ? ሁሉም ነገር አበቃ። የሁለት ጦርነቶች ተሳታፊ ሆንኩ፤ በሁለቱም ተማረክሁ። ከፖለቲካው ጦርነት ምርኮ ነፃ ወጣሁ፤ የተዘጋጀሁበትና አልሜ የተነሳሁበት ጉዞ በመሆኑ እርምጃዬ ሁሉ ወኔ የተሞላበት ነበር።

ከሁለተኛው ምርኮም አላመለጥኩም። የፈቃደን ሁኔታ ሳስብ እራሴን ልከላከል የምችልበት ዕድል እንደነበረኝ ይገባኛል። ሆኖም ያን ጊዜ አንዳንዴ፤ እንዲያው አንዳንዴ በአእምሮዬ ኤች.አይ.ቪ ውልብ ቢልብኝም ጠንክሬ አላሰብኩበትም ነበር። ወትሮውንም እኮ በሚገባ የለዩትንና ያወቁትን ጠላት መከላከል ቀላል ነው፡፡ በጉያ ከሸሸጉት ጠላት ማምለጥ ግን ጠንከር ያለ ውሳኔን ይጠይቃል? ኤች.አይ.ቪ እንደዛ ነው፤ በማንነት ውስጥ የተሸሸገ ጠላት፤ እናም የራሴን ማንነት ብቻ እያሰብኩ ችላ በማለቴ ከምርኮው ማምለጥ አልቻልኩም። እኔም ከዚህ ወዲያ ያለው ሕይወት አያጓጓኝም። ከእንግዲህ የምፈልገው አንድና አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ልጆቼ ሕይወታቸውን ወደሚቀጥሉበት ምዕራፍ መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ” ትላለች ፍርዬ ለብቻዋ።

ሰሞኑን ለልጆቿ ስለውጭ ሀገር ሕይወት መልካምነት ማውራት ጀምራለች። ስታወራላቸው አፋቸውን ከፍተው ያዳምጧታል፤ ከዛ ደግሞ እዚያ አገር የሚኖሩ ብዙ ዘመዶች እንዳሉዋቸው ትነግራቸዋለች። ከአባታቸው ዘመዶች ጋር በመገናኘታቸው እንዴት እንደተደሰተች ስትነግራቸው የነበራቸው ስሜት በጣም ገርሚት ነበር። የዘመድ ዐይን ናፍቆአቸው በማደጋቸው አክስትና አጎት የሚሉት ቃላት ራሳቸው ብርቅ ሲሆኑባቸው ማየት በጣም ካሳዘኗት ነገሮች አንዱ ነው።

አንድ ቀን ታዲያ እንደተለመደው ሲጫወቱ “አሁን የአባታችሁ እህት አሜሪካ ብትወስዳችሁስ?” አለቻቸው ድንገት። በመጀመሪያ ሁለቱም በጣም ተደሰቱ፤ ጥቂት ቆይተው ደግሞ እንደማይፈልጉ ነገሯት። እርሷም አሜሪካ መሄድ እንደምትፈልግ ነገረቻቸው፤ ስለሮቤልና

እናት ሆና ስለወሰደችው ስለአክስቷ ልጅ ስለ ኑሮ አጫወተቻቸው፤ እነርሱ ከሄዱ እርሷም ልትሄድ እንደምትችል አስረዳቻቸው። ልጆቿ ወደውጭ የመሄድን ፍላጎት በውስጣቸው እንዲፈጥሩ በማድረጓም ደስ አላት።

ያ የአውቶቡስ ላይ ጓደኛዋ ዘሪሁን በየጊዜው እየመጣ ይጠይቃታል፣ ያበረታታታል፣ ያደንቃታል እናም የነገዋን ፀሐይ የማየት ጉጉት እንዲያድርባት ያደርጋል። እርሷም ልጆቿ በሰላም እስኪሄዱ ድረስ ራሷን በምትችለው ሁሉ ለመንከባከብ ጥረት ታደርጋለች፡፡ እግዚአብሔርም እያገዛት ከቀን ወደቀን ያሽጋግራታል።

የመሄጃቸው ጊዜ ቁርጡ ታወቀ፡፡ ለልጆቹ መንገር ከበዳት፡፡ የከበዳት ግን ለራሷ ነው፤ ባብታ እንዳታባባቸው ፈርታ። ዘሪሁንና ዘውዱ አብረዋት ነበሩ። ዘውዱ ከፈቃደ ቤተሰቦች ጋር ቤተኛ መሆኑን ስለሚያውቁ ለልጆቹ መንገር እንደሚቀለው ተነጋገሩ።

“ዛሬ ከአዲስ አበባ ጥሩ መልእክት ይዤ መጥቻለሁ” አለ ዘውዱ አንድ ማታ ወደ ቤታቸው ሲመጣ።

“የምን መልእክት?” አለች ፍርዬ።

“የሩታና የማተ: አክስት መጥታለች፡፡ ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ ይዛቸው እንደምትሄድ ነግራኛለች” አለ ዘውዱ።

“እንዴት ዕድለኞች ናቸው? እንኳን ደስ ያላችሁ” አለ ዘሪሁን በመቀጠል።

ፍርዬ የምትናገረው ስለጠፋባት ተነስታ ወደውስጥ ገባች ልጆቿም ተከትለዋት ገቡ።

“እማ እውነት ነው እንዴ?” አሏት በአንድነት።

“አዎ እውነት ነው እኔም ደስ ብሎኛል” አለቻቸው።

“አንቺም ትሄጃለሽ?” የሚቀጥለው ጥያቄ ነበር።



“አዎን እመጣለሁ፤ ግን ትንሽ ቆይቼ ነው የምመጣው” አለቻቸው። ደስ አላቸው እርሷም ደስታዋን ለማሳየት ጥረቷን ቀጥላለች ሊሊቱ እስኪደርስላት፤ ያለተመልካች የውስጧን ብሶት የምታወጣበት የእፎይታ ጊዜዋ ደርሶ ብቻዋን እስከምትሆን ማስመሰሏ ግድ ነው።

ለልጆቿ ያስፈልጋል ያለችውን ሁሉ አዘጋጀች፡፡ የምትችለውን ያህል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልታስደስታቸው ታጥቃ ተነስታለች። ልጆቿ በጣም ተደሰቱ፡ ጓደኞቻቸው እስኪቀኑባቸው ድረስ ፍንድቅድቅ አሉ።

የመጨረሻው መለያያ ዕለት ጊዜውን ጠብቆ መጣ። ዘውዱና ጓደኛዋ መቹም ሁሌም አብረዋት ናቸው፡፡ ጎረቤቶቿ ሐዘናቸውንና ቁጭታቸውን በውስጣቸው አምቀው ከጎኗ ናቸው። በየአቅጣጫው ድጋፋቸው አልተለያትም።

ልጆቿ ወደአዲስ አበባ መሄጃቸው ቀን እንደነገ ሲሆን “እዛ ቤት መሄድ አልፈልግም ዘውዱ ምን ይሻለኛል?” አለችው። እነፈቃደ ቤት ሄዳ የመጣው ሁሉ እንዲጠቋቆምባት አልፈለገችም። በደህናው ቀን ያልተዋወቀቻቸውን ዘመዶቹን እርሱ በሌለበት መተዋወቅ ምን ሊያደርግላት?

“እባክሽን ለመጨረሻ ጊዜ እንደምንም ሞክሪ?” አላት ዘውዱ።

“እባክህን ተረዳኝ ዘውዱ አንተ ይዘሃቸው ሂድ እኔ ቦሌ ልምጣ” አለችው።

“እሺ በቃ አንቺ ልጆቹን አሳምኛቸው” አለና አስደሰታት። ልጆቿን ማሳመን አልቸገራትም። ልጆቿ እርሷ ለምትነግራቸው ነገር ሁሉ ምክንያት እንዳላት የሚያምኑ በመሆናቸው በቀላሉ እንደምታሳምናቸው እርግጠኛ ነበረች።

“ሩታዬ! እናንተ ከዘውዱ ጋር ትሄዳላችሁ እኔ ደግሞ ነገ ቦሌ እመጣለሁ” አለቻት።

"ለምን እማ? እኛ ከአንቺ ጋር ማደር እንፈልጋለን" አለች ሩታ እንባዋ እየመጣባት።

"እዛ ቤት ከሄድኩ ፈቃደን አስበዋለሁ፤ ካሰብኩት ደግሞ እጨነቃለሁ፣ አለቅሳለሁ ያን ማድረግ ደግሞ አለፈልግም። እሺ በይኝና ወንድምሽም እሺ እንዲል አድርጊልኝ ሩታዬ" አለቻት።

"እሺ በቃ! ነገ ግን ትመጫለሽ አይደል?" አለች ወዲያውኑ ተቀብላት።

"በሚገባ እንጂ! እናንተ ሰዓታችሁን ጠብቃችሁ ቦሌ ከደረሳችሁ ቀድሜ ታገኙኛላችሁ" አለችና አረጋገጠችላት። ከዛ በኋላ ማቲን ማሳመን ቀላል ነበር።

ያን ቀን ከራሷ ጋር ታላቅ ጦርነት አደረገች፤ ዘውዱና ልጆቿ ከቤት እስኪወጡ ድረስ እንደምንም ራሷን ተቆጣጥራ በሰላም ሸኘቻቸው። እነሱን ሸኝታ ጎረቤቶቿን ሁሉ አሰናብታ ደጃፏን ዘግታ ወደመኝታ ቤቷ ስትገባ የሕይወቷን የመጨረሻ ምዕራፍ ዘጋችው። አንዲት ተግባር ብቻ ቀረቻት ኃይሏን ሁሉ አሰባስባ ቦሌ መሄድ ልጆቿን ለመጨረሻው መሰናበት በቃ ከዛ በኋላ...

ውስጧ ተንሰፈሰፈባት፡፡ ሁሉ ነገር ከአቅሟ በላይ ሆነ፡፡ ልጆቿ ሰላም አግኝተው እንዲሄዱ ከመፈለጓ ዕናት የተነሳ ካልሆነ በስተቀር ሕይወቷ ከዚያን ቀን እንዲያልፍ በፍፁም አትፈልግም ነበር። የሚፈታተናትን ክፉ መንፈስ ለማባረር ተንበረከከች፡፡ በታላቅ ተመስጦ ለልጆቿ ጸለየችላቸው። ከብዙ ፈተና በኋላ አእምሮዋ ሰላም አገኘና የተረጋጋ ሀሳብ ማሰብ ጀመረ፤ ለማን አልፀለየችም? እናቷን፣ አባቷን፣ ወንድሞቿን፣ እህቷን፣ በላይሁንንና እንትነህን፣ መስዋዕትነት የከፈሉ ጓደኞቿን፣ በኤች.አይ.ቪ. ምክንያት ለሞቱና ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ወገኖቿ ሁሉ ፀለየች። ከረጅም ጊዜ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላም አገኘችና የሰላም እንቅልፍ ተኛች።

በጠዋት ተነሳች፤ ለብሳ የምትሄደውን ልብስ ለመምረጥ ቁምሳጥኑን ከከፈተች በኋላ ነው ብዙ ምርጫ እንደሌላት ያወቀችው፤ ጠቆር ያለ



ግን ቆንጆ ልብስ አወጣች። የሚያስፈልጋትን ዝግጅት ሁሉ አድርጋ ለባብሳ ከቤቷ ወጣች፡፡ እንዳለችውም ቦሌ ቀድማቸው ደረሰች።

ልጆቿን ከሩቅ አየቻቸው በጣም አምሮባቸዋል። የማቲ ቁመት ረጅም ከመሆኑ በስተቀር ብዙ ነገሩ አረማመዱ ሳይቀር ፈቃደን ይመስላል፡፡ አይገርምም እንዲህ አስተውላው አታውቅም። ዐይኖቹ ግን የእርሷን እንደሚመስሉ ታውቃለች። ሩታ ሙሽራ መስላለች፡፡ ረጅም ጸጉሯ ትከሻዋ ላይ ተዘናፍሏል፣ ፍልቅልቅ ፈገግታዋ ከሩቅ ይስባል፣ ብዙ ሰዎች "ቁርጥ ፍርዬ ናት" ይላሉ። ዛሬ ስታያት የእውነትም ራሷን በልጅነቷ የምታይ መሰላት።

በዓይኖቻቸው እርሷን ፍለጋ ሲንከራተቱ ተመለከተችና ዛሬ ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚያዩዋት ስታስበው እንባዋን መገደብ አቃታት። አጠገቧ ከመድረሳቸው በፊት ግን እራሷን ተቆጣጠረች ጠንክራ ልታጠነክራቸው ለራሷ ቃል ገባች።

ሁለቱም እንደወፍ በረው አንገቷ ላይ ተጠመጠሙ። የምትወስዳቸው አክስታቸው ራሷን መቆጣጠር አቅቷት ጮክ ብላ አለቀሰች። የፈቃደ ትንሽ እህት፣ ወንድሞቹ፣ ሌሎች ቤተሰቦች ሁሉ ተላቀሱ። እርሷ በውስጧ ፀለየች፤ እግዚአብሔር ብርታትን እንዲሰጣት ተማፀነች፤ እርሱም ብርታትን ሰጣት።

"እማ ትመጫለሽ አይደል? እንገናኛለን አይደል?" የሁለቱም ልጆቿ ጥያቄ ነበር።

"አዎን እንገናኛለን" አለቻቸው።

በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ጥያቄ በአእምሮዋ ውስጥ መጣባት፤ "ከሞት በኋላ መገናኘት ቢኖር ምን ነበረበት?" የሚል። ልታገኛቸው የምትፈልጋቸውን ሰዎች ለአፍታ ያህል አሰበቻቸው፡፡ የታዩዋት የመጀመሪያዋ ሰው እናቷ ናቸው ከዚያ አባቷ ከዚያ ብዙዎች ሌሎች።

“ጀግና ነሽ ፍርዬ!” የሚለው የልጆቿ አክስት ሹክሹክታ ከሄደችበት በድንገት መለሳት “ልጆችሽን ከልጆቼ ላለያቸው ቃል እገባልሻለሁ” አለቻት አንገቷን አቅፋ በእንባ እየታጠበች።

“አመሰግንሻለሁ። እግዚአብሔር ውለታሽን ይክፈል” አለቻት ፍሬሕይወትም። ልጆቿ ዐዓይን ዐይኗን እንደሚያዩዋት ስታያቸው ተንቆርዝዞ የነበረ እንባዋ ከመቅጽበት ተመለሰ።

ለመጨረሻ ጊዜ ከልጆቿ መሰናበቷ ግድ ሆነ፡፡ አሁንም ጸሎቷን አላቋረጠችም  እግዚአብሔር እንዲያጽናናት መለመኗን ቀጥላለች። ሁለቱንም ልጆቿን አቀፈቻቸው ሳመቻቸው በመጨረሻም

“እንግዲህ ሂዱ ሁሌም አብሬያችሁ ነኝ። እኔን እንደምትወዱኝ አክስታችሁን ውደዷት ከዚህ በኋላ እናታችሁ ናት” አለቻቸው እንደምንም ተጣጥራ ፈገግ ለማለት እየሞከረች።

ዘውዱ አጠገቧ መሆን ፈርቶ በሩቅ እየተከታተለ እንደነበር አይታዋለች፡፡ ልጆቿ ወደውስጥ ሲገቡ ግን ምን ጊዜ አጠገቧ እንደደረሰ አላወቀችም፡፡ ምድር ሰማዩ ሲጨልምባት የደገፋት እርሱ ነው። ቤተሰቡ ወደቤት እስኪመለስ ድረስ ዞር ብለው እንዲቆዩ ጠየቀችው ተስማማላት። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሁሉም ሰው ወደየቤቱ ሄደ፤ እርሷና ዘውዱ ብቻ ቀሩ።

ልጆቿ የቦሌን ምድር ለቀው እስኪወጡ ድረስ ተቀመጡ፡፡ በውስጧ ውሀ የሚባል የቀረ እስከማይመስላት ድረስ አነባች። ከዚያ በኋላ በሕይወት ባትቆይ የነበራት ምኞት እንደገና አገረሸባት፤ ግን ወዲያውኑ ሀሳቧን ለወጠች፤

“ለልጆቹ ቀነጫጭቤ የነገርኳቸውን ታሪኬን በደንብ ጽፌ መለስ ብለው የሚያነቡት ነገር ሳላቆይላቸው መሞት የለብኝም!” አለች ለራሷ። እናም በሕይወት ለመቆየቷ ምክንያት ኖራት፤ ለልጆቿ የማንነታቸው መገለጫ የሆነውን ታሪኳን መጻፍ!

“እንሂድ?” አለችው ዘውዱን።

* * * *



ታረቀኝና የምወድሽ ዘውዱ በነገራቸው ሰዓት ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ደረሱ። በእርጋታ መጫወት የቻሉት ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው፤ ታረቀኝ በየደቂቃው ሰዓቱን እየተመለከተ፤ ጨዋታውን እያቋረጠ መቸገሩን በመመልከቷ “ለምን ዞር ዞር ብለህ አታያቸውም?” አለችው።

“እውነትሽን ነው ይሻላል” አላትና ወዲያውኑ ተነስቶ ሄደ።

የምወድሽ ታረቀኝን ከጀርባው እያየችው “የእውነቱን እኮ ነው ታረቀኝ፤ ባል ለሌላት ሴት እንዲህ ልቡ ሲሰረቅ ማየትን መቀበል ከባድ ነው” አለች ለራሷ። በፍሬሕይወት ላይ መንፈሳዊ ቅናት አደረባት። “ታድላ! ዘውዱም ሆነ ታረቀኝ ለፍሬ ያላቸው ፍቅር እንዴት ጠንካራ ነው” አለች ፍሬን በዐይነሕሊናዋ ለማየት እየሞከረች።

ደግሞ የራሷንም ተፈጥሮ አደነቀች፤ ባለቤቷ በአንድ ወቅት አፍቅሯት የነበረችን ሴት እንዲህ በንጹሕ ስሜት ማሰብ ፈታኝ ነው። እርሷም ይህ ስሜት ብዙ አስቸግሯት ነበር፤ ታረቀኝ ስለፍሬሕይወት ባወራላት ቁጥር ስሜቷ እየተቆጣባት ራሷን ለመቆጣጠር ታደርጋቸው የነበሩትን ጥረቶች አስታወሰች።  ቀስ በቀስ ፍሬሕይወትን የታረቀኝ ንጹሕ ጓደኛ አድርጋ ልትቀበል ያስቻላት የታረቀኝ ግልጽነትና ለእርሷ ያለው ፍቅር ጽናት ነው። “እንዴት የታደለ ሰው ነው ታረቀኝ” አለች ደግሞ።

ታረቀኝን ወደእርሷ ሲመጣ አየችው፤ ገጽታው ላይ የሚታየት ነገር የተመሳቀለ ይመስላል።

“አገኘኋቸው” አላት አጠገቧ ሲደርስ።

“ሁሉንም?” ብላ ጠየቀችው።

“አዎ ሁሉንም” አላት ሀዘኑ እየታዩ

“አነጋገርካት?” አለችው ደግሞ። እራሱን በማነቃነቅ ያለማነጋገሩን ገለጸላት።

"እንዴት ናት?" አለችው።

"አሳዘነችኝ፤ የወትሮው እርጋታዋ አብሯት አለ፤ የውስጥ ስሜቷን ላለማሳየት እየጣረች መሆኗ የሚገባው እንደኔ ፍሬን በሚገባ የሚያውቃት ሰው ብቻ ነው። በተለይ ልጆቿን የምታይበት መንገድ ልቤን ሰበረው፤ ሴት ልጇ ቁርጥ ፍሬ ናት" አለና ስሜቱን ሁሉ ዘረገፈላት።

"እኔ ከሩቅ አይቻት ብሄድ ደስ ይለኛል፤ አንተ ግን ቆይተህ አግኛት" አለችው። ቀና ብሎ ተመለከታት ያለችውን ያላመነ ይመስል።
"ከልቤ ነው ታረቀኝ! በዚህ ቀን ፍሬሕይወት ሰው ያስፈልጋታል፤ ራሴን በእርሷ ቦታ ለማድረግ ስሞክር በጭራሽ የምችለው ሸክም አልመስልሽ አለኝ። በዚህ ዙሪያው ገደል በሚሆንብህ ሰዓት ታዲያ ለልብህ ቅርብ የሆነ ሰው ያስፈልጋል። ለፍሬ ከአንተና ከዘውዱ የቀረበ ማን ሊኖራት ይችላል?" አለችውና ተነሳች።

"ለዚህ እኮ ነው ታዲያ እድለኛ ነኝ የምልሽ" አላት እርሱም እየተነሳ።

"በጣም አመሰግናለሁ የኔንም ዕድለኛነት አትርሳ፤ እንዲህ ሙሉ እምነትን ሊጥሉበት የሚበቃ ባል ማግኘት መታደል ነው። ና! ከሩቅ ላያቸው የምችልበት ቦታ እንሁንና አሳየኝ" አለችው እጁን ያዝ አድርጋ ጎተት እያደረገችው።

ታረቀኝ ፍሬሕይወትንና ልጆቿን ለምወድሽ አሳየት፤ ረዘም ላሉ ደቂቃዎች ዐይኖቿን ሳታረግብ ተመለከተቻቸውና ዐይኖቿን ከደን ስታደርጋቸው እንባዋ ወረደ።

"እቤት ነኝ። ጊዜ ወስዳችሁ ቆዩ" አለችው።

"ባለዕዳ እያደረግሽኝ ነው የምወድሽ!" አለና እቅፍ አድርጎ ሳማት።

የምወድሽ ከሄደች በኋላ የፍሬሕይወትን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ ሊያይ የሚችልበት ቦታ ሆኖ ሲከታተል ቆየ። በቆይታው ሁሉ ፍሬሕይወት ሲጨንቃት፤ ልጆቿ እንዳያዩባት ለማድረግ ከውስጥ ስሜቷ ጋር ግብ ግብ ስትገጥም... ጭንቀቷን ተጨነቀላት፤ ስሜቷንም



ተጋራት፤ እርሷ እንዳይወርድ የምታግደውን እንባ እርሱ ያለገደብ አፈሰሰው፤ አካባቢው ያሉ ሰዎችን ትኩረት እስኪስብ ድርስ።

ፍሬሕይወትና ዘውዱ ታክሲ ወደሚይዙበት ቀስ እያሉ ሲያዘግሙ ታረቀኝ ደረሰባቸውና ትከሻዋን ነካ አደረጋት። ቀና አለች ፍሬሕይወት፤ ድንጋጤዋ ሰውነቷን እንደመንቀጥቀጥ እስከሚያደርገው ድረስ ደነገጠች። ማልቀሱን የሚያሳብቁ ቀይ ዐይኖቹን ተመልክታ ግራሞቷን ለመግለጽ አቅቷት ስትንተፋተፍ እጆቹ ቀደሟት። ታረቀኝ አንገቷን አቅፎ ተንሰቀሰቀ፤ እንባ እርሷንስ ምን ይገዳታል? ተላቀሱ። ዘውዱ በመደነቅ ተመለከታቸው፤ ተላቅሰው የሚበቃቸው አልመሰለውም፡፡ ሊያረጋጋቸው ሞከረ፤ ከብዙ ሙከራ በኋላ በመጠኑ ተረጋጉ።
"ታረቀኝ ይባላል ጓደኛዬ ነው" አለች ከዘውዱ ጋር ልታስተዋወቀው።

ሁለቱም ተያዩና ተሳሳቁ፤ ግራ በመጋባት በየተራ አየቻቸው።

"ከዘውዱ ጋር እንተዋወቃለን፤ ስለአንቺ ሳልሰማ ይህን ሁሉ ጊዜ ልቆይ የምችል ይመስልሻል?" አላት ታረቀኝ።

"እናንተ ትንሽ ብትጫወቱስ፤ እኔ ዘመድ ጋ ደረስ ብዬ እመጣለሁ" አላቸው ዘውዱ ጊዜ ለመስጠት ፈልጎ።

"ታረቀኝ የሚቸኩልበት ከሌለው" አለች ቀበል አድርጋ።

"ብንቆይ ደስ ይለኛል" አለ ታረቀኝ።

ወደየትም መሄድ አላስፈለጋቸውም፤ ካሉት ካፌቴሪያዎች አንደኛው ጋ ተቀመጡ።

"ልጆችሽን አየኋቸው" አለ ታረቀኝ ዘውዱ እንደሄደ።

"እንዴት አወቅሃቸው?" አለችው ገርሟት።

"ልጅሽ አንቺን ትመስላለች በዚያ ላይ ከአንቺ ጋር አየኋት። ወንድ ልጅሽም አባቱንም አንቺንም ይመስላል" አላት።

"ለምን መጥተህ ነው?"

"እንቺን ለማግኘት፤ ዘውዱ ላደረገው ሁሉ ምስጋና ይግባው" አለ።

ከታረቀኝ ጋር ብዙ ተጫወቱ፤ የሆነውን ሁሉ አንድም ሳታስቀር ነገረችው። እየነገረችው ታረቀኝ በዝምታ እንባውን አወረደው፡፡ ምንም ዓይነት ጥያቄም አልጠየቃትም አስተያየትም አልሰጣትም።

በመጨረሻም "ታረቀኝ! መምጣትህ ይቅርታ እንድጠይቅህ ዕድሉን ስላመቻቸልኝ በጣም ደስ ብሎኛልና ስላደረግሁት ሁሉ እባክህን ይቅርታ አድርግልኝ" አለችው።

"ፍርዬ ያደረግሽው ሁሉ እንድቀየምሽ ሳይሆን እንዳከብርሽ፣ እንድጠላሽ ሳይሆን የበለጠ እንድወድሽ ነው ያደረገኝ። ለዚህ ማረጋገጫው የዛሬው አጋጣሚ ነው እስከመጨረሻው እንድጠብቅሽና እንዳገኝሽ ማን አስገደደኝ?"

አንዳች ነገር ቀለል አላት፤ ከዚህ በኋላ አይቆጫትም። ታረቀኝ ይቅርታ አድርጎላታል ዛሬም ለእርሷ ያለው አመለካከት መልካም ነው። ከዚህ የበለጠ ምን የሚያጽናና ነገር አለ?

"አገባህ?" አለችው ታረቀኝን ድንገት ወደእርሱ ሕይወት ተመልሳ።

"አዎን ፍርዬ አግብቻለሁ ልጆችም ወልጃለሁ" አላት በሀሳቡ ሩቅ ሄዶ። ከዛ በኋላ የመጠየቅ ሀሳብ አልነበራትም። በየሀሳባቸው ተውጠው ብዙ ቆዩ።

"ፍርዬ! እንግዲህ የሆነው ሁሉ ሆኗል፡፡ ከሮቤል ጋር መለያየታችሁንም አውቃለሁ፤ አሁን ግን ሮቤልና ልጆችሽ መገናኘት አለባቸው..."

"እንዴት መገናኘት ይችላሉ ታረቀኝ?" አለችው ሳታስጨርሰው።

"እኔ ኃላፊነቱን እወስዳለሁ፤ አድራሻቸውን ትሰጭኝና ለሮቤል እጽፍለታለሁ" አላት። በጣም ገረማት፤ ታረቀኝና ሮቢ ይጠያየቃሉ



ብላ በፍጹም አላሰበችም። ተስፋ በውስጧ አቆጠቆጠ፤ ምናልባትም ሮቤልም ይቅር ሊላት ይችላል። ከታረቀኝ ጋር አድራሻ ተለዋውጠው ተሰነባበቱ።

በተከታዩ ቀን ከዘውዱ ጋር ወደአዋሳ ተመለሱ። ጎረቤቶቿ ተዘጋጅተው ብቸኝነቷን ሊያቀሉላት ተመካከረው ጠበቋት። እንዴት መልካም ሰዎች ናቸው፡፡ በደረሰባት የሕይወት ፈተና ሁሉ ከጎኗ ሳይለዩ አበረታቷት ደገፏት። እርሷስ እንዴት እድለኛ ነች፡፡ የኔ ያለቻቸውን ስታጣ አለንሽ የሚሏት አለማጣቷ እንዴት ያለ መታደል ነው።

በእነርሱ ድጋፍ ተጠናከረችና ሥራ ገባች፡፡ ልጆቿ ደህና መግባታቸውን ሰማች አክስታቸው በየጊዜው ፎቶግራፎቻቸውን ትልክላታለች። በጣም ተደሰተች። ዘሪሁንና ዘውዱ መቼም ሁሌም አብረዋት ናቸው።

የልጆቿን አድራሻ ለታረቀኝ ላከችለት ከሮቤል ጋር እንዲያገናኛቸው። ታረቀኝም በየጊዜው ይደውልላት ጀመር፤ የእርሱ መልካም ድርጊት ግን ለእርሷ ሰላም ሊሰጣት አልቻለም፤ ልትረሳው የምትፈልገውን የትናንት ሕይወቷን እያስታወሳት ጤና ነሳት። ቢሆንም በደወለላት ቁጥር ደስ ይላታል።

ከልጆቿ ጋር እንደማይገናኙ ባሰበች መጠን ናፍቆት ይብሰባታል። የአእምሮዋ መጨነቅ ደግሞ በደሟ ውስጥ ካለው ቫይረስ ተዳምሮ ጤንነቷን ተፈታተነው። ዕድሚዋን በዓመታት ሳይሆን በወራት መለካት ጀመረች። ቢሆንም ለተወሰኑ ወራት ጥርሷን ነክሳ የተቻላትን ሁሉ አደረገች፡፡ ቀን ሥራዋን ትሠራለች ማታ ቁጭ ብላ በቁርጥራጭ ወረቀት የጻፈቻቸውን የህይወት ስንክሳሮች እያሳካች ትጽፋለች። መጻፏን እንጂ ስትጨርስ ምን እንደምታደርገው አታውቅም። የጤንነቷ ሁኔታ ደግሞ ሞት አደጋ እንደደረሰ ይነግራት ጀመር።

በጣም ሲብስባት የውስጧን ተስፋ መቁረጥ ለዘውዱ ነገረችው።

"እባክህን የስቃይ ጊዜዬ እንዲያጥርልኝ ጸልይልኝ" አለችው።

" ፍርዬ ከዘሪሁን ጋር እኮ እየተነጋገርን ነበር፡፡ መድሀኒቱ በቅርብ ጊዜ ሊጀመር እንደሚችል ተስፋ አለ። እባክሽን መንፈስሽን አጠንክሪና ታገይ" አላት ዘውዱ

"ምን ያደርግልኛል ዘውዱ? ሕይወት ከእንግዲህ ለእኔ ምኔ ነው? ልጆቼ ከመሄዳቸው በፊት ቢሆንና ልጆቼን እንዳሳድግ የሚረዳኝ ቢሆን ነበር የሚጠቅመኝ። አሁን ለኔ የሚያስፈልገኝ የመጨረሻውን የሰላም እንቅልፍ ማንቀላፋት ብቻ ነው" አለችው።

ከሥራ ከቀረች ሰንብታለች፤ ብዙውን ጊዜም የምታሳልፈው በመተኛት ነው፡፡ ህመሙም እየደር እየጠነከረ ሄዷል። የሥራ ባልደረቦቿ ከጠበቀችው በላይ ተመላልሰው ይጠይቋታል። ከሁሉም በላይ ግን ዘውዱንና ዘሪሁንን ግራ እያጋባቻቸው መሆኑ ይሰማታል፤ ግን ምን ማድረግ ትችላለች። ሰሞኑን ዘውዱ በጣም ሲጨነቅ አስተዋለችውና እርሷም ተጨነቀች።

"ምነው ዘውዱ ምን ሆነሀል?" አለችው አንድ ቀን እንደምንም ተበረታታ።

"እንዴት እንደምነግርሽ ግራ ገብቶኝ ነው ፍርዬ፤ ወደአዲስ አበባ ተቀየርኩ" አላት

"ለእኔ ብለህ ነው አይደል የምትጨነቀው?" አለችው።

"እንዴት አልጨነቅም ፍርዬ? ትቼሽ መሄድን መቼም ላደርገው አልችልም"

"እሺ ካልከኝ ወደ አንድ ገዳም አድርሰኝና ወደቤተሰቦችህ ሂድ"

"በፍጹም አላደርገውም"፤ እኛ ቤት ብትሆኚ ምናለበት?" አላት በመለመን ዓይነት

"ይሄ እንኳን የሚሆን አይደለም" አለችው ያልነበራትን ኃይል አግኝታ።



"ለምን ፍርዬ? ባለቤቴ የቱን ያህል ስለአንቺ እንደምትጨነቅ እነግርሽ የለ? አንቺ እሺ ብለሽ አብረን ብንሄድ እርሷ በደስታ ነው የምትቀበልሽ" አላት ዘውዱ። እርሷ ግን በፍጹም የምትቀበለው አልሆነም። ብዙ ተከራከሩ፤ በመጨረሻው በጣም አመረረችበት።

"ለምን ቤቴ አትወስደኝም?" አለችው

"እሺ በይኝና ለሚስጥረ ልንገራት" አላት ደግሞ ሲጨንቀው።

"እባክህን የባሰ እንድጎዳ አታድርገኝ ዘውዱ፤ ሚስጥረ በጣም የምወዳት ጓደኛዬ ነች ዛሬም እወዳታለሁ። ሁሉን ነገር ያበላሸሁት እኔ ነኝ፤ እነሚስጥረ ዛሬም ቢሰሙ "አለንልሽ" እንደሚሉኝ አልጠራጠርም፤ ግን አእምሮዬ የበለጠ ይጎዳል። እባክህን የበለጠ እንዳልጎዳ አድርግልኝ?" አለችው።

"እቤተሰቦችሽ ቤት ብቻሽን መሆንሽ ከሚያስጨንቀኝ በስተቀር ለኔ አያስቸግረኝም" አለና ተስማማላት። ዘውዱ ስልክ ደውሎ ለበላይሁን እናት ሁኔታውን እንዲነግራቸው ስልክ ቁጥር ሰጠችው።
ያን ዕለት ፍሬሕይወት እንቅልፍ አልወሰዳትም፤ በሀሳብ ስትማስን እንባዋ እየፈሰሰ ትራሷን ሲያርሰው ነው ያነጋችው። ቤተሰቦቿን ስታስብ፤ ቃለአብንና ሚሚን ስታስታውስ፤ በላይሁንን በዐይነህሊናዋ ስትመለከት... ሌሊቱ ሌሎች ሲነጋ አብሮ ነጋላት።

* * * *

"እኔ የምልህ" አለች ሄዋን በአዲስ ዓመት በዓል ዋዜማ ለመዝናናት ወጥተው ሳሉ። "እሺ አንቺ የምትይኝ" አለ አንተነህ በቀልድ መልኩ።

"እኔማ የምልህ ለምን አገር ቤት አንሄድም?" አለችው ዐዓይን ዐይኑን እያየችው።

"እባክሽን አንቺ ብቻ ሂጂ" አላት ጥቂት አሰብ አድርጎ።

"ለምን? ለምን ብቻዬን ልሂድ አንተነህ? አንተ ቤተሰቦችህን ማየት አትፍልግም እንዴ?" አለችው ቅሬታ እየተሰማት።

"አንች አይተሽልኝ ትመጫለሽ" አላት ባጭሩ።

"አልስማማበትም፤ ለምን መሄድ እንደማትፈልግም አይገባኝም" አለችው ማኩረፏ በደንብ እየታወቀባት። ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዝምታ ዋጣቸው።

"ሂዊ! ችግሬን አልተረዳሽልኝም" አላት አንተነህ ቆይቶ።

"ችግሩን ያለመረዳት ሳይሆን መጋፈጥ እንደሚያስፈልግ አምኜበት ነው። ምን እንደሚሰማኝ ታውቃለህ? አብሮ የሚያኖረን ርቀት ይመስለኛል፤ ፍሬሕይወት ቅርብ ብትሆን እኔ በአንተ ዘንድ ቦታ የሌለኝ ይመስለኛል" አለችው።

አንተነህ ደነገጠ፤ ወዲያውኑ ውስጡን መመርመር ያዘ። ለምን መሄድ እንደማይፈልግ አሳምሮ ያውቀዋል፤ በቅርብ ርቀት ሆኖ ፍሬሕይወት የሌላ ሰው ሆና ማሰብን ሊቋቋመው ያለመቻሉ ነው አገር ቤት እንዳይገባ የሚያደርገው። ሂዋን በትክክል ተረድታዋለች። ሊጋፈጠው የማይፈልገውና ሁል ጊዜ የሚሸሸው ሀሳብ ነው።

"ሂዊ! ያን ፈተና ተፈትኜ ሳልፍ ነው ማለት ነው እንደማፈቅርሽ የሚረጋገጠው?" አላት።

"ሊገባኝ አልቻለም አንተነህ፤ ዛሬ እርሷም አንተም ባለትዳር ሰዎች ናችሁ። በአንድ ወቅት ተፈቃቅረው፤ ሁኔታዎች አብረው እንዲኖሩ ያልፈቀዱላቸው ሰዎች እኮ መኖራቸው የተለመደ ነው። ለምንድነው እንዲህ አዲስ ነገር የሆነብህ?" አለችው።
የሚመልስላት ነገር አጥቶ ዝም አለ። ዝምታ እንደማያዋጣው ግን ገብቶታል።

"እሺ ሂዊ! እንሂድ፤ ከሄድኩ ግን ፍሬሕይውትን ሳላያት አልመለስም" አላት ደግሞ የሚያሸንፍበት ነገር ፍለጋ።

"ይሄማ ጀግንነት ነው" አለችው ባጭሩ።

"እንዳገኛት ትፈቅጅልኛለሽ?" አላት።



"እየቀለድክ ከሆነ እኔ እየቀለድኩ አይደለም። ማወቅም የምፈልገው ይህንኑ ነው። ከዚህ በኋላ ብታገኛትና ከፍሬሕይወት ጋር የመሆን ዕድል ቢኖርህ ምን ውሳኔ እንደምትወስን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ" አለችው ሂዋን በተለመደው ግልጽ ንግግሯ።

"ይህን ያህል ራሴን የምወድ ሰው ነኝ እንዴ ሂዊ? አሁን ገና የምታውቂኝ አልመስልህ አለኝ" እርሱም ኮስተር አለባት።

"በሚገባ አውቅሃለሁ፤ ስለማውቅህም ነው የወደድኩህ። ያለኝ እምነትም ከብረት የጠነከረ ነው፤ ግን ለፍሬሕይወት ያለህ ስሜት ያስጨንቀኛል፤ ለእርሷ ያለህ ፍቅር ዛሬም ህያው ይመስለኛል... እናም ለእኔ ያለህን ፍቅር የሚደመስስብኝ ይመስለኛል" አለችው።

"በፍጹም አትጠራጠሪ! ፍሬሕይወትን ባገኛት በጣም ደስ ይለኛል፤ ያለችበትን ሁኔታ ባይም እንዲሁ፤ ግን አንቺን ትቼ ወደእርሷ ለመሄድ በጭራሽ አልፈልግም። እውነቱን ለመናገር ግን እፈራለሁ፤ የፍሬሕይወት ፍቅር ምትሃታዊ ይመስለኛል፤ ይህንን የምነግርሽ አሳምረሽ ስለምታውቂው ነው። ከራሴ መታገል ይጠበቅብኝ ይሆናል እንጂ ትዳሬን እንደማልከዳ እርግጠኛ ነኝ። በዚህ ፈተና ውስጥ ለማለፍ አንቺም ዝግጁ መሆን አለብሽ፤ ልትረጅኝ መቻል አለብሽ" አላት የምሩን።

"ደስታውን አልችለውም!" አለችው ።

እናም አገር ቤት ለመግባት ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ። ሻንጣዎቻቸው በአልባሳትና በልዩ ልዩ ቁሳቁስ እየተሞሉ ተቀመጡ።

"ለፍሬሕይወት ስጦታ ይዘንላት እንሄዳለን፤ ምርጫው ደግሞ የኔ ነው። ባይሆን ልኳን በመገመት ታግዘኛለህ" አለችው መነሻቸው ሲዳረስ።

"ቆይ ግን እንዴት ነው ልናገኛት የምንችለው?" አላት።

"እሱን ለኔ ትተወዋለህ" አለችው አሁንም፤ አንተነህ በታመመበት ጊዜ ለፍሬሕይወት እንዲነግራት የላከችውን ዘመዷን እያሰበችው ነበር።

ምርጥ ያሏቸውን ስጦታዎች ገዙላትና ሁለቱም ተደሰቱ። ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደኢትዮጵያ የመብረሪያቸውን ዕለት ሆነ የሚጠብቁት።

* * * *

ወደአመሻሽ ላይ የነበላይሁን እናት ቤት ስልክ ጮኸ። "እየሩስ! እባክሽን ስልኩን አንሺው" አሉ የበላይሁን እናት። እየሩስ ስልኩን አነሳችና "ለእንቺ ነው እማ!" አለቻቸው።

እንደምንም ተነስተው እየተጎተቱ ደረሱና ተቀበሏት። "ሄሎ!" አሉ ስልኩን ወደጆሮአቸው አስጠግተው። እጃቸው በመጠኑ መንቀጥቀጥ ጀምሯል።

"ጤና ይስጥልኝ የበላይሁን እናት" አላቸው ከወዲያኛው ጫፍ ያለው ሰው።

"ጤና ይስጥልኝ፤ ማን ልበል" አሉ የማያውቁት ድምጽ ሆኖባቸው።

"ዘውዱ እባላለሁ፤ ከፍሬሕይወት ጋ ተልኬ ነው" አላቸው።

"ምነው ፍሬ ደህና አይደለችም እንዴ?" አሉት።

"ትንሽ አመም ስላደረጋት ወደቤት መምጣት ትፈልጋለች፤ ቤቱን እንዲያስለቅቁላት አስባ ነበር" አላቸው የቻለውን ያህል ተረጋግቶ።

"እኔን! እኔን ይመመኝ! ልጄን ምን ነካት ይሆን?" አሉ ድምጻቸው ሀዘናቸውን እየተናገረ። ዘውዱ የሚመልሰው አልነበረውም፤ ዝም ሲልባቸው ጊዜ "ታዲያ መቼ መምጣት ታስባለች?" አሉት።

"እርሷ በማንኛውም ሰዓት ለመምጣት ትችላለች፤ እርስዎ ቤቱን ለማስለቀቅ ምን ያህል ጊዜ ይወስድብዎታል?" አላቸው ጥያቄያቸውን በጥያቄ እየመለሰ።

"አሁኑኑ እንነግራቸዋለን፤ ባይሆን ቤት በመፈለግ እናግዛቸዋለን። ደግሞስ ቤቱ ባይለቀቅ እኔ ዘንድ መሆን ትችል የለም እንዴ?" አሉ የበላይሁን እናት። መልሶ እንደሚደውልላቸው ነገራቸውና ስልኩን ዘጋው።



እየሩስ ስታዳምጥ ቆየችና "እማ! ፍሬ ታመመች ነው እንዴ ያሉሽ?" አለቻቸው።

"አዎን ልጄ እኔ አፈር በሆንኩት!" አሉ ትክዝ ብለው።

"የቀብር ቀን የሰማሁት እውነት ነው ማለት ነው?" አለች ኢየሩስ።

"ምን ሲሉ ሰማሽ?" አሏት እናቷ።

"ባለቤቷ የሞተው በዘመኑ በሽታ ..."

"አንቺ በስማም በይ! ምን ወሬ ነው የምታወሪው?" አሉና ተቆጡ የበላይሁን እናት። "ይህንን የሰይጣን ጆሮ አይስማው!" አሉና ወደነፍሬሕይወት ቤት ሄዱ ለተከራዮቹ ሊነግሩ።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ዘውዱ ፍሬሕይወትን ወደቤቷ አመጣት። ቤቱ በሚገባ ተጸድቶ፣ ዕቃዎቻቸው ከታሸጉበት ክፍል ወጥተው ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶ ጠበቃቸው። ፍሬሕይወት ሶፋው ላይ ጋደም አለችና ዐይኖቿን ግድግዳው ላይ ተክላ ብዙ ቆየች።

"ምኑ አገኘሽ ልጄ?" አሏት የበላይሁን እናት ወደአጠገቧ ተጠግተው።

"ባለቤቴ በኤድስ ሞተ... የኔም እጣ ፈንታ ያው ሆነ" አለቻቸውና አስድነገጠቻቸው። ዘውዱም በቀጥተኛ ንግግሯ ደነገጠ። ቤቱ ለአፍታ ያህል ፀጥ፣ ረጭ አለ። ቀስ እያለ የፍሬሕይወት ስቅስቅታ ቤቱን ሞላው፤ ሰውነቷ በስቅስቅታዋ ኃይል እየተናጠ አለቀሰች። በለቅሶዋ ውስጥ የምታስበው ስለአንተነህ ነበር። "አንተነህ እንዲህ ሆኜ ቢያየኝ የቱን ያህል ያዝን ይሆን?" አለች ለራሷ። ሀሳቡ የበለጠ አስለቀሳት። ማንም ሊያጽናናት አቅም አልነበረውም። የበላይሁን እናት፣ እየሩስና ዘውዱ አብረዋት አለቀሱ።

ቆይቶ ግን ዘውዱ ተነሳና ወደአጠገቧ ቀረበ፤ ሊያጽናናት የሚችለውን ያህል ሞከረ፤ አደመጠችው። ትንፋሿ እየተረጋጋ፤ ስቅስቅታዋ እየቀነሰ ሄደ። "ይቅርታ! ረበሽኳችሁ አይደል?" አለች ደግሞ ተጨንቃ።

"አይዞሽ" አላት ዘውዱ።

ሰሞኑን የሰፈራቸው ሰዎች ሲጠይቋት ሰነበቱ፤ ወሬው በአካባቢው ሁሉ ተዳረሰ። ዘውዱና ታረቀኝ ተመላልሰው ጠየቋት፤ ሠራተኛም ቀጠሩላት። ታረቀኝ አንድ ቀን ረዘም ላለ ጊዜ ሲያጫውታት ቆይቶ ሲሄድ ለተወሰነ ጊዜ እንደማይኖር ነግሯት ሄደ። የበላይሁን እናት ደግሞ ታመሙና ዘመዶቻቸው ወሰዷቸው።

አንድ ቀን ገርበብ ብሎ የተዘጋው መዝጊያ ሲንኳኳ እንደተለመደው እነዘውዱ ሊጠይቋት የመጡ መስሏት ራሷን ለማጠናከር ስትሞክር በርከት ያሉ ሰዎች ተከታትለው ገቡ። በጣም ደነገጠች። ሰዎቹ በአካባቢው አልጋ ላይ የቆዩ ህሙማንን የሚንከባከቡ መሆናቸውንና ሊረዷት መፈለጋቸውን ነገሯት። እነርሱ የዕድር መሪዎች መሆናቸውንና አብረዋቸው የሚሠሩ በጎ ፈቃደኞች መኖራቸውን አስረዷት። በሚቀጥለው ቀን ፍቅርተን አምጥተው አስተዋወቋት። ፍቅርተን በአንድ ቀን እጅግ መልካም ወጣት ሆና አገኘቻት፤ ልጇን መሰለቻት ወደደቻት።

ፍቅርተ ደግሞ የጤና ባለሙያዋን ሰናፍቅሽን ይዛ መጣች፤ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ያደርጉላት ጀመር። የሚያደርጉላትን ስታስብ "እንዴት የተባረኩ ልጆች ናቸው?" ትላለች ፍሬ። ሰናፍቅና ፍቅር ሁሌም ባይለዩዋት እንዴት ደስ ባላት! እነርሱን ስታይ ወጣትነቷን ታስባለች፤ የቆሙለት ዓላማና አካሄዱ ይለያይ እንጂ ሁሉም ከራሳቸው ያለፈ የሕይወት ዓላማ አላቸው። እርሷ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋምና የሕዝብ እኩልነት እንዲሰፍን ታገለች፤ ብዙዎች የሕይወት መስዋዕትነት ከፈሉ። እነሰናፍቅና ፍቅር ደግሞ በበሽታና ድህነት የሚንገላቱ ሰዎች የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ፤ አለያም የሰላም ሞት እንዲሞቱ ይጥራሉ። ስታያቸው ደስ ይላታል።



እነርሱ ከመጡ ወዲህ በውስጧ ተስፋ ሲለመልም ተሰማት፤ የመጻጉ ፍላጎት በውስጧ ተፈጠረ፤ "ማን ያውቃል፤ ልጆቼን አገኛቸውም ይሆናል" አለች ለራሷ። ለዘውዱ ስለሰናፍቅሽና ፍቅርተ፤ ስለዕድሮቹም" አወራችለት፤ "እነርሱ አሉኝ፤ ሁሉን ያደርጉልኛል አትመላለስ" አለችው። በአገልግሎት ሰጪዎች ላይ ያላት መተማመን በጣም" አስደሰተው፤ ዘውዱን ደስ ሲለው ማየት ደግሞ ለመንፈሷ እርካታን ይሰጣታል።

"ዘውዱ እንዴት የተባረከ ሰው ነው? ባለቤቱስ እንዴት ደግ ሴት ናት? ማን ያውቃል! ሰናፍቅሽ መድሃኒቱን ስታመጣልኝ ጤንነቴ ይመለስና አመሰግናቸው ይሆናል" አለች ለራሷ።

* * * *

እነአንተነህ የጉዞአቸው ዕለት በተቃረበ ቁጥር ጭንቅ ማለታቸው አልቀረም። አንተነህ ፍሬሕይወትን ሲያገኛት ምን ሊሰማው እንደሚችልና ከባለቤቷ ጋር ሲተዋወቅ ሊፈጠር የሚችለውን ሁኔታ ሲያስበው "ምናልባትም ስለኔ ነግራው ሊሆን ይችላል" ይላል። እንዴት አድርጎ ሰላም እንደሚላት ያስበውና የባለቤቷን ስሜት ሊፈታተንበት እንዳይችል ይሰጋል።

ሂዋን ደግሞ ፍሬሕይወት እርሷንና አንተነህና አብረው ስታያቸው ልትናደድ እንደምትችል ታስብና "ይሄ እንኳን ጊዜያዊ ነው የሆነውን ሁሉ ስትሰማ ትተወዋለች" ትላለች፤ አንተነህ በአሸናፊነት መወጣት ሳይችል ቢቀርና ከፍሬ መለየት ቢያቅተው ሊገጥማት የሚችለውን የሕይወት ትርምስ ስታስበው ግን ይጨንቃታል።

ያም ሆነ ይህ የጉዞው ዕለት ጊዜውን ጠብቆ ደረሰ፤ አንተነህና ሂዋን ወደአገር ቤት ለመግባት አውሮፕላናቸው ውስጥ ገብተው የበረራውን ደቂቃ መጠበቅ ያዙ።

አውሮፕላኑ ማኮብኮብ ሲጀምር "አንተነህ! እወድሃለሁ" አለችው ሂዋን።

"እመቤቴ ሂዋን! ከእንግዲህ ምንም ይመጣል ብለሽ አትስጊ፤ እኔም በጣም እወድሻለሁ" አላት።

አውሮፕላኑም ምድርን ለቆ አየሩን እየሰነጠቀና ከፍታውን እየጨመረ ቀስ በቀስ ከደመናው በላይ ዋለ።

አዲስ አበባ በገቡበት ዕለት ሄዋን የመጀመሪያ ሥራዋ ያደረገችው ያንን ዘመዷን መፈለግ ነበር። ቤት ደውላ ላገኘችው ሰው በጣም እንደምትፈልገው ስትነግር ልታገኘው የምትችልበት ቁጥር ሰጧት። ወዲያውኑ ደወለች።

"አንድ ነገር ላስቸግርህ?" አለችው ከሰላምታ በኋላ።

"እነፍሬሕይወት ቤት ሄደህ አድራሻዋን ልታገኝልኝ ትችላለህ? በጣም እፈልጋታለሁ" አለችው።

"ከአንድ ሰዓት በኋላ እደውልልሻለሁ" ብሏት ስልኩን ዘጋው።

አንድ ሰዓት ከአንድ ቀን በላይ የረዘመ መሰላት። የቱንም ያህል ቢረዝምባትም ሰዓቱ ደረሰና ስልኩ ተደወለላት።

"ሄሎ" አለች ስልኩን አንስታ።

"መልካም ዜና አይደለም የምነግርሽ" አላት መልክተኛው።

"ማለት?" አለችው ድንጋጤዋ ከግምት ውጭ ሆኖባት።

"ፍሬሕይወት ታማለች" አላት እርሱም ድምጹ ስሜቱን እየገለጸ።

"በጣም ነው እንዴ የታመመችው?"

"በጣም ብቻ አይገልጸውም" አላት ተስፋ በሚያስቆርጥ አባባል።

"የት ነች?"

"እቤት"

"መልሼ እደውልልሃለሁ" አለችና ስልኩን ዘጋችው።



ሄዋን ወደኢትዮጵያ ለመምጣት ያሰበችበትን ቀን ረገመችው። አሁን ግን ምንም ማድረግ አትችልም፤ አንተነህ እዚህ ደርሶ ሳያያት ብትሞት ይቅርታ አያደርግላትም፤ ልትነግረው ይገባታል። መፍጠን አለባት።

ሄዋን አንተነህ ወዳለበት ክፍል ገባች፤ ገና ስትገባ "ምን ሆንሽ?" አላት አንተነህ የፊቷን መለዋወጥ ተመልክቶ።

"አንተነህ! አዝናለሁ ፍሬ በጣም ታማለች" አለችው።

"አይሆንም!" አለና ጮኸ።

ሄዋን አንተነህን ለማረጋጋት ረጅም ጊዜ ወሰደባት። ራሷን እንደሃጢያተኛ ቆጠረችው፤ በጣም አዘነች።

"በጣም ይቅርታ አንተነህ! ለዚህ ሁሉ ያበቃሁህ እኔ ነኝ" አለችው ጥቂት ሲረጋጋ ጠብቃ።

"የት ነው ያለችው?" አላት በሰለለ ድምጽ።

"እቤቷ ነው ብሎኛል"

"ሊያደርሰኝ የሚችል ሰው አገኛለሁ?"

"ልጠራው እችላለሁ" አለችና ስልኩን ወዲያውኑ ደወለች።

* * * *

አንተነህ ፍሬሕይወት የተኛችበት ክፍል ሲገባ ዐይኖቹን ሊያምን ስሜቱንም ሊቆጣጠር አልቻለም። "አይሆንም ይህች ሴት ፍሬሕይወት ልትሆን አትችልም" አለ ለራሱ።

"ፍሬሕይወት ናት ነው የምትሉኝ?" አለ ማንን እንደሚጠይቅ ባያውቅም።

"እስኪ ያንን ፎቶግራፍ ተመልከተው፤ አንተ የምታውቃት ፍሬሕይወት ያች ከሆነች፤ አልተሳሳትክም" አለችው አልጋው ላይ የተቀመጠችውና የፍሬሕይወትን ትንፋሽ አሁንም አሁንም የምታየው ወጣት ነርስ ስናፍቅሽ።

አንተነህ የሚሆነውን አጣ፤ አልጋው አጠገብ ተንበረከከና በድን በመሆን ላይ ያለውን ግንባሯን ሳማት፤ አጥንታቸው የሾለውን ጉንጮቿንም እየደባበሰ ሳማቸው። እርሷ የቀረቻት ጥቂት ትንፋሽ እንጂ ምንም አትሰማም። አለቀሰ፤ ወንድ ልጅ የማያለቅሰው የሚባል ዓይነት ለቅሶ አለቀሰ። አልቅሶ ሁሉንም አስለቀሳቸው። እነርሱ ሲያለቅሱ ብዙ ቀን ቢሆናቸውም እንደአዲስ አብረውት አለቀሱ።

ቤት ውስጥ ያሉት ሰዎች ሁሉ ተቆጡት፤ ከተንበረከከበት ተነሳ። ይዞት የመጣው ሰው በግድ ይዞት ወጣ። እንደምንም አድርጎ መኪናው ውስጥ አስገባውና ወደቤቱ መለሰው።

ፍሬሕይውት ትንፋሿ እየቀነሰ ሄደ፤ አካላዊ እንቅስቅሴ አቋረጠች እእምሮዋ ግን ብቻውን ሌላ ዓለም ውስጥ ገብቷል። እናትና አባቷን ያየቻቸው ይመስላታል ግን ሩቅ ናቸው፤ ቢሄዱት የማያልቅ ሰፊ ለምለም መስክ ላይ ነጫጭ ልብሳቸውን ለብሰውና አጠገብ ላጠገብ ሆነው ወደእርሷ የሚመጡ ይመስላታል፤ ግን አይደርሱም። እርሷ ወደእነርሱ ለመሄድ ትሮጣለች ግን በመሃላቸው ያለው ርቀት ይጨምራል እንጂ አይቀንስም። ድንገት ከእይታዋ ጠፉባትና ተጣራች፤ የሚሰማት ግን የለም፤ ማልቀስ አማራት፤ ወዲያው ደግሞ በላይሁንን ያየች መሰላት፤ ገና ልጅ ሳለ የነበረውን በላይሁንን፤ ከዛ ደግሞ ሚሚ፤ ቃለአብና እየሩስ ልክ እንደልጅነታቸው የሚጫወቱ ይመስላታል፤ ሮቤል ራቅ ብሎ ይመለከታቸዋል፤ ተጫውታ ሳትጠግብ ከአጠገቧ አጣቻቸው። ፈቃደን፤ ያንን የጃኬቱን ቁልፎች እስከአንገቱ ድረስ ቆልፎ "አይዞሽ" ያላትን ፈቃደን አየችው፤ ከዛ ደግሞ ልጆቿ እንደድሮአቸው በግራና በቀኝ ተቀምጠው ራሳቸውን የምታሻሽላቸው ይመስላታል፤ ወዲያውኑ ወደውጭ በሄዱበት ዕለት በነበሩበት ሁኔታ አየቻቸው ከሩቅ ታዩአት፤ ለመጣራት ሞከረች የሰሟት አልመሰላትም፤ እየራቋት ሄዱ። ተበሳጨች። ዘውዱ አይዞሽ የሚላት መሰላት፤ ከዛ ደግሞ ታረቀኝ... ብዙዎቹን ጓደኞቿን አየቻቸው፤ ከማናቸውም ጋር ግን የምትፈልገውን ያህል መነጋገርና



መጫወት አልቻለችም፤ አዘነች። በመጨረሻ አንተነህ፤ አንተነህ እየሮጠ ወደእርሷ ሲመጣ አየችውና እርሷም ወደእርሱ ሮጠች። እርሱም እርሷም ይሮጣሉ፤ በመሃላቸው ያለው ርቀት የጠበበ መሰላት ግን አልተገናኙም፤ እጁን ዘረጋላት እጇን ዘረጋች፤ ሁለቱም ተንጠራሩ ሊያያዙ ግን አልቻሉም። በጣም ስትንጠራራ የረገጠችው መሬት ተናደባትና ደነገጠች፤ የሆነ ኃይል ወደላይ ነጠቃት፤ የምትንሳፈፍ፣ የምትበር መሰላት፤ አንተነህ እየነሰ እየነሰ ሄደና ከዕይታዋ ተሰወረ፤ እርሷ ግን የተንሳፈፈች ሄደች...።

ወደሌሊቱ ላይ የፍሬሕይወት የመጨረሻ ህቅታ ሆነ። የመጨረሻዋን ትንፋሽ ተንፍሳ ለዘለአለሙ አንቀላፋች።

አንተነህ ቀብሯ ላይ ሊገኝ አልቻለም፤ ፍሬሕይወትን ባየት ምሽት ነበር ሆስፒታል የገባው፤ መንፈሱ በመረበሹ ምክንያት ሊያረጋጋውና እንቅልፍ ሊያስወስደው የሚችል መድኃኒት ተሰጥቶት ፍሬሕይወት ለመጨረሻው ስታንቀላፋ እርሱ ደግሞ ለጊዜውም ቢሆን በከፍተኛ እንቅልፍ ውስጥ በሚያቆየው መድሃኒት ቁጥጥር ስር ዋለ።

ለፍሬሕይወት በርካቶች የሚያውቋት ሰዎች እየተሰማሙ በቀብሯ ላይ ተገኝተው አለቀሱላት፤ በርካታ የአበባ ጉንጉኖችም በመቃብሯ ላይ ተከመሩ። አንዲት ሴት ለቅሶዋን መቆጣጠር እየቃታት በፍሬሕይወት መቃብር ላይ የመጨረሻውን የአበባ ጉንጉን አስቀመጠች፤ "ከአንተነህና ከሂዋን" ይላል በአበባ ጉንጉን ላይ የተጻፈው።

********** ተፈፀመ *************